# መርሐ ሕይወት
## ሁለተኛ መጽሐፍ

አዘጋጅቶ ያቀረበው

ዓምራት ገብረማርያም

1992 ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

«ሰው የሚኖረው እግዚአብሔር

በሚናገረው ቃል ሁሉ እንጂ

በእንጀራ ብቻ አይደለም።»

(ዘዳ 8፥3)



ዓሥራት ገብረ ማርያም

«የምሥራቹን ቃል ማብሠር ግዴታዬ ስለሆነ የምመካበት ነገር አይደለም፤ እንዲያውም የምሥራቹን ቃል ሳላበሥር ብቀር ወዮልኝ።» (1ኛ ቆሮ 9፥16)

## የሁለተኛው መጽሐፍ ይዘት

### አምስተኛ ክፍል


| | |
|---|---|
| ምዕራፍ 1:- ትምህርተ ሃይማኖት | 11 |
| የእግዚአብሔር ስጦታዎች | 11 |
| መንፈሳዊ ስጦታዎች | 11 |
| ጊዜያዊ የሆኑ ዓላማዊ ስጦታዎች | 13 |
| የሙታን ትንሣኤ | 14 |
| ነፍስ፥ ዘለዓለማዊ ፍርድና ሺህ ዓመት | 16 |
| የሰው ነፍስ | 16 |
| ዘለዓለማዊው ፍርድ | 19 |
| ሺህ ዓመት | 21 |
| የምዕራፉ አጠቃላይ ሐሳብ | 25 |
| ጌታችን ተመልሶ የሚመጣው ለ ድ ጊዜ ብቻ መሆኑ | 26 |
| ጥያቄዎች | 27 |
| ምዕራፍ 2:- መጽሐፍ ቅዱስ | 29 |
| ብሉይ ኪዳን | 29 |
| በግብጽ ላይ የወረዱ መቅሠፍቶች | 29 |
| 1. የውሃ ወደ ደም መለወጥ | 29 |
| 2. የሀገሪቱ በጓጉንቸር መሸፈን | 30 |
| 3. ከትቢያ ወደ ቅማልነት መለወጥ | 30 |
| 4. ተናካሽ ዝንብ | 30 |
| 5. የእንስሳት እልቂት | 30 |
| 6. ብጉንጅ የመሰለ ቍስል | 31 |
| 7. የበረዶ መዘነብ | 31 |
| 8. የአንበጣ መንጋ | 31 |
| 9. ጨለማ | 32 |
| 10. የበኵር ልጆች ሞት | 32 |
| የእስራኤላውያን የበረሃ ጉዞ ሂደት | 32 |
| የጉዞው አጀማመር | 32 |
| የእስራኤላውያን በኵር | 33 |
| በጉዞው መጀመሪያ ላይ የተከሠቱ ድንቅ ነገሮች | 33 |
| መጽሐፈ ዕዝራ | 34 |
| ሐዲስ ኪዳን | 37 |
| ጴጥሮስና ቆርኔሌዎስ | 37 |


www.ethiopianorthodox.org

| | |
|---|---|
| የቤተ ክርስቲያን ታላቅ ስደት | 39 |
| የቤተ ክርስቲያን ጸሎት ውጤት | 39 |
| የሄሮድስ አሟሟት | 40 |
| ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት | 40 |
| ጥያቄዎች | 43 |
| ምዕራፍ 3:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ | 45 |
| የጌታችን ትምህርቶች | 45 |
| ደብረ ታቦር | 45 |
| ሰባው ደቀ መዛሙርት ለማስተማር መላካቸው | 46 |
| ስለ ጾም የቀረበ ጥያቄ | 47 |
| የዳስ በዓል | 47 |
| የጌታችን ተአምራት | 47 |
| ጋኔን ያደረበት ልጅ መፈወስ | 47 |
| ጌታችን አራት ሺህ ሰዎችን መመገቡ | 48 |
| ደንቆሮና ድዳ የነበረው ሰው መፈወስ | 48 |
| የጌታችን ምሳሌዎች | 49 |
| የወይን አትክልቱ ገበሬዎች ምሳሌ | 49 |
| የዐሥሩ ልጃገረዶች ምሳሌ | 50 |
| ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት | 50 |
| ጥያቄዎች | 55 |
| ምዕራፍ 4:- ቤተ ክርስቲያን | 56 |
| አራት የቤተ ክርስቲያን ቅጽል ስሞች | 56 |
| አንዲት | 56 |
| ቅድስት | 57 |
| ዓለም ዐቀፋዊት | 58 |
| ሐዋርያዊት | 58 |
| የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት | 59 |
| ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ | 59 |
| ሐዋርያው ቅዱስ ስምዖን (ቀናኢ) | 60 |
| ትልቁ ቅዱስ እንጦንስ | 61 |
| በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የኢትዮጵያና የግብጽ አብያተ ክርስቲያን ግንኙነት አጭር ታሪክ | 63 |
| በኮፕት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና (ኮኦቤ) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን (ኢኦተቤ) መካከል የተደረገ ፕሮቶኮል | 74 |
| መግቢያ | 74 |
| ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት | 80 |
| ጥያቄዎች | 81 |
| ምዕራፍ 5:- መንፈሳዊነትና ግብረ ገብነት | 83 |
| ወደ ኃጢአት ከሚገፋፉ ሁኔታዎች መጠበቅ | 83 |
| ክፉ ሁናቴን ከማየት መቈጠብ | 83 |
| ክፉ ነገርን ከመስማት መቈጠብ | 84 |
| ክፉ መጻሕፍትን ከማንበብ መቈጠብ | 85 |
| ከክፉ አሉባልታ ራስን መጠበቅ | 86 |
| ሰጪ ከተቀባይ ይልቅ የተመሰገነ ነው | 88 |
| ደግና ክፉ ነገሮች በድምፅ ብልጫ የሚወሰኑ አይደሉም | 89 |
| ጥያቄዎች | 90 |
| ስድስተኛ ክፍል | 91 |
| ምዕራፍ 1 :- ትምህርተ ሃይማኖት | 91 |
| የእግዚአብሔር ሕጎች | 91 |
| የሕግ ዓላማ | 91 |
| ሕጉን ማክበርና አላማክበር የሚያመጡአቸው ውጤቶች | 92 |
| ሕጉን ብናከብር | 92 |
| ሕጉን ባናከብር | 93 |
| የሕጉ አመሠራረት | 94 |
| ትውፊት | 95 |
| ነገረ ማርያም | 99 |
| የእመቤታችን ድንግልና | 100 |
| የአምላክ እናትነትዋ | 105 |
| ክብርዋ | 106 |
| ጥያቄዎች | 107 |
| ምዕራፍ 2:- መጽሐፍ ቅዱስ | 109 |
| ብሉይ ኪዳን | 109 |
| ሁለቱ ጽላቶች | 109 |
| ሐዲስ ኪዳን | 115 |
| የኢየሩሳሌም ጉባኤ | 115 |
| ወደ ዕብራውያን የተላከ መልእክት | 117 |
| ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት | 119 |
| ጥያቄዎች | 122 |
| ምዕራፍ 3:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ | 124 |
| የጌታችን ትምህርት | 124 |
| ጌታችንና ዘኬዎስ | 124 |
| የጌታችን ተከታዮች ምን መሆን አለባቸው | 125 |
| የጌታችን ተአምራት | 126 |


www.ethiopianorthodox.org

የዐሥር ለምጻሞች መፈወስ 126
የአልዓዛር ከሞት መነሣት 126
የሹሙ ልጅ መፈወስ 127
የጌታችን ምሳሌዎች 128
የሚያድግ ዘር 128
ስውር መብራት 128
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት 128
ጥያቄዎች 134
ምዕራፍ 4:- ቤተ ክርስቲያን 136
የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት 136
የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን 136
ወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ 138
ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ 140
ቅዱስ ፍሬምናጦስ 141
ቅዱስ ቴዎዶጦስ 142
ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾክያ 142
አባ አርያቆስ 144
ቅዱስ በርናባስ 145
የቤተ ክርስቲያን ዜማ 145
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት 145
ጥያቄዎች 148
ምዕራፍ 5:- መንፈሳዊነትና ግብረ ገብነት 152
ራስን የመግታት ጥንካሬ አስፈላጊነት 152
ክፉ ነገሮችን ከማየት መቈጠብ 153
ከክፉ ሐሳብና ከክፉ ምኞት መገታት 153
ከፍትወት መጠበቅ 154
ከክፉ ትውስታዎች አሳሳችነት መጠንቀቅ 154
ከትዕቢት መገታት 155
ከፍርሀት የተነሣ የእግዚአብሔርን ክብር መቀነስ 155
ክፉ ከመናገርና ክፉ ከማድረግ (በግልፍተኝነት) 156
ከክፉ ሙከራ መቈጠብ 156
የመንፈሳዊነትና የግብረገብነት ምንጮች 157
ጥያቄዎች 161
ሰባተኛ ክፍል 164
ምዕራፍ 1:- ትምህርት ሃይማኖት 164
የእግዚአብሔር ጠባዮች 164
የእግዚአብሔርን ህላዌ የሚያመለክቱ ጠባዮች 165
1. እግዚአብሔር ውሱንነት የለበትም 165
2. የእግዚአብሔር በራሱ መኖር 165
3. የማንም እርዳታ የማያስፈልገው መሆኑ 166
4. የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊነት 167
5. የእግዚአብሔር አለመለወጥ 168
6. እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ የሚገኝ መሆኑ 170
7. እግዚአብሔርን ማየትና ሙሉ ለሙሉ ማወቅ አለመቻሉ 170
ከፍጠረቱ ጋር ባለው ግንኙነት የእግዚአብሔር ጠባዮች 172
1. የእግዚአብሔር ሁሉን ዐዋቂነት 172
2. የእግዚአብሔር ጥበበኛነት 173
3. የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት 173
4. የእግዚአብሔር ቅዱስነት 174
5. የእግዚብሔር ጽድቅ (ፍትሕ) 176
6. የእግዚአብሔር ፍቅርና ደግነት 177
7. የእግዚአብሔር እውነተኛነትና ታማኝነት 178
8. የእግዚአብሔር መንፈስነት 179
9. የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃ 184
ምሥጢረ ተዋሕዶ 185
ሀ. መግቢያ 185
ለ. የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት 186
ሐ. የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት 188
ቅዱስ አትናቴዎስ 188
ቅዱስ አቡሊዲስ 188
ቅዱስ ቄርሎስ 189
ቅዱስ ሳዊሮስ 189
ቅዱስ ባስልዮስ 189
መ–የቤተ ክርስቲያን መከፋፈል 190
ጥያቄዎች 192
ምዕራፍ 2:- መጽሐፍ ቅዱስ 195
ብሉይ ኪዳን 195
የእስራኤል ዐመፀኛነት 195
መጽሐፈ አስቴር 199
መጽሐፈ ዮዲት 203
ሐዲስ ኪዳን 208
ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ተለያዩ አገሮች 208

www.ethiopianorthodox.org

ወደ ኤፌሶን ሰዎች የተላከ መልእክት 212
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት 216
ጥያቄዎች 219
ምዕራፍ 3:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 222
የጌታችን ትምህርት 222
ስለ ፍቅር ማስተማሩ 222
ከሁሉ የሚበልጥ ማነው? 223
ስለ አባቶች ወግ 224
የጌታችን ተአምራት 224
የአንዲት መበለትን ልጅ ከሞት ማስነሣቱ 224
ሽባውን ሰው መፈወሱ 225
ሁለት ዕውራንን መፈወሱ 226
ዕውርና ድዳ የነበረውን ሰው መፈወሱ 226
የጌታችን ምሳሌዎች 226
ትዕቢተኛው ፈሪሳዊና ትሑቱ ቀራጭ 226
የሀብታሙ ሰው ምኞት 227
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት 228
ጥያቄዎች 223
ምዕራፍ 4:- ቤተ ክርስቲያን 235
የቤተ ክርስቲያን ኀላፊነት 235
ወንጌልን የማስተማር ኀላፊነት 236
የምሥጢራትን ሥርዓት የማከናወን ኀላፊነት 237
ልዩ ልዩ ሥርዓተ ጸሎትን የማከናወን ኀላፊነት 237
ችግረኞችን የመርዳት ኀላፊነት 238
የአምልኮን ሥርዓት የመጠበቅና የማስጠበቅ ኀላፊነት 239
የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳንና ቅዱሳት 240
ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ 240
ማርያም መግደላዊት 241
ቅዱስ ሙሴ ጸሊም 241
ቅዱስ አቡሊዲስ 242
የቤተ ክርስቲያን ዜማ 243
ጥያቄዎች 250
ምዕራፍ 5:- መንፈሳዊነትና ግብረ ገብነት 251
ከሰዎች ጋር የመወያየት ውጤት 251
መስማማትና አለመስማማት 252
ተስፋ መቍረጥ አይገባም 252
አንቀጸ ብፁዓን 254
ጥያቄዎች 255
ስምንተኛ ክፍል 257
ምዕራፍ 1:- ትምህርተ ሃይማኖት 257
የእግዚአብሔር ቅጣቶች 257
ምድራዊ ወይም ጊዜያዊ የእግዚአብሔር ቅጣቶች 257
ዘለዓለማዊ የመጨረሻ ቅጣቶች 260
እምነትና ተግባር 261
በእምነት ብቻ የሚለው አስተሳሰብ ችግር 265
ጥያቄዎች 270
ምዕራፍ 2:- መጽሐፍ ቅዱስ 271
ብሉይ ኪዳን 271
መልከ ጼዴቅ 271
ኢያሱ ወልደ ነዌ 280
መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 281
ሐዲስ ኪዳን 288
የቅዱስ ጳውሎስ መያዝ፥ መከሰስ፥ መታሰር 288
ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች የተላከ መልእክት 290
ወደ ቆላስይስ ሰዎች የተላከ መልእክት 293
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት 295
ጥያቄዎች 301
ምዕራፍ 3:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 303
የጌታችን ትምህርት 303
እምነትን በእግዚአብሔር ላይ ማድረግ 303
ስለ ጠባብዋ በር 304
ከመጥምቁ ዮሐንስ የተላኩ መልእክተኞች 304
የጌታችን ተአምራት 304
የአንዲት ጐባጣ ሴት መፈወስ 304
ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው መፈወሱ 305
የጌታችን ምሳሌዎች 306
ሀብታሙ ሰውና ድኻው አልዓዛር 306
ጠፍቶ የተገኘው በግ ምሳሌ 307
የብልኅ መጋቢ ምሳሌ 307
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት 308
ጥያቄዎች 317
ምዕራፉ 4:- ቤተ ክርስቲያን 320


www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያንና ምእምናን 320
የሃይማኖት ትምህርትን ማስተማር 321
ችግረኞችን መርዳት 323
ያዘኑትን ማጽናናትና የተጣሉትን ማስታረቅ 324
መባረክ 324
ጸሎትን መምራት 326
በቤተ ክርስቲያን የምእመናን ሚና 326
የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን 327
ተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ 327
ቅዱስ አትናቴዎስ 329
ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ 334
ቅዱስ ዮሐንስ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ 336
ቅዱስ ቴዎዶስዮስ የእስክንድርያ ኤጲስቆጶስ 337
የቤተ ክርስቲያን ዜማ 339
ጥያቄዎች 341
ምዕራፍ 5:- መንፈሳዊነትና ግብረገብነት 343
ጠቃሚ ካልሆነ ተጽዕኖ መጠንቀቅ 434
ከባለ ሥልጣን፥ ከቅርብ አለቃ፥ ወይም ከአሠሪ 343
የዘመድ፥ የጓደኛ፥ ወይም የወዳጅ ተጽዕኖ 344
የዓለማዊ ፍላጎት ተጽዕኖ 345
ከማይጠቅም ተጽዕኖ መከላከል 346
ጥያቄዎች 348

# አምስተኛ ክፍል

## ምዕራፍ 1

## ትምህርተ ሃይማኖት

### የእግዚአብሔር ስጦታዎች

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጣቸው ስጦታዎች ተቈጥረው ሊያልቁ የማይችሉ በጣም ብዙዎች ናቸው። እነርሱም ከሕይወታችን ጀምረው መንፈሳዊና ሥጋዊ ፍላጎታችንን ሁሉ የሚያጠቃልሉ ናቸው። በአጠቃላይ ግን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ። እነርሱም መንፈሳዊና ሥጋዊ ስጦታዎች ናቸው።

የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ስጦታዎች:- መንፈሳዊ ስጦታዎች ስንል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለዘለዓለማዊ ድኅነታችን የሚጠቅሙ ስጦታዎች ለማለት ነው።

ለምሳሌ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ፍጥረትን ሁሉ በፈጠረ ጊዜ ለሰው የሰጠው ስጦታ ከሌሎቹ ፍጥረቶች ሁሉ የተለየ ነበር። ሰውን ከፈጠረው በኋላ አስቀድሞ በአፍንጫው እፍ ብሎበት የሕይወት እስትፋስን ሰጠው። በዚህም ምክንያት ሰው ሥጋው እንጂ ነፍሱ አትሞትም።

«ሥጋን ከመግደል አልፈው ነፍስን መግደል የማይችሉትን ሰዎች አትፍሩ፤ ይልቁንስ ነፍስንና ሥጋን በገሃነም ሊያጠፋ የሚችለውን አምላክ ፍሩ» (ማቴ:ም:10ቍ:28)።

ሌላው የመንፈሳዊ ስጦታዎች ምሳሌ ደግሞ ቃለ እግዚአብሔር ነው። ምንም እንኳ ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል የእግዚአብሔር ሐሳብ ከእኛ ሐሳብ ከፍ ያለ ቢሆን የእርሱን ፈቃድ በመፈጸም ሕይወትን እናገኝ ዘንድ እግዚአብሔር ሁልጊዜ መንፈሳዊ መመሪያዎቹን ይሰጠናል። እነዚህም መመሪያዎቹ የተጀመሩት ክፉና ደግን ለይታ ከምታስታውቀዋ ዛፍ ፍሬ ብትበሉ ትሞታላችሁና ከእርሱ እንዳትበሉ ተብሎ ነው። በዚህም ዐይነት ከአዳም እስከ ሙሴ ባሉት ዘመናት እግዚአብሔር መመሪያዎቹን ሁሉ ለሰው ልጆች ሲያስተላልፍ የቈየው በቃል እንጂ በጽሑፍ አልነበረም። መመሪያዎቹን በጽሑፍ ማስተላለፍ የተጀመረው ግን በሙሴ ዘመን ነው። ሙሴም የእስራኤልን ሕዝብ የሚመራባቸው መንፈሳውያንና ዓለማውያን ሕጎች ከእግዚአብሔር በቀጥታ እየተነገረው መዝግቦአቸዋል። ነቢያት፥ ቅዱሳን፥ ሐዋርያትና ወንጌላውያን በራእይና በዐይን ምስክርነት ያዩትን ቃለ እግዚአብሔር ጽፈዋል። ቃለ እግዚአብሔርም የተባለበት ምክንያት ጸሐፊዎቹ በሚጽፉበት ጊዜ ስሕተት እንዳያደርጉ የመንፈስ ቅዱስ ድጋፍ ያልተለያቸው በመሆኑ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

እንደገና ደግሞ ሌላው ትልቁ የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ስጦታ የሰውን ሥጋ በለበሰው በእግዚአብሔር ወልድ ቤዛነት ያገኘነው ድኅነታችን ነው።

«በእርሱ ያመነ ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ፥ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲህ አድርጎ ወድዶታል» (ዮሐ:ም:3ቁ:16)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተለያዩ ስጦታዎችን ሀድሎናል፤ የእግዚ. አብሔር ልጆች የመሆንን ጸጋ ሀድሎናል፤ በሥጋውና በደሙ አማካይነት ከኃጢአት ይቅር የመባልንና ከእርሱ ጋር ኅብረት የማግኘትን ጸጋ ሀድሎናል። እርሱ በእኛ ቦታ ሆኖ ሕማማትንና ሞትን ስለተቀበለ በጥምቀት አማካይነት ከጥንተ አብሶ ማለት ከአዳም ከተወረሰው ኃጢአት ነጻ አውጥቶናል።

ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ከቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ ለመጥቀስ የሚቻል ቢሆንም ለጊዜው ጥቂቶቹን ብቻ ቀጥለን እንመልከት።

«ጌታችንና አምላካችን ሆይ፥ አንተ እንደ ፀሐይና እንደ ጋሻ ነህ፤ በቸርነትና በክብር ትጠብቀናለህ፤ ደግ ለሚሠሩ ሰዎች ማናቸውንም መልካም ነገር አትከለክላቸውም» (መዝ:84ቁ:11)።

«አዲስ ልብና አዲስ መንፈስ እሰጣቸዋለሁ፤ ከሰውነታቸው የድንጋይ ልብን አውጥቼ የሥጋ ልብን እሰጣቸዋለሁ፤ በዚያን ጊዜ ሕጌን ይፈጽማሉ፤ ትእዛዞቼንም ሁሉ ያከብራሉ፤ እነርሱ ሕዝቤ ይሆናሉ እኔም አምላካቸው እሆናለሁ (ሕዝ: ም: 11 ቁ: 19 -20)።

ከኃጢአት የሚገኘው ዋጋ ሞት ነው፤ ከእግዚአብሔር የሚሰጠው ስጦታ ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘው የዘለዓለም ሕይወት ነው» (ሮሜ 6፥ 23)።

«መንፈስ ቅዱስ ለአንዱ ሰው በጥበብ የመናገር ችሎታን ይሰጠዋል፤ ለሌላው ሰው ደግሞ ያው መንፈስ በዕውቀት የመናገር ችሎታን ይሰጠዋል፤ ያው አንዱ መንፈስ ለአንዱ እምነትን ይሰጠዋል፤ ለሌላውም የመፈወስ ስጦታን ይሰጠዋል፤ እንዲሁም ለአንዱ ተአምራት የማድረግ ኀይልን ይሰጠዋል፤ ለሌላው የትንቢትን ቃል የመናገር ችሎታ ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ ሰጦታዎች ከመንፈስ ቅዱስ መሆናቸውን ወይም ከርኩሳን መናፍስት መሆናቸውን ለይቶ የማወቅ ችሎታን ይሰጠዋል፤ እንዲሁም ለአንዱ በተለያዩ ቋንቋዎች የመናገር ችሎታን ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ በተለያዩ ቋንቋዎች የተነገረውን የመተርጐም ችሎታን ይሰጠዋል፤ ይሁን እንጂ ይህን ሁሉ የሚያደርገው፥ ያው አንዱ መንፈስ ቅዱስ ነው፤ መንፈስ ቀዱስ እንደፈቀደ ለእያንዳንዱ ሰው የተለየ ስጦታን ይሰጠዋል» (1ኛ:ቆሮ:12፥8–11)።

«ከእናንተ ማንም ጥበብ የጐደለው ሰው ቢኖር እግዚአብሔርን ይለምን፤ እግዚአብሔርም ይሰጠዋል፤ እርሱም ምንም ቅር ሳይለው ለሁሉም በልግሥና የሚሰጥ ቸር አምላክ ነው» (ያዕ: ም: 1: ቁ : 5)።



«መልካም ስጦታና ፍጹም በረከት ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ ይህም የሚመጣው እንደ ጥላ መዘዋወር ወይም መለዋወጥ ከሌለበት ከብርሃን አባት ከእግዚአብሔር ነው»(ያዕ: ም : 1 ቁ :17)።

<u>ጊዜያዊ የሆኑት ዓለማዊ ስጦታዎች</u>:- ወደ ኦሪት ዘፍጥረት መለስ ብለን የተመለከትን እንደሆነ እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ለኑሮው አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ካመቻቸለት በኋላ መሆኑን እናነባለን።

በምድር ፍጥረቶችም ሁሉ ላይ የበላይ አድርጎ ሾመትን ሰጠው።

ለምግብነትም የምድርን ዘር፥ ቡቃያዎችንና ሕይወት ያለውን ተንቀሳቃሽ ሁሉ ሰጣቸው።

መሬት ለማብቀል እንድትችል ዝናብን፥ መልካም አየርንና ፀሐይን ሰጣቸው።

ለመናገር አንደበትን፥ ለማየት ዐይንን፥ ለማሽትት አፍንጫን፥ ለመያዝና ለመሥራት እጅን፥ ለመራመድ እግርን የሰጠን እግዚአብሔር ነው።

የሰው ልጅም ኑሮውን በማሻሻል የተሻለ ኑሮ ለመኖር እንዲችል ዕውቀትን ሰጥቶታል። በዚህም በተሰጠው ዕውቀትና ችሎታ ነው ሰዎች ጠቀሚዎች የሆኑ የተለያዩ ዘመናዊ ግኝቶችን የሚፈለሰፉት። የሰው ልጆች ለመጓጓዣነት መኪናዎችን፥ ባቡሮችንና አውሮፕላኖችን ሠርተው ለመጠቀም የቻሉት ከፈጣሪ አምላክ በተሰጣቸው ዕውቀት ነው።

ስለ እነዚህም ስጦታዎች ከተገለጡባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው:-

«ከዚህ በፊት የአትክልት ዐይነቶችን ምግብ አድርጌ እንደ ሰጠኋችሁ እነዚህንም ተንቀሳቃሽ ፍጥረቶች ሁሉ ምግብ እንዲሆኑአችሁ ሰጥቼአችኋለሁ» (ዘፍ:ም:9ቁ:3)።

«በሕጌ ብትመሩና ትእዛዛቴን ብትጠብቁ ምድራችሁ በሰብል፥ ዛፎቻችሁም በፍሬ የተሞሉ ይሆኑ ዘንድ ዝናብን በወቅቱ እልክላችኋለሁ» (ዘሌ: ም: 26ቁ:3–4)።

«እነዚህ ሁሉ ምግባቸውን በየጊዜው እንድትሰጣቸው ተስፋ የሚያደርጉት አንተን ነው፤ አንተ ምግብ ስትሰጣቸው እነርሱ ይመገባሉ፤ አንተ እጅህን ስትዘረጋ እነርሱም መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ በልተው ይጠግባሉ» (መዝ:104ቁ:27–28)።

«ደግሞ ለሰው የድካሙ ዋጋ በመብላትና በመጠጣት መደሰት ሲሆን ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው» (መክ:ም:3ቁ:13)።

«እግዚአብሔር ለሰው ሀብትንና ብልጽግናን መስጠቱ የደከመበትን ድርሻ አግኝቶ በመብላትና በመጠጣት ደስ እንዲለው ፈቅዶለት ነው፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው» (መክ:ም:5ቁ:19)።

www.ethiopianorthodox.org

# የሙታን ትንሣኤ

የሙታን ትንሣኤ ማለት ውሱን ከሆነ ውሱን ወደ አልሆነ ቦታ መሸጋገር፥ ከተወሰነ ዕድሜ ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት መዛወር፥ በዘመን ውስጥ ከመኖር ከመዘመን በላይ ወደመኖር መዛወር ማለት ነው፤ እንዲሁም ከሚታዩት ወደማ ይታዩት ነገሮች መዛወር ነው። መጽሐፍ እንደሚለውም:- «ዐይን ወደ አላየው፥ ጆሮ ወደአልሰማው፥ በሰውም ልብ ወደ አልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወድዱት ወደ አዘጋጀው ቦታ መግባት ነው» (1ኛ:ቆሮ:ም:2ቍ:9)። ይኸውም ከእግዚአብሔርና ከመላእክቱ ጋር ወደሚገናኙበት መንፈሳዊ ዓለም መግባት ነው። በዚያም ቦታ ቀደም ብለን የማናውቃቸውን ነገሮች ሁሉ እናውቃለን፤ የማይታየውንም እናያለን። እነዚህ ከላይ የተሰጡት መግለጫዎች የሚያመለክቱት የጌታችንን ዳግመኛ መምጣት በንስሓ ተዘጋጅተው ለሚጠባበቁት እንጂ ንስሓ ለማይገቡትማ የጌታችን ዳግመኛ መምጣት የዘለዓለማዊውን የሥቃይ ፍርድ የሚያስከትልባቸው ስለሆነ አስደንጋጭ ነው።

በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 2ቍ: 7 መሠረት እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ከምድር ዐፈር ካበጀው በኋላ በአፍንጫው የሕይወት እስትንፋስ እፍ ያለበት መሆኑ ተገልጾአል። ነፍስም የእግዚአብሔር እስትንፋስ በመሆንዋ ሰው የሚሞተው በሥጋው ብቻ ነው። በሌላ አነጋገር ደግሞ ሥጋ በድን የሚሆነው ነፍስ ሲለየው ነው። ከሥጋ የተለየው ነፍስ እስከ ዳግመኛ የጌታችን መምጫ ቀን ድረስ ከፈጣሪው በተዘጋጀለት ቦታ ይቈያል። ሥጋ ግን ወደተፈጠረበት ወደ ዐፈር ይመለሳል። ይህን አባባል በሚከተለው ማስረጃ እንመልከት።

«ሥጋ ዐፈር ስለሆነ ወደ ዐፈር ይመለሳል፤ ነፍስም ወደ ፈጠራት ወደ እግዚአብሔር ትሄዳለች» (መክ:ም:12ቍ:7)።

ሰው ሲሞት ሥጋና ነፍስ ተለያይተውና ሥጋም ከፈረሰና ከበሰበሰ በኋላ በእግዚአብሔር ተአምር በትንሣኤ ሙታን ጊዜ ኅብረት እንዲኖራቸው ተደርገው እንደገና በማይሞት መንፈሳዊ ሰውነት የሚነሡ መሆናቸው የቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ነው።

የሰው ልጆች ከሞት በሚነሡበት ጊዜ የሚኖራቸው ምን ዐይነት አካል ነው? ይህን ጥያቄ በመመለስ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲያብራራ እንዲህ ይላል:-

«የሚጠፋ ሟች አካል ሆኖ የተዘራው የማይጠፋ ሕያው አካል ሆኖ ይነሣል፤ በውርደት የተዘራው በክብር ይነሣል፤ ደካማ ሆኖ የተዘራው ኀይለኛ ሆኖ ይነሣል። ... እነሆ፥ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችንም አንሞትም፤ ነገር ግን ሁላችንም እንለወጣለን። የምንለወጠውም የመጨረሻው መለከት በሚነፋበት ጊዜ እንደ ዐይን ቅጽበት በአንድ ጊዜ ነው፤ መለከቱ ይነፋል፤ የሞቱትም ሰዎች የማይጠፉ ሕያዋን ሆነው ይነሣሉ፤ እኛም እንለወጣለን» (1ኛ:ቆሮ:ም:15ቍ:42–44፥51–52)።



እንደገናም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- «ከጌታችን በተቀበልነው ቃል መሠረት የምንነግራችሁ ይህ ነው፤ ጌታችን እስከሚ መጣበት ቀን ድረስ ሕያዋን ሆነን የምንገኝ የሞቱትን አንቀድምም። የትእዛዝ ድምፅ፥ የመላእክት አለቃ ድምፅ፥ የእግዚአብሔር መለከትም ይሰማል፤ ጌታ ራሱም ከሰማይ ይወርዳል፤ ከዚያ በኋላ በሕይወት የምንገኘው ጌታችንን በአየር ላይ ለመገናኘት ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ ለዘለዓለምም ከጌታ ጋር እንሆናለን» (1ኛ:ተሰ:ም:4ቍ:15–17)።

ክርስቶስ የሙታን ትንሣኤ በኵር ነው የተባለው በሙታን ትንሣኤ ጊዜ የምንነሣበት ሰውነት፥ ጌታችን በተነሣ ጊዜ የተነሣበትን መንፈሳዊ ሰውነት ስለሚመስል ነው (1ኛ:ቆሮ:ም:15ቍ:20፥ቈላ:ም1ቍ:18)። ይህን አባባል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሌላ ጊዜ ሲያብራራው እንዲህ ብሏል:-

«እርሱ ይህን የተዋረደውን ሰውነታችንን በመለወጥ የእርሱን ክቡር ሰውነት እንዲመስል ያደርገዋል» (ፊልጵ:ም:3ቍ:21)።

የሙታን ትንሣኤም ዋነኛውና ትልቁ ተስፋችን ነው። የእምነታችንም ዋና መሠረትና አለኝታችን ነው። በትንሣኤ ሙታን ጊዜ ተነሥተን ለወዲያኛው ዘለዓለማዊ ሕይወት እንደምንበቃ ተስፋ የማናደርግ ከሆነ ሁናቴአችን ሁሉ ትርጒም የሌለው ከንቱ ነው። ስለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ያለው:-

«በክርስቶስ ተስፋ የምናደርገው ለዚህ ዓለም ሕይወት ብቻ ከሆነ ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ የሚታዘንልን ምስኪኖች ነን» (1ኛ:ቆሮ:ም:15ቍ:19)።

ሰው ሲፈጠር ለመኖር እንጂ ለመሞት አልነበረም። ኃጢአት ስለሠራ ለሞት ተዳርጎአል። ለዚህ መድኀኒቱ ግን በንስሓ ተዘጋጅተን የምንጠብቀው የሙታን ትንሣኤ ነው። በሙታን ትንሣኤ ጊዜ ከተነሣን በኋላ እንደየተ ግባራችን ተገቢ ዋጋችን ተሰጥቶን ለዘለዓለም እንኖራለን እንጂ ከዚያ በኋላ ሞት አይኖርም። ይሁን እንጂ ዘለዓለማዊ ሥቃይ የሚፈረድባቸው ሰዎች ምንም ዕረፍት የማያገኙ ስለሆነ ያ ሥቃይ እንደ ሁለተኛ ሞት ይቈጠራል (ራእ፡ም: 20ቍ:6 እና 14)።

በማቴዎስ ወንጌል ም:25ቍ:31–46 እንደተገለጠው በሙታን ትንሣኤ ማለት በመጨረሻው ፍርድ ጊዜ ምን እንደሚሆን ሲያመለክት ጌታችን በመላእክቱ ታጅቦ እንደሚመጣ ይገልጣል። ከዚያም በክብር ዙፋኑ ላይ በመቀመጥ ጻድቃንን በቀኙ ኃጢአተኞችን በግራው ያቆማቸውና ፍርዱን ይሰጣል። ጻድቃን የፈጸሙትን በጎ ተግባር በመዘርዘርና በማመስገን ወደ ዘለዓለም ሕይወት እንዲገቡ ይፈቅድላቸዋል። ኃጢአተኞችን ደግሞ መፈጸም ሲገባቸው ያልፈጸሙትን ተግባር በመዘርዘር ወቅሶ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀው ዘለዓለማዊ እሳት ይልካቸዋል። ከሙታን ትንሣኤ በኋላ ለሰው ሁሉ ከሁለት አንዱ ፍርድ መስጠቱ ቍርጥ ስለሆነ በቀኝ በኩል ከሚቆሙት

www.ethiopianorthodox.org

ጻድቃን ጋር ዕድል ፈንታ ይኖረን ዘንድ ከአሁኑ መትጋት የምርጫ ግዴታ ነው።



የትእዛዛት ድምፅ የመላእክት አለቃ ድምፅ የእግዚአብሔር መለከትም ይሰማል ጌታ ራሱም ከሰማይ ይወርዳል:: (1ኛ ተሰ. ም: 4 ቍ 16)::

ክርስቶስ የሙታን ትንሣኤ በኩር ሆኖ የተነሣው የሙታን ትንሣኤ መኖሩን ሊያረጋግጥልን ፈቅዶ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው የኃጢአት ዋጋው ሞት ነው (ሮሜ:ም:6ቍ:23)። ክርስቶስ በመሞት የእኛን የኃጢአት ዋጋ ከመክፈሉም በላይ ከሞት በመነሣትም ሞትን ድል ነሥቶታል። እኛም የጌታችንን መንገድ በመከተል የዚህን ዓለም ዕድሜአችንን ካሳለፍነው ሁለተኛውን ሞት ድል የመንሣት ዕድል ይኖረናል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን በትንሣኤው ድል በነሣው ጊዜ የሞት ኃይል ለዘለዓለም ወደቀ። ቅዱሳንም ሞትንና የሞትን ምክንያቶች መፍራታቸው ቀረ። ሞትን የሚፈራ ንስሓ ያልገባ ኃጢአተኛ ብቻ ነው። ኃጢአተኛ ሰው ዓለማዊ ምኞቱን ስለሚያስቀርበት ሞትን ይፈራዋል። ጻድቅ ሰው ግን በሙታን ትንሣኤ ስለሚያምን ሞትን አይፈራውም። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ከክርስቶስ ጋር መሆን ከሁሉ የሚበልጥ ነገር ስለሆነ ከዚህ ሕይወት ተለይቼ ከክርስቶስ ጋር መሆን እፈልጋለሁ» ያለው (ፊል: ም:1 ቁ:23)። በእርግጥ ጌታችንንና የወዲያኛውን ሕይወት የሚወድዱ ሞትን ይመኙታል። ከዚህም ከተበላሸ ዓለም የተሻለ ሆኖ ያገኙታል። እነርሱም በሙታን ትንሣኤ የሚያምኑ ስለሆነ ሞትን የሚመለከቱት እንደመጥፋት ሳይሆን ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት እንደመዛወር አድርገው ነው።

## ነፍስ፥ ዘለዓለማዊ ፍርድና ሺህ ዓመት

የሰው ነፍስ:- የሰው ነፍስ ሲባል በሰው ተፈጥሮ ውስጥ ሕያው ሆኖ የሚኖረውና የማይሞተው ክፍል ነው። እግዚአብሔር ሰውን ከምድር ዐፈር ከፈጠረው በኋላ በአፍንጫው የማትሞት ነፍስን እፍ ብሎበት ሰው ሕያው



ነፍስ ያለው ፍጡር ሆነ። ነፍስም ሰው ሲሆን ደምሮ በሥጋው ያድራል፤ ተዋሕዶትም ይኖራል፤ የሚለየውም በሞት ጊዜ ነው (ዮሐ: ም: 19 ቍ: 30፥ 1ኛ:ጴጥ:ም:3ቍ:19)።

«ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከቀመሰ በኋላ ‹ተፈጸመ› አለ፤ ራሱንም ዘንበል አድርጎ ነፍሱን ሰጠ»(ዮሐ:ም:19ቍ:30)።

«ሥጋ ዐፈር ስለሆነ ወደ ዐፈር ይመለሳል፤ ነፍስም ወደ ፈጠራት ወደ እግዚአብሔር ትሄዳለች » (መክ: ም 12 ቍ: 7)።

ነፍስ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቀረበው በተለያዩ ትርጉሞች ነው። ከዚህም መካከል የሰው ሕይወት፥ የሰው ፈቃድ፥የእንስሳት ተፈጥሮ፥ስሜት፥ ሰው፥ እንስሳት ይገኙባቸዋል። ከእነዚህ ሌላ ግን ዋነኛውና እኛ አሁን የምንነጋገርበት የሰው ነፍስ ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ ወገኖች ነፍስ ማለት ሌሎቹ ትርጉሞች ናቸው እንጂ ከእግዚአብሔር የተሰጠና በሰውነት ውስጥ ሕያው የሆነ ክፍል፥ ማለት የማይሞት ክፍል የለም በማለት ይከራከራሉ። ለክርክራቸውም የሚያቀርቡአቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው።

በኦሪት ዘፍጥረት ም:2ቍ:7 ላይ:- «እግዚአብሔር አምላክ ከመሬት ዐፈር ወስዶ ሰውን ከዐፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም ሕይወትን የሚሰጥ እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕይወት ያለው ፍጡር ሆነ» የሚለውን ጥቅስ ወስደው የተቃራኒ ሐሳብ የሚያቀርቡት ሰዎች እንዲህ ይላሉ:- «ሰው ሕይወት ያለው ፍጡር ሆነ ማለት ነፍስ ሆነ እንጂ ነፍስ ተሰጠው አይልም»። ነፍስ የሚለው ቃል ሰው ማለት ስለሆነ ከዚያ ተለይቶ ሊታሰብ አይገባውም ይላሉ።

እኛ የምንጠይቃቸው ደግሞ እግዚአብሔር ሌሎቹን ፍጥረቶች ሁሉ ሲፈጥር በቃሉ ይሁን ከማለቱ በቀር ለሰው እንዳደረገው በአፍንጫው የሕይወት እስትንፋስ እፍ ያላለባቸው በምን ምክንያት ነው?

እንስሳቱን ነፍሳት ያለበት ምክንያት የሚንቀሳቀሱና የሚተነፍሱ በመሆናቸው ነው እንጂ እንደ ሰው የሕይወት እስትንፋስ እፍ ተብሎባቸው አይደለም። ሰውም የእግዚአብሔር እስትንፋስ የሆነው ነፍስ ስላለው በምድር በተፈጠሩ ፍጥረቶች ሁሉ ላይ የበላይ አስተዳዳሪ ሆኖ ተሾመ። እነርሱ እንደሚሉት በሰውነት ውስጥ ያለው ነፍስ ሕያው ነገር ባይሆን ኖሮ ለምን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ሥጋችሁን የሚገድሉትን አትፍሩ፤ ነፍሳችሁን ግን ለመግደል አይችሉም» አለ? ነፍስ የማይሞት የእግዚአብሔር ስጦታ ስለሆነ አይደለምን? ሌሎችም የሚያቀርቡአቸው ጥቅሶችና ለእነዚያ የተሰጡ መልሶች ቀጥለው ቀርበዋል:-

1ኛ:ቆሮ:ም:15ቍ:45:- «የመጀመሪያው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ ተብሎ ተጽፎአል፤ የመጨረሻው አዳም ክርስቶስ ግን ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ።» እዚህ ላይ አዳምን ሕያው ፍጡር ወይም ነፍስ በማለቱ ነፍስ የሚለው ቃል ሰው ማለት ነው እንጂ ከሰው የተለየ ፍጡር አይደለም ይላሉ።



www.ethiopianorthodox.org

ሰው ነፍስና ሥጋ ያለው እንደመሆኑ [illegible] ለባሽ እንደሚባል ሁሉ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ነፍስ መባሉ ሁለቱም የእርሱ የተፈጥሮ ይዘቶች በመሆናቸው ነው እንጂ ለነፍስ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ሆኖ አይደለም።

ዘፍ:ም:9 ቍ:5:- «ነፍሳችሁ ያለችበት ደማችሁ» በዚህ አባባል ነፍስንና ደምን አንድ ሊያደርጉአቸው ይፈልጋሉ። እግዚአብሔር ደም እንዳይበላ መከልከሉ ማንም ሰው ደሙ ፈሰሶ ካለቀ ስለሚሞት ወይም ነፍሱ ከሥጋው ስለሚለይ ሰውን አትግደሉ ለማለት ነው። ሌላው አማራጭ ትርጉም ደግሞ በዚያን ጊዜ በነበረው የመሥዋዕት ሥነ ሥርዓት የደምን አስፈላጊነት ለማመልከት ነው። ቀጠል አድርጎም ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ስለተፈጠረ የሰውን ደም አታፍስሱ ይላል። በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠረ የሚባለውም ሰው የተፈጠረው ከሥጋና ከደም ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር እስትንፋስ ከሆነው ከነፍስ ጭምር በመሆኑ ነው። ሌሎች እንስሳት ተንቀሳቃሾች በመሆናቸው ነፍሳት የሚባል ስም ቢሰጣቸውም የእግዚአብሔርን እስትንፋስ በአፍንጫቸው የተቀበሉ አይደሉም። የሚኖሩትም በደመ ነፍስ ነው።

ሕዝ <u>: ም:18ቍ:4:</u>- «ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ራስዋ ትሞታለች።»

<u>ማቴ:ም:10ቍ:28</u>:- «ነፍስንም፥ ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ።»

<u>ሐ:ሥ:ም:3ቍ:23</u>:- «ያን ነቢይ የማትሰማው ነፍስ ከሕዝብ ተለይታ ትጠፋለች።»

ከላይ በቀረቡት በትንቢተ ሕዝቅኤልና በሐዋርያት ሥራ ጥቅሶች ነፍስ የተባለው ሰው ለማለት ነው። በማቴዎስ ወንጌል ግን በፍርድ ቀን ሥጋና ነፍስ የሚወሐዱ መሆናቸውን ያመለክታል። በዚሁ በማቴዎስ ወንጌል ላይ የተነገረው በገሃነም ስለመሠቃየት ማለት ስለሁለተኛው ሞት ነው። ታዲያ፥ እነዚህንና መሰሎቹን ጥቅሶች እንደ አመጣጣቸውና እንደ ቅደም ተከተላቸው ተገቢውን ትርጉም በመተርጐም ፈንታ ነፍስ የምትባል ነዋሪ ነገር እንደሌለችና ብትኖርም ምናልባት በፍርድ ቀን የሚፈረድባቸው ሰዎች ንብረት የሆነች ነፍስ ሁሉ ብን ብላ እንደምትጠፋ እንጂ የዘለዓለም ሥቃይ እንደሌለ ለማስመሰል የሚጠቅሱአቸው ናቸው።

<u>መክ:ም:3ቍ:19</u>:- «በእርግጥም የሰው ልጅችና የእንስሳ ዕድል ፈንታ አንድ ዐይነት ነው፤ አንዱ እንደሚሞት ሌላውም እንዲሁ ይሞታል፤ የሁለቱም የተፈጥሮ እስትንፋስ አንድ ዐይነት ነው፤ ታዲያ ሁለቱም ከንቱ ስለሆኑ ሰው ከእንስሳ አይሻልም።»

ይህን ጥቅስ መነሻ በማድረግ ሰው ከእንስሳት የተለየ የሚያደርገው የማይሞት ነፍስ ስላለው ነው የሚለውን ሐሳብ ለመቃወም ይሞክራሉ። እነርሱ አላስተዋሉትም እንጂ ከቍጥር 19 ከመጀመር ይልቅ ከቍጥር 16 ጀምረው



ሊያገባቡ የጸሐፊውን [illegible] ሰዎች በሚፈጽሙአቸው ክፉ ተግባሮች ከአውሬ የማይሻሉ መሆናቸውን ነው። ሌላው ከእንስሳት ጋር ለማወዳደር የተፈለገበት ምክንያት የሰውን ከንቱነት ለማመልከትና የሰው በድን እንደ እንስሳት በድን ሁሉ ፈርሶ የሚበሰብስ መሆኑን ለማመልከት ነው እንጂ የሰው ነፍስና የእንስሳት ነፍስ አንድ ነው ለማለት አይደለም። የጸሐፊውን ትክክለኛ አስተሳሰብ ለመገንዘብ በዚሁ መጽሐፍ ምዕራፍ 12ቍ:7 ላይ ሥጋ ወደ ተፈጠረበት ምድር እንደሚመለስና ነፍስ ግን ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር እንደሚመለስ የሰጠውን መግለጫ ይመለከቷል።

የሰው ነፍስ የማይሞት ሕያው መሆኑን ከሚገልጡት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«እስትንፋሳቸውን ስትወስድባቸው ይሞታሉ፤ ወደ ተገኙበትም ዐፈር ይመለሳሉ፤ እስትንፋስ ስትሰጣቸው ግን ይፈጠራሉ» (መዝ:104 ቍ :29 – 30 )

«ማዳን ስለማይችሉ በመሪዎች ፥ ይም በማንኛውም ፍጡር አትተማመኑ፤ እነርሱ በሚሞቱበት ጊዜ ወደ ዐፈር ይመለሳሉ፤ በዚያኑ ቀን ዕቅዳቸው ሁሉ ይጠፋል» (መዝ:146ቍ:3–4)።

«ሥጋ ዐፈር ስለሆነ ወደ ዐፈር ይመለሳል፤ ነፍስም ወደ ፈጠራት ወደ እግዚአብሔር ትሄዳለች» (መክ:ም:12ቍ:7)።

«ሥጋን ከመግደል ሀልፈው ነፍስን መግደል የማይችሉትን ሰዎች አትፍሩ» (ማቴ:ም:10ቍ:28)።

ኢየሱስም ሆምጣጣውን ከተቀበለ በኋላ ተፈጸመ አለ፤ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን ሰጠ» (ዮሐ:ም:19ቍ:30)።

«በድንጋይ ሲወግሩት ሳሉ እስጢፋኖስ:- «ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ጸለየ» (የሐ:ሥ:ም:7ቍ:59)።

በጣም የሚገርመው ጉዳይ ግን የነፍስን ሕያውነትና ዘለዓለማዊነት የማያምኑት ወገኖች እነዚያን ከላይ የቀረቡትን አብዛኛዎቹን ጥቅሶች ለእምነታቸው እንደማስረጃ ማቅረባቸው ነው። ይህን ሲያደርጉ አንድም የጥቅሱ ትርጉም አልገባቸውም፤ ወይም ደግሞ ብዙ ማስረጃ ያላቸው ለማስመሰል ዐውቀው ጠቅሰዋቸው ነው። እውነት ግን መቼም ቢሆን ቦታውን አይስትም።

እኛ በነፍስ ሕያውነት የምናምነው፥ የቅዱሳት መጻሕፍትን ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ነው እንጂ እነርሱ እንደሚሉት ከግሪኮች አስተሳሰብና ከባቢሎናውያን ሃይማኖት በመቅዳት አይደለም።

<u>ዘለዓለማዊው ፍርድ</u>:- ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዘለዓለማዊው ፍርድ ሲናገር ንጉሡ በመላእክት ሁሉ ታጅቦ በመምጣት በክብር ዙፋኑ ላይ ይቀመጣል ብሏል። ከዚያም በበጎች የመሰላቸውን ጻድቃንን



www.ethiopianorthodox.org

በቀኙ፥ በፍየሎች የመሰላቸውን ኃጢአተኞችን በግራው ያቆሞና ዘለዓለማዊ ፍርዱን ይሰጣል። በቀኙ በኩል ያሉትን ካመሰገናቸው በኋላ ወደ ዘለዓለማዊ ደስታ ያስገባቸዋል፤ በግራ በኩል ያሉትን ስለ ኃጢአታቸው ከወቀሳቸው በኋላ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው ዘለዓለማዊ የሥቃይ ቦታ ይልካቸዋል ብሏል (ማቴ:ም:25ቍ:31–46)።

ጌታችንና የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች ሁሉ ይህን ዘለዓለማዊ ፍርድ ቢያረጋግጡም እንኳ አንዳንድ ወገኖች ዘለዓለማዊ ጽድቅ ቢኖርም ዘለዓለማዊ ኵነኔ የለም ይላሉ። እነርሱም ለዚህ አባባላቸው ማስረጃ ብለው ከሚያቀርቡአቸው ጥቅሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ራስዋ ትሞታለች» (ሕዝ: ም:18 ቍ:4፥20)።

«ነፍስንና ሥጋን በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ» (ማቴ: ም: 10ቍ:28)።

እነዚህ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ለዓላማቸው ደጋፊ ሆነው በማያገኙአቸው ጊዜ አንድም ከጉዳዩ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለውን ጥቅስ ይጠቅሳሉ፤ አለበለዚያም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆነ ምክያታዊነትን ያቀርባሉ። ከእነዚህም በአፈ ጮሌነት ከሚያቀርቡአቸው ትችቶች መካከል:- እግዚአብሔር ርኅሩኅና መሐሪ በመሆኑ ሰውን በዘለዓለማዊ ሥቃይ አይቀጣውም የሚለው ሐሳብ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ግልጥ ማስረጃ እንደሚያረጋግጠው ግን ጻድቃን ዘለዓለማዊ ሕይወት እንደሚሰጣቸውና በኃጢአተኞች ላይ ዘለዓለማዊ ሥቃይ እንደሚፈረድባቸው ነው።

ስለእግዚአብሔር ፍርድ ዘለዓለማዊነት ከተነገሩት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«ወጥተው ሲሄዱም በእኔ ላይ በማመፃቸው የተገደሉትን ሰዎች በድን ያያሉ፤ እነርሱን የሚበላቸው ትል አይሞትም፤ የሚያቃጥላቸውም እሳት አይጠፋም፤ እነርሱን የሚያያቸው የሰው ዘር ሁሉ ይጸየፋቸዋል» (ኢሳ:ም: 66ቍ:24)።

«በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎቹ ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘለዓለም ሕይወት እኩሌቶቹ ደግሞ ወደ ዕፍረትና ወደ ዘለዓለም ጉስቍልና» (ዳን:ም:12ቍ:2)።

«በዚያን ጊዜ በግራው በኩል ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል:- እናንተ ርጉማን ለሰይጣን እና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘለዓለም እሳት ከእኔ ወዲያ ሂዱ» (ማቴ:ም:25ቍ:41)።

«ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግዱ፥ ምልክቱንም በግንባራቸው ወይም በእጃቸው የሚያደርጉ ሁሉ በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሠቃያሉ፤ እነርሱን



ከሚያሠቃየው እሳት የሚወጣው ጢስ ለዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ወደ ላይ ይወጣል፤ ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግዱ የስሙንም ምልክት ያደረጉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም» (ራእ:ዮ:ም14ቍ:9–11)

«ያሳታቸው ዲያብሎስ፥ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወደ አሉበት በዲን በሚቃጠል እሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ፤ ሌሊትና ቀን ለዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ይሠቃያሉ» (ራእ:ዮ:ም:20ቍ:10)።

«ነገር ግን ፈሪዎች፥ እምነተቢሶች፥ ርኩሶች፥ ነፍሰ ገዳዮች፥ አመንዝሮች፥ አስማተኞች ጣዖት አምላኪዎች፥ ውሸታሞች ሁሉ ዕጣ ክፍላቸው በዲን በሚቃጠለው በእሳት ባሕር ውስጥ ይሆናል፤ ይህም ሁለተኛው ሞት ነው» (ራእ:ዮ:ም:21ቍ:8)።

የዘለዓለማዊ ፍርድ እምነታችንም በዚህ ዓይነት በቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃነት የተመሠረተ ነው እንጂ እነርሱ እንደሚሉት በባቢሎናውያን፥ በአሦራውያንና በቡዳ እምነቶች ላይ የተመሠረተ አይደለም። ለእምነታቸው ማስረጃ የሚሆን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በሚያጡበት ጊዜ መሠረትነት የሌለው ዓለማዊ ምክንያቶችን ማቅረብ፥ ወይም ደግሞ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ራሳቸው ከፈለሰፉት ትርጓሜ ጋር ማቅረብ ልማዳቸው ነውና አባባላቸው ሊያስገርመን አይገባም።

ሺህ ዓመት:- በቅዱሳት መጻሕፍት በተለያዩ ቦታዎች በግልጥ እንደተነገረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ ወደዚህ ዓለም የሚመጣው ማንም ሰው ሊያውቅ በማይችልበትና ለአንድ ጊዜ ብቻ መሆኑን እናንብባለን። ይሁን እንጂ አንዳንድ ወገኖች የራእየ ዮሐንስን ምዕራፍ 20 አባባል መሠረት በማድረግ ጌታችን ከቅዱሳኑ ጋር የአንድ ሺህ ዓመት ምድራዊ ንግሥ ለመንገሥ ከመጨረሻው ፍርዱ በፊት ይመጣል ይላሉ። ይህንንም ለማለት የበቁት የራእዩን ትርጓሜ በፊደል ወይም ቃል በቃል የእምነታቸው መሠረት እንዲሆን ስላደረጉ ነው።

ይህ አስተሳሰብ አዲስ አይደለም። ክርስትና በተጀመረበት ዘመን ከአይሁድ ወገን የሆኑ ክርስቲያኖች ተመሳሳይ አስተሳሰብ ነበራቸው። እነርሱም የቀድሞ ክብራቸውን የመመኘት ዝንባሌ አደረባቸው። በሰብአዊነታቸው ይህን ምድራዊ ክብር ተመኙ። እንደሚታወቀው ቤተ መቅደስ ፈረሰ፤ ኢየሩሳሌም ተቃጠለች፤ በጌታችንም ትንቢትና ማስጠንቀቂያ መሠረት ሕዝቡ በሚያሳዝን ሁናቴ ተፈጀ። ይህን የቃል በቃል ትርጓሜ የተመኙት ለዚህ ችግር ማካካሻ ያገኙ መስሎአቸው ነው። ከክርስቶስ ጋር አንድ ሺህ ዓመት የመንገሥን ምድራዊ ክብር ተመኙ።

ቤተ ክርስቲያን ከመሳደድ ዐርፋ ሰላም ባገኘች ጊዜ ይህን የቃል በቃል ትርጓሜ መቃወም ጀመረች። በጥብቅ ከተቃወሙትም መካከል ፓትርያርክ ዲዮናስዮስና ሌሎችም መምህራን ይገኙበታል። እነርሱም ትርጓሜ መሰጠት

www.ethiopianorthodox.org

ያለበት ምሳሌያዊ አነጋገር መሆኑ ታውቆ ነው እንጂ እንዳለ ቃል በቃል ታምኖበት አይደለም ብለዋል።

ነገሮችን በምሳሌ ማቅረቡም የራእዩ መጽሐፍ ጠባይ ነው። ለምሳሌ የሚከተሉትን ጉዳዮች እንመልከት።

1. መልአኩ ሰይጣንን በትልቅ ሰንሰለት አሰረው ይላል። ሰይጣን መንፈስ እንደመሆኑ በሰንሰለት ሊታሰር የሚችል አይደለም (ም:20ቍ:1–2) ። ሲኦል ደግሞ መናፍስትን አግብቶ ለማሰርና ለመቈለፍ ቁሳዊ ቁልፍ ያለው አይደለም።

2. ሰማይና ምድር ከእግዚአብሔር ፊት ሸሹ ሲባል መንፈሳዊ ትርጓሜ እንጂ የቃል በቃል ትርጓሜ ያለው አይደለም (ም:20ቍ:11)።

3. ሞትና ሲኦል በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ ሲል የቃል በቃል ትርጓሜ እንደማይሆን ግልጥ ነው (ም:20ቍ:14)።

<u>ስለ ጉዳዩ መንፈሳዊ አስተያየት</u>:- ይህ የቃል በቃል ትርጓሜ ራእየ ዮሐንስን የተወሳሰበ ያደርገዋል። መንፈሳዊው አስተያየት ግን ቀላልና ከምድራዊ ንግሥ ጋር ያልተያያዘ ነው። በቁሳዊ ነገርና በዓለማዊ ክብር ላይ ተመሥርቶ አምስት ወይም ዐሥር ከተሞችን አሸንፎ የሚይዝ አይደለም። ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ሰይጣንን የጣለ መሆኑን የሚገልጥ ነው።

«ሰይጣንን እንደመብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ» (ሉቃ:ም:10ቍ:18)።

«አሁን የዚህ ዓለም ገዥ (ሰይጣን) ወደ ውጪ ይጣላል» (ዮሐ: ም:12ቍ:31)።

«ስለ ፍርድ የሚያስረዳው የዚህ ዓለም ገዥ ስለተፈረደበት ነው» (ዮሐ:ም:16ቍ:11)።

ሰይጣን ታሰረ ማለት፥ በሰዎች ላይ ከሚያደርገው ተጽዕኖ ታገደ ወይም ተገታ ማለት ነው። ከዚያ በኋላ እኛ ካልፈቀድንለት በስተቀር በእኛ ላይ ሥልጣን የለውም።

የአንድ ሺህ ዘመን ንግሥ ደግሞ በዚያን ዘመን የመንግሥትን ወይም የንጉሥነትን ሕይወት ስለምናካሄድ ነው። ይህም የሆነው እግዚአብሔር ራሳችንን ለመግዛት ነገሥታት ስላደረገን ነው። ጌታችን:- «እነሆ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ነች» ብሎናል (ሉቃ:ም:17ቍ:21)።

ሺህ ዓመት የተባለው ያልተወሰነ ጊዜ ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፥ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን ነው (2ኛ:ጴጥ: ም:3ቍ:8)።

ባለ ሺህ ዓመት ንግሥ አማኞች ማስረጃ ብለው ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የሚያቀርቡአቸው ጥቅሶች የራሳቸው መንፈሳዊ ትርጓሜዎች አሉአቸው። ለምሳሌም በብሉይ ኪዳን ማስረጃዎች ብለው ከሚያቀርቡአቸው ጥቅሶች



መካከል ምን ዐይነት መንፈሳዊ ትርጓሜ እንዳላቸው ለመረዳት ቀጥሎ ለናሙና ያኽል የቀረቡትን እንመልከት:-

<u>ኢሳ:ም:11 እና 12</u>:- በዚህ ትንቢት ውስጥ ተኵላ ከበግ ጠቦት ጋር፥ ነብር ከፍየል ጠቦት ጋር ይተኛሉ፤ ጥጃና ፍሪዳም ከአንበሳ ደቦል ጋር በአንድነት ያድራሉ ተብሎአል።

ጡት የሚጠባው ሕፃን በእባብ ጒድጓድ ላይ መጫወቱና በእፉኝት ቤት ላይ እጁን መጫኑ የሚያመለክተው የክርስቲያንነትን ቅን ልቡናና በዚህ ዓለም ጥበብ ላይ ድል መንሣቱን ነው።

<u>ኢሳ:ም:65</u>:- እነሆ፥ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እፈጥራለሁ፤ እነሆ፥ ኢየሩሳሌምን ለሐሴት፥ ሕዝብዋንም ለደስታ እፈጥራለሁና... ቤቶችን ይሠራሉ፤ ይቀመጡባትማል።

ይህ አባባል ነፍስን አሳርፎ፥ ልብን የሚያስደስተውንና በፍሬውም የሚያጠግበውን ወደፊት ሊመጣ ያለውን የክርስቶስን አዳኝነት ያመለክታል።

<u>ዘካ:ም:14</u>:- አሕዛብን ሁሉ በኢየሩሳሌም ላይ ለሰልፍ እሰበስባለሁ፤ ከተማይቱ ትያዛለች፤ ቤቶችም ይበዘበዛሉ፤ ... እግዚአብሔር ይወጣል፤ በሰልፍም ቀን እንደተዋጋ ከእነዚያ አሕዛብ ጋር ይዋጋል።.... ደብረ ዘይትም በመካከል ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ይሰነጠቃል፤ እጅግም ታላቅ ሸለቆ ይሆናል።

በእርግጥ ይህ ሁሉ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። ጦርነቱም የስሜት ወይም የመንፈስ ይሆናል። ሸለቆ ለመሆን የሚሰነጠቀውም ተራራ በጸጋ ምንጭ የመንፈስ መርካት ነው እንጂ ሌሎች ወገኖች እንደሚሉት ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በመርከብ መሳፈር እስከሚያስፈልግ ድረስ የውሃ መሙላት አይደለም።

መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለም ያለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ላይ ሺህ ዓመት ምድራዊ ንግሥ ይነግሣል ማለት የእርሱን ማረጋገጫ መቃወም ነው (ዮሐ:18:36) ።

የተለመደው አሠራር፥ ጠንከር ያለውን ሐሳብ በቀላል አገላለጽ ማስረዳት እንጂ ቀላሉን ሐሳብ ጠንከር ባለ መንገድ ማብራራት አይደለም።

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25 የተመለከትን እንደሆነ የደጎችና የክፉዎች ሰዎች ፍርድ አንድ ጊዜ ብቻ መሆኑን እንረዳለን። ሰዎችን ሁሉ በአንድነት ሰብስቦ በቀኙ በኩል ያሉትን ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ሲያሰባስባቸው በግራው በኩል ያሉትን ደግሞ ወደ ዘለዓለማዊ ሥቃይ ልኮአቸዋል። በዚህ ዐይነት እነዚህኛዎቹ ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ሲሄዱ እነዚያኛዎቹ ደግሞ ወደ ዘለዓለማዊ ሥቃይ ይሄዳሉ (ማቴ:ም:25ቍ:31–46)።

ወደ ዮሐንስ ወንጌል መለስ ያልን እንደሆነ ደግሞ የሚከተለውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ንግግር እናነብባለን:-

www.ethiopianorthodox.org

«በዚህ ነገር አትደነቁ፤ በመቃብር ውስጥ ያሉት ሁሉ የእርሱን ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል። መልካም የሠሩ ከሞት ተነሥተው በሕይወት ይኖራሉ፤ ክፉ የሠሩ ከሞት ተነሥተው ይፈረድባቸዋል» (ዮሐ: ም: 5 ቍ: 28–29)።

በዚህም አባባል መሠረት የጌታችን ዳግመኛ መምጣት አንድ ብቻ፥ የሙታን ትንሣኤ አንድ ብቻ፥ እንዲሁም ሁለተኛው ሞት አንድ ብቻ መሆናቸው ግልፕ ነው። አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት የድብቅና የግልፕ መምጣት፥ ማለት ሁለት መምጣት የለም። የጻድቃን ትንሣኤና የኃጥአን ትንሣኤ ለየብቻው አይደለም።

የሲኦልን መክፈቻና ትልቅ ሰንሰለት የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ መታየቱ ተገልጾአል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የሞትና የሲኦል መክፈቻ አለኝ» ማለቱ ይታወቃል (ራ:ዮሐ:ም:1ቍ:18)። ሰይጣንን እንዲያስር ለመልአኩ ሥልጣን የሰጠው ጌታችን ነው።

ሆኖም ሰይጣን መንፈስ ስለሆነ መልአኩ ይዞታል የተባለው ቁሳዊ ማሰሪያ ሳይሆን ሰይጣን በሰብአዊ ፍጡር ላይ ከሚያመጣው ጉዳት ነጻነቱን መገደብ ማለት ነው።

መልአኩ ሰይጣኑን ይዞ አንድ ሺህ ዓመት አሰረው ሲባል በታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ዕቅድ የሚፈጸምበት አንድ የተወሰነ ረጅም ዘመን ማለት ነው። ወደ ሲኦል ጥሎ ቈለፈበት ማለት ያ የተወሰነው ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ሕዝብን እንዳያስት በይፋ መከልከል ማለት ነው። ይህም ሺህ ዘመን ከስቅለት ጀምሮ እስከመጨረሻው ዘመን ለጥቂት ጊዜ እስከሚፈታበት ወቅት ድረስ ነው። በማኅተም አትሞ መዝጋቱ አንዳንዶች እንደሚመስላቸው ለሰይጣን የመጨረሻ የንስሓ ዕድል ለመስጠት ሳይሆን ምእመናን የበለጠ ፍጹማን እንዲሆኑ ለማመቻቸት ነው። ሰይጣን በወደቀ ጊዜ ሁለንተናው የጨለመ ስለሆነ የንስሓ ዕድል የለውም።

እንዲሁም ባለ ራእዩ የመፍረድ ሥልጣን የተሰጣቸው የተቀመጡባቸውን ዙፋኖች ማየቱን ገልጾአል። የእግዚአብሔር ልጆች በሕይወት ያሉ ወይም የሞቱ ለአውሬው ያልሰገዱ ሰማዕታት ወይም ቅዱሳን ሁሉም በክርስቶስ ዕቅፍ ሥር በዚያን ጊዜ በገነት ወይም በምድር ሆነው ይነግሣሉ። ቀሪዎቹ ሟቾች ግን አንድ ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ አይኖሩም። ይህም ማለት ኃጢአት በመሥራታቸው እንደሞቱ ይቈጠራሉ ማለት ነው። ይህም የመንፈስ ሞት ስለሆነ በአዲሱ የንግሥ ዘመን የመደሰት ዕድል አላጋጠማቸውም ማለት ነው። በሌላ አባባል የመጀመሪያው ተንሣኤ ማለት ከኃጢአት መቃብር መነሣት ወይም ትንሣኤ ልቡና ማለት ነው። ይህም «አንተ የምታንቀላፋ ንቃ፤ ከሞትም ተነሥ» ተብሎ እንደተጻፈው ነው (ኤፌ:ም:5ቍ:14) ። ወይም ጌታችን እንዳለው:- «የሞቱ ሰዎች የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ጊዜ



www.ethiopianorthodox.org

ይመጣል፤ ጊዜውም አሁን ነው፤ የሚሰሙትም ሁሉ በሕይወት ይኖራሉ» (ዮሐ:ም:5ቍ:25)።

ሺሁ ዓመት በተፈጸመ ጊዜ ማለት በመጨረሻው ዘመን በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል። በዚህ ሁኔታ ክፋት ይበዛል፤ የብዙዎች ፍቅር ይቀዘቅዛል (ማቴ:ም:24ቍ:12)።

ስለእነዚያ ቀኖች ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክት ውስጥ እንዲህ ብሎ የተናገረው:- «መንፈስ ቅዱስ ግን በግልፕ እንዲህ ይላል፤ <በኋለኛው ዘመን አንዳንድ ሰዎች አሳሳች መናፍስትንና የአጋንንትን ትምህርት በመከተል ሃይማኖትን ይክዳሉ። እንዲህም ዐይነቱ ትምህርት የሚመነጨው በግብዝነት፥ ሐሰትን ሲናሩ በጋለ ብረት እንደተተኰሰ ያኽል ሆኖ የደነዘዘ ኅሊናቸው ከማይወቅሳቸው ሰዎች ነው» (1ኛ:ጢሞ:4:1–2) ። ይህንኑ አባባሉን በሁለተኛው መልእክቱ ደግሞታል።

«ሰዎች ራሳቸውን የሚወድዱ ይሆናሉ።» (2ኛ:ጢሞ:ም:3ቍ1–9)። ስለዚሁ ጉዳይ እንደገና በ2ኛ ተሰ:ም:2ቍ:1–12 ተናግሮአል። በዚህም ውስጥ ስለመጨረሻው ዘመን፥ ስለ ሰይጣን ከእስራቱ መፈታት፥ ስለ ሐሳዌ መሲሕና ብዙ ተአምራትን ስለሚያደርገው ስለ ሐሰተኛው ነቢይ ይናገራል።

ሰይጣን የጎግና ማጎግን ሕዝብ ለማሳት ከእስራቱ ተለቅቆ ወጣ። እነርሱንም ለጦርነት አሰለፋቸው። የቅዱሳንም ሰፈርና የተወደደችውን ከተማ ከበቡ። ይህ አባባል ቃል በቃል ኢየሩሳሌም ማለት ሳይሆን በምድር ሁሉ የሚገኙትን የእግዚአብሔር ልጆች ለማለት ነው። እነርሱም የተወደደችው ከተማ ናቸው። ስለዚህ እግዚአብሔር ከሰማይ እሳት አውርዶ ጠላቶችን ይበላና ልጆቹን ያድናል።

ሰይጣን ወደ እሳትና ክብሪት ሐይቅ ይጣላል፤ በዚህም ከሐሳዊ መሲሑ፥ ከሐሰተኛው ነቢይና ከአውሬው ጋር አብሮ የዘለዓለምን ሥቃይ ይወርሳል፤ ይህም የመጨረሻው ፍርድ ነው።

ከዚህ በኋላ ባለራእዩ ካለፉት ዙፋኖች ሁሉ የበለጠ ትልቅ ነጭ ዙፋን አየ። ትልቅነቱ ውሱንነት ለሌለው ለእግዚአብሔር ክብር ምሳሌ ሲሆን፥ ነጭነቱ ደግሞ የፍጹም ቅድስናው ምሳሌ ነው።

## የምዕራፉ አጠቃላይ ሐሳብ:-

1. መልአክ ከሰማይ ወረደ፤ ሰይጣንን አሰረው፤ ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ ወደ ሲኦል ጣለው፤ ከዚያ በኋላ ለጥቂት ጊዜ መፈታት አለበት።
2. በዚህ በሺህ ዓመት ጊዜ ሰማዕታትም ሆኑ ቅዱሳን የእግዚአብሔር ልጆች በዙፋን ላይ ተቀመጡ። የመጀመሪያውን ትንሣኤ (ንስሐ) የተነሡ ሁለተኛው ሞት (ዘለዓለማዊ ሥቃይ) አይጐዳቸውም፤ ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር እንደ ነገሥታትና እንደ ካህናት ይኖራሉ፥ እዚህ የሚኖሩት የመንፈሳዊ ኑሮ ለዘለዓለማዊው ክብር መያዣ (ቀብድ) ነው።

3. ይህ ሺህ ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል፤ ጎግ፥ ማጎግንና ሁሉንም ለጦርነት ይሰበስባል። ከዚያም የቅዱሳንን ሰፈር ያጠቃና ከሰማይ እሳት ወርዶ ይበላቸዋል።

4. ከዚያም በኋላ ሰይጣን፥ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ለዘለዓለም በሚሠቃዩበት በእሳት ሐይቅ ውስጥ ይጣላሉ።

5. ጌታችንም አስፈሪ በሆነው በነጭ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ለጻድቃንና ለኃጢአተኞች ፍርዱን ይሰጣል። ጻድቃን ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ሲሄዱ ኃጢአተኞች ግን ወደ ዘለዓለማዊ ሥቃይ ይላካሉ። ይህም ዘለዓለማዊ ሥቃይ ሁለተኛ ሞት ነው።

<u>ጌታችን ዳግመኛ የሚመጣው አንድ ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ</u>:- በወንጌሎችና በተለያዩ መልእክቶች እንደተገለጠው ጌታችን ዳግመኛ የሚመጣበት ጊዜ ማንም በማያውቀው፥ በድንገትና አንድ ጊዜ ብቻ ነው።

ጌታችን ከቅዱሳኑ ጋር ምድራዊ ንግሥ ለመንገሥ ወደዚህ ዓለም ይመጣል የሚሉት ሰዎች እምነታቸውን የመሠረቱት በራእየ ዮሐንስ ምዕራፍ 20 ላይ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደፊት ለሚሆኑ ለብዙ ነገሮች ግልጽ የሆኑ ትንቢቶችን የተናገረ ሲሆን ስለሺህ ዓመት ንግሥ ጉዳይ ምንም የተናገረው ነገር የለም። ራእየ ዮሐንስን የጻፈው ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ራሱ ከዚያ ሌላ አንድ ወንጌልና ሦስት መልእክቶችን የጻፈ ሆኖ ሳለ ስለሺህ ዘመን ንግሥ ያነሣው ነገር የለም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስና ሌሎች መልእክቶችን የጻፉ ሐዋርያትም ሰለ ሐሰተኛ መሲሕና ስለ ሐሰተኛ ነቢይ መነሣት እንጂ ስለሺህ ዘመን የክርስቶስ ምድራዊ ንግሥ ምንም የተናገሩት ነገር የለም።

ታዲያ፥ ጌታችንም ሆነ የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች ስለ ሺህ ዓመት ንግሥ ሳይናገሩ ያለፉት ለምንድነው?

ይህ የሆነበት ምክንያት በራእየ ዮሐንስ ውስጥ የተነገረው የአንድ ሺህ ዓመት ንግሥ ትንቢታዊ ራእይ በመሆኑና፥ ራእይንና ትንቢትን ደግሞ ማንም ሰው እንደፈለገ ሊተረጉማቸው የማይችል በመሆኑ ነው። ይህንንም በሚከተሉት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች እንመልከት።

1. ራእይንና ሕልምን ማንም ሰው እንዳሻው ሊተረጉማቸው ባለመቻሉ የፈርዖንን ሕልም ለመተርጐም ዮሴፍ፥ የናቡከደነፆርን ሕልም ለመተርጐም ደግሞ ዳንኤል አስፈልገዋል (ዘፍ:ም:40፥ዳን:ም:2)።

2. የትንቢት ትርጉም በጣም ከባድ ከመሆኑ የተነሣ ትንቢቱን ለተናገሩት ሰዎች እንኳ ምሥጢር የሚሆንበት ጊዜ መኖሩን በሚከተሉት ጥቅሶች እንመልከት። «ሰማሁም፤ ነገር ግን አላስተዋልሁም፤ የዚያን ጊዜም:- ጌታዬ ሆይ፥ የዚህ ሁሉ ፍጻሜ ምንድር ነው? አልሁ። እርሱም እንዲህ አለኝ:- ዳንኤል ሆይ፥ ቃሉ እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ የተዘጋና የታተመ ነውና ሂድ» (ዳን:ም:12ቍ:8–9)።



«ከእኔ ጋር ይነጋገር ለነበረው መልአክ መልሼ:- ጌታዬ ሆይ፥ እነዚህ ምንድር ናቸው? አልሁት። ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረውም መልአክ መልሶ:- እነዚህ ምን እንደሆኑ አታውቅምን? አለኝ፤ እኔም:- ጌታዬ ሆይ አላውቅም አልሁት» (ዘካ:ም:4ቍ:4–5)።

3. በትንቢተ ሚልክያስ ም:4ቍ:5–6 በኤልያስ ስም የተነገረው ትንቢት ስለመጥምቁ ዮሐንስ የተነገረ መሆኑን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ም:17ቍ:10–12 ላይ የገለጸው የትንቢት አባባሎች ቃል በቃል የማይተረጐሙ በመሆናቸውና የትንቢቱንም ትርጉም ማንም ሰው ሊያውቀው የማይችለው በመሆኑ ነው።

4. «ከሁሉ በፊት ማስተዋል የሚገባችሁ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም ትንቢት ማንም ሰው በራሱ ግላዊ አስተሳሰብ ሊተረጉም አለመቻሉን ነው። ማንኛውም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣም፤ ነገር ግን ትንቢት በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር ተቀብለው የተናገሩት ነው» (2ኛ:ጴ:ም:1ቍ:20–21)

በራእየ ዮሐንስ ም:20 ላይ የተዘረዘረው ትንቢታዊ ራእይ በመሆኑና ራእይንና ትንቢትን ደግሞ ከላይ በቀረቡት ማስረጃዎች መሠረት ማንም ሰው እንደፈለገ ሊተርጉማቸው ስለማይችል የክርስቶስን ወደዚህ ዓለም መመለስና ምድራዊ ንግሥ መንገሥ እምነት በራእይ መጽሐፍ አባባል ላይ መመሥረት ነፋስን እንደመጨበጥ ይቈጠራል። ለሌሎች ጉዳዮች የተነገሩትን ጥቅሶች ለዚህ ለሺህ ዓመት ንግሥ እንደተነገሩ ለማስመሰል ከመሞከር በቀር በማናቸውም የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል ውስጥ የቀረበ ግልጥ ማስረጃ እንደሌለ ለመረዳት ጥቅሶቹን ትክ ብለን ብንመለከታቸው ከመሳሳት እንድናለን።

የሺህ ዓመት ንግሥ አማኞች እንደሚሉት ይህ ጉዳይ ቃል በቃል መተርጐም የሚገባው ጉዳይ ቢሆን ኖሮ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች መካከል አንዳቸው እንኳ በግልጥ ባቀረበው ነበር። እነርሱ ግን ይህን ያላደረጉት ያ ክፍል ከቃል ለቃል ትርጉም ሌላ ምሥጢራዊ ትርጉም ያለው እንጂ በቃል ለቃል ትርጉም የማይወሰን በመሆኑ ነው።

ስለዚህ እኛ ወደፊት በዚህ ምድር ላይ ከክርስቶስ ጋር አንድ ሺህ ዓመት እንነግሣለን ብለን ለምድራዊ ክብር ከመጓጓት ይልቅ እግዚአብሔር በሰማይ ላዘጋጀልን ከተማ መጓጓትና እርሱንም መናፈቅ ይገባናል (ዕብ: ም: 11 ቍ:15–16)።

(የትምህርተ መለኮተን መጽሐፍ ይመለከቷል)

## <u>ጥያቄዎች</u>

1. እግዚአብሔር ለሰው ዘር የሰጠው ስጦታ ስንት ነው?
2. ስጦታዎቹ በአጠቃላይ በስንት ይከፈላሉ?

www.ethiopianorthodox.org

3. የሚከፈሉትስ በምንና በምን ነው?
4. መንፈሳዊ ስጦታዎች ስንል ምን ማለታችን ነው?
5. ሦስት የመንፈሳዊ ስጦታዎችን ምሳሌ አቅርብ።
6. ስለዓለማዊ ስጦታዎች ምሳሌዎችን አቅርብ።
7. የሙታን ትንሣኤ ስንል ምን ማለታችን ነው?
8. የሰው አሟሟት እንዴት ነው?
9. የሙታን ትንሣኤስ እንዴት ነው?
10. ክርስቶሰ የሙታን ትንሣኤ በኵር ነው የተባለው በምን ምክንያት ነው?
11. የሙታን ትንሣኤ ዋነኛው ተስፋችን ነው የተባለው ለምንድነው?
12. ሰው የተፈጠረው እንዲሞት ነበርን?
13. ሞት የመጣው ለምንድን ነው?
14. አንደኛና ሁለተኛ ሞት በምን ይለያሉ?
15. በሙታን ትንሣኤ ጊዜ ጌታችን የሚመጣው እንደምን ሆኖ ነው?
16. ከዚያስ በኋላ ምን ያደርጋል?
17. ጻድቃንና ኃጢአተኞች በምንና በምን ይመሰላሉ?
18. ጻድቃንን ምን ይላቸዋል?
19. ኃጢአተኞችንስ ምን ይላቸዋል?
20. ክርስቶስ የሙታን ትንሣኤ በኵር የሆነልን በምን ምክንያት ነው?
21. የሞት ኀይል ድል የተነሣው መቼ ነው?
22. ሞትን የሚፈራ እንደምን ያለ ሰው ነው?
23. ለምንስ ሞትን ይፈራዋል?
24. ሞትን የሚመኙት እነማን ናቸው?
25. ሞትንስ የሚመለከቱት እንደምን አድርገው ነው?
26. የሰው ነፍስ ማለት ምን ማለት ነው?
27. ሰው ሕያው ነፍስ ያለው ፍጡር የሆነው መቼ ነው?
28. ነፍስ በሰው ሥጋ የሚያድረው መቼ ነው?
29. ነፍስ ከሥጋ የሚለየው መቼ ነው?
30. የሰውን ነፍስ ሕያውነት የሚቃወሙ ሰዎች ምን ይላሉ?
31. ነፍስ ለሚለው ቃል ሌሎች ምን ትርጉሞች አሉ?
32. እንስሳት ነፍሳት የተባሉት በምን ምክንያት ነው?
33. የእንስሳትና የሰው አፈጣጠር በምን ይለያል?
34. ነፍስ የማይሞት መሆኑን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያረጋገጠው ምን ብሎ ነው?



www.ethiopianorthodox.org

35. ክርስትና በተጀመረበት ዘመን ስለሺህ ዓመት ንግሥ ቃል በቃል ትርጉም ያምኑ የነበሩ ክርስቲያኖች እነማን ነበሩ? ምክንያታቸውስ ምን ነበር?
36. የሺህ ዓመትን የቃል በቃል ትርጓሜ ከተቃወሙት የቀድሞ አባቶች መካከል እነማን ነበሩበት?
37. የሰይጣን መታሰር ማለት ምን ማለት ነው?
38. ሺህ ዓመት የተባለው ምን ለማለት ተፈልጎ ነው?
39. አብረው ሊኖሩ የማይችሉት አውሬዎች አብረው ይኖራሉ ተብሎ በኢሳ:ም:11 እና 12 የተነገረው ትንቢት ምን ለማለት ተፈልጎ ነው?
40. በትንቢተ ኢሳይያስ ም:65 ላይ እነሆ፥ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እፈጥራለሁ የሚለውስ ምን ለማለት ነው?
41. የትንቢተ ዘካርያስ ም:14 ትንቢትስ ምንን የሚያመለክት ነው?
42. የመጀመሪያው ትንሣኤ ማለት ምን ማለት ነው?
43. የራእየ ዮሐንሱ ሺህ ዓመት ንግሥ በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ሳይጠቀስ የታለፈው ለምንድነው።

# ምዕራፍ 2

# መጽሐፍ ቅዱስ

## ብሉይ ኪዳን

<u>በግብጽ ላይ የወረዱ መቅሠፍቶች</u>:- የግብጹ ንጉሥ ፈርዖን የእስራኤልን ሕዝብ ከባርነት ቀንበር ለቅቆ እግዚአብሔር ወደ ወሰነው ቦታ እንዲሄድ ለማድረግ በሙሴና በአሮን አማካይነት ተመላልሶ የተጠየቀውን ጥያቄ በእልኸኛነት እምቢተኛ በመሆኑ እርሱን አስገድዶ የእስራኤልን ሕዝብ ነጻ ለማውጣት እግዚአብሔር በግብጽ ሕዝብ ላይ ዐሥር መቅሠፍቶችን አወረደ።

1. <u>የውሃው ወደ ደም መለወጥ</u>:- አሮን በትሩን ወደ እባብነት በለወጠ ጊዜ የግብጽ አስማተኞችም እንዲሁ ስላደረጉ ፈርዖን ልቡን አደንድኖ ነበር። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ንጉሡን ወደ ወንዝ ሲሄድ አገኘውና የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር «በበረሓ ያገለግሉኝ ዘንድ ሕዝቡን ልቀቅ ይልሃል» ብሎ ነገረው። አንተ ግን በእምቢተኛነትህ ስለጸናህ እኔ ዛሬ የወንዙን ውሃ መትቼ ወደ ደም እለውጠዋለሁ አለው። አሮን እጁን አንሥቶ ውሃውን እንዲመታ እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው። አሮንም እጁን አንሥቶ በንጉሡና በመኳንንቱ ፊት የወንዙን ውሃ መታው። የወንዙም ውሃ ተለውጦ ደም ሆነ። በወንዙ ውስጥ ያሉት ዓሣዎች ሁሉ ሞቱ። ውሃውም መጥፎ ሽታ ስላመጣ ግብጻውያን ሊጠጡት አልቻሉም የንጉሡ አስማተኞችም

በአስማታቸው እንደዚያው ስላደረጉ ልቡን በማጽናቱ ሙሴንና አሮንን የማያዳምጣቸው ሆነ።

2. <u>የሀገሪቱ በጓጉንቸር መሸፈን</u>:- እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ወደ ፈርዖን ላከው:- «ያገለግለኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ፤ በእምቢተኛነትህ ብትቀጥል ግን ሀገርህን ሁሉ በጓጉንቸር እሸፍነዋለሁ፤ ጓጉንቸሮቹም ከወንዙ በብዛት ወጥተው ወደ ቤትህ፥ ወደ መኝታ ቤትህ፥ ወደ አልጋህ፥ ወደ ምድጃህና ወደ ቡኾ ዕቃህ ሳይቀር ይመጣሉ፤ ይህም በአንተ ቤት ብቻ ሳይሆን በባለሟሎችህና በሕዝብህ ሁሉ ላይ ይሆናል።» ሙሴም በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት ውሃ ባለበት ሁሉ ላይ በትሩን እንዲዘረጋ አሮንን አዘዘው። አሮንም በትሩን በዘረጋ ጊዜ ጓጉንቸሮች ሀገሪቱን ሞሉአት። ይሁን እንጂ አስማተኞችም በአስማታቸው እንዲሁ አደረጉ።

ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን አስጠርቶ ጓጉንቸሮቹ ከሀገሬ እንዲወገዱልኝ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩልኝ፤ እኔም ሕዝቡን እለቅቃለሁ አላቸው። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ ጓጉንቸሮቹ እንዲወገዱ አደረገ። ጓጉንቸሮቹ መወገዳቸውን ባየ ጊዜ ፈርዖን ልቡን በማደንደን እምቢተኛ ሆነ እንጂ ሕዝቡን አልለቀቀም።

3. <u>የትቢያ ወደ ቅማልነት መለወጥ</u>:- ሙሴ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት አሮን ትቢያውን በበትሩ እንዲመታ ነገረው። አሮንም በበትሩ ትቢያውን በመታው ጊዜ ትቢያው ሁሉ ወደ ቅማልነት ተለወጠ። የግብጽ አስማተኞች እንዲሁ ለማድረግ ሞክረው አልሆነላቸውም። ለንጉሡም ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው ብለው ነገሩት። ንጉሡ ግን በእምቢተኛነቱ ጸና እንጂ እሺ ብሎ ሕዝቡን አልለቀቀም።

4. <u>ተናካሽ ዝንብ</u>:- እግዚአብሔር ሙሴን ወደፈርዖን ሄዶ ሕዝቡን ይለቅቅ ዘንድ፥ ባይለቅ ግን ተናካሽ ዝንብ የሚያመጣበት መሆኑንና የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚኖርበት የጌሤም ምድር ግን ከተናካሹ ዝንብ ነጻ የሚሆን መሆኑን እንዲነግረው አዘዘው። በማግስቱም መላዋ የግብጽ ምድር በተናካሽ ዝንብ መንጋ እንድትወረር አደረገ።

ከዚያ በኋላ ንጉሡ ሙሴንና አሮንን ጠርቶ ርቃችሁ ሳትሄዱ፥ ሄዳችሁ ለአምላካችሁ መሥዋዕት አቅርቡ አላቸው። ሙሴ ግን ግብጻውያን የእኛን መሥዋዕት ስለሚጸየፉ የሦስት ቀን መንገድ ርቀን መሄድ አለብን አለው። ፈርዖንም ርቃችሁ የማትሄዱ ከሆነ እለቅቃችኋለሁ፤ ለእኔም ጸልዩልኝ አላቸው። ሙሴም ለእግዚአብሔር በጸለየ ጊዜ የዝንቡ መንጋ ተወገደለት። ንጉሡም የዝንቡ መንጋ መወገዱን ባየ ጊዜ ልቡን አደንድኖ የእስራኤልን ሕዝብ የማይለቅ ሆነ።

5. <u>የእንስሳት እልቂት</u>:- ሙሴ በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት ወደ ግብጹ ንጉሥ ሄዶ ያገለግለኝ ዘንድ ሕዝቡን ልቀቅ፤ እምቢ ብትል ግን በግብጻውያን እንስሳት ሁሉ ላይ በሽታን እልካለሁ፤ በእስራኤላውያንና



በግብጻውያን መካከል ልዩነት ይኖራል። በእስራኤላውያን እንስሳት አንድ እንኳን አይሞትም አለው።

በማግስቱም እግዚአብሔር እንደተናገረው የግብጻውያን እንስሳት ሁሉ ሲያልቁ የእስራኤላውያን እንስሳት ግን አንዳችም ጉዳት አልደረሰባቸውም። ይህ ሁሉ ሲሆን ንጉሡ ልቡን በማደንደን እምቢተኛ ሆነ እንጂ ሕዝቡን አልለቀቀም።

6. <u>ብጉንጅ የመሰለ ቍስል</u>:- በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት ሙሴ ከምድጃ ዐመድ ወስዶ በንጉሡ ፊት ወደ ዐየር በበተነው ጊዜ በግብጻውያን ሁሉ ላይ ብጉንጅ የመሰለ ቍስል ወጣባቸው። በዚያን ጊዜ አስማተኞች ወደ ሙሴ ፊት ሊቀርቡ አልቻሉም። እነርሱም እንደ ሌሎች ግብጻውያን ሁሉ በቍስሉ ተመትተው ነበር።

አሁንም እንደገና ንጉሡ ልቡን በማደንደን እምቢተኛ ሆነ እንጂ እስራኤልን አልለቀቀም።

7. <u>የበረዶ መዝነብ</u>:- ሙሴ በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት እጁን ወደሰማይ በዘረጋ ጊዜ በግብጽ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ከባድ የበረዶ ዝናብ ዘነበ። ይህም የሆነው ለግብጹ ንጉሥ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኋላ ነው። ይህም በረዶ በሜዳ የተገኘውን ነገር፥ ሰውን፥ እንስሳቱንና ዛፎቹን ሁሉ ጨፈጨፈ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ ሙሴንና አሮንን አስጠርቶ በደለኛነቱን ከተናዘዘላቸው በኋላ በረዶው ይወገድ ዘንድ ለእግዚአብሔር እንዲጸልዩለት ለመናቸው። ሙሴም ለእግዚአብሔር ከጸለየ በኋላ በረዶ መዝነቡ ቆመ። ንጉሡ የበረዶው ዝናብ መቆሙን ባየ ጊዜ ልቡን አደንድኖ ሕዝቡን አልለቅም በማለት እምቢተኛ ሆነ።

8. <u>የአንበጣ መንጋ</u>:- «እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው:- «እንደገና ወደፈርዖን ሂድና ለፈርዖን እንዲህ በለው:- ያገለግለኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ፤ አልለቅም ብለህ እምቢተኛ ብትሆን ግን በነገው ቀን በግብጽ ላይ የአንበጣ መንጋ አመጣለሁ፤ ከበረዶ የተረፈውን አንበጣው ይጨርሰዋል።» የንጉሡም ባለሟሎች ሀገሪቱ እየጠፋች ስለሆነች ወንዶቹ ብቻ ሄደው አምላካቸውን አምልከው እንዲመለሱ ፍቀድላቸው ብለው መከሩት። ይህንኑም ለሙሴና ለአሮን ነገራቸው። ሙሴ ግን ከእስራኤላውያን መካከል አንድም ሰው ሊቀር አይችልም ሲል መልስ ሰጠ። ንጉሡም ሴቶቻችሁንና ልጆቻችሁን ይዛችሁ እንድትሄዱ አልፈቅድላችሁም። ከፈለጋችሁ ወንዶች ብቻ ልትሄዱ ትችላላችሁ ብሎ ሙሴና አሮን ተባርረው እንዲወጡ አደረገ።

ሙሴም በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት እጁን በዘረጋ ጊዜ ከዚያ በፊትም ያህል ታይቶ የማያውቅ ብዛት ያለው አንበጣ ሀገሪቱን አለበሳት። አንበጣውም ምንም ነገር ሳያስቀር ከበረዶ የተረፈውን ነገር ሁሉ በልቶ ጨረሰ።

ንጉሡም ሙሴንና አሮንን አስጠርቶ አምላካችሁንም እናንተንም በድያለሁ። ስለዚህ ሄዳችሁ አምላካችሁን እንድታመልኩ ይህ የአንበጣ መንጋ



www.ethiopianorthodox.org

ይወገድልኝ ዘንድ ጸልዩልኝ አላቸው። ሙሴ ወደ እግዚአብር ጸልዮ አንበጣው መወገዱን ባየ ጊዜ ንጉሡ እንደገና ልቡን አደንድኖ እምቢተኛ ሆነ እንጂ ሕዝቡን አልለቀቀም።

9. <u>ጨለማ</u>:- በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት ሙሴ እጁን በዘረጋ ጊዜ በሀገሪቱ ሁሉ ለሦስት ቀን ጨለማ ሆነ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ ሙሴንና አሮንን ጠርቶ ሄዳችሁ ለአምላካችሁ ስገዱ። ነገር ግን እንስሶቻችሁን ትታችሁ ሂዱ አላቸው። ሙሴ ግን የግድ እንስሶቻችንን ይዘን መሄድ አለብን አለው። ንጉሡ ልቡን አደንድኖ ሕዝቡን ሊለቅ ስላልፈለገ ሁለተኛ ፊትህን እንዳላይ ወዲያ ሂድ፥ እኔን በምታይበት ጊዜ እንደምትሞት ዕወቅ አለው። ሙሴም እውነትህን ነው ዳግመኛ አላይህም አለው።

10. <u>የበኵር ልጆች በሞት መቀሠፍ</u>:- እኩለ ሌሊት ሲሆን እግዚአብሔር ከንጉሡ አልጋ ወራሽ ጀምሮ በጨለማ ቤት ውስጥ እስከተጣለው የእስረኛ ልጅ ድረስ በግብጽ ምድር በኵር የሆነውን ወንድ ልጅ ሁሉ በሞት ቀጣ፤ በኵር ሆነው የተወለዱ እንስሳትም ተገደሉ። ወንድ ልጅ ያልሞተበት ቤት አንድም ስላልነበረ በግብጽ ምድር ሁሉ ከፍተኛ ለቅሶ ተሰማ። ንጉሡና ሕዝቡ ሁሉ እስራኤላውያን በቶሎ እንዲወጡላቸው ያጣድፉአቸው ጀመር። በዚህ ዐይነት የአስራኤል ሕዝብ ከምድረ ግብጽ ወጣ።

## <u>የእስራኤላውያን የበረሓ ጕዞ ሂደት</u>

<u>የጕዞው አጀማመር</u>:- እግዚአብሔር በግብጽ ሕዝብ ላይ የበኵር ወንዶች ልጆችና በኵር የሆኑ እንስሳትን የመግደል መቅሠፍት ባመጣበት ቀን የእስራ ኤል ልጆች ሁሉ በየደጃፎቻቸው መቃኖች ላይ ደም እንዲረጩ ታዘዙ። ይህን እንዲያደርጉ የታዘዙት የሞት መልአክ የግብጻውያንን በኵር ሁሉ በሚገድልበት ጊዜ የእስራኤላውያንን ቤቶች ሳይነካ ዐልፎ እንዲሄድ ለማድረግ ነው። በዚህም መሠረት የሞት መልአክ በተላከ ጊዜ የደም ምልክት በጉበኑ ላይ ተረጭቶ ያየውን የእስራኤላውያንን ቤት ሁሉ ዐልፎት ሄዷል። ስለዚህም ነው እስራኤላውያን የፋሲካን በዓል እንዲያከብሩ የታዘዙት። ፋሲካም በመጀ መሪያው መጽሐፉ በተጻፈበት ቋንቋ ዐልፎ መሄድ ማለት ነው። ይህም የሚያመለክተው የሞቱ መልአክ በእስራኤላውያን ላይ ጉዳት ሳያደርስ እያለፈ መሄዱን ነው።

ግብጻውያንም የበኵር ልጆቻቸው መሞት በጀመሩ ጊዜ እስራኤላውያንን ከሀገር እንዲወጡላቸው አጣደፉአቸው። በዚያን ጊዜም ዱቄቱን ለማቡካት ጊዜ ስላልነበራቸው ቂጣ ጋግረው መብላት ግድ ሆነባቸው። ስለዚህም ነው በፋሲካ በዓል ጊዜ ቂጣ የመብላት መታሰቢያ የሚያደርጉት።

እስራኤላውያን በግብጽ ምድር አራት መቶ ሠላሳ ዓመት ኖረው በወጡ ጊዜ እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል በገባለት መሠረት በግብጻውያን ዘንድ ሞገስ እንዲያገኙና የጠየቁትንም ሁሉ ማግኘት እንዲችሉ አደረገ። ስለዚህም



ግብጻውያን ለእስራኤላውያን የወርቅና የብር ጌጣጌጥ እንዲሁም የልብስ ስጦታዎችን ሰጡአቸው።

እስራኤላውያንም ከሚኖሩበት አካባቢ ከራምሴ ተነሥተው ጉዞ በጀመሩ ጊዜ ሴቶችና ልጆች ሳይቈጠሩ ስድስት መቶ ሺህ ነበሩ። ከእነርሱም ጋር ቍጥሩ የበዛ ሌላ ሕዝብ፥ ብዙ የበግ፥ የፍየልና የቀንድ ከብት መንጋ እየነዳ ወጣ።

<u>የእስራኤላውያን በኵር</u>:- የግብጻውያን በኵር ሁሉ በሞተበት ቀን እግዚአ ብሔር የእስራኤላውያንን በኵር ስላዳነ የእስራኤላውያን በኵር ሁሉ ለእግዚ አብሔር የተለየ እንዲሆን ተወሰነ። የንጹሕ እንስሳት በኵር ለመሥዋዕትነት ሲቀርብ የሰውና ንጹሕ ያልሆኑ የእንስሳት በኵር ግን በገንዘብ ይዋጃሉ።

<u>በጕዞው አጀማመር የተከሠቱ ድንቅ ነገሮች</u>:- እግዚአብሔር እስራኤ ላውያንን ከግብጽ ምድር ካስወጣ በኋላ ቀን በደመና ዐምድ ሌሊት ደግሞ በእሳት ዐምድ ይመራቸው ጀመር።

እስራኤላውያን በሚግዶልና በቀይ ባሕር መካከል ባለው ፒሃሒሮት ፊት ለፊት በባዓልጻፎን አጠገብ ሰፈሩ።

የግብጽ ንጉሥና ባለሟሎቹ እስራኤላውያን ማምለጣቸውን በሰሙ ጊዜ:- «ይህ ያደረግነው ነገር ምንድነው? እስራኤላውያን በመሄዳቸው አገልጋዮቻ ችንን ሁሉ ማጣታችን አይደለምን? ብለው በመጠያየቅና ሐሳባቸውን በመለ ወጥ ንጉሡ በግብጽ ምድር ያሉትን ሠረገላዎች አዘጋጅቶ የጦር አዛዦች መደበላቸው። የግብጽም ሠራዊት በፈረሶችና በሠረገላዎች ከፈረሰኞች ጋር ሆኖ እስራኤላውያንን ተከታተላቸው። በቀይ ባሕር ፊት ለፊት ባሉት በፒሃ ሒሮት በባዓልጻፎን አጠገብ በሰፈሩበት ቦታ ደረሱባቸው።

እስራኤላውያንም የግብጽ ንጉሥና ሠራዊቱ በእነርሱ ላይ አደጋ ለመጣል መምጣታቸውን ባዩ ጊዜ እጅግ ፈሩ። በሙሴም ላይ አጕረመረሙ። ሙሴም አይዞአችሁ አትፍሩ፤ እግዚአብሔር ዛሬ ምን እንደሚያደርግ ታያላችሁ፤ እነዚህን ዛሬ የምታዩአቸውን ግብጻውያን ዳግመኛ አታዩአቸውም አላቸው። እግዚአብሔርም ሙሴ በባሕሩ ላይ በትሩን በሚያነሣበት ጊዜ ባሕሩ ለሁለት እንደሚከፈልና እስራኤላውያንም ወደፊት እንዲሄዱ ነገረው። የእስራኤልን ሠራዊት ፊት ፊት ይመራ የነበረው መልአክ ወደ ኋላ ተመልሶ ደጀን ሆነ፤ የደመናውም ዐምድ ዐልፎ በግብጻውያንና በእስራኤላውያን መካከል ቆመ፤ ደመናውም ግብጻውያንን በጨለማ ሲጋርድ ለእስራኤል ሕዝብ ግን ብርሃን ይሰጥ ነበር። ስለዚህ የግብጽ ሠራዊት ሌሊቱን ሙሉ ወደ እስራኤላውያን መጠጋት አልቻለም። ሙሴም እጁን በዘረጋ ጊዜ ባሕሩ ለሁለት ተከፍሎ እንደግድግዳ ቆመና እስራኤላውያን በደረቅ መሬት ላይ ተሻገሩ። ግብጻ ውያንም በሠረገሎቻቸው፥ በፈረሶቻቸውና በፈረሰኞቹ አሳደዱአቸው። ተከ ታትለውም ወደ ባሕሩ ውስጥ ገቡ። እግዚአብሔርም የሠረገሎቻቸውን መንኰራኵሮች ስላጣበቀባቸው ሠረገላዎቻቸውን ማንቀሳቀስ አልቻሉም።

www.ethiopianorthodox.org

ግብጻውያንም «እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ረድቶ እኛን እየተዋጋን ስለሆነ ከፊታቸው እንሽሽ ተባባሉ። በእግዚአብሔርም ትእዛዝ ሙሴ እጁን ወደ ባሕሩ በዘረጋ ጊዜ እንደ ግድግዳ ቆሞ የነበረው ውሃ ወደ ቦታው ተመለሰ። የግብጽን ሠራዊት፥ ሠረገሎቻቸውን፥ ፈረሰኞቻቸውንና ፈረሶቻቸውን አሰጠማቸው። በዚህም ዐይነት እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብጻውያን እጅ አዳናቸው። በባሕሩ ጠረፍ የተረፈረፈውን የግብጻውያንን ሬሳ ተመለከቱ። እግዚአብሔር በግብጻውያን ላይ ያደረገውን ታላቅ ሥራ እስራኤላውያን ባዩ ጊዜ እግዚአብሔርን ፈሩ፤ በእርሱና በአገልጋዩ በሙሴ አመኑ።



ሙሴም እጁን በባሕር ላይ ዘረጋ እግዚአብሔርም ግብጻውያንን በባሕር መካከል ጣላቸው። (ዘጸ. ም 14 ቁ 2)

<u>መጽሐፈ ዕዝራ:</u>- ይህን መጽሐፍ ካህኑ ዕዝራ እንደጻፈው ይታመናል። መጽሐፉን የጻፈው በዕብራውያን ቋንቋ ሲሆን አንዳንድ የአረማይክ (የጥንት ሶርያውያን) ቃላት ተቀላቅሎበታል። መጽሐፉ ዐሥር ምዕራፎች አሉት። መጽሐፈ ዕዝራ በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ስድስት ድረስ ንጉሥ ቂሮስ የእስራኤል ልጆች ወደ አገራቸው በተለየም ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ማወጁን የሚገልጠው ነው። ንጉሡም ይህን ዐዋጅ ያወጀው በከለዳውያን መንግሥት ውስጥ ታላቅ ክብርና ተሰሚነት በነበረው በነቢዩ በዳንኤል አማካይነት ነው ይባላል። እርሱም ነቢያት ስለ እርሱ ማለት ስለቂሮስ የተናገሩትን ትንቢት አሳይቶታል። በትንቢቱ ከመደሰቱም በላይ እርሱ የደረሰበት ደረጃ ድረስ ለመድረስ የቻለው በእግዚአብሔር እርዳታ መሆኑን እንደአመነበት በአነጋገሩ ለመረዳት ይቻላል:-

«የፋርስ ንጉሠ ነገሥት በዐዋጅ የሰጠው ትእዛዝ እንዲህ የሚል ነበር:- የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር የዓለም ሁሉ ገዢ አድርጎኛል፤ እርሱም ቤተ መቅደስን በይሁዳ ምድር በምትገኘው በኢየሩሳሌም እንድሠራለት አዝዞኛል» (ዕዝ:ም:1ቍ:2)።



ይህም የቂሮስ ትእዛዝ የተላለፈው ከእስራኤል ምርኮ ከሰባ ዓመት በኋላና ከኢየሩሳሌምና ከቤተ መቅደስ መፍረስ፥ እንዲሁም ከይሁዳና ከብንያም ነገዶች ምርኮ ከኀምሳ ሁለት ዓመት በኋላ ነው። በዚህም ጊዜ ብዙዎቹ ምርኮኞች ተመልሰዋል። ከተመላሾቹም አብዛኞዎቹ ከይሁዳ፥ ከብንያምና ከሌዊ ነገዶች ነበሩ።

ስለዚህም ጉዳይ አስቀድመው በነቢያት ከተነገሩ በኋላ ቂሮስ እንዲያያቸው የተደረጉት የትንቢት ቃሎች የሚከተሉት ናቸው:-

«ቂሮስን ሕዝቤን የምታስተዳድርልኝ፥ ዕቅዴንም ሁሉ የምትፈጽም፥ ኢየሩሳሌም እንድትሠራና የቤተ መቅደሱም መሠረት እንዲጣል የምታደርግልኝ አንተ ነህ > እለዋለሁ» (ኢሳ:ም:44ቍ:28)።

«የነገሥታትን ኀይል ላደከመለት፥ ቀብቶ ላነገሠው ለቂሮስ እንዲህ ይለዋል:- በፊትህ በሮች ሁሉ ይከፈታሉ፤ መዝጊያዎችም አይዘጉም» (ኢሳ:ም:45ቍ:1)።

«የፍትሕን ሥራ እንዲያራምድ ቂሮስን ለሥራ ያነቃቃሁት እኔ ነኝ፤ የሚሄድበትን መንገድ ሁሉ አቃናለታለሁ፤ የእኔ ከተማ የሆነችውን ኢየሩሳሌምን እንደገና ይሠራታል፤ የተማረኩትን ሕዝቤን ነጻ ያወጣል፤ ይህንንም ሁሉ የሚያከናውነው ማንም ቀጥሮት ወይም ገንዘብ ሰጥቶት አይደለም፤ እኔ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይህን ተናግሬአለሁ» (ኢሳ:ም:45ቍ:13)።

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- ‹በባቢሎን የምትኖሩበት ሰባ ዓመት ከተፈጸመ በኋላ እንደገና እናንተን በምሕረት ወደ አገራችሁ እንድመልሳችሁ የገባሁትን ቃል ኪዳን እፈጽማለሁ > » (ኤር:ም:29ቍ:10)።

ለተመለሱትም ስደተኞች መሪዎች ሆነው የመጡት ዘሩባቤል፥ ኢያሱ፥ ነህምያ፥ ሠራያ፥ ረዔላያ፥ መርዶክዮስ፥ ቢልሻን፥ ሚስፖር፥ ቢግዋይ፥ ሬሁምና በዓና ተብለው የሚጠሩት ነበሩ። በዚህ ጊዜ ከስደት የተመለሱት ሰዎች ጠቅላላ ብዛት አርባ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ስድሳ ነበር። የኢዮጼዴቅ ልጅ ኢያሱና የሰላትያል ልጅ ዘሩባቤል ከሌሎች ጋር በመተባበር የእስራኤልን አምላክ የእግዚአብሔርን መሠዊያ ሠሩ። በኦሪት ሕግም መሠረት የሚቃጠል መሥዋዕት ለማቅረብ ቻሉ። ምንም እንኳ በምድሪቱ በሚኖሩ ሰዎች ፍርሃት ቢያድርባቸው መሠዊያውን ቀድሞ በነበረበት ቦታ አቆሙት። ከዚያም በኋላ ዘወትር ጧትና ማታ የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ ጀመሩ። ቀስ በቀስም በሕጉ የታዘዙትን የሃይማኖት በዓላት ማክበር ጀመሩ። ወደ ኢየሩሳሌምም ከደረሱ ከሁለት ዓመት በኋላ ቤተ መቅደሱን መሥራት ጀመሩ። ከስደት ተመልሰው የመጡት ሁሉ በሥራው ተባበሩ። ነገር ግን በመድረቱ ከሚኖሩት ነዋሪዎች አይሁድን በማስፈራራትና ተስፋ ለማስቈረጥ በመሞከር ቤተ መቅደሱን እንዳይሠሩ ሊከለክሉአቸው ተነሣሡ። ለባለሥልጣኖችም ጉቦ በመስጠት ተጽዕኖ ሊያደርጉባቸው ሞከሩ። እንዲያውም እነዚህ የአይሁድ ጠላቶች አርጤክስስ በነገሠ ጊዜ የአይሁድ ሕዝብ ዐመፀኛ ስለሆነ ቤተ

www.ethiopianorthodox.org

መቅደሱንም ሆነ ኢየሩሳሌምን መሥራት እንዳይፈቀድለት ብለው ስለጻፉ ሥራው እንዲቆም ንጉሡ ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር። ዳርዮስ በነገሠ ጊዜ ግን አይሁድ አቤቱታ በማቅረባቸው ንጉሡ በመዝገብ አገላብጦ ቤተ መቅደሱን እንዲሠሩ ቂሮስ ፈቅዶላቸው የነበረ መሆኑን ለማወቅ ቻለ። በዚህ ጊዜ ዳርዮስ እነዚያ ባለሥልጣኖች ሥራውን እንዳይከለክሉአቸውና እንዲያውም እርዳታ እንዲያደርጉላቸው ትእዛዝ አስተላለፈ። በዚህም መሠረት ሥራውን እያፋጠኑ ሠርተው አጠናቀቁ።

የመጽሐፉ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከምዕራፍ ሰባት እስከ ምዕራፍ 10 ድረስ ሲሆን በዕዝራ መሪነት ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሰውን የስደተኞች ቡድን የሚመለከት ነው። ይህም የሆነው በንጉሡ በአርጤክስስ ዘመን ነው። ይህ አርጤክስስ ቀደም ተብሎ የተጠቀሰው አርጤክስስ ሳይሆን በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ ያለው አርጤክስስ ነው።

ዕዝራ ከሌዊ ነገድ የአሮን ዘር ነበር እርሱም እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት ለእስራኤል ሕዝብ የሰጠውን ሕግ በማጥናት ዐዋቂ ሰው ነበር፤ እግዚአብሔርም ይረዳው ስለነበረ የጠየቀውን ነገር ሁሉ ንጉሡ ነገሥቱ ይፈቅድለት ነበር።

እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች የሰጣቸውን ሕግና ትእዛዝ ሁሉ በከፍተኛ ደረጃ ያውቅ ስለነበር ለካህኑ ዕዝራ ንጉሡ ነገሥት አርጤክስስ የሰጠው የጽሑፍ ፈቃድ ከዚህ የሚከተለው ነው:-

«ከንጉሡ ነገሥት አርጤክስስ፥ የሰማይ አምላክን የእግዚአብሔርን ሕግ በማጥናት ረገድ ታላቅ ምሁር ለሆነው ለካህኑ ዕዝራ:- ሰላም ላንተ ይሁን፤ እኔ በማስተዳድረው የንጉሡ ነገሥት መንግሥት ግዛት ውስጥ የሚገኙና ከአንተ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ የሚፈልጉ እስራኤላውያን፥ ካህናትና ሌዋውያን ሁሉ እንዲመለሱ ፈቅጃለሁ፤ ከዚህም ጋር እኔ ራሴ ከሰባቱ አማካሪዎቼ ጋር በአንድነት ያስተላለፍነው ውሳኔ ለአንተ የተሰጠው የአምላክህ ሕግና ትእዛዝ በተገባር መፈጸሙን እየተመለከትህ በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ያለውን ሁኔታ እንድትመረምር ልኬሃለሁ። በተጨማሪም በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ለተሠራለት ለእስራኤል አምላክ እኔና አማካሪዎቼ በበጎ ፈቃድ የሰጠነውን ብርና ወርቅ ይዘህ ሂድ። ከዚህም ሁሉ ጋር አንተ ራስህ ከባቢሎን ምድር የሰበሰብከውን ወርቅና ብር፥ የእስራኤል ሕዝብና ካህናቱም ጭምር በኢየሩሳሌም በተሠራው የአምላካቸው ቤተ መቅደስ እንዲቀርብላቸው የሚፈልጉትን መባ ሁሉ ይዘህ ሂድ። ይህም ገንዘብ በጥንቃቄ ሥራ ላይ እንዲውል አድርግ። ... ለቤተ መቅደሱ መገልገያ የሚያስፈልግህንም ሌላውን ነገር ሁሉ ከቤተ መንግሥቱ ግምጃ ቤት ለማግኘት እንድትችል ተፈቅዶልሃል» (ዕዝ: ም: 7ቍ:12–17፥20)።

ዕዝራም ጉዞውን ከመጀመሩ በፊት መላውን ጉባኤ በአህዋ ወንዝ አጠገብ ሰብስቦ እግዚአብሔር ጉዞአቸውን ያቀናላቸው ዘንድ፥ እነርሱን፥ ልጆቻቸውንና ንብረታቸውን ይጠብቅላቸው ዘንድ ጾም ዐወጀ። ከዓለማዊ ጠባቂ



www.ethiopianorthodox.org

ይልቅ እግዚአብሔር ራሱ ይጠብቃቸው ዘንድ በጾምና በጸሎት እርሱን ተማጠኑት።

ከዚያም በኋላ ዕዝራና ሌሎቹ ከስደት ተመላሾች ጕዞአቸውን ቀጥለው በእግዚአብሔር ጥበቃ ምንም ችግር ሳይደርስባቸው በመጨረሻ ወደ ኢየሩሳሌም ደረሱ።

ይህም ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ ሕዝቡና ካህናቱ ከአይሁድ ዘር ውጪ ከባዕዳን ሴቶች ጋር ጋብቻ በመፈጸማቸው እነዚያ አረማውያን ሕዝቦች ሲፈጽሙት የነበረውን አስጸያፊ ነገር ሁሉ ያደረጉ መሆናቸውን ካህኑ ዕዝራ በመስማቱ መጐናጸፊያውንና ካባውን ቀደደ። የራስ ጠጕሩንና ጢሙን በመንጨት በብዙ ሐዘን ላይ ሆኖ ተቀመጠ።

በዚህ ጉዳይ ዕዝራ በእግዚአብሔር ፊት ተንበርክኮ ምርር ባለ ለቅሶ በሚናዘዝበት ጊዜ የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ አብሮት አለቀሰ። በዚህ ጊዜ ሰዎች ሁሉ ባዕዳን ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን ለማባረር በመሐላ ቃል ገቡ። በመጨረሻም በይሁዳና በብንያም ግዛት የሚኖሩ ከስደት ተመላሾች ሁሉ አንድ የስብሰባ ቀን ተወስኖላቸው በዚያ ስብሰባ ላይ በተወሰነው መሠረት ያገቡአቸውን የባዕድ ሴቶች ከነልጆቻቸው አባረሩ።


ብዙዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የዕዝራንና የነህምያን መጽሐፍ ያጣምሩታል። የተጻፈውም በአንድ ሰው እንጂ በሁለት ሰዎች እንዳልሆነ ያምናሉ። ለአባባላቸውም የሚሰጡት ምክንያት የሁለቱም ይዘት ተመሳሳይ መሆኑን ነው። በመጽሐፈ ዕዝራ ላይ ለመጀመሪያዎቹ ከስደት ተመላሾች መሪዎች ነበሩ ተብለው ስሞቻቸው ከተጠቀሱ ሰዎች መካከል ነህምያ ይገኝበታል። በመጽሐፈ ነህምያ ደግሞ በምዕራፍ 8 እና 9 ላይ ካህኑ ዕዝራ የእግዚአብሔርን ሕግ አንብቦ ሕዝቡ ኃጢአቱን እንደተናዘዘ ተገልጦአል።

ሌሎች ምሁራን እንደሚሉት ደግሞ አንደኛና ሁለተኛ ዜና መዋዕል ተከታታይ የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ሲሆን መጽሐፈ ዕዝራና መጽሐፈ ነህምያም ከዚያ የሚቀጥል ነው። እነዚህም መጻሕፍት ቀደም ብለው አራት ሳይሆኑ በአንድ መጽሐፍ የተጠቃለሉ እንደነበሩ ይታመናል። እንዲያውም የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ መግቢያ እንደሚለው ከሆነ እነዚህ መጻሕፍት የተዘጋጁት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአንድ የኢየሩሳሌም ሌዋዊ ሳይሆን አይቀርም። ታሪኩም የሚያተኵረው ወደ ታላቁ ንጉሥ ወደ ዳዊትና ወደ ልጁም ወደ ሰሎሞን ቤተ መቅደስን መሥራት ዘመን ለመድረስ ነው። ዜና መዋዕሎቹ ወደ ባቢሎን ምርኮ የሚያደርሱ ሲሆኑ ከዚያ በኋላ ያለውን ታሪክ መጽሐፈ ዕዝራና መጽሐፈ ነህምያ ይረከባሉ በማለት የመጻሕፍቱን አንድ መሆን ለመግለጥ ሞክረዋል።

## <u>ሐዲስ ኪዳን</u>

<u>ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስና ቆርኔሌዎስ</u>:- የኢጣልያ ጓድ በሚባለው ክፍለ ጦር ውስጥ የመቶ አለቃ የነበረና በቂሣርያ የሚኖር አንድ ሰው ነበረ። እርሱም

ለድኾች ምጽዋት የሚሰጥና ዘወትር ወደ እግዚአብሔር የሚጸልይ ነበር። አንድ ቀን ወደ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ ገብቶ ቆርኔሌዎስ ብሎ ሲጠራው በራእይ አየ። እርሱም ደንግጦ ጌታ ሆይ ምንድ ነው? አለ። መልአኩም ጸሎትህና ለችግረኞች የምታደርገው ችሮታ በእግዚ አብሔር ዘንድ ታስቦልሃል። አሁንም ልታደርገው የሚገባህን እንዲነግርህ በኢዮጴ የሚገኘውን ስምዖን ጴጥሮስን አስጠራ። እርሱም በባሕር አጠገብ ባለው በቍርበት ፋቂው በስምዖን ቤት እንግድነት ተቀምጦአል አለው። መልአኩም ከሄደ በኋላ ከጭፍሮቹ መካከል የሚያምናቸውን ጠርቶ ጉዳዩን ገለጠላቸውና ወደ ኢዮጴ ላካቸው። በማግስቱም ወደ ተላኩበት ቦታ ሄደው ወደ ከተማው ሲደርሱ ስድስት ሰዓት ገደማ ነበር። በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ምሳ እስኪዘጋጅ ድረስ ሊጸልይ ወደ ሰገነት ላይ ወጥቶ ሳለ እራበውና አንድ ራእይ አየ። ያየውም ራእይ ሰማይ ተከፍቶ በአራት ማእዘን የተያዘ ትልቅ የመጋረጃ ጨርቅ ወደ ምድር ሲወርድ ነው። በጨርቁም ላይ ልዩ ልዩ እንስሳት፥ በልባቸው የሚሳቡ ፍጥረቶችና በሰማይ የሚበርሩ ወፎች ነበሩበት። በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ተነሥና እያረድህ ብላ የሚል ድምፅ ሰማ። እርሱ ግን «አይሆንም ጌታ ሆይ፥ እኔ ከቶ የሚያስጸይፍ ርኩስ ነገር በልቼ አላውቅም» አለ። ይህንንም ራእይ ሦስት ጊዜ ካየው በኋላ ያ መጋረጃ መሰል ጨርቅ ወደ ሰማይ ተወሰደ።



ቅዱስ ጴጥሮስ ያየው ራእይ (የሐ : ሥ : ም 10)

ይህ ሲሆን ሳለ እነዚያ ከቆርኔሌዎስ ዘንድ የተላኩት መልእክተኞች ደር ሰው ጴጥሮስ የተባለው ስምዖን በእንግድነት የተቀመጠው እዚህ ነውን? ብለው ተጣሩ። ጴጥሮስም የራእዩን ነገር በማሰላሰል ላይ ሳለ መንፈስ ቅዱስ እነሆ፥ ሦስት ሰዎች ይፈልጉሃልና ተነሥና ውረድ፤ የላክኋቸውም እኔ ስለሆንኩ ሳታ መነታ ከእነርሱ ጋር ሂድ አለው። ጴጥሮስም ወርዶ እነሆ፥ የምትፈልጉት ሰው እኔ ነኝ አላቸውና የመጡበትን ምክንያት ጠየቃቸው። እነርሱም የመጡ በትን ምክንያትና የቆርኔሌዎስን ማንነት ዘርዝረው አስረዱት። በዚያን ቀን እዚ ያው ከጴጥሮስ ጋር ዐደሩና በማግስቱ ተነሥተው ወደ ቂሣርያ አብረው ሄዱ።



www.ethiopianorthodox.org

በኢዮጴም ከነበሩ ወንድሞች አንዳንዶቹ አብረውት ሄዱ። በማግስቱ ወደ ቂሣርያ በደረሱ ጊዜ ቆርኔሌዎስ ዘመዶቹንና የቅርብ ወዳጆቹን ጠርቶ እነ ቅዱስ ጴጥሮስን ይጠባበቅ ነበር። ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ቤት ሲገባ ቆርኔሌዎስ በእግሩ ሥር ወድቆ ሰገደለት። ቅዱስ ጴጥሮስ ግን ተነሥ እኔም እንደ አንተው ሰው ነኝ ብሎ አስነሣው። እያነጋገረውም ወደ ቤት ሲገባ ብዙ ሰዎች ተሰብስበው አግኝቶ እንዲህ አላቸው:- አንድ አይሁዳዊ ከሌላ ወገን ጋር እንዲተባበር ያልተፈቀደ መሆኑን እናንተ ታውቃላችሁ። እኔ ግን ማንንም ሰው አስጸያፊና ርኩስ ነው እንዳልል እግዚአብሔር አዝዞኝ ብትጠሩኝ መጥቼአለሁና በሉ አሁን ለምን እንደጠራችሁኝ ንገሩኝ አላቸው።



ቅዱስ ጴጥሮስ ከቆርኔሌዎስ የተላኩ መልእክተኞች (የሐ:ሥ 10 ፥19 – 23)።

በዚህ ጊዜ ቆርኔሌዎስ ያየውን ራእይና የእግዚአብሔር መልአክ የሰጠውን ትእዛዝ ዘርዝሮ አስረዳ። ከዚያ በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘርዝሮ በማስረዳት አስተማረ። ቅዱስ ጴጥሮስ በመናገር ላይ እያለ በሚሰሙት ሰዎች ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው። በሌሎች ቋንቋዎች መናገርና እግዚአብሔርንም ማመስገን ጀመሩ። ይህም በመሆኑ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስና አብረውት የመጡት ወንድሞች በጣም ተገረሙ። ከዚያም ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ሁሉንም አጠመቃቸው።

<u>በቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰ ታላቅ ስደት</u> :- በሐዋርያት ዘመን ንጉሥ ሄሮድስ የቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ማሳደድ ጀመረ። ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስን አስገደለው። ቅዱስ ያዕቆብን ማስገደሉ አይሁድን እንዳስደሰታ ቸው ባየ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስንም ደግሞ አስያዘ። ይህንንም ያደረገው በአይሁድ የፋሲካ በዓል ጊዜ ስለነበረ ከበዓሉ በኋላ ለሕዝቡ እስኪያቀርበው ድረስ ወደ ወህኒ ቤት አስገባው። እዚያም አራት የወህኒ ቤቱ ዘበኞች እንዲጠብቁት አደረገ። ቅዱስ ጴጥሮስ በወህኒ ቤት ይጠበቅ በነበረ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ በጣም ትጸልይ ጀመር።

<u>የቤተ ክርስቲያን ጸሎት ውጤት</u>:- ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በዚያች ሌሊት በሁለት ሰንሰለት ታስሮ በሁለት ወታደሮች መካከል ተኝቶ ነበር።

ሌሎቹ ወታደሮች ደግሞ የወህኒ ቤቱን በር ይጠብቁ ነበር። በዚያን ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ በነበረበት በወህኒ ቤቱ ውስጥ ብርሃን በራ፤ የእግዚአብሔርም መልአክ ታየ። መልአኩ የቅዱስ ጴጥሮስን ጐን መታና ቀሰቀሰው። ቅዱስ ጴጥሮስንም ቀበቶውን እንዲታጠቅ፥ ጫማውን እንዲያደርግና ነጠላውን ለብሶ እንዲ ከተለው መልአኩ አዘዘው። ቅዱስ ጴጥሮስም እንደታዘዘው በማድረግ መልአ ኩን ተከትሎት ሲሄድ ራእይ የሚያይ እንጂ እውነት አልመሰለውም ነበር። በሮቹም ማንም ሳይነካቸው ተከፈቱ። በሮቹንም ወጥተው መንገድ ውስጥ ከገቡ በኋላ በድንገት መልአኩ ተለይቶት ሄደ። ቅዱስ ጴጥሮስም ወደ ልቡናው በተመለሰ ጊዜ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ከእስር ቤት እንዳወጣው ተገነዘበ። ከዚያም ክርስቲያን ወንድሞች ተሰብስበው ወደሚጸልዩበት ቤት መጥቶ የሆነውን ሁሉ ከነገራቸው በኋላ ተለይቶአቸው ወደሌላ ቦታ ሄደ። በማግስቱ ጠዋት ቅዱስ ጴጥሮስ ተፈልጎ በጠፋ ጊዜ ሄሮድስ ጠባቂዎቹ እንዲገደሉ ትእዛዝ አስተላለፈ።




የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ጴጥሮስን ከእስር ቤት እንዳወጣው (የሐ:ሥ 12፥ 6—10)።

<u>የሄሮድስ አሟሟት</u>:- ሄሮድስ በጢሮስና በሲዶና ሰዎች ላይ በጣም ተቈጥቶ ነበር። እነርሱም ሀገራቸው ምግብ የምታገኘው ከንጉሡ ግዛት ስለነበረ ዕርቅ ጠየቁ። ለዕርቅ በተቀጠረበት ቀን ሄሮድስ ልብሰ መንግሥቱን ለብሶና በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ንግግር አደረገ። ሰዎቹ ይህ የአምላክ ድምፅ ነው እንጂ የሰው ድምፅ አይደለም እያሉ ጮኹ። በዚህ ጊዜ ሄሮድስ ለእግዚአብሔር ክብር ባለመስጠቱ የእግዚአብሔር መልአክ ቀሠፈውና ተልቶ ሞተ።

## <u>ከዚህ ምዕራፍ የሚገኝ ትምህርት</u>

የግብጽ አስማተኞች የመጀመሪያዎቹን አንዳንድ ድንቅ ነገሮች በማድረግ ከሙሴና ከአሮን ጋር ለመፎካከር መሞከራቸው እግዚአብሔር ለሰይጣን የተወሰኑ ተአምራትን ማድረግ እንደሚፈቅድለትና ከዚያ በላይ ግን የማይፈቅ



www.ethiopianorthodox.org

ድለት መሆኑን ያመለክታል። ይህንንም ሲያረጋግጡ በኦሪት ዘጸአት ም:8 ቍ:19 ላይ እንደ እነ ሙሴና አሮን ድንቅ ነገሮችን ማድረግ ባቃታቸው ጊዜ አስማተኞቹ ለፈርዖን ይህስ የእግዚአብሔር ጣት ነው ብለውታል።

የእግዚአብሔር ኀያል እጅ መሆኑን የሚያመለክተውም ቅጣቶቹ እስራኤላ ውያንን ሳይነኩ በግብጻውያን ላይና በተወሰነላቸው ጊዜ መፈጸማቸው ነው።

ሙሴንና አሮንን ሊፎካከሩ የተነሡት ጠንቋዮች እንደ ብጉንጅ ባለው የቁስል ቅጣት ጊዜ በሙሴ ፊት ሊቆሙ ያልቻሉት እነርሱም እንደሌሎቹ ግብጻውያን ሁሉ በቍስሉ ይሠቃዩ ስለነበረ ነው።

ፈርዖንም ምንም እንኳ ልቡን ቢያደነድን ጥፋቱን አምኖ ይቅርታ እንዲደረግለት ጠይቆአል። ነገር ግን ምንም ኑዛዜ መሰል ንግግር ቢናገር ልቡን ማደንደኑን አልተወም። ሌላ ቀርቶ የበኵር ልጆች እንኳ ከሞቱ በኋላ ሐሳቡን ለውጦ እስራኤልን ለማሰደድ ወጣ።

በነዚህ ሁሉ ሁናቴዎች እግዚአብሔር ምን ያኽል ታጋሽ እንደሆነና ለንስሓም ምን ያኽል ዕድል የሚሰጥ መሆኑን ለመገንዘብ እንችላለን። ከዚህም በላይ የእግዚአብሔርን ኀያልነትና ገናናነት መረዳት እንችላለን።

እግዚአብሔር ግብጻውያንን በአንድ ጊዜ ሊያጠፋቸው ሲችል ዐሥር የተለያዩ መቅሠፍቶችን ማምጣት ለምን አስፈለገ? ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል። የእግዚአብሔር ዕውቀት ጊዜና ቦታ የማይወስነው በመሆኑ ፈርዖን በምንም የማይመለስ ልቡናው ደንዳና መሆኑን አስቀድሞ ያውቃል። እግዚአብሔር የሚፈቅደው ሰው ሁሉ ንስሓ ገብቶ እንዲድን እንጂ እንዲጠፋ አይደለም። ሰው ግን ከእግዚአብሔር በተሰጠው ተፈጥሮአዊ ነጻነት መልካሙን ወይም ክፉውን መንገድ የመምረጥ ነጻ ፈቃድና ነጻ ፍላጎት አለው። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሰውን ያለ አንዳች ጥበቃ፥ እረኛ እንደሌለው በግ የተወው አይደለም። ከበጎ ተግባር የሚገኘውን ቅጣት አስተምሮታል፤ ይህም ሁሉ ሆኖ ማንም ሰው እንዲጠፋ ሰለማይፈልግ ለረጅም ጊዜ ይታገሠዋል። እግዚ አብሔር የፈርዖንን ልብ አጸና በሚባልበት ጊዜ እግዚአብሔር ለፈርዖን እምቢተኛነት ምክንያት ሆነ ማለት አይደለም። ለሰው ሁሉ የሰጠውን ነጻ ፈቃድ ለእርሱም ስለፈቀደለትና ሐሳቡን ወደ በጎ ዝንባሌ እንዲመለስ ሳያደርግ ዝም ስላለው ልቡን አደነደነው ተባለ። እግዚአብሔር የፈርዖንን ጠባይ ለመለወጥ በጉዳዩ ቢገባበት ኖሮ የሰውን ልጅ ነጻ ፈቃድ ገደበ ማለት ነው። ይህን ባለማድረጉም እግዚአበሔር የፈርዖንን ልብ አጸና ተባለ። ከዚህ የተለየ ሁናቴ የሚደረገው እኛ ድካማችንን ዐውቀን እግዚብሔር ለበጎ ተግባርና ክፉውን ለመቋቋም እንድንችል ብርታቱን ይሰጠን ዘንድ ስንጸልይ መንፈሱን በእኛ አሳድሮ ኀይሉን ሲሰጠን ነው እንጂ እግዚአብሔርን አላውቅም እስራ ኤልንም አልለቅም እንዳለው እንደ ፈርዖን ከሐዲዎች ስንሆን አይደለም።

እስራኤሎች ግን ደካማነታቸውን ተገንዝበው የእግዚአብሔርን እርዳታ በለመኑ ጊዜ ታላላቅ ድንቅ ነገሮችን በማድረግ ከግብጽ ምድር አወጣቸው፤ ከግብጻውያን ጦር አዳናቸው፤ በታላቅ ተአምር ቀይ ባሕርን አሻገራቸው፤ ጠላቶቻቸውን በባሕር ውስጥ አስጥሞ ፈጀላቸው፤ ከዚያም እስራኤላውያንን እጃቸውን ይዞ መራቸው።

እግዚአብሔር ለሚጠራው መልስ የሚሰጥ፥ ለሚፈልገው የሚገኝ፥ ለሚለምነው ልመናን የሚቀበል በመሆኑ ግብጻውያን ሁሉ በሚቀጡበት ጊዜ በጊዜው የነበሩትን እስራኤላውያንን ጠበቃቸው እንጂ ምንም ችግር አላደረሰባቸውም።

እንዲሁም የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ ምድር በሚወጣበት ጊዜ ሌሎች ወገኖችም እነርሱን ተከትለው መውጣታቸው የሚያመለክተው እግዚአብሔር በእርሱ አምኖ የሚከተለውን ሰው ሁሉ የሚቀበለው መሆኑን ነው። ይህም ሁናቴ እግዚአብሔር ወገን የማይለይ መሆኑን ያመለክታል (የሐ : ሥ : 10 ፥34) ።

እግዚአብሔርም ከዘር ዘርን ከወገን ወገንን የማይለይና እግዚአብሔርን በመፍራት ፈቃዱን የሚፈጽመውን ማንኛውንም ሰው እንደሚቀበል የእግዚአብሔር ነቢያት ስለቂሮስ የተናገሩት ትንቢት አንድ ማስረጃ ነው። በትንቢቱም መሠረት ቂሮስ እስራኤላውያን ከምርኮኛነት ነጻ ሆነው ወደ ሀገራቸው እንዲሄዱ ፈቅዶላቸዋል፤ ቤተ መቅደስ እንዲሠራ ፈቅዶአል፤ እርዳታም አድርጎአል።

ዕዝራና አብረውት ሊጓዙ የነበሩት ከስደት ተመላሾች ጉዞአቸውን ከመጀመራቸው በፊት እግዚአብሔር ይጠብቃቸው ዘንድ ስለጸለዩ ያለምንም ችግር ወደ ኢየሩሳሌም ለመድረስ በቅተዋል። ይህም የጸሎትን ኀይል ያሳየናል።

የቆርኔሌዎስን ታሪክ ስንመለከት ደግሞ እግዚአብሔር አንዱን ሰው ከሌላ ሰውና አንዱን ዘር ከሌላ ዘር የማይለይ መሆኑን ለመገንዘብ እንችላለን። ይህንኑም እግዚአብሔር ለቅዱስ ጴጥሮስ ባሳየው ራእይ እንደምንመለከተው እግዚአብሔር ለቅዱስ ጴጥሮስ ሦስት ጊዜ መላልሶ ሲያረጋግጥለት በአይሁዳዊና አይሁዳዊ ባልሆኑ ሰዎች መካከል ልዩነት እንዳያደርግ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶታል።

በቤተ ክርስቲያን ስደት ጊዜ ምንም እንኳ ምድራዊው ኀይል ክርስቲያንነትን ለማዳከም ቅዱስ ያዕቆብን በመግደልና ቅዱስ ጴጥሮስን በማሰር ክርስቲያኖችን ለማስደንገጥ ቢሞክር፥ እግዚአብሔር ቅዱስ ጴጥሮስን ከእስር ቤት በማውጣትና የክርስትናን ጠላት ሄሮድስን ተልቶ እንዲሞት በማድረግ ጠላቶች እንዲደነግጡ አድርጓል። ይህም ምን ያኽል የእግዚአብሔር ጥበቃ ከክርስቲያኖች ጋር እንደነበረ ያስገነዝበናል።



## ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር በግብጽ ሕዝብ ላይ ዐሥር መቅሠፍቶችን ያመጣበት ምክንያት ምንድነው?
2. ውሃውን ወደ ደም ለመለወጥ አሮን ምን አደረገ?
3. የወንዙ ውሃ ወደ ደም በተለወጠ ጊዜ ምን ችግር አመጣ?
4. ፈርዖን ከዚህ ቅጣት በኋላ በምን ምክንያት ልቡን አደነደነ?
5. ሀገሪቱ በጓጉንቸር በተሸፈነች ጊዜ ምን ችግር ተከሠተ?
6. ጓጉንቸሮቹ ቢወገዱልኝ ሕዝቡን እለቅቃለሁ ያለው ፈርዖን ከዚያ በኋላ ለምን ሐሳቡን ለወጠ?
7. ትቢያው ወደ ቅማልነት የተለወጠው እንዴት ነው?
8. አስማተኞቹ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው ያሉት በምን ምክንያት ነው?
9. በግብጽ ምድር ተናካሹ ዝንብ ያልደረሰበት ቦታ የት ነው?
10. በዚህ ጊዜ ፈርዖን ሙሴን ምን አለው?
11. ሙሴስ ምን መልስ ሰጠው?
12. በግብጽ ምድር የእንስሳት እልቂት ያልደረሰበት ቦታ የት ነው?
13. ብጉንጅ የመሰለ ቍስል እንዲመጣ ሙሴ ምን አደረገ?
14. አስማተኞች ወደ ሙሴ ፊት ሊቀርቡ ያልቻሉት በምን ምክንያት ነው?
15. የበረዶ ዝናብ እንዲዘንብ ሙሴ ምን አደረገ?
16. የበረዶው ዝናብ ምን ችግር አመጣ?
17. የአንበጣው መንጋ የመጣው ሙሴ ምን ባደረገ ጊዜ ነው?
18. የአንበጣው መንጋ ምን ችግር አመጣ?
19. የንጉሡ ባለሟሎች ለንጉሡ ምን አሉት?
20. ንጉሡ ለሙሴና ለአሮን ምን አላቸው?
21. ሙሴስ ምን መልስ ሰጠ?
22. የሦስት ቀን ጨለማ እንዲመጣ ሙሴ ምን አደረገ?
23. በዚህኛው ቅጣት ጊዜ ንጉሡ ሙሴንና አሮንን ምን አላቸው?
24. ሙሴስ ምን መልስ ሰጠው?
25. በመጨረሻስ ንጉሡ ምን አለው?
26. የሙሴስ መልስ ምን ነበር?
27. የበኵር ልጆች ሞት መቅሠፍት የመጣው በማን ላይ ነው?
28. ግብጾች እስራኤላውያንን እንዲወጡላቸው ያጣደፉአቸው መቼ ነው?
29. በኵሮች በተገደሉበት ቀን እስራኤላውያን ምን ታዘዙ?
30. እግዚአብሔር ይህን ያዘዛቸው በምን ምክንያት ነው?

www.ethiopianorthodox.org

31. ፋሲካ ማለት ምን ማለት ነው?

32. የፋሲካ በዓል ምክንያት ምንድነው?

33. በፋሲካ በዓል ጊዜ ቂጣ የሚበላው ለምንድነው?

34. የእስራኤል ልጆች በግብጽ ምድር ስንት ዓመት ኖሩ?

35. እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡበት ጊዜ ግብጻውያን ምን ሰጡአቸው?

36. እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡበት ጊዜ ሴቶችና ልጆች ሳይቈጠሩ የወንዶቹ ብዛት ስንት ነበር?

37. ከእስራኤላውያን ጋር አብሮ ከግብጽ የወጡ ሌላ ማንና ምን ናቸው?

38. ስለ እስራኤል ልጆችና ስለ እንስሳቱ በኵሮች የተነገረው ምን ተብሎ ነው?

39. ምክንያቱስ ምንድነው?

40. በጕዞው አጀማመር ላይ የተከሠቱ ድንቅ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

41. ከግብጽ ምድር ከወጡ በኋላ በመጀመሪያ እስራኤላውያን የሰፈሩበት ቦታ ስም ምን ይባላል?

42. እስራኤላውያን ከግብጽ ለመውጣት ጕዞ በጀመሩበት ጊዜ ንጉሡና ባለሟሎቹ ምን ተባባሉ?

43. ከዚያስ በኋላ ንጉሡ ምን አደረገ?

44. የግብጽ ሠራዊት በእስራኤላውያን ላይ የደረሰባቸው ምን በሚባል ቦታ ነው?

45. እስራኤላውያን በሙሴ ላይ ምን ብለው አጕረመረሙ?

46. ሙሴስ ምን መልስ ሰጣቸው?

47. እስራኤላውያንን ይመራ የነበረው መልአክ ምን አደረገ?

48. የደመናው ዐምድስ እስራኤላውያንን የጠበቃቸው እንደምን አድርጎ ነው?

49. እስራኤላውያን ቀይ ባሕርን እንዴት ተሻገሩ?

50. የግብጽ ሠራዊትስ ምን አደረገ?

51. ግብጻውያን ሁናቴውን ሲያዩ ምን አሉ?

52. ግብጻውያን እስራኤላውያንን ተከትለው ወደ ቀይ ባሕር ውስጥ በገቡ ጊዜ ምን ደረሰባቸው?

53. ሙሴ በግብጻውያን ላይ ምን አደረገ?

54. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብጻውያን እጅ ያዳናቸው እንዴት ነው?

55. መጽሐፈ ዕዝራ በምን ቋንቋ ተጻፈ?

56. መጽሐፉ ስንት ምዕራፎች አሉት?

57. ንጉሡ ቂሮስ የአይሁድ ሕዝብ ወደ ሀገሩ እንዲመለስ የፈቀደው በማን አማካይነት ነው?



www.ethiopianorthodox.org

58. ምክንያቱስ ምንድነው?

59. ዐዋጁ የታወጀው እስራኤላውያን ከተማረኩ ከስንት ዘመን በኋላ ነው?

60. አብዛኛዎቹ ተመላሾች ከማን ከማን ነገድ ነበሩ?

61. ተመላሾቹ መሥዋዕያውን የሠሩት መቼ ነው?

62. ቤተ መቅደሱን መሥራት የጀመሩትስ መቼ ነው?

63. ማን በሚባለው ንጉሥ ጊዜ ነው ሥራቸውን እንዲያቆሙ የታዘዙት?

64. እንደገና ሥራውን እንዲቀጥሉ የፈቀደላቸውስ ንጉሥ ስም ማን ይባላል? በምን ምክንያትስ ፈቀደላቸው?

65. ዕዝራ ከየትኛው ነገድና ከምን ዘር ነበር?

66. ዕዝራ ጾምና ጸሎትን ያወጀው ለምንድነው?

67. የባዕድ ሴቶች ስላገቡ እስራኤለውያን ምን ተወሰነ?

68. አንዳንድ ምሁራን የዕዝራና የነህምያ መጻሕፍት በአንድ ሰው የተጻፈ አንድ መጽሐፍ እንጂ ሁለት መጻሕፍት አይደሉም የሚሉት በምን ምክንያት ነው?

69. ሌሎች ሰዎች ደግሞ ሁለቱ የዜና መዋዕል መጻሕፍት ከዕዝራና ከነህምያ መጻሕፍት ጋር በአንድ ጸሐፊ የተጻፈ አንድ መጽሐፍ እንጂ አራት መጻሕፍት አይደሉም የሚሉት በምን ምክንያት ነው?

70. የቆርኔሌዎስን ማንነት ዘርዝረህ አስረዳ።

71. የቅዱስ ጴጥሮስንና የቆርኔሌዎስን ራእዮች ተናገር።

73. በቤተ ክርስቲያን ስደት ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ እንደምን ሊድን ቻለ?

74. የቤተ ክርስቲያን ጸሎት ውጤት ምን ነበር?

75. ሄሮድስ የተቀሠፈው በምን ምክንያት ነው?

## ምዕራፍ 3

## ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ

### የጌታችን ትምህርቶች

በደብረታቦር የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መልክ መለወጥ:- አንድ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ:- እዚህ ካሉት አንዳንዶች፥ የሰው ልጅ በመንግሥቱ ክብር ሲመጣ ሳያዩ አይሞቱም አላቸው።

ይህን ከተናገረ ከስድስት ቀን በኋላ ጴጥሮስን፥ ያዕቆብንና ዮሐንስን አስከትሎ ወደ አንድ ከፍተኛ ተራራ ላይ ወጣ። እዚያም በደቀ መዛሙርቱ ፊት መልኩ ተለወጠ፤ ፊቱም እንደ ፀሐይ አበራ፤ የልብሱም ንጣት አንጸባረቀ።

ሦስቱ ደቀ መዛመርትም ጌታችንን ከሙሴና ከኤልያስ ጋር ሲነጋገር አዩት። እነርሱም ይነጋገሩ የነበሩት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ሕማማትን

ተቀብሎ እንደሚሞት ነበር። በዚያን ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ጌታችን ቀርቦ «እዚህ ብንኖር መልካም ነው፤ ይህንንም ሐሳብ ብትፈቅድ አንድ ለአንተ፥ አንድ ለሙሴና አንድ ለኤልያስ ሦስት ዳሶችን ልሥራ» አለው።

ቅዱስ ጴጥሮስ ገና ይህን ሲናገር ሳለ ብሩህ ደመና መጥቶ ጋረዳቸው፤ ከደመናውም ውስጥ:- «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነውና እርሱን ስሙት» የሚል ድምፅ መጣ። ደቀ መዛሙርቱም ደንግጠው በመሬት ላይ በግንባራቸው ተደፉ። ጌታችን ግን አይዞአችሁ ብሎ በመዳሰስ አስነሣቸው። እርሱም ይህን ያዩትን ነገር እርሱ ከሞት እስኪነሣ ድረስ ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው (ማቴ:ም:17ቍ:1–8) ።



በደብረ ታቦር የመገለጥ ተአምር

<u>ሰባ ሁለት ደቀ መዛሙርት ለማስተማር መላካቸው</u>:- ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ሌላ ሰባ ሁለት አስተማሪዎችን (አርድእት) መረጠ። እርሱ ሊሄድበት ወደአሰበውም ልዩ ልዩ ቦታዎች ሁሉ ቀድመውት እንዲሄዱ ሁለት፥ ሁለት አድርጎ ላካቸው። እነርሱንም እንዲህ አላቸው:- «እነሆ፥ መከሩ ብዙ ነው፤ የመከሩ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ ስለዚህ ለመከሩ ሥራ ተጨማሪ ሠራተኞችን እንዲልክ የመከሩን ጌታ ለምኑት»።

እንግዲህ ሂዱ፤ እነሆ፥ እንደበጎች በተኵላዎች መካከል እልካችኋለሁ፤ ለመንገዳችሁ ምንም አትያዙ፤ የገንዘብ ኮረጆም ቢሆን፥ ከረጢትም ቢሆን፥ ጫማም ቢሆን አትያዙ፤ ከሰው ጋር ሰላምታ በመለዋወጥ በመንገድ ላይ ቆማችሁ ጊዜ አታጠፉ፤ በገባችሁበት ቤት ሁሉ አስቀድማችሁ ‹ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን› በሉ፤ ሰላም ወዳድ ሰው በዚያ ቤት ቢኖር ሰላማችሁ ያድርበታል፤ አለበለዚያ ግን ሰላማችሁ ወደ እናንተ ይመለሳል። ለሠራተኛ ደመወዝ ይገባል፤ ስለዚህ በገባችሁበት ቤት ያቀረቡላችሁን እየበላችሁና እየጠጣችሁ ቈዩ፤ ከቤት ወደቤትም አትዘዋወሩ። ወደማናቸውም ከተማ ስትገቡና ሰዎችም ሲቀበሉአችሁ የሚያቀርቡላችሁን ብሉ። በዚያች ከተማ የሚገኙትን በሽተኞች ፈውሱ፤ ለሕዝቡም የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ቀርባለች እያላችሁ ተናገሩ። ነገር ግን በማናቸውም ከተማ ስትገቡ ሰዎቹ የማይቀበሉአችሁ



ቢሆን ወደ ከተማይቱ አደባባይ ውጡና እንዲህ በሉአቸው:- ‹እነሆ፥ በእግራችን ላይ ያለውን የከተማይቱን ትቢያ እንኳ እናራግፍላችኋለን፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ እንደቀረበች ዕወቁ፤ በፍርድ ቀን ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶም ከተማ ይቀልላታል እላችኋለሁ» (ሉቃ: ም:10ቍ:1–12)።

<u>ስለ ጾም የቀረበ ጥያቄ</u>:- የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጥተው:- «እኛና ፈሪሳውያን ዘወትር እንጾማለን፤ የአንተ ደቀ መዛሙርት ግን የማይጾሙት ለምንድነው?» ብለው ጠየቁት። ጌታችንም እንዲህ ሲል መለሰላቸው:- «ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎች ማዘን ይገባቸዋልን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚለይበት ጊዜ ይመጣል፤ በዚያን ጊዜ ይጾማሉ። በአረጀ ልብስ ላይ አዲስ ዕራፊ የሚጥፍ ማንም የለም። ይህን ቢያደርግ ግን አዲሱ ዕራፊ አሮጌውን ልብስ ቦጭቆ ቀዳዳውን የባሰ ያሰፋዋል። እንዲሁም በአረጀ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር ማንም የለም፤ ይህን የሚያደርግ ቢኖር ግን አቁማዳው ይፈነዳል፤ የወይን ጠጁም ይፈስሳል፤ አቁማዳውም ተበላሽቶ ከጥቅም ውጪ ይሆናል። ነገር ግን አዲሱን የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ማኖር ይገባል፤ በዚህ ዐይነት ሁለቱም በደኅና ተጠብቀው ይኖራሉ» (ማቴ:ም:9ቍ:14–17)።

<u>የዳስ በዓል</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አይሁድ ሊገድሉት ይፈልጉት ስለነበረ ለብዙ ጊዜ በገሊላ እንጂ በይሁዳ ክፍል ሀገር መመላለስ አይፈቅድም ነበር። የዳስ በዓል የሚከበርበት ጊዜ ደርሶ ስለነበረ ወደ በዓሉ ወጥቶ በትምህርቱና በተአምራቱ ራሱን እንዲገልጥ ፈልገው መጽሐፍ ወንድሞቹ የሚላቸው የአክስቱ ልጆች፥ ተነሥና ወደ ይሁዳ ወጥተህ ራስህን ለዓለም ግለጥ፤ ራሱን ሊገልጥ እየፈለገ በስውር የሚሠራ የለም አሉት። ይህም የሚያመለክተው በዚያን ጊዜ እነርሱ እንኳ ገና ያላመኑበት እንደነበረ ነው። ጌታችን ግን:- ጊዜዬ ገና አልደረሰም፤ የእናንተ ጊዜ ግን ዘወትር የተመቸ ነው። ዓለም እናንተን ሊጠላችሁ አይችልም፤ እኔ ግን ሥራው ክፉ መሆኑን ስለም መሰክርበት ይጠላኛል፤ እናንተ ወደ በዓሉ ሂዱ፤ እኔ ግን ጊዜዬ ገና ስላልደረሰ ወደ በዓሉ አልሄድም ብሎአቸው በገሊላ ቀረ። እነርሱ ወደ በዓሉ ከወጡ በኋላ እርሱ ደግሞ በግልጥ ሳይሆን በስውር ወደ በዓሉ ወጣ። በበዓሉም እኩሌታ ወደ ቤተ መቅደስ ወጥቶ ማስተማር ጀመረ። ትምህርቱን ያዳምጡ የነበሩት ሰዎች ይህ ሰው ሳይማር መጻሕፍትን እንዴት ያውቃል? ብለው ተደነቁ። እርሱም ለመደነቃቸው የሰጠው መልስ:- «ትምህርቴ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም» በማለት ነው (ዮሐ. ም7)።

## የጌታችን ተአምራት

<u>ጋኔን ያደረበት ልጅ መፈወስ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አንድ ተራራ ላይ ወጥቶ መለኮታዊ ክብሩን ለሦስት ደቀ መዛሙርቱ ገልጦላቸው

www.ethiopianorthodox.org

በተመለሰ ጊዜ አንድ ሰው በእግሩ ሥር ወድቆ እንዲህ አለው:- «እባክህን ለልጄ ራራለት፤ እየጣለ የሚያሠቃይ የጋኔን በሽታ አለበት፤ ብዙ ጊዜ በእሳትና በውሃ ውስጥ ይወድቃል። ወደ ደቀ መዛሙርትህም አምጥቼው ሊፈውሱት አልቻሉም»። ጌታችንም ልጁን ወደ እኔ አምጡት ብሎ ጋኔኑን ገሠጸው። ጋኔኑም ከልጁ ወጣና በዚያኑ ጊዜ ተፈወሰ። በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን ወደ ጌታችን ቀርበው እኛ ጋኔኑን ለማውጣት ያልቻ ልንበት ምክንያት ምንድነው ብለው ጠየቁት። እርሱም «እምነታችሁ ጐደሎ በመሆኑ ነው፤ በእውነት እላችኋለሁ፤ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያኽል እምነት ካላችሁ ይህን ተራራ ከዚህ ተነሥተህ ወደዚያ ሂድ ብትሉት ይሄዳል፤ የሚሳናችሁም ምንም ነገር አይኖርም፤ እንደዚህ ዐይነቱ ግን በጾምና በጸሎት ካልሆነ በቀር አይወጣም» አላቸው (ማቴ:17፥14–21)።

<u>ጌታችን አራት ሺህ ሰዎችን መመገቡ</u>:- ድዳዎች ሲናገሩ፥ ሽባዎች ሲድኑ፥ አንካሳዎች በደኅና ሲራመዱ፥ ዕውሮች ሲያዩ በተመለከቱ ጊዜ አንድም በሽተኞቻቸው እንዲፈወሱላቸው ለማድረግ፥ አለበለዚያም የሚፈ ጸሙትን ተአምራት ለማየት ብለው ብዙዎች ሰዎች ጌታችንን ተከትለውት ይሄዱ ነበር። በዚህም መሠረት አንድ ጊዜ በረሓማ ወደ ሆነ ቦታ ሲሄድ ሴቶችና ሕፃናት ሳይቈጠሩ አራት ሺህ የሚሆኑ ወንዶች ተከትለውት ሄዱ። ርኅሩኅ ፈጣሪ ነውና ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ እነዚህ ሰዎች ከእኔ ጋር ሦስት ቀናቸው ስለሆነና የሚበሉት ስለሌላቸው እንዲሁ ያለምግብ ባሰናብታቸው በመንገድ ላይ ዝለው ይወድቃሉ ብዬ ያሳዝኑኛል አላቸው። ደቀ መዛሙርቱም ታዲያ፥ በዚህ በረሓ ለዚህ ሁሉ ሕዝብ የሚሆን ምግብ ከወዴት እናመጣለን አሉት። እርሱም ስንት እንጀራ አላችሁ ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱ ሰባት እንጀራና ጥቂት ዓሣዎች ብቻ አሉን አሉት። ከዚያ በኋላ ጌታችን ሕዝቡ በመሬት ላይ እንዲቀመጥ አዘዘ። ሰባቱን እንጀራና ዓሣውን አንሥቶ የምስጋና ጸሎት በማድረግ ቈርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ከሰጠ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ለሕዝቡ አቀረቡ። የነበሩት ሰዎች ሁሉ በልተው ከጠገቡ በኋላ የተረፈ ሰባት መሶብ ፍርፋሪ አነሡ (ማቴ:5፥32–38)።

<u>ደንቆሮና ድዳ የነበረው ሰው መፈወስ</u>:- ጌታችን ወደገሊላ ባሕር በደረሰ ጊዜ አንድ ድዳና ደንቆሮ የሆነ ሰው ወደ እርሱ አምጥተው እጁን እንዲጭንበት ለመኑት። ጌታችንም ሰውየውን ከሕዝቡ ለይቶ ለብቻው ወሰደና ጣቶቹን በሰውየው ጆሮዎች ውስጥ አገባ፤ ምራቁንም እንትፍ ብሎ የሰውየውን ምላስ ዳሰሰ፤ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አይቶ ሰውየውን «ኤፍታህ» አለው። ትርጕሙም ተከፈት ማለት ነው። ወዲያው ጆሮዎቹ ተከፈቱ፤ አንደበቱም ተፈታ፤ ያለአንዳች ችግርም አጥርቶ መናገር ጀመረ (ማር:ም:7ቍ:31–37)።



## <u>የጌታችን ምሳሌዎች</u>

<u>የወይን አትክልቱ ገበሬዎች ምሳሌ:-</u> ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተናገራቸው ምሳሌዎች መካከል ቀጥሎ የተዘረዘረው ምሳሌ አንዱ ነው።

የወይን አትክልት የተከለ አንድ ሰው ነበረ፤ እርሱም በወይን አትክልቱ ዙሪያ አጥር አጠረ፤ የወይን መጭመቂያ የሚሆን ጕድጓድ ቈፍሮ አበጀ፤ ለወይኑ ጥበቃ የሚያገለግል ረዥም ግንብ ሠራ፤ ከዚህ በኋላ የአትክልቱን ቦታ ለገበሬ ዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ። የፍሬ ወራት በደረሰ ጊዜ ድርሻውን እንዲቀበሉለት አገልጋዮቹን ወደ ገበሬዎቹ ላከ። ገበሬዎቹ ግን አገልጎዮቹን ይዘው አንዱን ደበደቡት፤ አንዱን ገደሉት፤ አንዱን ደግሞ በድንጋይ ወገሩት። የወይኑ አትክልት ጌታ እንደገና ቍጥራቸው ከፊተኞቹ የሚበልጥ ሌሎችን አገልጋዮች ደግሞ ላከ። ገበሬዎቹ በእነርሱም ላይ ተመሳሳይ ድርጊት ፈጸሙባቸው። በመጨረሻ የወይኑ አትክልት ጌታ ልጄንስ ያከብሩታል በማ ለት ልጁን ወደ ገበሬዎቹ ላከ። ገበሬዎቹ ግን ልጁን ባዩ ጊዜ ይህማ ወራሹ ነው፤ ኑ እንግደለውና ርስቱን እንውሰድ ተባባሉ። ልጁንም ይዘው ከአትክልቱ ውጪ ወሰዱና ገደሉት።



ይህ ወራሹ ስለሆነ ኑ እንግደለውና ርስቱን እንውሰድ ተባባሉ ማር: ም 12 ቍ 1–12)።

ጌታችንም ይህን ምሳሌ ከተናገረ በኋላ፥ ታዲያ፥ የወይኑ አትክልት ጌታ ምን ያደርግ ይመስላችኋል? ሲል ጠየቀ። እነርሱም:- እነዚያን ክፉ ገበሬዎች ያለ ርኅርኄ ይገድላቸዋል፤ ያትክልቱንም ቦታ ፍሬውን በጊዜው ለሚሰጡት ለሌሎች ገበሬዎች ይሰጠዋል አሉት።

ከዚያም ጌታችን:- «ግንበኞች የናቁት ድንጋይ የማእዘን ራስ ሆነ» የተባ ለውን አላነበባችሁምን? ስለዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ተወስዳ

www.ethiopianorthodox.org

ፍሬ ለሚያፈራ ለሌላ ሕዝብ ተሰጥታለች አላቸው። የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ይህ ምሳሌ የተነገረው በእነርሱ ላይ መሆኑን በተገነዘቡ ጊዜ ሊይዙት ፈልገው ነበር። ነገር ግን ሕዝቡ እንደ ነቢይ ያየው ስለነበረ ፈሩ (ማቴ : ም:21 ቊ: 33 –46)።

<u>የዐሥሩ ልጃገረዶች ምሳሌ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መንግሥተ ሰማያት ሌላ ምሰሌ ሲናገር እንዲህ ብሏል:- ወደ መንግሥተ ሰማይ የመግባት ሁኔታ መብራታቸውን ይዘው ሙሽራ ለመቀበል የወጡ የዐሥር ልጃገረዶችን ታሪክ ይመስላል። ከእነርሱ አምስቱ ሞኞች፥ አምስቱ ደግሞ ብልኖች ነበሩ።

ሞኞቹ ልጃገረዶች መብራታቸውን ይዘው ለመብራቱ የሚሆን ትርፍ ዘይት አልያዙም ነበር። ብልኖቹ ልጃገረዶች ግን ከመብራታቸው ጋር ትርፍ ዘይት በዕቃ ይዘው ነበር፤ ሙሽራው በመዘግየቱ ሁሉም በእንቅልፍ ተሸንፈው ተኙ። እኩለ ሌሊት ሲሆን ግን:- እነሆ፥ ሙሽራው መጣ፤ ውጡና ተቀበሉት የሚል ሁካታ ተሰማ፤ በዚያን ጊዜ ልጃገረዶቹ ሁሉ ተነሡና መብራታቸውን አዘጋጁ። ሞኞቹ ልጃገረዶች ብልኖቹን:- መብራታችን መጥፋቱ ስለሆነ እባካችሁ ከዘይታችሁ ስጡን አሉአቸው። ብልኖቹ ልጃገረዶች ግን «ለእኛና ለእናንተ የሚበቃ ዘይት የለንም፤ ይልቅስ ዘይት ወደሚሸጡ ሰዎች ሂዱና ለእናንተ የሚሆን ዘይት ግዙ» አሉአቸው።

ሞኞቹ ልጃገረዶች ዘይት ለመግዛት በሄዱበት ጊዜ ሙሽራው መጣ፤ ተዘጋጅተው የነበሩት ልጃገረዶች ከሙሽራው ጋር ወደ ሠርጉ ግብዣ ገቡ፤ በሩም ተዘጋ። ከዚያም በኋላ የቀሩት ልጃገርዶች መጡና ጌታ ሆይ፥ እባክህ ክፈትልን አሉት። እርሱ ግን በእውነት እላችኋለሁ አላውቃችሁም ሲል መለሰላቸው።



የዐሥር ልጃገረዶች ምሳሌ (ማቴ 25፣ 1–12)።

ስለዚህ ቀኑንና ሰዓቱን ስለማታውቁ ተግታችሁ ጠብቁ (ማቴ 25 ቍ:1–13)



## <u>ከዚህ ምዕራፍ የሚገኝ ትምህርት</u>

ሞቶ ከመነሣቱ በፊት የጌታችን የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊ ክብር ደቀ መዛሙርቱም ሆኑ ሌሎች ሰዎች እጅግም የተገነዘቡት አይመስልም። ስለዚህም ከሕማምና ከሞቱ በፊት ቢያንስ ለሦስት ደቀ መዛሙርቱ መለኮታዊ ክብሩን ገለጠላቸው። ይህንንም በማድረጉ እምነታቸው እንዲጠናከር አድርጎአል። ያም ሆኖ ከትንሣኤው በፊት እምነታቸው የተፈለገውን ያኽል የተጠናከረ አልነበረም። ይህም ባለመሆኑ ጌታችን ወደ ፍርድ ሸንጎ በቀረበ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ አላውቀውም ብሎ ካደው። ይሁን እንጂ የሦስቱ ደቀ መዛዘሙርት ምስክርነት ከጌታችን ትንሣኤ በኋላ የተገኘውን እምነት ለማጠናከር እንደረዳ የታመነ ነው። ለምሳሌ ከጌታችን ትንሣኤና ዕርገት በኋላ ሐዋርያት በአይሁድ ሸንጎ ፊት ቀርበው በጌታችን በኢየሱስ ስም እንዳያስተምሩ ባዘዙአቸው ጊዜ በነበራቸው የእምነት ጥንካሬ እኛስ ከእናንተ በፊት ለእግዚአብሔር መታዘዝ አለብን፤ ያየነውንና የሰማነውን እንመሰክራለን ብለው በድፍረት ተናግረዋል።

ጌታችንም በተራራው ላይ ከመገለጡ በፊት እንደማንኛውም ሰው በትስብእቱ ይታይ ስለነበረ መለኮታዊ ክብሩን በግልጥ ለማየት አልቻሉም ነበር።

ሙሴና ኤልያስ በአይሁድ ሕዝብ ዘንድ በጣም የተከበሩ ነበሩ። እነርሱ ተገልጠው ከጌታችን ጋር የተነጋገሩት የእርሱን ልዕልና ለደቀ መዛሙርቱ ለማሳየት ተብሎ ነው።

ቅዱስ ጴጥሮስም ምን እንደሚናገር ሳያውቅ ሦስት የመኖሪያ ዳሶች ልሥራ በሚልበት ጊዜ ደመና መጥቶ መሸፈኑና የእግዚአብሔር አብ ድምፅ መሰማቱ፥ ከዚያም ሙሴና ኤልያስ አለመታየታቸው እነርሱ ምድራዊ ዳስ የማያስፈልጋቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው። የእግዚአብሔር አብ ድምፅ ይህ ልጄ ነውና እርሱን ስሙት ማለቱ የእግዚአብሔር ወልድን መለኮታዊ ክብር ለደቀ መዛሙርቱ መግለጡ ነው። በእርግጥ ቀደም ብሎ በጌታችን ጥምቀት ጊዜ የመሰከረለት ቢሆንም አሁን ደግሞ የደቀ መዛሙርቱን እምነት ለማጠናከር ስለፈቀደ እንደገና መመስከርን አስፈላጊ ሆኖ አገኘው። በብሉይ ዘመን እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች አንድ ነገር ሊነግራቸው በሚፈቅድበት ጊዜ ሁሉ በደመና ውስጥ ሆኖ ይናገር ነበር። አሁንም ድምፁን በደመና ውስጥ ሆኖ ለደቀ መዘሙርቱ ማሰማቱ ያ የቀድሞ አባቶቻቸው አምላክ መሆኑን ሊያሳስባቸው ፈቅዶ ነው።

ይህ የመገለጥ ምሥጢር ተከናውኖ ከተራራው በወረዱበት ጊዜ ያን ጉዳይ ከትንሣኤው በፊት ለማንም እንዳይናገሩ ማዘዙ በዚህ ዓለም ላይ በሥጋ ተገልጦ በሚኖርበት ጊዜ ይህን ምሥጢራዊ ዜና የሚያምን ሰው እንደማይኖር በማወቁ ነው። ከትንሣኤ በኋላ ግን ተጨማሪ ማስረጃ ስለሆነ ሊታመን እንደሚችል ያውቃልና ከዚያ በኋላ እንዲነገር ፈቀደ።



www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዐሥራ ሁለት ሐዋርያትን የመረጠው በዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ምሳሌነት ሲሆን ከዚያ በኋላ ደግሞ ሰባ ሰዎችን የመረጠው በአስተዳደር ሥራ እርሱን እንዲረዱት ሰባ ሽማግሌዎችን እንዲ መርጥ እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ነው (ዘኍ:ም:11ቍ:6–17)። አብዛኛውን ጊዜ የብሉይ ኪዳን ሰዎችና ድርጊቶች ለሐዲስ ኪዳን ምሳሌነት የቆሙ ናቸው። የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ማስተማር ወደሚፈለጉት ቦታዎች ሁሉ ሊያደርስ የማይችል በመሆኑ መከሩ ብዙ ነው፤ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ ስለዚህ የመከሩን ጌታ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት ያለው ሰባዎቹን ከመረጠ በኋላ ነው። ይህም ማለት ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው ለመዳን የሚፈልጉት ብዙዎች ናቸው፤ እነርሱን ለማስተማር ችሎታውና ፍላጎቱ ያላቸው ግን ጥቂቶች ናቸው ማለት ነው። እንደ በጎች በተኵላዎች መካከል እልካችኋለሁ ብሎ የገለጠላቸው እነዚያ ተመራጮች ለሚደርስባቸው ነገር ሁሉ ትዕግሥትና ብቃት ያላቸው መሆናቸውን ስለሚያውቅ ነው። አለበ ለዚያማ በመፍራት ደንግጠው በበረገጉ ነበር እንጂ ወደ ተልእኮው ባልሄዱም ነበር። ኮሮጆ፥ ከረጢትና ጫማ አትያዙ ማለቱ የሚሄዱበት ቦታ ሩቅ ባለመሆኑና የሸክሙ ክብደት ለሥራው መሰናክል እንዳይሆን ተብሎ ነው።

በመንገድ ላይ ከማንም ጋር ሰላምታ አትሰጡ መባላቸው ከማኅበራዊ ግዴታዎች ሁሉ ራቁ ለማለት ሳይሆን የምሥራቅ አገሮች የሰላምታ አሰጣጥ ብዙ ጊዜ የሚፈጅ በመሆኑ በዚያ፥ ጊዜ በሚፈጀው የሰላምታ አሰጣጥ በመጠመድ ከሥራቸው እንዳይዘናጉ ለማለት ነው። ሰላምታ መስጠት አስፈ ላጊ መሆኑን ለማመልከት ግን ወደምትገቡበት ቤት ሁሉ አስቀድማችሁ:- ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን በሉ ብሎአቸዋል።

የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የጠየቁት ጥያቄ እነርሱና ፈሪሳውያን የሚጾሙ ሲሆኑ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ለምን እንደማይጾሙ ነው። ጌታችን ይህን ጥያቄ በተጠየቀ ጊዜ ጾም አስፈላጊ አይደለም፤ ወይም ሊጾሙ አይገባም አላለም። እርሱ ግን መልስ የሰጠው በምሳሌ ነው። ሙሽራ ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎች የማይጦሙ መሆናቸው እንዲያውም ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እስካለ ድረስ መደሰት እንጂ ማዘን እንደሌለባቸው ገልጦላቸዋል። ሙሽራው ከእነርሱ ሲወሰድ ግን ያን ጊዜ ይጾማሉ ብሎአቸዋል። ይህንንም ካለ በኋላ አዲስ ዕራፊ በአሮጌ ጨርቅ ላይ የሚጥፍና፥ አዲስ የወይን ጠጅ ደግሞ በአሮጌ አቁማዳ የሚያስቀምጥ የለም በማለት በምሳሌ ተናግሮአል።

እዚህ ላይ ሙሽራ ያለው ራሱን ሲሆን ሚዜዎች ያላቸው የእርሱን ተከታዮች ነው። ሙሽራው በሚወሰድበት ጊዜ ይጾማሉ የተባለው ከጌታችን ዕርገት በኋላ ለማለት ነው። አሮጌ ልብስና አሮጌ አቁማዳ የተባለው የኦሪቱ ሥርዓት ነው። አዲስ ልብስና አዲስ አቁማዳ የተባለው የሐዲሱ ሥርዓት ነው። ጌታችንም ሊል የፈለገው የኦሪቱ የጾም ሥርዓት ከሐዲሱ የጾም ሥርዓት የተለየ ስለሚሆን ደቀ መዛሙርቱና ምእመናን ከጌታችን ዕርገት በኋላ በአዲስ ሥርዓት



www.ethiopianorthodox.org

ይጾማሉ ማለቱ ነው። በዚህም አባባል መሠረት ቤተ ክርስቲያን ከጌታችን ዕርገት በኋላና በቤተ ክርስቲያን አባቶች ዘመን ከኦሪቱ ሥርዓት በተለየ ሁናቴ አጽዋማትን ዐውጃ ሠርታበታለች፤ ትሠራበታለችም።

የአይሁድ የዳስ በዓል በደረሰ ጊዜ መጽሐፉ ወንድሞቹ ብሎ የሚጠራቸው በሥጋ የአክስቱ ልጆች የነበሩት ወደጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀርበው ብዙ ሰዎች ወደሚሰበሰቡበት ወደበዓሉ ወጥቶ ራሱን ለደቀ መዛሙርቱና ለዓለም እንዲያሳውቅ ነገሩት። ያም በዓል ከአይሁድ ታላላቅ በዓላት አንዱ የነበረው የዳስ በዓል የሚባለው ነበር። በበዓሉም ላይ ሊገድሉት የሚፈልጉት ጸሐፍት፥ ፈሪሳውያን፥ ሰዱቃውያንና ሌሎችም ብዙዎች እስራኤላውያን እንደሚገኙ ይታወቃል። በዚህም ምክንያት ጌታችን ወደ ይሁዳ መሄድ ተቈጥቦ በገሊላ አውራጃ ብቻ ይመላለስ ነበር።

ከዚህ ሁሉ አደጋ ጋር ወንድሞቹ የተባሉት የአክስቱ ልጆች በኢየሩሳሌም ይሁዳ ተገኝቶ በዓሉን እንዲያከብር መጐትጐታቸው አንድም ዝነኛ እየሆነ በመሄዱ ቀንተውበትና ተመቅኝተውት እንዲሞትላቸው ስለፈለጉ ነው፤ አለበለዚያም ለምድራዊ ክብር የሚሠራ መሆኑን ገምተው በእርሱ ክብርና ገናናነት ሹመትና ሽልማት እንደሚያገኙ በመጓጓት ነው የሚሉ ሁለት የተለያዩ አስተያየቶች አሉ። ያም ሆነ ይህ ጌታችን የሰጣቸው መልስ ጊዜዬ ገና አልደረሰም፤ የእናንተ ጊዜ ግን ዘወትር የተመቸ ነው ብሎ ነው። እናንተ ወደ በዐሉ ሂዱ፤ እኔ ግን ጊዜዬ ገና ስላልደረሰ ወደ በዓሉ አልሄድም አላቸው። ይሁን እንጂ እነርሱ ከሄዱ በኋላ በግልጥ ሳይሆን በስውር ወደበዓሉ ወጣ። የእግዚአብሔር ድርጊቶች ሁሉ በጊዜ የተወሰኑ በመሆናቸው ያ የተወሰነው ሰዓት እስኪደርስ ድረስ ጊዜዬ ገና አልደረሰም ብሎአቸዋል። ይህንኑ አባባል ነው ለእናቱም በገሊላው ቃና ሠርግ ቤት ገና ጊዜዬ አልደረሰም ያላት (ዮሐ:ም:2ቍ:4)።

እየጣለ የሚያሠቃይ የጋኔን በሽታ ስላለበት እባክህ ለልጄ ራራለት፤ ወደ ደቀ መዛሙርትህ ባመጣው ሊፈውሱት አልቻሉም ብሎ አንድ ሰው በጌታችን እግር ሥር ወደቀ። በዚህ ጊዜ ጌታችን እናንተ የማታምኑ ጠማማ ትውልድ ሆይ፥ እስከመቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ፤ እስከመቼስ እታገሣችኋለሁ አለ። ይህን አባባል የሰነዘረው ብዙ ተአምራትንና ድንቅ ነገሮችን ሁሉ እያደረገ ሕዝቡ አለማመኑን ለመገሠጽነው የሚለው ሐሳብ አንድ አስተያየት ሲሆን፥ ደቀ መዛሙርቱ ያን ሕመምተኛ ልጅ ከሰይጣን ለማላቀቅ በቂ እምነት ስላልነበ ራቸው ለመገሠጽ ነው የሚለው ደግሞ ሌላው አስተያየት ነው።

የሕዝቡን አለማመን ለመገሠጽ ነው ተብሎ ለሚቀርበው አስተያየት የሚሰጠው ማስረጃ በማርቆስ ወንጌል ም9ቍ:22 ላይ ርኩስ መንፈስ ያደረበት ልጅ አባት ቢቻልህ እርዳኝ ማለቱ ነው። ጌታም ቢቻልህ ትላለህን? ለሚያምን ሁሉ ነገር ይቻላል ብሎታል።

ደቀ መዛሙርቱን ለመገሠጽ ነው ለሚለው አስተሳሰብ የሚሰጠው ማስረጃ ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ እኛ ያን ርኩስ መንፈስ ለምን ልናስወጣው አልቻልንም

ብለው በጠየቁት ጊዜ እምነታችሁ ጐደሎ ስለሆነ ነው ብሎ መመለሱ ነው። (ማቴ:ም:17ቍ:20)።

በዚህም ሆነ በዚያ በጉዳዩ ላይ ጌታችን አለማመንን ገሥጾአል። ሰይጣኑንም ገሥጾ አስወጥቶታል።

ጌታችን አራት ሺህ ሰዎችን በሰባት እንጀራና በጥቂት ዓሣ ብቻ እስኪበቃቸው ድረስ መመገቡ በአንድ በኩል ሁሉን ቻይነቱን ለመግለጥ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሰው መንፈሳዊ ምግብ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ሥጋዊ ምግብም የሚያስፈልገው መሆኑን ለማመልከት ነው።

በወይን አትክልት ገበሬዎች ምሳሌ እግዚአብሔርን እንደወይን አትክልቱ ባለቤት፥ አትክልቱን መትከሉ ማኅበረሰቡን በመመሥረቱ፥ አጥር ማጠሩ ደግሞ ለማኅበረሰቡ በጥንቃቄ ጥበቃ ማድረጉ፥ በአትክልቱ ቦታ ውስጥ የወይን መጭመቂያ የሚሆን ጉድጓድና የመጠበቂያ ግንብ መሥራቱ በቤተ መቅደስና በመሠዊያው ይመስላል። ከዚያም ያትክልቱን ቦታ አከራይቶ መሄዱ ማኅበረሰቡን በዐደራ ለአይሁድ በተለየም ለሊቃነ ከህናትና ለሽማግሌዎች መስጠቱን ያመለክታል። ከዚያም ተነሥቶ መሄዱ በሁሉም ነገር ለእነርሱ ሙሉ ሥልጣን የሰጣቸው መሆኑን ያመለክታል።

የመከር ጊዜ መቃረቡ የሚያመለክተው በአንድ በተወሰነ ጊዜ ከአይሁድ ሃይማኖታዊ ፍሬ ይጠበቅ የነበረ መሆኑን ነው። እግዚአብሔርም የአይሁድ ወገኖች የሚጠበቅባቸውን ፍሬ ባለማፍራታቸው ይወቅሱና ያስተምሩአቸው ዘንድ ነቢያትን ቢልክ አንዱን ደበደቡት፤ አንዱን ገደሉት፤ ሌላውን ደግሞ በድንጋይ ወገሩት። ይህም አይሁድ በእግዚአብሔር ነቢያት ላይ ያደረጉት ድርጊት ነው። ኤርምያስን ደበደቡ፥ ኢሳይይያስን ገደሉ፤ ዛካርያስን በመሠዊያው መካከል ወገሩ። እግዚአብሔርም ሌሎችን ቢልክ እንደቀድሞዎቹ አደረጉባቸው። እነዚህም መጥምቁ ዮሐንስና ሌሎች ናቸው። ምሳሌው በመጨረሻም ልጁን መላኩን ሲናገር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ዓለም መምጣቱን ያመለክታል። እንደተባለውም የአይሁድ አለቆች ጌታችንን ለሞት አሳልፈው እንደሰጡት የሚታወቅ ነው።

ጌታችንም ምሳሌውን ብቻ ከነገራቸው በኋላ የአትክልቱ ባለቤት በገበሬዎቹ ላይ ምን ያደርግባቸው ይመስላችኋል ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም ሲመልሱ እነርሱን ደምስሶ የአትክልቱን ቦታ ፍሬውን በየጊዜው ለሚሰጡ ለሌሎች ገበሬዎች ይሰጠዋል አሉት። ይህም በራሳቸው ላይ መፍረዳቸው መሆኑ ግልጥ ነው። በዚህም መሠረት አይሁድ በሮማውያን እጅ እንዲጠፉ ሆነው ቤተ ክርስቲያንን አረማውያን እንዲረከቡት ተደረገ።

ጌታችንም ይህን ያረጋገጠው «ስለዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ተወስዳ ፍሬ ለሚያፈራ ሕዝብ ትሰጣለች» በማለት ነው (ማቴ: ም: 21ቍ:43)።



## ጥያቄዎች

1. ወደ ከፍተኛ ተራራ ላይ የወጡት የጌታችን ደቀ መዛሙርት ምን አዩ?
2. ስለዚህ ትርኢት ጌታችን አስቀድሞ የተናገረው ምን ብሎ ነበር?
3. በተራራው ላይ ከጌታችን ጋር ሲነጋገሩ የታዩት ሁለት ሰዎች እነማን ናቸው?
4. በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ ምን አለ?
5. ደቀ መዛሙርቱ የደነገጡት ምን አይተው ነው?
6. ጌታችን አብረውት የነበሩትን ደቀ መዛሙርት ምን አዘዛቸው?
7. ለምን ይህን ትእዛዝ አዘዛቸው?
8. ጌታችን ሰባ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ለምን መረጠ?
9. በመንገዳቸው ምን እንዳያደርጉ ከለከላቸው? ለምን?
10. በሚገቡበት ቤት ምን እንዲያደርጉ ታዘዙ?
11. በሚገቡበት አገር ምን እንዲያደርጉ ታዘዙ?
12. ባይቀበሉአቸውስ ምን እንዲያደርጉ ታዘዙ?
13. ያቺስ ከተማ በፍርድ ቀን ምን ትሆናለች?
14. የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ስለጾም የጠየቁት ምን ብለው ነው?
15. እርሱስ ምን ብሎ መለሰላቸው?
16. ስለ አሪቱና ስለሐዲሱ የጾም ሥርዓቶች ምን ሁለት ምሳሌዎችን ሰጠ?
17. የጌታችን ወንድሞች የተባሉት ያክስቱ ልጆች ጌታችን የዳስ በዓል ወደሚከበርበት ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድ የፈለጉት በምን ምክንያት ነው?
18. ጌታችንስ ምን መልስ ሰጣቸው? መልሱስ ምን ለማለት ነው?
19. ሰዎች በትምህርቱ በተደነቁ ጊዜ ምን አሉ?
20. አንድ ሰው በጌታችን እግር ሥር ወድቆ ምንን ለመነው?
21. የልጁ በሽታ ምን ነበር?
22. ደቀ መዛሙርቱ ለምን ልጁን ሊፈውሱት አልቻሉም?
23. ደቀ መዛሙርቱ ጌታችንን ምን ብለው ጠይቀውት ምን መልስ ሰጣቸው?
24. ብዙ ሰዎች ጌታችንን የሚከተሉት ለምን ነበር?
25. ጌታችን አራት ሺህ ሰዎችን እንደምን መገበ?
26. ሰዎቹን የመገበበት ምክንያት ምንድነው?
27. ደቀ መዛሙርቱ ስንት እንጀራ ነበራቸው?
28. ስንት መሶብ ፍርፋሪ ተነሣ?
29. ጌታችን ደንቆሮውንና ድዳውን ሰው እንደምን አድርጎ ፈወሰው?
30. ስለወይን አትክልቱ ገበሬዎች ምሳሌ ተናገር።
31. ስለሠርጉ ግብዣ ምሳሌ ተናገር።
32. ስለ ዐሥሩ ልጃገረዶች ምሳሌ ተናገር።



www.ethiopianorthodox.org

33. ጌታችን ለሦስት ደቀ መዛሙርቱ በተራራ ላይ መለኮታዊ ክብሩን የገለጠላቸው ለምንድነው?

34. ጌታችን ከሞት ከመነሣቱ በፊት ደቀ መዛሙርቱ በተራራው ላይ ያዩትንና የሰሙትን ተአምር እንዳይናገሩ የታዘዙት ለምንድነው?

35. ሙሴና ኤልያስ እንዲገለጡ ለምን አስፈለገ?

36. እግዚአብሔር አብ ይህ ልጄ ነውና እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ ያሰማው በምን ምክንያት ነው?

37. ይህንኑ ድምፅ ቀደም ብሎ ያሰማው መቼ ነበር?

38. ቀደም ብሎ የእስራኤልን ልጆች ሊያነጋግራቸው ሲፈልግ እግዚአብሔር ምን ምልክት ያሳያቸው ነበር?

39. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያትና ሰባ ሁለቱን አርድእት በምን ምሳሌ መረጣቸው?

40. ሰባ ሁለቱን በላከ ጊዜ ለጉዞአቸው ምንም ነገር እንዳይዙ ያዘዛቸው በምን ምክንያት ነው?

41. በመንገድ ላይ ከማንም ጋር ሰላምታ እንዳይሰጣጡ ያዘዛቸው ለምንድነው?

42. በጾም ጥያቄ መልስ ላይ:- «ሙሽራ፥ ሚዜዎችና መወሰድ» የተባሉት ቃላት ምን ማለት ናቸው?

43. ጌታችን «እስከመቼ እታገሣችኋለሁ» ያለው ማንን ነው?

44. በመጨረሻ ልጁን መላኩስ በምን ይመሰላል?

45. የዐሥሩ ደናግል ምሳሌ ምንን ያሳስበናል?

# ምዕራፍ 4
# ቤተ ክርስቲያን

## አራቱ የቤተ ክርስቲያን ቅጽል ስሞች

በኒቅያና በቍስጥንጥንያ ጉባኤዎች በተላለፈው የሃይማኖት ቀኖና (የሃይማኖት ጸሎት) ውሳኔ መሠረት ቤተ ክርስቲያን አንዲት፥ ቅድስት፥ ዓለም ዐቀፋዊትና ሐዋርያዊት እንደሆነች እናምናለን።

<u>አንዲት</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም የባሕርይ አምላክ በመሆኑ ጸሎት የማያስፈልገው ቢሆንም እንኳ ለእኛ አርአያ ለመሆንና የእኛን ተግባር ለመፈጸም ለአባቱ በጸለየ ጊዜ «እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው» ብሎአል (ዮሐ:ም:17ቍ:11)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ማለት ስለምእምናን አንድነት በተለያዩ ሁናቴዎች ከገለጠባቸው አባባሎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«በአንዱ አካላችን ብዙ ክፍሎች አሉ፤ እያንዳንዱም ያአካል ክፍል የተለያየ ሥራ አለው፤ እንዲሁም እኛ ብዙዎች ሆነን ሳለ በክርስቶስ አንድ



አካል ነን፤ የአንድ አካል ክፍሎች እንደመሆናችንም እርስ በርሳችን ተጣምረናል» (ሮሜ:ም:12ቍ:4–5፥1ኛ:ቆር:ም:12ቍ:12–27)።

«የተለያዩት የሰውነት ክፍሎች የሚገጣጠሙት በክርስቶስ ነው፤ አካልም በሙሉ የተያያዘው በመገጣጠሚያዎቹ ነው፤ ስለዚህ እያንዳንዱ የአካል ክፍል የተመደበለትን ተግባር ሲያከናውን አካል በሙሉ ያድጋል፤ በፍቅርም ይታነጻል» (ኤፌ:ም:4ቍ:16)።

«በተጠራችሁ ጊዜ ለአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ እንዲሁም አንድ ጌታ፥ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ» (ኤፌ:ም:4ቍ:4–5)።

ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍት የተናገሩላት አንዲት ብትሆንም ይህ አንድነት ግን በእግዚአብሔር በኩል ሳይሆን በእኛ በኩል በየጊዜው እየተናጋ ነው። አብያተ ክርስቲያን የሚባለውን ስም ይዘው በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ያሉ የተለያዩ ወገኖች ብዙዎች ናቸው። በዓለም አብያተ ክርስቲያን ስብሰባ ላይ የሚደረግ የአንድነት ጥሪና ሙከራ ቢኖርም በተለያዩ ወገኖች ልዩነትን ለማንጸባረቅ የሚደረገው እንቅስቃሴ ግን ለአንድነት ከሚደረገው እንቅስቃሴ እየተጠናከረ በመሄዱ ልዩነቶቹ እየከፉ እንጂ እየረገቡ ስለማይሄዱ ሁላችንም በየአለንበት ለቤተ ክርስቲያን አንድነት እንጸልይ።

<u>ቅድስት</u>:- በሃይማኖቱ ቀኖና መሠረት ቤተ ክርስቲያን የምትጠራበት ሌላው መጠሪያ ደግሞ ቅድስና ነው። ቤተ ክርስቲያንም ቅድስት የተባለችበት ምክንያት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ምእመናን ሁሉ ቅዱሳን በመባላቸው፥ የቅዱሱ የእግዚአብሔር ተከታዮች በመሆናቸው፥ የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ ስለተቀበሉ፥ ራሳቸውን እንደ እግዚአብሔር ቅዱሳን የማድረግ ግዴታ ስላለባቸውና ለእግዚአብሔር የተለዩ ቅዱሳን በመሆናቸው ነው። የቤተ ክርስቲያንን ማለት የምእመናንን ቅድስና በተመለከተ የቅዱሳት መጻሕፍትን ማስረጃዎች ቀጥለን እንመልከት:-

«እነርሱም ደግሞ በእውነት ቅዱሳን እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ ቅዱስ አደርጋለሁ» (ዮሐ:ም:17ቍ:19)።

«የእነርሱና የእኛ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሚጠሩት ሁሉ ጋር በኢየሱስ ክርስቶስ ለተቀደሱትና ቅዱሳን ተብለው ለተጠሩት በቆሮንቶስ ለምትገኘው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን አባሎች» (1ኛ:ቆሮ:ም:1ቍ:2)።

«እንግዲህ ወዳጆቼ ሆይ፥ ይህ ሁሉ ተስፋ የተሰጠው ለእኛ ስለሆነ ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ከማናቸውም ነገር ራሳችንን እናንጻ እግዚአብሔርንም በመፍራት ቅድስናችንን ፍጹም እናድርግ» (2ኛ:ቆሮ:ም:7ቍ:1)።

«ለርኵሰት ሳይሆን እግዚአብሔር ለቅድስና ጠርቶናል» (1ኛ:ተሰ:ም:4ቍ:7)።



www.ethiopianorthodox.org

«በዚህም ፈቃድ [illegible] ኢየሱስ ክርስቶስ በማያዳግም ሁኔታ በሥጋ መሥዋዕት ሆኖ በመቅረቡ ምክንያት ተቀድሰናል» (ዕብ:ም:10ቍ:10)።

«ነገር ግን የጠራችሁ እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ እናንተም በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ። እኔ ቅዱስ ስለሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ተጽፎአል» (1ኛ:ጴጥ:ም:1ቍ:15–16) ።

ምንም እንኳ እኛ ብዙ የርኵሰት ሥራ በመሥራት የቤተ ክርስቲያንን ቅድስና ብንፈታተን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳረጋገጠው ቤተ ክርስቲያንን የሲኦል ኀይል እንኳ አያሸንፋትም (ማቴ:ም:16ቍ:18)።

<u>ዓለም ዐቀፋዊት:</u>- የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ያልተከፋፈለችና ያልተለያየች አንዲት መሆንዋ ብቻ ሳይሆን ይህች አንዲቱ ቤተ ክርስቲያን ከአጽናፍ አጽናፍ መድረስ ያለባት ዓለም ዐቀፋዊት ነች። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ቤዛ ከሆነልን በኋላ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተው ለዓለም በሙሉ ነው እንጂ ለተወሰኑ ወገኖች ብቻ አይደለም። በዚህም ምክንያት ነው ከዕርገቱ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ የሚከተለውን ትእዛዝ የሰጣቸው።

«እንግዲህ ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱና በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው የእኔ ደቀ መዛሙርት አድርጉአቸው» (ማቴ:ም:28ቍ:19)።

በክርስትና መሠረታዊ እምነት ውስጥ የወገን፥ የዘር፥ የቋንቋ፥ የጾታና የጐሣ ልዩነት የለም፤ ክርስቶስ የሁሉም ነው፤ ለሁሉም ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን አባባል ሲያብራራው እንዲህ ብሏል።

«ሁላችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ስለሆናችሁ በአይሁዳዊና በግሪካዊ፥ በአገልጋይና በጌታ፥ በወንድና በሴት መካከል ምንም ልዩነት የለም» (ገላ:ም:3ቍ:28)።

«በግሪካዊና በአይሁዳዊ፥ በተገረዘና ባልተገረዘ፥ በሠለጠነ አረመኔና ባልሠለጠነ አረመኔ፥ ነጻነት ባለውና ነጻነት በሌላው ሰው መካከል ልዩነት የለም፤ ክርስቶስ ሁሉም ነው፤ በሁሉም ነው» (ቆላ:ም:3ቍ:11)።

በዚህም መሠረት ክርስቲያንነትን የአንድ አገር፥ የአንድ ወገን፥ የአንድ ጐሣ ወይም የአንድ ብሔር ሃይማኖት አድርገው የሚያስቡ ሰዎች ስሕተታቸውን ሊገነዘቡት ይገባል።

<u>ሐዋርያዊት</u>:- ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት ነች የተባለው የሐዋርያትን ትውፊትና ትምህርት ስለምታስተምርና ይህንንም ለመጠበቅ እንዲቻል ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ተከታታይነቱ ያልተቋረጠ የካህናት አሿሿምን ሥርዓት ስለምትከተል ነው። በሐዋርያዊትነትዋም ከጥንትዋ ከመጀመሪያይቱ ቤተ



ክርስቲያን ጋር የተያያዘች ነች። የቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊነት ሲያረጋግጥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:-

«በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፤ የማእዘኑም ራስ ድንጋይ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ሕንጻው በሙሉ በእርሱ ተገጣጥሞ የጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ለመሆን ያድጋል» (ኤፌ:ም:2ቍ:20–21)።

የቤተ ክርስቲያን አባሎችም ከሐዋርያት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣላቸውን ሐዋርያዊ ትምህርት አጥብቀው መያዝና መጠበቅ ይኖርባቸዋል እንጂ ከመንገዱ መውጣት የለባቸውም። ቤተ ክርስቲያንም ሐዋርያዊት የተባለችው የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሁሉ ከሐዋርያት ተቀብለው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የእርስዋን መመሪያዎች እንዲከተሉ ነው እንጂ መመሪያዎቹን ችላ ብለው መረን እንዲለቀቁ አይደለም። ይህን አባባል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲያብራራው እንዲህ ብሏል:-

«ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፥ ጸንታችሁ ቁሙ፤ በቃላችንም ሆነ በመልእክታችን እኛ ባስተማርናችሁ ትውፊት ጽኑ» (2ኛ:ተሰ:ም:2ቍ:15)።

«ወንድሞች ሥራ ፈት ከሆነውና ከእኛ በተቀበላችሁት ትውፊት መሠረት ከማይኖር ክርስቲያን ሁሉ እንድትለዩ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችኋለን» (2ኛተሰ:ም:3ቍ:6)።

## <u>የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን</u>

<u>ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ</u>:- ይህ ያዕቆብ የዮሐንስ ወንጌላዊ ታላቅ ወንድም ነው። እርሱም ታላቁ ያዕቆብ በመባል ይታወቃል። ቅዱስ ያዕቆብና ቅዱስ ዮሐንስ ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋር ዓሣ አጥማጆች ነበሩ። ቅዱስ ያዕቆብንና ቅዱስ ዮሐንስን ጌታችን የነጐድጓድ ልጆች የሚል ስም ሰጥቶአቸዋል (ማር:ም:3ቍ:17) ። ጌታችን በጣም ያቀርባቸው የነበሩትም ቅዱስ ጴጥሮስና ሁለቱ የዘብዴዎስ ልጆች ነበሩ።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በይሁዳና በሰማርያ ካስተማረ በኋላ ወደ እስፓንያ ሄዶ ወንጌልን አስተምሮአል። ከእስፓንያም ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ ማስተማሩን ቀጠለ። በትምህርቱም ሕዝቡን ዐደራ ከሚልባቸው ትምህርቶች መካከል ለድኾችና ለደካሞች ምጽዋት እንዲሰጡ ነበር።

በሄሮድስ ዘንድ ስለአሳጡት ሄሮድስ አስጠራውና «ለቄሳር ግብር እንዳይከፈል ለድኾችና ለአብያተ ክርስቲያን ስጡ የምትል አንተ ነህን?» ብሎ በመጠየቅ በሰይፍ መታውና አንገቱን ቈረጠው።

በሁለተኛው መቶ ዓመት የነበረው የእስክንድርያው ቀሌምንጦስ እንዲህ ብሏል:- «ቅዱስ ያዕቆብን የያዘው ወታደር ድፍረቱን በተመለከተ ጊዜ ከዚህ ዓለም የተሻለ ሌላ ሕይወት መኖር አለበት አለ።የቅዱስ ያዕቆብን ይቅርታ ጠይቆ «ልጄ ሆይ፥ እግዚአብሔር የዘለዓለምን ሕይወት ይስጥህ አለው።



www.ethiopianorthodox.org

ከዚያም ኃጢአቱን ተናዝዞ አጠመቀውና በ44 ዓ.ም. ከሐዋርያው ጋር የሰማዕትነትን አክሊል ተቀዳጀ።»

ምእመናንም የቅዱስ ያዕቆብን አስከሬን ወስደው በቤተ መቅደስ አጠገብ ቀበሩት።

የሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም ዐፅም ወደ ስፓንያ ተወስዶአል ይባላል (የሚያዝያ 17 ቀን ስንክሳር)።

<u>ሐዋርያው ቅዱስ ስምዖን (ቀናኢ)</u>:- ቀናተኛው ስምዖን የተባለው ሐዋርያ በሌላ ስሙ ናትናኤል የተባለው ነው።

ስለናትናኤል የዮሐንስን ወንጌል ም:1ቍ:45–51 ይመለከቷል። እርሱም የኦሪትንና የነቢያትን መጻሕፍት የተማረ እንደነበረ ይነገርለታል።

ከፍ ያለ የሃይማኖት ቀናኢነት ስለነበረው ቀናኢ የሚል ቅጽል ተሰጥቶታል፤ ሌሎች ምሁራን እንደሚሉት ደግሞ የሮምን አገዛዝ በመቃወም የአይሁድ ምሥጢራዊ የፖለቲካ ድርጅት አባል ስለነበረና ድርጅቱም የቀናኢ ዎች ድርጅት ይባል ስለነበረ እርሱም ቀናኢ ተብሎአል የሚል ነው።

ለማንም የማያዳላ ንጹሕ ጻድቅ ሰው ነበር። ስለዚህ ነው ፊልጶስ ሙሴና ነቢያት ስለ እርሱ የጻፉለት ክርስቶስን አገኘነው፤ እርሱም የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው ባለው ጊዜ በውኑ ከናዝሬት መልካም ነገር ይወጣልን ብሎ የጠየቀው። ፊልጶስም ናና እይ አለው።

እንዲሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ:- «እነሆ፥ ተንኰል የሌለበት እውነተኛ እስራኤላዊ» ባለው ጊዜ ምስጋናው ሳያሸንፍ ወዴት ታውቀኛለህ ብሎ ማስረጃ ጠየቀ። ጌታችንም ገና ፊልጶስ ሳይጠራሁ ከበለሱ ዛፍ ሥር በነበርክ ጊዜ አየሁህ አለው። ከዚያ በኋላ የተደበቀውን ነገር የሚያውቅ መሆኑን ስላረጋገጠ «አንተ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ» አለው። ስለዚህ አባባል የሚነገሩ ታሪኮች:-

ከሰዓት በፊት ከአንድ ሰው ጋር ተጣልቶ ያን የተጣላውን ሰው በመግደል በበለሱ ዛፍ ሥር የቀበረው መሆኑ ይነገራል። ይህን ጉዳይ ማንም ሰው አያውቅም ነበር።

ሌላው ታሪክ ደግሞ ሄሮድስ ሕፃናትን ባስፈጀ ጊዜ የስምዖን እናት በግቢዋ ውስጥ በነበረ በአንድ የበለስ ዛፍ ላይ እንደደበቀችው ይነገራል። የሕፃናቱ ግድያ እስኪቆም ድረስ በየሌሊቱ እያጠባችው በየቀኑ ትደብቀው ነበር። ዐድጎ ጐልማሳ እስከሆነ ድረስ ይህን ጉዳይ አልነገረችውም። ሌላ ማንም ያወቀ ሰው የለም።

በዚህም ምክንያት ጌታችን በሰጠው መልስ ሁሉንም ነገር የሚያውቅ መሆኑን አረጋገጠ። ስለዚህም ለጌታችን ተገዥ ሆኖ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ በመሆን ተከተለው። የመንፈስ ቅዱስንም ጸጋ ከተቀበለ በኋላ በቋንቋዎች ተናገረ፤ በወንጌል ትምህርቱም ለዓለም ብርሃን ሆነ። ካስተማረባቸውም



አገሮች ኖብያና የእንግሊዝ ደሴቶች ይገኙበታል። በሥራውም ድፍረትን ያበዛ ስለነበረ ብዙ ችግር ደርሶበታል።

በእርሱም እጅ እግዚአብሔር ብዙ ተአምራትን አድርጓል።

በመጨረሻም በእንጨት ላይ ተሰቅሎ የሰማዕትነትን አክሊል ተቀዳጀ። (የግንቦት 15 ቀን ስንክሳር)

<u>ትልቁ ቅዱስ እንጦንስ</u>:- ቅዱስ እንጦንስ በ251 ዓ.ም. ቤተ ክርስቲያንንና ድኾችን ከሚወድድ ሀብታም ቤተሰብ በምድረ ግብጽ ተወለደ። ዕድሜው 20 ዓመት በሞላው ጊዜ ወላጆቹ ሞተውበት እኅቱን መንከባከብ ነበረበት።

አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰባኪው በሚሰብክበት ጊዜ «ፍጹም ልትሆን ብትወድድ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድኾች ስጥ፤ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፤ መጥተህም ተከተለኝ» የሚለውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት ሲያነብብ ሰማው። በሌላ ቀን ደግሞ ለነገ አታስቡ የሚለውን ቃል ሰማ። እነዚህ ሁለት ትምህርቶች የተነገሩት ለእርሱ እንደሆነ አምኖ በተግባር ላይ ሊያውላቸው በመወሰን ወደ ቤቱ ተመለሰ። ከዚያም በኋላ ገንዘቡን ለድኾችና ለችግረኞች ማከፋፈል ጀመረ። እኅቱን ከትንሽ ገንዘብ ጋር ለደናግል አስረከባት። በዚያን ጊዜ ገና የምንኵስና ሥርዓት አልተመሠረተም ነበር። ነገር ግን የብሕትውናን ኑሮ ለመኖር የሚፈልግ ሰው ሁሉ ከከተማ ውጪ ወዳለ ቦታ ይሄድ ነበር። ትልቁ እንጦንስም ያደረገው ይህንኑ ነው። በብሕትውና ባለበት ቦታ ሁሉ ሰይጣን በጭንቀት፥ በስንፍናና የሴቶችን መልክ በማሳየት ይዋጋው ነበር። እርሱም ይህን ሁሉ ፈተና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ኀይል ድል ይነሣው ነበር። ከዚህ በኋላ ወደ አንድ የመቃብር ቦታ ሄደና በር ዘግቶ ተቀመጠ። በዚህ ጊዜ ሰይጣን ራሱን የቅዱስ እንጦንስ ወዳጅ በማስመሰል መጣበት። የብሕትውናውንና የአምልኮቱን ጥንካሬ በተመለከተ ጊዜ ተመቀኘውና በጣም ደብድቦ ጥሎት ሄደ። ወዳጆቹ ሊጠይቁት በመጡ ጊዜ በዚያ ሁናቴ አግኝተውት ወደ ቤተ ክርስቲያን ተሸክመውት ሄዱ። ትንሽ ሲሻለው ወደቀድሞ ቦታው ተመለሰ። ሰይጣንም በተለያዩ አራዊት፥ ማለት በድቦች፥ በአንበሶች፥ በእባቦችና በተርቦች መልክ እየሆነ ውጊያውን መቀጠሉን ልማድ አደረገ። ሁላቸውም ሊቦጫጭቁት እንደተዘጋጁ ያስመስለው ነበር። ቅዱስ እንጦንስ ግን:- «በእኔ ላይ ሥልጣን ቢኖራችሁ ኖሮ እኔን ለመዋጋት ከእናንተ አንዱ በበቃ ነበር» ብሎ ያላግጥባቸው ነበር። እንደዚያ ሲላቸው ከፊቱ እንደ ጢስ በነው ይጠፉ ነበር። ይህም የሆነው ጌታችን በሰይጣን ላይ ድልን ሰጥቶት የነበረ በመሆኑ ነው። እርሱም:- «እግዚአብሔር ይነሣ፤ ጠላቶቹም ይበተኑ፤ የሚጠሉትም ከፊቱ ይሸሹ» የሚለውን መዝሙር ይዘምር ነበር (መዝ:68 ቍ:1)።

ለስድስት ወር የሚበቃውን ዳቦ ለራሱ ያዘጋጃል፤ ማንም ሰው ወደ ክፍሉ እንዲገባ አይፈቅድም። ምክሩን ለመስማት የሚፈልገውን ሰው በውጭ ሆኖ እንዲያዳምጥ ያደርገዋል። በዚህ ዐይነት በታላቅ ብሕትውና ሆኖ እግዚአ



www.ethiopianorthodox.org

ብሔርን እያመለከ ለኻያ ዓመቶች ቀጥሎአል። ከዚያ በኋላ በጌታችን ትእዛዝ ፈፅም ወደምትባል ክፍለ ሀገር ሄዶ ወንድሞችን ካበረታታ በኋላ ወደ ገዳሙ ተመልሶአል።

በሰማዕታት ዘመን የሰማዕትነትን አክሊል ለመቀዳጀት በመፈለግ ገዳሙን ትቶ ወደ እስክንድርያ ከተማ ሄደ። እዚያም እስረኞችን እየጐበኘ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ሰበከላቸው። አገር ገገርው ቅዱስ እንጦንስን ያለምንም ፍርሀትና በግዴለሽነት ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር ባየው ጊዜ ዳግመኛ በከተማዋ ውስጥ እንዳይታይ አዘዘ። ቅዱስ እንጦንስ ግን ማስጠንቀቂያውን ችላ ብሎ እየተጋፈጠ ወደ ሥቃይ ተወስዶ በሰማዕትነት ለመሞት እንዲችል ይገፋፋ ነበር። ጌታችን ግን ስለ ብዙዎች ጥቅም ሲል ስለጠበቀው አገረ ገገርው እንደፈለገው ይሁን ብሎ ተወው። በእግዚአብሔር ዝግጅት ቅዱስ እንጦንስ ወደ ገዳሙ ተመለሰ።

ትምህርቱን ለማዳመጥ ወደ እርሱ የሚመጡት ሰዎች እየበዙ ስለሄዱ ይህ ሁናቴ የአምልኮ ጊዜውን እንደሚወስድበት ተመለከተ። በዚህም ምክንያት በምሥራቅ በኩል ወደ በረሓው ርቆ ሄደ። ከአንዳንድ ዐረቦች ጋርም እስከ ሦስት ቀን በሚያስኬድ ጉዞ ወደ በረሓው ውስጥ ገባ። እዚያም የውሃ ምንጭና የተምር ዛፍ አግኝቶ ያን ቦታ ለመኖሪያነት መረጠው። ዐረቦቹ ዳቦ ያመጡለት ነበር። በበረሓው ብዙ አራዊት የነበሩ ቢሆኑም እግዚአብሔር ግን ለእርሱ ሲል አባረራቸው። አንዳንድ ጊዜ ውጪ ወደ አለው ገዳም እየሄደ እዚያ ያሉትን ወንድሞች እየጐበኘ ይመለስ ነበር። የቅዱስ እንጦንስ ዝና የእግዚአብሔር ወዳጅ ወደነበረው ወደ ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ ዘንድ ደረሰ። ንጉሡም የምስጋናና በጸሎቱ እንዲያስታውሰው የሚለምን ደብዳቤ ጻፈለት። ወንድሞች በንጉሡ ደብዳቤ ደስ ተሰኙ። ቅዱስ እንጦንስ ግን ለደብዳቤው ትኩረት አልሰጠውም። ለወንድሞችም እንዲህ አላቸው:- የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ የእግዚአብሔር መጽሐፍ ይኸውላችሁ፤ እርሱም በየዕለቱ ምክር ይሰጠናል፤ ስለ እርሱም ገለጻ እናደርጋለን፤ እኛ ግን ትክ ብለን አናስተውለውም። ወንድሞች ግን ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ እኮ የቤተ ክርስቲያን ወዳጅ ነው አሉት።

ቅዱስ እንጦንስን ቅዱስ መቃርዮስ በጐበኘው ጊዜ የምንኵስና ልብስ አልብሶ ወደፊት ምን እንደሚሆን ነገረው። የቅዱስ ጳውሊ የዕረፍት ጊዜ ሲደርስ ቅዱስ እንጦንስ ሄዶ እንክብካቤ በማድረግ ፓትርያርኩ ቅዱስ አትናቴዎስ ሰጥቶት በነበረው ሸማ ከፈነው።

ቅዱስ እንጦንስ የዕረፍቱ ጊዜ መቃረቡን ዐውቆ ሥጋውን እንዲደብቁ፥ በትሩን ለመቃርዮስ፥ ቆቡን ለአትናቴዎስ እንዲሰጡ ልጆቹን አዘዛቸው። ከዚያም በመሬት ላይ ተዘርግቶ ተኝቶ ነፍሱን ሰጠ። ቅዱሳን መላእክትም ነፍሱን ተረክበው ወደ ዘለዓለም ዕረፍት ወሰዱአት። ይህ ቅዱስ ለቅድስናና ለንጽሕና ሲታገል የኖረው አንድ መቶ አምስት ዓመት ነው (የጥር:22 ቀን:ስንክሳር)።



# በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ

# የኢትዮጵያና የግብጽ አብያተ

# ክርስቲያን ግንኙት ታሪክ በአጭሩ

የሁለቱ አብያተ ክርስቲያን ግንኙነት የጀመረው ቅዱስ አትናቴዎስ መጀመሪያ የኢትዮጵያ ጳጳስ የሆነውን ቅዱስ ፍሬምናጦስን ሾሞ ወደ ኢትዮጵያ በላከበት በ330 ዓ.ም. ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በእነዚያ በሀሥራ ስድስት መቶ ዘመናት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በተከታታይ የኢትዮጵያ ጳጳሳት እንዲሆኑ የተሾሙት ሁሉም ግብጻውያን ነበሩ እንጂ አንድ እንኳ ኢትዮጵያዊ አልነበረም።

ጳጳሳቱ ኢትዮጵያውያን ባለመሆናቸው በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ከደረሱት ችግሮች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል:-

' በመጀመሪያ ጳጳሳቱ የእኛን ቋንቋ ባለማወቃቸውና እኛም የእነርሱን ቋንቋ ባለማወቃችን ካህናትን ከመሾምና ቡራኬ ከመስጠት ዐልፈው በቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ሥራ ተሳታፊ ሊሆኑና መመሪያ ሊሰጡ አልቻሉም። ሕዝቡም ከእነርሱ ጋር ሊግባባና የእነርሱን ጸሎት ሊከታተል አልቻለም።

ሁለተኛ/አንዱ ጳጳስ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ በምትኩ ሌላ ጳጳስ ለማስመጣት የሚደረገው ጥረት በጣም አስቸጋሪ ነበር። በአንድ በኩል በጊዜው በመንበሩ ላይ ያለው ፓትርያርክ ተተኪውን ጳጳስ ሾሞ ለመላክ ፈቃደኛ እንዲሆንና የተሾመውም ጳጳስ ወደ ኢትዮጲያ እንዲመጣ የግብጽ ባለ ሥልጣን ፈቃድ እንዲሰጥ ለማድረግ በጣም አድካሚ ጥረትን ይጠይቅ ነበር። ከእነዚህ ችግሮች ጋር በጊዜው የነበረው የመጓጓዣ ችግር ተጨምሮበት ተተኪውን ጳጳስ ለማስመጣት ብዙ ዘመናት ይወስድ ነበር።

ሦስተኛ/ ተተኪው ጳጳስ ሳይመጣ ብዙ ዘመን ከመዘግየቱ የተነሣ ቤተ ክርስቲያኒቱ የቀሳውስትና የዲያቆናት እጥረት ያጋጥማት ነበር።

አራተኛ/ በተተኪው ጳጳስ መዘግየት ምክንያት የሚያጋጥመውን የካህናት እጥረት ችግር ለመቋቋም ሲባል አጋጣሚ ሆኖ ጳጳስ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ ስለ ሃይማኖት ምንም የማያውቁ ሕፃናት የዲቁና ማዕረግ እንዲቀበሉ ይደረግ ነበር። ለሃይማኖት ትምህርቱ ምንም ትኩረት ሳይሰጠው በዲቁና እንዲያገለግሉ ይደረጉና ካደጉም በኋላ ምንም ለዚያ የሚያበቃ የሃማኖት ትምህርት ሳይኖራቸው የቅስናውን ማዕረግ ተቀብለው እንዲያገለግሉ ይደረግ ነበር። በዚህም ምክንያት በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በቂ የሃይማኖት ትምህርት የሌላቸው ካህናት ሊኖሩ ቻሉ።

ለቦታው ማለት ለሹመቱ ብቃት የነበራቸው የሀገር ተወላጆች እያሉ ብቃት ያልነበራቸውን የውጪ ሀገር ሰዎች መንፈሳውያን የበላይ አባቶች አድርጎ

www.ethiopianorthodox.org

ለአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዘመን መቈየቱ ብዙዎቹን የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሲያሳዝንና ሲያበሳጭ የኖረ ጉዳይ ነበር። ይሁን እንጂ የቀድሞዎቹ አባቶቻችን ጉዳዩን ዝም ብለው በመበሳጨት ብቻ የተመለከቱት አልነበሩም። እነርሱ ግን የቤተ ክርስቲያኒቱ ንብረት በውጪ አገር ሰው ቊጥጥር ሥር እንዳይገባ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ንብረት የሚቈጣጠርና በበላይነት የሚመራ ዕጨጌ የሚባል ኢትዮጵያዊ ከፍተኛ መንፈሳዊ ሹም እንዲኖር አድርገው ሲሠሩበት ኖረዋል። ይህ አሠራር ግን ግብጻውያኑን ጳጳሳት አያስደስታቸውም ነበር።የማይደሰቱበትም ምክንያት ሥልጣናቸው በዕጨጌው እንደተወሰደባቸው ይገምቱ ስለነበረ ነው።

ጉዳዩ ሳይሳካ በመቅረቱ ነው እንጂ የቀድሞዎቹ ሰዎች ዕጨጌ በመሾም ብቻ የረኩ አልነበሩም። ለምሳሌ ከ1035 እስከ 1045 የነገሡት ንጉሥ ሐርቤ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትን ለመሾም በጊዜው በእስክንድርያ መንበር ላይ ተቀምጠው ከነበሩት ከአባ ገብርኤል ጋር በመላላክ ብዙ ሙከራ አድርገው ነበር። ይሁን እንጂ ሙከራቸው ሳይሳካ ቀርቶአል። (የአቡነ ጎርጎርዮስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ ገጽ: 41–42)።

በሐርቤ ዘመን ተጠይቆ ያልተሳካውን ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትን የማሾም ጉዳይ እንደገና በዐፄ ዮሐንስ ዘመን ሙከራ ተደርጎ አሁንም ሳይሳካ ቀርቶአል።

በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ግን ቀደም ብሎ በንጉሥ ሐርቤና በዓፄ ዮሐንስ ጊዜ የተሞከረውና ያልተሳካው በከፊልም ቢሆን ተግባራዊ መሆን ጀመረ። በኢትዮጵያና በግብጽ ቤተ ክርስቲያን መካከል ከተደረገው ከሦስት ዓመት ውይይት በኋላ በተደረሰው ስምምነት በ1921 ዓ.ም. በካይሮ አራት ኢዮጵያውያን ጳጳሳት ተሹመዋል።

የተሾሙትም ጳጳሳት ስም:-

1. አቡነ አብርሃም፥ የቀድሞ ስማቸው መምህር ደስታ፥
2. አቡነ ይስሐቅ፥ የቀድሞ ስማቸው መምህር ወልደ ኪዳን፥
3. አቡነ ጴጥሮስ የቀድሞ ስማቸው መምህር ኃይለ ማርያም
4. አቡነ ሚካኤል የቀድሞ ስማቸው መምህር ሐዲስ ነው።

የእስክንድርያው ፓትርያርክ እነዚህ ጳጳሳት በተሾሙ በዓመቱ ኢትዮጵያን ለመጐብኘት በመጡ ጊዜ ማለት በ1922 ዓ.ም. ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስን አቡነ ሳዊሮስ ብለው ስለሾሙአቸው የተሾሙት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ቊጥር አምስት ሆነ።

እነዚህ አምስት ጳጳሳት ለመጀመሪያ ጊዜ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የሾመቻቸው ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ቢሆኑም እንኳ የንጉሥ ሐርቤና የዐፄ ዮሐንስ ሙከራ በከፊል ተግባራዊ ሆነ የተባለው ከእነርሱ በላይ አቡነ ቄርሎስ የተባሉት ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ ስለተሾሙባቸው ነው።



ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በተሰኘው መጽሐፋቸው ኢትዮጵያ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሥር ይህን ያኽል ዘመን የቈየችበትን ምክንያት ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል።

«ኢትዮጵያ ከግብጽ ጳጳሳት ስታስመጣ የቆየችው በሚከተለው ምክንያት ነው። በሠለስቱ ምዕት ስም በጉባኤ ኒቅያ ቀኖና አንቀጽ 42 በስርዋጽ የገባ- «ኢትዮጵያውን ከሊቃውንቶቻቸው ጳጳስ አይሹሙ» የሚል ትእዛዝ ነበር። ይህ በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጨመረ ነው። ይኸው ሕግ በሰማኒያኛው ቀኖናው ኢትዮጵያውያን ጳጳስ እንዳይሾሙ ይከለክላል። ግብጻውያን ይህን ምክንያት አድርገው ኢትዮጵያውያን ጳጳስ መሆን አይገባቸውም እያሉ ሲከራከሩ ከላይ የተጠቀሰው ረጅም ዘመን አልፏል። እርግጥ ሠለስቱ ምዕት ይህን የግብጾችን ጥቅስ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን መለያየት እንዳይፈጠር በማሰብ በኒቅያው ቀኖና በስድስተኛው አንቀጽ «የግብጽ፣ የሊቢያንና የጴንጣጶሊስ መንበሮች ክርስትናን ከእስክንድርያ መንበር ስለ ተቀበሉ ለመሪያቸው ለእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ እንዲታዘዙ ሕግ ሠርተዋል። ቀኖና ወስነዋል። የሮምና የአንጾኪያ ሊቃነ ጳጳሳትም በየሀገረ ስብከታቸው ተመሳሳይ ሥልጣን ነበራቸው፤ በዚህ ሳቢያ ኢትዮጵያም ከእስክንድርያ ሀገረ ስብከት ክፍል ስለነበረች ለእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መታዘዝ ነበረባት የሚል የኮነቶች እምነት ብዙ ጊዜ ሲሠራበት ኖረ» (ገጽ:86–87)።

በመሠረቱ የኒቅያ ጉባኤ ቀኖናዎች ኻያ ብቻ ናቸው። ይህ የኒቅያ ጉባኤ ውሳኔ ነው ተብሎ ኢትዮጵያ የሃይማኖት አባት ከልጆችዋ መካከል እንዳትሾም የሚከለክለው ደንብ በኻያዎቹ ቀኖናዎች ውስጥ የሌለ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳ ለኢትዮጵያ ጳጳስ የተሾመላት በ330 ዓ.ም. ቢሆን የክርስትናን እምነት የተቀበለችው ግን በመጀመሪያው መቶ ዓመት በሕንደኬው ጃንደረባ አማካይነት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ የሚመሰክር ሲሆን ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ የነበረው ሐዋርያው ማቴዎስም ክርስትናን በኢትዮጵያ እንዳስተማረ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያረጋግጣል።

ከዚያም በላይ ቅዱስ ፍሬምናጦስ ለኢትዮጵያ ጳጳስ ሆኖ የተሾመው የኒቅያ ጉባኤ በ325 ዓ.ም. ስብሰባውን ከፈጸመ በኋላ በ330 ዓ.ም. ነው። ታዲያ የኒቅያ ጉባኤ ስለ ኢትዮጵያ መንበር ጉዳይ በትንቢት ወሰነ ማለት ነውን?

ፍሬምናጦስ ወደ ግብጽ ሄዶ ቢሾምም ዘሩ ሶርያዊ ነበር እንጂ ግብጻዊ አልነበረም።

የክርስትና ሃይማኖት የክህነት ሥርዓት ደግሞ እንደ ኦሪቱ ሥርዓት ለተወሰነ ዘር ብቻ የተፈቀደ አይደለም።

ግብጾችም እኛ በእነርሱ ሥር ሆነን እንድንተዳደር ለማድረግ ያን በፍትሐ ነገሥቱ ውስጥ በስርዋጽ የገባውን አንቀጽ ይጠቅሱታል እንጂ እነርሱ ራሳቸው እንኳ አያምኑበትም። እንዲያውም ትክክል አይደለም በማለት ይተቹበታል።

www.ethiopianorthodox.org

እንደ እነርሱ አባባል የዚያ አንቀጽ በፍትሐ ነገሥቱ ውስጥ መገኘት የሌሎች ወገኖች ኀላፊነት ነው እንጂ የእነርሱ አይደለም።

በዚህ ጉዳይ በኢትዮጵያውያን በኩል የነበረውን ስሜት ለመገንዘብ ቀጥሎ ያለውን የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌን አባባል ይመለከቷል:-

በስም ብቻ መክበር ሥራውን ሳይሠሩ፥
የግብጦች ዱለት ነው መቼ የማኀበሩ፤
በሀገራችንም ንብሪድና እጨጌ፥
የጳጳሳት ስም ነው መቼ የባለጌ።
ነጻነት ከሌላት ክህነት በሀገርዋ፥
ፍጹም አይባልም የነጻነት ክብርዋ፤
ንጉሥ ሳይኖራቸው ሶርያና አርመን፥
መርጠው ይሾማሉ በትረክና አቡን፤
ከወገኑ መርጦ ጳጳሰ የማይሾም፥
ከጦቢያችን በቀር ሌላ ሕዝብ የለም

(አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ)

ይህ የቤተ ክርስቲያናችንና የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የታሪክ ሂደት እስከ 1928 ዓ.ም የፋሺሽት ወረራ ድረስ ቀጠለ። ከላይ ከተጠቀሱት ከአምስት ኢትዮጳያውያን ጳጳሳት በላይ በዚያን ጊዜ የነበሩት ግብጻዊው ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ ይባሉ ነበር።

በጊዜው ከነበሩ ሰዎች በተላለፈልን ምሥክርነት መሠረት በጠላት ወረራ ጊዜ እንደ እነአቡነ ጴጥሮስና እንደ እነአቡነ ሚካኤል ያሉት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ከወራሪው ጠላት ጋር ላለመተባበር ስለ ሀገራቸው ሕይወታቸውን አሳልፈው ሲሰጡ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑት አቡነ ቄርሎስ ግን የዕጨጌነቱን ሥልጣን ከኢትዮጵያውያን እጅ ወስዶ ያስረከባቸው ዘንድ ከወራሪው ጠላት ተወካይ ጋር ይደራደሩ ነበር። የጠየቁት ጥያቄ ሳይሳካላቸው በቀረ ጊዜና ሕዝቡም ድርጊታቸውን ዐውቆ ፊት በነሣቸው ጊዜ ወደ ግብጽ ተመልሰው የጣልያን መንግሥት እንዳባረራቸው አድርገው አወሩ። የግብጽ ሕዝብም አምኖአቸው እንደ ቅዱስ ገመታቸው።

ንጉሠ ነገሥቱ ከስደት በተመለሱ ጊዜ አቡነ ቄርሎስም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ነበር። ይሁን እንጂ የእርሳቸውን ድርጊት ያውቁ የነበሩ ሰዎች ሁሉ የጥላቻ ስሜታቸውን ስላሳዩአቸው ወደ ሀገራቸው ተመልሰው እስከሞ ቱበት ቀን ድረስ በኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስነት ማዕረጋቸው ቈዩ።





አቡነ ቄርሎስ የመጨረሻው ግብጻዊ የኢትዮጵያ ጳጳስ።

የአቡነ ቄርሎስ ድርጊት የኢትዮጵያን ሕዝበ ክርስቲያን በጣም ቅር አሰኝቶ ስለነበረ እርሳቸው ከሞቱ በኋላ ዳግመኛ ግብጻዊ ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመጣ ለማድረግ ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጋር ረጅም ውይይት ተደርጎና ስምምነት ተደርሶ ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም በአቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳስነት አምስት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ተሾሙ። ይሁን እንጂ የአቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጵጵስና ተግባራዊ የሆነው ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ ጥቅምት 12 ቀን 1943 ዓ.ም ካረፉ በኋላ ነው። በዚህም መሠረት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ጥር 6 ቀን 1943 ዓ.ም. በካይሮ ከተማ የሊቀ ጵጵስናውን ማዕረግ ከግብጽ ፓትርያርክ ከአቡነ ዮሳብ እጅ ተቀብለዋል። ይህም ሊሆን የቻለው ከግብጾች ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት ከግብጻዊው ሊቀ ጳጳሳት ከአቡነ ቄርሎስ በኋላ ሊቀ ጳጳሳት የሚሆነው ኢትዮጵያዊ እንዲሆን ተወስኖ ስለነበረ ነው።



ጥር 6 ቀን 1843 ዓ.ም. በግብጽ ፓትርያርክ በአቡነ ዮሳብ እጅ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው የተሾሙት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ

www.ethiopianorthodox.org

ሐምሌ 20 ቀን 1940 ዓ.ም. በአቡነ ዮሳብ እጅ ተቀብተው የጵጵስና ማዕረግ የተቀበሉት አምስት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት የሚከተሉት ናቸው።

1. እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ – አቡነ ባስልዮስ ተብለው።
2. ሊቀ ሥልጣናት መልእክቱ – አቡነ ቴዎፍሎስ ተብለው
3. መምህር ገሪማ – አቡነ ሚካኤል ተብለው
4. መምህር ጌታሁን – አቡነ ጢሞቴዎስ ተብለው
5. መምህር ዘፈረ ብርሃን – አቡነ ያዕቆብ ተብለው

ጳጳሳትን ለመሾም ሥልጣን ያለው አንድ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳሳት ሲሾም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው አባት ነበሩ።

ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው እነዚያን ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ቀብተው የሾሙ አባ ዮሳብ የተባሉት የእስክንድርያ መንበር ፓትርያርክ ነበሩ። ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳሳትና ጳጳሳትን በመሾማቸው ለብዙ ዘመናት ይዘነው የነበረውን ሥልጣን ለኢትዮጵያውያን አሳለፈው ሰጡብን በማለት ግብጾች አባ ዮሳብን በጣም ጠልተዋቸው በየምክንያቱ ይከስሱአቸው ጀመር። በመጨረሻም መስከረም 12 ቀን 1948 ዓ.ም በተሰበሰበው በግብጾች የጳጳሳት ጉባኤ ውሳኔ መሠረት ከመንበራቸው ተነሥተው ወደ ደብረ ቍስቋም ገዳም ተላኩ። በዚህ ጊዜ ነው ኢትዮጵያ መልእክተኞችዋን ልካ ከፍተኛ ተቃውሞዋን የገለጠችው።



አንድ ሊቀ ጳጳሳት እና አራት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት የሾሙት ግብጻዊ ፓትርያርክ አቡነ ዮሳብ።

በአባ ዮሳብ ከሥልጣን መባረር ኢትዮጵያ የተቃወመችባቸው ዝርዝር ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ. አባ ዮሳብ ለፓትርያርክነት በተመረጡ ጊዜ ኢትዮጵያም በተወካይዋ አማካይነት የምርጫው ተካፋይ ሆና ነበር። በምርጫና በሹመታቸው ላይ ተካፋይ የነበረች እንደመሆንዋ እርስዋ ሳታውቀው ሊሻሩ ባልተገባም ነበር። መብትዋ ስላልተጠበቀላትም ተቃውማለች።



www.ethiopianorthodox.org

2ኛ. የአባ ዮሳብ ፓትርያርክነት ለግብጽ ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያም መሆኑ እስከታመነበት ድረስ ጉዳዩ ለኢትዮጵያ ሳይቀርብና ሐሳብዋ ሳይጠየቅ የሁለቱን አገሮች የጋራ ፓትርያርክ ግብጾች ብቻቸውን ሊሽሩአቸው ባልተገባቸውም ነበር። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ ውሳኔውንና ድርጊቱን ተቃውማለች።

3ኛ. የኢትዮጵያ ጳጳሳት በእስክንድርያው መንበር ሥር የነበሩ እስከሆነ ድረስ የእስክንድርያው መንበር የሲኖዶስ አባሎች መሆናቸው የታመነ ነው። ይሁን እንጂ ፓትርያርክን ከመንበሩ ማስነሣት ለሚያኽል ከፍተኛ ጉዳይ ሳይጠሩ ቀርተዋል። የኢትዮጵያ ጳጳሳትም መብት ስላልተከበረ ኢትዮጵያ ተቃውማለች።

4ኛ. ፓትርያርኩ የተከሰሱበት ጉዳይ በቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት ከፓትርያክነት ማዕረግ የሚያስወርድ አልነበረም።

አንድን ፓትርያርክ ከፓትርያርክነት ማዕረጉ እንዲሻር የሚያደርጉ ሦስት ምክንያቶች ብቻ ሲሆኑ እነርሱም:-

ሀ. በዕብደት ኅሊናውን ከሳተ፥

ለ. የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ከካደና

ሐ. ለሃይማኖት አሳፋሪ የሆነ ተግባር ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ የተያዘ እንደሆነ ናቸው።

አባ ዮሳብ ግን ከእነዚህ ምክንያቶች በአንዱም አልተከሰሱም። በዚህም መሠረት ከመንበራቸው የተባረሩት በሕገ ወጥ መንገድ በመሆኑ ኢትዮጵያ ተቃውማለት።

ግብጾችም እነዚህ የመቃወሚያ ምክንያቶች በቀረቡላቸው ጊዜ መልስ ስላጡ የግል ጉዳያቸው እንደመሆኑ በዚህ ጉዳይ ውስጥ የሌላ አገር ሰዎች ምንም የሚያገባቸው ምክንያት እንደሌለ ለመግለጽ ቃጣቸው። ይህን አባባል በውይይቱ ላይ በግልጥ ባይናገሩትም እንኳ የተለያዩ ጋዜጦቻቸው በዐምዶቻቸው ላይ ሐሳባቸውን ገልጠውላቸዋል።

የጳጳሳትና የመኳንንት አባሎች የሚገኙባቸው የኢትዮጵያ መልእክተኞች ሁለት ጊዜ ወደ ግብጽ ተልከው ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች ጋር ብዙ ውይይት አድርገዋል።

በመጀመሪያ ወደ ግብጽ የተላኩት የኢትዮጲያ መልእክተኞች ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ፥ ብላታ ትርፌ ሹምዬና አቶ አበራ ጀምበሬ ሲሆኑ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅም በአስተርጓሚነት በስብሰባዎቹ ሁሉ ላይ ተገኝቶአል። ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ብዙ ጥረት ቢደረግም እንኳ በግብጾች በኩል በነበረው ሐሳበ ግትርነት ምንም ዐይነት ስምምነት ላይ ሳይደረስ ቀርቶአል። የኢትዮጵያም መልእክተኞች ሦስት ወር ያኽል ማለት ከኅዳር እስከ ጥር ድረስ ቈይተው ያለምንም ውጤት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል።

በመጀመሪያ ጊዜ ወደ ግብጽ መጥተው የነበሩት የኢትዮጵያ መልእክተኞች ንግግር ተቋርጦ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ ፓትርያርኩ አባ ዮሳብ ተባርረው በተቀመጡበት በቍስቋም ገዳም በግንቦት ወር 1948 ዓ.ም የሲኖዶስ ጉባኤ እንዲሰበሰብ ለጳጳሳት ጥሪ አስተላለፉ። በዚህ ስብሰባ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትም ተጠርተው ነበር።

በፓትርያርኩ ጥሪ መሠረት በሲኖዶሱ ስብሰባ ለመገኘት ወደ ግብጽ የሄዱት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ስም ቀጥሎ የተገለጸው ነው።

1. አቡነ ቴዎፍሎስ፥ የሐረር ጳጳስ
2. አቡነ ጢሞቴዎስ፥ የሲዳሞ ጳጳስ
3. አቡነ ፊልጶስ፥ የኢየሩሳሌም ጳጳስ
4. አቡነ ያዕቆብ፥ የወለጋ ጳጳስ
5. አቡነ ማርቆስ፥ የጐጃም ጳጳስ
6. አቡነ ሉቃስ፥ የአሩሲ ጳጳስ
7. አቡነ ጎርጎርዮስ የጅማ ጳጳስ

የፓትርያርኩ ደጋፊዎች የነበሩ ግብጻውያን ጳጳሳትና እንዲሁም ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በአንድነት ስለተሰበሰቡ ምልአተ ጉባኤው የተሟላ ሆነ። የተሰበሰቡት ጳጳሳት በስብሰባው ካልተገኙት ጳጳሳት ይበልጥ ብዛት ነበራቸው። በዚህም መሠረት ይህ ጉባኤ ፓትርያርኩ የተባረሩበትን ውሳኔ ሽሮ ወደ መንበራቸው እንዲመለሱ ወሰነ።

በውሳኔውም መሠረት ፓትርያርኩ ወደ መኖሪያቸው ተመልሰው ሊገቡ ሲሉ የፓትርያርኩ መኖሪያ በፖሊስ እየተጠበቀ መሆኑን ስለሰሙ ወደ ኮፕት ሆስፒታል ሄደው በሕክምና እየተረዱ ቈዩ። ከሰኔ 17ቀን 1948 ዓ.ም ጀምሮ በሆስፒታል ቆይተው ኅዳር 4 ቀን 1949 ዓ.ም ዐረፉና አስከሬናቸው በፓትርያርክነት ክብር ተቀበረ።

ይህ ጉባኤ ሊሰበሰብ በዝግጅት ላይ በነበረበት ጊዜ የሲኖዶስ ጸሐፊ የነበሩት አባ ቶማስና የጊዛ ሀገረ ስብከት ጳጳስ የነበሩት አባ ዮሐንስ የተጠራው ጉባኤ ውጤት የተሳካ እንዳይሆን ለማድረግ ብዙ መሯሯጥ ጀመሩ። በዚህም የተቃዋሚነት ተግባራቸው በእስክንድርያ የሚገኙ ጳጳሳትን ለማሳደም ባቡር ተሳፍረው በሚሄዱበት ጊዜ ባቡሩ ተገልብጦ ሌላ ማንም ሰው ምንም ጉዳት ሳይደርስበት እነርሱ ሁለቱ ብቻ በባቡሩ መገልበጥ ምክንያት ሞቱ። ይህም ሁናቴ በብዙዎቻችን ዘንድ የእግዚአብሔር ተአምር እንደሆነ ታምኖበታል።

ከፓትርያርኩ ከአባ ዮሳብ ዕረፍት በኋላ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ መሠረት ከፍተኛ የኢትዮጵያ መልእክተኞች ወደ ግብጽ ተላኩ።

እነዚህም መልእክተኞች:-

ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ

ብፁዕ አቡነ ሉቃስ



ልዑል ራስ ዓሥራተ ካሣ

ደጃዝማች መኰንን ደስታ

ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ሲሆኑ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅም በአስተርጓሚነት በስብሰባዎቹ ሁሉ ተገኝቶአል።





በውይይት ላይ የኢትዮጵያና የግብጽን የውይይት አባላት የሚያሳይ ሁለት ፎግራፍ።

ይህ ለሁለተኛ ጊዜ የተካሄደው ንግግር የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን መብት በማስከበር ረገድ ወሳኝ ነበር።

የኢትዮጵያ መልእክተኞች ያቀረቡት የመደራደሪያ ሐሳብ:-

«እኛ የራሳችን ፓትርያርክ እንደሆኑ ቈጥረን አብረን የመረጥናቸውን ፓትርያርክ እኛ ሳናውቀው ሕጋዊ ባልሆነ ዘዴና መንገድ በምታባርሩአቸው ጊዜ የእኛን መብት ለመጠበቅ ፍላጎት እንደሌላችሁ አመልክታችኋል። ይህም በመሆኑ እኛም የራሳችንን ፓትርያርክ መርጠን መሾም አለብን እንጂ በዚህ ሁናቴ ከእናንተ ጋር መቀጠል አንችልም» የሚል ነበር።

ይህ የመደራደሪያ ሐሳብ ግብጾችን አስደንግጦአቸው የኢትዮጵያን መልእክተኞች እንዲህ በማለት ለማግባባት ሞከሩ:- እስከ ዛሬ ባለው አሠራር መሠረት የኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያን በእስክንድርያ መንበር ሥር ትቆይ እንጂ ለምን ከማርቆስ መንበር ትለያለች? ብለው ጠየቁ።



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ጉዳይ የኢትዮጵያውያን መልስ «እንግዲያውስ ይህን ካላችሁ በፓትርያርክነቱ መንበር ላይ የመቀመጡ መብት ዘር ለይቶ ሳይሆን በመንበሩ ሥር ለሚገኙ ወገኖች ሁሉ የመመረጥ ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል፤ ኢትዮጵያም በእስክንድርያ መንበር ሥር እስከሆነች ድረስ የመመረጥ ዕድሉ ሊነፈጋት አይገባም» የሚል ነው። ግብጾች ይህን አማራጭ ሐሳብ በጣም ተቃወሙት።

ስለዚህ ከብዙ ውይይትና ድርድር በኋላ ኢትዮጵያ የራስዋ ፓትርያርክ እንዲኖራት ወደ ስምምነት ተደርሶ ሰኔ 20 ቀን 1951 ዓ.ም. ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው በእስክንድርያው ፓትርያርክ በአቡነ ቄርሎስ ስድስተኛ ተሾሙ።



ሰኔ 20 ቀን 1951 ዓ.ም. አቡነ ባስልዮስን በፓትርያርክነት ማዕረግ የሾሙ የግብጽ ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስ 6ተኛ



አቡነ ባስልዮስ በፓትርያርክነታቸው

ኢትዮጵያ ጉዳዩን በመግባባት መስመር ለማስያዝ ብላ ከግብጾች ጋር ብዙ ውይይቶችን አደረገች እንጂ ሁለት አማራጭ መንገዶች ነበሩአት። የመጀመሪያው አማራጭ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ ከዐሥር የሚበልጡ ጳጳሳት ስለነበሩ



www.ethiopianorthodox.org

አት በቀኖናው መሠረት ፓትርያርክ ለመሾም ትችል ነበር። ያም አይሆንም ከተባለ እንደ ሶርያና አርመን ባሉ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያን አማካይነት ለመሾም በተቻለ ነበር። ግብጾችም ቢሆኑ በመጨረሻ ላይ ሊስማሙ የበቁት እነዚህን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባታቸው እንደሆነ ይገመታል።

ከዚያ በኋላ ሁለተኛው ፓትርያርክ ሲሾሙ ወደ ግብጽ መሄድ ሳያስፈልግ ሹመቱ በኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ብቻ ተፈጽሞአል።



ለሁለተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የፓትርያርክነት ዘውድ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ሲጭኑላቸው።

ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው ይሠየሙ እንጂ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን በኩል የሥልጣን ተዋረድን በተመለከተ በየጊዜው ቅሬታ ይሰማ ነበር። በእኛ በኩል የነበረው አስተሳሰብ ከፓትርያርክ ሹመት በኋላ የሥልጣን ተዋረድ የቀረ መሆኑ ነው።

ለቅሬታው መነሻ የሆነው ምክንያት በስምምነቱ ጊዜ በተጽዕኖ ገብቶ የነበረው ጉዳይ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን ግን ስላላመነችበት ለተጽዕኖው አልተገዛችም። ሁላችንም እንዳመንንበት አንድ ፓትርያርክ ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም የሌላ ፓትርያርክ ፈቃድ አያስፈልገውም።

በነበረውም አለመግባባት ምክንያት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ችግር በደረሰባት ጊዜ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የችግርዋ ተካፋይ ከመሆን ይልቅ ደስ የማያሰኝና ከእኅት ቤተ ክርስቲያን የማይጠበቅ አቋም ወሰደች።

አሁን ግን የሰላም አምላክ ይመስገንና የኢትዮጵያና የግብጽ አብያተ ክርስቲያን የተስማሙበት የሰላም ስምምነት ከዚህ ቀጥሎ ቀርቦአል።

# በኮፕት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና (ኮኦቤ) በኢት ዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን (ኢኦተቤ) መካከል የተደረገ ፕሮቶኮል

## መግቢያ

ሁለቱም አብያተ ክርስቲያን የሐዋርያው የቅዱስ ማርቆስ ልጆች እንደመ ሆናቸው የክርስትና እምነት ከተመሠረተበት ከመጀመሪያው ምዕት ዓመት አንሥቶ በመካከላቸው በጣም የተቀራረበ ግንኙት መሥርተው ቈይተዋል። ይህ ግንኙነት ሊመሠረት የበቃው በሁለቱ የኢትዮጵያ ክርስቲያን ነገሥታት፥ በአብርሐና በአጽብሐ ጥያቄ ኻያኛው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ (ፓፓ) ሐዋርያው ቅዱስ አትናቴዎስ በ329 ዓ.ም. ፍሬምናጦስን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ እንዲሆን ቀብቶ በሾመው ጊዜ ነው። ፍሬምናጦስም አባ ሰላማ ተብሎ በመሰየም በ330 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ ማገልገል ጀመረ። ቅዱስ ተብሎም ይከበራል።

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን፥ አባ ሰላማን ቀብቶ በማጳጳስ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ጵጵስናን መሠረተች። መንበረ ጵጵስናውም የሐዋር ያው ቅዱስ ማርቆስ ሀገረ ስብከት አካል ሆነ። የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ቀብታ እየሾመች ወደ ኢትዮጵያው መንበረ ጵጵስና ስትልክ ቈየች። የኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያን ባቀረበችው ጥያቄ መሠረት፥ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሱን ከመላክ በተጨማሪ ለኢትዮጵያ አህጉረ ስብከት በርካታ ጳጳሳትን እየቀባች መሾም ጀመረች።

ከኢኦተቤ በቀረበው ጥያቄ መሠረትና የቤተ ክርስቲያኒቱንም ዕድገት በመገንዘብ፥ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በ1951 ዓ.ም. ብፁዕ አቡነ ባስልዮስን የመጀመሪያው የኢኦተቤ የበላይ ኃላፊ (ፓትርያርክ) አድርጋ ቀብታ ሾመች።

ከአራተኛው እስከ ኻያኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላለው ጊዜ የእስክ ንድርያ ቤተ ክርስቲያን የኢኦተቤ እናት ቤተ ክርስቲያን ተደርጋ ትቆጠር ነበር። ከአራተኛው ምዕተ ዓመት እስከ 1959 ዓ.ም. ድረስ የቅዱስ ማርቆስ መንበር ወራሽ ሆነው የተሾሙት ፓትርያርኮች የኢኦተቤ መንፈሳዊ አባቶች ሆነው ቈይተዋል።

ሁለቱ አብያተ ክርስቲያን በመካከላቸው ያለው ግንኙነት በመልካም ሁኔታ እንዲጠበቅ፥ እንዲከበርና የተቀራረበ ግንኙትም ይፈጠር ዘንድ በማሰብ፥ በመካከላቸው ያለውን ችግር ለመፍታትና በሁለቱ መካከል አሁንም ሆነ ወደፊት ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ለመመካከር እንዲቻል የጋራ ኮሚቴ ለማቋቋም ተስማምተዋል።



ብዙ ስብሰባና የሐሳብ ልውውጥ ከተረገ በኋላ፥ በየካቲት ወር 1986 ዓ.ም. ይህ የጋራ ኮሚቴ በአዲስ አበባ–ኢትዮጵያ ተሰብስቦ የፕሮቶኮል ሐሳብ አቀረበ። የዚህም ፕሮቶኮል አንድ አንቀጽ በመጨረሻ ከተሻሻለ በኋላ በመጋ ቢት ወር 1986 ዓ.ም. በሁለቱ አብያተ ክርስቲያን ሲኖዶሶች ጸድቋል።

የጋራው ኮሚቴ ዘጠኝ አባላት የሚከተሉት ነበሩ:-

የኮፕት ልዑካን

1. ብፁዕ ሜትሮፖሊታን ቢሾይ
2. ብፁዕ ጳጳስ እንጦንስ ማርቆስ
3. ብፁዕ ጳጳስ ሙሳ
4. ብፁዕ ጳጳስ ሰራፒዮን

የኢትዮጵያ ልዑካን

1. ብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አቡነ መቃርዮስ
2. ብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ናትናኤል
3. ብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ገብርኤል
4. ብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጢሞቴዎስ
5. ብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ገሪማ

### አንቀጽ 1

የኢኦተቤን የሥልጣን ተዋረድ ለማወቅና በዚህም ፕሮቶኮል መንፈስ፥ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የኢኦተቤ ነጻ ሆና በራስዋ እንደምትተዳደር ታውቃለች።

### አንቀጽ 2

በቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት፥ ሁለቱም አብያተ ክርስቲያን በሚቀበሏቸው የአብያተ ክርስቲያን የቀኖና ጉባኤ ውሳኔዎች መንፈስ፥ በሁለቱ አብያተ ክርስቲያን መካከል ፀንቶ በቆየው ታሪካዊ ግንኙት አንፃርና የኢኦተቤንንም ነጻ አሠራርና አስተዳደር በማያሳንስ መንፈስ የእስክንድርያው ፓፓ የሐዋርያው የቅዱስ ማርቆስ መንበር ወራሽ እንደመሆናቸው ቅድሚያ የክብር ቦታ ይሰጣቸዋ ል።

### አንቀጽ 3

ሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት የቅዱስ ማርቆስ መንበር አባል ከመሆና ቸውም በላይ አንድ ዐይነት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቀኖናን የሚቀበሉ፥ የሚያስተምሩና እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ነጻ አስተዳደርና አሠራር አላቸው።



www.ethiopianorthodox.org

አንቀጽ 4

በሁለቱ አብያተ ክርስቲያን መካከል ያለውን መንፈሳዊ ግንኙት ለመግለጽና ለማጠናከር የእስክንድርያው ቅዱስ ፓፓና የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ስም በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ በሚከተለው አኳኋን ይነሣል:-

1. የሁለቱ አብያተ ክርስቲያን መሪዎች ሲገናኙ፥

2. ከሁለቱ አብያተ ክርስቲያን የአንደኛው መሪ ቅዳሴ በሚቀድስበት ወቅት፥

3. የአንደኛው ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ወይም ቄስ በሌላው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚቀድስበት ጊዜ ወይም ሁለቱ አብያተ ክርስቲያን በጋራ በሚቀድሱበት ወቅት፥

4. እንደ ፋሲካ፥ የጌታችን ልደት፥ ጥምቀት፥ መስቀልና የመሳሰሉ ዓበይት በዓላት በሚከበሩበት ወቅት፥

በነዚህ ሁኔታዎች የእስክንድርያው ፓፓ ስም በቅድሚያ ይነሣል።

አንቀጽ 5

እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የየራሱን ጉዳይ የሚወስን የራሱ ቅዱስ ሲኖዶስ አለው። በየጊዜው የቅዱስ ሲኖዶሶቹ ውሳኔዎች ልውውጥ ይደረጋል።

አንቀጽ 6

የሁለቱን አብያተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ የኦርቶዶክስ እምነትና ትውፊት አንድነት ለማረጋገጥ እንዲቻል በየሦስት ዓመቱና አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ የሁለቱ አብያተ ክርስቲያን ጠቅላላ ቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ይካሄዳል። የስብሰባው ቦታ በእስክንድርያ ይጀመርና በአዲስ አበባና በእስክንድርያ በየተራ ይደረጋል።

አንቀጽ 7

እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የራሱን ፓትርያርክ ለመምረጥ መብት አለው፤ ምርጫ የማያካሂደው ቤተ ክርስቲያን ምርጫ ወደሚያካሂደው 5 አባላት ያሉትና ድምፅ መስጠት የሚችል የልዑካን ቡድን ይልካል።

አንቀጽ 8

ከሁለቱ ለአንደኛው ቤተ ክርስቲያን ወደፊት ፓትርያርክ በሚሾምበት ጊዜ፥ አንደኛው ቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ እንዲሳተፍ የሚጋብዝ የልዑካን ቡድን ይላካል፤ የተሳታፊው ባሕርይ በወቅቱ ይወሰናል።

አንቀጽ 9

ሁለቱም አብያተ ክርስቲያን ትላልቅ በዓላት በሚያከብሩበት ጊዜ አንደኛው ወገን ለመሳተፍ ወይም ለመመልከት እንዲችል ይገባበዛሉ።



አንቀጽ 10

አንደኛው ቤተ ክርስቲያን የሌላ እምነት ተከታይ ከሆኑ ተቋማት ጋር እምነትን በተመለከተ ይፋ ውይይት በሚያደርግበት ጊዜ ሌላኛው ቤተ ክርስቲያን ቢያንስ አንድ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል በመላክ በውይይቱ ተሳታፊ እንዲሆን ጥሪ ያደርጋል።

ሁለቱም አብያተ ክርስቲያን እምነትን በተመለከተ ዓለም ዐቀፍ ጉዳዮች ላይ ምክክር ያደርጋሉ።

አንቀጽ 11

ሁለቱም አብያተ ክርስቲያን የየራሳቸውን ፓትርያርክ ወይም ጳጳስ በሕይወት ዘመኑ ከሥልጣኑ ማውረድ ወይም መለወጥ የሚችሉት በየራሳቸው ቅዱስ ሲኖዶስ ሥርዓትና ቀኖና በተከተለ መንገድ ሲወሰን ብቻ መሆኑን ተስማምተዋል።

አንቀጽ 12

ይህ ስምምነት በሥራ ላይ መዋሉን ለመከታተል ሁለቱም አብያተ ክርስቲያን በተለያዩ መስኮች የሚያርጉትን ትብብር ለማጎልመስ የሚረዳ ከሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት ሲኖዶሶች የተውጣጡ አንድ ቋሚ የጋራ ኰሚቴ ይቋቋሟል። የትብብር መስኮቹ የሚከተሉት ይሆናሉ።

1. የጉብኝት ልውውጥ:- የፓትርያርኮች፥ የሊቃነ ጳጳሳት፥ የቀሳውስት፥ የመነኰሳት፥ የፕሮፌሰሮች፥ የተማሪዎችና የዲያቆናት ልውውጥ

2. ትምህርተ ሃይማኖት

3. ክርስቲያናዊ ትምህርት:- የሰንበት ትምህርት ቤቶች፥ የወጣትና የቤተ ሰብ ፕሮግራሞች

4. ማኅበራዊ አገልግሎት:- የልማት ፕሮጀክቶች

5. የአበነፍስ አገልግሎት:- የሁለቱም አብያተ ክርስቲያን ተከታዮች ባሉበት የአበነፍስ አገልግሎት ለማግኘት እንዲችሉ አንደኛው ቤተ ክርስቲያን ለሌላው ዕድል ይሰጣል።

አንቀጽ 13

ይህ ፕሮቶኮል በሁለቱም አብያተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶሶች ጸድቆ በሁለቱም አብያተ ክርስቲያን ፓትርያርኮች ተፈርሞ ሥራ ላይ እንደዋለ፥ ከዚህ በፊት በሁለቱም አብያተ ክርስቲያን መካከል የነበሩ ስምምነቶች እና ወይም ፕሮቶኮሎች ዋጋ እንደሌላቸው ተቈጥረው ውድቅ ይሆናሉ።

አንቀጽ 14

ይህ የፕሮቶኮል ስምምነት በሁለቱም አብያተ ክርስቲያን ሲኖዶሶች ጸድቆ በሁለቱም አብያተ ክርስቲያን ፓትርያርኮች ተፈርሞ ሥራ ላይ ሲውል

www.ethiopianorthodox.org

አንቀጽ 15

ይህ የፕሮቶኮል ስምምነት በአማርኛ፥ በአረብኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ተዘጋጅቷል። የአተረጓጎም ችግር ከተከሠተ የእንግሊዝኛ ቅጂው የጸና ይሆናል።

ይህ ከዚህ በላይ የተመለከተው ዐሥራ አምስት አንቀጾች ያሉት ፕሮቶ ኮል፥ መግቢያውን ጨምሮ አምስት ገጽ ያለው ሲሆን የዚህ ፕሮቶኮል ስምምነት አንቀጽ 14 በደነገገው መሠረት በሁለቱም አብያተ ክርስቲያን ፓትርያርኮች በሚያዝያ ወር 1986 ዓ.ም. ተፈርሟል።

( የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓለም መድረክ ገጽ 8–10 መስከረም 16 ቀን 1988 ዓ.ም)

## የቤተ ክርስቲያን ዜማ

የቤተ ክርስቲያን ዜማ የሚባሉት ልዩ ልዩ ዐይነት እግዚአብሔርን የመለመኛና የማመስገኛ ዜማዎች ናቸው። ከእነርሱም መካከል የሰዓታት ጸሎት፥ የነግህ ጸሎት፥ የሠርክ ጸሎት፥ የቅኔ ማኅሌቱ ስብሐተ እግዚአ ብሔርና የቀዳሴ ጸሎት ይገኙባቸዋል። አሁን ግን በዚህ መጽሐፍና በተከታ ታዮቹ መጻሕፍት የሚቀርበው ሕዝብ ተሳትፎ ሊያደርግበት የሚገባው የቅዳ ሴው ጸሎት ነው።

<u>የቅዳሴ ተሰጥዎ</u>:- በቅዳሴው ጸሎት ውስጥ የካህኑ የዲያቆኑና የሕዝቡ ድርሻ የሆኑ ዜማዎች አሉ። የቅዳሴ ተሰጥዎ የሚባለው የሕዝብ ድርሻ የሆነው ዜማ ነው። በዚህም መሠረት ሁሉም ሰው አጥንቶት ተገቢውን ተሳትፎ ያደርግ ዘንድ የሕዝብ ድርሻ የሆነው ክፍል በዚህ ተከታታይ በሆነ መጽሐፍ ውስጥ በተከታታይ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ድረስ ቀርቦአል።

<u>በግዕዝ</u>

ዝ: ውእቱ: ጊዜ: ባርኮት ወዝ ውእቱ: ጊዜ ዕጣን ኅሩይ።

ጊዜ: ሰብሐቱ: ለመድኃኒነ: መፍቀሬ: ሰብእ: ክርስቶስ፤

ዕጣን ይእቲ ማርያም ዕጣን ውእቱ፤

እስመ: ዘውስተ ከርሣ: ዘይትሜዐዝ: እምኵሉ ዕጣን:

ዘወለደቶ መጽአ ወአድኀነነ

ዕፍረት ምዑዝ ኢየሱስ ክርስቶስ:

ንዑ: ንስግድ ሎቱ።

ወንዕቀብ: ትእዛዛቲሁ ከመ ይሥረይ ለነ: ኃጣውኢነ

ተውህቦ: ምሕረት: ለሚካኤል፤ ወብሥራት ለገብርኤል ወሀብተ ሰማያት ለማርያም ድንግል፥

ተውህቦ ልቡና ለዳዊት ወጥበብ ለሰሎሞን ወቀርነ ቅብዕ_ለሳሙኤል እስመ ውእቱ ዘይቀብዕ ነገሥተ። ተውህቦ መራኁት ለአቡነ ጴጥሮስ።

ወድንግልና ለዮሐንስ፤ ወመልእክት ለአቡነ ጳውሎስ፥

እስመ ውእቱ ብርሃና ለቤተ ክርስቲያን።

ዕፍረት ምዕዝት ይእቲ ማርያም፤ እስመ ዘውስተ ከርሣ ዘይትሌዐል እምኵሉ ዕጣን መጽአ ወተሠገወ እምኔሃ።

ለማርያም ድንግል ንጽሕት ሠምራ አብ፥

ወአሠርገዋ ደብተራ ለማኅደረ ፍቁር ወልዱ።

ተውህቦ ሕግ ለሙሴ ወክህነት ለአሮን፥

ተውህቦ ዕጣን ኅሩይ ለዘካርያስ ካህን

ደብተራ ስምዕ ገብርዋ፥ በከመ ነገረ እግዚእ ወአሮን ካህን በማእከላ የዐርግ ዕጣነ ኅሩየ።

ሱራፌል ይሰግዱ ሎቱ፤ ወኪሩቤል ይሴብሕዎ፤ ይጸርሑ እንዘ ይብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር በኀበ አእላፍ ወክቡር በውስተ ረበዋት

አንተ ውእቱ ዕጣን ኦ መድኃኒነ።

እስመ መጻእከ ወአድኀንከነ ተሣሃለነ።

<u>በአማርኛ</u>

የማመስገን ጊዜ ይህ ነው

የተመረጠ: የዕጣን: ጊዜም ይህ: ነው:

ሰው ወዳጅ መድኃኒታችንን ክርስቶስን ማመስገኛ ጊዜ ዕጣን የተባለች ማርያም ናት ዕጣን የተባለ እሱ ነው።

በማኅፀንዋ ያደረ ከተመረጠው ዕጣን ሁሉ የሚበልጥ ነውና የወለደችው መጥቶ አዳነን፤ ኢየሱስ ክርስቶስ መዓዛ ያለው ሽቱ ነው።

ኑ: እንስገድለት

ትእዛዞቹንም እንጠብቅ፥ ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ።

ለሚካኤል ምሕረት ተሰጠው፤ ለገብርኤል ብሥራት ተሰጠው፤ ለድንግል ማርያምም ሰማያዊ ሀብት ተሰጣት፤

ለዳዊት ልቡና፥ ለሰሎሞን ጥበብ፥ ለሳሙኤል ነገሥታትን የቀባ እርሱ ነውና የሽቱ ቀንድ ተሰጠው፤



www.ethiopianorthodox.org

ለዮሐንስ ድንግልና ተሰጠው፤ መልእክትም መጻፍ ለአባታችን ለጳውሎስ ተሰጠው፤ የቤተ ክርስቲያን ብርሃንዋ እርሱ ነውና።

መዓዛ ያላት ሽቱ ማርያም ናት።

በማኅፀንዋ ያለው ከዕጣን ሁሉ የሚበልጥ ነውና መጥቶ ከርስዋ ሰው ሆነ።

ንጽሕት ድንግል ማርያምን አብ ወደዳት።

ለተወደደ ልጁ ማደሪያ ልትሆን በንጽሕና አስጌጣት

ለሙሴ ሕግ ለአሮን ክህነት ተሰጠው፤ ለካህኑ ለዘካርያስም የተመረጠ ዕጣን ተሰጠው፤ የምስክር ድንኳን አደረጉአት፤ ጌታ እንደ ተናገረ፥

ካህኑ አሮንም በመካከሏ የተመ ረጠውን ዕጣን ያሳርጋል።

ሱራፌል ይሰግዱለታል። ኪሩቤልም ያመሰግኑታል፤

እግዚአብሔር በብዙ መላእክት ዘንድ ንጹሕ ክቡር ልዩ ነው፤ በአለቆችም ዘንድ ክቡር ነው እያሉ ይጮኻሉ።

መድኃኒታችን ሆይ ዕጣን አንተ ነህ።

መጥተህ አድነኸናልና ይቅር በለን።

## ከዚህ ምዕራፍ የሚገኝ ትምህርት

ቤተ ክርስቲያን አንዲት፥ ቅድስት ዓለም ዐቀፋዊትና ሐዋርያዊት ነች የሚለውን ስያሜ ዓለም ዐቀፋዊዎቹ ሲኖዶሶች የቅዱሳት መጻሕፍትን አባባል መሠረት በማድረግ ወስነውታል። ይህ አባባል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያገኘ ለመሆኑ የሲኖዶሶቹ ቅዱስነትና የቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ያረጋግጣሉ። ነገር ግን ከቀድሞ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተነሠቱ አሳዛኝ ፈተናዎች የቤተ ክርስቲያንን አንድነት፥ ቅድስና፥ ዓለም ሀፋዊነትና ሐዋርያዊነት ተፈታትነውታል እየተፈታተኑትም ነው።

አንድነትን የተፈታተኑት በቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ልዩነት ላይ ነው። ለአብያተ ክርስቲያን ሁሉ ማዕከላዊ የሆነ ትርጓሜ ከሌለ ይህ ልዩነት አሁንም እየቀጠለ ይሄዳል። የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለመመለስ የግድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ማዕከላዊነት አስፈላጊ ነው። ለዚህም ማዕከላዊነት የቀድሞዎቹ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶች መሠረት የጣሉ በመሆናቸው አስፈላጊው ነገር የሃይማኖት ሊቃውንት ተገናኝተው መወያየትና መስማማት ብቻ ነው። ዋናው ትልቁ ነገር ግን እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ይመልስ ዘንድ ዘወትር መጸለይ ነው።

የዮሐንስን ወንጌል ምዕራፍ 17 በምንመለከትበት ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለተከታዮቹ አንድነተ ሲጸልይ እናገኘዋለን። ይህም የሚያመለ ክተው የእግዚአብሔር ፈቃድ የቤተ ክርስቲያን አንድነት እንጂ የቤተ ክርስቲያን መለያየት አለመሆኑን ነው። ታዲያ በየጥቃቅኑ ምክንያት የእግዚአ ብሔርን ፈቃድ ጥሶ መለያየትን ምን አመጣው?



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር እኔ ቅዱስ ስለሆንሁ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ባለው መሠረት የቤተ ክርስቲያንን ቅድስና ለመጠበቅ እያንዳንዳችን የቅድስናን ኑሮ መኖር ያስፈልገናል። ቤተ ክርስቲያንም ማለት ክርስቲያን ምእመናን ማለት እንደ መሆኑ የእያንዳንዳችን ቅድስና ማለት የቤተ ክርስቲያን ቅድስና ማለት ነው።

ቤተ ክርስቲያን ዓለም ዐቀፋዊት እንደመሆንዋ ክርስትናን የአንድ አገር ወይም የአንድ ወገን ሃይማኖት አድርጎ መገመት ስሕተት ነው።

ቤተ ክርስቲያንን ከሐዋርያት ትምህርት ልንለያት አንችልም። ቤተ ክርስቲያንን በክርስቶስ ራስነት ላይ የመሠረቱአት ሐዋርያት ናቸው።

ከቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ታሪክ ብዙ መማር እንችላለን። ለምሳሌ ቅዱስ ያዕቆብን የያዘው ወታደር የሐዋርያውን ድፍረትና ለዚህ ዓለም መከራ አለመጨነቅ ባየ ጊዜ የእርሱ ሁናቴ ስቦት ይቅርታ ለመጠየቅ ተገደደ። ሰውን ወደ ቀናው መንገድ ለመመለስ መንፈሳዊ ሕይወታችን ከአንደበታችን ጋር እኩል ቃለ እግዚአብሔርን ማዳረስ ይችላል፤ የሰውንም ሕይወት ይለውጣል። በዚህም መሠረት ነው ያ ወታደር ሕይወቱን በአንድ ጊዜ ለውጦ ለሰማዕትነት ክብር የበቃው።

ሰው ራሱን ለእግዚአብሔር ካስገዛ ሥጋዊ ተፈጥሮው በመንፈሳዊ ሰውነቱ ሊሸነፍ ይችላል። ለምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ጊዜ ስለባለጸጋ ሰው ሲናገር ባለጸጋ ወደመንግሥተ ሰማያት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል ብሎ ነበር። ይህንንም ያለው ባለጸጋ ሰው ለመንግሥተ ሰማይ ብሎ ሀብቱን ማጣት የማይፈቅድ መሆኑን ለማመልከት ነው። ራሱን ለእግ ዚአብሔር ያስገዛው ቅዱስ እንጦንስ ግን ከቤተሰቡ የወረሰውን ሀብት ሁሉ ለድኾችና ለችግረኞች ካከፋፈለ በኋላ ራሱን ለአምልኮተ እግዚአብሔር ለመለየት ይህችን ዓለም ትቶ ወደ ምድረ በዳ ሄደ። ራሱንም ለእግዚአብሔር በማስገዛቱ ታላላቅ የሰይጣን ፈተናዎችን ድል ለመንሣት አስችሎታል። ለእግዚአብሔር መንግሥትና ለከፍተኛው ሰማያዊ ጸጋ ለመብቃት የአሚ ሚቱን መንገድ እያማረጠ ነበር። በሰማዕትነት መሞትን ፈልጎ ሕይወቱን በአደጋ ላይ ጥሎ ነበር። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ፈቃድ ያ ስላልነበረ በአረማውያን ገዢዎች እጅ አልወደቀም። አሚሚቱም በሰማዕትነት አልነ በረም።

በሞተ ጊዜ ሥጋውን እንዲደብቁ ማዘዙና ለንጉሥ ቈስጠንጢኖስ ደብዳቤ ትኵረት አለመስጠቱ የዚህን ዓለም ክብር ሁሉ ይንቅ ስለነበረ ነው።

### ጥያቄዎች

1. አራቱ የቤተ ክርስቲያን ቅጽል ስሞች የሚገኙት በምን ውስጥ ነው?
2. የተወሰነውስ በየትኞቹ ጉባኤዎች ነው?
3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጸለየው ስለምን ነው?

4. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸሎት ያስፈልገው ኖሯልን? ካላስፈለገው ታዲያ ለምን ጸለየ?

5. የጸለየውስ ምን ብሎ ነው?

6. ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ጠቃሚ ነው ተብሎ የቀረበው ሐሳብ ምን እንዲደረግ ነው?

7. ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ተብላ የምትጠራባቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?

8. በዚህ ክፍል ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ስንል ምን ማለታችን ነው?

9. ቤተ ክርስቲያን ዓለም ዐቀፋዊት ነች ስንል ምን ማለታችን ነው?

10. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያንን ዓለም ዐቀፋዊነት የገለጠው ምን ብሎ ነው?

11. ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት ነች የምንለው በምን በምን ምክንያቶች ነው?

13. ይህን አባባል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያረጋገጠው ምን በማለት ነው?

14. በዚህ ክፍል ታሪኩ የቀረበው የትኛው ያዕቆብ እንደሆነ ግለጥ

15. ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ያስተማረባቸው አገሮች ማንና ማን ነበሩ?

16. እርሱ የተከሰሰው ምን ብሎ በማስተማሩ ነው?

17. እርሱን የያዘው ወታደር ምን አደረገ? ያንንስ ያደረገው በምን ምክንያት ነው?

18. ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብና ወታደሩ ምን ደረሰባቸው?

19. ሐዋርያው ቅዱስ ስምዖን ቀናኢ የተባለው ለምንድነው?

20. እርሱስ ምን ዐይነት ሰው ነበር?

21. ፊልጶስ ለናትናኤል ምን ብሎ ነገረው?

22. ናትናኤልስ ምን መልስ ሰጠው?

23. ጌታችን ናትናኤልን ሲያየው ምን አለ?

24. ናትናኤልስ ምን መልስ ሰጠው?

25. የእግዚአብሔር ልጅነቱን ያመነው ምን ስላለው ነው?

26. ጌታችን በሰጠው መልስ ላይ ስለ ናትናኤል የሚነገሩ ሁለት ታሪኮች ምንና ምን ናቸው?

27. ሐዋርያው ቅዱስ ስምዖን ያስተማረባቸው አገሮች የት የት ናቸው?

28. ብዙ ችግር የደረሰበት በምን ምክንያት ነው?

29. ሰማዕትነትን የተቀዳጀው በምን ዐይነት ነው?

30. ቅዱስ እንጦንስ የየት አገር ሰው ነበር?

31. ወላጆቹ ምን ዐይነት ሰዎች ነበሩ?

32. እኅቱን መንከባከብ የነበረበት ለምንድነው?

33. ሐሳቡ ወደ ፍጹም መንፈሳዊነት የተለወጠው ምንን በመስማቱ ነው?



34. ከዚያ በኋላስ ምንን ወሰነ?

35. ስለ እኅቱስ ምን አደረገ?

36. በቅዱስ እንጦንስ ላይ ምን ፈተና ደረሰበት?

37. ሰይጣን ቅዱስ እንጦንስን ተመቅኝቶ ምን አደረገው?

38. በአራዊቱ ላይ ምን ብሎ አላገጠባቸው?

39. የሰማዕትነትን አክሊል ለመቀዳጀት ፈልጎ ምን አደረገ?

40. አገረ ገገርው ምን ትእዛዝ አስተላለፈ?

41. በኋላስ ምን አደረገ?

42. ራቅ ብሎ ወደ በረሓ የሄደው ለምንድነው?

43. ለመኖሪያ የመረጠው ቦታ ምን ዐይነት ነበር?

44. ዳቦ የሚያመጣለት ምን ነበር?

45. ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ ለቅዱስ እንጦንስ ምን ዐይነት ደብዳቤ ጻፈለት?

46. ቅዱስ እንጦንስ ቅዱስ ጳውሊ በምን ከፈነው?

48. ቅዱስ እንጦንስ ከመሞቱ በፊት ልጆቹን ምን አዘዛቸው?

## ምዕራፍ 5

## መንፈሳዊነትና ግብረ ገብነት

### ወደ ኃጢአት ከሚገፋፉ ሁኔታዎች መጠበቅ

ሰዎች ክፉ ሁናቴዎችን ከማየታቸው፥ ክፉ ሁናቴዎችን ከመስማታቸው፥ ክፉ መጻሕፍትን ከማንበባቸው፥ ክፉ ሥራ በሚሠራበት ቦታ ከመገኘታቸውና ከክፉ አድራጊዎች ጋር ከመተባበራቸው የተነሣ ከኃጢአት ጋር ይገናኛሉ፤ ኃጢአት መሥራትን ይለማመዳሉ፤ ኃጢአተኞችም ይሆናሉ።

ሰይጣን ሁላችንንም የእርሱ ተባባሪዎች ለማድረግ ክፉ ሁናቴዎችን መልካም አድርጎ ያቀርብልናል። ሥጋዊ ተፈጥሮአችንም ደካማ ስለሆነ በቀላሉ ለክፉ ነገር ይሸነፋል። ይሁን እንጂ በጾምና በጸሎት የአምላካችንን እርዳታ ከለመንን ሰይጣንን ድል ለመንሣት አምላካችን ኃይሉን ይሰጠናል። በዚህም ዐይነት ሰይጣን የሚመጣበትን መንገድ ለመዝጋት መጣር አለብን።

<u>ክፉ ሁናቴን ማየት</u>:- ክፉ ነገር ወይም ክፉ ሁናቴ ስንል በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ድርጊት ማለታችን ነው። እንደእነዚህ ያሉ ክፉ ትርኢቶች ለምሳሌ በሲኒማ ቤት፥ በቲአትር ቤት፥ በዳንኪራ ጭፈራ ቤት፥ በምሽት የመዝናኛ ክበቦች፥ በቪዲዮም አማካይነት ሊታዩ ይችላሉ። በእርግጥ በሲኔማ፥ በቲአትር ቤቶችና፥ በቪዲዮ አማካይነት የሚታዩት ትርኢቶች ሁሉ ክፉ ትርኢቶች ናቸው ማለት አይደለም። ተምህርታዊ ትርኢቶችም በእነርሱ አማካይነት ሊታዩ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ክፉውንና ደጉን መለየት የሁላችንም ፈንታ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ክፉ ትርኢቶች በኅሊናችን ውስጥ የፍርሀት፥ የክፉ ሐሳብ፥ ወይም የክፉ ምኞት ትውስታን ያሳድሩብናል። ጠላት ዲያብሎስም እነዚህን ትውስታዎች ለክፉ ዐላማውና ምኞቱ መጠቀሚያ ያደርጋቸዋል። ጉዳዩን እንኳ የማናውቀው ብንሆን ሰይጣን ክፉ ነገር የማወቅ ፍላጎትን ያሳድርብናል።

ለምሳሌ አዳምና ሔዋን የደግና የክፉ ነገር ልዩነቶችን አያውቁ በነበረበት ጊዜ እናንተ ይህን ፍሬ ብትበሉ እንደ እግዚአብሔር ዐዋቂዎች ትሆናላችሁ ብሎ እባብ ስላግባባቸው ያን ፍሬ የመብላት ፍላጎት አድሮባቸው በሉ። ሰይጣንም ፍሬውን እንዲበሉ ያደረገበት ዋናው ዘዴ ያ ፍሬ የሚያስደስትና የሚያጓጓ ሆኖ ለሔዋን እንዲታያት በማድረግ ነው።

ብዙ ወንጀለኞች፥ ቀማኞችና ሌቦች ክፉ ድርጊቶችን የሚያደርጉት በሲኔማ ቤት በፊልም ያዩትን በተግባር ላይ በማዋል ነው። ስለዚህ ክፉ ትርኢትን ከሚያሳየው ፊልምና ቪዲዮ ራሳችንን ብንገታ፥ ፈንጠዝያ ከሚደረግበት፥ ዳንኪራ ከሚመታበት፥ መዝናኛ ነው ከሚባለው የማታ ክበብ ራሳችንን ብናርቅ ለሰይጣን ክፉ መንገድን ከመክፈት መቈጠባችን ይሆናል። በእርግጥ በፊልምና በቪዲዮ መንፈሳዊ ትምህርትን ማስተላለፍ ይቻላል። ነገር ግን ደጉን ከክፉው ለይቶ የመጠቀም ኀላፊነት አለብን።

<u>ክፉ ነገርን መስማት</u>:- አንድን ነገር የሚያሰማ ሰው የማግባባት ዘዴ ካለው ሰሚው ሰው የበለጠ ለማወቅ ይጓጓል፤ የሰማው ስለአንዳች ድርጊትም ከሆነ ያን ድርጊት አድርጎ የመሞከር ፍላጎት ያድርበታል።

ለምሳሌ እባብ ሔዋንን «ሞትን አትሞቱም ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ዐዋቂዎች ትሆናላችሁ» ባላት ጊዜ ቃሉን አምና ፍሬውን በላች፤ ለአዳምም ሰጥታው በላ። ስለዚህ ክፉ ነገርን አለመስማት ነው እንጂ ከሰሙና ክፉነቱን አስቀድሞ ባለማወቅ ካልተጠነቀቁበት ወደአልታሰበ ክፉ ችግር ሊያደርስ ይችላል።

ክፉውን ነገር እንደ መልካም ነገር አድርጎ የሚያቀርብ ዘመድ፥ ወዳጅ፥ ጓደኛ ወይም ሌላ የቅርብ ሰው ሲኖር እርሱን አምኖ የመቀበል ዝንባሌ ይኖራል። የመቀበሉም ዝንባሌ የሚመጣው አንድም የነገሩን ክፉነት ካለማወቅ የተነሣ ነው፤ ወይም ክፉነቱንም እያወቁ እስቲ እንዴት እንደሆነ ልሞክረው ከሚል አስተሳሰብ ነው። ለምሳሌ ሲጃራ የሚያጤስ ሰው ካለ የሲጃራ ማጤስ ችግር ተመላልሶ ቢነገርም እን እስቲ ልሞክረው በሚል ፈሊጥ ይጀመርና ወደ ሱሰኝነት ደረጃ የደረሳል። ሲጃራ ማጤሱንም አንዳንድ ሰዎች የወንድነት ምልክት፥ ሌሎች ደግሞ የጭንቀትና የብስጭት ማስታገሻ ነው ብለው ስለሚያወሩ የዋሁ ሰሚ በንግግራቸው ይታለልና ወደ ችግሩ ጥልቅ ብሎ ይገባል። እንደዚህ ያሉት አሳሳች ወሬዎች በሚወሩበት ጊዜ ነገሩን ሰምቶ ላወራው ሰው ስሕተተኛነቱን በማስረዳት ለማሳመን ከሆነ መልካም ይሆናል፤ ነገር ግን ክፉ ነገር ተናጋሪው ሰው ክፉ ነገር የሚናገር መሆኑን እያወቁ እርሱን አሳምኖ ለመመለስ ሳይሆን በእርሱ ተሸንፎ ወደ ክፉ ለመነዳት ከሆነ አለማዳመጡ ይመረጣል።



ክፉን ነገር የሚያዳምጠው ሰው ለተናጋሪው ሐሳብ ርእስ ሊያደርገው አስቦ ከሆነ መልካም ነው። ለምሳሌ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊ ክብር የሚክድ ሰው ይህን ክሕደቱን በትምህርት መልክ በሚያቀርብበት ጊዜ ለእርሱ መልስ ለመስጠት የሚችል ሰው ካልሆነ በቀር አለማዳመጡ ይመረጣል። የሃይማኖታችን መሠረቱና መመኪያችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ያን እምነት ማቃወስ ማለት ያለንን ሁሉ ማፍረስ መሆኑን ማወቅ ይገባል።

የክፉ ድርጊቶችንና የውጤታቸውን ታሪክ ሰምቶ ለመሞከር ማሰብ በደል ነው: ክፉ ነገር እስከሆነ ድረስ ክፉ ነውና ሙከራም አያስፈልገውም። ክፉ ሠሪዎችም የእግዚአብሔርና የሰው ጠላቶች ናቸው። ታዲያ፥ ክፉ በመሥራት የእግዚአብሔርም የሰውም ጠላቶች ከሆንን መድረሻችን ወዴት ነው? ድርጊቶች እግዚአብሔር የማይፈቅዳቸው ክፉ መሆናቸው እስከታወቀ ድረስ ለምን ስለ እነርሱ መስማት እንፈልጋለን? ለምንስ እንሸነፍላቸዋለን? ለምሳሌ ኅሊናን የሚያስቱ ሱስ አምጪ ነገሮችን የለመደ ሰው ሌላ ሰው እንደርሱው ሱሰኛ እንዲሆን ለማግባባት ሲሞክር ለምን እናዳምጠዋልን? ለምንስ ሙከራ የማድረግ ፍላጎት ያድርብናል? ሰው እኮ ከሌሎች ከባለ ደመ ነፍስ እንስሳት የሚበልጠውና የሚሻለው ደግን ከክፉው የመለየትና የማመዛዘን ችሎታ ስላለው ነው። ይህ ችሎታ ግን ክፉውን ጥሎ ደጉን ለመያዝ ካልሆነ ጥቅሙ ምንድነው? በዚህም መሠረት ከሃይማኖት የምናገኛቸውን በጎ ትምህርቶች ዘወትር በማዳመጥና በማንበብ በደግ መንገድ መመራት እንጂ ክፉ ወሬን፥ ክፉ ምክርንና ክፉ ታሪክን ለማዳመጥ ጆሮአችንን አንፍቀድለት።

<u>ክፉ መጻሕፍትን ከማንበብ መቈጠብ</u>:- እግዚአብሔርን ለማስካድ የሚጥሩ፥ ከኅብረተሰቡ ባህል ጋር የማይስማሙና ብልግናን የሚሰብኩ፥ እንዲሁም የኅብረተሰቡን መልካም ባህል በማጥላላት የሰውን መልካም አኗኗር የሚያናጉ ጽሑፎች በየጊዜው ብቅ ብቅ ይላሉ። ተፈጥሮአችንም በቀላሉ ለክፉ ነገር ተሸናፊ መሆኑን ስለሚያውቁ ለደካማው ሰውነታችን በሚያጓጓ መልክ ያቀርቡታል። እንደዚህ ያሉትም ክፉ ጽሑፎች በሰው ጠላት በሰይጣን ረዳትነትና አቀነባባሪነት የሚቀርቡ ናቸው። ታዲያ፥ እንደእነዚህ ያሉትን መጻሕፍት በማንበብ ለምን ለጠላታችን ለሰይጣን መንገድ እንከፍትለታለን? ለምንስ አሸናፊ እናደርገዋለን? እርሱ ሁልጊዜ እንደ መርዘኛ እባብና እንደ ነጣቂ ተኵላ አድፍጦ ይጠብቀናል። በመንገዱ ካልሄድንለት ግን አያገኘንም።

መጻሕፍትን የማንበብ ፍላጎት ካለን ለትምህርትነት የሚያገለግሉ ብዙ መጻሕፍት አሉ። ትምህርት ሊሰጡ በሚችሉ በእነዚያ መጻሕፍት ላይ ማተኰር ሲቻል ለምን እግዚአብሔር በማይፈቅዳቸው፥ ለራሳችንም ሆነ ለኅብረተሰቡ በማይጠቅሙ፥ እንዲያውም በሚጐዱ መጻሕፍት ላይ ጊዜአችንን እናጠፋለን? ዕድሜአችን ውሱን እንደመሆኑ በዚህ በተወሰነው ዕድሜአችን መልካም ትምህርት የሚሰጡትን መጻሕፍት አሰባስበን ለማንበብ ብንፈልግ እንኳ ሁሉን ማዳረስ አንችልም። ታዲያ የሚቻለንን ያኽል እነዚያን



www.ethiopianorthodox.org

በጎ መጻሕፍት ማንበብ ይመስል እንጂ ያን ውስጥ የሆን ውድ ጊዜ ክፉ መጻሕፍትን በማንበብ እናባክነዋለን?

ክፉዎቹን መጻሕፍት በማንበብ የምናተርፈው ክፉ ሐሳብ፥ ጭንቀት፥ ፍርሀት፥ ድንጋጤ፥ ጥርጣሬ፥ የእምነት መናጋት፥ ሰላም ማጣትን የመሳሰሉ የጎሊና ዕረፍት መታጣት ናቸው። ደጋጎቹን መጻሕፍት ስናነብ ግን ትምህርት፥ የአስተሳሰብ ሰላም፥ የጎሊና ዕረፍት እምነትና በጎ አስተሳሰብ፥ እንዲሁም ለሰው ሁሉ ፍቅርና የመርዳት ፍላጎት ይኖረናል። ይህም የሚያመለክተው በጎ መጻሕፍትን በምናነብበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የመፈጸም ፍላጎትና ክፉ መጻሕፍት በምናነብበት ጊዜ ደግሞ የጠላት ዲያብሎስን ፈቃድ የመፈጸም ፍላጎት ያድርብናል ማለት ነው። ምርጫችንም ትምህርት ሰጪና እግዚ አብሔር የሚፈቅደውን በጎ መጽሐፍ አንብቦ ለዘለዓለም ሕይወት መዘጋጀትና በእግዚአብሔርም ሆነ በኅብረተሰቡ ዘንድ ተወዳጅነት የሌላቸውን ክፉ መጻሕ ፍት አንብቦ ለዘለዓለም ጥፋት መዘጋጀት ነው። ክፉንና ደግን ለይቶ የሚያው ቅና ትክክለኛ አስተሳሰብ ያለው ሰው ምን መምረጥ እንደሚገባው ያውቃል። በዚህ ጉዳይ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እንመልከት:-

የእስራኤል ልጆች በአምልኮ ረገድ ወላዋዮች ሆነው ባገኛቸው ጊዜ ኢያሱ ወልደ ነዌ እንዲህ ብሎአቸዋል:-

«እግዚአብሔርን አምልኩ፤ እግዚአብሔርን ማምለክ መልካም መስሎ ካልታያችሁ የቀድሞ አባቶቻችሁ ከኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኩአቸ ውን አማልክት ወይም በምድራቸው የምትኖሩባቸውን የአሞራውያንን አማል ክት ታመልኩ እንደሆነ የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ። እኔና ቤተሰቤ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን» (ኢያ:ም24ቍ:14–15)። እንዲሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሏል:-

«ሰው የዓለምን ሀብት ሁሉ ቢያገኝ ነፍሱን ግን ቢያጠፋ ምን ይጠቅመዋል» (ሉቃ:ም:9ቍ:25)።

በዚህም መሠረት የአምልኮተ እግዚአብሔር ክሕደትን ከሚሰብክ፥ በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃልን ከሚናገር፥ በመሠረታዊ እምነት ላይ የጥርጣሬ ስሜት ከሚያመጣ፥ የኅብረተሰቡን ባህላዊ ጨዋነት ከሚያናጋ፥ ብልግናንና ስድነትን ከሚጋብዝ ክፉ መጽሐፍ ራስን መጠበቅና እንደዚያ ያለውን መጽሐፍ አለማንበብ የመንፈሳዊነትና የግብረገብነትን አኗኗር ጠብቆ በመኖር ላይ እንቅፋትን ማስወገድ ነው። አንብቦ በመቃወም በመጽሐፉ የተሰናከሉትን ለመርዳት ከሆነ ግን አስመስጋኝ ይሆናል።

<u>ከክፉ አሉባልታ ወሬ ራስን መግታት:-</u> ቀደም ተብሎ ክፉ ነገር መስማት በሚል ርእስ ሥር የቀረበው ትምህርት በዚህ ርእስ ሥር ከቀረበው ሐሳብ ይለያል። ይኸኛው ተራ የአሉባልታ ወሬ ነው።

ወሬ ሲባልም ሁለት ክፍሎች አሉት። አንዱ ክፍል አውሪነት ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ሰሚነት ነው። የሚያወራውም ሰው ስለሌላ ሰው ክፉ



ተግባር አየሁ ወይም ሰማሁ ብሎ በሚናገርበት ሰው ላይ ሳያውቅና ሳይሰማ በሌለበት ይናገራል። ወሬውም እውነት ወይም ውሸት ሊሆን ይችላል፤ ወይም ትንሽ የእውነት መነሻ ኖሮት ተጋንኖ የተወራ ወሬ ሊሆን ይችላል። በዚህም ሆነ ባዚያ እንደዚህ ያለው ሰው ሆን ብሎ ሰውን ለመበደል ሳይሆን ልማድ ሆኖበት ሊሆን ይችላል። እንደዚህ ያለው ሰው በአንድ ጊዜ ሁለት ኃጢአት ይሠራል። አንዱ ኃጢአት ሐሜት ሲሆን ሁለተኛው ኃጢአት ደግሞ ውሸት ነው።

አንድ ሰው የፈጸመውን ወይም ያልፈጸመውን በደል በማንሣት ከእርሱ ተደብቆ ከሌላ ሰው ጋር ማውራት እግዚአብሔር የማይፈቅደው ከመሆኑም በላይ ሰሚውን፥ ሌላውን ኅብረተሰብና የተነገረበትን ሰው መበደል ነው። ሰሚውና ኅብረተሰቡ የሚበደሉት ቀደም ብለው በሚያምኑት ሰው ላይ እምነት እንዲያጡና ጠቃሚ ሊሆን የሚችለውን ሰው እንዳይጠቀሙበት ስለሚ ያደርግ፥ የተነገረበት ሰው ደግሞ እንደ ክፉ አድራጊ እንዲታይና እምነት እንዳይጣልበት በመደረጉ ይበደላል።

ከእንደዚህ ያለው የሐሜትና የሐሰት ወሬ ኃጢአት ለመከላከል የሚቻለው ሐሜትን ከመናገርና የሐሜተኛን ወሬ ከመስማት በመቈጠብ ነው።

ሐሜትን ቅዱሳት መጻሕፍት መላልሰው አውግዘውታል። ይህንኑም:- በመዝ:50ቍ:20፥101 ቍ:5፥1፥1ኛ ጴጥ: ም:2 ቍ:1 ይመለከቷል።

ከዚህም በላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰይጣን ምንነት ሲናገር እንዲህ ብሎአል:-

«እውነት በእርሱ ስለሌለ ከእውነት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፤ እርሱ ሐሰተኛና የሐሰት አባት ስለሆነ ሐሰትን በሚናገርበት ጊዜ ከገዛ ራሱ አውጥቶ ይናገራል» (ዮሐ:ም8ቍ:44)።

እዚህ ላይ እንደተገለጠው ሰይጣን የሐሰት አባት መሆኑን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አረጋግጦአል። ይህ ከሆነ ታዲያ፡ ሐሰትን መናገር የሰይጣን ሥራ መሆኑ ነው። ሐሰትም የሚናገር ሰው በሰይጣን እየተመራ ስለሚናገር የሰይጣን መሣሪያ ላለመሆን ከውሸት ራስን መግታት ያስፈልጋል።

በመጨረሻም ለማጠቃለል በዋናው ርእስና በንዑሳን ርእሶቹ በዝርዝር እንደተገለጠው ወደ ኃጢአት የሚገፋፉ ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም ለጊዜው በዝርዝር የተገለጡት የክፉ ድርጊት ምንጮች:- ክፉ ነገር ሲደረግ ማየት፥ ስለክፉ ድርጊት መስማት፥ ክፉ ድርጊትን የሚሰብኩ መጻሕፍትን ማንበብና ክፉ አሉባልታን መስማት ወይም ማስተጋባት ናቸው።

ከእነዚህም የኃጢአት መመንጫዎች ለመዳን የምንችለው በመጀመሪያ ደረጃ በጾምና በጸሎት ከዚያም በእግዚአብሔር እርዳታ ክፉ ነገር ከማየት፥ ክፉ ነገር ከመስማት፥ ክፉ መጻሕፍትን ከማንበብና ከሐሜት በመራቅ ነው። ይህን ለማድረግ እንችል ዘንድ ዘወትር በጸሎት እንትጋ።



www.ethiopianorthodox.org

## ሰጪ ከተቀባይ ይልቅ የተመሰገነ ነው

አንድ ጊዜ አንድ ሀብታም ሰው ወደ ጌታችን ዘንድ ቀርቦ የዘለዓለምን ሕይወት አገኝ ዘንድ ምን ላድርግ ብሎ ጠየቀው። ጌታችንም:- «ሕግጋቱን ታውቅ የለምን? እነርሱን ፈጽም» አለው። ሰውየው ግን «ሕግጋቱንማ ከልጅነቴ ጀምሬ ፈጽሜአለሁ፤ ሌላስ ምን የሚጐድለኝ አለ?» ብሎ ጠየቀው። በዚህ ጊዜ ጌታችን ፍጹም ለመሆን ብትፈልግ ሂድና ያለህን ሀብት ሁሉ ሸጠህ ለድኾች ስጥ፤ መጥተህም ተከተለኝ» አለው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ አባባሉ መስጠት ማለት ለድኻ መመጽወት ወደ ፍጹምነት እንደሚያደርስ አመልክቶአል። ይህንኑ አባባል ጌታችን ስለመጨረሻው ፍርድ ቀን ባደረገው ገለጻ ላይ በበለጠ አብራርቶታል። እዚያ ላይ ኃጢአተኞች ከሚወቀሱባቸው ምክንያቶች መካከል:- «ብራብ አላበላችሁኝም፤ ብጠማ አላጠጣችሁኝም፤ ብታረዝ አላለበሳችሁኝም» ተብለው ሲሆን ጻድቃን ከተመሰገኑባቸው ምክንያቶች መካከል ደግሞ «ብራብ አብልታችሁኛል፤ ብጠማ አጠጥታችሁኛል፤ ብታረዝ አልብሳችሁኛል» ተብለው ነው። አባባሉንም ሲያብራራ ለድኾችና ለችግረኞች ያደረጉት ወይም ያላደረጉት ለእርሱ እንዳደረጉት ወይም እንዳላደረጉት መሆኑን ገልጾላቸዋል። ስለዚህ በዚያን ጊዜ ከሚወቀሱባቸው ጉዳዮች ለምን አልሰጣችሁም ተብለው እንጂ ለምን አልተቀበላችሁም ተብለው አይደለም (ማቴ:ም:9:16–22፥ም:25)።

በቅዱሳት መጻሕፍት በተለያዩ ቦታዎች ደጋግ ሰዎች ከሚመሰገኑባቸው ምክንያቶች መካከል ለድኾችና ለችግረኞች መርዳት ዋነኛው ነው። ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ ም:10 ላይ ቆርኔሌዎስ ከተመሰገነባቸው ምክንያቶች አንዱ ምክንያት ምጽዋት ይሰጥ የነበረ መሆኑ ነው። ምጽዋትም መስጠት ለእግዚአብሔር እንደመስጠት የሚቈጠር መሆኑን ጌታችን ራሱ ገልጦታል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ራሱ ሠርቶ በሚያገኘው ገንዘብ በመኖር ከማንም ላይ ምንም ገንዘብ ለመውሰድ እንደማይፈልግ ገልጦአል። ለዚህም ድርጊቱ የሰጠው ምክንያት «ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው» የሚለውን የጌታችንን አባባል ነው (የሐ:ሥ:ም:20ቍ:35)።

ምናልባት አንዳንድ ሰዎች ያለኝ ገንዘብ ከእኔ መቼ ተረፈና ነው ለሌላ ሰው ለመስጠት የምችለው ይሉ ይሆናል። ከማንም ሰው ቢሆን እንዲሰጥ የሚጠበቀው እንደየዐቅሙ ነው እንጂ ከዐቅሙ በላይ አይደለም። ለምሳሌ ጌታችን በቤተ መቅደስ ስጦታ የሚሰጡ ሰዎችን በተመለከተበት ጊዜ ብዙ ሰዎች የገንዘብ ስጦታ ሲሰጡ አየ። ከእነርሱ መካከል ጌታችን ያመሰገነው አንዲት ሳንቲም የሰጠችውን መበለት ነው። ከዚያ ካላት ትንሽ ገንዘብ ላይ ከሁሉ ያነሰ ብትሰጥም ተመሰገነች።

ከማንም ሰው ላይ የሚጠበቀው እንደየችሎታው ስለሆነ ገንዘብ ስለሌለኝ ምኑን እሰጠዋለሁ ብሎ ማሰብ አስፈላጊ አይደለም።እንዲያውም ጌታችን የሰጠው ተስፋ:- «ስጡ፤ ለእናንተም ይሰጣችኋል፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ



ታምቆና ተጠቅጥቆ እስኪትረፈረፍ ድረስ ተሰፍሮ ይሰጣችኋል» የሚል ነው (ሉቃ:ም:6ቍ:38)።

ስለ ስጦታ የሚከተሉትን የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች እንመልከት:-

«በቤቴ ሲሳይ ይበዛ ዘንድ ዐሥራቱን በሙሉ ወደ ጐተራ አግቡ፤ እናንተ ይህን ብታደርጉ እኔ ደግሞ የሰማይን መስኮቶች ከፍቼ በረከትን አትረፍርፌ ባልሰጣችሁ በዚህ ፈትኑኝ ይላል ጌታ እግዚአብሔር» (ሚል:ም:3ቍ:10)።

«ለስጦታዎችህ ሁሉ የፈገግታ ገጽታ አክልባቸው የዐሥራት ግዴታህንም ደስ ብሎህ ክፈል፤ አስቀድሞ ለሰጠህ ለልዑል እግዚአብሔር ዐቅምህ በሚችለው መጠን በልግሥና ስጥ፤ ጌታም መልካም ውለታ ከፋይ ስለሆነ ሰባት ጊዜ አስበልጦ ይከፍልሃል» (ሢራክ:ም:35ቍ:9–11)።

«እግዚአብሔር የሚወድደው በደስታ የሚሰጠውን ሰው ስለሆነ እያንዳንዱ ሰው ለመስጠት የፈለገውን በልቡ ፈቅዶ በደስታ ይስጥ እንጂ እያመነታ ወይም በግዴታ አይስጥ» (2ኛ:ቆሮ:ም:9ቍ:7)።

በዚህም መሠረት እያንዳንዳችን ትንሽ ነው ወይም ብዙ ነው ሳንል በመስጠት ከስጦታ የሚገኘውን በረከት እንታደል።

## ደግና ክፉ ነገሮች በድምፅ ብልጫ የሚወሰኑ አይደሉም

ብዙ ሰዎች የሚወዱት ነገር ሁሉ ደግ ነገር፥ ብዙ ሰዎች የሚጠሉት ነገር ሁሉ ክፉ ነገር ነው ማለት አይደለም። የደግና የክፉ ነገሮች መመዘኛዎች መንፈሳዊነትና ግብረ ገብነት ናቸው። መንፈሳዊነት ሃይማኖተኛነት ሲሆን ግብረገብነት ደግሞ ከባህል ጋር የተያያዘ ነው።

ለምሳሌ የኖኅ ጊዜ ሰዎችንና የሰዶምና የገሞራ ሰዎችን ታሪክ ብንመለከት አብዛኛዎቹ ሰዎች ከሃይማኖታዊና ከግብረ ገባዊ ተግባር የራቁ ነበሩ። ስለዚህ በዚያን ጊዜ የነበሩ ሰዎች ወድደውና ፈልገው የሚያደርጉአቸው ድርጊቶች ደግ ነገሮች ነበሩ ማለት አይደለም። በሌላ በኩል ደግሞ ኖኅ ብቻ ያደርገው የነበረው ድርጊት በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም። እንዲሁም በሰዶም ከተማ የነበረው ሎጥ ያደርገው የነበረው ድርጊትና የነበረው እምነት በሰዶም ከተማ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም። ሆኖም የኖኅና የሎጥ ተግባርና እምነት ክፉ ነበሩ ማለት አይደለም።

ሌላው ምሳሌ ደግሞ የሰማዕታት ዘመን ነው። በዚያን ዘመን አብዛኛው የዓለም ሕዝብ ጣዖትን አምላኪና የክርስትና ጠላት ነበር። ጣዖት አምላኪዎቹም ክርስትናን መጥላት ብቻ ሳይሆን ክርስቲያኖች ሃይማኖታቸውን ክደው ጣዖትን እንዲያመልኩ ለማስገደድ ያሠቃዩአቸውና ይገድሉአቸው ነበር። አምላካቸውን ከመካድ ይልቅ ሞትን የመረጡት ክርስቲያኖች በሰማዕትነት ሞተው ሰማዕታት ተብለዋል። ታዲያ፥ ክርስቲያኖቹ እንደ ጣዖት አምላኪዎቹ ብዙዎች ስላልነበሩ የፈጸሙት ተግባርና የነበራቸው እምነት ክፉ ነበርን?



www.ethiopianorthodox.org

## ጥያቄዎች

1. ወደ ኃጢአት የሚገፋፉ ሁናቴዎች ናቸው ተብለው የቀረቡ አራት አርእስት ማን ማን ናቸው?
2. ሁላችንንም የእርሱ ተባባሪዎች ለማድረግ ሰይጣን ምን ያደርጋል?
3.ሰይጣንን ድል ለመንሣት የምንችለው እንዴት ነው?
4. ክፉ ሁናቴዎችን ከምናይባቸው ቦታዎች መካከል ቢያንስ ሁለቱን ጥቀስ።
5.ከእነርሱ መካከል ትምህርታዊ ትርኢቶችን ልናይባቸው የምንችል ምን ምን ናቸው?
6. ክፉ ትርኢቶች በኅሊናችን ውስጥ ምን ዐይነት ትውስታን ያሳድሩብናል?
7. ሰይጣን እነዚህን ትውስታዎች ምን ያደርጋቸዋል?
8. ሰይጣን ሔዋንን ያግባባት እንደምን አድርጎ ነው?
9. ብዙ ወንጀለኞች በተግባር ላይ የሚያውሉት ምኑን ነው?
10. አንድ ክፉ ነገርን የሚሰማ ሰው ምን ዐይነት ፍላጎት ያድርበታል?
11. የማንን ክፉ ንግግር ነው የመቀበል ዝንባሌ የሚኖረው?
12. አንድን ነገር አለማዳመጥ የሚመረጠው ምን ሲሆን ነው?
13. ክፉ መጻሕፍት የሚባሉት ምን ዐይነቶቹ ናቸው?
14. ክፉዎችን መጻሕፍት ስናነብብ ምን ያጋጥመናል?
15. ደጋጎቹን መጻሕፍት ስናነብብስ ምን እናገኛለን?
16. የወሬ ሁለት ክፍሎች ምንና ምን ናቸው?
17. ወሬ የሚያወራ ሰው በሚያወራበት ሰው ላይ የሚያደርሰው በደል ምንድነው?
18. በኅብረተሰቡ ላይስ ምን በደል ያደርሳል?
19. ጌታችን ከተቀባይ ሰጪ የሚበልጥ መሆኑን የገለጠው ምን ብሎ ነው?
20. ድኾችን በመርዳቱ የተመሰገነ የአንድ ሰው ስም አስታውስ።
21. ደግና ክፉ ነገሮች በድምፅ ብልጫ አይወሰኑም የተባለው ምን ለማለት ተፈልጎ ነው?



# ስድስተኛ ክፍል

## ምዕራፍ 1

## ትምህርተ ሃይማኖት

### የእግዚአብሔር ሕጎች

የእግዚአብሔር ሕግ ሲባል የእግዚአብሔር ትእዛዝ፥ ዐዋጅ፥ ወይም ድንጋጌ ማለት ነው፤ እርሱም አድርግ ወይም አታድርግ በሚል ትእዛዝ ላይ የተመሠረተ ነው።

ይህም ሕግ የተጀመረው እግዚአብሔር አዳምን ባዘዘው ትእዛዝ ነው።

«እግዚአብሔር አምላክ ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው:- በአትክልቱ ቦታ ከሚገኙት ዛፎች ሁሉ ፍሬ ልትበላ ትችላለህ፤ ነገር ግን ከእርሱ በበላህበት ቀን በእርግጥ ስለምትሞት ደጉን ከክፉ ለመለየት የሚያስችል ዕውቀት ከሚሰጠው ዛፍ ፍሬ አትብላ» (ዘፍ:ም:2ቁ:16–17)።

ከዚያ በኋላ ሕገ እግዚአብሔር በጽሑፍ መቅረብ እስከጀመረበት ዘመን ድረስ ሕግጋትና የአምልኮ ሥርዓቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ በትውፊት አማካይነት ሲተላለፉ ቈይተዋል። ይህንንም የምንረዳው እንደ አቤል፥ ሔኖክ፥ ኖኅና አብርሃምን በመሳሰሉ የእግዚአብሔር ወዳጆች ምሳሌነት ነው።

አቤል መሥዋዕት የመሠዋትን ሥርዓት ከምን ተማረ? ሔኖክ መንገዱን ከእግዚአብሔር ጋር የማድረግን ዘዴ በምን ዐወቀ? አብርሃምስ መሥዋዕት የማቅረብን ሥርዓት እንዴት ዐወቀ? ለኖኅስ የመሥዋዕትን ሥርዓት ያስተማረው ማነው?

እነዚህና ሌሎችም ሁሉ የአምልኮተ እግዚአብሔርን ሥርዓቶችና የእግዚአብሔርን ሕግጋት ያወቁት በትውፊት አማካይነት ነው።

<u>የሕግ ዓላማ:-</u> ሕግ የሚደነገገው በአጠቃላይ የሰውን ልጆች ሰብአዊ መብት ለማስከበር ነው። ይህ አባባል የሚያመለክተው ስለዓለማዊው ሕግ ነው። ስለሕገ እግዚአብሔር ስንነጋገር ኀይለኛው በጕልበቱ ተመክቶ ደካማውን እንዳያጠቃው የሰብአዊ መብትን ማስከበር ከዓላማዎቹ አንዱ ቢሆንም የብዙዎቹን ሕጎች፥ ትእዛዞች፥ ድንጋጌዎችና የአምልኮ ሥርዓቶች ምክንያቶች ወይም ዓላማ የሚያውቃቸው እግዚአብሔር ብቻ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

## ሕጉን በማክበርና ሕጉን ባለማክበር የሚመጡ ውጤቶች

<u>ሕጉን ያከበርን እንደሆነ ምን ጥቅም እናገኛለን:-</u> የእግዚአብሔርን ትእዛዞች ብናከብር እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግልን የሚገልጡትን ጥቅሶች ቀጥለን እንመልከት

«በጥሞና ቃሌን ብታዳምጡና በፊቴ መልካም የሆነውን ነገር በታዛዥነት ብታደርጉ፥ ሕግጋቴንም ሁሉ ብትጠብቁ፥ በግብጻውያን ላይ ካመጣሁባቸው በሽታዎች በአንዱ እንኳ አልቀጣችሁም፤ ፈዋሻችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝ» (ዘጸ:ም:15ቍ:26)።

«ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ብትታዘዝና እኔ ዛሬ የምሰጠህንም ሕግጋት ሁሉ በታማኝነት ብትጠብቅ በምድር ላይ ከሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ (ዘዳ:ም:28ቍ:1)።

«ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ባትታዘዝና እኔ ዛሬ የምሰጥህንም ሕግጋትና ትዛዛት በታማኝነት ባትጠብቅ እነዚህ መርገሞች ሁሉ ይደርሱብሃል» (ዘዳ: ም:28ቍ:15)።

«እግዚአብሔር ሆይ፥ ወደ መኖሪያህ መግባት የሚችል ማነው? በተቀደሰችው ተራራህ በጽዮን ላይ ሊኖር የሚችል ማነው? እርሱ ለእግዚአብሔር የሚታዘዝ፥ መደረግ የሚገባውን ነገር የሚያደርግ፥ እውነትን የሚናገር፥ ሌሎች ሰዎችን የማያማ በሰው ላይ ክፉ ነገርን የማይደርግ፥ በጐረቤቱ ላይ አሉባልታ የማያሠራጭ፥ እግዚአብሔር የጠላቸውን ሰዎች የሚንቅ፥ ለእግዚአብሔር የሚታዘዙትን ግን የሚያከብር፥ ምንም ያኽል ከባድ ቢሆን የገባውን ቃል ኪዳን የሚፈጽም፥ ያለ ወለድ የሚያበድር፥ በንጹሖች ላይ በሐሰት ለመመስከር ጉቦ የማይቀበል፥ እነዚህን ነገሮች የሚያደርግ ሰው፥ ከማናቸውም ክፉ ነገር ተጠብቆ በሰላም ይኖራል እንጂ ከቶ አይናወጥም» (መዝ:15)።

«ወደ እግዚአብሔር ተራራ ማን ይወጣል? በተቀደሰ ስፍራው ማን ይቆማል? ይህን ማድረግ የሚችል እጆቹ ከክፉ ሥራና ልቡ ከክፉ ሐሳብ ንጹሓን የሆኑ፥ ጣዖትን የማያመልክ፥ ዋሽቶ የማይምል ነው። እንዲህ ዐይነቱ ሰው ከአዳኝ አምላኩ ከእግዚአብሔር በረከትንና ፍትሕን ይቀበላል» (መዝ: 24ቍ:3–5)።

«ሰው ጻድቅ፥ፍትሓዊና ትክክለኛ ቢሆን ለእስራኤል ጣዖታት አይሰግዱም ወይም በተከለከለ ቦታ የተሠዋውን ማንኛውንም ነገር አይመገቡም፤ የሌላ ሰው ሚስት አይደፍርም ወይንም ሴትን በወር አበባዋ ጊዜ አይገናኝም ማንንም አይጨቍንም ነገር ግን በመያዣ የያዘውን ይመልሳል፤ አይቀማም፤ ለተራበ ያበላል፤ ለታረዘ ያለብሳል። ገንዘቡን በአራጣ አያበድርም፤ ወይም ከፍተኛ ወለድ አይወስድም፤ ክፉ ነገር ከመሥራት ይቈጠባል፤ ጠበኞችን ለማስታረቅ ትክክለኛ ፍርድን ይሰጣል፤ እንዲህ ዐይነቱ ሰው ትእዛዜን ይፈጽማል ፤



ሕጌንም ያከብራል፤ ያ ሰው ጻድቅ ሆኖ በሕይወት ይኖራል፤ ይህን የተናገርሁ እኔ ጌታ እግዚአብሔር ነኝ» (ሕዝ:ም:18ቍ:5–9)።

«ወደ ሕይወት ለመግባት ብትፈልግ ግን ትእዛዞችን ፈጽም» (ማቴ: ም:19:ቍ17)።

« እውነት እውነት እላችኋለሁ ማንም ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር ፈጽሞ አይሞትም (ዮሐ:ም:8ቍ:51)።

«እናንተ እኔ የማዝዛችሁን ብትፈጽሙ ወዳጆቼ ናችሁ» (ዮሐ:ም 15ቍ:14)

«በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚፈጽም እንጂ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም» (ማቴ:ም:7ቍ:21)።

«እግዚአብሔር ለያንዳንዱ እንደየሥራው ይሰጠዋል» (ሮሜ:ም :2:ቍ 6)።

<u>ሕጉን ባናከብር ምን ይደርስብናል?</u>

«አምላካችሁን እግዚአብሔርን ብትረሱ ሌሎችንም አማልክት ብትከተሉ፥ ብታመልኳቸውም፥ ብትሰግዱላቸውም ፈጽሞ እንደምትጠፉ እኔ ዛሬውኑ አረጋግጥላችኋለሁ» (ዘዳ:ም:8ቍ:19)።

«እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች አሉ፤ እንዲያውም እርሱ የሚጸየፋቸው ሰባት ናቸው፤ እነርሱም ሐሰተኛ ምላስ፥ ንጹሕን ደም የምታፈስስ እጅ፥ ክፉ ሐሳብን የሚያፈልቅ አእምሮ፥ ወደ ክፉ ለመሮጥ የሚቸኵሉ እግሮች፥ በሐሰት የሚናገር ሐሰኛ ምስክር፥ በወዳጆች መካከል ጠብን የሚያነሣሣ ናቸው» (ምሳ:ም6ቍ:16–19)።

ፈሪሳውያን ለጠየቁት ጥያቄ ጌታችን መልስ በሰጠ ጊዜ፥ «ሰውን የሚያረክሱት ከሰው ልብ የሚወጡ ነገሮች ናቸው፤ እነርሱም ክፉ ሐሳብ፥ ዝሙት፥ ስርቆት፥ ሰውን መግደል፥ ምንዝርነት፥ ስግብግብነት፥ ክፋት፥ አታላይነት፥ ስድነት፥ ምቀኝነት፥ ሐሜተኛነት፥ ትዕቢት፥ ግዴለ ሽነት ናቸው» ብሏል (ማር: ም:7 ቍ: 21–22)

« አንተ ንስሓ ባለመግባትህና እልኸኛ በመሆንህ የእግዚአብሔር ቍጣና ትክክለኛ ፍርድ በሚገለጥበት ጊዜ ቅጣትህ እንዲበዛ ታደርጋለህ» (ሮሜ: ም:2ቍ:5)።

«ዐመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ አታውቁምን? በዚህ ነገር አትታለሉ፤ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ፥ ወይም አመንዝሮች፥ ወይም ግብረ ሰዶም የሚፈጽሙ፥ ወይም ሌቦች፥ ወይም ስግብግቦች፥ ወይም ሰካራሞች፥ ወይም የሰው ስም አጥፊዎች፥ ወይም ቀማኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም» (1ኛ: ቆሮ: ም: 6ቍ: 9–10)።

www.ethiopianorthodox.org

ሕግን በማክበር፥ ወይም ባለማክበር ምክንያት ስለሚደርሱ ሁኔታዎች የሚያመለክቱት ጥቅሶች ከላይ የተዘረዘሩት ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ማቅረብ ይቻላል። እነዚህ ግን ለዐይነት ያኽል ብቻ የቀረቡ ናቸው።

__የሕጉ አመሠራረት__:- ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው የእግዚአብሔር ሕግ የተጀመረው ለአዳም በተሰጠው የእግዚአብሔር ትእዛዝ ሆኖ እነዚያ ሁሉ ትእዛዞች በጽሑፍ መቅረብ እስከቻሉበት ዘመን ድረስ ቃለ እግዚአብሔር ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የኖረው በትውፊት አማካይነት ነው።

የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ እየሰማ እግዚአብሔር ከሲና ተራራ ላይ ያስተላለፋቸው ዐሥር ትእዛዞች የሚከተሉት ናቸው:-

1. ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ።
2. ማናቸውንም ምስል ሠርተህ አትስገድለት።
3. የአምላክህን ስም በከንቱ አታንሣ።
4. የሰንበትን ቀን አክብር።
5. አባትህንና እናትህን አክብር።
6. አትግደል
7. አታመንዝር።
8. አትስረቅ።
9. በማንም ሰው ላይ በሐሰት አትመስክር።
10. የሌላ ሰው የሆነውን ማንኛውንም ነገር አትመኝ (ዘጸ:ም:20)

እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት በሰጣቸው የምስክር ጽላቶች ላይ የተጻፉት እነዚህ ዐሥር ትእዛዞች ናቸው። እነርሱም ለመንፈሳዊም ሆነ ለዓለማዊ ሕጎች መሠረት ናቸው።

ትእዛዞቹን ብንፈጽም በምድርም፥ በሰማይም ሰላምንና ዕረፍትን እናገኛለን። ነገር ግን እነዚህን ትእዛዞች ብንተላለፍ ምድራዊም ሰማያዊም ቅጣት ያመጡብናል። በምድር በሕገ ሰብእ፥ በሰማይ በሕገ አምላክ መሠረት እንቀጣለን። ልዩነቱ ግን ምድራዊው ቅጣት ጊዜያዊ ሲሆን ሰማያዊው ቅጣት ዘለዓለማዊ መሆኑ ነው።

እንዲሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግጋትን ፍጹም ሊያደርጋቸው ፈቅዶ በተራራው ላይ ስብከቱ ጊዜ የሚከተሉትን ስድስቱን ቃላቱ ወንጌል ደንግጎአል።

1. አትግደል የሚለውን ትእዛዝ በወንድምህ ላይ በከንቱ አትቈጣ በማለት ፍጹም አድርጎታል።

2. አታመንዝር የሚለውን ሕግ ሴትን ተመልክቶ የተመኛት በልቡ አመንዝሮ በማለት ፍጹም አድርጎታል።

3. ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት ይስጣት የተባለውን ካለዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል ብሎአል።

4. በሐሰት አትማል የሚለውን ትእዛዝ በፍጹም አትማሉ በማለት ፍጹም አድርጎታል።

5. ዐይን ስለ ዐይን፥ ጥርስ ስለ ጥርስ ተብሎ የተደነገገውን ሕግ በቀልን አትበቀሉ በማለት ፍጹም አድርጎታል።

6. ወዳጅህን ውደድ ጠላትህን ጥላ የተባለውን ጠላትህን ውደድ በማለት ፍጹም አድርጎታል።

የእግዚአብሔርን ሕግጋት በትክክል ፈጽመን ብንገኝ በኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 28 ከቍጥር 1 እስከ ቍጥር 14 ድረስ የተዘረዘረው የበረከት ተስፋ ይኖረናል፤ ሕግጋቱን ሳንጠብቅ ብንቀር ደግሞ በዚሁ ከላይ በተገለጠው ምዕራፍ ከቍጥር 15 እስከ ቍጥር 68 ድረስ የተዘረዘረው እርግማን ይደርስብናል።

## __ትውፊት__

የክርስትና ትምህርት ምንጩ ምንድነው? የክርስትና ትምህርት ምንጮች:-

1. መጽሐፍ ቅዱስ፥
2. ትውፊት፥
3. ዲድስቅልያ፥
4. ቅዱሳን አባቶችና ሲኖዶሶቻቸው ናቸው።

በዚህ ትምህርት ውስጥ ግን መግለጫ የሚሰጠው ስለትውፊት ነው።

ትውፊት ማለት ምን ማለት ነው?

ትውፊት ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ የማይገኝ ከአባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ትምህርት ነው። ሆኖም ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር አይቃረንም።

ትውፊትን የማይቀበሉ ወገኖች ከጥንት ተያይዞ የመጣ ትምህርት ባለመቀበላቸው የአባቶችን ትምህርት፥ የቅዱሳን ሲኖዶሶች ውሳኔዎችን፥ የቤተክርስቲያን ቀኖናዎችንና ሥርዓቶችን፥ እንዲሁም መሠረተ እምነትን ችላ ማለታቸው ነው።

የትውፊትን የት መጣና ምክንያታዊነቱን የሚከተሉት ዝርዝር ሁኔታዎች ይመለከቷል።

ትውፊት ከመጀመሪያው የሰው ልጅች አባት ስለሚጀምር መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻፉ በፊት የነበረ ነው። ቃለ እግዚአብሔር በጽሑፍ የተመዘገበው ከክርስቶስ ልደት በፊት በዐሥራ አምስትና በዐሥራ ስድስት መቶ ዓመቶች በሙሴ አማካይነት ሲሆን ሰዎች በጽሑፍ የሰፈረ የሃይማኖት መመሪያ ሳይኖራ

www.ethiopianorthodox.org

ቸው ሃይማኖታዊ ተግባርን እያከናወኑ ለብዙ ሺህ ዓመታት ኖረዋል ማለት ነው። ይህ ከሆነ ታዲያ፥ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመልኩት በምን መመሪያ ነበር? በዚያን ጊዜ ሰዎች እግዚአብሔርን ያመልኩ የነበሩት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድና ሲዋረድ በመጣው በትውፊት አማካይነት ነበር።

ለዚህም አባባል የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

ሀ. አቤል ከበጎቹ መንጋ በመጀመሪያ የተወለደውን አንድ ጠቦት አመጣ፥ ካረደውም በኋላ የሰባውንና መልካም የሆነውን ክፍል ሁሉ መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ (ዘፍ:ም:4ቍ:4)።

ለ. በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 8:ቍጥር: 20 ላይ:-

«ኖኅ ለእግዚአብሔር መሠዊያን ሠራ፤ ለምግብነት ንጹሕ ከሆኑት እንስሳትና አዕዋፍ ሁሉ ከየዐይነቱ አንዳንድ ወሰደ፤ መሥዋዕት እንዲሆኑም ሁሉንም በመሠዊያው ላይ አቃጠላቸው» ሲል የቀድሞዎቹ አባቶች የመሥዋዕትንና የመሠዊያን ሥርዓት እንዴት ሊያውቁ ቻሉ? መሥዋዕቱስ ከንጹሕ እንስሳት መሆን እንደሚገባው እንዴት ሊያውቁ ቻሉ?

እንደሚታወቀው መሥዋዕቶችና የአሠራር ሥርዓቶቻቸው በጽሑፍ ላይ በዝርዝር የቀረቡት ከብዙ ዓመቶች በኋላ በሙሴ ዘመን ነው።

ሐ. በኦሪት ዘፍጥረት ም:14 ቍ:17–20 የልዑል እግዚአብሔር ካህን የነበረው መልከጼዴቅ ከአብርሃም ጋር የመገናኘቱ ታሪክ ይነበባል።

በሙሴ ዘመን በአሮን የተጀመረው የክህነት ማዕረግ እንዴት በአብርሃም ዘመን ሊከሠት ቻለ? በዚሁ በአብርሃምና በመልከ ጼዴቅ መገናኘት ታሪክ ውስጥ አብርሃም ለመልከጼዴቅ ዐሥራት እንዳቀረበለት ተገልጾአል።

መልከጼዴቅ አብርሃምን መባረኩና አብርሃምም ለመልከጼዴቅ ዐሥራት መክፈሉ የክህነት ክብርና የዐሥራት ክፍያ ሥርዓት ሕገ እግዚአብሔር በጽሑፍ ከመቅረቡ በፊት በትውፊት ይሠራበት የነበረ መሆኑን ያመለክታል።

መ. በኦሪት ዘፍጥረት ም:5ቍ:24 ላይ «ሔኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፤ እግዚአብሔር ወስዶታልና» ተብሏል። ከላይ እንደተገለጠው የሃይማኖት መመሪያዎች በጽሑፍ የቀረቡት በኋላ በሙሴ ዘመን ስለሆነ ሔኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር የማድረግን መንገድ እንዴት ተማረ? ሔኖክ የእግዚአብሔርን መንገድ የተማረው በትውፊት አማካይነት መሆኑ ግልጥ ነው።

ሠ. በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 28 ቍ:11–22 ላይ እንደተገለጠው ያዕቆብ ከወንድሙ ከኤሳው ሸሽቶ በሄደ ጊዜ በሕልሙ ከምድር እስከ ሰማይ በሚደርስ መሰላል መላእክት ሲወጡና ሲወረዱበት አይቶአል።

በዚህ ጊዜ ያዕቆብ ምን አደረገ? ያን ራእይ ያየበትን ቦታ ቤቴል ማለት፥ ቤተ እግዚአብሔር ብሎ ሰየመው። ሌሊት ተንተርሶት ተኝቶ የነበረውን ድንጋይ እንደ ሐውልት በማቆም ዘይት አፍስሶበት መታሰቢያ አድርጎታል።



ታዲያ ያዕቆብ የእግዚአብሔር ቤት [illegible]
ለእግዚአብሔር ቤት ሥራብ መሠረት የመጣል ሐሳብ ከወዴት አገኘው? ያዕቆብ ይህን ሐሳብ ያገኘው ከአባቶች ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው ትውፊት ነው።

ረ. እግዚአብሔር ሕግጋቱን፥ ትእዛዙትንና ሥርዓቱን ለሰው ልጆች በጽሑፍ እንዲደርስ ቢያደርግም እንኳ ትውፊቱም እንዲቀጥል እንጂ እንዲቋረጥ አላደረገም። በየጊዜው ወላጆችን ለልጆቻቸው ትምህርትን እንዲያስተላልፉ አዘዞአቸዋል። ለምሳሌ በኦሪት ዘዳግም ም:4ቍ : 9 ላይ:- «እንግዲህ በምትኖሩበት ዘመን ሁሉ በዐይናችሁ ያያችሁትን እንዳትረሱና ከአእምሮአችሁ እንዳይጠፉ ተጠንቀቁ፤ ለልጆቻችሁና ለልጅ ልጆቻችሁም አስተምሩአቸው» ብሎአቸዋል።

ሰ. በሐዲስ ኪዳን ውስጥ በብሉይ ኪዳን ተጽፈው የማይገኙ ጉዳዮች ተጠቅሰዋል። እነርሱም በትውፊት ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፉ ናቸው። ለምሳሌ የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት።

1. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሁለተኛ በጻፈው መልእክቱ ም:3ቍ:8 ላይ ሙሴን የተቃወሙ ኢያኔስና ኢያንበሬስ የተባሉ የሁለት ጠንቋዮችን ስም ጠቅሶአል። ይህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ አልተጻፈም።

2. ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም:12 ቍ:21 ላይ :- «የታየው ድርጊት እጅግ አስፈሪ ከመሆኑ የተነሣ ሙሴ እንኳ እኔ ፈራሁ፤ ተንቀጠቀጥኩ› አለ» ተብሏል። ሙሴ እንደዚህ ማለቱ በብሉይ ኪዳን ውስጥ አልተገለጠም።:

ስለዚህ እነዚህ በብሉይ ኪዳን ዘመን ተፈጽመው አፈጻጸማቸው በጽሑፍ ሳይገለጥ ኖሮ አሁን በሐዲስ ኪዳን መነገሩ በትውፊት ይታወቅ ስለነበረ ነው።

ሸ. በሐዋርያት ሥራ ም:1ቍ3ላይ እንደተገለጠው ጌታችን ከሞት ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ እየተገለጠላቸው አርባ ቀን ሙሉ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እንዳስተማራቸው ተነግሮአል። እንዲሁም በሉቃስ ወንጌል ም24 ቍ:27 ላይ ወደ ኤማሁስ ይሄዱ ከነበሩት ሁለት ደቀ መዛሙርት ጋር ጌታችን እየተጓዘ ሳለ ከሙሴና ከነቢያት መጻሕፍት እየጠቀሰ እንዳስረዳቸው ተገልጦአል። ታዲያ፥ ጌታችን ስለመንግሥት ሰማያት የሰጠው ትምህርትና ያደረገው ገለጻ በወንጌል ውስጥ አለመጻፋቸው አስፈላጊ ባይሆኑ ቀርተው ነውን? ብዙዎች ተመሳሳይ ትምህርቶች በጽሑፍ ሳይሆን በትውፊት ይተላለፋሉ።

ቀ. በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 20 ቍጥር 35 ላይ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ:- «ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው» ብሏል ተብሎ በሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ተጠቅሶአል። ጌታችን በዚህ ዓለም ላይ ሰው ሆኖ በተመላለሰባው ዘመናት ያደረጋቸውን ድርጊቶችና የሰጣቸውን ትምህርቶች ከመዘገቡት አራቱ ወንጌላውያን አንዳቸው እንኳ ይህን አባባል አልጠቀሱትም።



www.ethiopianorthodox.org

ታዲያ፥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከወዴት አምጥቶ ጠቀሰው? አባባሉን ጌታችን ተናግሮታል። በጽሑፍ ላይ ግን አልሰፈረም። ይህም የሚያመለክተው የሃይማኖት ትምህርቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉት በጽሑፍ ብቻ ሳይሆን በቃልም ጭምር መሆኑን ነው። በቃልም የሚተላለፈው ትምህርት ትውፊት ይባላል።

በ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረጋቸውና የተናገራቸው ነገሮች ሁሉ አልተገለጡም ከተናገራቸው ንግግሮች፥ ከአስተማራቸው ትምህርቶችና ከአደረጋቸው ተአምራት ለምሳሌ ያኽል ብቻ ቀረቡ እንጂ ሁሉም ተጽፈው የቀረቡ አይደሉም። ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ ማጠቃለያ ላይ የሚከተለውን መግለጫ የሰጠው ያለምክንያት አልነበረም።

«ኢየሱስ ያደረጋቸው ሌሎች ብዙ ነገሮች ደግሞ አሉ። እኔ እንደሚመስለኝ እርሱ ያደረጋቸው ነገሮች ሁሉ አንድ በአንድ ቢጻፉ ኖሮ የሚጻፉትን መጻሕፍት ዓለም ራሱ መሸከም ባልቻለም ነበር» (ዮሐ:ም:21ቁ:25)።

በዚህም መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማራቸውና በወንጌሎቹ ውስጥ ሳይጻፉ የቀሩ ትምህርቶች በትውፊት መልክ ከአባቶች ወደ እኛ ተላልፈዋል ማለት ነው። ትውፊትም ሳይጻፍ የታለፈውን የሚያሟላ እንጂ ትርፍ ትምህርት አይደለም።

ተ– ትውፊትን አለመቀበል ማለት ወንጌልን ወይም መልእክትን ያልጻፉ ሐዋርያት ያስተማሩት ትምህርት ዋጋ እንደሌለው መቍጠር ነው። ሐዋርያት በየአይሁድ ጸሎት ቤቶች እየገቡና በሌሎችም ቦታዎች ያስተምሩት የነበረው ትምህርት በጽሑፍ ወደ እኛ አልደረሰም። እነዚያ ትምህርቶች ሁሉ ለመጻፍ ብቃት የሌላቸውና አስፈላጊ ያልነበሩ ሆነው ነውን? አይደለም፤ ሐዋርያቱ ብቻ ሳይሆኑ ጌታችን ራሱ እንኳ ያስተማራቸው ትምህርቶች በጣም ብዙ ስለሆኑ ሊጻፍ የተቻለው የተወሰነው ክፍል ብቻ ነው። ይህ ሲባል ግን ያልተጻፈው ክፍል አይጠቅምም ለማለት ሳይሆን ትምህርቱ በጽሑፍና በትውፊት የሚተላለፍ መሆኑን ለማመልከት ነው።

ቸ – የማስተማሩ ተልእኮ ሐዋርያት ከመጻፍ ይልቅ በቃልና በስብከት የሚያስተምሩት ተልእኮ ነበር። ወንጌልን ወይም መልእክትን በጽሑፍ ያቀርቡ የነበሩት የጌታችን ተከታዮች አጠቃላይ የሆነ መሠረተ እምነትን ለመጻፍ እንጂ የሃይማኖትን ዝርዝር ሁኔታ ለማቅረብ አይደለም። የአምልኮ ደንብንና ሥርዓትን፥ እንዲሁም ዝርዝር ሁናቴዎችን ግን በየአብያተ ክርስቲያኑ ተግባራዊ እንዲሆኑ ትተዋቸዋል። ስለ እነዚህ ጉዳዮች የቅዱሳት መጻሕፍትን ማስረጃዎች ከዚህ ቀጥለን እንመልከት።

«ስለቀረው ነገር እኔ እዚያ ስመጣ ተጨማሪ መመሪያ እሰጣችኋለሁ» (1ኛ:ቆሮ:ም:11ቁ:34)።



ወንድሞች ሆይ እንግዲህ ቁሙ፤ በቃልም ሆነ በመልእክታችን ብን ባስተማርናችሁ ትውፊት ጽኑ» (2ኛ:ተሰ:ም 2ቁ:15)።

ወንድሞች ሆይ፥ ሥራ ፈት ከሆነውና በእኛ በተቀበላችሁት ትውፊት መሠረት ከማይኖር ክርስቲያን ሁሉ እንድትለዩ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችኋለን» (2ኛ:ተሰ:ም:3ቁ:6)።

«ልጽፍላችሁ የምፈልገው ብዙ ነገር ነበረኝ፤ ነገር ግን ሁሉንም በመልእክት ልገልጸው አልፈልግም፤ ይልቅስ ደስታችን ፍጹም እንዲሆን ወደ እናንተ መጥቼ ቃል በቃል ላነጋግራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ» (2ኛ:ዮሐ:ቁ:12፥3ኛ:ዮሐ:ቁ:13እና 14)።

በእነዚህም ማስረጃዎች መሠረት የሃማኖት ትመህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን በትውፊትም አማካይነት የሚተላለፍ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል።

## ነገረ ማርያም



እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም።

ስለ እመቤታችን ስለቅድስት ድንግል ማርያም የተለያዩ አብያተ ክርስቲያን ያላቸውን የተለያየ አባባል በተመለከተ ዘርዝሮ የሚያስረዳው ትምህርት ነገረ ማርያም ይባላል። እመቤታችንም ትንቢት የተነገረላትና በብሉይ ኪዳን የተለያዩ ምሳሌዎች የቀረቡላት ቅድስት እመቤት ነች።

በብሉይ ኪዳን ከቀረቡት ምሳሌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

1. በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 28 ላይ እንደተገለጠው ያዕቆብ ከወንድሙ ከዔሳው ሸሽቶ ወደ አጐቱ ወደ ላባ በሄደ ጊዜ ሎዛ ወደምትባል ሰፈር ሲደርስ ስለመሸበት ድንጋይ ተንተርሶ ተኛ። ተኝቶም ሳለ በሕልሙ አንድ በምድር ላይ ተተክሎ ወደ ሰማይ የደረሰ፥ መላእክት ይወጡና ይወርዱበት የነበረና እግዚአብሔር ከበላዩ ቆሞበት የነበረ መሰላል አይቶአል።

ምድራዊ ትስብእትን ከሰማያዊ መለኮት ጋር ያዋሐደባት አገናኝ በመሆንዋ እመቤታችን ያዕቆብ ባየው መሰላል ትመሰላለች ሲል ቅዱስ ኤፍሬም እመቤታችንን ባመሰገነበት ድርሰቱ ተናግሯል (የማግሰኞ ውዳሴ ማርያም)።



www.ethiopianorthodox.org

2. በኦሪት ዘጸአት ም:3 ላይ እንደተገለጠው ሙሴ ከምድረ ግብጽ ሸሽቶ በምድያም አገር በነበረበት ጊዜ የዐማቱን በጎች ሲጠብቅ በኮሬብ ተራራ ላይ እሳቱ እየነደደ ሳለ የማይቃጠል ቊጥቋጦ ተመልክቶአል። እዚህም ቅዱስ ኤፍሬም ያ እሳቱ እየነደደ ሳይቃጠል ሙሴ ያየው ቊጥቋጦ አንቺ ነሽ ይላታል። ይህንንም ያለው እመቤታችን ጌታችንን ፀንሳ ስትወልድ ማኅተመ ድንግለልናዋ ካለመለወጡ ጋር በማመሳሰል ነው (የሐሙስ ውዳሴ ማርያም)።

3. በኦሪት ዘጸአት :ም :25 ቊ:10-22 ዕብ ም:9:ቁ4 ላይ የቃል ኪዳኑ ታቦት አሠራር ከውስጥም፥ ከውጭም በወርቅ የተለበጠ መሆኑ የእመቤታችንን ክብርና ንጽሕና የሚያመለክት ነው። ታቦቱ ከማይነቅዝ እንጨት መሠራቱ የእመቤታችንን ቅድስና የሚያመለክት ነው። በታቦቱ ውስጥ ከሰማይ የወረደው መና መቀመጡ በእምቤታችን ማሕፀን ውስጥ የተወሰነውን የክርስ ቶስ ሕያው እንጀራነት የሚያመለክት ነው። እንዲሁም በታቦቱ ውስጥ ቃለ እግዚአብሔር የተጻፈበት ጽላት መኖሩ በቃለ እግዚአብሔር፥ በክርስቶስ ይመሰላል(ውዳሴ ማርያም ዘሰንበተ ክርስቲያንን ይመለከቷል)።

4. በኦሪት ዘኊልቊ: ም:17 ቊ:8-11 ላይ የዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ተወካዮች ከነበሩት በትሮች መካከል የአሮን በትር ብቻ አቈጥቊጣ፥ ለምልማና አበባ አውጥታ የበሰለ ለውዝ ማፍራትዋ ተነግሮአል።

እመቤታችን ያለወንድ ዘር ጌታችንን ፀንሳ መውለድዋን ለማመልከት ቅዱስ ኤፍሬም እርስዋን ባመሰገነበት ድርሰቱ ክርስቶስ አምላካችንን የወለድሽ ልን አንቺ ሳይተክሉአት እንደበቀለችው፥ ውሃ ሳያጠጡአት ለምልማና አብባ እንዳፈራችው የአሮን በትር ነሽ በማለት ምሳሌነትዋን ተገልጦአል (የእሑድ ውዳሴ ማርያም)።

<u>የእመቤታችን ድንግልና</u>:- እመቤታችን ጌታችንን ከመውለድዋ በፊት፥ በምትወልድበት ጊዜና ከወለደችውም በኋላ ድንግልናዋ እንደተጠበቀ የኖረ መሆኑ የቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ትምህርት ነው።

ነቢዩ ኢሳይያስ «እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች› በማለት ድንግልናዋን አረጋጦአል (ኢሳ:7:14)።

እንዲሁም ነቢዩ ሕዝቅኤል:- «ወደ ምሥራቅም ወደሚመለከተው በስተ ውጪ ወደ አለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ፤ ተዘግቶም ነበር። እግዚአ ብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፥ ሰውም አይገባበትም፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል «በማለት እመቤታችን ሁልጊዜ ድንግል ስለመሆንዋ ትንቢት ተናግሮአል (ሕዝ:ም 44ቊ:1-2)።



እመቤታችን ሁልጊዜ ድንግል ስለመሆንዋ ትንቢት ተናግሮአል (ሕዝ:ም 44ቊ:1-2)።

ወንጌላውያን ማቴዎስና ሉቃስም በላይ የተነገሩት ትንቢቶች እንዴት በተግባር እንደተተረጐሙ መስክረዋል (ማቴ:ም: 1ቊ:18፥ ሉቃ:ም: 1ቊ: 34-35)።

ይሁን እንጂ አንዳንድ ወገኖች የእመቤታችንን የሁልጊዜ ድንግልና በመቃወም የሚከተሉትን ጥቅሶች ያቀርባሉ።

1. በሉቃስ ወንጌል ም:2ቊ:ቊ:7 ላይ:- «የበኵር ልጅዋን ወለደች» መባሉ ሌሎች ልጆች ያሉአት መሆኑን ያመለክታል ይላሉ።

2. በማቴዎስ ም:1ቊ:25 ላይ:- «የበኵር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም» መባሉ ከወለደች በኋላ ዐውቆአታል ማለት ነው ይላሉ።

3. በተለያዩ ቦታዎች የጌታችን ወንድም ወይም ወንድሞች ተብሎ መጠቀሱ እመቤታችን ሌሎች ልጆች ለመውለድዋ ማስረጃ ነው ብለው ይከራከራሉ (ማቴ:ም:12 ቊ:46፥ም:13ቊ:5-56፥ ሐ:ሥ:ም:1 ቊ: 14፥ ገላ:ም:1ቊ:18-19)።

ለእነዚህ ተቃውሞዎች ቤተ ክርስቲያን የሚከተሉትን መልሶች ትሰ ጣለች።

<u>በኵር</u>:- በኦሪት ዘጸአት ም:13ቊ:2 ላይ:- «በእስራኤል ልጆች ዘንድ ከሰውም፥ ከእንስሳም ማሕፀን የሚከፍተውን በኵር ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ፤ የእኔ ነው» ተባለ እንጂ በኵር ለመባል የግድ ሌላ ልጅ መወለድ አለበት አልተባለም። መጀመሪያ የሚወለድ ልጅ ሁሉ በኵር ለመባል ሌላ ልጅ መወለድ አያስፈልገውም። ጌታችን ለእመቤታችን የመጀመሪያም የመጨ ረሻም ልጅ ቢሆንም በኵር ተብሏል። ጌታችን ኢየሱስ ለእግዚአብሔር አብም የበኵር ልጅ ተብሏል። ታድያ፥ እግዚአብሔር አብ ሌላ ልጅ አለው ማለት አይደለም (ዕብ:1:6)።

<u>እስከ</u>:- የበኵር ልጅዋን እስከወለደች ድረስ በተባለው ጥቅስ ላይ እስከ የሚለው ቃል ፍጻሜ የሌለው እስከ ነው፤ ለዚህም የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች እንመልከት:-

በ2ኛ ሳሙኤል:ም:6ቊ:23 ላይ:- «የሳኦል ልጅ ሜልኮል እስከሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አልወለደችም» ሲል እስከመቼም ድረስ አለመውለድዋን እንጂ ከሞተች በኋላ ወለደች ለማለት አይደለም።

በመዝሙር 110 ቊ:1 ላይ:- «እግዚአብሔር ጌታዬን:- ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው» ሲል ከዚያ በኋላ በቀኝ መቀመጡ ቀረ ማለት አይደለም።



www.ethiopianorthodox.org

በእነዚህም ማስረጃዎች መሠረት በለእመቤታችን የተነገረው እስከ» የሚለው ቃል ፍጻሜ የሌለው እስከ ነው።

<u>የጌታችን ወንድሞች</u>:- በእስራኤሎች ባህል፥ በዚህ ረገድ ግን በብዙ የምሥራቅ አገሮች ባህል የቅርብ ዘመድ የሆነ ሰው ወንድም ወይም እኅት መባሉ የተለመደ ነው። ለዚህም የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት።

<u>ሎጥ</u>:- የአብርሃም የወንድሙ ልጅ መሆኑ በኦሪት ዘፍጥረት ም:11ቍ:31 በኦሪት ዘፍጥረት ም:14ቍ:14 ላይ ግን ወንድሙ ተብሎ እናገኘዋለን።

<u>ላባ</u>:- የያዕቆብ አጐት መሆኑ በኦሪት ዘፍጥረት ም:29ቍ:10–12 የተገለጸ ሲሆን በዚሁ ምዕራፍ ቍ 15 ላይ ወንድሙ ተብሎ እናገኘዋለን።

<u>ሴዴቅያስ</u>:- የኢዮአኪን አጐት መሆኑ በ2ኛ ነገሥታት ም:24 ቍ:17 የተገለጸ ሲሆን በ2ኛ ዜና መዋዕል ም 36 ቍ:10 ላይ ወንድሙ ተብሎ እናገኘዋለን።

ከእነዚህም ማስረጃዎች በኋላ ሌሎች ዝርዝር ሁናቴዎችን እንመልከት።

በዮሐንስ ወንጌል ም:19 ቍ:25 ላይ:- «በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱና የእናቱ እኅት የቀለዮጳ ሚስት ማርያምና መግደላዊት ማርያም ቆመው ነበር» የሚል ሲሆን በማቴዎስ ወንጌል ም:27 ቍ:56፥ በማርቆስ ወንጌል ም:15 ቍ:40 እና 47፥ በሉቃስ ወንጌል ም:24 ቍ:10 ላይ ይህች የቀለዮጳ ሚስት የነበረችው የእመቤታችን እኅት ማርያም ያዕቆብና ዮሳ: የሚባሉ ልጆች እንደልዋት ተገልጾአል።

ስለዚህ የጌታችን ወንድሞች የተባሉት በባህሉ መሠረት የአክስቱ ልጆች ናቸው እንጂ የእመቤታችን ልጆች አይደሉም።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም በድንግልናዋ ጸንታ የኖረች የአምላክ እናት ነች እንጂ ሌሎች ወገኖች እንደሚሉት ጌታችንን ከወለደች በኋላ ዮሴፍን አግብታ ሌሎች ልጆችን የወለደች አይደለችም።

ለዚህም አባባል ከሚቀርቡት ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙ ባቸዋል።

1. በማቴዎስ ወንጌል ም:1ቍ:20 እና 24፥ በሉቃስ ወንጌል ም:1፥27፥ ም 2 ቍ:5 ላይ እመቤታችን የዮሴፍ እጮኛ ስትባል ከቈየች በኋላ በማቴዎስ ወንጌል ም:2ቍ:13፥ 14፥ 20፥ እና 21 ላይ የዮሴፍ እጮኛ መባልዋ ቀርቶ ሕፃኑን ከእናቱ ጋር መባል ተጀመረ። ይህም የሚያመለክተው ዮሴፍ እመቤ ታችንን ወደ ቤቱ እንዲወስዳት የታዘዘው እንዲጠብቃት እንጂ እንዲያገባት አለመሆኑን ነው። ታዲያ፥ ለምን በእጮኛነት ስም ተደረገ ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል። አዎን በኦሪት ዘዳግም ም :22 ቍ: 23 እና 24 እንደተገለጸው አንዲት ድንግል የዝሙት ኀጢአት ፈጽማ ብትገኝ በድንጋይ ተወግራ እንድትገደል ታዝዟል። እመቤታችን ወደ ዮሴፍ ቤት ገብታ ባትወልድ ኖሮ



ጌታችንን የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ መ... የማያውቁ ሌሎች ሰዎች በዝ ሙት ሊከስሱአትና የሞት ፍርድም ሊፈ...ዱባት በቃጣቸው ነበር። እጮኛ ካልተባለች ደግሞ ወደ ዮሴፍ ቤት ለመሄ... ምክንያት ባልኖራትም ነበር።

2. ምንም እንኳን የመልአኩን ብሥራት ከመስማትዋ በፊት እመቤታችን የዮሴፍ እጮኛ የነበረች መሆንዋ ቢገለጽ፥ መልአኩ ገብርኤል ወንድ ልጅ ትወልጂአለሽ ብሎ ባበሠራት ጊዜ «እኔ ድንግል ነኝ፤ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ብላ መጠየቅዋ በድንግልና ለመኖር የነበራትን ቍርጥ ሐሳብ ያረጋጥልናል፤ እንደዚያ ባይሆን ኖሮ ባል ካገባሁ በኋላ ስለምወልደው ልጅ የተነገረኝ ብሥራት ነው ብላ ትቀበለው ነበር እንጂ እንደዚያ ያለ ጥያቄ ባልጠየቀችም ነበር። መልአኩም ቢሆን እጮኛ እያለሽ ለምን እንደዚህ ያለ ጥያቄ ትጠይቂያለሽ ያላት ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል የእግዚአ ብሔርም ኀይል ይጋርድሻል ያለው ማኅተም ድንግልናሽ ሳይለወጥ በእግዚአ ብሔር ተአምር ትወልጂአለሽ ማለቱ ነው።

3. በዮሐንስ ወንጌል ም:19ቍ 26 እና 27 ላይ ጌታችን ተሰቅሎ በነበረበት ጊዜ በመስቀሉ አጠገብ እናቱና የሚወድደው ደቀ መዝሙር ቆመው አይቶ እናቱን ለሚወድደው ደቀ መዝሙር ዐደራ መስጠቱና ያም ደቀ መዝሙር ከዚያ ሰዓት ጀምሮ ወደ ቤቱ እንደወሰዳት ተገልጾአል። በማቴዎስ ወንጌል ም: 13 ቍ: 54 – 56 ላይ የተገለጸውና ተከራካሪዎቹም ያመኑበት አባባል እመቤታችን አራት ወንዶችና ቍ...ራቸው ያልተገለጸ ሴቶች ልጆች አልዋት የሚል ነው። ታዲያ፥ እነዚህ ሁሉ ልጆች ያሏት ከሆነ እንዴት አድርጋ ነው ከልጆቿ ተለይታ ልጅዋ ወዳልሆነ ሰው ቤት የሄደችው። ይህ ሊሆን የማይችል ጉዳይ ነው። እንግዲህ ከዚህ የምናገኘው ትምህርት ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱን እመቤታችንን ለሚወድደው ደቀ መዝሙር ዐደራ መስጠቱ እና እርስዋም ከዚያን ጊዜ ጀምራ ወደ ተጠቀሰው ደቀ መዝሙር ቤት መሄድዋ ከጌታችን በቀር ሌሎች ልጆች የሌሏት መሆኑን ነው።

4. ጌታችን ከመወለዱ በፊት ጀምሮ የእግዚአብሔር መልአክ በግንባር ለእመቤታችን፥ ቀጥሎም ለዮሴፍ በሕል... የነገራቸው ትንቢት መድኀኒታ ችን የሚወለደው በመንፈስ ቅዱስ ተአምር ያለወንድ ዘር መሆኑን ነው። ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ የተሞላችው ኤልሣቤጥ ጌታችን ገና በእመቤታችን ማሕፀን እያለ የጌታዬ እናት በማለት ከእመቤታችን የሚወለደው ጌታ መሆኑን አረጋግጣለች። መልአኩ ገብርኤልም ለእመቤታችን ያረጋገጠላት ብሥራት «ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል» ብሎ ነው። ጌታችን በተወለደ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ለእረኞች ተገልጦ» ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ ተወልዶላችኋል» ብሎ የነገራቸውን የደስታ ዜና ለዮሴፍና ለእመቤታችን በነገሩአቸው ጊዜ እመቤ ታችን ይህን ሁሉ በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር ተብሎአል። እመቤ ታችንና ዮሴፍ በሙሴ ሕግ መሠረት ሕፃን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደቤተ



www.ethiopianorthodox.org

የነገራቸውን የደስታ ዜና ለዮሴፍና ለእመቤታችን በነገሩአቸው ጊዜ እመቤታችን ይህን ሁሉ በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር ተብሎአል። እመቤታችንና ዮሴፍ በሙሴ ሕግ መሠረት ሕፃን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደቤተ መቅደስ በወሰዱት ጊዜ ስምዖንና ሐና የተባሉ ሁለት የእግዚአብሔር ሰዎች ስለሕፃን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት መስክረዋል። እመቤታችንም ስለምትወልደው ሕፃን ማንነት አምና የተቀበለች መሆንዋን የምንረዳው በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ የተናገረችው ኤልሣቤጥ «እንደሚፈጸም ከጌታ የተነገራትን ያመነችው ብፅዕት ናት» በማለትዋ ነው።

እመቤታችን ክርስቶስ ከድንግል እንደሚወለድ በነቢያት የተነገረውን ትንቢት የምታውቅ ከመሆንዋም በላይ ያየችውንና የሰማችውን በልብዋ አኑራ ስለሁናቴው የተነገራትን ሁሉ ያመነችው እንደመሆንዋ እንዴት የአምላክ እናትነትን ከሚያኽል ታላቅ ክብር ተነሥታ ባል ወደማግባት ዝቅተኛ ማዕረግ ወረደች ብለን እንገምታለን? ዮሴፍስ ቢሆን ስለጌታችንና ስለ እመቤታችን ያን ሁሉ ክብር ካየና ከሰማ በኋላ እንዴት አድርጎ የአምላክ እናትን ሚስት የማድረግ ዝንባሌ ዐደረበት ብለን እንገመታለን። ዮሴፍ ግን ጻድቅ ሰው ስለነበረ ጌታችን የተፀነሰው በመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ከማወቁ በፊት እንኳ እመቤታችንን ሊያስጣት ያልፈለገ መሆኑ በማቴዎስ ወንጌል ም:1ቍ:19 ላይ ተገልጾአል። ጻድቅም በመሆኑና ማድረግ የሚገባውንና የማይገባውን ነገር ለይቶ የሚያውቅ በመሆኑ እመቤታችንን ለመጠበቅ እንጂ ሚስት ለማድረግ ወደቤቱ እንዳልወሰዳት እንገነዘባለን።

5. በማቴዎስ ወንጌል ም:13 ቍ: 55-56 ላይ:- «ይህ የዚያ የእንጨት ጠራቢው ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም አይደለችምን ወንድሞቹስ ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንና ይሁዳ አይደሉምን? እኅቶቹስ ሁሉ ከእኛ ጋር አይደሉምን?» የሚለውን የንቀት አነጋገር የተናገሩት በጌታችን መለኮታዊ ክብር የማያምኑት አይሁድ መሆናቸው የታወቀ ነው። ይህ ዐረፍተ ነገር ውሸት እንጂ ምንም እውነት የሌለበት መሆኑን ቤተ ክርስቲያናችን ታምናለች፤ ይህንኑም ታስተምራለች። ይሁን እንጂ አንዳንድ ተከራካሪዎች ጌታችን የዮሴፍ ልጅ ነው የሚለውን የአይሁድን አባባል የማያምኑ ሲሆኑ እነያዕቆብ የጌታችን ወንድሞች ናቸው የሚለውን አባባል አምነው ከመቀበላቸውም በላይ ምእመናን ሁሉ በዚሁ እንዲያምኑ ለማድረግ ብዙ ጥረት ያደርጋሉ። ይህን የአይሁድን አባባል እንደ እውነት ቈጥረውና በወገናዊነት መልክ ከቤተ ክርስቲያን መለያ ምክንያቶች አንዱ አድርገው በነቀፋ መልክ ክርክር ያቀርቡበታል። የጌታችንን ክብር ዝቅ ለማድረግ ታስቦ የተነገረውን አሉባልታ የእምነት መሠረት አድርጎ መከራከር በጉዳዩ ከአይሁድ ጋር እንደመተባበር የሚያስቈጥር መሆኑን ተከራካሪዎቹ የተገነዘቡት አይመስልም።

በአይሁድ አባባል እምነታቸውን የሚመሠርቱ ከሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራትን ያደርግ የነበረው ከብዔል ዜቡል ማለት ከአጋንንት አለቃ ጋር በመስማማት ነው የሚለውን የአይሁድን አሉባልታ ያምኑበታል ማለት



ነውን? (ማቴ:ም:12ቍ:24)። በዮሐንስ ወንጌል ም:9ቍ:24 ላይ አይሁድ ጌታችንን ኃጢአተኛ ነው ብለው የተናገሩትን አሉባልታ እውነት ነው ብለው ያምኑታል ማለት ነውን? እንደገናም አይሁድ የጌታችን ከሞት መነሣት ባስፈራቸው ጊዜ አስከሬኑን ደቀ መዛሙርቱ መጥተው ሰረቁት ብለው ያስወሩትን ወሬ እውነት ነው ብለው ይቀበሉታል ማለት ነውን? (ማቴ ም: 28 ቍ: 11–15)። ከነዚህም ምሳሌዎች ሌላ አይሁድ በጌታችን ላይ የተናገሩአቸው የሐሰት ንግግሮች አሉ። ታዲያ እንዴት የእነርሱን አባባሎች ለእምነታቸው መሠረት ለማድረግ ፈቀዱ?

ቤተ ክርስቲያናችን ግን በእመቤታችን የሁልጊዜ ድንግልና ላይ ያላት እምነት የአይሁድን አሉባልታ በተመረኰዘ ዐረፍተ ነገር ሊለወጥ የማይችል መሆኑን ታረጋግጣለች።

6. የእመቤታችንን የሁልጊዜ ድንግልና በሚመለከት የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት ቀጥሎ ይቀርባል።

<u>ቅዱስ ቴዎዶጦስ የዕንቈራ ኤጲስ ቆጶስ</u>:- «ዛሬ እግዚአብሔር ከቅድስት ድንግል ተወልዶ ታየ። ድንግልም እንደ ቀድሞዋ በድንግልና ጸንታ ኖረች። እናትም ተባለች፤ ሕይወትን የሚለውጥ በድንግል ተፈትሐ ማሕፀንን አላመጣም» (ሃይ:አበ:ገጽ:172)።

<u>ቅዱስ ጎርጎርዮስ የእንዚናዙ</u>:- «ሥጋ የሌለው እርሱ ሥጋዋን ተዋሕዶ እንደ ሰው ሁሉ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በጌትነቱ ሳለ በማሕፀኗ ተወሰነ፤ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀንም ከተፈጸመ በኋላ የሚወለድበት ቀን ቢደርስ በማይመረመር ግብር በጎቱም ድንግልና ተወለደ፤ ማኅተመ ድንግልናዋ አልተለወጠም፤ ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ ተወለደ እንጂ» (ሃይ: አበ: ገጽ:212)።

<u>ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ</u>:- «ከአዳም ጐን የጐድን አጥንት እንደነሣ አዳምንም አካል እንዳልጐደለው እንዲሁ ከድንግል የምትናገር፥ የምታውቅ ነፍስ ያለችው ሥጋን ነሣ፤ ማኅተመ ድንግልናዋ አልተለወጠም፤ አዳም የጐድን አጥንት ከእርሱ ከተነሣ በኋላ አካል ሳይጐድለው ፍጹም ሆኖ ኖረ፤. ድንግልም ሕፃን ክርስቶስ ከእርስዋ ከተወለደ በኋላ እንዲህም ያለመለወጥ በድንግልና ጸንታ ኖረች (ሃይ:አበ:ገጽ:240)።

<u>ቅዱስ ሳዊሮስ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት</u>:- አምላክን የወለደች ማርያም ለዘለዓለሙ ድንግል እንደሆነች መውለድዋም የማይመረመር ድንቅ እንደሆነ ከወለደችም በኋላ በድንግልና ጸንታ እንደኖረች አስረዳን» (ሃይ: አበ: ገጽ: 375)።

<u>የአምላክ እናትነትዋ</u>:- ማንኛውም ክርስቲያን ነኝ የሚል ሰው ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ መሆኑን የማያምን የለም። እርሱም በቤተልሔም ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱ የታወቀ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

እመቤታችን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት በመሆንዋና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ የባሕርይ አምላክ በመሆኑ እመቤታችን የአምላክ እናት መሆንዋ ምንም ሊካድ የማይችል እውነት ነው። በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን በተሰበሰበው ጉባኤ ውሳኔ መሠረት ንስጥሮስ ከተወገዘባቸው ምክንያቶች መካከል ዋነኛው ምክንያት የእመቤታችንን የአምላክ እናትነት በመካዱ ነው።

የእመቤታችንን የአምላክ እናትነት ከሚገልጹት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል» (ሉቃ: ም1ቍ:35)።

«ኤልሣቤጥም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ በታላቅ ድምፅ እንዲህ አለች፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፤ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?» (ሉቃ: ም:1 ቍ:41–43)።

«ነገር ግን የተወሰነው ዘመን በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከልን፤ እርሱም ከሴት ተወለደ፤ ለሕግም ታዛዥ ሆነ» (ገላ:ም:4ቍ:4)።

ስለ እመቤታችን የአምላክ እናትነት የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት ቀጥሎ የተመለከተው ነው:-

<u>የእስክንድርያው ቅዱስ ቄርሎስ</u>:- «ዳግመኛም በኋላ ዘመን ቅድስት ድንግል እርሱን በሥጋ ወለደችው፤ ስለዚህም ቅድስት ድንግልን ወላዲተ አምላክ እንላታለን» (ሃይ:አበ:ገጽ:305)።

<u>የአንጾኪያው ቅዱስ ሳዊሮስ</u>:- «ንጽሕት ድንግል በውነት አምላክን የወለደች እንደሆነች እንናገራለን፤ እግዚአብሔር ቃል ከእርስዋ ሥጋን ተዋሕዶአልና (ሃይ:አበ:ገጽ 372)።

<u>ክብርዋ</u>:-

1.ተመላልሶ እንደተገለጸው ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኀጢአት በቀር በሁሉም ነገር እንደሰው ልጅ ሆኗል። የሰው ልጆች ሁሉ አባትና እናታቸውን እንዲያከብሩ መታዘዛቸው የሚታወስ ነው። ጌታችንም ለእናቱና ለአሳዳጊው ዮሴፍ ይተዘዛቸው እንደነበረ በሉቃስ ወንጌል ም:2 ቍ:51 ላይ ተገልጾአል።

እኛ የምንወደውን ሌላም ሰው እንዲወድድልን፥ እኛ የምናከብረውን ሌላም ሰው እንዲያከብርልን ሰብአዊ ስሜታችን የሚያስመኘን እንደመሆኑ ጌታችንም ሰው የሆነ አምላክ በመሆኑ እናቱን እንድናከብርለት ፈቃዱ እንደሚሆን ግልጽ ነው። ዓለማዊ ምሳሌ እንኳ ብንወስድ የአንድን ንጉሥ እናት የምናከብርበት ምንክንያት ንጉሡን ራሱን በማክበራችን ነው። ታዲያ፥ እናት የምናከብርበት ምንክንያት ንጉሡን ራሱን በማክበራችን ነው። ታዲያ፥ በሞት ወይም በሽረት ሊያልፍ የሚችለውን የምድራዊ ገዢ እናት የምናከብር



ከሆነ የዘለዓለማዊውን የጌታችን የአም[illegible] ማክበር እንደ ሚገባን እንገምት። በዚህም መሠረት እመቤታችንን ማክበር ጌታችንን ራሱን ማክበር እንደሆነ በማመን የተለማኝ እናት የሆነችውን አማላጃችንን ማክበር የሚገባን መሆኑን አንዘንጋ።

2. ጌታችን ከእርስዋ እንደሚወለድ ለማብሠር፥ መልአኩ ገብርኤል ወደ እመቤታችን ተልኮ በመጣ ጊዜ «ጸጋን የተመላሽ ማርያም ሆይ፥ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ» ብሎአታል። እነሆ ትፀንሺአለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጂአለሽ ባላት ጊዜ ወንድ የማላውቅ ድንግል እንደመሆኔ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ብትለው መንፈስ ቅዱስ እንደሚያድርባትና የልዑል ኀይልም እንደሚጋርዳት በመዘርዘር በአክብሮት መልስ ከመስጠቱ በቀር እርስዋ በጠየቀችው ጥያቄ ቅር ያልተሰኘው አክብሮት የሚገባት የአምላክ እናት በመሆንዋ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ከስድስት ወር በፊት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ዘካርያስ ተልኮ ሚስቱ እንደምትወልድለት በነገረው ጊዜ በዚህ ዕድሜአችን እንዴት ልንወልድ እንችላለን ብሎ በመጠየቁ ልጁ እስከተወለደበት ጊዜ ድረስ በድዳነት እንዲቀጣ ተደርጎአል። ዘካርያስ በጠየቀው ጥያቄ የተወቀሰና የተቀጣ ሲሆን እመቤታችን ግን በጠየቀችው ጥያቄ አለመወቀስዋ የተከበረች የአምላክ እናት በመሆንዋ ነው።

3. እመቤታችን ዘመድዋን ኤልሣቤጥን ለመጠየቅ በሄደች ጊዜ የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል ብላ በመንፈስ ቅዱስ የተመላችው ኤልሣቤጥ እመቤታችንን በማክበር የትሕትና አነጋገር ከመናገርዋም በላይ እመቤታችንን ከማክበሩ የተነሣ ፅንሱ እንኳ በኤልሣቤጥ ማሕፀን ውስጥ ዘልሎአል። ይህም በመንፈስ ቅዱስ ቀስቃሽነት የተፈጸመው ሁናቴ እመቤታችን ምን ያኽል ክብር የሚገባት መሆኗን ያመለክተናል።

4. ከመልአኩ ከቅዱስ ገብርኤል ብሥራትና ኤልሣቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ የአክብሮት ምስጋናዋን ካቀረበችላት በኋላ እመቤታችን እግዚአብሔርን ባመሰገነችበት ጸሎትዋ እነሆ፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል ብላ ተንቢት ተናግራለች። በዚህም ትንቢት መሠረት እመቤታችንን እናከብራታለን እንጂ ተከራካሪዎቹ እንሚያደርጉት ክብር የምንነሣት አይደለንም።

5. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት አድርጎ እናቱን እንደሚያከብርና አማላጅነትዋን እንደሚቀበል በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ላይ ተመልክቶአል። ምንም እንኳ የተአምራት ማድረጊያ ጊዜው ገና የነበረ ቢሆን ለእርስዋ ክብርና አማላጅነትዋን ለመቀበል ሲል የመጀመሪያ የነበረውን ታምራቱን አድርጎአል፤ ይህም ማለት ውሃን ወደ ወይን ጠጅነት ለውጦአል።

## ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ሕግ በምን ላይ የተመሠረተ ነው?

-----------------------------------------------



www.ethiopianorthodox.org

2. የእግዚአብሔር ሕግ የተጀመረው በምንድነው?

3. የእግዚአብሔር ሕግ በጽሑፍ መቅረብ እስከቻለበት ጊዜ ድረስ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕግ እንዴት ያውቁ ነበር?

4. ሕግ የሚደነገገው ለምንድነው?

5. እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ለእስራኤል ሕዝብ ያወጀው ሕግ ምን የሚባለው ነው?

6. ይህስ ሕግ መጀመሪያ በምን ላይ ተጻፈ?

7. ሕግጋቱን ብንፈጽም ምን እናገኛለን?

8. ሕግጋቱንስ ባንፈጽም ምን ይደርስብናል?

9. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጣቸው ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ከቀድሞው ሕግ ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን ዐይነት ነው?

10. በኦሪት ዘዳግም:ም:28 ላይ ስለ ሕግ አፈጻጸም የተገለጠው አጠቃላይ ሐሳብ ምን የሚል ነው?

11. የክርስትና ትምህርት ምንጮች ምን ምን ናቸው?

12. ትውፊት ማለት ምን ማለት ነው?

13. ትውፊትና መጽሐፍ ቅዱስ በምን ይለያያሉ?

14. በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተጽፈው የማይገኙና ሐዲስ ኪዳን ከጠቀሳቸው ጉዳዮች ቢያንስ አንዱን አቅርብ።

15. ጌታችን ተናገረው ተብሎ በወንጌል ውስጥ ያልተገኘ ነገር ጌታ እንደተናገረው በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተጠቀሰው ጥቅስ ምን የሚለው ነው?

16. ስለትውፊት ጠቃሚነት በሐዲስ ኪዳን ውስጥ አንዱን አቅርብ።

17. ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም የሚሰጠው ትምህርት ምን ይባላል?

18. በብሉይ ኪዳን ከቀረቡ ጉዳዮች ለእመቤታች ምሳሌ የሆነ ቢያንስ አንድ አቅርብ።

19. በዂርናኸ እስከ ለተባሉት ቃላት መልስ ስጥ።

20. ወንድም ለተባለው ቃል መልስ ስጥ።

21. ድንግል ማርያም በድንግልና ጸንታ የኖረች ለመሆንዋ ማስረጃ አቅርብ።

22. ስለ እመቤታችን ክብር ተናገር



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ 2

## መጽሐፍ ቅዱስ

### ብሉይ ኪዳን

ሁለቱ ጽላቶች:- እግዚአብሔር እስራኤላውያን ሁሉ እየሰሙት ዐሥሩን ትእዛዛት ካስተላለፈ በኋላ የነጐድጓድና የመለከቱ ድምፅ ስላስፈራቸው አንተ ተናገረን እንጂ እግዚአብሔር ቢናገረን እንሞታለን ብለን እንፈራለን ብለው ለሙሴ ነገሩት። ከዚያ በኋላ እግዚአአብሔር በቀጥታ ለሕዝቡ ሳይሆን በሙሴ አማካይነት ትእዛዙን ያስተላልፍ ጀመር።


በመጀመሪያ ስለመሠዊያ አሠራር ሕግ፥ ቀጥሎ የባሪያዎችን አያያዝ በመተመለከተ፥ ዐመፅ የሚፈጽሙ ሰዎች ስለሚቀጡበት ሕግ፥ ስለባለ ንብረቶች ኀላፊነት፥ የንብረት አጠባበቅ ሕግ፥ ስለግብረ ገብነትና የእምነት ሕግ፥ ስለትክክለኛ ፍርድ፥ ስለሰባተኛው ዓመትና ሰባተኛው ቀን፥ ስለ ሦስቱ ታላላቅ በዓላት፥ ስለ ተስፋ ቃሎችና መመሪያዎች እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት ለሕዝቡ ተናገረ።

ከዚህ በኋላ ሙሴ ሁለቱን የድንጋይ ጽላቶች ይረከብ ዘንድ ወደ ሲና ተራራ እንዲወጣ ታዘዘ። የነዌ ልጅ ኢያሱም ከእርሱ ጋር ነበረ። ሙሴ ለእስራኤል ማኅበረሰብ እንዲህ አላቸው:- «ተመልሰን እስክንመጣ በዚህ ቈዩን። በመካከላችሁ አንዳች ጥልና ክርክር ቢነሣ አሮንና ሖር አሉላችሁና ወደ እነርሱ ሄዳችሁ እነርሱ ዳኝነትና ፍርድ ይስጡአችሁ።» ሙሴ ወደ ተራራው በወጣ ጊዜ ተራራውን ደመና ሸፈነው። የእግዚአብሔርም ክብር በሲና ተራራ ላይ ተቀመጠ። ደመናው ተራራውን ስድስት ቀን ሸፈነው። ከሰባተኛው ቀን በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን ጠራው። ሙሴም በደመናው ውስጥ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ተቀመጠ።

እዚያም በደመናው ውስጥ እንዳለ ለቤተ እግዚአብሔር ስለሚቀርብ ስጦታ፥ ስለቃል ኪዳኑ ታቦት አሠራርና አጠቃቀም፥ ስለመባው ኅብስት ማስቀመጫ ጠረጴዛ አሠራርና አጠቃቀም፥ ስለመብራቱ መቅረዝ አሠራር፥ ስለ ተቀደሰው ድንኳን አሠራር፥ ስለመሠዊያው፥ ስለድንኳኑ አደባባይ፥ ለመብራት ስለሚደረግ ጥንቃቄ፥ ስለ ልብሰ ተክህኖ ስለ ክህነት ሥልጣን፥ ስለ ሠርክ መሥዋዕት፥ ስለ ዕጣን መሠዊያ፥ ስለ ቤዛነት ክፍያ፥ ስለመታጠቢያው ሳሕን፥ ስለቅባት ዘይት፥ ስለ ዕጣን ዝግጅት፥ ስለ ሰንበት የተለያዩ የእግዚአብሔር መመሪያዎች በሙሴ አማካይነት ለእስራኤል ልጆች ተላልፈዋል።

ሙሴ በተራራው ላይ ለአርባ ቀኖች ያኽል በመዘግየቱ የእስራኤል ልጆች ትዕግሥት አጡ። ተሰባስበውም ወደ አሮን መጥተው በመከበብ ከግብጽ

ምድር መርቶ ያወጣን ሙሴ ምን እንደደረሰበት አናውቅም፤ አሁንም በፊት በፊታችን እየሄዱ የሚመሩን አማልክት ሥራልን አሉት። እርሱም ምንም ሳያመነታና ቅሬታ ሳያሳይ የጆሮ ወርቅ ግጊጫዎችን እንዲያመጡለት ጠየቀ። ሰዎች ሁሉ የወርቅ ጉትቻዎቻቸውን አመጡለት። የመጣለትን የወርቅ ጉትቻ ሁሉ ወስዶ በእሳት ካቀለጠው በኋላ የወርቅ ጥጃ አድርጎ ሠራው መሠዊያም ሠርቶ ሕዝቡ ለወርቁ ጥጃ እንዲሰግድለት አደረገ። እስራኤላውያንም ከግብጽ ምድር መርቶ ያወጣን አምላካችን ይህ ነው አሉ። ለወርቁ ጥጃም መሥዋዕት አቅርበው ከበሉና ከጠጡ በኋላ ተነሥተው መዝፈንና መጨፈር ጀመሩ።



ሙሴ በተራራ ላይ አርባ ቀኖችን ስለዘገየ ሕዝቡ የወርቅ ጥጃ ጣዖት አመለከ (ዘጸ. ም 32)::

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን ከግብጽ ምድር መርተህ ያወጣኸው ሕዝብ ጣዖት ሠርቶ በማምለክ ረክሶአልና ፈጥነህ ከዚህ ተራራ ውረድ አለው። እነዚህ ሰዎች ትእዛዞቼን በመጣስ ዘወትር እልኸኞች ስለሆኑ እነርሱን ፈጽሜ ልደመስሳቸው ወስኜአለሁ፥ አንተን ግን ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁና ተወኝ አለው።

ሙሴ ግን:- «አምላክ ሆይ፥ በታላቅ ኀይልና በታላቅ ክንድህ ከግብጽ ምድር ያወጣኸውን ሕዝብህን እስከዚህ የምትቈጣው ለምንድነው? ግብጻውያን ይህን ሕዝብ ከግብጽ ምድር ያወጣኸው በተራራዎች ላይ ልትገድላቸው እንደሆነ አድርገው እንዲዘባበቱብን ለምን ትፈቅዳለህ? ባሪያዎችህን አብርሃምን፥ ይስሐቅንና ያዕቆብን አስበህ ከቍጣህ ተመለስ፤ ለእነርሱ የገባኸውንም ቃል ኪዳን አስብ ብሎ በመጸለዩ እግዚአብሔር ሊያመጣ የነበረውን መቅሠፍት እንዲገታ አደረገ።



ከዚህ በኋላ ሙሴ ሁለቱን የድንጋይ ጽላቶች ይዞ ከተራራው ወረደ። እነዚህ ጸላቶች የእግዚአብሔር ሥራ ሲሆኑ በላያቸው ተቀርጾ የነበረው ጽሑፍም የእግዚአብሔር ሥራ ነበር። ሙሴ ወደ ሰፈሩ ተጠግቶ የወርቁን ጥጃ ምስልና የሕዝቡን ጭፈራ ሲያይ በጣም ተቈጥቶ ይዞአቸው የነበሩትን ጽላቶች ወርውሮ ሰባበራቸው።

ያንንም የወርቅ ጥጃ ሰባብሮ በማድቀቅ እስራኤላውያን ከውሃ ጋር ቀላቅለው እንዲጠጡት አደረጋቸው። አሮንም ለምን ይህን ሕዝብ ይህን ኃጢአት እንዲሠራ አደረግኸው ብሎ በቍጣ ተናገረው። ሙሴ በሰፈሩ ደጃፍ ቆሞ የእግዚአብሔር ወገን የሆነ ሁሉ ወደ እኔ ይምጣ ብሎ ድምፁን ከፍ በማድረግ ተናገረ። ሌዋውያን ሁሉ ወደ እርሱ መጡ። እርሱም ሌዋውያንን ሰይፋችሁን መዝዛችሁ ከዚህ እስከ ወዲያኛው በር ድረስ በመመላለስ ያለምንም ምሕረት ወንድሞቻችሁን፥ ወዳጆቻችሁንና ጎረቤቶቻችሁን እንድትገድሉ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር አዝዞአል አላቸው። እነርሱም ለቃሉ ታዛዥ ሆነው በዚያን ቀን ሦስት ሺህ ሰዎችን ገደሉ።

ሙሴም እንደገና ስለ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ:- «እባክህ ኃጢአታቸውን ይቅር በል፤ ይቅር የማትላቸው ከሆነ ግን የሕዝብህ ስሞች ከተጻፉበት መዝገብ የእኔን ስም ደምስስ» አለ። እግዚአብሔር ግን:- «ስሞቻቸውን ከመዝገቤ የምደመስሰው ኃጢአት በመሥራታቸው ያሳዘኑኝን ሰዎች ነው» አለው።

የወርቅ ጥጃ ጣዖት እንዲሠራላቸው አሮንን በማስገደዳቸው እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ከባድ በሽታ ላከ።

እግዚአብሔር ሙሴን አንተ የሰበርካቸውን ጽላቶች የሚመስሉ ሌሎች ሁለት ጽላቶች ሥራ፤ እኔም በቀድሞዎቹ ጽላቶች ላይ የነበሩትን ቃላት እጽፍባቸዋለሁ አለው። ሙሴም የታዘዘውን ሁለት ጽላቶች አዘጋጅቶ ወደ ተራራው ወጣ። እዚያ እንደገና አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ቆይቶ፥ ጌታ በጽላቶቹ ላይ ዐሥሩን ትእዛዛት ከጻፈባቸው በኋላ ሙሴ እነዚያን ጽላቶች ይዞ ወደ ሕዝቡ ተመለሰ። እርሱም ከተራራው ላይ ሲወርድ ፊቱ ያበራ ነበር። ፊቱ እንደሚያበራ እርሱ ባይታወቀውም አሮንና ሕዝቡ ሁሉ ፊቱ እንደሚያበራ ተመልክተው ወደ እርሱ ለመቅረብ ፈሩ። ፊቱም ለተመልካች በጣም ያንጸባርቅ ስለነበረ ግንባሩን በሻሽ ይሸፍን ነበር። ፊቱንም የሚገልጠው ወደ ተቀደሰው ድንኳን ሲገባ ብቻ ነበር (ዘዳ:ም:32እና 34)።

www.ethiopianorthodox.org



እግዚአብሔር ለሙሴ ጽላቱን እንደሰጠው (ዘጸ. 24 ቁ 12 -18)፡፡

<u>ኦሪት ዘሌዋውያን</u>:- በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተለየ የሚቀርበው ስለካህናትና ለእስራኤላውያን የአምልኮ ሥርዓት ትምህርት ነው።

ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 7 ድረስ ስለመሥዋዕት አቀራረብ ህግ ተዘርአል1. አንድ ሰው ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት ለማቅረብ ቢፈልግ ከቀንድ ከብት ከሆነ ምንም ነውር የሌለበት አንድ ኮርማ መርጦ ያምጣ፤ መሥዋዕት አቅራቢውም በእንስሳው ራስ ላይ እጁን ይጫን፤ ለኃጢአት ማስተሰረያም የሰመረ መሥዋዕት ይሆንለት ዘንድ በተቀደሰው ድንኳን መግቢያ በኩል ያቅርበው። የእንስሳውንም የሥጋ ክፍሎች ቈራርጠው በእሳት ያቃጥሉአቸው። ይህ ዐይነቱ መሥዋዕት መዓዛው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ይሆናል።

1. አንድ ሰው ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት ለማቅረብ ቢፈልግ ምንም ነውር የሌለበት አንድ ኰርማ መርጦ ያምጣ የሚቃጠል መሥዋዕት አቅራቢው የሚያቀርበው ከበግ ወይም ከፍየል ቢሆን ምንም ነውር የሌለበት ተባዕት ይሁን። እርሱንም ከመሠዊያው በስተ ሰሜን በኩል በእግዚአብሔር ፊት ይረደው። ብልቱ ሁሉ ተቈራርጦ በሙሉ ይቃጠል። ይህም ዐይነቱ መሥዋዕት መዓዛው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ይሆናል።

ወይም ደግሞ የሚቃጠል መሥዋዕት አቅራቢው ለማቅረብ የሚፈልገው ከወፎች ወገን ከሆነ የርግብ ጫጩት ወይም ዋኖስ መሆን ይችላል። ካህኑም ተቀብሎ አንገቱን ይቈልምመው። ክንፎቹንም ይዞ ሳይከፋፍል አካሉን በመከፋፈል በመሠዊያው ላይ በሚገኘው እሳት በሙሉ ያቃጥለው። ይህም ዐይነቱ መሥዋዕት መዓዛው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ይሆናል።



2. ሌላው የመሥዋዕት ዐይነት ደግሞ የእህል መባ ነው። አንድ ሰው ለእግዚአብሔር የእህል መባ በሚያቀርብበት ጊዜ የላመ ዱቄት መሆን አለበት፤ በእርሱም ላይ የወይራ ዘይትና ዕጣን ይጨምርበት። በአገልግሎት ላይ ያለው ካህን ከዚያ መባ በእፍኙ ሙሉ ወስዶ ሁሉም ለእግዚአብሔር የቀረበ መሆኑን ለማሳወቅ በመሠዊያው ላይ በእሳት ያቃጥለው። ይህም ዐይነቱ የምግብ መባ ሽታው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሆናል። ከእህል መባውም የተረፈው ለካህናቱ ይሰጥ። እርሱም ለእግዚአብሔር ከቀረበው መባ ተከፍሎ የተወሰደ በመሆኑ የተቀደሰ ነው። ዳቦውም ሲጋገር ቂጣ ይሁን። ካህኑም ከዚያ መባ ከፊሉን ወስዶ በሙሉ ለእግዚአብሔር የቀረበ መሆኑን ለማስታወስ በመሠዊ ያው ላይ በሚገኘው እሳት ያቃጥለዋል። ይህም መዓዛው እግዚአብሔርን ደሰ የሚያሰኝ ይሆናል።

3. ማንም ሰው የደኅንነት መሥዋዕት አድርጎ የሚያቀርበው ኮርማ ወይም ጠቦት ቢሆን ነውር የሌለበት ሆኖ መሥዋዕት አቅራቢው እጁን በእንስሳው ራስ ላይ ይጫንና በተቀደሰው ድንኳን ደጃፍ ይረደው። ካህናቱ ደሙን ተቀብለው በመሠዊያው ጐኖች ሁሉ ላይ ይርጩት። እንዲሁም የሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ስብ በሙሉ፥ ኵላሊቶቹንና በእነርሱ ላይ የሚገኘውን ስብ፥ እንዲሁም እንደ መረብ ሆኖ ጉበቱን ከሚሸፍነው ሰብ ምርጥ የሆነውን ወስደው በመሠዊያ ላይ ያቃጥሉት፤ ይህም ዐይነቱ መዋዕት መዓዛው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ይሆናል።

4. ባለማወቅ ስለተፈጸመ በደል የሚቀርብ መሥዋዕት:- ኃጢአተኛው ሊቀ ካህናት ቢሆን አንድ ኮርማ፥ ወይም ከእስራኤል ማኅበረ ሰብእ አንዱ ቢሆን አንድ ወይፈን፥ ወይም የሕዝቡ መሪ ቢሆን አንድ ተባዕት ፍየል አቅርቦ መሥዋዕት አቀራቢው እጁን በእንስሳው ራስ ላይ ይጫንና የሚቃጠል መሥዋዕት በሚታረድበት በኩል ይረድ፤ ካህኑም ደሙን በሚቃጠል መሥዋዕት ጕጦች ላይ ያኑር፤ ከዚያም የተረፈውን በመሠዊያው ላይ ያፍስሰው። ከዚያ በኋላ ስለ ደኅንነት መሥዋዕት በሚደረገው ዐይነት ይደረግ። በመጨረሻም ካህኑ ያስተስርይለትና ኃጢአቱ ይቅር ይባልለታል።

አንድ ሰው በፍርድ አደባባይ የሚያውቀውን ባይመሰክር፥ የእንስሳትን በድን በመንካት ቢረክስ፥ ከሰውነት የሚፈስስ አንዳች ርኩስ ነገር ቢነካ፥ ለክፉም ሆነ ለደግ በግዴለሽነት ስእለት ቢሳል፥ እነዚህ ሁሉ ድርጊቶች በደል መሆናቸውን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በደል ስለሚሆንበት የበደል መሥዋዕት አቅርቦ ካህኑ ያስተሰርይለታል።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው:- ማንም ሰው በዐደራ የተሰጠውን ንብረት ባለመመለስ እግዚአብሔርን ቢበድል፥ ወይም የሰውን ንብረት በመቀማት፥ ወይም አታልሎ በመውሰድ፥ ወይም የጠፋ ነገር አግኝቶ አላየሁም ቢል፥ ወይም በሐሰት ቢምል፥ ማንም ሰው እነዚህን በደሎች ፈጽሞ ኃጢአተኛ ቢሆን፥ በቅድሚያ፥ በማታለል፥ በዐደራ የተቀበለውንና ጠፍቶ ያገኘውን ንብረት ይመልስ፥ ወይም በሐሰት ምሎ የወሰደውን ሁሉ ኻያ በመቶ

www.ethiopianorthodox.org

ጨምሮ ለባለቤቱ ይከፈል። ለበደሉም ምንም ነውር የሌለበት ተባዕት በግ መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቅርብ።

5. <u>የኃጢአት ስርየት መሥዋዕት</u>:- ለኃጢአት መሥዋዕት የሚቀርበው እንስሳ የሚታረደው የሚቃጠል መሥዋዕት በሚታረድበት ስፍራ በእግዚአብሔር ፊት ነው። ይህም መሥዋዕት እጅግ ቅዱስ ነው። እንስሳውን የሚሠዋው ካህን በመገናኛው ድንኳን አደባባይ ባለው የተቀደሰው ስፍራ ይብላው።

እነዚህ ከላይ የቀረቡት የመሥዋዕት ዐይነቶችና የአቀራረብ ደንቦች ለዐይነት ያኽል ቀረቡ እንጂ የመሥዋዕት ዐይነቶችና አቀራረባቸው እነዚህ ብቻ አይደሉም።

ከምዕራፍ ስምንት አስከ ምዕራፍ ዐሥር ድረስ የአምልኮ ሥርዓት አመሠራረት፥ አመሠራረቶች ተዘርዝረዋል። በዚህም ክፍል ስለ ክህነት አመሠራረት፥ በአሮን ልጆች በናዳብና በአቢሁ ላይ የተሰጠው የእግዚአብሔር ፍርድ ተግባራዊ መሆን፥ እንዲሁም ካህናት የሚያሰክር መጠጥ ጠጥተው ወደ መገናኛው ድንኳን እንዳይገቡ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል።

በምዕራፍ 8 ላይ የአሮንና የልጁ የክህነት ሹመት ሥነ ሥርዓት ተካሄዷል። በምዕራፍ 9 አሮን ስላቀረበው መሥዋዕት ተዘርዝሮአል። በምዕራፍ ዐሥር የአሮን ልጆች ናዳብና አቢሁ ያልተቀደሰ እሳት በማቅረባቸው በሞት መቀጣታቸው ተገልጦአል።

ከምዕራፍ ዐሥራ አንድ እስከ ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት ድረስ ስለመንጻት ሕግ ተዘርዝሮአል። በምዕራፍ 11 ንጹሕ የሆኑና ንጹሕ ያልሆኑ እንስሳት ተለይተው ተገልጸዋል። ምዕራፍ 12 ልጅ ከወለደች በኋላ የሴትን የመንጻት ሥርዓት ይዘረዝራል። በምዕራፍ 13 እና 14 ደግሞ ስለቆዳ በሽታ ምርመራና የመንጻት ሥርዓት ተዘርዝሮአል። በእነዚሁ ምዕራፎች በቤት ላይ ስለሚታይ ሻጋታም ተዘርዝሮአል። በምዕራፍ 15 ከሰውነት በመፍሰስ ርኵሰትን ስለሚያመጣ ፈሳሽ ተገልጦአል። በተለየ ከወንድና ከሴት አባላዘር ስለሚፈስስ ፈሳሽ ትኵርት ተሰጥቶበታል።

በምዕራፍ 16 ስለ ስርየት ቀን ሥርዓት በተለየም የተቀደሰውን ድንኳን ስለማንጻት የታቀደ ነው። ይህም የሚሆነው ማኅበረሰቡን በማንጻት ነው።

ከምዕራፍ 17 እስከ ምዕራፍ 26 ድረስ የተዘረዘረው ስለ ቅድስና ሕግ ነው። በምዕራፍ 17 ላይ የመሥዋዕት ማቅረቢያ ቦታ ከመወሰኑም በላይ ነፍስ ያለው ፍጡር ሕይወቱ በደሙ ውስጥ ስለሆነ ደም መብላት ተከልክሎአል። ደሙም በመሬት ላይ እንዲፈስስ ታዝዟል። በምዕራፍ 18 በሰፊው ትምህርትና ማስጠንቀቂያ የተሰጠበት ማንም ሰው ከዘመድ ጋር ወሲባዊ ግንኙት ማድረግ የሌለበት መሆኑ ነው። እነዚህን ትእዛዞች ቢጠብቁ የእስራኤል ልጆች ቅድስናቸውን ከሚጠብቁባቸው አንዱ መንገድ ይሆናል ማለት ነው።

በምዕራፍ 19 የተለያዩ ሕጎችንና ደንቦችን በመዘርዘር እነዚያን ጠብቆ መኖር የፍትሕንና የቅድስናን ሕግ ማክበር መሆኑን ያመለክታል። በምዕራፍ



www.ethiopianorthodox.org

20 ላይ ለሕግጋቱ አለመታዘዝ የሚያስከትለው ቅጣት ተዘርዝሮአል። በተለያዩ የበደል ሥራዎች ላይ የሚገኙትን ሰዎች እግዚአብሔር የሚያመጣባቸው የቅጣት ዐይነት ከመገለጹም በላይ ኅብረተሰቡ ደግሞ በአንዳንድ የበደል ዐይነቶች ላይ ምን ማድረግ እንደሚገባው ታዝዟል።

በምዕራፍ 21 ላይ የቅድስናን ኑሮ በተመለከተ ካህናቱ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ትእዛዝ ተላልፎአል።

በምዕራፍ 22 ላይ ለእግዚአብሔር የሚሰጡ ስጦታዎች እንዴት በቅድስና መጠበቅ እንደሚገባቸው መመሪያ ተሰጥቶበታል።

በምዕራፍ 23 ላይ ስለሃይማኖት በዓላት አከባበር መመሪያ ተሰጥቶበታል። በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሱት በዓላት:- የፋሲካና የቂጣ በዓል፥ የመከር በዓል፥ የዓመት መባቻ ቀን በዓል፥ የኃጢአት ስርየት ቀን በዓል፥ የዳስ በዓል ናቸው።

በምዕራፍ 24 ላይ የተሰጡት መመሪያዎች ስለመብራት የሚደረግ ጥንቃቄ፥ ለእግዚአብሔር ስለሚቀርብ መባ፥ አንዳንድ በደሎችን የሚበድሉ ሰዎች ምን ዐይነት ቅጣት መቀጣት እንዳለባቸው የሚዘረዝር ነው።

በምዕራፍ 25 ውስጥ ስለሰባተኛው ዓመት ማለት የምድር ሰንበት፥ ስለኢዮቤልዩ ማለት 49 ዐልፎ 50ኛ ዓመት፥ ለድኻ ብድር ስለመስጠት መመሪያዎች ቀርበዋል። ገበሬው ስድስት ዓመት ሠርቶ በሰባተኛው ዓመት ምድሪቱን እንዲያሳርፋት ታዝዟል። በኢዮቤልዩ ዓመት ደግሞ ንብረቱን ሸጦ የነበረ ሰው ዕዳውን ከፍሎ መሬቱን ሊያስመልስ ይችላል። በባሪያነት የተሸጠ ሰው በኢዮቤልዩ ዓመት ነጻነትን ያገኛል። ገንዘብ ተበድሮ የነበረም ሰው ዕዳው ይሰረዝለታል።

በምዕራፍ 26 በመታዘዝ ስለሚገኘው በረከትና አለመታዘዝ የሚያስከትለው ቅጣት ተገልጦአል።

በምዕራፍ 27 ስለ ስእለት፥ ዐሥራትና በኵራት የተዘረዘረ ሲሆን ለእግዚአብሔር የተሰጠውን ለመዋጀት ምን መደረግ እንዳለበት በዝርዝር ተመልክቶአል።

## ሐዲስ ኪዳን

<u>የኢየሩሳሌም ጉባኤ</u>:- አንዳንድ ሰዎች ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ በርናባስ የክር ስትናን ትምህርት በሰፊው ያስተምሩበት ወደነበረው ወደ አንጾኪያ ከይሁዳ መጡ፥ እነርሱም በሙሴ ሕግ ካልተገረዛችሁ በቀር አትድኑም እያሉ ከአረ መኔነት የተመለሱትን ክርስቲያኖች ማስቸገር ጀመሩ። ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ በርናባስም በዚህ ጉዳይ ከሰዎቹ ጋር በጣም ተከራከሩ። ከዚያ በኋላ ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ በርናባስ በአንጾኪያ ከሚገኙ ከሌሎች ወንድሞች ጋር

ሆነው ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ጉዳዩን ለሐዋርያትና ለሽማግሌዎች እንዲያቀርቡ ተወሰነ። እነርሱም በውሳኔው መሠረት ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ። ኢየሩሳሌምም በደረሱ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ተቀበለቻቸው። መልእክተኞቹ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ነገር ሁሉ ዘርዝረው አስረዱ። ከፈሪሳውያን ወገን የሆኑ አንዳንድ አማኞች ግን ተነሥተው አረማውያን የነበሩ ክርስቲያኖች የግድ መገረዝና የሙሴን ሕግ መጠበቅ አለባቸው አሉ። ከዚህ በኋላ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ይህን ጉዳይ ለመመርመር ተሰበሰቡ። ብዙ ክርክርም ከተደረገ በኋላ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ተነሥቶ እርሱ ያገኘውን ልምምድ ለጉባኤው አሰማ። ከአረመኔነት ወደ ክርስትና የተመለሱትን ምእመናን ከአይሁድነት ወደ ክርስትና ከተመለሱት ምእመናን የማያንስ ተቀባይነት እንዳላቸው ገለጠ። እግዚአብሔርም በሁለቱ ወገኖች መካከል ምንም ልዩነት እንደማያደርግ የዐይን ምስክርነቱን ሰጠ። እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም አባባል እግዚአብሔር በሁለቱ ወገኖች መካከል ልዩነት ያላደረገ ከሆነ አይሁድ ወገኖችና አባቶቻቸው ሊሸከሙ ያልቻሉትን ቀንበር በአረማውያን ተመላሾች ላይ መጫን ተገቢ አለመሆኑን ሲያብራራ የጉባኤው አባሎች ጸጥ ብለው ያዳምጡት ነበር።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ንግግሩን እንዳቆመ ቅዱስ በርናባስ እና ቅዱስ ጳውሎስ በእነርሱ አማካይነት እግዚአብሔር በአረማውያን መካከል ያደረገውን ተአምርና ድንቅ ነገር ሁሉ ተናገሩ።

ከቅዱስ በርናባስና ከቅዱስ ጳውሎስ ቀጥሎ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ የነበረው ቅዱስ ያዕቆብ ከአረመኔነት ተመላሾች ክርስቲያኖችን ማስጨነቅ አይገባም የሚለውን ሐሳብ በመደገፍ የነቢያትን መጻሕፍት እየጠቀሰ ተናገረ። እርሱም ያቀረበው ሐሳብ ስምምነትን አግኝቶ ሁሉም ተቀብሎታል።

ቅዱስ ያዕቆብም ሐሳቡን ሲያቀርብ እንዲህ በኋል:- «እኛ ልንነግራቸው የሚገባው ለጣዖት የተሠዋ ምግብ እንዳይበሉ: ከዝሙት እንዲርቁ: ሳይታረድና ደሙ ሳይፈስስ ታንቆ የሞተ እንስሳ እንዳይበሉ: ደም እንዳይበሉ ነው።»

በዚህም መሠረት ጉባኤው የቅዱስ ያቆብን አነጋገር አጽድቆ ይሁዳንና ሲላስን ከቅዱስ በርናባስና ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ሆነው የጉባኤውን ውሳኔ ለምእመናን ለማቅረብ እንዲሄዱ መረጣቸው። ለምእመናን የተጻፈውም ደብዳቤ እንዲህ የሚል ነበር።

«እኛ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ወንድሞቻችሁ: በአንጾኪያና በሶርያ: በኪልቅያም ለምትኖሩ ከአረማውያን ወገን ለሆናችሁ ወንድሞቻችን ሰላምታ እናቀርባለን፤ ከእኛ መካከል አንዳንድ ሰዎች እኛ ሳናዝዛቸው ወደ እናንተ መጥተው በነገሩአችሁ ቃል እንዳስቸገሩአችሁና ግራ እንዳጋቡአችሁ ሰምተናል፤ ስለዚህ በአንድነት ከተሰበሰብን በኋላ መልእክተኞችን መርጠን ከተወደዱት ወንድሞቻችን ከበርናባስና ከጳውሎስ ጋር ወደ እናንተ ልንልካቸው ተስማማን። በርናባስና ጳውሎስ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ ናቸው። ውሳኔአችንን በቃልም ጭምር እንዲነግሩአችሁ ይሁዳንና ሲላስን ልከናል። ከሚከተሉት አስፈላጊ ነገሮች በስተቀር ሌላ ከባድ ሸክም እንዳንጭንባችሁ መንፈስ ቅዱስና እኛ መልካም ሆኖ አግኝተነዋል፤ ለጣዖት በመሠዋቱ ምክንያት የረከሰ ምግብ አትብሉ፤ ሳይታረድና ደሙ ሳይፈስስ ታንቆ የሞተ ሥጋ አትብሉ፤ ደም አትብሉ፤ ከዝሙት ራቁ፤ ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ ብትጠበቁ መልካም ታደርጋላችሁ፤ ደኅና ሁኑ» (የሐ:ሥ:ም:15ቊ:23–29)።

መልእክተኞቹ ተሰናብተው ወደ አንጾኪያ ሄዱ፤ አማኞችንም ሰብስበው ደብዳቤውን ሰጡአቸው። ምእመናን መልእክቱን ባነበቡ ጊዜ እጅግ ደስ አላቸው። በመልእክቱም ተጽናኑ።



የሐዋርያት ጉባኤ (የሐ.ሥ. ም 15 ቊ 1-35)።

<u>ወደ ዕብራውያን ሰዎች የተላከ መልእክት:-</u> የዚህን መልእክት አዘጋጅ በተመለከተ ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ የተለያዩ አስተያየቶች አሉ። ይህን መልእክት የጻፈው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አይደለም የሚሉት ሰዎች ከሚያቀርቡአቸው ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

1. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሌሎቹን መልእክቶቹን ሁሉ የሚጀምረው ማንነቱን ማለት ስሙን በመግለጥ ሰላምታ አቅርቦ ነው። ይህ መልእክት ግን በቀጥታ ትምህርቱን ይጀምራል እንጂ የአዘጋጁን ስም ጠቅሶ ሰላምታ አያቀርብም።


www.ethiopianorthodox.org

2. የአጻጻፉ ዘይቤና የዐረፍተ ነገሮች አመሠራረት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሌሎቹ መልእክቶቹ ላይ ከአቀረባቸው አሠራሮች የተለየ ነው።

3. የዐረፍተ ነገሮቹ አመሠራረት የዕብራይስጥ ቋንቋ ዐረፍተ ነገር አመሠራረት ሳይሆን የግሪክ ቋንቋ ዐረፍተ ነገር አመሠራረት ነው። መልእክቱ ለዕብራይውያን ሰዎች የተላከ እንደመሆኑ ጽሑፉም በዕብራይስጥ ቋንቋ መሆን ነበረበት ፤ የመልእክቱ ይዘት እንደሚያመለክተው ከሆነ ይህ መልእክት የተጻፈው በግሪክ ቋንቋ ነው።

መልእክቱን ያዘጋጀው ቅዱስ ጳውሎስ ነው የሚሉት ወገኖች ደግሞ የሚከተሉትን ምክንያቶች ያቀርባሉ።

1. እንደሚታወቀው ቅዱስ ጳውሎስ በአይሁድ ዘንድ እንደ የኦሪት ሕግ ጠላት ተደርጎ ይታይ ነበር። ቅዱስ ጳውሎስ ስሙን ቢጽፍ ኖሮ ማንኛውም ይሁዳዊ የእርሱን ስም በማየቱ ብቻ መጽሐፉን ከማንበብ ይገታ ይሆናል ብሎ በመፍራት ስሙን ሳይጽፍ ቀርቶአል። ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብዙዎቹ አዘጋጆች ስማቸውን ያልገለጡ እንደመሆናቸውና አይሁድም በዚያ ዐይነት የለመዱት በመሆኑ ለአይሁድ አዲስ ነገር አይሆንባቸውም። በሐዲስ ኪዳንም ቢሆን ለምሳሌ የመጀመሪያው የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት የቅዱስ ዮሐንስን ስም ባይጠቅስም የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት መሆኑን ግን ማንም የካደ የለም።

2. በሌሎች መልእክቶቹ ከሚጽፉቸው አጻጻፎች ይለያል የሚለው ግን ትክክል አይደለም። ለምሳሌ የደቀ መዝሙሩን የጢሞቴዎስን ስም ማንሣቱ ከሌሎቹ መልእክቶቹ አጻጻፍ ያልተለየ መሆኑን ያመለክታል (ምዕ 13ቍ :23)።

3. ከላይ የቅዱስ ጳውሎስን አዘጋጅነት በማስተባበል በተራ ቍጥር 2 እና 3 ላይ በቀረቡት ተቃውሞዎች በዕብራይስጥ ቋንቋ ያልተጻፈ መሆኑ ተገልጾአል። መልእክቱ የተጻፈው በዕብራይስጥ ቋንቋ ቢሆንም ቅዱስ ሉቃስ ወደግሪክኛ በተረጐመው ጊዜ የግሪኮችን አጻጻፍ አስመስሎታል።

4. ቅዱስ ጳውሎስ በሌሎች መልእክቶቹ ሁሉ በእርሱ እንደተጻፉ ማረጋገጫ አድርጎ የተናገረው የሰላምታ ቃል በዚሁ መልእክት 13፥25 ላይ ተገልጦአል (ቆላ. 4፥18)።

የዕብራይውያን መልእክት 13 ምዕራፎችን የያዘ ሲሆን አራት ዐላማዎች አሉት።

አንደኛ የኦሪቱ ሕጋቸው በመላእክት አማካይነት በመሰጠቱ እግዚአብሔር ምን ያኽል ያከበራቸው መሆኑን በማሰብ አይሁድ በኵራት ይመኩ ነበር። በዚህ መልእክት ውስጥ ግን ከነቢያት መጻሕፍት በመጥቀስ ክርስቶስ ምን ያኽል ከመላእክት በላይ መሆኑና ልዩነቱም በፈጣሪና በፍጡር መካከል እንደሆነ ተገልጦአል።



ሁለተኛ/እስራኤላውያን ሕግ የተሰጠው ለእኛ ነው በማለት ይመኩ ስለነበረ ቤትን የሚሠራ ሰው ከቤቱ ይልቅ ክብር እንዳለው ሁሉን የፈጠረው ጌታችን ኢየሱስ ከሙሴ ይበልጣል ብሎአል።

ወደፊት መባል ለሚገባው ነገር ምስክር እንዲሆን ሙሴ በእግዚአብሔር ቤት ሁሉ እንደ አገልጋይ ሆኖ ታማኝ ነበር። ክርስቶስ ግን በእግዚአብሔር ቤት ታማኝ የሆነው እንደ ልጅ ሆኖ ነው ተብሎአል።

ሦስተኛ/ እስራኤላውያን የሌዊ ልጆች የሆኑትን ካህናትን ማሞገስ ይወድዱ ነበር። ነገር ግን አብርሃምና የሌዊ ልጆች ለመልከጼዴቅ ተገዙለት። የክርስቶስ ክህነት በመልከ ጼዴቅ ክህነት እንደሚመሰልና የነገድ አባት የሆነው አብርሃም ዐሥራት እንደከፈለው ተገልጦአል። ስለዚህም የሌዊ አያት አብርሃም ዐሥራት መክፈሉ በራሱና በሌዋውያን ቦታ ሆኖ ነው። ከሕዝቡ ዐሥራት የሚቀበሉት ካህናት በአብርሃም አማካይነት ለመልከጼዴቅ ዐሥራት ከፍለዋል። በዚህም መሠረት የክርስቶስ ክህነት ከሌዋውያን ክህነት የበለጠ ክብር ያለው ነው።

አራተኛ/ አይሁድ እንደ መሥዋዕትና ቍርባን ባሉት የአምልኮ ሥርዓታቸው ይመኩ ነበር። ይህ ዋጋ የሌለው ትምክሕት ነው በማለት እነዚያ ሥርዓቶች ምሳሌ (ጥላ) ብቻ መሆናቸው ተገልጦላቸዋል። የኃጢአቱ ስርየትም በክርስቶስ መሥዋዕትነት የተገኘ መሆኑን በመልእክቱ ተገልጾላቸዋል።

በዚህም መሠረት የዕብራውያን መልእክት በሕገ ኦሪት፥ በነቢዩ ሙሴ፥ በካህናት ሥርዓትና በኦሪቱ ያምልኮ ሥርዓት ይመኩ ለነበሩትና የክርስቶስን አዳኝነት ላልተቀበሉት እስራኤላውያን ትምህርት እንዲሆናቸው የተጻፈ ነው። ክርስቶስም ከቀድሞ ጀምሮ ትንቢት የተነገረለት እንጂ ሳይታሰብ ድንገት የመጣ አለመሆኑን ያብራራል። ከዚያም በላይ የኦሪቱ የአምልኮ ሥርዓት ለሐዲሱ ምሳሌ (ጥላ) መሆኑን ዘርዝሮ የሚያስረዳ ትምህርት ነው። በመልእክቱም መጨረሻ ምክርና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶበት መልእክቱ ይጠናቀቃል።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

እግዚአብሔር እንደ አምላክ፥ እንደ ታዳጊ ጌታ፥ እንደ ንጉሥ፥ እንዲሁም እንደ ወላጅ አባት ሆኖ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ባርነት ነጻ ካወጣቸው በኋላ በምድረ በዳ የመራቸው አስፈላጊዎቹን ነገሮች ሁሉ እያመቻቸላቸው ነው። በምድረ በዳው ጉዞ ጊዜ ከተሰጡአቸው የአምላክ ስጦታዎች መካከል ሃይማኖታዊና ዓለማዊ መተዳደሪያ ሕጎች ይገኙበታል። ከእነዚህም ሕጎች መካከል ዐሥሩ ትእዛዛት ከሕግ ስብስቦች አንዱ ነው።

ከእነዚህም ከዐሥሩ የመጀመሪያዎቹ አራቱ ትእዛዛት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ግንኙነት የተመለከተ ሲሆን የቀሩት ስድስቱ ትእዛዛት በሰዎች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች የተመለከተ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር የሚያደርጋቸው ድርጊቶችና የሚሰጣቸው ትእዛዞች ሁሉ ለሰው ልጆች ደኅንነት የታቀዱ ናቸው። በእግዚአብሔርና በሰው ልጆች መካከል ባሉት ግንኙቶች ላይ የተመሠረቱትን ትእዛዞች በሚያስተላልፍበት ጊዜ ሰዎች ሕግጋቱን ፈጽመው የዘለዓለምን ሕይወት እንዲወርሱ ስለፈቀደ መሆኑን ያመለክታል። በሌላ በኩል ደግሞ በሰዎች መካከል ባለው ግንኙት ላይ የተመሠረተ ትእዛዝ በሚያስተላልፍበት ጊዜ በአንድ በኩል ኀይለኛው ደካማውን እንዳያጠቃው የአምላክ ጥንቃቄ ሲሆን ኀይለኛው ደግሞ ደካማውን እንዳያጠቃና በእግዚአብሔር ፍርድ እንዳይቀጣ የአምላክ ፈቃድ ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር ትክክለኛ ዳኛ በመሆኑ ለሰው ሁሉ እንደየተግባሩ ዋጋውን የሚሰጠው መሆኑ ግልጥ ነው።

1. እግዚአብሔር አንድ ብቻ ስለሆነ እንደ ባዓል ያሉ የጣዖት አማልክት ተጨማሪ ተመላኪዎች መሆን የለባቸውም።

2. እግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ ተቀርጸው የተሠሩ ጣዖታት የእግዚ. አብሔርን ቦታ ይዘው ሊመለኩ አይገባም።

3. እውነትን አጥፍቶ ሐሰትን እውነት ለማስመሰል በሐሰት የእግዚ. አብሔርን ስም መጥራት ምሕረት የማይደረግለት ኃጢአት ነው።

4. የሰንበትን ቀን ማክበር፥ ለበጎ ተግባር ግን ማዋል ተገቢ ነው።

5. አባትንና እናትን ማክበር ሲባል ትእዛዛቸውን መፈጸም ብቻ ሳይሆን መጦርን የመሰለ ተግባርን ይጨምራል። ይህም ማኅበራዊና (ብሔራዊ) ግለሰባዊ ምቾት ሳይጓደል መቀጠል ነው።

6. አትግደል በሚለው ትእዛዝ የሰው ሕይወት ክቡርነት ይንጸባረቃል። ጊዜው ደርሶ፥ በአደጋ ወይም በጦርነት መሞት ግን ከዚህ የተለየ ነው።

7. አታመንዝር በሚልበት ጊዜ የጋብቻን ክቡርነት ያመለክታል። ይህም የኅብረተሰብ መሠረትና ሥርዓት ነው።

8. አትስረቅ በሚልበት ጊዜ የግለሰብ ሀብትና ንብረት የማፍራት መብትን ያመለክታል። ይህንንም መብት ማንም ሊጋፋው የማይገባ መሆኑን ለማ መልከት አትስረቅ ተብሎአል።

9. በሐሰት መስክሮ አንዱን መጥቀምና ሌላውን መበደል ይቅርታ የሌለው ኃጢአት ነው

10. ከላይ በቍ:8 የቀረበውን የሚመስለው የሌላውን ሰው ሀብትና ንብረት መመኘት የማይገባ መሆኑ ነው።

ለሙሴ የተሰጠው ጽላት በታቦቱ ውስጥ ሆኖ የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበት ነበር። እግዚአብሔርም የሚገለጥበት ስለነበረ ለታቦቱ ታላቅ ክብር ይሰጠው ነበር። ሊቀ ካህናቱ እንኳ በዓመት አንድ ጊዜ በቀር ታቦቱ ወደሚገኝበት ቅድስተ ቅዱሳን መግባት አይፈቀድለትም ነበር። ያም ቢሆን ከሊቀ ካህናቱ በቀር ለማንም ለሌላ ሰው አይፈቀድም ነበር።



በካህኑ በዔሊ ዘመን ታቦቱ በፍልስጥኤማውያን በተማረከ ጊዜ እግዚ. አብሔር ፍልስጥኤማውያንን በከባድ ቅጣት ስለቀጣቸው ወደ እስራኤላውያን መመለስ ግድ ሆኖባቸዋል።

ይህ የቃል ኪዳን ታቦት ከአሚናዳብ ቤት ወደ ኢየሩሳሌም በተወሰደበት ጊዜ ሠረገላውን የሚስቡት በሬዎች በመደናቀፋቸው ታቦቱ እንዳይወድቅ እጁን ዘርግቶ የደገፈውን ዑዛን በድፍረቱ እግዚአብሔር ተቈጥቶበት ወዲያው ገድሎታል (2ኛ:ሳሙ:ም6ቍ:7)። ስለዚህ ታቦቱ የእግዚአብሔር መገኛ ወይም የእግዚአብሔር መገለጫ ነበር።

የዚህን የጽላቱን አመጣጥ መለስ ብለን ስንመለከት ብዙ ጠቃሚ ጉዳዮችን እናስተውላለን። ሙሴ ዐሥሩ ትእዛዛት የተጻፉበትን ጽላትና የተለያዩ መመሪ ያዎችን ለመቀበል በሲና ተራራ ላይ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በቈየ ጊዜ እስራኤላውያን ጣዖት በማምለክ ኃጢአት ስለሠሩ እግዚአብሔር ተቈጥቶ ሊያጠፋቸው ማቀዱን ለሙሴ ነገረው። ሙሴንም የአንድ ትልቅ ሕዝብ አባት እንደሚያደርገው ቃል ገባለት። ሙሴ ግን ሁለት ምክንያቶችን በማቅረብ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። ምክንያቶቹም የእግዚአብሔር ክብርና የእስራኤል ሕዝብ ደኅንነት ነበሩ።

የእግዚአብሔርን ክብር በተመለከተ ሌሎች ሕዝቦች እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከምድረ ግብጽ ያወጣቸው በምድረ በዳ ሊያጠፋቸው ፈልጎ ነው ይላሉ፤ ከዚያም በላይ ለአባቶቻቸው ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባውን ቃል ኪዳን ሳይፈጽምስ እንዴት ይቀራል በማለት ተከራከረ። የእስራኤላውያንን ደኅንነት በተመለከተ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ እባክህ የሕዝቡን ኃጢአት ይቅር በል፤ የእነርሱን ኃጢአት ይቅር የማትል ከሆነ ግን የሕዝብህ ስሞች ከተጻፉት መዝገብ የእኔን ስም ደምስስ አለ።

እግዚአብሔር ሙሴን አንተንና ዘርህን ታላቅ ሕዝብ አደርጋለሁ ያለው ተስፋ አጓጉቶት ራስ ወዳድ አልሆነም። ነገር ግን እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ እንዲጸናና አረማውያን መዘባበቻ ምክንያት እንዳያገኙ ለእግዚአብሔር ክብር በማሰብና በመጨነቅ፥ እንዲሁም የእስራኤል ሕዝብ ከሚጠፋ እርሱ በእነርሱ ቦታ ሆኖ ከክብር መዝገብ ቢፋቅ እንደሚመርጥ መናገሩ ምን ያኽል ለእግዚአብሔር የሚያስብና ለሕዝቡም የፍቅር ጭንቀት እንዳለው ያመለ ክታል። ይህ የሙሴ ቅን አስተሳሰብ ለሁላችንም ትልቅ ትምህርትን ይሰጠናል።

በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ የቀረቡትን የተለያዩ የአምልኮ ሥርዓቶች ትክ ብሎ በመመልከት የምንማረው እግዚአብሔር አምላክ በሥርዓት እንድ ናመልከው የሚፈቅድ መሆኑን ነው። እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት ለእስራኤል ሕዝብ ዝርዝር የአምልኮ ሥርዓቶችን ያስተማረው በዚሁ በኦሪት ዘሌዋውያን ነው።

ብዙዎቹ የሥርዓት መመሪያዎች በሐዲስ ኪዳን ላሉ ሁኔታዎች ምሳሌ (ጥላ) ናቸው። ለምሳሌ ብዙዎቹ የመሥዋዕት ዐይነቶች ለኃጢአት ስርየት

www.ethiopianorthodox.org

እንደመሆናቸው ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነትና ቤዛነት ምሳሌ (ጥላ) ናቸው። እንስሳቱ ምንም እንከን የሌላባቸው መሆናቸው የጌታችንን ቅዱስነትና ፍጹምነት የሚያመለክቱ ናቸው።

ዓለማዊ አስተሳሰብ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን አንድነት ለመፈታተን ሰርጎ ከመግባቱ በፊት ለማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ችግር መፍትሔ የሚገኝለት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተሰባስበው በሚያሳልፉት ውሳኔ ነበር። እነርሱም ለተቀደሰው የቤተ ክርስቲያን አንድነት ዓላማ ይሠሩ ስለነበረ መንፈስ ቅዱስ አይለያቸውም ነበር። ለምሳሌ የመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በ51 ዓ.ም በኢየሩሳሌም በአደረጉት ስብሰባ ከአረማዊነት ወደ ክርስትና የተመለሱትን ምእመናን በማስጨነቅ፥ የመጡትን ለማስደንበርና ለማባረር፥ ያልመጡትን እንዳይመጡ ለማድረግ የሰው ልጅ ጠላት ያደርግ የነበረውን የሽምቅ ውጊያ አክሽፈዋል። ብዙዎቹ የኦሪት ሥርዓቶች ለሐዲሱ እንደ ጥላ ሆነው የቀረቡ እንጂ በራሳቸው ድኅነት የማይገኝባቸው መሆናቸው ግልጥ መሆኑን በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ዐውቀውና አስተምረው ውሳኔ አሳልፈዋል። በዚያን ጊዜ የተነሣው ዋናው ክርክር ከአረመኔነት ወደ ክርስትና የገቡት አረማውያን መገረዝና ሌሎችንም የኦሪት ሥርዓት መፈጸም አለባቸው የሚል ነበር። ለምሳሌ ግዝረት ለሐዲስ ኪዳኑ ጥምቀት በጥላነት የቀረበ ሥርዓት ነበር። በዚህም መሠረት በኢየሩሳሌም ጉባኤ የተሰበሰቡት ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ከአረመኔነት ወደ ክርስትና የተመለሱት ምእመናን ለክርስትና ሃይማኖት ጥላ የነበሩትን የኦሪት ሥርዓቶች የመፈጸም ግዴታ የለባቸውም ብለው በመወሰን በጊዜው ለተነሣው ችግር መፍትሔ አስገኙለት።

በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ ጳላኤ ሰናይ በተሰብሳቢዎቹ መካከል እየገባ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን መለያየት ውሳኔ እንዲያሳልፉ ያደረገበት ጊዜ አለ። መንፈስ ቅዱስ የማይለየውና የሚጠብቀው ደግሞ የስብሰባው ዓላማ የመንፈስ ቅዱስን ዓላማ የተከተለ እንደሆነ ብቻ ነው።

## ጥያቄዎች

1. እስራኤላውያን እግዚአብሔር ሲናገራቸው ምን እንሆናለን ብለው ነው ለሙሴ የነገሩት? በምንስ ምክንያት ነው?
2. ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር እንዴት ተናገራቸው?
3. ሙሴ የድንጋይ ጽላቶቹን የተረከበው ከወዴት ነው?
4. ሙሴ በሄደ ጊዜ ኀላፊነቱን ለማን አስረከበ?
5. ከሙሴ ጋር አብሮት የሄደ ማነው?
6. ሙሴ በደመናው ውስጥ ስንት ጊዜ ቈየ?
7. እግዚአብሔር ሙሴን የጠራው ከስንት ቀን በኋላ ነው?
8. እስራኤላውያን በምን ምክንያት ትዕግሥት አጡ?



9. ትዕግሥት አጥተው ምን አደረጉ?
10. አሮን እስራኤላውያንን ምን እንዲያደርጉ ጠየቃቸው?
11. ከዚያስ በኋላ አሮን ምን አደረገ?
12. በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን ምን አለው?
13. ሙሴ እግዚአብሔርን የለመነው ምንድነው?
14. ሙሴ ወደ ሕዝቡ ሲመለስ ምን አደረገ?
15. ሙሴና ኢያሱ ድምፅ ሲሰሙ ምን ተባባሉ?
16. ሙሴ ሌዋውያንን ምን ብሎ አዘዛቸው?
17. እግዚአብሔር ለሙሴ ስሞቻቸውን ከመዝገቤ የምደመስሰው ኃጢአት በመሥራት ያሳዘኑኝን ሰዎች ነው ያለው በምን ምክንያት ነው?
18. ሙሴ ሌሎች ሁለት ጽላቶችን እንዲሠራ የታዘዘው በምን ምክንያት ነው?
19. ሙሴ በሲና ተራራ ላይ ስንት ጊዜ ቈየ?
20. ሙሴ ከሲና ተራራ ላይ ሲመለስ በፊቱ ምን ምልክት ታየ?
21. ኦሪት ዘሌዋውያን ምን ትምህርት ይገኝበታል?
22. በኦሪት ዘሌዋውያን ከሚገኙት የመሥዋዕት ዐይነቶች ሦስቱን ጥቀስ፡
23. የአሮን ልጆች ናዳብና አቢሁ ለምን ተቀሠፉ?
24. የኢየሩሳሌም ጉባኤ ምክንያት ምን ነበር?
25. የጉባኤውን ሂደቶች በአጠቃላይ ግለጥ።
26. በጉባኤው ውሳኔ መሠረት አራቱ የተከለከሉ ነገሮች ምን ምን ነበሩ?
27. ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ወደ አንጾኪያ የተላኩት ሁለት ሰዎች ማንና ማን ናቸው?
28. በዕብራውያን መልእክት አጻጻፍ ሁለቱ አስተያየቶች ምንና ምን ናቸው?
29. ሁለቱ አስተያየቶች በየበኩላቸው የሚያቀርቡአቸው ማስረጃዎች ምን ምን ነበሩ?
30. የዕብራውያን መልእክት ስንት ምዕራፎች አሉት?
31. የኦሪቱ ሕግ በመላእክት የተሰጠ ለመሆኑ አይሁድ በሚያቀርቡት ትምክሕት ላይ ምን መልስ ተሰጠ?
32. በሙሴ ላይ ስለሚያደርጉት ትምክሕትስ ምን መልስ ተሰጠበት?
33. የሌዊ ነገዶች በሆኑት ካህናት ላይ ስለሚደረገው ማሞገስ ምን መልስ ተሰጠበት?
34. በአምልኮ ሥርዐቶቹ ረገድ ምን መልስ ተሰጠበት?



www.ethiopianorthodox.org

35. እስራኤላውያን በምድረ በዳው ጉዞአቸው ጊዜ ምን እንክብካቤ ተደረገላቸው?

36. ዐሥሩ ትእዛዛት በሁለት ክፍሎች የሚከፈሉት በምንና በምን ነው?

37. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሚሰጣቸው ሕጎችና ትእዛዞች ለምን የታቀዱ ናቸው?

38. ዐሥሩ ትእዛዛት በመጀመሪያ በጽሑፍ የቀረቡት እንዴትና መቼ ነው?

39. እስራኤላውያን ከወርቅ ጣዖት አምልኮ ኃጢአታቸው እንዴት ይቅርታ አገኙ?

40. ሙሴ ሁለት ምክንያቶችን በማቅረብ ጸለየ፤ ምክንያቶቹ ምንና ምን ናቸው?

41. ሙሴ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን የትኛውን ክብር ነው እንቢ ያለው?

42. በምትኩ ግን ምንን ለምነ?

43. ለኢየሩሳሌም ጉባኤ ያበቃው የሰይጣን ውጊያ ምን ነበር?

44. አንዳንድ ጊዜ ሰይጣን በተሰብሳቢዎች መካከል እየገባ ምን ያደርጋል?

## ምዕራፍ 3

# ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ

## የጌታችን ትምህርት

ጌታችንና ዘኬዎስ ፦ በኢያሪኮ ከተማ የሚኖር አንድ ዘኬዎስ የተባለ የቀራጮች አለቃ ነበር። ይህም ሰው ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰምቶ እርሱን ለማየት ይመኝ ነበር። አንድ ጊዜ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢያሪኮ በኩል የሚያልፍ መሆኑን ሰማ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ብዙ ሰዎች ይከተሉት ስለነበረና ዘኬዎስ ደግሞ ቁመቱ አጭር ስለነበረ ምን ማድረግ ይሻለኛል ብሎ ማሰብ ጀመረ። በዚህ ጊዜ አንድ መላ ተከሠተለትና እንዲህ አለ። ይህን ብዙ ነገር ያደርጋል የሚሉትን ኢየሱስን የግድ ማየት አለብኝ። ከሚያልፍባቸው መንገዶች በአንድ ቦታ ቆሜ ብጠብቅ ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ በዚህ በአጭር ቁመቴ ላይው አልችልም። ስለዚህ የሚያልፍበትን መንገድ ካየሁ በኋላ ከእርሱ ቀድሜ እሄድና ወደ አንድ ዛፍ ላይ ወጥቼ በመቈየት ላየው እችላለሁ ብሎ ዐቀደ። በዚህም መሠረት ጌታችን የሚያልፍበትን አቅጣጫ ካስተዋለ በኋላ ወደፊት ሮጦ ሄደና ወደ አንድ የሾላ ዛፍ ላይ ወጥቶ ይጠባበቅ ጀመር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘኬዎስ ይጠብቅበት ወደ ነበረው ዛፍ አጠገብ ሲደርስ ቀና ብሎ ተመለከተና ዘኬዎስ ሆይ፥ «ዛሬ በአንተ ቤት መዋል ይገባኛልና ፈጥነህ ከዛፉ ውረድ» አለው። ዘኬዎስም በፍጥነት ከዛፉ ወርዶ ጌታችንን በቤቱ ተቀበለው። ይህን የተመለከቱ ሰዎች ሁሉ ይህ ሰው ወደ ኃጢአተኛ ቤት ሊጋበዝ ገባ ብለው በጌታችን ላይ አጕረመረሙ። ዘኬዎስ ግን ቆሞ ጌታችንን እንዲህ አለው:- «ጌታ ሆይ፥ እነሆ ካለኝ ሀብት ሁሉ እኩሌታውን ለድኾች እሰጣለሁ፤ በማታለል ከሰው ላይ የወሰድሁት ገንዘብ ቢኖር አራት እጥፍ አድርጌ እመልሳለሁ።» በዚህ ጊዜ ጌታችን እንዲህ አለ:- «ይህ ሰው የአብርሃም ዘር ነውና ዛሬ ደኅንነት ለዚህ ቤት ሆኗል፤ የሰው ልጅም የመጣው የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው (ሉቃ:ም:19ቊ:1–10)።



ጌታችና ዘኬዎስ (ሉቃ 19፡ 1-10)

የጌታች ተከታዮች ምን መሆን አለባቸው? አንድ ጊዜ አንድ የሙሴ ሕግ መምህር ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ መጥቶ:- «መምህር ሆይ ወደምትሄድበት ሁሉ ልከተልህ» አለው። ጌታችን ግን ለቀበሮዎች ጕድጓድ አላቸው፤ ለሰማይ ወፎችም የሚያርፉበት ጎጆ አላቸው፤ የሰው ልጅ ግን ራሱን አስጠግቶ የሚያሳርፍበት ቦታ የለውም» ብሎ መለሰለት።

ሌላውን ሰው ግን ተከተለኝ አለው። ይሁን እንጂ ሰውዬው:- «ጌታ ሆይ፥ መጀመሪያ ሄጄ አባቴን ጦሬ እንድቀብር ፍቀድልኝ» አለው። ጌታችንም ሙታንን ተዋቸው ሙታናቸውን ይቅበሩ፤ አንተ ግን ሂድና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት አስተምር አለው።


www.ethiopianorthodox.org

አንድ ሌላ ሰው ደግሞ:- «ጌታ ሆይ፥ እኔ ልከተልህ እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን መጀመሪያ ሄጄ ቤተሰቤን እንድሰናበት ፍቀድልኝ» አለው። ጌታችን ግን «ለማረስ በእጁ ዕርፍ ይዞ ወደኋላ የሚመለከት ሰው ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም ብሎ መለሰለት።

በሌላ ጊዜ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው:- «ሊከተለኝ የሚወድድ ቢኖር ራሱን ይካድ፤ በየቀኑም መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ፤ ከእኔ ይልቅ ለሕወቱ የሚሳሳ ሁሉ ያጠፉታል፤ ስለእኔ ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ግን ያድናታል። ሰው የዓለምን ሀብት ሁሉ ቢያገኝ ነፍሱን ግን ቢያጠፉ ምን ይጠቅመዋል? በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ የሰው ልጅም በራሱ ክብርና በአባቱ ክብር፥ እንዲሁም በመላእክቱ ክብር በሚመጣበት ጊዜ በእርሱ ያፍርበታል (ማቴ:ም:8ቍ:18–22)።

## <u>የጌታችን ተአምራት</u>

<u>የዐሥር ለምጻሞች መፈወስ</u>:- አንድ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ እግረ መንገዱን በሰማርያና በገሊላ በኩል ያልፍ ነበር። በዚያም በኩል ሲያልፍ ወደ አንዲት መንደር ደረሰ። በዚያችም መንደር ዐሥር ለምጻሞች ወደ እርሱ መጥተው ራቅ ብለው ቆሙ። በቆሙበትም ቦታ እንዳሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ጌታ ሆይ፥ እባክህ ራራልን ብለው ጮኹ። ጌታችንም መሐሪና ርኅሩኅ ነውና ራርቶላቸው ሂዱና ሰውነታችሁን ለካህን አሳዩ ብሎ አዘዛቸው። ሰውነታቸውን ለካህን ለማሳየት እየሄዱ ሳለ ከለምጻቸው ነጹ። ከእነርሱ አንዱ ከለምጽ በሽታው መዳኑን ባየ ጊዜ ወደ ጌታችን ተመልሶ በእግሩ ሥር በግንባሩ በመደፋት ምስጋናውን አቀረበ። ይህም እንደዚህ ያደረገው የሰማርያ ሰው ነበር። ጌታችንም ይህን በከፍተኛ ድምፅ እግዚአብሔርን እያመሰገነ የተመለሰውን ሰው ተመልክቶ ከለምጽ በሽታ የነጹት ሰዎች ዐሥር አልነበሩምን? እግዚአብሔርን ለማመስገን የመጣ ይህ የባዕድ አገር ሰው ብቻ ነውን? ዘጠኙስ የት አሉ? አለ።

ከዚያ በኋላ ጌታችን ያን ሰው ተነሥና ሂድ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው (ሉቃ:ም:17ቍ:11–19)።

<u>የአልዓዛር ከሞት መነሣት</u>:- ቢታንያ በምትባል መንደር የሚኖሩ ማርታና ማርያም የተባሉ እኅትማማች አልዓዛር የተባለ ወንድም ነበራቸው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዚያ ቤተሰብ በጣም የቅርብ ወዳጅ ነበር። ጌታችን ከቢታንያ ራቅ ብሎ ሄዶ በነበረበት ጊዜ አልዓዛር በጠና ታመመ። ማርታና ማርያም ወንድማቸው መታመሙን የሚነግር መልእክተኛ ወደ ጌታችን ላኩ። እርሱ ግን ከተላከበት በኋላ ዋለ ዐደረ እንጂ በፍጥነት አልሄደም። በዚህ ጊዜ አልዓዛር ሞተ። ጌታችንም አልዓዛር ከሞተ ከአራት ቀን በኋላ ወደ ቢታንያ መጣ። ይህም በመሆኑ ማርታና ማርያም ስለወንድማቸው ስለ አልዓዛር በፍጹም ተስፋ ቈርጠው ስለነበረ ወደ ጌታችን ቀርበው:- «አንተ በዚህ ብትሆን ኖሮ ወንድማችን ባልሞተ{ም} ነበር» በማለት የተ{ሰ}ፋ መቍረጥ ንግግር ተናገሩ። እርሱም አይዞአችሁ ወንድማችሁ ከሞት ይነሣል ብሎ ቃል ገባላቸው። እነርሱ ግን ስለትንሣኤ ሙታን ትምህርት የሚነግራቸው መሰላቸው እንጂ አሁን እርሱ የሚያስነሣው መሆኑ አልገባቸውም ነበር። ማርታ ወንድምሽ ከሞት ይነሣል ባላት ጊዜ አዎ ጌታ ሆይ፥ በመጨረሻው በትንሣኤ ጊዜ ከሞት እንደሚነሣ ዐውቃለሁ አለችው። እርሱም ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚያምን ቢሞት እንኳ በሕይወት ይኖራል፤ በሕይወት የሚኖርና በእኔም የሚያምን ሁሉ ከቶ አይሞትም አላት። እርስዋም አዎ ጌታ ሆይ፥ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው መሲሕ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንህን አምናለሁ» አለች። ከዚያም በኋላ ማርያም መጥታ በጌታችን እግር ሥር ወደቀችና በዚያው ተስፋ በቈረጠ አነጋገር ጌታ ሆይ፥ አንተ እዚህ ብትሆን ኖሮ ወንድሜ ባልሞተም ነበር አለችው። ጌታችንም ማርያምና አብረዋት የነበሩት ሰዎች ሲያለቅሱ ባየ ጊዜ በመንፈሱ አዘነና እንባውን አፈሰሰ። ከዚያም በኋላ አልዓዛር የተቀበረበትን ቦታ ጠየቀና ወደዚያ ሄደ። እዚያም ሄዶ ድንጋዩን አንሡት አለ። ጌታችን ድንጋዩን አንሡት ባለ ጊዜ ማርታ ከሞተ አራት ቀኑ ስለሆነ ይሸታል አለችው። ጌታችንም ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር እንደምታዩ አልነገርኩሽምን አላት። ጌታችንም ወደ አባቱ ከጸለየ በኋላ አልዓዛር ና ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። በዚህ ጊዜ ሟቹ በመገነዣው እንደተጠቀለለ ከመቃብር ወጣ። ጌታችም ፍቱትና ይሂድ አላቸው (ዮሐ:ም:11ቍ1–44)።



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አልዓዛርን ከሞት እንዳስነሳው ( ዮሐ. ም 11)።

<u>የሹሙ ልጅ መፈወስ</u>:- በቅፍርናሆም አንድ የመንግሥት ሹም ልጁ በጠና ታሞበት ነበር። ጌታችን ከይሁዳ ወደ ገሊላ መምጣቱን ስለሰማ ወደ እርሱ ሄዶ ልጄ በጠና ስለታመመብኝ እባክህ መጥተህ ፈውስልኝ ብሎ ለመነው። ጌታችንም እናንተ መቼም ተአምራትና ድንቅ ነገር ካላያችሁ በቀር አታምኑም አለው። ሹሙ ግን ጌታ ሆይ፥ እባክህ ልጄ ሳይሞት በቶሎ ሄደህ ፈውስልኝ አለው። ጌታችንም ልጅህ የዳነ ስለሆነ ወደቤትህ ሂድ አለው። በዚህ ጊዜ

www.ethiopianorthodox.org

ሰውዬው ጌታችን የተናገረውን አምኖ ሄደ። ወደ ቤቱ ለመሄድ በመንገድ ላይ እያለ አገልጋዮቹ አገኙትና ልጁ መዳኑን ነገሩት ። እርሱም የዳነበትን ሰዓት ጠየቃቸው። እነርሱም ትናንትና በሰባት ሰዓት ትኩሳቱ ለቀቀው አሉት። ጌታችን ልጅህ ድኖአል ያለው በዚያን ሰዓት ነበር። ስለዚህም ከዚያን ቀን ጀምሮ እርሱና ቤተሰቡ በጌታችን አመኑ (ማቴ:ም:8ቍ:5–13)።

## የጌታችን ምሳሌዎች

የሚያድግ ዘር:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለመንግሥተ ሰማይ ከተናገራቸው ምሳሌዎች መካከል የሚያድግ ዘር ምሳሌ ይገኝባቸዋል። ምሳሌውም እንዲህ የሚል ነው:- የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ ዘር የሚዘራውን ሰው ትመስላለች። ሰውዬው ሌሊት ይተኛል፤ ቀንም ይነቃል፤ እንዴት እንደሆነም ሳያውቅ ዘሩ ይበቅላል፤ ያድጋልም። ምድሪቱም በገዛ ራስዋ በመጀመሪያ ቡቃያውን፥ ቀጥሎም ዛላውን ታሳያለች። በኋላም በዛላው ፍሬ ይገኛል። ሰብሉም በደረሰ ጊዜ መከር በመሆኑ ሰውዬው ወዲያውኑ ማጭድ ያዘጋጃል (ማር:4፥26–29)።

ስውር መብራት:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተናገራቸው ምሳሌዎች መካከል ቀጥሎ ያለው አንዱ ነው። «ሰው መብራትን አብርቶ በእንቅብ ውስጥ ወይም በአልጋ ሥር ያስቀምጠዋልን? የሚያስቀምጠው ብርሃኑ በሚታይበት በመቅረዝ ላይ አይደለምን? እንዲሁም የተሸሸገ ሳይገለጥ፥ የተሰወረም ሳይታወቅ አይቀርም። እንግዲህ ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ። ስለምትሰሙት ነገር ተጠንቀቁ፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ለእናንተም ይሰፈርላችኋል፤ በይበልጥም ይጨመርላችኋል። ላለው ይሰጠዋል፤ ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል (ማቴ:5፥14–16)።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢያሪኩ በደረሰ ጊዜ የተገናኘው ማንን ነው? የተገናኘው ተራ ቀራጭ ሳይሆን የቀራጮችን አለቃ ነው። ቀራጮች በአይሁድ ዘንድ በጣም የተጠሉ ነበሩ። ለዚህም በሕዝብ ዘንድ ለነበረው የጥላቻ ስሜት ሁለት ምክንያቶች ይሰጣሉ። የመጀመሪያው ምክንያት በዚያን ጊዜ የአይሁድ ሕዝብ የሚገዛው በሮማውያን ነበር። ሮማውያንም ቅኝ ገዢዎች ስለነበሩ በአይሁድ ዘንድ በጣም የተጠሉ ነበሩ። ቀራጮች የእነርሱ ተቀጣሪዎች በመሆናቸው የጠላት፥ ያውም የጣዖት አምላኪ ተባባሪዎች ናቸው በመባል ይጠሉ ነበር። ሌላው የሚጠሉበት ምክንያት ደግሞ ለራሳቸው ሀብት ለማካበት ብለው በመንግሥት ከተፈቀደላቸውና ከታዘዙት በላይ ሕዝቡን አስገድደው ያስከፍሉ ነበር። በእነዚህም ምክንያቶች ቀራጮች በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ በጣም ኃጢአተኞች እንደሆኑ ተደርገው ይታሰቡ ነበር። በዚህም ምክንያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቀራጮች ጋር በተገናኘ ቍጥር የኃጢአተኞች ወዳጅ ሆነ ተብሎ በአይሁድ ይወቀስ ነበር። የቀራጮች አለቃ



www.ethiopianorthodox.org

የነበረው ዘኬዎስ ያን በሕዝብ ዘንድ ስሙ እየገነነ የመጣውን ጌታችንን ኢየሱስን የማየት ፍላጎት ዐደረበት። በዚህም ምክንያት ለእርሱ እንደመሰለው በዛፍ ላይ ወጥቶ እርሱ ሳይታይ ለማየት ሞከረ። ጌታችን ግን ምንም ከዚያ በፊት ያልተገናኘው ቢሆን በዛፉ አጠገብ ሲደርስ ራሱን ቀና በማድረግ በስሙ ጠርቶ ዘኬዎስ ሆይ፥ እኔ ዛሬ በቤትህ መዋል ይገባኛልና ፈጥነህ ውረድ አለው። ይህም የሚያመለክተው ጌታችን ለዐዋቂነቱ ውሱንነት የሌለው መሆኑን ነው። አንደኛ ያ ሰው ዘኬዎስ የሚባል ስም እንዳለው፥ ሁለተኛ በሾላው ዛፍ ላይ ወጥቶ ተቀምጦ የነበረ መሆኑ፥ ሦስተኛ ዘኬዎስ በኃጢአቱ ተጸጽቶ ከልቡ የተመለሰ መሆኑን ሁሉን ዐዋቂው ጌታችን ዐወቀው። ፈጥነህ ከዛፉ ላይ ውረድ ባለው ጊዜ ፈጥኖ ወርዶ በደስታ ጌታችንን በቤቱ ማስተናገዱ የሚያመለክተው ነፍሱን፥ ልቡን፥ ኅሊናውንና ስሜቱን አድሶ በጌታችን አማካይነት ለንስሓ የተዘጋጀ መሆኑን ነው። ከጌታችን ጋር የነበሩት ሰዎችም ሁሉ ከአስተሳሰባቸው ጒድለት የተነሣ ወደ ኃጢአተኛ ቤት ተጋብዞ ገባ ብለው አጒረመረሙ። እነርሱ በዚህ ዐይነት በጌታችን ላይ በሚያጒረመርሙበት ጊዜ ጌታችን በሉቃስ ወንጌል ም:15 ቍ:3–7 ባቀረበው የመቶ በጎች ምሳሌ ንስሓ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሓ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል ያለውን አባባል ትክ ብለው አልተመለከቱትም ማለት ነው። የቀራጮቹ አለቃ ዘኬዎስ ግን ቆሞ:- ጌታ ሆይ፥ ካለኝ ሁሉ እኩሌታውን ለድኾች እሰጣለሁ፤ ማንንም በሐሰት ከስሼ አንዳች ነገር ወስጄበት ከሆነ አራት እጥፍ እከፍላለሁ አለ። ይህም አባባሉ ለኃጢአቱ ኑዛዜ ነበር። ጌታችንም ዛሬ ለዚህ ቤት ደኅንነት ሆነ አለ። የዘኬዎስ አባባልና የጌታችን መልስ የሚያመለክቱት የዘኬዎስ ንስሓ ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ነው።

የንስሓ መሠረቶች አራት ናቸው። የመጀመሪያው ስላለፈው ኃጢአት ከልብ መጸጸት፥ ይኸውም በኃጢአት ተግባር ላይ የዋለውን ያለፈውን የራስ ማንነት መናቅና ኃጢአትን መጥላት፥ ሁለተኛው ስምንና ዝናን ለማደስ ቍርጥ ሐሳብ ማድረግ፥ ሦስተኛ የሰውን ጸሎት ሰምቶ ፈጻሚነቱ እርግጠኛ በሆነው በእግዚአብሔር መተማመን፥ በመሐሪነቱና ንስሓ ለሚገቡም ይቅርታ የሚያደርግ በመሆኑ መተማመን፥ አራተኛ ከልብና በአንደበትም ኃጢአትን መናዘዝ፥ በካህን አማካይነት ለእግዚአብሔር መናዘዝ፥ ከዚሁም ጋር ለንስሓው አስፈላጊ የሆነውን ተግባር ለመፈጸምና ኀላፊነቱን ለመቀበል ዝግጁ መሆን፥ ኃጢአትን በተግባር ማረምና ውጤቱን መቀበል ናቸው።

እነዚህ አራት የንስሓ መሠረቶች በዘኬዎስ ንስሓ ውስጥ ተትረፍርፈው ይገኛሉ። በኃጢአቱ ተጸጽቶአል፥ ስሙንና ዝናውን ለማደስ ቍርጥ ሐሳብ አድርጎአል፤ ጌታችንም እንደሚቀበለው በደስታ ሙሉ ተስፋ አድሮበታል። ካለው ሀብት ግማሹን ለድኾች በመስጠትና ያታለለውም ሰው ካለ አራት እጥፍ በመክፈል የንስሓውን ግዴታ ለመቀበል ዝግጁነቱን ገልጦአል። በዘኬዎስ ንስሓ ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታም ካህንም ሆኖአል። እንደካህንነቱ

የዘኬዎስን ኑዛዜ አዳምጦአል፤ እንደ አምላክነቱ ድኅነት ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖአል በማለት ለኃጢአት ይቅርታ አድርጎአል። ጌታችን ለዚህ ቤት መዳን ሆነ ባለ ጊዜ ጌታችን ሞቶ የአዳኝነት ቤዛነቱን ከማከናወኑ በፊት ዘኬዎስ ድኅነትን አገኘ ማለት ሳይሆን ዘኬዎስ ለመዳን የተገባ ሆነ ማለት ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በመንገድ ላይ ሲሄድ ሳለ አንድ የሕግ መምህር ወደ እርሱ መጥቶ በምትሄድበት ሁሉ ልከተልህ አለው። ያ የሕግ መምህር ጌታችንን ልከተልህ ያለው ብዙዎች ሰዎች ሲከተሉት አይቶና እርሱንም በመከተል ዓለማዊ ጥቅም የሚያገኝ መስሎት ነው። ጌታችን ልብ ያሰበውን ጠልቆ የሚያውቅ በመሆኑ ለቀበሮዎች ጉድ ጓድ፥ ለሰማይ ወፎችም የሚያርፉበት ጎጆ አላቸው፤ የሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያሳርፍበት ቦታ የለውም ብሎ መልስ ሰጠው በዚህም አባባሉ የሰውዬው አስተሳሰብ ከጌታችን ተልእኮ ጋር ስለማይስማማ ሊያባርረው ፈልጎ ነው። እንዲሁም የእርሱ ሀብት መንፈሳዊ እንጂ ሥጋዊ፥ ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ አለመሆኑን አመልክቶአል። በሌላ በኩል ደግሞ የእርሱ ሀብት በተወሰኑ ንብረቶች የሚቈጠር ሳይሆን ዓለሙ ሁሉ የእርሱ መሆኑን ለማመልከትና በአንድ በተወሰነ ቦታ ብቻ የማይኖር መሆኑን ለመግለጥ የሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያሳርፍበት ቦታ የለውም ብሎታል። የእርሱ ያልሆነ ምንም የለም ለማለት ነው።

ጌታችንም ለተከታይነት ብቃት ያልነበረውን የዚህኛውን ሰው ተከታይነት አይቀበል እንጂ ለተከታይነት ተገቢ ሆኖ ያገኘውንና እርሱ ራሱ የመረጠውን ሰው ግን ተከተለኝ ብሎታል። ይህኛው ሰው:- ጌታ ሆይ፥ እባክህ ፍቀድልኝና አባቴን ቀብሬ ልምጣ አለው። እርሱም ምናልባት አባቱ በዚያን ጊዜ ሞቶአል፤ ወይም በጣም አርጅቶ ስለነበረ እስኪሞት ድረስ ልጡረው ማለቱ ነው። በዚህም ሆነ በዚያ ይህ ድርጊት በጎ ተግባር መሆኑ አይካድም። ነገር ግን ጌታችን ሙታንን ተዋቸው ሙታናቸውን ይቅበሩ፤ አንተ ግን ሄደህ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት አስተምር ሲለው የተጠራበት አገልግሎት ከማንኛውም ከሌላ አገልግሎት ማለት ለምድራዊ አባቱ ከሚሰጠው አገልግሎት ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል ማለቱ ነው። ሙታንን ተዋቸው ሙታናቸውን ይቅበሩ ሲል በመንፈስ ሙታን የሆኑት በሥጋ የሞቱትን ይቅበሩ፤ ወይም በሌላ አባባል ለምድራዊ ነገር የሚጨነቁት ሰዎች እንደሞቱ የሚቈጠሩ ናቸውና በሥጋ የሞቱትን ይቅበሩ ለማለት ነው። ስለ መንግሥተ ሰማይ ማስተማርን ለመሰለ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለሚያስጠው ሰማያዊ ተግባር ምንም ያኽል መሥዋዕትነት የሚከፍሉ ቢሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመርጣቸው ከማንኛውም ሌላ ነገር ሁሉ ራሳቸውን አግልለው ለጥሪው ብቻ ራሳቸውን የተለዩ ማድረግ ይኖርባቸዋል ማለት ነው።

ሌላው ሰው ደግሞ ልከተለህ እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን አስቀድሜ ቤተሰቤን ተሰናብቼ እንድመጣ ፍቀድልኝ አለው። ይህም ሰው ቤተሰቡን ተሰናብቶ ለመምጣት ማሰቡ በጎ ተግባር እንጂ ክፉ ተግባር አይደለም። ጌታችን ግን ያ



ሰው የተጠራበት ተልእኮ ከሌላ ከማንኛውም ተግባር የላቀ መሆኑንና ሰማያዊ አገልግሎትን የመረጠ ሰው ለዚያ ሲል ምድራዊ አገልግሎትን ሁሉ መተው ያለበት መሆኑን ለማመልከት ብሎ ለማረስ በእጁ ዕርፍ ይዞ ወደ ኋላ የሚመለከት ሰው ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም ሲል መልስ ሰጥቶታል።

እንዲሁም ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱና ለሌሎችም እኔን ለመከተል የሚፈልግ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ ብሎአቸዋል። ይህም ማለት የጌታችን ተከታይ ለመሆን የሚፈልግ ሰው ሥጋዊ ፍላጎቱን ሁሉ መግታት አለበት ለማለት ነው። ስለምድራዊ ሕይወቱ ምንም መጨነቅ አይኖርበትም። መስቀሉን መሸከም አለበት ማለት ነው። ምድራዊ ሕይወቱ ማለት ሥጋዊ ሕወቱን ለማዳን ብሎ ሰማያዊ ሕይወቱን ማጣት የለበትም። መስቀሉን መሸከም አለበት ማለት ለሰማያዊው ሕይወት ሲባል ሕማማትን ችግርንና መሥዋዕቶችን ችሎ መኖር አለበት ማለት ነው።

አንድ ጊዜ ጌታችን በሰማርያና በገሊላ በኩል አድርጎ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ወደ አንዲት መንደር ውስጥ ደረሰ። እዚያም ዐሥር ለምጻሞች አገኙትና ድምፃውን ከፍ አድርገው እባክህ ራራልን እያሉ ጮኹ። ጌታችንም ባያቸው ጊዜ ራራላቸውና ሄዳችሁ ራሳችሁን ለካህን አሳዩ አላቸው። እነርሱም በትእዛዙ መሠረት ሲሄዱ ሳለ ከለምጹ በጊዜ በመዳናቸው ከእነርሱ አንዱ ጌታችንን ለማመስገን ወደኋላ ተመለሰ። ጌታችንም በወቀሳ መልክ የዳኑት ዐሥር አልነበሩምን? ዘጠኙ የት አሉ? እግዚአብሔርን ለማመስገን የአይሁድ ወገን ካልሆነ ከዚህ በቀር ተመልሶ የመጣ የለምን? አለ።

ከዚህ ተአምርና ከጌታችን አነጋገር የምንማረው ምንድነው?

አንደኛ እምነት ለድኅነት ምክንያት ከሚሆኑ መሠረቶች አንዱ መሆኑን እንማራለን። እነዚያ ለምጻሞች መምህር ሆይ፥ እባክህ ራራልን ብለው መለመናቸው እርሱ ከፈቀደ ሊያድናቸው የሚችል መሆኑን እንዳመኑ ያመለክታል። ወደ ካህን ሄደው ራሳቸውን እንዲያሳዩ በታዘዙ ጊዜ ያለምንም ማወላወል መሄዳቸው እምነታቸውን ያመለክታል። ይሁን እንጂ በእዚህ በእምነታቸው ውስጥ ተግባርም ታክሎበታል። ወደካህን ሄዳችሁ ራሳችሁን አሳዩ ተብለው የታዘዙትን ትእዛዝ ባያከብሩ ኖሮ ባልዳኑም ነበር።

ሁለተኛ ጌታ በዚህ ዓለም ላይ በነበረበት ዘመን ሁሉ ሕገ ኦሪትን እየፈጸመ የኖረ መሆኑን የሚያመለክተው በኦሪቱ ሕግ አንድ ለምጽ የያዘው ሰው ከለምጽ በሽታው የዳነ መሆኑ የሚረጋገጠው በካህን ምስክርነት ስለነበረ እነዚያን ዐሥር ለምጻሞች ሄዳችሁ ራሳችሁን ለካህን አሳዩ ማለቱ ነው (ዘሌ:ም:14ቁ1–14፥ ገላ:ም:4ቍ:4)።

ሦስተኛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዳኑት ዐሥር ለምጻሞች መካከል እግዚአብሔርን ለማመስገን ተመልሶ የመጣው አንድ ብቻ በመሆኑ ቅሬታውን የገለጠው እግዚአብሔር ለሚያደርግልን ድርጊት ሁሉ ምስጋና ማቅረብ እንደሚገባን ሊያስተምረን ብሎ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

የቢታንያው አልዓዛር ታሞሞ እኅቶቹ ማርያምና ማርታ መጥቶ እንዲፈውሰው ወደ ጌታችን በላኩበት ጊዜ የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ እንዲከብርበት ለእግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ይህ ሕመም ለሞት አይደለም ብሎአል። የአልዓዛር መታመምም መልእክት ከመጣለት በኋላ ዘገየ እንጂ በፍጥነት ተነሥቶ አልሄደም። ይህንንም ማድረጉ የሚወድደውን አልዓዛርን ችላ በማለት፥ የእኅቶቹ ጭንቀት ሰይሰማው ቀርቶ ሳይሆን ለበለጠና ለተሻለ መለኮታዊ ዕቅድ ነው። ከፍተኛ ተአምር በማድረግ ብዙዎች እንዲያምኑና የደቀ መዛሙርቱም እምነት እንዲጠናከር ነው።

ወዳጃችን አልዓዛር አንቀላፍቶአል፤ እኔ ግን ከእንቅልፉ ላስነሣው እሄዳለሁ ሲል የዚህ ዓለም ሞት በመጨረሻው ዘመን ለመነሣት እንደ እንቅልፍ መሆኑን ያመለክታል። እንዲሁም ሞት በዚያን ጊዜ ሰው ከሥጋዊ ስሜት የሚላቀቅበትና ነፍስም በዚያን ጊዜ የምድራዊ ፍላጎት መሣሪያ ከመሆን የምታርፍበት ጊዜ በመሆኑ ምድራዊ ሞት አንድ የእንቅልፍ ዐይነት ነው። በመጨረሻው ዘመን ግን መንቃት አለ (ትንሣኤ ሙታን)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን እንቅልፍ ሲለው ይህ የመጀመሪያው ጊዜ አይደለም። የኢያኢሮስ ልጅ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም ብሎአቸዋል (ሉቃ :ም :8ቍ:52)።

ጌታችንም የአልዓዛር እኅቶችና ሌሎችም ሰዎች ሲያለቅሱ ባየ ጊዜ አዘነና አለቀሰ። እዚህ ላይ የጌታችንን ሥጋዊና መለኮታዊ ባሕርይ እናስተውላለን። ምንም እንኳ ከሞተና ከተቀበረ አራት ቀኖች ያለፈውን አልዓዛርን ከሞት የሚያስነሣው መሆኑን ቢያውቅ፥ በመለኮታዊ ኃይሉም ከሞት ሊያስነሣው እንደሚችል ምንም የሚያጠራጥር ነገር ባይኖር፥ በተወዳጅ ድንገተኛ ሞት ጊዜ ሊከሠት የሚችለውን ጥልቅ ስሜት በእርሱ ዘንድ እናያለን። ወዳጃችን አልዓዛር አንቀላፍቶአልና ሄጄ አስነሣዋለሁ ያለው ጌታችን የአልዓዛር እኅቶች ሲያለቅሱ ባየ ጊዜ በመንፈሱ አዘነና አለቀሰ።

ወዴት ነው የቀበራችሁት የሚለው ጥያቄ ተራ ጥያቄ አልነበረም። ይህ ጥያቄ የሚያመለክተው አልዓዛር በሞተ ጊዜ ጌታችን በዚያ እንዳልነበረና የተቀበረበትን ቦታ እንዳላየውና እንደማያውቀው ሲሆን ይህም ከዮርዳኖስ ማዶ በነበረ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ እኔ እዚያ ባለመሆኔ ስለ እናንተ ደስ ብሎኛል ያለውን ለማረጋገጥ ነው። ከሞተና ከተቀበረ አራት ቀን ሆኖት የነበረ በመሆኑ በአይሁድ ዘንድ ትክክለኛ ተአምር መሆኑ ተረጋግጦአል።

ጌታችን አለቀሰ የሚለውን በምናነብበት ጊዜ የጌታችን ማልቀስ ሰብአዊ ባሕርዩን የሚያመለክት ነውን? ወይስ በኃጢአት ምክንያት በፍጡሩ ላይ በተፈረደው የሞት ፍርድ ምክንያት ለፍጡሩ በማዘን ነውን? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ወይስ ደግሞ ከአዘኑ ሰዎች ጋር የሐዘን ተካፋይነትን ለመግለጥ ይሆን? ከሚያለቅሱ ጋር አልቅሱ (ሮሜ:ም:12ቍ:15)። ወይስ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ነው? ይህም ከሰዎች ጋር በችግራቸውና በሐዘናቸው ጊዜ እንድንተባበር ለእኛ ትምህርት ነው። ይህም ደግሞ የሰው ልጅ ተግባር



ነው። ይህን ስናደርግ በዳግማዊ አዳምነቱ ምሳሌ ስለሆነልን እርሱን እንመስለዋልን (1ኛ ጴጥ:ም:2ቍ:21)።

ድንጋዩን አንሡ ብሎ በትእዛዙ መሠረት ድንጋዩን ካነሡ በኋላ ራሱን ወደ ላይ አቅንቶ አባት ሆይ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ፤ ሁልጊዜም እንደምትሰማኝ ዐውቃለሁ፤ ይህን የምለው እነዚህ በዙሪያ የቆሙት ሰዎች አንተ እንደላክኸኝ ያውቁ ዘንድ ነው። በዚህ አባባሉ ጌታችን ለሚያደርጋቸው ተአምራት ዋንኛው ምክንያት አይሁድ እርሱ ነቢያት የተናገሩለት የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ መሆኑን በተጨባጭ ማስረጃ ተረድተው በእርሱ እንዲያምኑ መሆኑን እንረዳለን። ተአምራቱንም የሚያደርገው በሥልጣኑ ስለነበረ ይህን አባባል ያረጋግጣል። የእግዚአብሔርም ልጅ ስለነበረ የእግዚአብሔር ከሃሊነትና ሌላም ለእግዚአብሔር የሆነ ነገር ሁሉ የእርሱም ነበር። እርሱ እንዳለው:- የአብ የሆነው ሁሉ የእርሱም ነው (ዮሐ:ም:16ቍ:15እና ም:17ቍ:10)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአልዓዛር መቃብር አጠገብ መጸለዩ የተረጋገጠ ነው። ጸሎቱ ግን የልመና ጸሎት አልነበረም፤ ነገር ግን በደቀ መዛሙርቱና በሚሰሙት ሁሉ ፊት ያደረገው ከአብ ጋር እኩልነትን የሚገልጥበት ነበር (ዮሐ:ም:12ቍ:30)። አልዓዛርንም ባስነሣ ጊዜ በሥልጣኑ አስነሣው እንጂ ያን ሥልጣን ከአብ አልጠየቀም።

የገሊላ አውራጃ ገዥ የነበረው የሄሮድስ አንቲፓስ ባለሟል የነበረ አንድ ሹም ልጁ በጠና ታሞበት ነበር። ይህ ሰው ስለ ጌታችን ሰምቶ ስለነበረ ልጁን እንደሚፈውስለት አምኖ ወደ ጌታችን መጣ። ቤቱም የሚገኘው በቅፍርናሆም ስለነበረ ልጁን እንዲፈውስለት ጌታችንን አጥብቆ ለመነው። ጌታችንም እናንተ መቼም ታምራትና ድንቅ ነገሮችን ካላያችሁ አታምኑም አለው። ልጁ የታመመበትም ሰው እባክህ ልጄ ሳይሞት ሄደህ ፈውስልኝ አለው። ይህ የጌታችን አባባል በዚያን ጊዜ የነበሩትን አይሁድን ለመውቀስ የተነገረ ነው። አይሁድ በነቢያት የተነገረለትን የእግዚአብሔርን ልጅ ክርስቶስን ከብዙ መቶ ዓመቶች ጀምረው ይጠባበቁ ነበር። የጌታችንን ሰማያዊ ትምህርት ቢሰሙና የሚያደርጋቸውን ተአምራት ቢያዩም የበለጡ ተአምራትና ድንቅ ነገሮችን ለማየት ከመፈለግ በቀር በአዩትና በሰሙት የማያምኑ በመሆናቸው ወቅሶአቸዋል። የእርሱን ማንነት የሚገልጡትን ትምህርቶቹንና የሚያደርጋቸውን ተአምራት አይተውና ሰምተው አላመኑም። ልጅ የታመመበት ሹምም ወደ ቅፍርናሆም እንዲሄድለት ጌታችንን የሚወተውተው እዚያ ካልሄደ በቀር የሚፈውሰው ስላልመሰለው ነው። ጌታችን ግን ልጅህ ድኖአልና ሂድ አለው። አምኖ ሄደ፤ ልጁም ተፈወሰለት። በዚያን ጊዜ ያ ሰው ከነቤተሰቡ በጌታችን አመነ።

በሚያድግ ዘር ምሳሌ እንደተገለጠው የወንጌል ቃል በደጎና ሰው ልብ ውስጥ ከተዘራ መሬቱ ደጎና እስከሆነ ድረስ ሳይታወቅና ቀስ በቀስ በራሱ



www.ethiopianorthodox.org

መውጣቱና ማደጉ አይቀርም። ጸጋም በሰዎች ልብ ውስጥ መልካም ፍሬዎችን በማፍራት እያደገ መሄዱ አይቀርም።

ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ብርሃን በሆነው ትምህርቱ ይጠቀሙ ዘንድ አዘዛቸው። እነርሱንም የብርሃኑ መገኛ እንዲሆኑ ያደረጋቸው እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ በማለት ነው። በዚህም ትምህርት ሌሎችን እንዲጠቅሙበት አዘዛቸው፤ ከእርሱ ያገኙትንም ትምህርት እንዳይሰውሩ ነገራቸው። ይህም ብርሃን ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚወስደውን መንገድ የሚያሳይ መሆን አለበት። ብርሃኑም ሊደበቅ ስለማይችል በግልጽ ማስተማር ይኖርባቸዋል። ጌታችን የሰጣቸው መመሪያ ይህ እስከሆነ ድረስ እግዚአብሔር የሰጣቸውን የአስተሳሰብና የመንፈሳዊነት ችሎታቸውን ሳይቈጥቡ በማስተማር ሊጠቀሙበት ይገባል። ይህን ካደረጉ ጌታችንም ችሎታውን ይጨምርላቸዋል፤ ያሳድግላቸዋልም። እነርሱ ግን ያን የተሰጣቸውን ችሎታ ምንም የማይሠሩበት ከሆነ ያው የተሰጣቸው ችሎታ እንኳ ይወሰድባቸዋል እንጂ ሌላ አይጨመርላቸውም። ያላቸው እየመሰላቸው የሌላቸው ይሆናሉ። ስለዚህም ነው ጌታችን ላለው ሰው ተጨምሮ ይሰጠዋል፤ የሌለው ግን አለኝ ብሎ የሚያስበው እንኳ ይወሰድበታል ያለው (ሉቃ:ም8:ቍ:18)።

## ጥያቄዎች

1. ዘኬዎስ የነበረበት ከተማ ማን ይባላል?
2. የዘኬዎስ ሥራ ምን ነበር?
3. ዘኬዎስ ምንን ይመኝ ነበር?
4. ምኞቱን እንዳይፈጽም ምን እንቅፋት አጋጠመው?
5. የተከሠተለትስ መላ ምንድነው?
6. ጌታችንስ ከዘኬዎስ ጋር እንዴት ተገናኘ?
7. ዘኬዎስ ለጌታችን ምን አደረገለት?
8. ጌታችንን ከዘኬዎስ ጋር ያዩት ሰዎች ምን አሉ?
9. ዘኬዎስ ለጌታችን ምን ቃል ገባለት?
10. ጌታችንስ ምን አለ?
11. አንድ የኦሪት ሕግ መምህር ጌታችንን ምን አለው?
12. ጌታችን ምን መልስ ሰጠው?
13. ጌታችን ተከተለኝ ብሎ ያዘዘው ሰው ምን አለ?
14. ጌታችንስ ምን መልስ ሰጠ?
15. ልከተልህ እፈልጋለሁ ያለው ሰው ምን አለ?
16. ጌታችንስ ምን መልስ ሰጠው?



17. ሊከተለው የሚወድድ ሰው ምን መሆን አለበት ብሎ ነው ጌታችን የተናገረው?
18. ጌታችን አፍርበታለሁ ያለው በምን ዐይነቱ ሰው ነው?
19. ጌታችን ለምጻሞቹን ያገኘው የት ነው?
20. ለምጻሞቹ ጌታችንን ምን አሉት?
21. ጌታችን ለምጻሞቹን ምን አዘዛቸው?
22. ለምጻሞቹስ በመንገድ ላይ ምን አጋጠማቸው?
23. ከለምጻሞቹ አንዱ ምን አደረገ?
24. በዚያን ጊዜ ጌታችን ምን አለ?
25. ያስ ለምጻም የወዴት አገር ሰው ነበር?
26. ጌታችንስ ለዚያ ለምጻም ምን አለው?
27. አልዓዛር የኖረበት ከተማ ስም ምን ይባላል?
28. አልዓዛር ሲታመም እኅቶቹ ምን አደረጉ?
29. የአልዓዛር እኅቶች ስም ማንና ማን ነበር?
30. አልዓዛር መታመሙን ሲሰማ ጌታችን ወዲያውኑ ፈጥኖ መጣን?
31. ጌታችን ወደ ቢታንያ ሲመጣ አልዓዛር ከሞተና ከተቀበረ ስንት ቀን ሆኖት ነበር?
32. አልዓዛር የሚነሣ መሆኑን ጌታችን ሲነግራት ማርታ ምን አለች?
33. ጌታችንስ ምን መለሰላት?
34. ከዚያስ በኋላ እርስዋ ምን አለች?
35. ጌታችን ያለቀሰው ምን ባየ ጊዜ ነው?
36. ጌታችን አልዓዛርን ያስነሣው እንደምን አድርጎ ነው?
37. ልጁ በጠና የታመመበት ሰው ማን ነበር?
38. ቤቱ ምን በሚባል ሰፈር ነበር?
39. ወደ ጌታችን መጥቶ ምንን ለመነው?
40. ጌታችንስ ምን አለው?
41. በኋላስ ምን አደረገለት?
42. ሰውዬውና ቤተሰቡ በጌታችን ያመኑት በምን ምክንያት ነው?
43. የሚያድግ ዘር ምሳሌ ተናገር።
44. ስለ ስውር ምብሬት ተናገር።
45. ቀራጮች በአይሁድ ዘንድ ለምን ይጠሉ ነበር?
46. ዘኬዎስ በንስሓ መመለሱን የሚያመለክተው በምንድነው?



www.ethiopianorthodox.org

47. አራት የንስሓ መሠረቶች ምን ምን ናቸው?

48. ጌታችን ልከተልህ ያለውን ሰው እንዲከተለው ያልፈቀደለት በምን ምክንያት ነው?

49. እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባን ለማመልከት ጌታችን ከለምጽ በሽታ ስለፈወሳቸው ሰዎች ምን አለ?

50. ጌታችን በማልቀሱ በሐሳባችን የሚመጡት ጥያቄዎች ምን ምን ናቸው?

## ምዕራፍ 4

# ቤተ ክርስቲያን

## የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት

እንደየአገልግሎቱ ዐይነት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚካሄደው በኤጲስ ቆጶሳት፥ በቀሳውስት፥ በዲያቆናት፥ በመዘመራንና በሌላውም ሕዝበ ክርስቲያን ነው። ጌታችን ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ፥ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱና በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው የእኔ ደቀ መዛሙርት አድርጉአቸው» ብሎ ባዘዛቸው መሠረት እነርሱ የማስተማሩን ተግባር ኀላፊነት ተረክበዋል (ማቴ:ም:28ቊ:19)።

ከዚያም በኋላ ደቀ መዛመርቱ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ሁሉ ብቻውን በኀላፊነት ይዘው በሚያካሂድበት ጊዜ የክርስቶስ ተከታዮች እየበዙ በመሄዳቸው ብቻቸውን ሊቋቋሙት የማይችሉት ሆነዋል። የጸሎቱን፥ የማስተማሩንና የሰብአዊ አገልግሎቱን ሥራ አጣመረው በሚሠሩበት ጊዜ ለማስተማር ተግባራቸው በቂ ጊዜ ያላገኙ ከመሆናቸውም በላይ ከተገልጋዮቹ የቅርታ ስሜት ተሰማ። ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ ምእመናንን ሰብስበው እኛ በጸሎትና በማስተማር አገልግሎት ላይ ብቻ እንድናተኵር ሌላውን ተግባር የሚያከናውኑ ዲያቆናትን ምረጡ ብለው ሰባት ዲያቆናትን አስመርጠዋል (የሐ : ሥ : ም : 6)። ከተመረጡትም መካከል እስጢፋኖስና ፊልጶስ ይገኙ ባቸዋል።

የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ክፍፍል በተመለከተ የሐዋርያት ትምህርት በሆነው በመጽሐፈ ዲድስቅልያ መቅድም ላይ ተዘርዝሮአል። በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን እየተስፋፋች በሄደች ጊዜ ለየዘመኑና ለየሁናቴው አስፈላጊ የሆኑትን አገልግሎቶች እያከለችበት አገልግሎቶችዋን ስታበረክት ኖራለች። ይህም ከክርስቶስ በተሰጣት ሥልጣን መሠረት ነው።

የዲድስቅልያውን ክፍፍል ቀጥለን እንመልከት:-



<u>ኤጲስ ቆጶሱ</u>:-

– መበለቶችንና ችግረኞችን ይረዳል፤
– ለሙት ልጆች እንክብካቤ ያደርጋል፤
– ለሀብታሞች አያዳላም፤
– ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ይሾማል፤
– ለምእመናን መንፈሳዊ ጥበቃ ያደርጋል።
– ያልወደቁትን ያጸናል፤
– ሁሉም ይድኑ ዘንድ ይተጋል፤
– ያለመታከት የምእመናንን ሁናቴ ዘወትር ይከታተላል፤
– ዘወትር ይጸልይላቸዋል፤
– እንደ አባትነቱ ያፈቅራቸዋል፤
– ያዘኑትን ያጽናናል፤
– የተጣሉትን ያስታርቃል፤

– በስብሰባ ጊዜ ለሀብታሙና ለድኻው እኩል አስተያየት ይኖረዋል እንጂ ከአንዱ ሌላውን አያስበልጥም።

– ወጣቶች ወንዶችና ሴቶች እንዲጋቡ ይመክራል:-

– ከቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት የሚያፈነግጡትን ይጠባበቃል፤

– ሊወድቁ የተቃረቡትን ብዙ ማስጠንቀቂያና ትምህርት በመስጠት ኀላፊነቱን ይሸከማል።

<u>ቀሳውስት</u> – (መምህራንም ይባላሉ)

– ሥራቸው ሕዝብን ማስተማር ነው፤
– ማጥመቅ
– መቀደስ
– መባረክ

– ከምሥጢረ ክህነት በቀር የሌሎቹን ምሥጢራት ሥርዓት ሁሉ መፈጸምና ሌሎችም የጸሎተ ሥርዓቶችን መምራት የቀሳውስት ተግባሮች ናቸው።

<u>ዲያቆናት</u>

– ኤጲስ ቆጶሱን ያገለግላሉ፤
– ችግረኞችን ይጐበኛሉ፤
– የችግረኞችን ሁናቴ ለኤጲስ ቆጶሱ ያቀርባሉ፤
– ሐሳቦችንና አስተያቶችን ለኤጲስ ቆጶሱ ያቀርባሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

– እንደ አባትነቱ፣ እንደ ሊቀ ጳጳስ ቆጶስነቱና እንደ መምህርነቱ ለእርሱ ታዛዦች በመሆን ትእዛዙን ይፈጽማሉ።

– የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ያስጠብቃሉ።

<u>መዘምራን</u>

እዚህ ላይ በመዘምራን ተራ ውስጥ የሚጠቃለሉት በቅኔ ማኅሌትና በሌሊት ሰዓታት ለእግዚአብሔር ምስጋናንና ልመናን የሚያቀርቡት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው።

የእነርሱም አገልግሎት የቤተ ክርስቲያኒቱን መንፈሳዊ አገልግሎት የተሟላና የተትረፈረፈ ያደርገዋል።

በዲድስቅልያው ያልተጠቀሱ ሌሎች

<u>ዐቃቤ ወይም ዐቃቢት</u>:- የመሥዋዕቱን ስንዴ ፈጭቶ ወይም ፈጭታ የሚያዘጋጅ ወይም የምታዘጋጅ ነው ወይም ነች።

<u>እንጨት ፈላጭ</u>:- ወይም ቀራፊ ለመሥዋዕት ማዘጋጃ እንጨትን በመፍለጥ የሚያገለግል ነው

ከነዚህም ሌላ ዲድስቅልያው ንፍቅ ዲያቆናት (ረዳ ቶች) ፥ አናጕንስጢሳውያን (አንባቢዎች)፥ በር ከፋቾች፥ የቤተ እግዚአብሔርን ጽዳት ጠባቂዎች የሚላቸው አሉ።

ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ከጌታችን ከመድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በተሰጣት ሥልጣን መሠረት የአገልጋዮቹን እርከንና የአገልግሎቱን ዐይነት እንደጊዜውና እንደ አስፈላጊነቱ እየወሰነች ስትሠራበት ኖራለች፤ ወደፊትም ትኖራለች።

<u>የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን</u>

<u>ወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ</u>:- ቅዱስ ማርቆስ ጌታችን ከመረጣቸው ከሰባ አርድእት አንዱ ነበር። መጽሐፍ እንደሚለው የቀድሞ ስሙ ዮሐንስ ነበር። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በመልአክ አማካይነት ከእስር ቤት ወጥቶ ወደ ልቡናው ከተመለሰ በኋላ ብዙ ሰዎች በአንድነት ተሰብስበው ወደሚጸልዩበት ወደ ማርያም ቤት ሄደ። ማርያም ማርቆስ የተባለው የዮሐንስ እናት ነበረች (የሐ:ሥ:12:12)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን:- «በከተማ ወደሚኖረው ወደ እንትና ቤት ሂዱና መምህር ጊዜዬ ቀርቦአልና ከደቀ መዛሙርቴ ጋር የፋሲካን ራት የምበላው በአንተ ቤት ነው ይላል» ብሎ የላካቸው ወደ ማርቆስ ነው ይባላል። በዚህ ዐይነት ቤቱ ፋሲካ የተበላበት፥ የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያን፣ ከጌታችን ሞት በኋላ የተደበቁበት፥ እንዲሁም በሰገነቱ ላይ ሆነው መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ የወረደበት የማርቆስ እናት ቤት ነው ማለት ነው።



ይህ ወንጌላዊ [illegible] አንድዋ በሆነችው በተርናፖሊስ ነው። አባቱ አርስጦፖሊስ፣ እናቱ ማርያም ይባሉ ነበር። እነርሱም በሰሜን አፍሪካ የሚኖሩ እስራኤላውያን ነበሩ። ልጃቸውንም የግሪክንና የዕብራይስጥን ሥነ ጽሑፍ አስተምረው አሳድገውት ነበር። ማርቆስ የተባለው ወላጆቹ ወደ ኢየሩሳሌም ከመጡ በኋላ ነው። የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ ሚስት የአርስጦፖሊስ የአጐት ልጅ ነበረች። ማርቆስም ወደ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ቤት ብዙ ጊዜ ይመላለስ ነበር። የክርስትናንም ትምህርት የተማረው ከሐዋርያው ከቅዱስ ጴጥሮስ ነው።

አንድ ጊዜ አርስጦፖሊስና ልጁ ማርቆስ ወደ አንድ ቦታ ይሄዱ ነበር። አንድ ወንድና አንዲት ሴት አንበሳ አንጓሩ ወጡባቸው። አባትየው ፈርቶ ለሞት እንደተቃረበ እርግጠኛ የሆነ መሰለው። ልጁ ሸሽቶ ራሱን እንዲያድን የመንገር የወላጅነት ስሜቱ ገፋፋው። ቅዱስ ማርቆስ ግን እኔ የማምንበት ክርስቶስ ከእነርሱ ያድነናልና አይዞህ አባቴ ሆ አትፍራ ብሎ አበረታታው። አንበሶቹ ወደ እነርሱ በተቃረቡ ጊዜ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋችሁ ተቈራርጦና ተሰነጣጥቃችሁ ትወድቁ ዘንድ ያዝዛችኋል ብሎ ጮኸ። እነርሱም ተሰነጣጥቀው ወድቀው ሞቱ። አባትየው ተገርሞ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምረኝ አለው። ማርቆስም አባቱን አስተምሮ በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምን አደረገው፤ ከዚያም አጠመቀው።

ከጌታችን ዕርገት በኋላ ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ በርናባስ ለወንጌል ትምህርት ወደ አንጾኪያ፥ ወደ ሴሌውቅያ፥ ወደ ቆጵሮስ፥ ወደ ሰላሚስና በጵንፍልያ ወደምትገኘው ጰርጌን ቅዱስ ማርቆስን ይዘውት ከሄዱ በኋላ ትቶአቸው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። ከኢየሩሳሌም ጉባኤ በኋላ በርናባስ ወደ ቆጵሮስ ይዞት ሄዷል።

ቅዱስ በርናባስ ካረፈ በኋላ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ ቅዱስ ማርቆስ ወደ አፍሪካ ሄደ። በአፍሪካ አገሮችም ብዙዎችን በክርስቶስ እንዲያምኑ አድርጓቸዋል። ከዚያም በኋላ በ61 ዓ.ም ወደ አስክንድርያ ሄዷል። ወደ እስክንድርያ ከተማ ሲገባ ጫማው ተበጠሰበት። በከተማው መግቢያ አንድ አንያኖስ የተባለ ጫማ ሰፊ ነበር። ማርቆስም የተበጠሰውን ጫማ እንዲሰፋለት ወደ አንያኖስ ወሰደው። አንያኖስ ጫማውን ሲሰፋ ሳለ መርፌው እጁን ወግቶ ስላሳመመው አንዱ አምላክ ብሎ ጮኸ። ማርቆስም አምላክን ታውቃላችሁን? ብሎ ጠየቀው። አንያኖስም አናውቀውም፤ ነገር ግን ሳናውቀው ስሙን እንጠራለን አለው። ማርቆስ በዐፈሩ ላይ እንትፍ ብሎ በአንያኖስ የተወጋ ጣት ላይ ሲያደርግለት ወዲያው ዳነለት። ከዚያም ከፍጥረት ጀምሮ እስከ ጌታችን ወደዚህ ዓለም መምጣት ድረስ በዝርዝር ገለጻ አደረገለት። አንያኖስም ቅዱስ ማርቆስን ወደ ቤቱ ጋብዞት ልጆቹን አቀረበለትና ሁሉንም አስተምሮ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠመቃቸው።

በቅዱስ ማርቆስ ማስተማር ምክንያት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑት ምእመናን መብዛታቸውን የከተማው ኑዋሪዎች በሰሙ ጊዜ ቅዱስ



www.ethiopianorthodox.org

ማርቆስን ሊገድሉት በጥብቅ ይፈልጉት ጀመር። ቅዱስ ማርቆስ ግን አንያኖስን ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ከእርሱም ጋር ሦስት ቀሳውስትንና ሰባት ዲያቆናትን ከሾመ በኋላ ወደ አምስቱ የምዕራብ ግብጽ ከተሞች ሄዶ ወንጌልን እያስተማረ ኤጲስ ቆጶሳትን፥ ቀሳውስትንና ዲያቆናትን እየሾመ ለሁለት ዓመቶች ቈየ።

ከሁለት ዓመት በኋላ ወደ እስክንድርያ ሲመለስ ምእመናን በዝተውና ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶላቸው አገኘ። ሚያዝያ 29 ቀን 68 ዓ.ም የትንሣኤን በዓል ሲያከብር ሳለ ጣዖት አምላኪዎቹም እንደ አጋጣሚ የሃይማኖት በዓላቸውን የሚያከብሩበት ቀን ነበር። ከመስገጃ ቦታቸው ወጥተው ቅዱስ ማርቆስ ወደነበረበት ቦታ ሄዱ። ከዚያም የቅዱስ ማርቆስን አንገት በገመድ አስረው በመጐተት በሬውን ጐትቱት እያሉ ይጮኹ ነበር። ሥጋው ተቈራረጠ፤ ደሙም በከተማው መንገዶች ፈሰሰ። ከዚያም በኋላ ወደ ማታ ጊዜ ወደ እስር ቤት ውስጥ አስገቡት። በዚያች ሌሊት የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦለት የእግዚአብሔር ባሪያ ማርቆስ ሆይ፥ ስምህ በሕይወት መዝገብ ውስጥ ስለተ መዘገበና ከቅዱሳን ጋር ስለተቈጠርህ ደስ ይበልህ ብሎት ሄደ። ጌታችንም ተገልጦለት ሰላምታ ሰለሰጠው ነፍሱ ተደሰተች።

በሚቀጥለው ቀን ማለት ሚያዝያ 30 ቀን ከእስር ቤት አስወጥተው እንደገና በከተማው መንገዶች ነፍሱን እስከሰጠበት ጊዜ ድረስ ጐተቱት። ሥጋውን ለማቃጠል እሳት ባነደዱ ጊዜ የመሬት መናወጥ፥ ነጐድጓድ፥ መብረቅና ከባድ ዝናብ ወረደ። ጣዖት አምላኪዎቹም ደንግጠው ሸሹ። ምእመናን የተቀደሰ ሥጋውን ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስደው ከጸለዩበት፥ ከከፈኑትና በሣጥን ውስጥ ካደረጉት በኋላ በቤተ ክርስቲያኑ በድብቅ ቦታ አስቀመጡት። (የሚያዝያ 30 ቀን ስንክሳር)።

<u>ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ</u>:- ቅዱስ ሉቃስ የተወለደው በአንጾኪያ ነው። ጌታችን መርጦ ለማስተማር ከላካቸው ከሰባ መልእክተኞች አንዱ ነው (ሉቃ :ም:10ቊ:1–12)። የሕክምና ትምህርትና የስዕል መሳል ሙያ እንደነበረው ይነገራል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሐኪሙ ሉቃስ ይለዋል (ቆላ: ም: 4ቊ:14)። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ባደረጋቸው ብዙ ጉዞዎች አብሮት ሄዷል። የሐዋርያት የቅዱስ ጴጥሮስንና የቅዱስ ጳውሎስን ታሪክ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፉ ውስጥ በመጻፉ ብዙ ጊዜ ከእነርሱ ጋር እንደነበረ ይታመናል። ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ቅዱስ ሉቃስ በሮማ አካባቢ ወንጌል ማስተማሩን ቀጠለ። አይሁድና ጣዖት አምላኪዎች በአንድነት ተስማምተው ጠንቋይ ስለሆነ በጥንቈላ ሥራው ብዙዎችን ወደሚ ያስተምረው ትምህርት ስቦአቸዋል ብለው በንገጉሡ በኔሮን ዘንድ ከሰሱት። ንጉሡም ቅዱስ ሉቃስ እንዲጠራ አዘዘ። ቅዱስ ሉቃስ የተጠራበትን ምክንያት በተረዳ ጊዜ መጻሕፍቱን ሁሉ ለአንድ ዓሣ አጥማጅ አስረከበው። እነዚህን መጻሕፍት ደኅና አድርገህ ጠብቃቸው፤ እነርሱም የእግዚአበሔርን መንገድ ያሳዩሃል አለው። በኔሮን ፊት በቆመ ጊዜ ንጉሡ:- «እስከ መቼ ድረስ ሰዎችን ታሳስታለህ» ብሎ ጠየቀው። ቅዱስ ሉቃስም:- «እኔ የልዑል እግዚአብሔር



www.ethiopianorthodox.org

ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ መልእክተኛ ነኝ እንጂ ጠንቋይ አይደለሁም ብሎ መልስ ሰጠው። ስታስተምር የነበረችውን ቀኝ እጁን ቍረጡ ብሎ ንጉሡ አዘዘ። ቅዱስ ሉቃስም እኛ ከዚህ ዓለም ተሰናብቶ የመሄድ ሞትን አንጠላም፤ የጌታዬንም ኀይል ታውቅ ዘንድ ብሎ የተቈረጠውን እጁን መልሶ በቦታው አስቀመጠውና እንደ ጤነኛ እጅ ሆነ። ከዚያም በኋላ እንደገና አንሥተውና አሳየው። በዚያ የነበሩ ሰዎች ተገረሙ። በዚህ ጊዜ ሚኒስትሩና ሚስቱ አመኑ። እንዲሁም ሁለት መቶ ሰባ የሚሆኑ ሰዎች አመኑ። ንጉሡ ግን ከቅዱስ ሉቃስ ጋር የሁላቸውም ራሶች እንዲቈረጡ አዘዘ። በዚህ ዐይነት ሁላቸውም የሰማዕ ትነትን አክሊል ተቀዳጁ። የቅዱስ ሉቃስ አስከሬን በጆንያ ውስጥ ወደ ባሕር እንዲጣል ተደረገ። በእግዚአብሔር ዝግጅት ማዕበሉ ወደ አንድ ደሴት ወረወረው። አንድ ምእመን አግኝቶ በመከፈን ቀበረው።

ቅዱስ ሉቃስ በስሙ የሚጠራውን ወንጌልና የሐዋርያትን ሥራ ጽፎአል (የጥቅምት 22 ቀን ስንክሳር)።

<u>ቅዱስ ፍሬምናጦስ</u>:- የክርስትና ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ መጀመሪያ የገባው በሐዋረያት ሥራ ምዕራፍ 8 ላይ በተገለጠው መሠረት ሐዋርያት ከሾሙአቸው ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱ በሆነው በፊልጶስ አስተማሪነትና በንግሥት ሕንደኬ ጀንደረባ አመካይነት መሆኑ ባይካድም ለኢትዮጵያ የመጀመሪያ ጳጳስ የተሾመላት ግን በ330 ዓ.ም ነው። የዚህም አባባል ዝርዝር ታሪክ እንደሚከተለው ነው።

በታሪኩ መሠረት ሜሮጵዮስ የተባለ አንድ ነጋዴ በጀልባ ከጢሮስ ወደ ሕንድ ይጓዝ ነበር። ከእርሱም ጋር ፍሬምናጦስና ኤዴስዮስ የሚባሉ ሁለት ወጣቶች ነበሩ። በጉዞአቸውም ወደ ኢትዮጵያ የባሕር ወደብ ደረሱና ጥቂት ዐርፈው አገር ለመጐብኘት በማሰብ ጀልባቸውን አቆሙ። በዚህ ጊዜ የአካባ ቢው ነዋሪዎች አደጋ ጥለው ሜሮጵዮስንና የጀልባይቱን ቀዛፊዎች በመግደል ዕቃቸውን ዘረፉ። ፍሬ ምናጦስና ኤዴስዮስ በአንድ ዛፍ ሥር ተጠግተው እግዚአብሔር ከአደጋው እንዲያድናቸው ሲጸልዩ አደጋ ጣዮቹ አገኙአቸውና ያዙአቸው። እነርሱንም በአክሱም ለነበረው ንጉሥ እንደ ስጦታ አድርገው ሰጡአቸው። በዚያን ጊዜ የነበረው ንጉሥ የአብርሃና የአጽብሃ አባት አይዛና ነበር። እነዚህ ሁለት ወጣቶች በዚያን ጊዜ ከነበረው አብዛኛው ሕዝብ ጋር በማነጻጸር የተማሩ ሆነው ስለተገኙ በቤተ መንግሥቱ ተወዳጅነትና ታማኝነትን እያገኙ ሄዱ። በዚህም ምክንያት ንጉሡ ፍሬምናጦስን ዐቃቤ ንዋይ፥ ኤዴ ስዮስን ጋሻ ጃግሬ አድርጎ ሾማቸው።

ንጉሡ ሊሞት በተቃረበ ጊዜ ልጆቹ ገና ለአካለ መጠን ያልደረሱ ስለነበረ መንግሥቱን ንግሥቲቱ በሞግዚትነት እንድትይዝ ከተናዘዘ በኋላ ሁለቱን ሶርያውያን ምርኮኞች በነጻ ለቀቃቸው። ንግሥቲቱ ግን ልጆችዋ እስኪያድጉ ድረስ በምክር እንዲረዷት ስለለመነቻቸው ወደሀገራቸው ሳይሄዱ ቆዩ። የንጉሡ ልጆች አካለ መጠን ደርሰው የአባታቸውን መንግሥት በተረከቡ ጊዜ ኤዴስዮስ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ሄደ፤ ፍሬመናጦስ ግን ስለ ጵጵስና

ጉዳይ ገለጸለት። ቅዱስ አትናቴዎስም ጉዳዩን በሰማ ጊዜ በጣም ደስ ተሰኘ። የኢትዮጵያን ባህልና ቋንቋ የሚያውቅ ከእርሱ የተሻለ ሰው እንደማይኖር ስለተገነዘበ ቅዱስ አትናቴዎስ ፍሬምናጦስን የመጀመሪያ የኢትዮጵያ ኤጲስ ቆጶስ እንዲሆን ቀብቶ ሾመው። ወደ ኢትዮጵያም በተመለሰ ጊዜ በሀገሪቱ በመላ የክርስትናን ትምህርት ማስፋፋት ጀመረ። በሰፊው ለማስተማርና የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ለማከናወን እንዲቻል ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ሾመ። እስከ እርሱ ድረስ ያልተተረጐሙ ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ ግዕዝ የተረጐመ እርሱ ነው። ፍሬምናጦስ በኢትዮጵያችን አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ይባላል። ይህም ለተግባሩ ተስማሚ የሆነ ስም ነው።

በዚህ ዐይነት ሐዋርያዊ አገልግሎቱን በትጋት ሲያበረክትና ብዙዎችንም ወደ ክርስትናው እምነት ሲመልስ ከቈየ በኋላ ዐረፈ። ዕረፍቱም በሐምሌ 26 ቀን ነው።

<u>ቅዱስ ቴዎዶጦስ ዘዕንቄራ (አንካራ)</u>:- በዛሬው አጠራር አንካራ በምትባለው በዕንቄራ የተሾመ ሊቀ ጳጳሳት ነበረ፤ በመጀመሪያ የንስጥሮስ ደጋፊ እንደ ነበረ ይነገራል። በኋላ ግን ከቅዱስ ቄርሎስ ጋር ተባብሮ በ431 ዓ.ም በኤፌሶን በተደረገው ዓለም ዐቀፍ ጉባኤ ላይ ከንስጥሮስ ቀንደኛ ተቃዋሚዎች አንዱ ሆኖአል።

ስለዚህም ንስጥሮሳውያን በ432 ዓ.ም. በተርሴስ ላይ ባደረጉት ጉባኤ ተወግዞ ነበር።

ቅዱስ ቴዎዶጦስ ብዙ መጻሕፍትን ጽፎአል፤ ከጽሑፎቹ መካከል:- (1ኛ) ስለ ንስጥሮስ ትምህርት መቃወሚያ ነበር፤ ግን ሁሉም ጠፍተዋል። (2ኛ) በኒቅያ ጸሎተ ሃይማኖት ላይ ያዘጋጀው ትርጓሜ ነው።

(3ኛ) የተለያየ ስብከቶች ሲሆኑ ከእነዚህ አንዱ በኤፌሶን ጉባኤ የተነበበ ስለ ልደት (ገና) የተናገረው ዝነኛ ጽሑፉ ነው። ስለ ቅዱስ ጊዮርጊስ ስማዕትነትና ተአምራዊነትም ጽፎአል። ቅዱስ ቴዎዶጦስ ከጻፋቸው ድርሰትና አጫጭር የሆኑ አራት ክፍሎች በመጽሐፈ ሃይማኖት አበው ተጽፈው ይገኛሉ።

ቅዱስ ቴዎጾጦስ በ445 ዓ.ም ዓ.ም ዐርፎአል፤ (ዕረፍቱ መታሰቢያም ግንቦት 18 ቀን እ.አ.አ) ነው።

<u>ቅዱስ ሳዊሮስ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት</u>:- የቅዱስ ሳዊሮስ አያት ሳዊሮስ ይባል ነበር። እርሱም «የልጅህ ልጅ ኦርቶዶክሳዊነትን ያጠናክራል፤ እርሱም በአንተ ስም የይጠራል» የሚል ራእይ አየ። እግዚአብሔር ለልጁ ወንድ ልጅ በሰጠው ጊዜ ስሙን ሳዊሮስ ብሎ ሰየመው። እርሱም የግሪኮችን ጥበብና የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ተማረ።

አንድ ጊዜ ከከተማ ወጥቶ ሲሄድ አንድ ባሕታዊ ከዋሻው ወጥቶ እንዲህ ሲል ጮክ ብሎ ተናገረው:- «ኦርቶዶክሳዊ መምህርና የአንጾኪያ ፓትርያርክ



ሳዊሮስ ሆይ፥ እንኳን ደኅና መጣህ።» ሳዊሮስም ከዚያ በፊት የማያውቀው ሰው ስሙን ጠርቶና ወደፊት ስለሚሆነው ጉዳይ ገልጾ በመናገሩ ተገረመ። ሳዊሮስም በመንፈሳዊ ትሩፋት እያደገ ሄደ። በሮማኖስ ገዳምም መነኰሰ። በጽድቅ ሥራውና በብሕትውናውም ቀጠለ። የአንጾኪያው ፓትርያርክ በሞት በተለየ ጊዜ ጳጳሳቱ እርሱን ለመሾም ተስማምተው ሾሙት። ይህም የሆነው በ512 ዓ.ም ነው። የትምህርቱም ብርሃን ለአንጾኪያ ብቻ ሳይሆን ለዓለም በመላ ተዳረሰ። ከዚያም ብዙ ሳይቆይ ንጉሥ አንስጣስዮስ ሞተ። በእርሱም ቦታ የኬልቄዶን ትምህርት ተከታይ የነበረው ንጉሥ ዩስጢኒያኖስ ተተካ። እርሱም ፓትርያኩን ሳዊሮስን አስጠርቶ በእምነቱ እንዲሸነፍለት ተጽዕኖ ማድረግ ጀመረ። ሳዊሮስ ግን አልተቀበለውም። በዚህ ጊዜ ንጉሡ በፓትርያርኩ ላይ ሃይለኛ ቍጣ ተቈጣ። ፓትርያርኩ ያለምንም ፍርሃት እምቢተኛነቱን ቀጠለ። ስለዚህ እንዲገደል ትእዛዝ አስተላለፈ። ኦርቶዶክሳዊት የነበረችውና ታኦዶራ ትባል የነበረችው የንጉሡ ሚስት ንጉሡ በፓትርያርኩ ላይ ያሳለፈውን ውሳኔ በሰማች ጊዜ ከንጉሡ ፊት ዞር እንዲል ማለት እንዲሸሽና ነፍሱን እንዲአድን መከረችው። እርሱ ግን ለትክክለኛው እምነት ለመሞት ዝግጁ ነኝ በማለት ሐሳብዋን አልተቀበለም። እግዚአብሔርን የሚወድዱ ወንድሞችና ንግሥቲቱ በጣም ስለ ጨቀጨቁት እርሱና ሌሎች ወንድሞች ሆነው በመውጣት ወደ ግብጽ አመሩ። ንጉሡ ግን ፈልጎ ባጣው ጊዜ ወታደርና ሌሎችም ሰዎች እንዲከታተሉት ልኮ ምንም እንኳ በቅርባቸው ቢሆን እግዚአብሔር ከእነርሱ ስለ ሰወራቸው ሊያኙአቸው አልቻሉም።

ወደ ግብጽም በደረሱ ጊዜ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታና ከአንዱ ገዳም ወደ ሌላ ገዳም መንከራተት ጀመረ። እግዚአብሔርም በእርሱ አማካይነት ብዙ ተአምራትን ያደርግ ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን በናትሩን ሸለቆ ሸሂት ወደሚባል ምድረ በዳ ሄዶ የተራ መነኵሴ ልብስ በመልበስ ወደ አንድ ቤተ ክርስቲያን እንግዳ መስሎ ገባ። እዚያም አስደናቂ ተአምር ተደረገ። ካህኑ ቍርባኑን በመንበሩ ላይ አስቀምጦ ዕጣን ለማጠን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዞረ። መልእክቶችና ወንጌል ከተነበቡ በኋላ ካህኑ ማኅፈዱን ቢገልጥ ቍርባኑን በጻሕሉ ላይ ሊያገኘው አልቻለም። በዚህ ጊዜ በጣም አዘነና አለቀሰ። ወደ ጸሎተኞቹ ዞር ብሎ መንድሞች ሆይ ቍርባኑን በጻሕሉ ላይ አላገኘሁትም። ይህ ነገር በእኔ ኃጢአት ይሁን ወይም በእናንተ ኃጢአት ሊገባኝ አልቻለም። በዚህም ምክንያት ጸሎተኞቹ አለቀሱ። በዚያ ወቅት የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦለት እንዲህ አለው:- «ይህ የሆነው በአንተ ወይም በጸሎተኞቹ ኃጢአት ምክንያት ሳይሆን ፓትርያርክ እያለ አንተ ቍርባኑን በማንሣትህ ነው» አለው። ካህኑም «ጌታዬ ሆይ፥ ወዴት ነው እርሱ ብሎ ጠየቀ። መልአኩም ሳዊሮስ ያለበትን አቅጣጫ አመለከተው። ቅዱስ ሳዊሮስ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ወደ አንድ ጥግ ተቀምጦ ነበር። ካህኑም በጸጋ ሊያውቀው ቻለ። ፓትርያርኩን በታላቅ አክብሮት ወደ መቅደስ ውስጥ ከአስገቡት በኋላ ቅዳሴውን እንዲቀጥል ካህኑን



www.ethiopianorthodox.org

አዘዘው። አሁን ካህኑ ወደመቅደስ ውስጥ ሲገባ ቍርባኑን በቦታው አገኘው። እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ ቅዱስ ስሙንም አከበሩ።

ቅዱስ ሳዊሮስ ከዚያ ወጥቶ ሰኻ ወደምትባል ከተማ በመምጣት ዱራታኦስ ተብሎ በሚጠራ አንድ አለቃ ቤት ውስጥ ኖረ። እስከ ኅልፈተ ሞቱ ድረስም የኖረው እዚያው ነው (የጥቅምት 2 ቀንና የጥር 14 ቀን ስንክሳር)።

<u>አባ ሕርያቆስ</u>:- ኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ በተነሣበት በ6ኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ላይ የነበረ አባት ነው። ሀገሩ በግብጽ ውስጥ የምትገኝ ብህንስ የምትባል አካባቢ ነች። በሌላም አጠራር ሙኑፍ ትባላለች። ብዙ ትምህርት አልነበረውም፥ ነገር ግን ፍጹም ግብረገብ የሆነ መንፈሳዊ አባት ነበረ። ታላቅ ግብረ ገብ ከመሆኑም የተነሣ በብህንሳ ገዳም የብዙ መነኮሳት አበ–ምኔት ሆኖ ተሾሞ ነበር።

አባ ሐርያቆስ ግብረ ገብ በመሆኑ ገዳማዊ ሥረዓት እንዲጠበቅ አጥብቆ ይቈጣጠር ስለነበር መነኰሳቱ ይጠሉት ነበር። ያልተማረ በመሆኑም ይንቁት ነበር። ይሁን እንጂ እንደ ጠሉኝ ልጥላቸው፥ እንደ ናቁኝም ልናቃቸው ሳይል በፍቅርና በትሕትና ሆኖ ይመክራቸው ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን ተሰብስበው ከአበ –ምኔትነቱ ለመሻር ተማከበሩ። ለዚህም በቂ ምክንያት ማግኘት አስፈላጊ ስለነበረ ቀድሶ እንዲያቈርባቸው ወሰኑ። እርሱን ከሹመቱ ለመሻር ቀድሶ እንዲያቈርባቸው የተወሰነበት ምክን ያትም ከላይ እንደተጠቀሰው በቂ ትምህርት ስላልነበረው ነው። መቀደስ ካልቻለ ወይም አስተካክሎ ካልቀደሰ ያልተማረ ሰው ሊመራን አይገባውም ብለው ለመሻር ነበር።

አባ ሕርያቆስም በመነኰሳቱ ጥያቄ መሠረት በነበረው መጠነኛ ችሎታ ለመቀደስ ተዘጋጅቶ ወደ መቅደስ ገብቶ ጸሎተ ቅዳሴውን ጀመረ፤ የመጀ መሪያውን ሥርዐተ ቅዳሴ ፈጽሞ ከሁለተኛው ክፍል ከፍሬ ቅዳሴው ሲደርስ በእመቤታችን አማላጅነት መንፈስ ቅዱስ ገልጦለት «ቅዳሴ ማርያምን ሰተት አድርጎ ተናግሮአል። በዚህ ጊዜ ይጠሉትና ይንቁት የነበሩ ሰዎች «ይህ ሰው ። የነገሩትን ትምህርት እንኳ አከናውኖ መቀበል አይችልም ነበር ። ዛሬስ አዲስ ድርሰት እደርሳለሁ ብሎ ይቀባጥራል» ብለው አፌዙበት። የሚወድ ዱትና የሚያከብሩት ግን ይህ ዐይነት ድርሰት ከመንፈስ ቅዱስ እንጂ ከማንም ተራ ሰው የሚነገር አይደለም በማለት አደነቁት። ይህም ቅዳሴ ማርያም ከዐሥራ አራቱ ቅዳሴያት አንዱ ሆኖ እስካሁን ቤተ ክርስቲያናችን ትጠቀ ምበታለች ።

አባ ሕርያቆስ በመንፈስ ቅዱስ ይህን የቅድስት ድንግል ማርያምን ቅዳሴ ከደረሰ በኋላ በአበ ምኔትነቱ በቆየበት ወቅት ብዙ ድርሳን ደርሷል፤ ብዙ ተግሣጽም ጽፏል። ከድርሳናቱ መካከል ሰባቱ በመጽሐፈ ግብረ ሕማማት ተጽፈው ይገኛሉ። እነዚህም «ላሐ ማርያም» በሚል ርእስ የተጻፉ ሲሆን በየዓመቱ በሰሙነ ሕማማት በዕለተ ስቅለት ዐርብና ቅዳሜ ይነበባሉ፤ ምክንያ



www.ethiopianorthodox.org

ቱም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ወላዲተ አምላክ ማርያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ባየችው ጊዜ የደረሰባትን ሐዘንና ያለቀሰ ችውን ለቅሶ የሚገልጡ በመሆናቸው ነው።

የአባ ሕርያቆስ የዕረፍቱ መታሰቢያ ጥቅምት ሁለት ቀን ነው። (የጥቅምት 2 ቀን ስንክሳር)።

<u>ቅዱስ በርናባስ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መርጦ ለማስተማር ከላካቸው ሰባ አርድእት አንዱ ነው። እርሱ ከሌዊ ነገድ ነበር። እርሱም ቤተሰቡን ቀድሞ ከይሁዳ ምድር አርቆአቸው በቆጵሮስ ደሴት ይኖሩ ነበር። በመጀመሪያ የእርሱ ስም ዮሴፍ ነበር። ጌታችን በመረጠው ጊዜ ግን በርናባስ ብሎ ጠርቶታል። የጌታችን ደቀ መዛሙርት የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በተቀበሉበት ቀን እርሱም ከእነርሱ ጋር አብሮ ተቀብሎአል። ከእነርሱም ጋር አብሮ ስለ ክርስቶስ አስተማረ፤ ሰበከ፤ እርሱ መሬት ነበረው። ያንንም መሬት ሸጠና ገንዘቡን አምጥቶ ለሐዋርያት አስረከበ። በትሩፋቱና በታማኝነቱ ሐዋርያት ያከብሩት ነበር። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን በክርስቶስ ባመነ በሦስተኛ ዓመት በኢየሩ ሳሌም ወደ ሐዋርያት ያቀረበው ቅዱስ በርናባስ ነው። በደማስቆ ከተማ አጠገብም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት አድርጎ ቅዱስ ጳውሎስን እንደተገናኘው ነገራቸው። እነርሱ በአንድነታቸው እስኪቀበሉት ድረስ የቅ ዱስ ጳውሎስን ቀናኢነት በፊታቸው መሰከረለት። መንፈስ ቅዱስም:- «እኔ ለጠራኋቸው ሥራ በርናባስንና ሳውልን ለዩልኝ» አለ።

እነሆ፥ ሁለቱ መልእክተኞች፥ ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ በርናስ በአንድነት ሆነው ስለ ክርስቶስ ለመስበክ ወደ ብዙ አገሮች ዞረዋል። ወደ ልስጥራ ደርሰው ቅዱስ ጳውሎስ አንዱን ሽባ በፈወሰ ጊዜ ለአገሬው ሰዎች አማልክት መሰለው ስለታዩአቸው መሥዋዕት ሊያቀርቡላቸው ፈልገው ነበር። እነርሱ ግን የሰውን ክብር ስላልፈለጉ እንደ ሁላቸውም ሰዎች መሆናቸውን በመግለጥ ልብሳቸውን ቀደዱ። ቅዱስ በርናባስና ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ብዙ አገሮች አብረው ከዞሩ በኋላ ተለያዩ። ቅዱስ በርናባስም ቅዱስ ማርቆስን ይዞ ወደ ቆጵሮስ ሄደ። እዚያም ወንጌልን አስተምረው ብዙዎችን በማሳመን አጠመቋቸው። አይሁድ በእነርሱ ላይ ተቈጥተው አገረ ገዢውንና ሽማግሌዎችን አነሣሡባቸው። ቅዱስ በርናባስንም ከደበደቡት በኋላ በድንጋይ ወገሩት፤ ከዚያም ሥጋውን አቃ ጠሉት። በዚህም ትግሉን ፈጽሞ የሰማዕትነትን አክሊል ተቀዳጀ። ሰዎቹ ከሄዱ በኋላ ቅዱስ ማርቆስ የቅዱስ በርናባስን አስከሬን ከፍኖ ከቆጵሮስ ወጣ ባለ ዋሻ አኖረው። (የታኅሣሥ 21 ቀን ስንክሳር)።

## <u>የቤተ ክርስቲያን ዜማ</u>

### <u>በግዕዝ</u>

ህየንተ ዝውእቱ እምትንሣኤ እስ፥ በዓለ ኅምሳ:- ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን ሞተ ወኬዶ ለሞት

ለእለ ውስተ መቃብር ወሀበ ሕይወተ ዘለዓለም ዕረፍተ።

ይ: ካ:- ቅዱስ

ይ:ሕ:እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት፤ ዘተወልደ እማርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት፥

ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ልፀ መስከቀል ተሣሃለነ እግዚኦ። ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት፥ ዘተንሥአ እሙታን አመ ሠልስት ዕለት፥

ዐርገ በሰብሐት ውስተ ሰማያት። ወነበረ በየማነ አቡሁ። ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ

ተሣሀለነ እግዚኦ። ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ።

ይእዜ ኒ ወዘልፈኒ ወለዓ ለመዓለም አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን። ቅዱስ ሥሉስ እግዚአአብሔር ሕያው ተሣሀለነ።

ይ:ካ:- ጸጋ ዘእግዚአአብሔር የሃሉ ምስሌክሙ።

ይ:ሕ:- ምስለ መንፈስከ።

ይ:ካ:- ንስብሎ ለአምላክነ።

ይ:ሕ :- ርቱዕ ይደሉ።

ይ:ካ:- አጽንቦ ሕሊና ልብክሙ።

ይ:ሕ :-ብነ ሮበ እግዚአብሔር።

አቡነ ዘመበሰማያት አቡነ ዘበሰማያት አቡነ ዘበሰማያት ኢታብአነ እግዚአ ውስተ መንሱት።

ይ: ሕ:- ኪያከ ንሴብሕ እግዚኦ።

ይ:ሕ:- ኪያከ ንዌድስ እግዚኦ።

ይ:ካ :- ጸጋሁ ለእግዚአብልር የሃሉ ምስሌክሙ።

ይ:ሕ:- ምስለ መንፈስከ።

ይ:ካ:- አእኵትዎ ለአምላክነ

ይ:ሕ:- ርቱዕ ይደሉ።

ይ:ሕ:- ንሴብሐከ እግዚኦ።



## በአማርኛ

ዳግመኛም ከትንሣኤ እስከ በዓለ ኀምሳ በዝውእቱ ፈንታ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ።

ሞትንም በሞቱ አጠፋው።

በመቃብር ላሉ ሕይወትን፥ የዘለዓለም ዕረፍትን ሰጠ።

ይ:ካ:- ቅዱስ።

ይ:ሕ:- እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት፥ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ

አቤቱ ይቅር በለን።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት፥ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣ በምስጋና ወደ ሰማይ ያረገ፥

በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ። ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ፈርድ ዘንድ በጌትነት ይመጣል። አቤቱ ይቅር በለን ለአብ ምስጋና ይሁን ለወልድ ምስጋና ይሁን ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይሁን፥ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን አሜን ይሁን ይሁን።

ሕያው እግዚአብሔር ሆይ ይቅር በለን።

ሕዝቡም ይህን ይቀበሉ።

ይ: ካ:- የእግዚአብሔር ጸጋ ከእናንተ ጋር ይኑር።

ይ:ሕ:- ከመንፈስህ ጋር

ይ: ካ:- ፈጣሪያችንን እናመስግነው።

ይ:ሕ:- እውነት ነው ይገባል

ይ:ካ:- የልባችሁን ሐሳብ አጽኑ።

ይ:ሕ :- ከእግዚአብሔር ዘንድ ነን።

በሰማያት ያለህ አባታችን በሰማያት ያለህ አባታችን በሰማያት ያለህ አባታችን አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን።

ይ:ሕ:- አቤቱ አንተን እናመሰግናለን።

ይ:ሕ:- አቤቱ አንተን እናከብርሃለን።

ይ:ካ:- የእግዚአብሔር ጸጋ ከእናንተ ጋር ይኑር፥

ይ:ሕ:- ከመንፈስህ ጋራ፥

ይ:ካ :- ፈጣሪያችንን አመስግኑት

ይ:ሕ :- እውነት ነው ይገባል

www.ethiopianorthodox.org

ይ:ሕ :- አቤቱ እናከብርሃለን።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

በዲድስቅልየ አንቀጽ 6 እንደተገለጠው ምእመናን ለቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ማዋጣት አለባቸው። ለቤተ ክርስቲያን መሰጠት ካለባቸው ስጦታዎች መካከል ከገቢአችን ሁሉ ከዐሥር አንዱን መክፈል በውዴታ ብቻ የሚከፈል ሳይሆን የግዴታ ክፍያ መሆኑን መገንዘብ አለብን። ዐሥራትን አለመክፈል እግዚአብሔርን መስረቅ መሆኑን ቃል እግዚአብሔር በግልጥና በማያሻማ ቋንቋ አብራርቶታል። ቃለ እግዚአብሔርም የዐሥራትን ግዴታነት በአብራራበት ጊዜ ዐሥራት በመክፈል የሚገኘውን መንፈሳዊውን ብቻ ሳይሆን ቍሳዊ በረከት አረጋግጧል። የዚህንም አባባል ተግባራዊነት ብዙዎች ምእመናን በሕይወታቸው ያጋጠማቸውን ሁናቴ በማስረጃነት በማቅረብ አረጋግጠዋል (ሚል:ም:3ቍ:6–12)።

የቅዱስ ማርቆስን ታሪክ በምናነብበት ጊዜ በእግዚአብሔር የተማመነ ሰው ምን ያኽል ታላላቅ ሁናቴዎች እንደሚያጋጥሙት ለመገንዘብ እንችላለን። ለምሳሌ ከአባቱ ጋር በመንገድ ላይ ሳለ አንድ ተባዕትና አንዲት እንስት አንበሶች ሲያጋጥሙት በእርሱ ዘንድ ምንም ፍርሃት ያልነበረ ከመሆኑም በላይ አባቱን አይዞህ ብሎ ማበረታታቱ በእግዚአብሔር ላይ ካለው ጠንካራ እምነት የተነሣ ነው። በዚህም በጠንካራ እምነቱ አንበሶቹ እንዲሞቱ አድርጓል። ያንንም የተመለከተው አባቱ አማኝ ለመሆን ታድሎአል። እግዚአብሔር ሁልጊዜ የታማኝ ወዳጆቹን ልመና ስለሚቀበልና ከክፉ ነገር ሁሉ ስለሚጠብቃቸው ቅዱስ ማርቆስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በጮኸባቸው ጊዜ ተሰነጣጥቀውና ተበጣጥሰው ወድቀዋል።

እንዲሁም እግዚአብሔር በጥበቡ የቅዱስ ማርቆስ ጫማ እንዲበጠስና ለወደፊቱ በሥራ ረዳቱ ሊሆን ያዘጋጀውን አንያኖስን እንዲገናኝ አድርጎታል። ይህም ብቻ ሳይሆን ለግንኙታቸው መነሻ የሆነውን ሁናቴ አመቻችቶለታል። አንደኛ አንያኖስ የማያምንበትን የእግዚአብሔርን ስም ይጠራል፤ በዚያም መነሻነት ወንጌላዊው የማስተማሩን ሥራ ይጀምራል፤ የቅዱስ ማርቆስም ትምህርት ተሰሚነትና ተቀባይነት እንዲያገኝ እግዚአብሔር የአንያኖስን ቍስል የመፈወስ ችሎታ ይሰጠዋል። በዚህም መሠረት አንያኖስ ከነቤተሰቡ አምኖ ከመጠመቁም በላይ የመጀመሪያው የእስክንድርያ ፖትርያርክ ለመሆን በቅቶአል።ሠ

ቅዱስ ማርቆስ በሚሞትበት ቀን ዋዜማ በእስር ቤት ሳለ በመጀመሪያ የእግዚአብሔር መልአክ ከዚያም በኋላ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጠለት ያበረታታው የሥጋችን ደካማነት የታወቀ በመሆኑ ነው።

ቅዱስ ማርቆስን አሰቃይተው የገደሉት አረማውያን በድኑን ሊያቃጥሉት በሞከሩ ጊዜ የመሬት መናወጥ መከሰቱ፥ የነጐድጓድና የመብረቅ ድምፅ



www.ethiopianorthodox.org

መሰማቱና ከባድ ዝናብ የመዝነቡ ምክንያት እግዚአብሔር ነፍስ ለተለየችው የወዳጆቹ ሰውነት እንኳ የሚጠነቀቅ በመሆኑ ነው።

ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ተከስሶ በሮማው ንጉሥ በኔሮን ፊት በቆመ ጊዜ እኔ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ መልእክተኛ ነኝ በማለት በሰው ሁሉ ፊት በድፍረት እምነቱን አረጋግጦአል። ይህንንም በሚናገርበት ጊዜ ጨካኙ ንጉሥ ኔሮን የበለጠ እንደሚጨክንበት ደኅና አድርጎ ያውቃል። ይሁን እንጂ ሊከተለኝ የሚወድድ ቢኖር ራሱን ይካድ ያለውን የጌታችንን መመሪያ በመከተል እምነቱን በግልጥ ለማወጅ ብሎ ራሱን ለምድራዊ አደጋ ያጋለጠው በድፍረት ነበር። ከዚሁም ጋር «በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔም በሰማይ ባለው ባባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ» የሚለው የጌታችን የማይታጠፍ ተስፋም የወንጌላዊው ሉቃስ አበረታችና አንቀሳቃሽ ነበር። በዚህ ጉዳይ ላይ ሌላው የጌታችን ትምህርታዊ መመሪያ ደግሞ «ሕይወቱን ለማዳን የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋታል፤ ሕይወቱን ስለ እኔ የሚያጠፋ ሁሉ ያድናታል» የሚለው አባባል ነው። ንጉሡ የቅዱስ ሉቃስን እጅ ባስቈረጠ ጊዜ እኛ ከዚህ ዓለም ተሰናብቶ የመሄድ ሞትን አንጠላም ካለው በኋላ የጌታዬንም ኀይል ታውቅ ዘንድ ብሎ የተቈረጠውን እጁን መልሶ በቦታው አስቀመጠውና እንደ ጤነኛው እጅ ሆነ። ከዚያም በኋላ እንደገና አነሣውና አሳየው። እግዚአብሔር እንደ ቅዱስ ሉቃስ ላሉ ታማኞችና ቅን ታዛዦቹ ሥራቸውን ሁሉ ስለሚያቃናላቸው ድንቅ ነገሮችንና ተአምራት የማድረግን ኀይልና ችሎታ ይሰጣቸዋል፤ ማለትም በእነርሱ አማካይነት ተአምራትን ይሠራል። ይህም በመሆኑ ሁለት መቶ ሰባ ሰዎች በጌታችን አምነው ከቅዱስ ሉቃስ ጋር ሰማዕትነትን ተቀበሉ።

ንስሓ ከማያስፈልጋቸው ዘጠና ዘጠኝ ሰዎች ይልቅ ንስሓ በሚገባ አንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ የሚሆን ከሆነ ወደጌታችን ተመልሰው በሰማዕትነት በሚሞቱት በሁለት መቶ ሰባ ሰዎችማ በሰማይ ምን ያኽል ደስታ እንደሚሆን እንገምት።

አብረዋቸው የነበሩት ሰዎች ሁሉ ሲገደሉ ፍሬምናጦስና ኤዴስዮስ ብቻ ሳይገደሉ መቅረታቸው ጸሎት ምን ያኽል ኀይል እንዳለው ያመለክተናል።

የቅዱስ ሳዊሮስን ታሪክ ስንመለከት ደግሞ ቅዱሳን ለእውነት ቆመው መንፈሳዊ ትግላቸውን በሚአካሄዱበት ጊዜ የዚህ ዓለም ሕይወታቸው ምንም የማያሳስባቸው መሆኑን ልንገነዘብ እንችላለን። እግዚአብሔርም የቅዱሳንን ማንነት በሌሎች ዘንድ እንዲታወቅ የሚያደርግ መሆኑን እንገነዘባለን።

የአባ ሕርያቆስንም ታሪክ ብንመለከት የእግዚአብሔር ወዳጆች የተማሩ እንኳ ባይሆኑ በአምላክ እርዳታ መንፈሳዊ ዕውቀት እንደሚገለጥላቸው እንረዳለን። እግዚአብሔርም መንፈሳውያን ልጆቹን መቼም ቢሆን አያሳፍራቸውም።

## ጥያቄዎች

1. የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚካሄደው በማን በማን ነው?
2. ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ያዘዛቸው ምን ዐይነት አገልግሎት ነው?
3. ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ለአገልግሎት ያዘዘበት ጥቅስ ምን የሚለው ነው?
4. ደቀ መዛሙርቱ አገልግሎቱን ብቻቸውን ሊቋቋሙት ያልቻሉት በምን ምክንያት ነው?
5. ለችግሩስ ምን ዐይነት መላ አገኙ?
6. ሐዋርያት አጣመረው የሚሠሩት ምን ምን አገልግሎቶችን ነበር?
7. በኋላስ ምን ዐይነት አገልግሎቶችን ብቻ ለማከናወን ወሰኑ?
8. የተገልጋዮቹ ቅርታ የተሰማው በምን ምክንያት ነው?
9. መጽሐፈ ዲድስቅልያ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትን  በማን በማን መካከል ከፋፈለው?
10. ከኤጲስ ቆጶሱ አገልግሎቶች ቢያንስ አምስቱን ዘርዝር።
11. በዲድስቅልያ የተገለጠው የምእመናን አገልግሎት የቱ ነው?
12. የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ማስጠበቅ የማን አገልግሎት ነው?
13. ሕዝብን ማስተማር የማን አገልግሎት ነው?
14. የምስጋናና የልመና ዜማ የሚያቀርቡት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እነማን ይባላሉ?
15. የመሥዋዕቱን ስንዴ በመፍጨት የሚያዘጋጅ የቤተክርስቲያን አገልጋይ ማን ይባላል?
16. ቤተ ክርስቲያን እንደጊዜውና እንደ አስፈላጊነቱ አገልግሎቶችን ልትወስን የምትችለው በምን መሠረት ነው?
17. የቅዱስ ማርቆስ የቀድሞ ስም ማን ነበር?
18. የቅዱስ ማርቆስ እናት ስም ማን ይባል ነበር?
19. ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በመልአክ አማካይነት ከእስር ቤት ሲወጣ የሄደው ወዴት ነው?
20. ጌታችን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን ራት የበላው የት ነው?
21. ቅዱስ ማርቆስ የተወለደው የት ነው?
22. የቅዱስ ማርቆስ አባት ማን ይባላል?
23. የቅዱስ ማርቆስ አባትና እናት ዘር ምን ነበር?
24. የቅዱስ ማርቆስ ወላጆች ምን አስተምረው አሳድገውት ነበር?

.................................................................................................



www.ethiopianorthodox.org

25. የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ ሚስት ለአርስጦፖሉስ ምኑ ነበረች?
26. ቅዱስ ማርቆስ የክርስትናን ትምህርት ከወዴት ተማረ?
27. አርስጦፖሊስና ልጁ ማርቆስ ምን አጋጠማቸው?
28. በዚያን ጊዜ አባትየው ምን ተሰማው?
29. የወላጅነት ስሜቱስ ወደምን ገፋፋው?
30. ቅዱስ ማርቆስስ አባቱን ምን ብሎ አበረታታው?
31. ከዚያስ በኋላ ቅዱስ ማርቆስ ምን አደረገ?
32. አባትየው ተገርሞ ቅዱስ ማርቆስን ምን አለው?
33. ቅዱስ ማርቆስስ ምን አደረገ?
34. ከጌታችን ዕርገት በኋላ ለወንጌል ትምህርት በመጀመሪያ ከማን ጋር ሄዶ ነበር??
35. ከኢየሩሳሌም ጉባኤ በኋላስ ከማን ጋር ሄደ?
36. ቅዱስ ማርቆስ በጌታችን ትእዛዝ የሄደው ወዴት ነው?
37. ወደ እስክንድርያስ ሲገባ ምን አጋጠመው?
38. በዚያስ የተገናኘው ማንን ነው?
39. የዚያ የተገናኘው ሰው ሥራ ምን ነበር?
40. ያ ሰው ምን ደረሰበት?
41. በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ምን አለ?
42. ቅዱስ ማርቆስ ምን ብሎ ጠየቀው?
43. እርሱስ ምን ብሎ መለሰ?
44. ከዚያ በኋላ የሁለቱ ንግግር ወደምን አመራ?
45. ሰውዬው በተጐዳ ጊዜ ቅዱስ ማርቆስ ምን አደረገለት?
46. ሰውዬው ወደ ቤቱ በጋበዘው ጊዜ ቅዱስ ማርቆስ ምን አደረገ?
47. በቅዱስ ማርቆስ ማስተማር ምክንያት ምን ሆነ?
48. ቅዱስ ማርቆስ ያን ወደ ቤቱ የጋበዘውን ሰው ምን አደረገለት?
49. የከተማው ኑዋሪዎች ቅዱስ ማርቆስን ሊገድሉት የፈለጉት በምን ምክንያት ነው?
50. ወደ አምስቱ የምዕራብ ግብጽ ከተሞች ሄዶ ስንት ጊዜ ቈየ?
51. ወደ እስክንድርያ በተመለሰ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኒቱን በምን ሁናቴ ላይ አገኛት?
52. ጣዖት አምላኪከዎቹ ቅዱስ ማርቆስን የያዙት ከወዴት አግኝተውት ነው?

.................................................................................................

53. ይዘውስ ምን አደረጉት?

54. እነርሱስ ምን እያሉ ጮኹ?

55. በእስር ቤት ውስጥ ሆኖ ሌሊት ማን ተገለጠለት? ምንስ አለው፤

56. በድኑን ሊያቃጥሉት በፈለጉ ጊዜ ምን ሁናቴዎች ተከሠቱ?

57. ምእመናንስ ምን አደረጉለት?

58. ወንጌላዊ ቅዱስ ሉቃስ የት አገር ተወለደ?

59. ምን ትምህርትና ምን ሙያ ነበረው?

60. ብዙ ጊዜ የተጓዘው ከማን ጋር ነው?

61. በሐዋርያት ሥራ መጽሐፉ እንደሚታየው ከነማን ጋር ብዙ ጊዜ እንደነበረ ያመለክታል?

62. ቅዱስ ሉቃስ በሮማ አካባቢ ወንጌል ማስተማሩን የቀጠለው መቼ ነው?

63. አይሁድና ጣዖት አምላኪዎች ቅዱስ ሉቃስን ምን ብለው ከሰሱት?

64. ንጉሥ ኔሮን ቅዱስ ሉቃስን ምን አለው?

65. ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስስ ምን መለሰለት?

66. ንጉሡ እጁን ካስቈረጠው በኋላ ቅዱስ ሉቃስ ምን አደረገ?

67. በጌታችን አምነው ሰማዕትነትን የተቀበሉት ሰዎች ስንት ናቸው?

68. ቅዱስ ሉቃስ የጻፋቸው መጻሕፍት ምንና ምን ናቸው?

69. የክርስትና ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ የገባው መቼ ነው?

70. ፍሬምናጦስና ኤዴስዮስ በአክሱም መንግሥት ምን ዐይነት ሹመት ተሰጣቸው?

71. ፍሬምናጦስን በ330 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ የሾመው ማነው?

## ምዕራፍ 5

# መንፈሳዊነትና ግብረገብነት

## ራስን የመግታት ጥንካሬ አስፈላጊነት

የድኅነትን መንገድ የመከተል ፍላጎት ካለን ከዚህ ዓለም አታላይና አሳሳች መንገዶች ራሳችንን መግታት ወይም መጠበቅ ይኖርብናል።

ይህ አሳሳች ወይም አታላይ የተባለው መንገድ የትኛው ነው?

-----



ክፉ ነገርን ማየት ነውን?

ክፉ ሐሳብ ነውን?

ክፉ ምኞት ነውን?

ክፉ ትውስታ ነውን?

ኩራት ወይም ትዕቢት ነውን?

ክፉ ነገርን መስማት ነውን?

በፍርሃትና በድንጋጤ መርበድበድ ነውን?

በቍጣ ተነሣሥቶ ክፉ ነገርን ማድረግ ወይም መናገር ነውን?

ተስፋ ቈርጦ እምነተቢስ መሆን ነውን?

ክፉ ድርጊትን መሞከር ነውን?

ራሳችንን መግታት ያለብን ከእነዚህ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ብዙዎች የኃጢአት ምንጮች ይኖራሉ። ለጊዜው ለዚህ ውይይታችን ያኽል ብቻ በሚቀጥሉት አርእስት ላይ እናተኵር:-

<u>ክፉ ነገሮችን ከማየት እንቈጠብ</u>:- ሥጋዊው ሰውነታችን አብዛኛውን ጊዜ ወደላይ ሳይሆን ወደ ተፈጠረበት ወደ ምድራዊ አስተሳሰብ ይስበናል። ዐይኖቻችን አይተው እኛን ከሰማያዊው አስተሳሰብ የመሳብ የስበት ኀይል አላቸው። ታዲያ፥ ወደምድራዊ አስተሳሰብ እንድናተኵር ከሚያደርጉን ክፉ ትርኢቶች ለመጠበቅ የምንችልበት ምን ዘዴ አለ?

ትርኢቱ ክፉ መሆኑን ስናውቅ ላለማየት መሞከር አለብን። የመዝናኛ ቦታዎች የሚባሉት አብዛኞቹ ክፉ ነገር የሚታይባቸውና የሚሰማባቸው ቦታዎች እንደመሆናቸው ከእንደነዚህ ዐይነቶቹ ቦታዎች ራሳችንን ማራቅ ወይም መጠበቅ አለብን። ክፉ ትርኢት ካለበት ቦታም መሸሽ እንጂ አለመ ዳፈር ያስፈልጋል፤ ሳንወድ በግድ፥ ወይም በአጋጣሚ ካየነው ሥጋዊ ስሜታችንን ለመግታት ወይም ለመቈጣጠር እንድንችል የእግዚአብሔርን እርዳታ መለመን የመጀመሪያ መንፈሳዊ ተግባራችን መሆን ይገባዋል። በእንደዚያ ያለ ጊዜ ማማተብ ይኖብርናል።

<u>ከክፉ ሐሳብና ከክፉ ምኞት መገታት</u>:- አንዳንድ ጊዜ ድንገት ሳናስበው ክፉ ሐሳብ በኅሊናችን ውስጥ ይመጣል። ይህም ክፉ ምኞትን ያመጣል። ክፉ ሐሳብና ምኞትም ክፉ ነገርን ከመስማትና ክፉ ነገርን ከማየት ሊመጡ ይችላሉ። ወይም ደግሞ ሌላው ሰው በእኛ ላይ ከሚያደርሰው በደል የተነሣ ለዚያ ለክፉ አድራጊ ክፉ እንመኝለት ይሆናል። ይህም ምኞት በተግባር እንኳ ባይገለጥ በምኞት ተፈጽሞአል ማለት ነው። ታዲያ፥ እነዚህን ክፉ ሐሳቦችና ክፉ ምኞቶች እንደምን አድርገን ልንከላከላቸው እንችላለን?

ክፉ ነገር ከሚታይበትና ክፉ ነገር ከሚሰማበት ቦታ መራቅ ያስፈልጋል። ክፉ ነገር በሚያደርግብን ሰው ላይ ክፉ እንዳናስብ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ

-----



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቶስ ሕማማትን አድርሰውበት በሰቀሉት ሰዎች ላይ አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ብሎ የጸለየው ጸሎት ትምህርት ሊሆነን ይገባል። እንዲሁም ሰማዕቱ እስጢፋኖስ አይሁድ በድንጋይ ወግረው በሚገድሉት ጊዜ አምላክ ሆይ ይህን በደል አትቍጠርባቸው ብሎ የጌታችንን አርአያነት ተከትሎአል። የሚቻለንን ያኽል በጠላቶች ላይ ክፉ ከማሰብ እንገታ። ከእነዚህ ክፉ ሐሳቦችና ምኞቶች ለመገታት በምናደርገው ጥረት ላይ ሥጋዊ ጕናችን የሚያጠቃን ሆኖ ጥረታችንን የሚያሰናክልብን ቢሆን ኀይሉንና ብርታቱን ይሰጠን ዘንድ ወደ አምላካችን መጸለይ ይኖርብናል። ቸሩ አምላካችንም ልመናችንን ሰምቶ ኀይሉንና ብርታቱን እንደሚሰጠን እርግጠኞች እንሁን።

<u>ከፍትወት መጠበቅ</u> :-እዚህ ላይ ፍትወት ስንል የወንድና የሴት ወሲባዊ ፍላጎት ወይም ምኞት ማለት ነው። ይህም ምኞት ወይም ፍላጎት ክልክል ሆኖ እንደኃጢአት የሚቈጠረው በሕጋዊ ጋብቻ በባልና በሚስትነት ላልተጣመሩ ሰዎች ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ሕግ ሲደነግግ:- «ሴትን ተመልክቶ የተመኛት ሁሉ፥ ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመነዘረ እላችኋለሁ» ብሏል። ታዲያ፥ ፍትወት ፈልገው የሚያመጡት ስሜት ሳይሆን እንዲሁ ሳያስቡት ከሥጋዊ ስሜት የሚመነጭ ስለሆነ ምን ማድረግ ይቻላል? ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል። አብዛኛውን ጊዜ ፍትወት የሚበረታው ባል ወይም ሚስት በሌላቸው ሰዎች ላይ ስለሆነ ይህን የሥጋ ተፈጥሮአዊ ስሜት ምን ማድረግ ይቻላል? ተብሎም ይጠየቅ ይሆናል።

በመሠረቱ የፍትወት ዋነኞቹ ምንጮች ምን፥ ምን ናቸው?

ዋነኞቹ የፍትወት ምንጮች:- ምቾት፥ ከባድ ምግብ፥ የአልኮል መጠጥ፥ ብዙ ዕረፍት፥ ፍትወታዊ ትርኢት፥ ፍትወትን የሚቀሰቅሱ ወሬዎችና ተረቶች ናቸው።

የምቾትንና የዕረፍትን ፍትወታዊ ምንጭነት ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑ የሰውነት እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ጠቃሚ ነው። በተለየም ጾም፥ ጸሎትና ስግደት ለዚህ ችግር ዋነኞቹ መፍትሔዎች ናቸው። ፍትወታዊ ትርኢት ከሚታይበት ቦታ ራስን ማራቅና ፍትወትን የሚቀሰቅስ ወሬና ተረት ከመስማት ራስን መግታት ደግሞ ሌሎቹ የችግሩ መፍትሔዎች ናቸው። ከከባድ ምግብና ከሚያሰክር መጠጥ ራስን መግታትንም ብዙዎች የተጠቀሙበት ዘዴ ነው።

<u>ከክፉ ትውስታዎች አሳሳችነት መጠንቀቅ</u>:- በወጣትነት ዘመን ወይም ራሳችንን ለእግዚአብሔር ማስገዛት ከመጀመራችን በፊት እናደርጋቸው የነበሩትን ክፉ ድርጊቶች እንደ አስደሳች ነገር አስታውሰን ያን ድርጊት የምንናፍቅበት ጊዜ ይኖር ይሆናል። ይህም ሰይጣን በሕይወታችን ውስጥ ገብቶ እኛን ወደ ጥፋት ከሚመራበት መንገድ አንዱ ነው። በንስሓ ወደ እግዚአብሔር ከተመለስን በኋላ ያለፈውን በደላችንን የምናስታውሰው በነፍረትና በጥላቻ መሆን አለበት እንጂ አለበለዚያ ግን ታጥቦ ወደ ጭቃ እንደመግባት ይሆን



ብናል። ክፉ ትውስታችን ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከቅዱሳን ታሪኮች ጋር በማነጻጸር ተጸጽተን ማዘንና መተከዝ፥ በደላችንንም ይቅር እንዲለን የእግ ዚአብሔርን ይቅርታ መለመን ይገባናል። ክፉ ነገርም መታወስ ያለበት እን ክፉነቱ ነው እንጂ ከዚያ የተለየ ሊሆን አይገባውም። ክፉነቱን እያወቅን እን አስደሳች ትውስታ አድርጎ የሚያቀርብልን ሰይጣን መሆኑን ዐውቀን የሰ ጣንን ፈተና ድል ለመንሣት ኀይሉንና ችሎታውን እንዲሰጠን ሳንታክ አምላካችንን በጸሎት ልንማጸነው ይገባል።

<u>ከትዕቢት መገታት</u>:- እንደ አጋጣሚ ሆኖ በተለያዩ ምክንያቶች ለምሳ በሀብት፥ በትምህርት፥ በኑሮ ደረጃ ማለት በሹመት፥ በትውልድ፥ በንግግ ችሎታ፥ በሥራ ውጤት መሳካት፥ ባለ ብዙ ወገን በመሆንና በሌሎችም እነዚህን በመሳሰሉ ዓለማዊ ጉዳዮች ከሌሎች ሰዎች የተሻልን እየመሰለን እንኰራለን ወይም እንታበያለን እንጂ ሰውስ በተፈጥሮው በእኩልነት ደረ የተወለደ መሆኑ ግልጥ ነው። በአስተያየት ወይም በአነጋገር ሌሎች ከእኔ ያነ ናቸው የማለት ትዕቢት ያድርብናል። ትዕቢትም እነዚህን በመሳሰሉ ዓለማ ጉዳዮች ላይ ብቻ የተመሠረተ አይደለም። መንፈሳዊ ድርጊታቸውን ሌላ ሰ እንዲያውቅላቸውና በሰዎችም እንዲመሰገኑ የሚፈልጉ ሰዎች አሉ። በዚህ ድርጊታቸው በተመሰገኑ ጊዜ የበለጠ እንዲመሰገኑ ድርጊቶቻቸውን ዘርዝረ ማውራት ይፈልጋሉ። በዚህ ዐይነት ትዕቢታቸውን ይገልጣሉ። ትዕቢት ደግ እግዚአብሔር የማይፈቅደው የሰይጣን ተግባር ነው። ሰይጣን ከታላቅ ክብ ወርዶ ርኩስ መንፈስ ለመባል የበቃው በትዕቢቱ ነው። ትዕቢት የሰይጣን ሥ ነው የሚባለው በዚሁ ምክንያት ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትም እግዚአብሔ አጥብቆ የሚጠላቸውን የኃጢአት ዐይነቶች ሲዘረዝሩ ትዕቢትን ሳይጠቅ አያልፉም።

<u>በመፍራት ምክንያት የእግዚአብሔርን ክብር እንዳንቀንስ መጠንቀቅ</u>: ለዚህ ዓለም ሕይወት ከማሰብና ከመጠንቀቅ የተነሣ እግዚአብሔርን ማክበ በሚገባን ቦታ ፈርተን ሳናከብረው እንቀራለን። ወይም ሰው ሳያውቅብን በድ ብቆሽ ልናከብረው እንፈልጋለን። እርሱ ግን ያለው «በሰው ፊት የሚያፍርብ በሰማዩ አባቴ ፊት አፍርበታለሁ» ነው። ወይም ደግሞ አንዳንድ ችግሮ ሲደርሱብን እምነታችንን በእግዚአብሔር ላይ በማድረግ ፈንታ እንደነ ጣለን፤ ወይም ተስፋ እንቈርጣለን። ጌታችን ግን:- «ልባችሁ አይጨነቅ በእ ዚአብሔር እመኑ፤ በእኔም እመኑ» ብሏል። ማንኛውም አስቸጋሪ ሁኔ በድንገት ሲያጋጥመን ጭንቀታችንን ለእግዘአብሔር ማስረከብ እንጂ አስበን ተጨንቀን በዕድሜአችን ላይ አንዲት ሰከንድ፥ ወይም በቁመታችን ላይ አ ዷት ስንዝር ለመጨመር እንደማንችል ተነግሮናል። መጨነቅና ተስፋ መቁ ረጥ በእግዚአብሔር አለመተማመንን ስለሚያመለክቱ መጠንቀቅ ይኖርብ ል። ጌታችን ግን ያስተማረን:- «ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ በር አንኳኩ ይከፈትላችኋል» ብሎ ነው። እኛም ይህን ጌታችን ያስተማረን ትምህርት ተግባራዊ ካደረግን የእግዚአብሔር እርዳታ አይለየንም።



www.ethiopianorthodox.org

በቍጣ ተነሣሥተን ክፉ ከማድረግና ክፉ ከመናገር መቈጠብ ;- አንዳንድ ጊዜ ከሌሎች ሰዎች ዘንድ ክፉ ነገር ሲያጋጥማቸው የሃይል ዕርምጃ በመውሰድ፥ ወይም ክፉ ነገር በመናገር የበቀል ዕርምጃ የሚወስዱ ሰዎች አሉ። አንዳንዶች ደግሞ ዝም ብለው ሌላውን ሰው የሚያስቀይም ንግግር ይናገራሉ። የኀይል እርምጃም ሆነ ክፉ ንግግር ተመሳሳይ ወይም የባሰ በቀልን ሊያስከትሉ ይችላሉ። ከዚያም በላይ በቀል የእኔ ስለሆነ ክፉ ላደረጉባችሁ ሰዎች ደግ አድርጉላቸው እንጂ ክፉን በክፉ አትበቀሉ ብሎ አምላካችን አስጠንቅቆናል። ለዚህ መፍትሔው እንግዲህ በትዕግሥት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም ሲሆን ያ የማይቻል ከሆነ ግን ቍጣው እስኪበርድ ድረስ ከዚያ ቦታ መራቅ ጠቃሚ ይሆናል። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ክፉ ንግግርን ሲያወግዝ እንዲህ ብሏል:- «ምላስ እንደ እሳት ናት፤ እርስዋ በአካል ክፍሎቻችን መካከል የምትገኝ ክፉ ዓለም ናት፤ ሥጋችንንም ሁሉ ታረክሳለች፤ እንደ ገሃነም እሳት ሰውነታችንን ሁሉ ታቃጥላለች» (ያዕ:ም:3ቍ:6)።

ክፉ ድርጊትን ለማድረግ ከመሞከር መቈጠብ:- አንዳንድ ሰዎች ሌላ ሰው የሚያደርገውን ድርጊት አይተው ለመሞከር ይፈልጋሉ። ለመሞከር የሚፈልጉትም ያ ድርጊት ክፉ መሆኑን እያወቁ ነው። ለምሳሌ ብዙ የአልኮል መጠጥ የሚጠጣ ወዳጅ ወይም ጓደኛ ካላቸው እንደ እርሱ ለማድረግ ይሞክራሉ። እንዲሁም ሲጃራ የሚያጤሱ ጓደኞች ካሏቸው እንደ እነርሱ ማጤስ ይሞክሩና ይቀጥላሉ። ወዳጆቻቸው ቁማር የሚጫወቱ ከሆነ እነርሱም የእነርሱን አሠራር ለመሞከር ቁማር መጫወትን ይጀምሩና ይቀጥላሉ። እንዲሁም ሰዎች በየመዝናኛ ቦታዎች ማምሸትንና ሌሎችን ጐጂ ልማዶችን ከወዳጆቻቸውና ከጓደኞቻቸው ይማራሉ። ታዲያ፥ እነዚህ ሁሉ ነገሮች እንደ ዋዛ ይጀመሩና ከዚያ በኋላ ለመተው ቢፈለግ ለመተው ወደማይቻልበት ደረጃ ይደረሳል። አንድ ጊዜ እነዚህ ክፉ ድርጊቶች ወደ ልማድነት ከተሸጋገሩ በኋላ ሊተውት የሚችሉት ሐሳባቸውንና ፍላጎታቸውን ሊቈጣጠሩ የሚችሉ አንዳንድ ሰዎች ብቻ ናቸው እንጂ ሁሉም አይደሉም።

እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠሉ፥ በሰዎች ዘንድ ያልተመሰገኑ፥ ለጤንነትና ለገንዘብ ቁጠባ የማይበጁ፥ የኅብረተሰቡ ባህል የማይደግፋቸው ናቸው።

ስለዚህ ጉዳት እንጂ ምንም ጠቀሜታ የሌላቸው መሆናቸውን ተገንዝበን ከክፉ ሐሳብና ምኞት፥ ከፍትወት፥ ክፉ ትውስታን ከመናፈቅ፥ ከኵራትና ከትዕቢት ክፉ ነገሮችን ከመስማት፥ በድንተኛ አጋጣሚ በፍርሃትና በድንጋጤ ከመሸበር፥ በቁጣ ተነሣሥቶ የኀይል ዕርምጃ ከመውሰድ፥ ወይ ክፉ ነገር ከመናገር፥ ተስፋ ከመቍረጥ፥ ሌሎች ሰዎች የሚያደርጉአቸውን ክፉ ነገሮች ለማድረግ ከመሞከር ራሳችንን አለመግታት እንደ ባለደመ ነፍሱ እንስሳ ገደብ በሌለው ፍላጎት፥ ስሜትና ምኞት መነዳት ይሆንብናል። አለበለዚያማ ከእንስሳት በምን እንሻላለን?



www.ethiopianorthodox.org

## የመንፈሳዊነትና የግብረ ገብነት ምንጮች

የመንፈሳዊነትና የግብረ ገብነት ምንጮች መጽሐፍ ቅዱስ፥ ትውፊት የኅሊና ፍርድና ባህል ናቸው። እነዚህ አራቱ ምንጮች አብዛኛውን ጊዜ አንድ ዐይነት አስተያየት ቢኖራቸውም እንኳ ልዩነታቸውን ለማሳየት የሚቻልበት ጊዜም አለ።

በመጽሐፍ ቅዱስ በቀረቡት የመንፈሳዊነት መመሪያዎች ላይ ትውፊት በተጨማሪ የሚያቀርባቸው ዝርዝር ሁኔታዎች ከመኖራቸው በቀር የመጽሐፍ ቅዱሱን መመሪያዎች የሚቃረን አይደለም። ለምሳሌ በመጽሐፈ ዲድስቅልያና በፍትሐ ነገሥት ውስጥ የሚገኙት መመሪያዎችና የአምልኮ ሥርዓቶች፥ እንዲሁም በዓለም– ዐቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች (ሲኖዶሶች) ደንቦችና መመሪያዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዝርዝርና በግልጥ የቀረቡ አይደሉም።

በባህል በኩል ግብረ ገባዊ ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸው የኅብረተብ አሠራሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ወይም በትውፊት ውስጥ የሚገኙት ሁላቸውም አይደሉም። ለምሳሌ ከእነዚህ ባህሎች መካከል በዕድሜ የገፉትን ሰዎች አንተ ወይም አንቺ በማለት ፈንታ እርስዎ በማለት ማክበር፥ አሳፈሪ ወይም ጸያፍ ቃል አለመናገር፥ የግድ መነገር ያለበት ከሆነ ለዚያ ለጸያፉ ቃል ሌላ ጸያፍ ያልሆነ አማራጭ ቃል መፈለግን ·የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል። እንዲሁም ኅሊናችን ክፉንና ደግን እንድናውቅ ይረዳናል።

ቅዱሳት መጻሕፍት ከሚዘረዝሩአቸው የመንፈሳዊነት ምልክቶች መካከል:- ፍቅር፥ ሰላማዊነት፥ ታጋሽነት፥ ቸርነት፥ እምነት፥ የዋህነት፥ ራስን መግዛት፥ ታማኝነት፥ መሐሪነት፥ ትሕትና፥ ሰውን አክባሪነትና ሌሎ ችም እነዚህን የመሳሰሉ ጠባዮች ይገኙባቸዋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረውና በኋላም ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደጋግመው እንዳብራሩት ከአምልኮተ እግዚአብሔር ቀጥሎ ፍቅር ትልቁ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው። ፍቅር ያለው ሰው ለሰው ሁሉ ደግነትን እንጂ በማንም ላይ ክፉ ነገርን አያደርግም። ፍቅር ያለው ሰው ሁልጊዜ በጎ ነገርን እንጂ ምንጊዜም ቢሆን ለሰው ክፉ ነገርን አያስብም፤ አይመኝም። ፍቅር ወደ በጎ አስተሳሰብና ወደ በጎ ተግባር ስለሚመራ ፍቅር ያለው ሰው እውነተኛ መንፈሳዊና ግብረ ገበባዊ ለመሆኑ አስተማማኝ ነው። ፍቅርም ሲባል ለሰው ሁሉ የሚኖር በጎ ስሜት ማለት እንጂ ሥጋዊ ፍትወትን ለማርካት በግለሰብ ላይ ያለ ስሜት ለማለት አይደለም። ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛ ትእዛዝ የሆነውን የፍቅር ስሜት በትውፊት፥ በኅሊና ፍርድና በባህላዊ አሠራር ሁሉ የተደገፈ እንጂ በማናቸውም በኩል የማይፈለግ አይደለም።

ፍቅር ካለ ከሁሉም ጋር በሰላም ይኖራል እንጂ ጠብና ክርክር አይኖርም። ከሁሉም ጋር በሰላም ለመኖር መቻል ደግሞ የመንፈሳዊነት ምልክት ነው።

ታጋሽነት ደግሞ ከማንኛውም አቅጣጫ የሚደርስብንን ክፉ ድርጊት አጸፋውን መልስ ሳንሰጥ ዝም ብለን ማሳለፍ ነው። ምናልባት ዘለፋ ወይም ሌላ ክፉ ድርጊት የደረሰብን ጉዳዮችን በትክክል ካለመረዳት የተነሣ መሆኑን ከተገነዘብን ቊጣንና ንዴትን በማያመለክት ቋንቋ ቀስ ብሎ በጥሞና ማስረዳት የታጋሽነት ምልክት ነው። ክፉ አድራጊም ሆነ ክፉ ተናጋሪ እንደዚህ ያለ ታጋሽ ሰው ሲያጋጥመው በድርጊቱ ዐፍሮና ተጸጽቶ ከድርጊቱ ይታቀባል እንጂ በክፉ ድርጊቱ ወደፊት አይቀጥልም። ይህን ስናደርግ ራሳችንን ከክፉ ነገር ከመጠበቃችንም በላይ ለክፉ አድራጊዎች ታላቅ ትምህርትን እናበረ ክታለን ማለት ነው።

ቸርነት ማለት ደግነት፥ ለጋስነት፥ ሳይሰስቱ መስጠትና ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉ በጎ ተግባሮች ናቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጌታችንን በመጥቀስ እንደተናገረው ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ የተባረከ ነው ብሎአል። እንዲሁም በመጽሐፈ መክብብ ም:11ቊ:1ላይ «እንጀራህን በውሃ ላይ ጣለው፤ ከብዙ ቀኖች በኋላ ታገኘዋለህ» ማለቱ ምንም ውለታ ሳትጠብቅ ስጥ፤ በኋላ ግን እግዚአብሔር ዋጋህን ይከፍልሃል ማለቱ ነው። ስለዚህም ቸርነት ከመንፈሳዊ ተግባሮች አንዱ ሲሆን በዚህም መጽሐፍ ቅዱስ፥ ትውፊት፥ ኅሊናና ባህል ይስማሙበታል።

እምነት ሲባል አብዛኛውን ጊዜ ሃይማኖት፥ ማለት በእግዚአብሔር መታመን ማለት ነው። በእግዚአብሔር አምላክነት ማመን ደግሞ ለመን ፈሳዊነት ኑሮ የመጀመሪያው ቅድመ ግዴታ ነው። በእምነታቸው ጠንካሮች ለሆኑ ሰዎች ደግሞ እግዚአብሔር ዋጋቸውን ሳይከፍላቸው አይቀርም። ለዚህ አባባል ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ማስረጃዎችን ቀጥለን እንመልከት:-

ናቡከደነፆር የተባለው የባቢሎን ንጉሥ የወርቅ ጣዖት አሠርቶ ሕዝብ ሁሉ ለጣዖቱ እንዲሰግድለት ባዘዘ ጊዜ ሲድራቅ፥ ሚሳቅና አብደናጎ የተባሉ ሦስት እስራኤላውያን ወጣቶች ለጣዖቱ አልሰገዱም ተብለው በንጉሡ ፊት ተከሰሱ። ንጉሡም እነርሱን አስጠርቶ፥ የመለከትና የእምቢልታ፥ የመሰንቆና የክራር፥ የበገናና የዋሽንት፥ የዘፈንም ሁሉ ድምፅ ስትሰሙ ላቆምሁት ምስል በመሬት ላይ ተደፍታችሁ ብትሰግዱ የተሻለ ነው፤ ባትሰግዱ ግን በሚነድደው የእሳት ነበልባል ውስጥ ትጣላላችሁ፤ ከእጄም የሚያድናችሁ አምላክ እንደሌለ ዕወቁ አላቸው። እነርሱ ግን:- ንጉሥ ሆይ፥ በዚህ ጉዳይ ላይ ራሳችንን የምንከ ላከልበት መልስ ልንሰጥህ አንፈልግም፤ እኛ የምናመልከው አምላክ ከዚህ ከሚነድደው ከእሳት ነበልባልም ሆነ ከአንተ እጅ ሊያድነን ይችላል ብለው በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት ገለጡ። ናቡከደነፆርም በአነጋገራ ቸው ተቈጥቶ በእሳት ነበልባል ውስጥ እንዲጣሉ አዘዘ። የአመኑበትም ጌታ የእሳቱ ነበልባል ምንም ሳይጐዳቸው ከእሳቱ ውስጥ እንዲወጡ ሲያደርግ እነርሱን ወደ እሳት ውስጥ የጣሉአቸውን ሰዎች ግን የእሳቱ ወላፈን አቃጥሎ ገደላቸው (ዳን:ም:3ቊ:25)።



የዋህነት ደግሞ ገርነትና ቅንነት ማለት ነው። የዋህ ሰው ነገሮችን ሁሉ በቅንነት ይቀበላቸዋል እንጂ ክፉ አያስብም፤ ወይም ሰውን በክፉ አይጠ ረጥርም።

ራስን መቈጣጠር ማለት ለሥጋዊ ስሜት ፍላጎት አለመሸነፍ ማለት ነው። ስለዚህ ጉዳይ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉትን እንመልከት:-

«ኀይለኛ ከመሆን ይልቅ ታጋሽ መሆን ይሻላል፤ ብዙ ከተሞችን በጦርነት ድል ነሥቶ ከመያዝ ይልቅ ራስን መቈጣጠር ይበልጣል» (ምሳ: ም:16ቊ: 32)።

ቍጣህን መቈጣጠር ባትችል መጠበቂያ አጥር እንደሌላትና ለጠላት ተጋልጣ እንደምትገኝ ከተማ ትሆናለህ» (ምሳ:ም:25ቊ:28)።

በዚህ ዐይነት ራስን መቈጣጠር በቅዱሳት መጻሕፍት አጥብቆ የተተ ኰረበት መሆኑን ተገንዝበን ድርጊታችንንና አነጋገራችንን መቈጣጠር አለብን እንጂ ሁሉን ነገር እንዳሻን አናደርግም። የሰው ተፈጥሮም ከእንስሳት ከሚለይ ባቸው ጠባዮች አንዱ ራሱን ወይም ፍላጎቱን ለመቈጣጠር መቻሉ ነው።

ታማኝ ማለት እውነተኛ፥ የሚታመን የማይጠረጠር፥ በቃሉ የሚረጋ፥ የሰጠውን ተስፋ የሚፈጽም፥ ሐሳቡን የማይለውጥ፥ ወይም የማይረሳ ማለት ነው። እግዚአብሔር ታማኝ ነው ስንል እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሚሰ ጠውን ተስፋና የሚገባውን ቃል ኪዳን የሚፈጽም መሆኑን ያመለ ክታል።

ቅዱሳት መጻሕፍት ስለታማኝነት ምን ይላሉ?

«እግዚአብሔር ታማኝ ስለሆነ እኛም ለእናንተ የምንነግራችሁ ‹አዎንና አይደለም› በማለት የማወላወል ቃል አይደለም» (2ኛ:ቆ:ም:1ቊ:18)።

«እኛ ታማኞች ባንሆን እርሱ ሁልጊዜ በታማኝነት ይኖራል እንጂ ክርስቶስ ማንነቱን አይክድም» (2ጢሞ ም:2ቊ:13)።

«ወንድሞቼ ሆይ፥ ከሁሉ በፊት በሰማይ ወይም በምድር፥ ወይም በሌላ በምንም ነገር አትማሉ፤ ንግግራችሁ አዎ ከሆነ በእውነት አዎ ይሁን፤ አይደለም ከሆነ በእውነት አይደለም ይሁን፤ እንዲህ ካልሆነ ግን ይፈረ ድባችኋል» (ያዕ:ም:5ቊ:12)።

«በትንሽ ነገር የታመነ ሰው በትልቁ ነገርም የታመነ ይሆናል፤ በትንሽ ነገር የማይታመን ሰው ግን በትልቅ ነገርም አይታመንም» (ሉቃ: ም: 16ቊ:10)።

አንድ ሰው በሌሎች ሰዎች ዘንድ ክብሮትንና ተወዳጅነትን ከሚያገ ኙባቸው ጠባዮች ዋነኛው ታማኝነት ነው። እገሌ ታማኝነት የለውም ከተባለ ማንም ሰው ከዚያ ሰው ጋር ለመዋዋል ወይም ሌላ ቁምነገር ያለው ሥራ ለመሥራት ፍላጎት አይኖረውም። ሰው ሁሉ ከእርሱ ይሸሻል እንጂ ወደ እርሱ መቅረብ አይፈልግም። ታማኝነት ደግሞ ለእግዚአብሔርም ለሰውም ነው። እንዲሁም ታማኝነት የሰውን መንፈሳዊነትና ግብረገብነት ገጽታ ያመለክ

www.ethiopianorthodox.org

ታል። ታማኝነት የሌለው ሰው የመንፈሳዊነት ወይም የግብረገብነት ጠባይ አለው ለማለት አይቻልም።

መሐሪነት ሲባል፥ በደልን ይቅር ባይነት፥ ዕዳን ይቅር ባይነትና ለሰው መራራትን የመሰለ የደግነት ጠባይ ነው። እግዚአብሔር መሐሪ ነው የሚባለው እግዚአብሔር አድርጉ ወይም አታድርጉ ብሎ ያዘዘውን ትእዛዝ በማፍረሳችን ተጸጽተን የእግዚአብሔርን ይቅርታ የለመንን እንደሆነ ይቅርታ አድርጎልን ስለሚምረን ነው። የተበደለ ሰው የበደለውን መበቀል ሲችል፥ ወም ደግሞ በሕጋዊ መንገድ መብቱን ማስከበር ሲችል ለበደለው ሰው ይቅርታ አድር ጎለት የተወው እንደሆነ ምሕረት አደረገለት ይባላል። ይህም ድርጊት መንፈሳዊነት አለው ከሚባል ሰው የሚጠበቅ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትስ ስለ መሐሪነት ምን ይላሉ?

«ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን እወድዳለሁ» (ሆሴ:ም:6ቍ:6)።

«እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድር ነው

ፍርድን ታደርግ ዘንድ፥ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ አይደለምን?» (ሚክ:ም:6ቍ:8)።

«ምሕረትን የሚያደርጉ ምሕረት የሚደረግላቸው ስለሆነ ብፁዓን ናቸው» (ማቴ:ም : :5ቍ:7)።

በቃል የእኔ ነውና ማንንም ሰው አትበቀሉ ያለውን የአምላክን ትእዛዝ አክብሮ ለበደለው ሰው ምሕረት የማያደርግ ሰው መንፈሳዊነት አለው ለማለት አይቻልም።

ትሕትና ከመንፈሳዊነትና ከግብረ ገብነት ጠባዮች አንዱ ነው። ትሕትና ማለት ምን ማለት ነው? አንድ ሰው በፍላጎቱና በፈቃድ ሌሎችን ሰዎች በማክበር ራሱን ዝቅ ማድረግ ትሕትና ነው። ስለትሕትና ቅዱሳት መጻሕፍት ምን ይላሉ?

«በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፤ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ» (2ኛ:16:መ:ም:7ቍ:14)።

«ክብርን መቀበል ከፈለግህ በቅድሚያ ትሑት መሆን አለብህ» (መሳ: ም:15ቍ:33)።

«እግዚአብሔርን መፍራትና ትሑት መሆን ሀብት፥ ክብርና ረጅም ዕድሜ ያስገኛል» (ምሳ:ም:22ቍ:4)።

«መጽሐፍ ‹እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑቶች ግን ጸጋን ይሰጣል› ስለሚል እግዚአብሔር የሚሰጠው ጸጋ ከሁሉ ይበልጣል» (ያዕ:ም:4ቍ:6)።



በዚህም መሠረት መንፈሳዊነትና ግብረገብነት ያላቸው ሰዎች ትሑቶች ናቸው። ቅዱሳት መጻሕፍትም ትሑቶች እንድንሆን ያዝዙናል።

ሰውን ማክበር ደግሞ ከትሕትና ጠባዮች አንዱ ሲሆን ቅዱሳት መጻሕፍት፥ ትውፊታዊው ቅርስና የሕዝባችን ባህል አጥብቀው የሚደግፉት ተግባር ነው። ሰውን ስለማክበር ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉትን ቀጥለን እንመልከት:-

«እግዚአብሔር በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር» (ሮሜ:ም:12ቍ:10)።

«በትሕትና ተሞልታችሁ ሌሎች ሰዎች ከእናንተ እንደሚሻሉ አድርጋችሁ ቍጠሩ» (ፊልጵ:ም:2ቍ:3)።

«ቤተ ክርስቲያንን በመልካም የሚያስተዳድሩ፥ ይልቁንም በመሰበክና በማስተማር የሚደክሙ እጥፍ ክብር ይገባቸዋል» (1ኛ:ጢሞ:ም:5ቍ:17)።

«ሰውን ሁሉ አክብሩ፤ አማኞችን ውደዱ፤ እግዚአብሔርን ፍሩ፤ ንጉሥን አክብሩ» (1ኛ:ጴጥ:ም:2ቍ:17)።

ሰውን ማክበር እንደዚህ አድርጎ በቅዱሳት መጻሕፍት የተደገፈ መሆኑን ልንረዳ እንችላለን።

## ጥያቄዎች

1. የድኅነትን መንገድ መከተል ከፈለግን ምን ማድረግ ይኖርብናል?
2. ከአሳሳቾቹ መንገዶች አርአስት ቢያንስ አምስቱን ተናገር።
3. ወደ ምድራዊ አስተሳሰብ የሚስበን ምንድነው?
4. ከክፉ ትርኢት ለመጠበቅ ምን ማድረግ አለብን?
5? ሳንወድድ በግድ ማየት ካለብን ምን ብናደርግ ይሻላል?
6. ክፉ ሐሳብን ወይም ክፉ ምኞትን በምን እንከላከላለን?
7. ሥጋዊ ጐናችን ያሸንፈን ይሆናል ብለን ብንሰጋ ምን ማድረግ አለብን?
8. ፍትወት ማለት ምን ማለት ነው?
9. ፍትወት ክልክል የሚሆነው እንዴት ሲሆን ነው?
10. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለፍትወት ክልክልነት ምን አለ?
11. የፍትወት ምንጮች ምን ምን ናቸው?
12. የፍትወት መከላከያዎች ምን ምን ናቸው?
13. ክፉ ትውስታ ማለት ምን ማለት ነው?
14. ትውስታዎቹን የሚጠቀምባቸው ማነው?
15. መፍትሔውስ ምንድነው?
16. ኩራትና ትዕቢት ከምን ይመነጫሉ?

www.ethiopianorthodox.org

17. ትዕቢት የማን ሥራ ነው?
18. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትዕቢት የተገለጠው እንዴት ነው?
19. ሰይጣን ከታላቅ ክብሩ ዝቅ ያለው በምንድነው?
20. አንዳንዴ የእግዚአብሔርን ክብር የምንቀንሰው እንዴት ነው?
21. እንዳንፈራ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠን መመሪያ ምን የሚል ው?
22. በቊጣ ተነሣሥተን የምናደርገው ክፉ ነገር ምንድነው?
23. በዚህ ጉዳይ የታዘዝነው ምንድነው?
24. ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ስለምላስ ምን ብሏል?
25. ክፉ ድርጊትን ማድረግ የሚሞከረው በምን በምን ነው?
26. የሙከራው አደገኛነት እምኑ ላይ ነው?
27. በምንስ መከላከል ይቻላል?
28. እነዚህ ነገሮች የተጠሉት በምን ምክንያት ነው?
30. ትውፊት መጽሐፍ ቅዱስን ይቃረናልን?
31. ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ ዝርዝር መመሪያዎች የሚቀርቡባቸው መጻሕፍት ምን ምን ናቸው?
32. በሰዎች ላይ የሚታዩ ከመንፈሳዊነት ምልክቶች የሚቻልህን ያህል ዘርዝር።
33. ከአምልኮተ እግዚአብሔር ቀጥሎ ያለው ታላቁ ትእዛዝ የትኛው ነው?
34. አንድ ሰው እውነተኛ መንፈሳዊና ግብረ ገባዊ ለመሆኑ አስተማማኝ የሚሆነው ምን ሲኖረው ነው?
35. የመንፈሳዊነትና የግብረ ገባዊነት ምንጮች ምን ምን ናቸው?
36. ምንጮቹ እርስ በርሳቸው ይቃረናሉን?
37. መጽሐፍ ቅዱስና ትውፊት በምን ይለያያሉ?
38. ባህል ማለትስ ምን ማለት ነው?
39. ኀሊና ከሌሎቹ ምንጮች በምን ይለያል?
40. እስቲ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተገለጡ ባህላዊ አሠራሮችን አቅርብ።
41. ቅዱሳት መጻሕፍት ከሚዘረዝሩአቸው መንፈሳዊ አዎንታዎች የሚቻልህን ያህል አስታውስ።
42. ፍቅር ማለት ምን ማለት ነው?
43. ታጋሽነት ማለት ምን ማለት ነው?



44. ቸርነት ማለት ምን ማለት ነው?
45. እምነት ማለት ምን ማለት ነው?
46. ታማኝነት ማለትስ?
47. የዋህነት ማለት ምን ማለት ነው?
48. ራስን መግዛት ማለትስ?
49. መሐሪነት ማለት ምን ማለት ነው?
50. ትሕትና ማለት ምን ማለት ነው?
51. ሰውን ማክበርስ?

www.ethiopianorthodox.org

ደብረ ፀሐይ ... ቤተ ክርስቲያን ... ማኅበረ ... ቤተ መጻሕፍት

# ሰባተኛ ክፍል

## ምዕራፍ 1

## ትምህርተ ሃይማኖት

### የእግዚአብሔር ጠባዮች

ጠባይ ማለት የአንድን ፍጡር ምንነት የሚገልጽ ቃል ነው። የእግዚአብሔር ጠባይ ሲባል ደግሞ በእግዚአብሔር ባሕርይ ውስጥ የሚገለጡትን ሁኔታዎች የሚያመለክት ነው።

የእግዚአብሔር ፍጥረቶችን ጠባዮች ለመግለጥ እንደሚቻለው የእግዚአብሔርን ጠባዮች በእኛ ውሱን አስተሳሰብ በትክክል ለመግለጥ አይቻለንም። በተለያዩ አርእስት ሥር ከፋፍሎ ለማስረዳት የተሞከረው ግን እኛ ውሱኖቹ በሚገባን ቋንቋና ለአስተሳሰባችን በሚያመች መንገድ ለማቅረብ ታስቦ ብቻ ነው።

<u>የእግዚአብሔርም ጠባዮች በሁለት አጠቃላይ ርእሶች ሥር ቀርበዋል።</u>

የመጀመሪያው አጠቃላይ ርእስ የእግዚአብሔርን ህልውና የሚመለከት ነው። በዚህ ርእስ ሥር ያሉት የእግዚአብሔር ጠባዮች ለእግዚአብሔር እንጂ ለፍጡር የማይነገሩ ናቸው። ከእነዚህም መካከል:- በማንኛውም ሁናቴ ውሱንነት የሌለው መሆኑ፥ በራሱ የሚኖር መሆኑ፥ የማንም እርዳታ የማያስፈልገው መሆኑ፥ ዘለዓለማዊነቱ፥ አለመለወጡ፥ በሁሉም ቦታ የሚገኝ መሆኑ፥ አለመታየቱና ሙሉ ለሙሉ አለመታወቁ የመሰሉት ጠባዮች ይገኙበታል።

ሁለተኛው አጠቃላይ ርእስ ደግሞ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር ባለው ግንኙት ላይ የተመሠረተ ነው። በዚህ አጠቃላይ ርእስ ሥር ከአሉት ንዑሳን አርእስት መካከል:- ሁሉን ዐዋቂነቱ፥ ጥበበኛነቱ፥ ሁሉን ቻይነቱ፥ ቅዱስነቱ፥ ትክክለኛ ዳኝነቱ፥ ፍቅሩና ደግነቱ፥ እውነተኛነቱና ታማኝነቱ የሚሉት ይገኙባቸዋል። እነዚህ የእግዚአብሔር ጠባዮች ለሰዎችም የሚነገሩ ቢሆኑም እንኳ የእግዚአብሔርና የሰው ጠባዮች አንድ ናቸው ማለት አይደለም። ጠባዮቹ ለእግዚአብሔር የባሕርዩ ሲሆኑ ሰዎች ግን እነዚህን ጠባዮች በተወሰነ ደረጃ የሚያገኙት በእግዚአብሔር እርዳታ ነው።

እንደዚህ ያለውን አከፋፈል አንዳንድ ሰዎች የኅብረትና ኅብረት የሌለው ጠባይ በሚሉ ስሞች ይከፋፍሉታል።



www.ethiopianorthodox.org

### የእግዚአብሔርን ህላዌ የሚያመለክቱ ጠባዮች

በዚህ ርእስ ሥር የሚጠቃለሉት የእግዚአብሔር ጠባዮች ሰብአዊ ፍጡር ሊኖረው የማይችል የእግዚአብሔር የባሕርዩ ገንዘቦች ብቻ ናቸው።እነርሱም ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ቀርበዋል።

1. <u>እግዚአብሔር ውሱንነት የለበትም</u>:- እግዚአብሔርን ምንም የሚወስነው ነገር የለም። እርሱ ከመወሰንና ከሕጸጽ (ጉድለት) ሁሉ የራቀ ነው። ያለምንም ዕቀባና ያለምንም መወሰን ፍጹምነት የእርሱ ገንዘብ ነው። በባሕርዩ ውሱንነት የለበትም። የእግዚአብሔርን ከውሱንነት በላይ መሆን ቅዱሳት መጻሕፍት በተለያዩ ጥቅሶች አረጋግጠዋል።

«የእግዚአብሔርን ታላቅነት መርምረን ልንደርስበት አንችልም፤ የዘመኑንም ልክ ሊቈጥር የሚችል የለም» (ኢዮ:ም:36ቍ:26)።

በሰማይና በምድር፥ በጥልቅ ባሕሮችም እግዚአብሔር የፈቀደውን ሁሉ ያደርጋል» (መዝ:135ቍ:6)።

እግዚአብሔር ታላቅ ነው፤ ከፍተኛ ምስጋናም የሚገባው ነው፤ ታላቅነቱም ሰው ከሚያስተውለው በላይ ነው» (መዝ:14ቍ:3)።

«አምላካችን ታላቅና ኀያል ነው፤ ለዕውቀቱም ወሰን የለውም» (መዝ:147ቍ:5)።

«በእግዚአብሔር ዘንድ ሕዝቦች ሁሉ እንዳሉ የሚቈጠሩ አይደሉም፤ እነርሱ በእርሱ ዘንድ እንደ ኢምንት የሚቈጠሩና ዋጋ የሌላቸው ናቸው» (ኢሳ:ም:40ቍ:17)።

በማንኛውም ነገር የእግዚአብሔርን ውሱን አለመሆን በምንገነዘብበት ጊዜ የፍጹምነቱንም አለመወሰን እንረዳለን። እርሱ በከሀሊነቱ ፍጹም ነው፤ በልዕልናው ፍጹም ነው፤ በዐዋቂነቱ ፍጹም ነው፤ በደግነቱ ፍጹም ነው፤ በጻድቅነቱ ፍጹም ነው፤ በፍቅሩ ፍጹም ነው፤ በሁሉም ነገር ፍጹም ነው። በአንዱ ነገር ፍጹም ሆኖ በሌላው የሚቀንስ አይደለም። ሆኖም ምንም ያኽል ገለጻ ለማድረግ ብንሞክር እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ የማወቅ ችሎታ ሊኖረን አይችልም። ውሱንነት የሌለው እግዚአብሔር ከማንምና ከምንም ጋር ሊመሳሰል አይችልም።

2. <u>የእግዚአብሔር በራሱ መኖር</u>:- የእግዚአብሔር በራሱ መኖር በምንም ነገር ውሱን ካለመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ጠባይ ለእግዚአብሔር እንጂ ለማንኛውም ፍጡር የሚነገር አይደለም።

እግዚአብሔር በራሱ የሚኖር ሲሆን ፍጥረቶቹ ግን በእግዚአብሔር አማካይነት ካልሆነ በቀር በራሳቸው ሊኖሩ አይችሉም። እግዚአብሔር የነበረ፥ ያለና ወደፊትም የሚኖር ነው።

እግዚአብሔር በእውነት ነዋሪና ለፍጥረቶች ሁሉ መገኘት ምክንያት ሲሆን ለእርሱ ለራሱ መገኘት ግን ከእርሱ ከራሱ በቀር ሌላ ምክንያት የለውም። ለእርሱ መገኘት የቀደመ ምክንያት፥ ድርጊት፥ ቁስ አካል፥ ወይም መነሻና መድረሻ የለውም። እርሱም የመጀመሪያው አንቀሳቃሽ እንደመሆኑ ለእርሱ መገኘት ሌላ ምክንያት የለውም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ቍጥር 26 ላይ:- አብና ወልድ በራሳቸው እንደሚኖሩ ወይም በራሳቸው ሕይወት እንዳላቸው የገለጠው በማያሻማ ቋንቋ ነው።

3. <u>የማንም እርዳታ የማያስፈልገው መሆኑ</u>:- እግዚአብሔር የማንም እርዳታ አያስፈልገውም ቅዱሳት መጻሕፍትም በሚቀጥሉት ጥቅሶች ይህን አባባል ያረጋግጣሉ።

«የሰው ሁሉ አምላክ ሆይ፥ አንተ ምንም የሚያስፈልግህ ነገር የለም» (2ኛ:መቃ:ም14ቍ:35)።

«ዓለምና በእርስዋ ያለው ሁሉ የእኔ ነው» (መዝ:50ቍ:12)።

«እግዚአብሔርን እንዲህ አድርግ ብሎ የሚያዝዘው ማነው? እርሱን ማስተማርና መምከር የሚችልስ ማነው? ገለጻ ያደርግለት ዘንድ እግዚአብሔር ማንን አማከረ? ትክክለኛውን መንገድ ያስተማረው ማነው? ዕውቀትን ያስተማረው፥ ወይም ትክክለኛውን መንገድ እንዲያስተውል ያደረገው ማነው? (ኢሳ:ም:40ቍ:13–14)።

«ሕይወትንና እስትንፋስን፥ ሌሎችንም ነገሮች ለሰው ሁሉ የሚሰጥ እርሱ ስለሆነ ምንም ነገር አይጐድለውም፤ የሰውም እርዳታ አያስፈልገውም» (የሐ:ሥ:ም:17ቍ:25)።

«የጌታን ሐሳብ የሚያውቅ ማነው? የእርሱ አማካሪ የሚሆንስ ማነው?» (ሮሜ:ም:11ቍ:34)።

እኛ እግዚአብሔርን የምናመልከው እርሱ የእኛ አምልኮ የሚያስፈልገው ሆኖ አይደለም። እኛ ግን ጸጋውና ሰማያዊ ስጦታው ስለሚያስፈልጉን እናመልከዋለን። እግዚአብሔር የማንም እርዳታ አያስፈልገውም በሚባልበት ጊዜ እንደራስ ወዳድነት መታየት የለበትም። እንዲያውም እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ሁሉን ነገር የሚሰጠው ምንም የውለታ መልስ ሳይጠብቅ ነው።

«እግዚአብሔር ከመንግሥታትና ክብሩም ከሰማያት ሁሉ በላይ ነው፤ እንደ አምላካችን እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም፤ ዙፋኑም ከሁሉ በላይ ነው። ነገር ግን ሰማይንና ምድርን ወደ ታች ይመለከታል፤ ድኾችን ከትቢያ፥ ችግረኞችንም ከዐመድ ቁልል ያነሣቸዋል፤ የልዑላን ጓደኞች ያደርጋቸዋል፤ ከሕዝብም አለቆች ጋር ያስቀምጣቸዋል» (መዝ:113ቍ:4:8)።



«ስሙ ቅዱስና ዘለዓለማዊ ንጉሥ በከፍተኛ ቦታ ላይ የሚኖር ሲሆን ቃላቱ እነዚህ ናቸው፤ ልቡ ከተሰበረና መንፈሱ ትሑት ከሆነው ሰው ጋር በተቀደሰው ከፍተኛ ቦታ ላይ እኖራለሁ፤ ይህንንም የማደርገው በመንፈሱ ትሑት ለሆነውና በልቡ ለተሰበረው ሕይወትን እሰጥና አበረታታ ዘንድ ነው» (ኢሳ:ም:57ቍ:15)።

መጽሐፍ ቅዱስም ሁለት ነገሮችን ያረጋግጥልናል።

የመጀመሪያው ማረጋገጫ እግዚአብሔር የማንም እርዳታ የማያስፈልገው መሆኑ ነው።

ሁለተኛው ማረጋገጫ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ሁሉን ነገር የሚሰጥ መሆኑ ነው።

4. <u>የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊነት</u>:- ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው እግዚአብሔር የማንም እርዳታ የማያስፈልገው በራሱ የሚኖር ህልው ነው። ህላዌውን በሚገልጡት ጠባዮቹ እርሱ ከዘመናት በላይ ሆኖ፥ እርሱ የፈጠራቸው ፍጥረቶች ግን በእርሱ አንቀሳቃሽነት በዘመናት ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ።

እግዚአብሔር መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ነው። እርሱ ከሰብአዊ ፍጡር ከሚለይባቸው ምክንያቶች አንዱ ምክንያት በዘመን ውስጥ መጀመሪያ የሌለውና እንደ ሰው መጨረሻ ኖሮት ሌላ ሕይወት የሚጀምር አለመሆኑ ነው። ስለ እግዚአብሔር ዘለዓለማዊነት ቅዱሳት መጻሕፍት ምን እንደሚሉ እንመልከት:-

«ተራሮችን ከመሥራትህና ዓለምንም ከመፍጠርህ በፊት አንተ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም አምላክ ነህ» (መዝ:90ቍ:2)።

«ለአንተ አንድ ሺህ ዓመት እንደ አንድ ቀን ነው፤ ዐልፎ እንደ ሄደው እንደ ትላንት ነው፤ እንደ ሌሊትም ጥቂት ሰዓቶች ነው» (መዝ:90ቍ:4)።

«እግዚአብሔር ሆይ፥ አንተ ግን ለዘለዓለም ንጉሥ ነህ፤ ስምህም ከትውልድ ወደ ትውልድ ገናና እንደሆነ ይተላለፋል» (መዝ:102 ቍ:12)።

«አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፤ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው፥ እነርሱ ይጠፋሉ፤ አንተ ግን ትኖራለህ፤ እነርሱ እንደ ልብስ ያረጃሉ እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፤ ይወገዱማል» (መዝ:102ቍ:25–26)።

«ግዛትህ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል፤ መንግሥትህም ዘለዓለማዊ ነው» (መዝ:145ቍ:13)።

«የእስራኤል ንጉሥና አዳኝ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር:- እኔ ፊተኛ ነኝ፤ ‹እኔም ኋለኛ ነኝ፤ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም› ይላል» (ኢሳ:ም:44ቍ:6)።



www.ethiopianorthodox.org

«ስለዚህ ለዘለዓለማዊው ንጉሥ፥ ለማይሞተው፥ ለማይታየው፥ ለአንዱ አምላክ ክብርና ምስጋና ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ይሁን፤ አሜን» (1ኛ:ጢሞ:ም:1ቊ:17)።

«እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፥ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፥ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደ ሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ» (2ኛ:ጴጥ:ም:3ቊ:8)።

«ያለው፥ የነበረው፥ የሚመጣውም፥ ሁሉን የሚችል አምላክ አልፋና ዖሜጋ፥ የመጀሪያውና የመጨረሻው እኔ ነኝ ይላል» (ራ:ዮሐ:ም:1ቊ:8)።

በዘመን ውስጥ የምንንቀሳቀስ ውሱኖች ሆነን ሳለን ስለ ዘለዓለማዊነት ለመናገር ጉድለት ያለብን በመሆኑ ዘለዓለማዊነትን በትክክል የማሰብ ዐቅም የለንም። እኛ የምናስበው ያልተወሰኑና መጨረሻ የሌላቸውን ወቅቶች ነው። እግዚአብሔር ግን በፍጹም ከዘመን በላይ ነው። በእርሱ ላይ ዘመን፥ ወይም የዘመን ክፍል የለበትም። እርሱም ለዘመን ሒሳብ የሚገዛ አይደለም። እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር ዘመን ተጀመረ። ስለዚህ እግዚአብሔር የጊዜዎች ወይም የዘመናት ንጉሥ ነው።

ከፍጥረቱ ጋር ባለው ግንኙት የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊነት ስንመለከት ከዘመን በፊት የነበረውና ከዘመን በላይ ያለው እግዚአብሔር በእርሱ ፈቃድ በዘመን ለተገኘው ፍጥረት ፍቅሩን እንደሚያሳየው እንገነዘባለን። በዚህም ዐይነት በዘመን ያልተወሰነው የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊነት በዘመን የሚፈጸም ሥራውን አያደናቅፈውም። እግዚአብሔር ዘመን የሚቆጠርለትን ፍጥረቱን የሚመለከተው በዘለዓለማዊ ብርሃኑ ነው።

5. <u>የእግዚአብሔር አለመለወጥ</u>:- መለወጥ ማለት ቀድሞ ያልነበሩትን ሁናቴ መሆን፥ ወይም ካሉበት ሁናቴ ወደ ሌላ ሁናቴ መዛወር ማለት ነው። ሳይለወጡ፥ ባለው ሁናቴ ጸንቶ መኖር ከዘለዓለማዊነት ጠባይ ጋር የተያያዘ ነው። የእግዚአብሔርም ባሕርይ መቼም ቢሆን ለምንም ዐይነት ለውጥ የሚጋለጥ አይደለም። ስለ እግዚአብሔር አለመለወጥ የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች የሚከተሉት ናቸው።

«እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም» (ሚል:ም:3ቊ:6)።

«ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን አያልፍም» (ማቴ:ም:24ቊ:35)

«ነገር ግን እኛ ኃጢአተኞች ሆነን ሳለ ክርስቶስ በእኛ ምትክ ሞቶአል፤ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር ምን ያኽል ታላቅ መሆኑን ያስረዳል» (ሮሜ:ም:5ቊ:8)።

(የእኛ ኃጢአተኛነት የእግዚአብሔርን ፍቅር አይለውጠውም ማለት ነው)

«እግዚአብሔር ከመረጠና ጸጋውን ከሰጠ በኋላ ባደረገው ነገር አይጸጸትም» (ሮሜ:ም:11ቊ:29)።



«መልካም በጎታ ፍጹም በረከት ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ ይህም የሚመጣው እንደ ጥላ መዘዋወር ወይም መለዋወጥ ከሌለበት ከእግዚአብሔር ነው» (ያዕ:ም:1ቊ:17)።

አለመለወጥ የእግዚአብሔር ባሕርይ በመሆኑ የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊነት ያመለክታል። በእግዚአብሔር ዘንድ ለውጥ ማለት ወደ ዘመን መሠረት መግባት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ነው ስንል እርሱ ከዘመን በላይ ነው ማለታችን ነው። ከዘመን በላይ መሆኑ ደግሞ ዘለዓለማዊነቱንና የማይለወጥ መሆኑን ያመለክታል። ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው እግዚአብሔር በምንም ሁናቴና በምንም ነገር ውሱንነት የለውም ተብሏል።

የእግዚአብሔር ውሱን አለመሆን ጠባይ ደግሞ ጭማሪን ወይም ቅነሳን አይቀበልም። አለመወሰኑ ጭማሪን ወይም ቅነሳን የሚቀበል ከሆነ ውሱን አለመሆኑ ቀረ ማለት ነው። ይህንንም የምንለው እግዚአብሔር በባሕርዩ በሁሉም ነገር ፍጹም ስለሆነ ከዚያ በላይ መጨመር ወይም ከዚያ በታች መቀነስ ስለማያስፈልገው ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ ም:4ቊ:8 ላይ:- «ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል» በማለቱ ይህ የእግዚአብሔርን መለወጥ ያመለክታል የሚል ወገን ይኖር ይሆናል።

ለሰው ልጆች የሚነገሩ ሰብአዊ ጠባዮች ማለት ስሜታዊ እንቅስቃሴዎች ለእግዚአብሔር በሚነገሩበት ጊዜ ለሰው በሚገባ ሰብአዊ ቋንቋ መነገሩ ነው እንጂ የሰዎችና የእግዚአብሔር ጠባዮች አንድ ናቸው ማለት አይደለም። መለዋወጥ የሚስማማቸው ቁሳዊ ነገሮችና የተፈጠረው መንፈስ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ከቁሳዊ ነገር የራቀ ነው። እርሱም በተፈጠረው መንፈስ ደረጃ መታየት የለበትም።

ዓለምንና ሰውን መፍጠርን የመሰሉ በዘመን የተፈጸሙ ድርጊቶች ሲኖሩ ከእግዚአብሔር አለመለወጥ ጠባይ ጋር አብረው መሄዳቸው ለእኛ ለውሱኖቹ ፍጥረቶች ጥልቅ ምሥጢር ነው። በዘመን የሚፈጸሙት የእግዚአብሔር ሥራዎች ከእግዚአብሔር ዘለዓለማዊነት ጋር እንዴት ሊታረቅ እንደሚችል ለእኛ አስተሳሰብ አስቸጋሪ ነው። ይሁን እንጂ ምንም ያኽል ምሥጢሩ ቢረቅቅብን እግዚአብሔር በፈቀደልን መጠን ለማወቅ መሞከር አለብን።

እግዚአብሔር በዘመን የሚሠራቸው ሥራዎች ሁሉ በዘለዓለም ዕቅዱ ውስጥ ከዘመን በፊት የታወቁ ናቸው። የወልደ እግዚአብሔር ሥጋ መልበስ ማለት የመለኮትና የሥጋ ተዋሕዶ ባለመቀላቀል ባለመደባለቅና ባለመለወጥ ነው ስለተባለ ምንም ለውጥን አያመጣም። የእግዚአብሔርን ዕውቀት ጊዜ የማይወስነው ከመሆኑ የተነሣ ሰውን በክርስቶስ አማካይነት የማዳን ዕቅዱ ዘለዓለማዊ ነው እንጂ በኋላ ዘመን አዲስ የመጣ ሐሳብ አይደለም። እግዚአብሔርም በማዳን ዕቅዱ ላይ አልጨመረም ወይም አልቀነሰም። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው ፍቅር አለመለወጡን የምንረዳው ሐዋርያው ቅዱስ



www.ethiopianorthodox.org

ጳውሎስ እንዳለው እ[illegible] መሆኑ ነው (ሮሜ:ም:5ቍ:8)። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ቍጣና ስለመጸጸቱ በሚናገርበት ጊዜ እነዚህና ሌሎችም ሰብአዊ ስሜቶች እግዚአብሔር በሰዎች ላይ ሊያመጣ ያለውን ቅጣት ለመግለጽ ተብሎ ነው እንጂ እግዚአብሔር ሐሳቡን ለወጠ ለማለት የይደለም።

6. <u>እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ የሚገኝ መሆኑ</u>:- በሁሉም ቦታ የመገኘቱ ትምህርት በሁለንተናው በሁሉ ቦታ መገኘት የሚለውን ሥነ መለኮታዊ ትምህርት ያስከትላል። እግዚአብሔር በጊዜ እንደማይወሰን ሁሉ በቦታም አይወሰንም። ስለዚህ እግዚአብሔር በጊዜ ወይም በዘመን ያልተወሰነ፥ ዘለዓለማዊ፥ የማለወጥ፥ በሁሉም ቦታ የሚገኝና በምንም ነገር ያልተወሰነ መንፈስ ነው። የእግዚአብሔር ውሱን አለመሆን ዋናው ምልክት በሁሉም ቦታ መገኘቱ ነው። ይህም የእግዚአብሔርን ህላዌ ያመለክታል። የእግዚአብሔር በሁሉም ቦታ መገኘት ጠባይ ደግሞ የእግዚአብሔር ውሱን አለመሆን ነው። እግዚአብሔርም በሁሉም ቦታ መገኘቱ ማለት በአንድ ወይም በተወሰኑ ቦታዎች ብቻ አለመወሰኑ፥ አንዳችም ነገር ሊይዘው አለመቻሉና ከነገሮች ሁሉ በላይ መሆኑ ምንም ቦታ የማይወስነው መሆኑን ያመለክታል።

ከፍጥረቱ ጋር ባለው ግንኙት ደግሞ እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ ይገኛል ሲባል ምንም ነገር ሳይይዘው እርሱ ሁሉንም ነገር ይይዛል ማለት ነው። እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ ስለመገኘቱ የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች እንመልከት:-

«በውኑ እግዚአበሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ፥ ሰማይ፥ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም» (1ኛ: ነገ:ም 8ቍ:27)።

«ከአንተ ለማምለጥ ወዴት መሄድ እችላለሁ? ከፊትህስ ርቄ ወዴት እሻሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ እዚያ ትገኛለህ፤ ወደ ሙታን ዓለም ብወርድ በዚያም አንተ አለህ። ከፀሐይ መውጫ ባሻገር በርሬ ብሄድ፥ ወይም በፀሐይ በኩል ርቄ ብኖር እዚያ ተገኝተህ በእጅህ ትመራኛለህ፤ በቀኝ እጅህም ትደግፈኛለህ» (መዝ:139ቍ:7–10)።

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- ሰማይ ዙፋኔ ነው፤ ምድርም የእግሬ ማሳረፊያ ናት፤ ታዲያ ለእኔ ምን ዐይነት ቤት ትሠሩልኛላችሁ?» (ኢሳ:ም: 66ቍ:1)።

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- እኔ የቅርብ አምላክ ብቻ ነኝን? የሩቅስ አምላክ አይደለሁምን? እኔ ሰማይንና ምድርን የመላሁ አይደለምን? ሰው በሰውር ቢሸሽግ እኔ አላየውምን?» (ኤር:ም:23ቍ:23–24)።

7. <u>እግዚአብሔርን ማየትና ሙሉ ለሙሉ ማወቅ አለመቻሉ</u>:- እግዚአብሔር ፍጹም መንፈስ ስለሆነ ሊታይና እንዲሁም ሙሉ ለሙሉ ሊታወቅ



አይቻልም። እግዚአብሔርን የሚመስል ከቶ [illegible] ነገር የለም። [illegible] ብልኀትና ሐሳብ የተቀረጸውን ወርቅ ወይም ብር፥ ወይም ድንጋይ እንዲመስል እናስብ ዘንድ አይገባም (የሐ:ሥ:ም:17ቍ:29)።

በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር እስራኤላውያንን አጥብቆ ያዘዛቸው እንዲህ ብሎ ነው:-

«በሰማይም ሆነ በምድር፥ ወይም ከምድር በታች ባለው ውሃ ውስጥ ከሚኖሩት ነገሮች የማንኛውንም ዐይነት ምስል ጣዖት አድርገህ አትሥራ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ እጅግ ቀናተኛ ስለሆንኩ ተቀርጾ የተሠራውን ማንኛውንም ጣዖት አታምልክ፤ አትስገድለትም፤ እኔ የሚጠሉኝን ሁሉ እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ድረስ እበቀላለሁ። ለሚወድዱኝና ትእዛዞቼን ለሚጠብቁ ሁሉ ግን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ዘለዓለማዊ ፍቅሬን አሳያቸዋለሁ» (ዘጸ:ም20ቍ:4–6)።

እነሆ፥ እግዚአብሔር መንፈሳዊ አካል ያለው መሆኑን ብናምንም ይህ የእግዚአብሔር አካል ግን ይህን ይመስላል፤ ይህን ያኽላል፥ ወይም እንደዚህ ያለ ነው ለማለት አንችልም። ለመገመት እንኳ ቢሞከር ለማየት ግን አይቻልም። እግዚአብሔርን ለማየት የሚፈልግ ሰው ሊታይ የማይቻለውን ለማየት መፈለጉ የእግዚአብሔርን ጠባይ አለማወቁ ነው።

እግዚአብሔርን ማንም ያየው ሰው እንደሌለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አረጋግጦአል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔርን ስለማየት ወይም ስለ እግዚአብሔር መገለጥ የተነገሩት አነጋገሮች፥ እግዚአብሔርን አየ የተባለለት ሰው ሁሉ በመለኮታዊ አካሉ ሆኖ አላየውም። ነገር ግን በተለያዩ ሁኔታዎች ምሳሌነት ብቻ አይቶታል።

በዚህም መሠረት አብርሃም እግዚአብሔርን ያየው እንደ ሰው ሆኖ ነው፤ ለሙሴ በእሳት ነበልባል መልክ ተገልጦለታል፤ ለኢሳያስ በራእይ በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦና የልብሱ ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ታይቶታል፤ ለዳንኤል በራእይ በሽማግሌ ሰው መልክ ታይቶታል፤ (ዘፍ:ም: 18፥ ዘጸ: ም:3፥ ኢሳ:ም:6፥ ዳን:ም:7 ቍ:13–14)።

ውሱን የሆነው የሰው ዐይን ውሱንነት የሌለውን እግዚአብሔርን ማየት አይችልም። ፀሐይን ትኵር ብለን በዐይናችን ለማየት የማንችል ከሆነ እንዴት አድርገን እግዚአብሔርን ማየት እንችላለን?

እግዚአብሔር ራሱ ምን እዳለ ቀጥለን እንመልከት:-

«ፊቴን አይቶ ለመኖር የሚችል ሰው ስለሌለ ፊቴን ለማየት አትችልም፤ ነገር ግን እዚህ በአጠገቤ በአለት ላይ የምትቆምበት ስፍራ አለ፤ የእኔ ክብር በዚያ ሲያልፍ በአለቱ ስንጣቂ አቆይሃለሁ፤ እስካልፍ ድረስ በእጄ እጋርድሃለሁ፤ ከዚያም በኋላ እጄን አነሣለሁ፤ አንተም ፊቴን ሳይሆን ጀርባዬን ታያለህ» (ዘጸ:ም:33ቍ:20–23)።



www.ethiopianorthodox.org

መላእክት እንኳ ከሰው በበለጠው ተፈጥሮአቸውና ሁናቴአቸው ችሎታቸው የሚፈቅድላቸውን ያኽል ካልሆነ በቀር እግዚአብሔርን ማየት አይችሉም። ስለዚህም ነው ነቢዩ ኢሳይያስ ሱራፌል የተባሉት መላእክት በክንፋቸው ፊታቸውን ሲሸፍኑ በራእይ ያየው (ኢሳ:ም:6ቍ2)። እግዚአብሔርም ራሱን ለፍጡሩ የሚገልጸው ፍጡሩ በሚችለው መጠን ብቻ ነው።

## ከፍጥረቱ ጋር ባለው ግንኙት የእግዚአብሔር ጠባዮች

የእግዚአብሔር ግርማና ልዕልና በሥራዎቹ ይገለጣል።በእግዚአብሔር ሐሳብ ውስጥ የሚጠቃለሉት ጠባዮች ሁሉን ነገር ዐዋቂ ነቱና ፍጹም ጥበበኛነቱ ናቸው።

በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ የሚጠቃለሉት ጠባዮች ደግሞ ሁሉን ቻይነት፥ ቅዱስነት፥ ጽድቅ፥ ደግነት ወይም ፍቅር፥ እውነተኛነት ናቸው።

ማወቅ የሚገባን ጉዳይ በእግዚአብሔር ፈቃድና በእግዚአብሔር ሐሳብ መካከል ያለው ልዩነት በሰው አስተሳሰብ መሠረት ብቻ መሆኑን ነው: በእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ሐሳብና ፈቃድ በሰዎች ዘንድ እንዳለው ሐሳብና ፍላጎት ተከታታይ አይደሉም። በዚህ አጠቃላይ ርእስ ሥር ያሉት የእግዚአብሔር ጠባዮች ቀጥለው በዝርዝር ቀርበዋል።

1. <u>የእግዚአብሔር ሁሉን ዐዋቂነት:-</u> ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳረጋገጠው:-

«ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም፤ እንዲሁም ከወልድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም፤ ማንም ወልድ ካልገጠለት በቀር አብን ሊያውቅ አይችልም» (ማቴ:ም:11ቍ:27)።

በሌላ አነጋገር ደግሞ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያያል ሲባል ሁሉን ነገር በአንድ ጊዜ እንደማየትና እንደማወቅ ማለት ነው።

በዚህ ትምህርት ላይ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን እንደሚሉ ቀጥለን እንመልከት:-

«እኔ እግዚአበሔር ግን የሰውን አእምሮና የሰውን ልብ እመረምራለሁ፤ ለያንዳንዱም ሰው በአካሄዱና በሥራው መጠን ዋጋውን እሰጠዋለሁ» (ኤር: ም: 17 ቍ:10)።

«ከእግዚአብሔር ፊት የሚሰወር ምንም ፍጥረት የለም፤ በእርሱ ዘንድ ሁሉ ነገር ግልጥና ዕርቃኑን ሆኖ የሚታይ ነው» (ዕብ:ም:4ቍ:13)።

እግዚአብሔር ሁሉን ዐዋቂና ዘለዓለማዊ በመሆኑ ሁሉን ነገር ዕርቃኑን ሆኖ ያየዋል እንጂ ከእርሱ ዕውቀት የሚያመልጥ አንዳች ነገር የለም።

እግዚአብሔር ከዘመን በላይ ዘለዓለማዊ ስለሆነ ያለፈውና ወደፊት የሚመጣው ለእርሱ በአሁኑ ጊዜ እንዳለ ነገር በግልጥ የሚታወቅ ነው። ይህ በእርሱ



ዘንድ አስቀድሞ መታወቁ ደግ ነገርም ቢሆን ወይም ክፉ ነገር የሰውን ልጅ ነጻ ፈቃድና ፍላጎት አይገድበውም። የእግዚአብሔር አስቀድሞ ማወቅ ደግሞ እርሱ ሰውን ወደሚፈልገው አቅጣጫ ይመራዋል ማለት አይደለም፤ ወይም ሰው ሁሉ እግዚአብሔር የወሰነለትን እንጂ ሌላ ለማድረግ መብት የለውም ማለት አይደለም።

2. <u>የእግዚአብሔር ጥበበኛነት</u>:- የእግዚአብሔር ጥበበኛነት ሁሉን ነገር ከማወቁ ጋር የተያያዘ ነው። ይህም የእግዚአብሔር ጥበበኛነት ጠባይ የእግዚአብሔርን ከፍተኛ ዓላማዎች የሚያመቻች ነው። በዚህም ጠባዩ አማካይነት ዓላማዎቹን ተግባራዊ የሚያደርግባቸውን የተሻሉ ዘዴዎችን ይመርጣል። በዚህም መሠረት የእግዚአብሔር ጥበበኛነት ራሱ እንደ እግዚአብሔር ዕውቀት መታየት ይችላል። እርሱም የእግዚአብሔር ዕውቀት ተግባራዊ ጐን ነው ሊባል ይቻላል።

የእግዚአብሔርን ጥበበኛነት በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያቀርባቸው ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«እግዚአብሔር ሆይ፥ አንተ ብዙ ነገሮችን ፈጥረሃል፤ ሁሉን በጥበብ አድርገሃል፤ ምድር አንተ በፈጠረሃቸው ነገሮች ተሞልታለች» (መዝ:104 ቍ:24)።

«እግዚአብሔር ጥበብን ይሰጣል፤ ዕውቀትና ማስተዋልም የሚገኙት በእርሱ ዘንድ ነው» (ምሳ:ም:2ቍ:6)።

«እግዚአብሔር ጥበብን ለጠቢባን፥ ዕውቀትንም ለአስተዋዮች ይሰጣል» (ዳን:ም:2ቍ:21)።

«እርሱ ብቻ ጥበብ ላለው ለአንድ አምላክ በኢየሱስ ክርስቶስ ለዘለዓለም ምስጋና ይሁን፤ አሜን» (ሮሜ:ም:16ቍ:27)።

«ይህም የሆነው በአሁኑ ዘመን በቤተ ክርስቲያን አማካይነት፥ በሰማይ ያሉት አለቆችና ባለ ሥልጣኖች የእግዚአብሔርን ጥበብ በየመልኩ እንዲያውቁ ነው» (ኤፌ:ም:3ቍ/10)።

«ከእናንተ መካከል ጥበብ የጐደለው ቢኖር እግዚአብሔርን ይለምን፤ እግዚአብሔርም ይሰጠዋል፤ እርሱም ምንም ቅር ሳይለው ለሁሉም በልግሥና የሚሰጥ ቸር አምላክ ነው» (ያዕ:ም:1ቍ:5)።

3. <u>የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት</u>:- ለእግዚአብሔር ምንም የሚሳነው ነገር የለም። እርሱ የፈቀደውን ነገረ ያደርጋል እንጂ የማንንም ምክር አይጠይቅም። ማንኛውንም ሥራ ሐሳብ አቅርቦለት ወይም ምክር ሰጥቶት ሊሠራ ያቀደውን ሥራ ሊያስለውጠው የሚችል የለም። የእግዚአብሔርም ሁሉን ቻይነት ፍጹምና በሁሉም ነገር ላይ ነው። በሰማይም ሆነ በምድር እርሱ ከቶ የሚያቅተው ነገር የለም።



www.ethiopianorthodox.org

ስለ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት ከሚቀርቡት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«ከቶ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?» (ዘፍ:ም:18ቍ:14)።

«በሰማይና በምድር፥ በጥልቅ ባሕሮችም፥ እግዚአብሔር የፈቀደውን ሁሉ ያደርጋል» (መዝ:135ቍ:6)።

«ውቅያኖስን በእፍኙ፥ ሰማይንም በስንዝሩ፥ የምድርን ዐፈር በቁና መለካት የሚችል ማነው? ተራራዎችንና ኮረብታዎችንስ በሚዛን የሚመዝን ማነው? እግዚአብሔርን እንዲህ አድርግ ብሎ የሚያዝዘው ማነው? እርሱን ማስተማርና መምከር የሚችልስ ማነው? ገለጻ ያርግለት ዘንድ እግዚአብሔር ማንን አማከረ? ትክክለኛውን መንገድ ያሰተማረው ማነው? ዕውቀትን ያስተማረው፥ ወይም ትክክለኛውን መንገድ እንዲያስተውል ያደረገው ማነው?» (ኢሳ:ም:40ቍ:12–14)።

«ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ በታላቁ ሥልጣንህና ኀይልህ ሰማይንና ምድርን ፈጥረሃል፤ ከቶም የሚሳንህ ነገር የለም» (ኤር:ም:32ቍ:17)።

«ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም» (ሉቃ:ም:1ቍ:37)።

«በእኛ ውስጥ በሚሠራው ኀይል አማካይነት ከምንለምነውና ከመናስበው እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው አምላክ» (ኤፌ:ም:3ቍ:20)።

እግዚአብሔር ሊያደርግ የሚፈቅደውን ነገር ሁሉ የሚያደርግ ቢሆንም ከጠባዩ ጋር የሚቃረን ድርጊት እንደማያደርግ ግን መገንዘብ አለብን። ከጠባዩ ውጪ ደግሞ ፍላጎትም ፈቃድም አይኖረውም። እግዚአብሔርም የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር ማድረግ ይችላል ብንልም ማድረግ የሚችለውን ሁሉ ይፈልገዋል ማለት አይደለም። እግዚአብሔርም ራሱን አይክድም፤እርሱም አይዋሽም።

«እኛ ታማኞች ባንሆን እርሱ ግን ሁልጊዜ ታማኝ ሆኖ ይኖራል፤ ክርስቶስ ማንነቱን አይክድም» (2ኛ:ጢሞ:ም:2ቍ:13)።

«በዚሁ ዐይነት እግዚአብሔር የማይለወጡትንና የማይዋሽባቸውን፥ ሁለቱን ነገሮች ማለትም ተስፋውንና መሐላውን ሰጥቶናል» (ዕብ:ም: 6ቍ: 18)።

4. <u>የእግዚአብሔር ቅዱስነት</u>:- ቅዱስ የሚለው ቃል ትርጒም ከተራ ነገር ወይም ከርኵሰት ልዩ መሆን ማለት ነው። እግዚአብሔር ከርኵስትና ከሕጸጽ (ጕድለት) ነጻ መሆኑን የሚያመለክተው ጠባይ ቅዱስነት ይባላል። በዕብራይስጥና በግሪክ ቅዱስነት ከመለኮት ጋር የተያያዘ ነው።

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ከእግዚአብሔር ጋር የተያያዙ፥ ወይም ለእግዚአብሔር ክብር የተለዩ ሕዝቦች፥ ነገሮች፥ ዕቃዎች፥ ቦታዎችና ድርጊቶች ቅዱሳን ይባላሉ። ለምሳሌ እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች ሲያዝዛቸው እኔ ቅዱስ ስለሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ብሎአቸዋል። ይህንንም ያለው



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከዓለም ሕዝቦች ሁሉ የተለየ የራሱ ሕዝብ አድርጎት ስለነበረ ነው። አብያተ እግዚአብሔር የእግዚአብሔር መገኛ ስለሆኑ ቅዱሳት ይባላሉ፤ እንዲሁም ለምሳሌ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመልክቶቹ ውስጥ ክርስቲያኖች ወይም ምእመናን ለማለት ቅዱሳን ይላል። በቤተ መቅደስም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ለአምልኮታዊ አገልግሎት መገልገያ የሆኑት ዕቃዎች ሁሉ ንዋያተ ቅድሳት ይባላሉ። እንዲሁም ሙሴና ኢያሱ እግዚአብሔርን ያነጋገሩባቸው ቦታዎች የተቀደሱ ስለሆኑ ጫማዎቻቸውን እንዲያወልቁ ታዝዘዋል። ነገሮች ሁሉ የተቀደሱ የሚሆኑት ለእግዚአብሔር ክብር የተለዩ በሚደረጉበት ጊዜ ነው። የሚቀድሳቸውም እግዚአብሔር ነው። ራሱ እግዚአብሔር ግን በባሕርዩ ቅዱስ ነው። ሁሉንም ነገር የሚቀድሰው እርሱ ራሱ ቅዱስ ስለሆነ ነው።

ከውስጣዊ ርኵሰትና ከፉ ስሜት ነጻ መሆኑ፥ የኀሊና ቀጥተኛነትና ፍጹም ደግነቱ፥ የፍርዱና የትእዛዛቱ ትክክለኛ መሆን፥ ምሕረቱ ብዙ፥ ለቍጣ የሚዘገይ፥ ንጹሕ፥ እንዲሁም ፍጡሩን አፍቃሪ የመሆንና ሌሎቹም መለኮታዊ ጠባዮቹ የእግዚአብሔርን ቅዱስነት ያመለክታሉ።

ስለ እግዚአብሔር ቅዱስነት ቅዱሳት መጻሕፍት ከሚያቀርቡአቸው ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«ከቍጥቋጦው መካከል ሆኖ «ሙሴ፥ ሙሴ ብሎ ጠራው፤ ሙሴም ‹እነሆ አለሁ› አለ፤ ወደዚህ አትቅረብ፤ የቆምህባት ምድር የተቀደሰች ስለሆነች ጫማህን አውልቅ አለው» (ዘጸ:ም:3ቍ:4–5)።

«እግዚአብሔር ሆይ፥ ከአማልክት መካከል አንተን የሚመስል ማነው? በቅድስና እንደ አንተ ያለ ባለ ግርማ ማነው?» (ዘጸ:ም:15ቍ:11)።

«እኔ አምላካችሁ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» (ዘሌ:ም:19ቍ:2)።

«ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አንተ ቅዱስ ሕዝብ ነህና በምድር ፊት ከሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ ይልቅ ለእርሱ ለራሱ ሕዝብ ትሆንለት ዘንድ አምላክህ እግዚአብሔር መረጠህ» (ዘዳ:ም7ቍ:6)።

«እግዚአብሔርም እንዲህ አለው:- «በፊቴ የጸለይኸውን ጸሎት ሰምቼ አለሁ፤ እርሱም ለዘለዓለም ለስሜ መጠሪያ እንዲሆን ይህን የሠራኸውን ቤተ መቅደስ ቀድሼዋለሁ፤ ዘወትርም እጠብቀዋለሁ» (1ኛ:ነገ:ም:9ቍ:3)።

«ቅዱስ ስለሆነ አምላካችንን እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ አድርጉት፤ ወደ እግሩም ማረፊያ ስገዱ» (መዝ:99:5)።

«እነርሱ በእውነት ቅዱሳን እንዲሆኑ እኔ ራሴን ቅዱስ አደርጋለሁ» (ዮሐ:ም:17ቍ:19)።

5. <u>የእግዚአብሔር ጽድቅ (ፍትሕ)</u>:- ከእግዚአብሔር ቅድስና ጋር የእግዚአብሔር ጽድቅ መኖሩ ግልጥ ነው። ፍትሕ ማለት ትክክለኛ ፍርድ ማለት ሲሆን ጽድቅ ማለት ደግሞ እውነተኛነት፥ ከሐሰትና ከኃጢአት መለየት ነው። እነዚህ ሁለት ቃላት በእግዚአብሔር ጠባይነታቸው በሚነገሩበት ጊዜ ተወራራሽነት አላቸው። በዚህም ምክንያት አብዛኛውን ጊዜ ጽድቅና ፍትሕ የሚቀርቡት በአንድነት ነው። ስለዚህ ፍትሕ ማለት የትክክለኛ ፍርድን ውሳኔ ማሳለፍ እንደመሆኑ ትክክለኛውን ፍርድ የሚያሳልፈው ሰው እውነተኛ ወይም ጻድቅ ይባላል። ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እግዚአብሔር ፍትሕና ጽድቅ ከሚያቀርቡአቸው ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«እግዚአብሔር ሁልጊዜ በክፉዎች ላይ የሚፈርድ ትክክለኛ ዳኛ ነው» (መዝ:7 ቍ:11)።

«እርሱም ዓለምን በፍትሕ ያስተዳድራል፥ ለሕዝቡም ቀጥተኛ ፍርድን ይሰጣል» (መዝ:9ቍ:8)።

«እግዚአብሔር በምድር ላይ ሊፈርድ ስለሚመጣ በደን ውስጥ ያሉ ዛፎች ሁሉ እልል ይበሉ፤ በዓለም ላይ በጽድቅ፥ በሰዎችም ላይ በእውነተኛነት ይፈርዳል» (መዝ:96ቍ:13)።

«እግዚአብሔር በአካሄዱ ሁሉ እውነተኛ ነው፤ በሥራውም ሁሉ ታማኝ ነው» (መዝ:145ቍ:17)።

«እንግዲህ አንተ ንስሓ ባለመግባትህና እልኸኛ በመሆንህ የእግዚአብሔር ቍጣና ትክክለኛ ፍርድ በሚገለጥበት ቀን ቅጣትህ እንዲበዛ ታደርጋለህ» (ሮሜ:ም:2ቍ:5)።

«የእግዚአብሔር ፍርድ እንዴት የማይመረመር ነው (:ሮሜ:11፥33)።

«እያንዳንዱ በምድራዊ ሕይወቱ ላደረገው ክፉም ሆነ ደግ ነገር እንደየሥራው ዋጋውን ለመቀበል ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት መቅረብ አለብን» (2ኛ:ቆሮ:ም:5ቍ:10)።

«ትክክለኛው ፈራጅ ጌታ» (2ኛ:ጢሞ:ም:4ቍ:8)

«ለማንም ሳያዳላ በእያንዳንዱ ላይ እንደየሥራው የሚፈርደው እግዚአብሔር» (1ኛ:ጴጥ:ም:1ቍ:17)።

ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው ስለ እግዚአብሔር ተግሣፅና ቍጣ በሚነገርበት ጊዜ በሰብአዊ ቍጣ ዐይነት ሆኖ መታሰብ የለበትም። እግዚአብሔር እንደ ሰው ልጆች በስሜታዊነት ወይም በግብተኝነት የሚመራ አይደለም። እነዚህ ሰብአዊ ስሜትን ሚያመለክቱት ቃላት ስለ እግዚአብሔር በሚነገሩበት ጊዜ የሰውን ልጅ በጥፋቱ የሚቀጣው መሆኑን ለማመልከት ብቻ ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ ካለ በኋላ የጥፋትን ውሃ አዘነበ። እንዲሁም እግዚአብሔር በነነዌ ሰዎች ላይ ሊያመጣባቸው በነበረው



ጥፋት ተጸጸተ ካለ በኋላ ለነነዌ ሰዎች ምሕረት አደረገላው። ሌሎችም ተመሳሳይ ምሳሌዎችን ማቅረብ ይቻላል።

6. <u>የእግዚአብሔር ፍቅርና ደግነቱ</u>:- ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ደግነት በመንነጋገርበት ጊዜ የእርሱ ደግነት ከሌላ ሁሉ የተለየ መሆኑን መገንዘብ አለብን። እግዚአብሔርም የደግነት ሁሉ ምንጭ ሲሆን የደግነቱም ዐይነት ፍጡር ከሚኖረው ደግነት የተለየ ነው። የሰዎች ደግነት ከእግዚአብሔር ደግነት ጋር ሊነጻጸር አይችልም። ደግነት በባሕርዩ ያለ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ደግነትም ከእግዚአብሔር ጠባዮች አንዱ ነው።

እግዚአብሔር ደግ ነው፤ መሐሪ ነው፤ በአጠቃላይም ፍቅር ነው በምንልበት ጊዜ እግዚአብሔርን እንደ ስሜታዊ ልንቈጥረው አይገባም። ቀደም ተብሎ እንደተነገረው እግዚአብሔር አይለወጥም እንደሰውም በስሜታዊነት አይመራም፤ ነገር ግን ሥራዎቹ ሁሉ በፍጹም ከራሱ እንደሚወጡ ብቻ ይመለከቷል።

የእግዚአብሔር ፍቅር ውሱንነት ከሌለበትና ፍጹም ከሆነው ከራሱ የሚመነጭ ነው። እዚህ ላይ የአብ ፍቅር በወልድ ዘንድ ይገለጣል።

ከራሱ ዐልፎ ወደ ፍጡሩ አቅጣጫ የሚያመራው ፍቅርና ደግነት የሚታየው በደግነቱ ነው። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የፈጠረው በራሱ ማለት በደግነቱ ነው እንጂ ሌላ ምንም ፍላጎት ኖሮት አይደለም።

እግዚአብሔር ደግነቱ አነሣሥቶት ስለ ፈጠረው ፍጥረት ምክንያት፥ ስለ እግዚአብሔር ደግነትና ፍቅር ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉትን እንመልከት:-

«በአንተ ለመከለል ወደ አንተ ለሚጠጉ፥ በሰዎች ሁሉ ፊት የምትሰጠው ለሚፈሩህ ያዘጋጀኸው ደግነት ምንኛ ትልቅ ነው? (መዝ:31ቍ:19)።

«ጽድቅንና ፍርድን ይወድዳል፤ የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላች» (መዝ:33ቍ:5)።

«የእግዚአብሔርን ደግነት እዩና ቅመሱ፤ እርሱን ከለላ ያደረገ የተባረከ ነው» (መዝ : 34 ቍ:8)።

«ምግባቸውን በጊዜው ትሰጣቸው ዘንድ እነዚህ ሁሉ አንተን ተስፋ ያደርጋሉ» (መዝ:104ቍ:27)።

«ምሕረትህ በሰማይ ላይ ታላቅ ናት፤ እውነትህም እስከ ደመና ድረስ ነው» (መዝ:108ቍ:4)።

«እግዚአብሔርን አመስግኑ ቸር ነውና ምሕረቱም ለዘለዓለም ነውና» (መዝ:118 ቍ:1)።

«ኃጢአተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንጂ ይሞት ዘንድ አልፈቅድም ይላል ጌታ እግዚአብሔር» (ሕዝ:ም:33ቍ:11)።



www.ethiopianorthodox.org

«ጌታ ለረጅም ጊዜ ይታገሣልና ኃጢአት ሠርቼ ምን ..ረሰብኝ አትበል» (ሢራ:ም:5ቍ:4)።

«እርሱ ለውለታቢሶችና ለክፉዎች እንኳ ሳይቀር ቸር ነው» (ሉቃ:ም:6ቍ:35)።

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳ ይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲህ አድርጎ ወድዶታል» (ዮሐ:ም:3ቍ:16)።

«የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነትን እንዲያውቁ ነው» (1ኛ:ጢሞ:ም:2ቍ:4)።

«አንዳንድ ሰዎች እንደሚመስላቸው ጌታ ኢየሱስ የተናገረውን የተስፋ ቃል ለመፈጸም አይዘገይም፤ ነገር ግን ሰው ሁሉ ለንስሓ እንዲበቃ እንጂ ማንም ሰው እንዳይጠፋ ፈልጎ ስለ እናንተ ይታገሣል» (2ኛ: ጴጥ: ም3 ቍ:9)።

7. <u>የእግዚአብሔር እውነተኛነትና ታማኝነት</u>:- ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ እንዳለው እግዚአብሔር እውነተኛ ነው (ዮሐ:ም:3ቍ:33)። ባለመዝሙሩም «የእግዚአብሔር መንገዶች ሁሉ ምሕረትና እውነት ናቸው» ብሎአል (መዝ: 25፥10)።

በዚህም መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር ሐሰት፥ ቃል ኪዳን አለመጠበቅና ቀጠሮ ማፍረስ እንደሌለበት ይገልጣል። ቀደም ተብሎ እንደተ ገለጠው እግዚአብሔር በሁሉም ነገር ፍጹም ነው፤ ውሰንነትም የለበት። እግዚአብሔር በኀያልነቱ፥ በደግነቱና በዐዋቂነቱ ውሱንነት የለበትም። እነዚ ህም ጠባዮች እርሱ በአነጋገሩና በቃል ኪዳኑ ታማኝና እውነተኛ መሆኑን ያመለክቱናል።

ስለ እግዚአብሔርም እውነተኛነትና ታማኝነት ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያቀ ርቡትን ምስክርነት እንመልከት:-

«እግዚአብሔር እንደ ሰው አይዋሽም፤ ሐሳቡንም እንደ ሰው አይለ ውጥም፤ የሰጠውን ተስፋ ሁሉ ይፈጽማል፤ የተናገረውንም ነገር ሁሉ ያደርጋል» (ዘኍ:ም:23ቍ:19)።

«የእስራኤል ክብር እግዚአብሔር አያብልም፤ ሐሳቡንም አይለውጥም፤ እርሱ እንደ ሰው ስላልሆነ ሐሳቡን አይለውጥም» (1ኛ:ሳሙ:ም1.ቍ:29)።

«እኛ ታማኞች ባንሆን እርሱ ግን ሁልጊዜ ታማኝ ሆኖ ይኖራል፤ ክርስቶስ ማንነቱን አይክድም» (2ኛ:ጢ.ሞ:ም:2ቍ13)።

«ይህም ሃይማኖት በዘለዓለም ሕይወት ተስፋ ላይ የተመሠረተ ነው፤ የማይዋሸው አምላክ ይህን ሕይወት ለመስጠት ከዘመናት በፊት ቃል ገባልን» (ቲቶ:ም:1ቍ:2)።



www.ethiopianorthodox.org

«ሰዎች ሲምሉ ከራሳቸው በሚበልጥ ስም ይምላሉ፤ ንግግራቸውንም በመሐላ በማጽናት በመካከላቸው ያለውን ክርክር ሁሉ ያስወግዳሉ፤ በዚህ ዐይነት እግዚአብሔር ውሳኔው የማይለወጥ መሆኑን ለማስረዳት ፈልጎ ለተስ ፋው ወራሾች ተስፋውን በመሐላ አጸናላቸው። በዚሁ ዐይነት እግዚአብሔር የማይዋሽባቸውንና የማይለወጡትን ሁለቱን ነገሮች፥ ማለትም ተስፋውንና መሐላውን ሰጥቶናል» (ዕብ:ም:6ቍ:16–18)።

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለሰዎች መታለልንና መሳሳትን ሲፈቅድ ከእውነተኛነቱና ከታማኝነቱ ጋር እንዴት ይታረቃል? ተብሎ ይጠየቅ ይሆ ናል። ለምሳሌ በ1ኛው መጽሐፈ ነገሥት ምዕራፍ 22 ላይ ብንመለከት ንጉሥ አክዓብ በሐሰት ትንቢት እንዲታለል ፈቅዶአል።

ንጉሥ አክዓብ በሐሰተኛ ትንቢት ሲታለል ለመታለሉ እግዚአብሔር ምክንያት ሆኖአል ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ንስሓ እንዲገቡ ለማድረግ ብዙ ዕድል ይሰጣቸዋል። የማይመለሱ ሆነው ሲያገኛቸው ግን ይተዋቸዋል እንጂ አያስገድዳቸውም። ተመሳሳይ አባባሎች በሁለተኛው ተሰሎንቄ ም:2ቍ:1–12 ይነበባል።

እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረ ጊዜ በሰጠው ነጻ ፈቃድ መሠረት የመታለሉ ምክንያት ሰው ራሱ ነው እንጂ እግዚአብሔር አይደለም።

8. <u>የእግዚአበሔር መንፈስነት</u>:- በዚህ የእግዚአብሔርን መንፈስነት ጠባይ በተመለከተ በሚቀርቡት ማስተረጃዎች ረገድ የተለያዩ አስተሳሰቦች ተሰን ዝረዋል። ለምሳሌ:- በኦሪት ዘፍጥረት ም.1፥ ቍ.26 ላይ እግዚአብሔርም አለ «ሰውን በመልካችንና በአምሳያችን እንፍጠር» ካለ በኋላ በትንቢተ ኢሳይያስ ም.40 ቍ.18 «እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ ወይስ በምን ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ» ይላል። እንዲሁም በኦሪት ዘጸአት ም.24 ቍ:9–10 ሙሴ፥ አሮን፥ ናዳብና አቢሁ ከእስራኤል ሰባ ሽማግሌዎች ጋር ወጥተው እግዚአብሔርን እንዳዩ ተገልጾአል። በዮሐንስ ወንጌል ም.4 ቍ. 24 እና ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ም.3 ቍ.17 መሠረት እግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ በኦሪት ዘጸአት ም.33 ቍ.20፥ በዮሐንስ ወንጌል ም.1 ቍ.18 እና በመጀመሪያ ወደ ጢሞቴዎስ በተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ም.6 ቍ.16 ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔርን ማንም ያየው ሰው አለመኖሩንና እግዚአ ብሔርንም አይቶ በሕይወት ለመኖር የማይቻል መሆኑ ተገልጦአል።

በዚህ ጉዳይ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በሁለት ዐይነት አስተሳሰብ ይለያያሉ።

የመጀመሪያዎቹ ወገኖች እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጡር ማለት ሰውን እንደሚመስልና ነቢያትና ጻድቃንም ሊያዩት እንደቻሉ ያምናሉ። ለዚሁ እምነታቸው ከሚያቃርቡአቸው ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸ ዋል:–

በኦሪት ዘፍጥረት ም.1 ቍ.26 ላይ «ሰውን በመልካችንና እንደ ምሳሌ አችን እንፍጠር» ማለቱ የእግዚአብሔር መልክ ልክ እንደ ሰው መልክ መሆኑን ያመለክተናል ይላሉ።

በኦሪት ዘጸአት ም.33 ቍ. 18–23 ላይ እግዚአብሔር ክብሩን እንዲ ያሳየው ሙሴ ለለመነው ልመና መልስ ሲሰጠው «እስካልፍ ድረስ እጄን በላይህ እጋርዳለሁ፥ ጀርባዬንም ታያለህ» ማለቱ እግዚአብሔር የሰው ዐይነት አቋም ኖሮት በስተጀርባው ለመታየት መቻሉን ነው ይላሉ።

በኦሪት ዘኍልቍ ም. 12 ቍ: 8 ላይ እግዚአብሔር ከአሮንና ከማርያም ጋር የተግሣፅ አነጋገር በተነጋገረ ጊዜ የእግዚአብሔርን መልክ እንደሚያይ ለሙሴ መስክሮለታል።

«ለእግዚአብሔር ዐይን፥ ጆሮ፥ እጅ፥ እግር እንዳለው የተነገረው ሁሉና ስለ እግዚአብሔር በከበሩ መጻሕፍት የተጻፈው ሁሉ የታመነ፥ የተረዳ ነው፤ የተናገርነው ሁሉ ለእግዚአብሔር አለው ተብሎ በቅዱስ አትናቴዎስ ጽሑፍ መገለጹ እግዚአብሔር በእኛ ሰውነት ውስጥ የሚገኙት የአካል ክፍሎች ያሉትና አቋሙ ሁሉ ሰውን እንደሚመስል ያመለክተናል» ይላሉ (ሃይ.አበ. ገጽ 88)።

የሁለተኛዎቹ ወገኖች አስተሳሰብ ደግሞ እንደሚከተለው ነው። በመልካ ችንና እንደ አምሳያችን ማለት ሥጋዊ ሰውነታችን እግዚአብሔርን ይመስላል ማለት ሳይሆን እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በምድር በፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ላይ የበላይነትን ስለሰጠውና የማትሞት ነፍስን በመስጠት ከሌሎቹ ፍጥረቶች ስላስበለጠው፥ እንዲሁም የሰው ልጅ አልጠበቀውም እንጂ እንደ እግዚአ ብሔር ጻድቅና ቅዱስ እንዲሆን ፈጥሮት ስለነበረ በእግዚአብሔር አምሳያ ተፈጠረ ተባለ።

በልዩ ልዩ ጊዜዎች አንዳንድ የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔርን ያዩት በተለያየ ሁኔታ ሆኖ ነው እንጂ እግዚአብሔርን ራሱን ያየው ማንም የለም። ይህንን አባባል ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ በኦሪት ዘጸአት ም.33 ቍ:18–21 በሚነበበው ቃለ እግዚአብሔር የሙሴን ልመናና የእግዚአብሔርን መልስ እንመልከት።

«ሙሴም እባክህን ክብርህን አሳየኝ አለ፤ እግዚአብሔር እኔ መልካምነቴን ሁሉ በፊትህ አሳልፋለሁ፤ የእግዚአብሔርንም ስም በፊትህ አውጃለሁ፥ ይቅርም የምለውን ይቅር እላለሁ፤ የምምረውንም እምራለሁ፤ ደግሞም ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለ።»

እንግዲህ ቀደም ተብሎ በተጠቀሰው ጥቅስ ከሌሎቹ ነቢያት ሁሉ የበለጠ ለእግዚአብሔር ቅርብነት እንዳለው እግዚአብሔር ራሱ የመሰከረለት ሙሴ የእግዚአብሔርን መልክ ያያል የተባለው በሕልሙ ሳይሆን በውኑ እግዚአ ብሔርን መሰል ሁናቴ ያያል ማለት ነው።



ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም.1ቍ:1እና 2 ላይ እንዲህ ተብሎአል:-

«ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ልዩ ልዩ መንገድ ለአባቶቻችን በነቢያት አማካይነት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገውና ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን።»

ይህ አባባል በግልጽ የሚያስረዳው እግዚአብሔር ለነቢያትና ለደጋግ ሰዎች የተገለጸላቸው በተለያየ መንገድ እንጂ በአንድ ዐይነት መንገድ አለመሆኑን ነው።

በዚህም መሠረት ለሙሴ በእሳት ነበልባል መልክ ተገልጾለታል፤ ለኢሳያስ በራእይ በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦና የልብሱ ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ታይቶታል። እንዲሁም ለዳንኤል በራእይ በሽማግሌ ሰው መልክ ታይቶታል (ዘጸ.ም. 3 ቍ.2–6፥ኢሳ. ም. 6 ቍ.1 ዳን. ም. 7 ቍ.13)።

ሙሴም ለእስራኤል ልጆች ገለጻ ባደረገላቸው ጊዜ እግዚአብሔርን ያላዩ መሆናቸውን ዘርዝሮ ያስረዳቸው በሚከተለው ሁናቴ ነው።

«እናንተም ቀርባችሁ ከተራራው በታች ቆማችሁ ነበር፤ እስከ ሰማይም መካከል ድረስ እሳት በተራራው ይነድድ ነበር፤ ድቅድቅ ጨለማም ነበር። እግዚአብሔርም በእሳት ውስጥ ሆኖ ተናገራችሁ የቃልን ድምፅ ሰማችሁ፤ መልክ ግን አላያችሁም፤ ድምፅን ብቻ ሰማችሁ፤ እግዚአብሔር በኮሬብ በእሳት ውስጥ ሆኖ በተናገራችሁ ጊዜ መልክ ከቶ አላያችሁምና እጅግ ተጠንቀቁ እንዳትረከሱ» (ዘዳ.ም.4 ቍ. 11–12 እና ቍ. 15)።

የእግዚአብሔርን መልክ አይቶ በሕይወት ለመኖር አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለተነጋገረ ብቻ እንኳ ፊቱ በጣም በማንጸባረቁ የእስራኤል ልጆች የሙሴን ፊት ማየት ያቃታቸው መሆ ኑን በኦሪት ዘጸአት ም. 34 ቍ. 30–35 እንመልከት።

እግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ በሕዋሳታችን አማካይነት ልናውቀው የምንችል አንድ ነገር፥ ወይም የአንድ ነገር አንድ ክፍል አይደለም። ይህም ማለት የማይከፋፈልና የማይለያይ፥ መቀላቀልና መሰባሰብ የሌለበት፥ በዐይን ሊታይ የሚችል ውሱን ትርኢት ያይደለና በሰውነታችን ሕዋሳት ሊዳሰስ የማይቻል ነው። ይህም በመሆኑ ለውሱን ነገሮች የሚሰጡት እንደ ክብደት፥ የመጠን ትንሽነትና ትልቅነት በመሳሰሉት ቃላት መግለጫ ማድረግ ተገቢ አይደለም። ስለዚህ ነቢዩ ኢሳይያስ «እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመሳሰ ሉታላችሁ? ወይስ በምን ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ?» ብሎአል (ኢሳ.ም.40 ቍ.18)።

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የእግዚአብሔር እጆች፥ ጣቶች፥ ዐይኖችና ጆሮዎች ተብለው የተነገሩበት ምክንያት ሊገባን በሚችል በሰው ልጅ ቋንቋ ካልሆነ በቀር እግዚአብሔር መንፈስ እንደመሆኑ የመንፈስን ድርጊት ልንረዳ

www.ethiopianorthodox.org

የማንችል በመሆናችን ነው እንጂ እግዚአብሔር በሰው ልጆች ቅርጽ ውሱን የሆኑ የአካል ክፍሎች አሉት ለማለት አይደለም።

በዚህም መሠረት የእግዚአብሔር እጅ ሲባል ኀይሉ፥ ጥበቡና ደግነቱ፥ መለኮታዊ ጥበቃውና እንዲሁም የእግዚአብሔር ኀይለኛ ቅጣት ማለት ለመሆናቸው የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት።

ኀይሉ ለመሆኑ:- «በጸናች እጅና በተዘረጋች ክንድ እስራኤልን ከመካከላቸው አወጣ» ተብሏል (መዝ:136፥11–12)።

ጥበቡና ደግነቱ ለመሆኑ:- «አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፤ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው» ተብሎአል (መዝ.105 ቍ:25)።

መለኮታዊ ጥበቃው ለመሆኑ:- «አቤቱ ነፍሴን ለእጆችህ እሰጣለሁ» ተብሎአል (መዝ. 31ቍ.5)።

ኀይለኛ ቅጣት ለመሆኑ:- «በቀንና በሌሊት እጅህ ከብዳብኛለች» ተብሎ አል (መዝ.32ቍ.4)።

የእግዚአብሔር ዐይንና ጆሮ ተብሎ በሚነገርበት ጊዜ ደግሞ በሰማይም ሆነ በምድር የሚደረገውን ማንኛውንም ድርጊት ሁሉ እንደሚያውቀው ለመግለጽ መሆኑን ለመረዳት የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት።

«እግዚአብሔር ከሰማይ ተመለከተ፤ የሰውንም ልጆች ሁሉ አየ፤ ከማደሪያው ቦታ ሆኖ በምድር ወደሚኖሩ ሁሉ ተመለከተ» (መዝ. 33 ቍ. 13–14)።

«ጆሮን የተከለው አይሰማምን? ዐይንን የሠራው አያይምን?» (መዝ.94 ቍ.9)።

«ማንኛውም ፍጡር ከእግዚአብሔር ሊደበቅ አይችልም ሁሉም ለዐይኖቹ የተጋለጠና ያልተሰወረ ነው» (ዕብ.ም.4ቍ.15)።

ስለእግዚአብሔር ፊት የተነገሩትን ጥቅሶች በሚመለከት ደግሞ ለአብርሃም፥ ለሙሴ፥ ለዳንኤልና ለሌሎችም የእግዘአብሔር ወዳጆች፥ አምላክ በሰው መልክ የተገለጠላቸው መሆኑ ይታወሳል። ይሁን እንጂ በኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 33 ቍጥር 20 እና በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ቍ. 18 ላይ በተገለጠው መሠረት እግዚአብሔርን ማንም ያየው ሰው አለመኖሩንና እግዚአብሔርን አዩ ተብሎ የተነገረላቸው የእግዚአብሔር ወዳጆች እግዚአብሔርን አዩት ወይም ደግሞ እግዚአብሔር እንደሰው ልጅ ውሱን የሆነ መልክና ቅርጽ አለው ለማለት አይደለም። እነዚያም የተጠቀሱት የእግዚአብሔር ሰዎች ታማኞች ለሆኑ ባርያዎቹ መልካም ፈቃዱን ለመግለጽ ሲል አንዳንድ ጊዜ የሚገለጥበትን ጊዜያዊ የሆነውን የሰውነት ቅርጽ አዩ እንጂ እግዚአብሔርን አላዩም።



## <u>የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት</u>

<u>ቅዱስ ጎርጎርዮስ፥ ገባሬ ተአምራት</u>:- «የሰውን ባሕርይ እስኪዋሐድ፥ ዘመዳቸውም ሆኖ ሰውን ሁሉ ወደ እርሱ እስኪያቀርብ ድረስ ሰው ፊትህን አይቶ ሕያው መሆን አይቻለውም ነበር» (ሃይ.አበ. ገጽ 45)።

<u>ቅዱስ ጎርጎርዮስ፥ የእንዚናዙ</u>:- «በባሕርየ መለኮቱ የማይታይ ሲሆን እርሱም የሌለበት ቦታ የሌለ ሲሆን በቦታው ሁሉ ሙሉ የሚሆን እርሱ እንደምን ይታያል?» (ሃይ:አበ:ገጽ:251)።

<u>ቅዱስ ቄርሎስ፥ ዘእስክንድርያ</u>:- «መለኮት ልክ፥ መጠን የለውምና በአንደበት ሊነገር አይቻልም፤ ልቡናም መርምሮ አይደርስበትም» (ሃይ አበ፥ ገጽ 276)።

«ሥጋን በመልበስ ሰው ባይሆንና በአምር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ባይገለጥ ፍጡራን ሊያዩት ባልቻሉም ነበር፤ ሊያዩት የማይችሉም ሰዎች ብቻ አይደሉም፤ መልካቸው ልዩ ልዩ የሚሆን የሚያመሰግኑ ረቂቃን የሚሆኑ በሰማይ ያሉ መላእክትም በነበረበት ባሕርዩ ያዩት ዘንድ ባልቻሉም ነበር እንጂ» (ሃይ. አበ ገጽ፥ 300)።

<u>አባ ሕርያቆስ፥ ዘብህንሳ</u>:- «መጠንና መመርመር የሌለበት እሳተ መለኮት በሆድሽ ዐደረ። በምድራዊ እሳት እንመስለው ዘንድ አይገባም፤ ለእሳትስ መጠን አለው፥ ልክም አለው። መለኮት ግን ይህን ያኽላል፤ ይህንም ይመስላል ሊባል አይቻልም። ለመለኮት እንደ ፀሐይና እንደ ጨረቃ ክበብ፥ እንደ ሰውም መጠን ያለው አይደለም፤ ድንቅ ነው እንጂ፤ የሰው ኅሊና፥ የመላእክትም አእምሮ በማይደርስበት በአርያም የሚኖር ነው እንጂ። ለመለኮት ወርድና ቁመት፥ ላይና ታች፥ ቀኝና ግን ያለው አይደለም፤ በሁሉ የመላ ነው እንጂ፤ ለመለኮት የሚዘረጋበትና የሚሰበሰብበት ያለው አይደለም፤ ግዛቱ ባገር ሁሉ ነው እንጂ ለመለኮት በላይ ጠፈር በታችም መሠረት ያለው አይደለም፤ ጠፈሩ እርሱ፥ መሠረቱም እርሱ ነው እንጂ። ለመለኮት ከምድር ከውስጥም የሆነውን ያነሣ ዘንድ ማጐንበስ፥ ራስንም ዝቅ ማድረግ ያለበት አይደለም፤ በሚወሰንም ገንዘብ ደረትና ፊት በኋላም ጀርባ ያለው አይደለም፤ በነደ እሳት የተሸፈነ ነው እንጂ። ነደ እሳት ግን እርሱ ነው። መለኮትስ ንጹሕና ጽሩይ ብሩህም ነው» (ቅዳሴ ማርያም ቍ. 47–53)።

<u>ቅዱስ ጎርጎርዮስ፥ (የኑሲሱ)</u> :- «ሰማይን የፈጠረ ይህ ነው። ምድርንም የፈጠረ ይህ ነው። ለመለኮቱ ጥንት መሠረት የለውም፤ ላይ የለውም፤ ታችም የለውም፤ ርዝመት የለውም፤ ቁመት የለውም፤ ቀኝ የለውም፤ ግራም የለውም፤ መካከል የለውም፤ በዓለም ዳርቻ ሁሉ የመላ ነው እንጂ» (የጎርጎርዮስ ቅዳሴ ቍ.10)።

በዚህም በሠረት ሁለቱ ወገኖች በየበኩላቸው እያንዳንዳቸው የሌላው አስተሳሰብ ልክ አለመሆኑን በማመን እምነታቸውን ሲያብራሩ:- የመጀ



www.ethiopianorthodox.org

መሪያዎቹ ወገኖች ለእግዚአብሔር መልክና ቅርጽ እንደሌለው መናገር እግዚአብሔርን ዝርው ነው ብሎ ማመን ነው ሲሉ ሁለተኛዎቹ ወገኖች ደግሞ እኛ መርምረን ልንደርስበት የማንችለው ረቂቅ አካል ያለው ከመሆኑ በቀር ለእግዚአብሔር መልክና ቅርጽ ወስኖ መናገር እግዚአብሔርን ውሱን እንደሆነ ማመን ስለሆነ ትክክል አይደለም በማለት ሁለቱም ወገኖች የተለያዩ ማስረጃ ዎችን እያቀረቡ ይከራከራሉ። (ይህ ክፍል ከትምህርት መለኮት መጽሐፍ የተወሰደ ነው)።

9. <u>የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃ</u>:- እግዚአብሔር በፈጠረው ዓለም ውስጥ ያለ እርሱ ፈቃድ፥ ያለ እርሱ ጥበቃ፥ ወይም ያለ እርሱ ትእዛዝ ትልቅም ሆነ ትንሽ ድርጊት አይደረግም፤ አይደርስም፤ አይሆንም፤ አይፈ ጸምም። በሁሉም ነገር ውስጥ የእግዚአብሔር እጅ መኖሩ የግድ ነው። እግዚአብሔር ወደር በማይገኝለት ኀይሉና ጥበቡ በዓለም ላይ የሚፈጸሙ ሕይወት ባለውም ሆነ፥ ሕይወት በሌለው ፍጥረት ድርጊት ላይ በፍጹም ጥንቃቄ ለማድረግ ሥልጣን ያለው እርሱ ነው። የእርሱ ጥበቃ የማያስፈልገው የግል ጉዳይ ነው፤ ወይም የተናቀ ጉዳይ ነው የሚባል ነገር አይኖርም።

በእኛ አስተሳሰብ ምንም ጥበቃ የማያስፈልገን ለሚመስለን ጉዳይ ሁሉ እርሱ ጥበቃ ያደርጋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን አባባል ሲያረ ጋግጥልን «የእናንተስ የራስ ፀጕራችሁ ሁሉ እንኳ የተቈጠረ ነው» ብሏል (ማቴ:ም:10ቍ:30)።

የዓለም ነገሥታትና ልዑላን፥ አማኞችም ሆኑ የማያምኑ በእርሱ ሥልጣን ሥር ናቸው። ማንኛውንም ድርጊት ቢሆን ያለ እርሱ ፈቃድ ሊያደርጉ አይችሉም። የሚያደርጉአቸው መልካም ነገሮች ከሆኑ በእርሱ ትእዛዝ ክፉ ነገሮችም ከሆኑ በእርሱ ፈቃድ ያደርጉአቸዋል። ሰይጣን በኢዮብ ንብረትና ጤንነት ላይ እጁን ለመዘርጋት የቻለው እግዚአብሔር ከፈቀደለት በኋላ ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ዓላማ በሥራ ላይ ከዋለና እርሱ ሁሉንም ነገር ከመለ ሰለት በኋላ ግን ሰይጣን በኢዮብ ላይ ምንም ለማድረግ አልደፈረም። እግዚአብሔር ሌሎችንም ነገሮች የሚፈጽመው የማንንም እርዳታ ሳይፈልግና ማንንም መነሻ ሳያደርግ ነው። ሌላው የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ ግን ያለ እግዚአብሔር አንቀሳቃሽነት ምንም ማድረግ አይችልም። በዚህ ትምህርት ላይ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን እንደሚሉ እንመልከት:-

«በሰማይና በምድር፥ በጥልቅ ባሕሮችም እግዚአብሔር የወደደውን ሁሉ ያደርጋል» (መዝ:135 ቍ:6)።

«እኔ ጨለማንና ብርሃንን እፈጥራለሁ፤ በረከትንና ጥፋትን አመጣለሁ፤ እኔ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ አደርጋለሁ» (ኢሳ:ም:45ቍ:7)።

«በምድር ላይ የሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ በእርሱ ዘንድ ኢምንት ናቸው፤ በሰማይ መላእክትም ሆነ በምድር በሚኖሩ ሕዝቦች ላይ የፈቀደውን ያደ



ርጋል፤ ፈቃዱን መቃወም የሚችልና ይህን ለምን ታደርጋለህ? የሚለው ማንም የለም» (ዳን:ም:4ቍ:35)።

«ለጦርነት የሚያዘጋጅ መለከት በከተማ ውስጥ ሲነፋ በፍርሃት የማይን ቀጠቀጥ ሕዝብ ይኖራልን? እግዚአብሔር ካልፈቀደ በቀር በከተማ ላይ ክፉ ነገር ይመጣልን?» (አሞ:ም:3ቍ:6)።

«እርሱ የሰውን ዘር ሁሉ ከአንድ ሰው ፈጠረ፤ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩም አደረገ፤ የተወሰኑ ዘመኖችንና የሚኖሩባቸውንም ቦታዎች መደበ ላቸው» (የሐ:ሥ:ም:17 ቍ: 26)።

«ሁሉም ነገር የተገኘው ከእርሱ፥ በእርሱና ለእርሱ ነው» (ሮሜ: ም: 11ቍ:36)።

# <u>ምሥጢረ ተዋሕዶ</u>

## <u>(የተዋሕዶ ባሕርይ ምሥጢር)</u>

### ሀ. <u>መግቢያ</u>

ባሕርይ ማለት ምን ማለት ነው? ባሕርይ ማለት የአንድን ነገር ትክክለኛ ምንነት የሚገልጽ ቃል ነው።

ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍትን ማስረጃዎችና የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን አባቶችን ትምህርት መሠረት በማድረግ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መለኮትና ትስብእት አንድ አካልና አንድ ባሕርይ ለመሆን የተዋሐደው መለኮት ከሙሉ መለኮታዊ ባሕርዩና ጠባዩ ጋር ሲሆን፥ እንዲሁም ትስብእት ከኀጢአት በቀር ከሙሉ ሰብአዊ ባሕርዩና ጠባዩ ጋር እንዳለ ሆኖ ነው እንጂ በተዋሕዶው ምክንያት መቀላቀል፥ መጠፋፋት፥ መለያየትና መለዋወጥ እንዳለ የማታምን ከመሆንዋም በላይ መለኮት እና ትስብእት ተቀላቅለው ትስብእት በመለኮት ተውጦ ጠፍቷል የሚለው የአውጣኬ ክሕደት የተወገዘ መሆኑን ታረጋግጣለች።

ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሕዶ አንድ አካል፥ አንድ ባሕርይና አንድ ፈቃድ እንዲኖረው ያስፈለገው የሰውን ልጅ ለማዳን የግድ መለኮትና ትስብእት አብረው መሆን ስላለባቸው ነው። ትስብእት መኖር ያስፈለገው በሰው ልጅ ምትክ መሞት ስላለበት ነው። መለኮት መኖር ያስፈለገው ደግሞ ውክልና የማይገኝለት በመሆኑ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

## ለ. የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት

ቤተ ክርስቲያን የመለኮትንና የትስብእትን ተዋሕዶ ብታምንና ብታስተምርም የተዋሕዶው ሁናቴ እንደዚህ ነው ወይም በዚህ ዐይነት ነው ተብሎ ሊገለጽበት የሚቻል በሰው ልጅ ቋንቋ ውስጥ ቃላት የማይገኙለት ምሥጢር መሆኑንና ምሥጢርነቱም የሰው ልጅ አስተሳሰብ ሊረዳው ከሚችለው በላይ መሆኑን ታውቃለች። ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እግዚአብሔር በሥጋ የተገለጸበት የአምልኮ ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው» ሲል የምሥጢረ ተዋሕዶን ረቂቅነት አረጋግጦአል (1ኛ ጢሞ.ም. 3ቍ. 16)።

መለኮትና ትስብእትም ከተዋሐዱ በኋላ አንድ አካል፥ አንድ ባሕርይና አንድ ፈቃድ እንላለን እንጂ ወደ ኋላ ተመልሰን ሁለት አንልም። መለኮት የመለኮትን ትስብእት ደግሞ የትስብእትን ሥራ ብቻ ይሠራሉ ካልን የትስብእት አዳኝነት በቂ ሊሆን የማይችል ከመሆኑም በላይ በዚህ አባባላችን የእግዚአብሔርን ውለታ ዋጋ ማሳጣት ይሆንብናል። እንዲሁም ይህ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ካልታመነበት አምላክ ሰው መሆን ባላስፈለገውም ነበር፤ የአምላክ ሰው መሆን እምነታችንም ከንቱ መሆኑ ነው። መለኮትና ትስብእት በመሐዳቸው የትስብእት ባሕርይ ከውሕደት በፊት ያልነበረውን መለኮታዊ ባሕርይ በመገናዘብ ሥራውም የእግዚአብሔር ልጅ ሥራ ለመባል በቃ።

ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ባለመጠፋፋት በመሆኑ ወልድ በሥጋው ሞተ እንላለን። ይህንኑም በሚከተሉት ጥቅሶች እንመልከት።

«ልጁ በሥጋ በመሞቱ ምክንያት እግዚአብሔር ከራሱ ጋር አስታረቃችሁ» (ቆላ:ም:1ቍ:22)።

«ክርስቶስ ራሱ ወደ እግዚአብሔር ያቀርበን ዘንድ እርሱ ጻድቅ ሆኖ ሳለ ጽድቅ ለሌለን ለእኛ በኃጢአታችን ምክንያት በማያደርግም ሁኔታ አንድ ጊዜ መከራ በመቀበል ሞቶአል፤ እርሱ በሥጋ ሞተ፤ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» (1ኛ:ጴጥ:ም:3ቍ:18)።

«ክርስቶስ በሥጋው መከራን ተቀበለ» (1ኛ:ጴጥ:ም:4ቍ:1)።

በሰው ልጅ ላይ የሚነገር ሰብአዊ ስሜት ለምሳሌ እንደ መደሰት፥ ማዘን፥ መጥላት፥ መራብ፥ መጠማት፥ መታመምና እነዚህንም የመሳሰሉት ስሜቶች ሊደርሱ የሚችሉት የሰው ልጅ ሥጋውና ነፍሱ አብረው ባሉበት ጊዜ መሆኑ ግልጽ ነው። ሥጋውና ነፍሱ ከተለያዩ በኋላ ማለት ከሞቱ በኋላ እነዚህ ስሜቶች አይኖሩም። ሰው ሲሞት ደግሞ ሥጋው እንጂ ነፍሱ አትሞትም። የሰውነታችን እንቅስቃሴ፥ እስትንፋሳችንና በአጠቃላይም ሕይወታችን ነፍሳችን እንደ መሆኑ ነፍሳችን ከሥጋችን በሚለይበት ጊዜ ሥጋችን በድን ይሆናል። ነፍሱ



ከሥጋው የተለየ ሰው ደግሞ ሰው መባሉ ቀርቶ ሬሳ የሚባል ስም ይሰጠዋል። ሆኖም አንድ ሰው ሲሞት በሥጋው ሞተ አይባልም፤ ምክንያቱም ሰው ሊባል የሚችለው ነፍስ ሲኖረው ብቻ ነውና። እንግዲህ የሰው ነፍስ ሞት የማይደርስበት ከሆነ ነፍስን ለሰው ልጅ የሰጠው መለኮትማ ሕማምና ሞት የማይደርስበት መሆኑ ግልጽ ነው።

የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ያለ መቀላቀልና ያለ መጠፋፋት መሆኑ ቢታመንበትም እንኳ አምላክ በትስብእቱ ሕማምን ተቀብሎ ሞተ እንላለን። ይህም ማለት ለቅጽበተ ዐይን ያኽል ጊዜ እንኳ መለኮት ከትስብእት ያልተለየ መሆኑን ለማመልከት ነው። ለዚህም የሚቀጥሉትን የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች እንመልከት።

«እነሆ ሕፃን ተወልዶልናል፤ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል፤ እርሱ መሪ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ፥ መካር፥ ኀያል አምላክ፤ የዘለዓለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል› (ኢሳ.ም.9ቍ.6)።

ሕፃን ሆኖ መወለድ የትስብእት ባሕርይ መሆኑ ቢታወቅም በመለኮትና በትስብእት ተዋሕዶ ምክንያት ያ የተወለደው ሕፃን ኀያል አምላክና የዘለዓለም አባት መባሉን እናስተውል።

«እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙም ዐማኑኤል ተብሎ ይጠራል። ዐማኑኤል ማለትም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለት ነው» (ማቴ.ም.1ቍ.23)።

እዚህም እንደ ፊተኛው ጥቅስ ተፀንሶ መወለድ የትስብእት ባሕርይ መሆኑ ባይካድም ዐማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው የተባለው የመለኮትንና የትስብእትን ተዋሕዶ ሲያመለክተን ነው።

«እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለሙን እንዲህ አድርጎ ወድዶታል (ዮሐ:ም:3ቍ16)።

የእግዚአብሔር አንድያ ልጅነት በመለኮቱ ቢሆንም ዓለምን ለማዳን ለሕማምና ለሞት ታልፎ ተሰጠ የተባለው መለኮቱ መቼም ቢሆን ከትስብእቱ ያልተለየ በመሆኑ ነው።

«በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ» (የሐ.ሥ.ም.20ቍ.28)።

ቤተ ክርስቲያንን ለመዋጀት ደሙን ያፈሰሰው እግዚአብሔር መባሉን እናስተውል።

«ዐውቀውትስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር» (1ኛ ቆሮ.ም.2 ቍ.8)።

የክብር ጌታ የተባለው ፈጣሪ አምላካችን ሲሆን ተሰቀለ መባሉም መለኮትና ተስብእት መቼም ቢሆን ያልተለያዩ መሆናቸውን ሲያመለክተን ነው።



www.ethiopianorthodox.org

«የመጀመሪያውና የመጨረሻው እኔ ነኝ፤ ሞቼ ነበር፤ ነገር ግን ለዘለዓለም ሕያው ነኝ» (ራ.ዮሐ.ም1ቍ:17–18)።

የመጀመሪያውና የመጨረሻው የሚለው የአምላክ ብቻ መጠሪያ ሲሆን ሞቼ ነበር ያለውም በትስብእቱ ሲሞት መለኮት ያልተለየው መሆኑን ያመለክተናል።

## ሐ. የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት

ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ:- «ለመወለዱ ጥንት በሌለው አስቀድሞ ዓለም ሳይፈጠር በመለኮቱ ከአብ በተወለደ፥ ዳግመኛም እኛን ለማዳን በኋላ ዘመን ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደ በእግዚአብሔር ልጅ እናምናለን፤ የቀኑ ቀጠሮ ሲደርስ እግዚአብሔር ልጁን ላከ፤ ከድንግል ተወለደ ያለው ብፁዕ ሐዋርያ እንዳስተማረን ይህ አንዱ አምላክ ነው፤ በመለኮት የእግዚአብሔር ልጅ በሥጋ የአዳም ነው፤ የእግዚአብሔር፥ የአዳም ልጅ ስለሆነም፥ ለወልድ ዋሕድ ለአንዱ የምንሰግድለት፥ ለአንዱ የማንሰግድለት ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ አለው የምንል አይደለም። ሰው የሆነ የእግዚአብሔር አካሉ ባሕርዩ አንድ ነው እንጂ፤ ከሥጋው ሳንለይ አንድ አድርገን አንዲት ስግደትን እንሰግድለታለን እንጂ» (ሃይ. አበ፥ ገጽ 68)።

ቅዱስ አቡሊዲስ፥ የሮም ሊቀ ጳጳሳት:- «ሁለት አካል፥ ሁለት ባሕርይ ብለው የሚያምኑ ለአንዱ እንዲሰግዱ ለአንዱ እንዳይሰግዱ፥ በመለኮት ባሕርይ እንዲጠመቁ በሥጋ ባሕርይም እንዳይጠመቁ ግድ ይሆንባቸዋል። ... እኛ ግን ስለ መለኮት ስንናገር ወልድ ከሰማይ እንደወረደ እንናገራለን፤ አንዱ አካል ሁለት መሆኑን አናውቅም። ሰማያዊ መለኮትን ከምድራዊ ሥጋ፥ ምድራዊ ሥጋንም ከሰማያዊ መለኮት አንለየውም፤ መክፈል ክሕደት ነውና፤ ሁለት አካል፥ ሁለት ባሕርይ ለሚሉ ሰዎች ምክንያት አንሰጣቸው። ሥጋም ሥጋ ነው፤ በገንዘቡ ብቻ ነዋሪ አይደለም፤ በገንዘቡ ባሕርይ ብቻ የዳነ አይደለም፤ ከሚያድን ከቃልም ተለይቶ በገንዘቡ ብቻ ሊኖር አይችልም። ቃልም ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ እንደነበረ ሁሉ በመለኮታዊ ባሕርዩ ከሥጋ አይለይም። ለብቻውም አንድ ወገን ሆኖ አይኖርም። ... ያልተፈጠረ ቃል ያለ ሥጋ ሰው ሆኖ አልታየምና ማንም ማን ያልተፈጠረ መለኮትን ከሥጋ ልዩ ነው እንዳይል እርስ በርሳቸው አንድ ስለሆኑበት አንድነት በነፍስ በሥጋ አምሳል ስለተዋሐዱበት ተዋሕዶ ሁለቱ በተዋሕዶ አንድ ሆነዋልና አሁንም በተዋሕዶ አንድ ለሆኑ ለሁለቱ አንድ ስም ይገባል» (ሃይ. አበ፥ ገጽ 134)።

«የእግዚአብሔር ልጅ ወልድ ዋሕድ ነፍስን ሥጋን ነሥቶ ሰው ሆነ ባልን ጊዜም ስለዚህም ነገር ቢሆን እነዚያ እንደሚያምኑ መቀላቀል የለበትም፤ የቃል ባሕርይ የሥጋን ባሕርይ ወደመሆን፥ የሥጋ ባሕርይም የቃል ባሕርይን ወደ መሆን አልተለወጠም፤ ሁለቱ ባሕርያት ባለመለዋወጥ፥ ባለመቀላቀል ጸንተው ይኖራሉ እንጂ» (ሃይ. አበ. ገጽ 147)።

ቅዱስ ቄርሎስ፥ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት:- «በእግዚአብሔር ቃል በረቂቅ ባሕርይ የሆነውን ተዋሕዶ አንካድ፤ ብረት ከእሳት በተዋሐደ ጊዜ፥ ከእሳትም በመዋሐዱ የእሳት ባሕርይ ገንዘብ እንዲያደርግ፥ ብረት በመዶሻ በተመታ ጊዜ ከእሳት ጋር በአንድነት እንደሚመታ፥ ግን ከመዶሻው የተነሣ የእሳት ባሕርይ በምንም በምን እንዳይጐዳ፥ ሰው የሆነ አምላክ ቃል በመለኮቱ ሕማም ሳይኖርበት በሥጋ እንደታመመ እንዲህ እናስተውል።

ፈቃድ ሥጋን እንድዋሐድ አደረገኝ፤ የኀጢአትን ፍዳ አጠፋ ዘንድ መከራም በሥጋዩ ተቀከበልኩ፤ የሁሉን ኀጢአት አጠፋ ዘንድ ስለ እነርሱ ሰው ሆኛለሁና ሁለተኛ አዳም ሆኜ ሞትኩ። መለኮቴ አልሞተም፤ ሲኦልን በዘበዝኩ እንጂ፤ በገዛ ሥልጣኔም ተነሣሁ እንጂ በገነት በነበረ ሰው በአዳም በንፍሐት መንፈስ ቅዱስን ያሳደርኩ ፈጣሪ እኔ መሆኔን አስረዳ ዘንድ በደቀ መዛሙርቴ ፊት እፍ ብዬ መንፈስ ቅዱስን አሳደርኩ አለ» (ሃይ. አበ. ገጽ 272)።

ቅዱስ ሳዊሮስ፥ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት:- «ከሓዲያን መናፍቃን እንደሚሉት ከሆነ ቤዛችን ሆኖ ክርስቶስ የሞተው ሞት የመለኮት ከሥጋ መለየት ነው እንጂ የነፍስ ከሥጋ መለየት አይደለም፤ እንደነሱ አነጋገር የእኛን ሞት ካልሞተማ ቤዛችን በሆነ በመድኀኒታችን ሞት እንደምን እንመካለን? የእኛ ባይደለ በሌላ ሞት ዲያብሎስ ድል ከተነሣ ቃል ከእኛ ባሕርይ ጋር አንድ አልሆነማ። ነገር ግን እርሱ ቤዛችን ሆኖ እንደ እኛ ሞት ያለ ሞትን እንደሞተ ነገሩ የታወቀ ነው፤ ይኸውም የነፍስ ከሥጋ መለየት ነው፤ ነፍሱን በሲኦል አልተወም፤ ሥጋውም እንዲፈርስ እንዲበሰብስ አላደረገም፤ ነቢይ እንደተናገረ፤ ነገር ግን ነፍሱ ከሥጋው በተለየች ጊዜ እግዚአብሔር ቃል በፈቃዱ ይህን ሠራ፤ ከተለያዩ ከሁለቱ ከነፍስና ከሥጋ አልተለየም፤ አንድ አካል በመሆን ከነፍስ ከሥጋ ጋር ተዋሕዶ ይኖራል እንጂ» (ሃይ. አበ. ገጽ 368)።

«አሁንም አንዱ የእግዚአብሔር ቃል ባሕርይ ሳይለወጥ ሳይናወጥ ሰው እንደሆነ ነገሩ የታወቀ የተረዳ ነው፤ እርሱ አንድ ባሕርይ፥ አንድ አካል እንደሆነ እናውቃለን፤ ይህ አንዱ እርሱ የአምላክነትን ሥራ ይሠራል፤ ወዲህም እርሱ መለወጥ የሌለበት ሰው ነው፤ እርሱ ወልድ ነው፤ እርሱ እግዚአብሔር ነውና በቅድምና የነበረ የእግዚአብሔር አብ ልጅ ነውና በፍጹም ቸርነቱ ከዳዊት፥ ከአብርሃም ወገን ተወልዶ የሰው ልጅ ሊሆን ወደደ። እንደ አይሁድ ሁለቱን ባሕርያት እርስ በርሳቸው ለያይቶ ተአምራትን ያደረገ የመለኮት ባሕር ነው፤ መከራን የተቀበለ የሥጋ ባሕርይ ነው እንደሚል እንደ ከሐዲው ንስጥሮስ አነጋገር ከተዋሕዶ በኋላ አንድ ወደ ሁለትነት ሊከፈል አይቻልም» (ሃይ. አበ፥ ገጽ 379)።

ቅዱስ ባስልዮስ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት:- ዐማኑኤል ተባለ፤ ትርጓሜውም እግዚአብሔር አምላካችን ከእኛ ባሕርይ ጋር አንድ ሆነ ማለት ነው፤ ያለመቀላቀል ያለ መለወጥ ሰው የሆነው አንድ ገጽ፥ አንድ አካል፥ አንድ ባሕርይ ነው፤ ከመለኮትና ከተብስእት የሆነ ተዋሕዶ የማይነገር የማይመረመር ነው፤ በውነት መቀላቀል የሚገባቸውስ ርጥበት ያላቸው ሥጋት ናቸው፤


www.ethiopianorthodox.org

እነዚህም ግዘፍ ከሌለው ባሕርይ የተለዩ ናቸው። ከተዋሕዶ በኋላ ወደ ሁለት ባሕር አይከፈልም፤ ተዋሕዶ መንታነትን አጥፍቷልና፤ ተዋሕዶም ከሁለት የተገኘ ሁለት መባል አለበት የሚለውን ፍርድ ይለውጣል፤ ይህ ተዋሕዶ የማይከፈል አካላዊ ነውና ፍጡር ያይደለ እግዚአብሔር ቃል ሥጋ ወደ መሆን ይለወጣል፤ በባሕርይ የሚመስገን፥ ከንጽሕት ድንግል የተገኘ ሥጋም ከባሕርዩ የመለኮት ባሕርይ ወደ መሆን ተለወጠ ብሎ መናገር እውነተኛ ነገር እንደሆነ የሚያስብ ማነው? የሙሴ በትር ተለውጣ የምድር እባብ እንደሆነች፤ የፈሳሽ ውሃም ተለውጦ ደም እንደሆነ፥ የግብጽ ብርሃንም ተለውጦ ጨለማ እንደሆነ፥ እንዲሁ የእግዚአብሔር ቃልም የሰው ባሕርይን ወደ መሆን የተለወጠ አይደለም፤ እነርሱ የተፈጠሩ ናቸውና፥ ስለዚህም መለወጥ አገኛቸው፤ የመለኮት ባሕርይ ግን መለወጥ የለበትም ፍጻሜ ሳይኖረውም ሁል ጊዜ ይኖራል፤ አይወሰንም፤ መለወጥ መናወጥ የለበትም» (ሃይ. አበ.፥ ገጽ 422)።

## የቤተ ክርስቲያን መከፋፈል

የአውጣኪን ክሕደት ለማረም ወይም ከሐዲውን ለማውገዝ በ449 ዓ.ም. በኤፌሶን የተሰበሰበው ጉባኤ ሰብሳቢ የእስክንድርያው ቤተ ክርስቲያን መሪ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ነበር። ስብሰባውን በሊቀ መንበርነት እንዲመራ ለቅዱስ ዲዮስቆሮስ ጥሪ የላከለት ትንሹ ቴዎዶስዮስ ነው። በዚህም መሠረት ጉባኤው ተካሄዶ አውጣኪ እምነቱን እንዲያብራራ በተጠየቀ ጊዜ የእርሱ እምነት ከኒቅያ ጉባኤ አባቶችና ከቅዱስ ቄርሎስ ትምህርት የተለየ አለመሆኑን ስለገለጸ ከውግዘቱ ተፈትቶ ወደ ሥራው እንዲመለስ ጉባኤው ወሰነለት። በዚሁ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ ፍላፕያኖስና ሌሎችም በንስጥሮሳዊ እምነታቸው ተወግዘዋል። በዚህ ጊዜ እነፍላፕያኖስና ሌሎችም ንስጥሮሳውያን ከሮማው ቤተ ክርስቲያን መሪ ከልዮን ጋር ግንባር በመፍጠር በዲዮስቆሮስ ላይ የበቀል እርምጃ የሚወስዱበትን ዘዴ ይፈልጉ ጀመሩ። ይህን ዕቅዳቸውን ለማመቻቸት ከረዱአቸው ሁናቴዎች አንዱ የአውጣኪ ወደ ቀድሞ የክሕደት ትምህርቱ ተመልሶ መገኘቱ ነው። ሆኖም በዲዮስቆሮስ ሰብሳቢነት የተካሄደውን ጉባኤ ትክክለኛነት የሚመለከት ሌላ ጉባኤ እንዲሰበሰብ በማለት ደጋግመው የጠየቁትን ጥያቄ ውሳኔው ትክክል ስለሆነ ሌላ ጉባኤ መሰብሰብ አስፈላጊ አይደለም በማለት ንጉሥ ቴዎዶስዮስ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ጥያቄአቸውን ውድቅ ሲያደርግባቸው ኖሮአል። በ450 ዓ.ም. ንጉሡ ቴዎዶስዮስ ያለ ልጅ ወራሽ ከዚህ ዓለም በሞት በተለየ ጊዜ እኅቱ ብርክልያ ከጦር መሪዎች አንዱ የነበረውን መርቅያኖስን አግብታ ዙፋኑን ወረሱ። ባልና ሚስትም ንስጥሮሳውያን ስለነበሩ የዲዮስቆሮስ ተቃዋሚዎች አመቺ ጊዜ አገኙ። በዚህም መሠረት በ451 ዓ.ም. በኬልቄዶን በተሰበሰበው አብዛኛዎቹ አባላት ንስጥሮሳውያን በነበሩበት ጉባኤ ፊት ዲዮስቆሮስ የአውጣኪ ክሕደት ተከታይ ነው የሚል ክስ ተመሥርቶበት ታላቅ ክርክር ተነሣ። ይህ ክስ እንደ ዋነኛው ክስ ተደርጎ ከመገመቱ በቀር ሌሎችም



www.ethiopianorthodox.org

ልዩ ልዩ ክሶች ቀርበውበት ነበር። ከመጀመሪያውም ቢሆን የስብሰባው ዋና ዓላማ በዲዮስቆሮስ ላይ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ስለነበረ ከሃይማኖት ሰዎች በማይጠበቅ ተንኰል በአንድ በኩል ከቤቱ እንዳይወጣ በዘበኛ አስጠብቀው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ብንጠራው ሳይመጣ ቀረ ለማለት ጥሪ አስተላልፈውለት ዲዮስቆሮስ በሌለበት እና ከዳኞችም ተደብቀው የፈለጉትን ውሳኔ በዲዮስቆሮስ ላይ አሳለፉ። ውሳኔአቸውን ከአመቻቹ በኋላ ዲዮስቆሮስ በስብሰባው እንዲገኝ ፈልገው ነበር። እርሱ ግን ተመልካች ዳኞች በሌሉበት በስብሰባው ለመገኘት ፈቃደኛ አልሆነም። ከዚያም ንጉሡን በውሳኔአቸው አሳምነው ዲዮስቆሮስን ጋግራ ወደ ተባለች ደሴት እንዲጋዝ አስደርገዋል። እስከ ዕለተሞቱም ድረስ ቀሪ የሕይወት ዘመኑን ያሳለፈው በዚያው በጋግራ ደሴት ግዞት ነው። የኬልቄዶኑን ጉባኤ ሕገ ወጥ ውሳኔ ካልተቀበሉት መካከል የግብጽ፥ የኢየሩሳሌም፥ የሶርያና የአርመን አብያተ ክርስቲያን ይገኙባቸዋል። በዚህም የምሥራቅና የምዕራብ አብያተ ክርስቲያን ወገናዊነትን በተከተለ ስያሜ ዓለም ዓቀፋዊነትዋ ቀርቶ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ተከፈለች።

የምዕራቦቹ ወገኖች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ባሕርይና አንድ ፈቃድ ብቻ አለው ብሎ ማመን የአውጣኪን ክሕደት መከተል ነው በሚል ምክንያት በሁለት ባሕርይና በሁለት ፈቃድ እምነት ላይ ሲጸኑ፥ የምሥራቆቹ ወገኖች ደግሞ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርይና ሁለት ፈቃድ አለው ብሎ ማመን የንስጥሮስን ክሕደት መቀበል ነው በማለት በአንድ ባሕርይ፥ በአንድ ፈቃድና በአንድ አካል እምነት ላይ ጸንተዋል።

ሁለቱም ወገኖች እምነታቸውን ለማብራራት ብለው በየበኩላቸው የሚያቀርቡአቸው የመከራከሪያ ሐሳቦች የሚከተሉት ናቸው።

የምዕራቦቹ ወገኖች ሁለት ባሕርይና ሁለት ፈቃድ የሚሉበትን ምክንያት ሲያብራሩም እንኳ መለኮትና ትስብእት የተዋሐዱ መሆናቸው ቢታመን ንበት ይህ ተዋሕዶ ግን ያለ መቀላቀልና ያለ መጠፋፋት እስከሆነ ድረስ ሁለት ባሕርይና ሁለት ፈቃድ እንላለን እንጂ አንድ ባሕርይ ብቻ ልንል አይገባንም፥ አለበለዚያማ አውጣኪ ለምን ተወገዘ ብለው ይጠይቃሉ።

የምሥራቆቹ ወገኖች ደግሞ አውጣኪ የተወገዘው አንድ ባሕርይ፥ አንድ ፈቃድና አንድ አካል በሚለው እምነት ላይ በመጽናቱ ሳይሆን ትስብእት በመቀላቀልና በመዋጥ ጠፍቶ የመለኮት ባሕርይ ብቻ ቀርቶአል በማለቱ ነው ሲሉ ማብራሪያቸውን ይቀጥሉና መለኮትና ትስብእት ተዋሕደዋል ከተባለ ከተዋሕዶ በኋላ አንድ ባሕርይና አንድ ፈቃድ እንጂ ሁለት ማለት አግባብ አይደለም። አለበለዚያማ ንስጥሮስ ለምን ተወገዘ ብለው ይጠይቃሉ።

የምዕራቦቹ ወገኖች የእኛ ሃይማኖት ዓለም ዐቀፋዊ ነው ለማለት ካቶሊክ፥ የምሥራቆቹ ወገኖች ደግሞ ትክክለኛው የእኛ ሃይማኖት ነው ለማለት ኦርቶዶክስ የሚባሉትን ስያሜዎች መርጠው ለመጨረሻ ጊዜ ሁለቱ ወገኖች ሲለያዩ የኦርቶዶክስ ቤት ክርስቲያን የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን ንስጥሮሳዊ ብላ አውግዛለች፤ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የኦርቶዶክስን ቤተ ክርስቲያን የአውጣኪ እምነት ተከታይ ብላ አውግዛለች። እነዚህም አባባሎች እንደ እውነት ተቈጥረውና ታምኖባቸው በሁለቱም አብያተ ክርስቲያን የኖሩ ታሪኮች ናቸው።

የኬልቄዶኑ ጉባኤ ቅንነትና መንፈሳዊነት የጐደለው ከመሆኑ የተነሣ ከዚያ በኋላ አንዳንድ ቅን አስተሳሰብ የነበራቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለችግሩ በውይይትና በመግባባት መፍትሔ ተፈልጎለት የቀድሞው የቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዲመለስ ሙከራ ቢያደርጉም ሐሳባቸውን የሚደግፍ ሰው ሳይገኝ ቀርቶ ጥላቻ እና በቀል፥ መናናቅና መነቃቀፍ መቀጠሉ የክርስትናን መሠረታዊ ዐላማ የሚቃረን ድርጊት ነው። ጌታችን በዚህ ዓለም እንደ ሰው ኖሮ፥ እንደ ሰው ጸሎት በጸለየ ጊዜ ስለ ምእመናን ማለት ስለቤተ ክርስቲያን አንድነት መጸለዩን በዮሐንስ ወንጌል ም. 17 ቍ. 20–23 መመልከት እንችላለን። ታዲያ፥ ያነጋገር ወይም ያቀራረብ ልዩነት ካልሆነ በቀር ከአንድነ ማንቲም ሁለት ገጽታ ያነሰ ልዩነት ባላቻው ሁለት ወገኖች መካከል አንድነት የሚመለስበትን ሁናቴ ከማመቻቸት ይልቅ ብዛትና ኀይል የነበራቸው የክርስቲያን ወገኖች እንደ እነርሱ የሕዝብ ብዛት ባልነበራቸው የክርስቲያን ወገኖች ላይ ባደረጉት ማሳደድ ምክንያት እነዚያ የተሳሰዱት ወገኖች ሕይወታቸውን ለማዳን ሲሉ ክርስትና ሃይማኖታቸው ያልሆነ ወገኖችን እስከ መጋበዝና አገራቸውን ክርስቲያን ያልሆነ መንግሥት እንዲገዛት እስከ ማድረግ ተገድደዋል። ይህም ሁናቴ በክርስቲያን ሃይማኖት ላይ አንድ የማይረሳ ጥቁር ነጥብ እንደሆነ ይኖራል።

እንደ እውነቱ ከሆነ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የአውጣኪን እምነት ተከታይ አይደለችም፤ የካቶሊክም ቤተ ክርስቲያን የንስጥሮስን እምነት ተከታይ አይደለችም። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የንስጥሮስን ክሕደት እንደምታወግዝ የአውጣኪንም ክሕደት ታወግዛለች። የካቶሊክም ቤተ ክርስቲያን የአውጣኪን ክሕደት እንደምታወግዝ የንስጥሮስንም ክሕደት ታወግዛለች። ስለዚህ ሁሉም በቅን አስተሳሰብ ተነሥቶ ሙከራ ቢያደርግ ኖሮ ጥንታዊው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አንድነት በተመለሰ ነበር።.

ይህ የምሥጢረ ተዋሕዶ ጽሑፍ ጠቅላላውን የተወሰደው ከትምህርተ መለኮት መጽሐፍ ነው።

## ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ጠባዮች ስንል ምን ማለታችን ነው?



www.ethiopianorthodox.org

2. የእግዚአብሔርን ጠባይ በሰብአዊ ቋንቋ ለመግለጥ የተፈለገው ለምንድነው?

3. የእግዚአብሔርን ጠባዮች ለመግለጥ የቀረቡት ሁለት አጠቃላይ ርእሶች ምንና ምን ናቸው?

4. በመጀመሪያ አጠቃላይ ርእስ ሥር ያሉት ንዑሳን ርእሶች ስንት ናቸው? እነርሱስ ምን፥ ምን ናቸው?

5. በሁለተኛው አጠቃላይ ርእስ ሥር ያሉት ንዑሳን አርእስት ስንት ናቸው? እነርሱስ ምን፥ ምን ናቸው?

7. የእግዚአብሔርን ጠባይና ባሕርይ የምናውቀው ምን ያኽል ነው?

8. በራሳቸው ሊገኙ የሚችሉ ፍጥረቶች አሉን?

9. የእኛ አምልኮ ለእግዚአብሔር የሚጠቅመው ምንድነው?

10. ዘለዓለማዊነቱን በተመለከተ እግዚአብሔር ከሰብአዊ ፍጡር የሚለየው በምንድነው?

11. የእግዚአብሔርና የዘመን ግንኙነት እንዴት ነው?

12. የእግዚአብሔር አለመለወጥና፥ ተጸጸተ የሚሉት አባባሎች በምን ይታረቃሉ?

13. ጭማሪን ወይም ቅነሳን የማይቀበለው ምንድነው?

14. በሁለንተናው በሁሉም ቦታ የሚለውን የሚያስከትለው ምንድነው?

15. የእግዚአብሔር ውሱን ያለመሆን ምልክት የቱ ነው?

16. ሰብአዊ ፍጡር እግዚአብሔርን ለማየት የማይችለው በምን ምክንያት ነው?

17. መላእክትም የእግዚአብሔርን ፊት ለማየት አለመቻላቸው ማስረጃ ምንድነው?

18. የሰው ነጻ ፈቃድና የእግዚአብሔር ሁሉን ነገር ዐዋቂነት እንዴት ይታረቃሉ?

19. የእግዚአብሔር ጥበበኛነት ምንን ያመቻቻል?

20. የእግዚአብሔር ዕውቀት ተግባራዊ ጐን ለመባል የሚችለው የትኛው የእግዚአብሔር ጠባይ ነው?

21. እንደ እግዚአብሔር ዕውቀት ሊታይ የሚችለው የትኛው የእግዚአብሔር ጠባይ ነው?

22. የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት በምን ላይ ነው?

23. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ሆኖ የማያደርገው ድርጊት የቱን ነው?

24. እግዚአብሔር ማድረግ የሚችለውን ነገር ሁሉ ይፈልገዋልን?

25. እግዚአብሔር ከርኵሰትና ከሕጸጽ (ጐድለት) ነጻ መሆኑን የሚያመለክተው ቃል ምን ይባላል?

26. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለራሱ የተለዩ ስላደረጋቸው ምን ብሎ አዘዛቸው?

27. ለእግዚአብሔር የተለዩ ነገሮች ሁሉ ምን ይባላሉ?

28. ፍትሕ ማለት ምን ማለት ነው?

29. ጽድቅ ማለትስ ምን ማለት ነው?

30. ፍትሕና ጽድቅ የሚሉት ቃላት ተወራራሽ የሚሆኑት እንዴት ነው?

31. ቊጣና ተግሣፅን የመሳሰሉ ሰብአዊ ስሜቶች ለእግዚአብሔር በሚነገሩበት ጊዜ ምን ለማለት ታስቦ ነው?

32. እግዚአብሔር በምድር ላይ ሰውን በመፍጠሩ ተጸጸተ በሚለውና እግዚአብሔር በነነዌ ሰዎች ላይ ሊያመጣባቸው በነበረው ጥፋት ተጸጸተ በሚሉት ጸጸቶች መካከል ምን ልዩነት አለ?

33. እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው ምን አነሣሥቶት ወይም ከምን ተነሥቶ ነው?

34. እግዚአብሔር ታማኝና እውነተኛ ሲሆን መታለልንና መሳሳትን ለምን ይፈቅዳል?

35. የእግዚአብሔር እጆች ሲባል ምን ማለት ነው?

36. የእግዚአብሔርን ፈቃድ በኢዮብ ታሪክ ውስጥ እንዴት ልንረዳ እንችላለን?

37. ባሕርይ ማለት ምን ማለት ነው?

38. መለኮትና ትስብእት ለምን ተዋሐዱ?

39. አምላክ በትስብእቱ ሞተ ማለት ምን ለማለት ነው?

40. ለቤተ ክርስቲያን መከፋፈል ምክንያት የሆነው ማነው?

41. በ449 ዓ.ም. በኤፌሶን የተሰበሰበው ጉባኤ ውሳኔ ምን ነበር?

42. በመጨረሻ ቤተ ክርስቲያን የተለያየችበት ጉባኤ ማን ይባላል? ዘመኑስ መቼ ነበር?

43. ሁለቱ ወገኖች በምን ተለያዩ?

44. የልዩነቱ ምክንያቶች የሚያለያዩ አልነበሩም የተባለው እንዴት ነው?



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ 2

## መጽሐፍ ቅዱስ

### ብሉይ ኪዳን

__የእስራኤል ዐመፀኛነት__:- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ነጻ ለማውጣት ብዙ ድንቅ ነገሮችን እነርሱ እያዩ ቢያደርግና ከዚያም ቀይ ባሕርን ለሁለት ከፍሎ ካሻገራቸው በኋላ እነርሱ እያዩ ግብጾችን ቢያሰጥምም፥ ሕዝቡ ምስጋና ቢስና አንገተ ደንዳና ስለነበረ በሙሴና በአሮን ላይ ማጉረምረም ጀመረ።

በበረሓው ጉዞአቸው ማራ ወደተባለ ስፍራ በደረሱ ጊዜ በዚያ የነበረው ውሃ መራራ በመሆኑ ሊጠጡት ስላልቻሉ በሙሴ ፊት ተሰብስበው አጉረመረሙ። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ባመለከተው መሠረት ሙሴ አንድ እንጨት ወስዶ በውሃው ላይ ስለጣለው ውሃው ወደጣፋጭነት ተለውጦ ሊጠጡት ችለዋል።

እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡ በሁለት ወር ተኩል በሲና በረሓ በነበሩ ጊዜ በእግዚአብሔር፥ በሙሴና በአሮን ላይ እንዲህ ብለው ማጉረምረም ጀመሩ:- ምነው በግብጽ እያለን እግዚአብሔር በገደለን ኖሮ፤ እዚያ በነበርን ጊዜ የፈለግነውን እናገኝ ነበር፤ እናንተ ግን ሁላችንም እንድናልቅ ወደዚህ በረሓ አመጣችሁን። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ድርጭትና መና ሰጣቸው።

እስራኤላውያን በሲና ምድረ በዳ እየተጓዙ ሳለ ረፊዲም ወይም ቃዴስ ወደሚባል ስፍራ ደርሰው ሰፈሩ። እዚያም የሚጠጣ ውሃ ስላልነበረ በሙሴ ላይ አጉረመረሙ። ሙሴም እግዚአብሔርን እንዳይፈታተኑት ቢመክራቸው እንዲያውም አንተ ከግብጽ ያስወጣኸን እኛን፥ ልጆቻችንንና እንስሶቻችን በውሃ ጥም ለመፍጀት ነው በማለት ሙሴን በድንጋይ ሊወግሩት ቃጣቸው። ሙሴም በእግዚአብሔር ትእዛዝ አለቱን በበትሩ በመታው ጊዜ ውሃ አፈለቀ። እስራኤላውያን እግዚአብሔርን በመፈታተናቸው ያ ቦታ ማሳህና መሪባ ተባለ። ማሳህ ማለት መፈታተን፥ መሪባ ደግሞ ማጉረምረም ማለት ነው (ዘጸ:ም: 15ቊ: 22–25፥ ም:17ቊ:7)።



የመሪባ ውሃ (ዘጸ. ም : 17 ቍ : 7)

የዚህ ቦታ ተአምር ግን በሙሴና በአሮን ላይ ሌላ ችግርን አመጣ እንጂ በዚሁ ያለቀ አልነበረም። ስለዚህ ጉዳይ በኦሪት ዘኁልቍ የተነገረውን አባባል እንመልከት:-

«እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት ለፊት ያለውን በትር ወስደህ አንተና አሮን ሆናችሁ መላውን ማኅበር በአንድነት ሰብስቡ፤ እዚያም በእነርሱ ሁሉ ፊት ሆነህ ያን አለት ውሃውን እንዲያወጣ እዘዘው፤ በዚህ ዐይነት ከአለቱ ውስጥ ውሃ ታወጣላቸዋለህ፤ እንዲሁም ለእነ ርሱና ለእንስሶቻቸው የሚጠጣ ውሃ ትሰጣቸዋለህ። ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ከእግዚአብሔር ፊት በትሩን አመጣ። እርሱና አሮን መላውን ማኅበር በአለቱ ፊት ለፊት እንዲሰበሰቡ ካደረጉ በኋላ ሙሴ ሰዎቹን እናንተ ዐመፀኞች፥ ከዚህ አለት ለእናንተ ውሃ እናውጣላችሁን? አላቸው። ከዚህ በኋላ ሙሴ በትሩን አንሥቶ አለቱን ሁለት ጊዜ መታው፤ ታላቅ የውሃ ምንጭም ከውስጡ ፈሰሰ፤ ሕዝቡና እንስሳቱም ሁሉ ጠጡ።

ነገር ግን እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዲህ ሲል ገሠጻቸው፤ በእስራኤ ላውያን ፊት ቅድስናዬን ትገልጡ ዘንድ ስላላመናችሁብኝ፥ ልሰጣቸው ቃል ወደ ገባሁላቸው ምድር የዚህ ሕዝብ መሪዎች ሆናችሁ አትገቡም» (ዘኁ: ም:20፥7–12)።

በዚህም በእግዚአብሔር ውሳኔ መሠረት አሮን በሖር ተራራ ላይ ሞቶ ከመቀበሩና ሙሴም በፒስጋ ተራራ ላይ ከመሞቱ በቀር የእስራኤልን ሕዝብ እየመሩ ዮርዳኖስን እንዲሻገሩ አልተፈቀደላቸውም። በእርግጥ ሙሴ የተቀበረበትን ትክክለኛ ቦታ ያወቀ ሰው አልተገኘም (ዘኁ:ም: 20ቍ: 22–29፥ ዘዳ:ም: 34ቍ: 1–8)።

እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ሃይማኖታዊ መተዳደሪያ ደንብ ይሰጥ ዘንድ ሙሴን ወደ ሲና ተራራ ጠርቶት አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በመዘግየቱ ምክንያት እስራኤላውያን አሮንን አስገድደው የወርቅ ጥጃ ጣዖት እንዲሠ



www.ethiopianorthodox.org

ራላቸው አደረጉት። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች ሁሉ ሊያጠፋ በነበረ ጊዜ በሙሴ ጸሎት ምሕረት አድርጎላቸዋል። ሙሴም ሌዋውያንን አዘዞ በአንድ ቀን ሦስት ሺህ ሰዎች እንዲገድሉ አደረገ። እንዲሁም አሮንን ጣዖት እንዲሠራላቸው በማስገደዳቸው ምክንያት እግዚአ ብሔር በእስራኤላውያን ላይ ከባድ በሽታ ላከ። በመንገዳቸውም እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ላለመሄድ ወስኖ ነበር። በኋላ ግን በሙሴ ጸሎት ምክንያት ከእነርሱ ጋር ለመሄድ ፈቀደ (ዘጸ:ም:32 እስከ ም:33ቍ:18)።

እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር ለመድረስ በተቃረቡ ጊዜ ሙሴ ከዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች አንዳንድ ሰው ማለት ዐሥራ ሁለት ሰዎችን በመምረጥ የሀገሪቱንና የሕዝቡን ሁናቴ አጥንተው (ሰልለው) እንዲመለሱ ልኮአቸው ነበር። ስለ ተልእኳቸው የሚገልጸውን የሚከተለውን ጥቅስ ይመለ ከቷል:-

«ዐልፈውም ወደ ኤሽኮል ሸለቆ ደረሱ፤ ከዚያም የወይን ዘለላ ያለበትን ቅርንጫፍ ቈረጡ፤ ያንንም የወይን ዘለላ አንድ ሰው ብቻውን ሊሸከመው የማይችል ከባድ ከመሆኑ የተነሣ ሁለት ሰዎች በመሎጊያ በትከሻቸው ተሸ ከሙ፤ ከዚህም ጋር የሮማንና የበለስ ፍሬ ይዘው መጡ» (ዘኁ: ም: 13 ቍ· 23)።



ሰላዮች ለዓይነት ያህል ያመጡት የከነዓን ምድር ፍራፍሬ (ዘኁ. 12 ፥ 23)

ከተላኩበት ቦታ በተመለሱ ጊዜ የይሁዳ ነገድ ተወካይ ከነበረው ከካሌብና፥ የኤፍሬም ነገድ ተወካይ ከነበረው ከኢያሱ በቀር የሌሎቹ የዐሥሩ ነገድ ተወካዮች ሁሉም ስላዩት ነገር ክፉ ወሬ አወሩ። እግዚአብሔር ክፉ ወሬ ያወሩትን ሰዎች ቀሠፋቸው እስራኤላውያንንም በወሬአቸው አሸበሩ። በዚ ህም ምክንያት ወደ ግብጽ ለመመለስ አስበው መሪ ለመምረጥ ተነሣሡ። ኢያሱና ካሌብም ሕዝቡን ለማረጋጋት በተናገሩ ጊዜ ያ ዐመፀኛ ሕዝብ ሊወግ ራቸው ተነሣ (ዘኁ:ም:14:ቍ 26 – 38)። የእግዚአብሔር ቍጣ ነድዶ ሁሉንም ሊያጠፋ በነበረ ጊዜ በሙሴ አማላጅነት ሳያጠፋቸው ቀር ቶአል። ይሁን እንጂ ከግብጽ የወጣው ትውልድ ሁሉ አልቆ የተስፋይቱን ምድር

የሚወርሱአት ልጆቻቸው ብቻ ናቸው ብሎ እግዚአብሔር ወሰነ። ኢያሱና ካሌብ ግን በእግዚአብሔር ስለተማመኑ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲገቡ ተፈቀደላቸው (ዘኍ:ም:13ቍ:1–ም:14ቍ:1–38)።

ከሌዊ ነገድ ከቀዓት ጐሣ የነበረው ቆሬ፥ ከሮቤል ነገድ የነበሩት ዳታን፥ አቤሮንና ኦን በሙሴ ላይ ለማመፅ በድፍረት ተነሣሡ። ከእነርሱም ጋር የሕዝብ አለቆች የነበሩ ሁለት መቶ ኀምሳ ሰዎች ተባበሩ። ወደ ሙሴና ወደ አሮንም ቀርበው የእስራኤል ሕዝብ በመላ በእግዚአብሔር የተመረጠና ለእግዚአብሔር የተለየ ሲሆን እናንተ ራሳችሁን ከፍ ከፍ የምታደርጉት ለምንድነው? አሉአቸው። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር እነዚያን ዐመፀኞች መሬት ተከፍታ እንድትውጣቸው አደረገ። የእግዚአብሔርን ወገኖች ገድላችኋል በማለት መላው ሕዝብ በሙሴና በአሮን ላይ ተነሥቶ ማጕረምረምና ወደ እነርሱ መሰብሰብ ጀመረ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ መቅሠፍት አውርዶ ዐሥራ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሰዎች እንዲያልቁ አደረገ። ሙሴና አሮን በግንባራቸው ተደፍረው ባይጸልዩና አሮንም ዕጣን በማጠን ባያስተሰርይላቸው ኖሮ ከዚያ የበለጠ የሕዝብ ቍጥር ባለቀ ነበር (ዘኍ:ም:16ቍ:1–50)።

እስራኤላውያን ከሖር ተራራ ተነሥተው ወደ ቀይ ባሕር በሚወስደው መንገድ በሚጓዙበት ጊዜ በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ ክፉ ቃል በመናገር ማጕረምረም ጀመሩ። እነርሱም «ምግብና ውሃ በሌለበት በዚህ በረሓ እንድ ንሞት ለምን ከግብጽ ምድር አስወጣችሁን? ይህን አስከፊ ምግብ ሰውነታችን ተጸይፎታል» አሉ።

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ተናዳፊ እባብ ስለላከባቸው ብዙዎች በእባብ ተነድፈው ሞቱ። ከዚያ በኋላ ወደ ሙሴ ሄደው ኃጢአቸውን በመናዘዝ ወደ እግዚአብሔር እንዲጸልይላቸው ለመኑት። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር በጸለየ ጊዜ የነሐስ እባብ አዘጋጅቶ እንዲሰቅለው በእግዚአብሔር ታዘዘ። በእባብ የተነደፈ ሰው ሁሉ ወደነሐሱ እባብ ሲመለከት ዳነ (ዘኍ:ም:21ቍ:4–9)።



በእባብ የተነደፉ ሰዎችን ለማዳን ሙሴ የሰቀለው የነሐስ እባብ (ዘኍ ም 1፥ቍ 4–9)።



__መጽሐፈ አስቴር:-__ ይህ መጽሐፍ ዐሥር ምዕራፎች ያሉት ሆኖ የእግዚአብሔር ስም በመጽሐፉ ውስጥ ሳይጠቀስ ቢታለፍም እንኳ እግዚአብሔር ለአይሁድ ሕዝብ ያደረገውን ጥበቃ ያሳያል። ስለጸሎትና ስለጸሎት ውጤት የተገለጠ ቢሆንም እንኳ የእግዚአብሔር ስምና ስለ ሃይማኖት በግልጥ ሳይጠቀስ መታለፉ አንዳንድ ምሁራን እንደሚሉት በዚያን ጊዜ የእግዚ አብሔርን ስም መጥራት ወይም ስለ ሃይማኖት አንሥቶ መነጋገር ችግርን ያስከትል ስለ ነበረ ነው። መጽሐፉንም በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ለማቅረብ ይቻላል።

የመጀመሪያው ክፍል ምዕራፍ አንድና ሁለት ሲሆን በዚህ ክፍል ውስጥ የፋርሱ ንጉሥ አርጤክስስ ሚስቱን አስጢንን ፈትቶ አይሁዳዊቱን አስቴርን ያገባ መሆኑንና ይህችም አስቴር አባትና እናት የሌላትና መርዶክዮስ የተባለው የአጐትዋ ልጅ እንደ አባት ሆኖ ያሳደጋት አይሁዳዊት ምርኮኛ የነበረች መሆንዋ ተገልጦአል።። መርዶክዮስም ሰዎች በንጉሡ ላይ ዐቅደውት የነበረውን አድማ በአስቴር በኩል ለንጉሡ እንዲነገረው አድርጓል።

የፋርስ ንጉሥ የነበረው አርጤክስስ በነገሠ በሦስተኛው ዓመት ለባለሚሎቹ ሁሉ ግብዣ አድርጎ ነበር። እንዲሁም የመናገሻ ከተማ በሆነችው በሱሳ ለሚኖሩ ነዋሪዎች ሁሉ ሌላ ግብዣ አደረገ። ንግሥት አስጢንም እንደዚሁ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ለሴት ወይዛዝርት ሌላ ግብዣ አድርጋ ነበር።

ግብዣው በተጀመረ በሰባተኛው ቀን ንጉሥ አርጤክስስ ወይን ጠጅ ጠጥቶ ደስ ባለው ጊዜ ንግሥት አስጢን ልብሰ መንግሥትዋን ለብሳና ዘውድ ጭና ወደ ግብዣው ቦታ እንድትመጣ ያደርጉ ዘንድ የእልፍኝ አገልጋዮቹን አዘዛቸው። ይህንንም ያደረገው የንግሥት አስጢንን ውበት ለእንግዶቹ ለማሳየት ነበር። ነገር ግን ንግሥቲቱ የንጉሡን ትእዛዝ ለመፈጸም እምቢ አለች። በዚህ ጊዜ ንጉሡ በጣም ተቈጥቶ ምን ማድረግ እንደሚገባው አማካሪዎቹን ጠየቃቸው።

አማካሪዎቹ የሰጡት ምክር ንግሥት አስጢን የንጉሡን ትእዛዝ አለማክበርዋ ወንዶችን ሁሉ እንዳዋረደች ስለሚቈጠር አስጢንን ሽረህ የእርስዋን የንግሥትነት ማዕረግ ከእርስዋ ለተሻለች ሌላ ሴት ስጥ አሉት። እርሱም ሐሳቡን ተቀብሎ በሥራ ላይ እንዲውል ወሰነ። ከዚያም በኋላ አማካሪዎቹ በንጉሡ ነገሥቱ ግዛት ውስጥ የሚገኙ ውብ የሆኑ ልጃገረዶች እየተመረጡ በሱሳ ለአንተ የተመረጡ ሴቶች መኖሪያ ወደሆነው ቤት እንዲመጡ ይደረግ፤ ከእነርሱ መካከል ይበልጥ የምትወድዳትን በአስጢን ምትክ ንግሥት እንድትሆን አድርግ አሉት። ንጉሡም ሐሳቡን ተቀብሎ በሥራ ላይ አዋለው።

በሱሳ ከተማ የሚኖር ከብንያም ነገድ የሆነ መርዶክዮስ የሚባል አንድ አይሁዳዊ ነበር። ወላጆችዋ የሞቱባትና መርዶክዮስ እንደ ልጁ አድርጎ የሚያሳድጋት አስቴር የተባለች ውብ የሆነች ሴት ልጅ ነበረች። እርስዋም በንጉሡ አማካሪዎች ምክር መሠረት ለንጉሡ ወደ ተመረጡ ሴቶች መኖሪያ ተወሰደች። አይሁዳዊት መሆንዋን በምሥጢር እንድትጠብቀው እንጂ ለማንም እንዳትናገር መርዶክዮስ አስጠነቀቃት።



www.ethiopianorthodox.org

የተመረጡት ሴቶችም የቍንጅና እንክብካቤ ከተረገላቸው በኋላ በየተራ ወደ ንጉሡ እንዲገቡ ይደረግ ነበር።

ንጉሥ አርጤክስስ በነገሠ በሰባተኛው ዓመት አስቴር ወደ ቤተ መንግሥቱ ተወሰደች። በንጉሡም ዘንድ ከሌሎቹ ልጃገረዶች ሁሉ ይበልጥ ተወዳጅነትን አገኘች። እርሱም መንግሥታዊውን ዘውድ አንሥቶ በራስዋ ላይ ደፋላትና በአስጢን ምትክ አነገሣት።

መርዶክዮስ በቤተ መንግሥቱ ደጅ ተቀምጦ ሳለ ጠባቂዎች ከነበሩት መካከል ሁለቱ ንጉሡን ለመግደል ሲያድሙ ሰማ። ይህንንም አድማ በአስቴር በኩል ለንጉሡ እንዲነገረው አደረገ። ስለጉዳዩ ምርመራ በተደረገ ጊዜ ነገሩ እውነት ሆኖ ስለተገኘ እነዚያ ሰዎች በስቅላት ተቀጡ። ንጉሡም ይህ ሁኔታ በንጉሠ ነገሥቱ የታሪክ መዝገብ እንዲመዘገብ አዘዘ።

ሁለተኛ ክፍል ምዕራፍ ሦስት ሲሆን በውስጡም በጠቅላላ ሀገሪቱ ላይ ሃማ የተባለው ሰው ወደ ከፍተኛ የሹመት ደረጃ ማደጉ፥ እርሱም ሲወጣና ሲገባ መርዶክዮስ የተባለው አይሁዳዊ እንደሌሎቹ ሰዎች የማይሰግድለት መሆኑ፥ በዚህም ምክንያት ሃማ ተቈጥቶ የአይሁድን ዘር ሁሉ ለማጥፋት መወሰኑ፥ ለዚህም የንጉሡን ፈቃድ ማግኘቱና የዚህንም የውሳኔ መግለጫ በንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ሁሉ እንዲተላለፍ ማድረጉ ይገኙበታል።

ንጉሥ አርጤክስስ ሃማ የተባለውን ሰው ከፍ ከፍ አድርጎ ከእርሱ ጋር ከነበሩት አዛውንት ሁሉ በላይ አከበረው። በንጉሡ በር የነበሩት አገልጋዮች ሁሉ ለሃማ ተደፍተው ይሰግዱ ዘንድ ንጉሡ ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር። በዚህም መሠረት ሃማ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሲገባና ሲወጣ ሁሉም እየተደፉ ሲሰግዱለት መርዶክዮስ ብቻ አይሰግድለትም ነበር። ሰዎችም ለምን ለሃማ እንደማይሰግድለት መርዶክዮስን በጠየቁት ጊዜ እኔ አይሁዳዊ ስለሆንኩ ለእርሱ አልሰግድም የሚል መልስ ሰጥቶአቸዋል። ከዚህ በኋላ ሰዎቹ ወደ ሃማ ሄደው መርዶክዮስ አይሁዳዊ ስለሆነ ስትወጣና ስትገባ አይሰግድልህም ብለው ነገሩት። ሃማም በዚህ ጉዳይ በጣም ተቈጥቶ መርዶክዮስን ብቻ ሳይሆን በአርጤክስስ ግዛት ውስጥ የነበሩትን የአይሁድን ሕዝብ በሙሉ ለማጥፋት ዐቀደ። በዚህም መሠረት ሃማ ወደ ንጉሡ ወደ አርጤክስስ ቀርቦ በአንተ ግዛት ውስጥ በየቦታው ተበታትኖ የሚገኝ አንድ ሕዝብ አለ። ይህም ሕዝብ የራሱ የሆነ ሕግ ስላለው ለመንግሥት ሕግ አይገዛም። እንደዚህ ያለ ሕዝብ ሊኖር ስለማይገባው ፈቃድህ ቢሆን መጥፋት አለበት አለው። ንጉሡም የማኅተብ ቀለበቱን አውልቆ ለሃማ በመስጠት አንተ የፈለግኸውን እንድታደርግ ሥልጣን ሰጥቼሃለሁ አለው።

ሃማ በአርጤክስስ የግዛት ክልል የሚኖሩ የአይሁድ ወገኖች የሆኑ ሁሉ ወንድና ሴት፥ ሽማግሌና ሕፃን ሳይለይ የሚፈጁበት ቀን ወስኖ በየቦታው የሚላክ የትእዛዝ ጽሑፍ ጽፎ የንጉሡን ማኅተም አተመበትና በፍጥነት ላከው።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ አራት እስከ ዐሥር ሲሆን በዚህም ውስጥ መርዶክዮስ የአስቴርን እርዳታ መጠየቁ፥ አስቴር ንጉሡንና ሃማን ግብዣ



መጥራትዋ፥ የመርዶክዮስ መሾምና የሃማ መሰቀል፥ አይሁድ ጠላቶቻቸውን መበቀላቸውና የፑሪም በዓል አከባበር ይገኙባቸዋል።

መርዶክዮስ የሃማን ዕቅድ በሰማ ጊዜ በሐዘን ልብሱን ቀደደ። አይሁድም በያሉበት መጾምና ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ማልቀስ ጀመሩ። አብዛኛዎቹም ማቅ ለብሰውና በራሳቸው ላይ ዐመድ ነስንሰው ተቀመጡ። መርዶክዮስ ማቅ የለበሰ መሆኑን አስቴር በሰማች ጊዜ ምክንያቱን ሚጠይቅ ሰው ላከችበት። እርሱም ጉዳዩን ካስረዳት በኋላ ወደ ንጉሡ ገብታ ስለሕዝብዋ ምሕረት እንድትለምን ጠየቃት። እርስዋም ማንም ሰው ሳይጠራ ወደ ንጉሡ መግባት እስከሞት የሚያስቀጣው መሆኑን ብታውቅም እንኳ ብገደልም ልገደል እንና ወደ ንጉሡ ለመግባት ዐቅጄአለሁና በሱሳ ለሚገኙ አይሁድ ሁሉ ይጸልዩልኝ ዘንድ ንገራቸው አለችው፤ መርዶክዮስም አስቴር እንደነገረ ችው አደረገ። አስቴርም እየፈራች ወደ ንጉሡ ክፍል አመራች። ንጉሡ ንግሥት አስቴርን በስተውጭ ቆማ ባያት ጊዜ በፊቱ ሞገስን አገኘችና አስቴር ሆይ፥ ምን ትፈልጊአለሽ አላት። እርስዋም በዚያን ዕለት ማታ ባዘጋጀችው ግብዣ ላይ እርሱና ሃማ እንዲገኙላት ጠየቀች። ንጉሡና ሃማ አስቴር ባዘጋጀችው ግብዣ ላይ በተገኙ ጊዜ አስቴር ምን እንደምትፈልግ ጠየቃት። እርስዋ ግን ነገ በማዘጋጀው ግብዣ አንተና ሃማ እንደገና እንድትገኙልኝ፥ በዚያም ግብዣ ላይ የእኔን ፍላጎት እነግርሃለሁ አለችው።

ሃማ በጣም ተደስቶ ከግብዣ ወጥቶ ሲሄድ መርዶክዮስ ምንም ክብር ሳይሰጠው ተቀምጦ ስላገኘው በጣም ተቈጣ። ወደቤቱም ገብቶ ለሚስቱና ለወዳጆቹ በመርዶክዮስ ምክንያት መበሳጨቱን ገለጠላቸው። እነርሱም ለመርዶክዮስ መስቀያ የሚሆን እንጨት እንዲያዘጋጅና ንጉሡን አስፈቅዶ እንዲሰቅለው፥ ከዚያም በኋላ በደስታ ወደ ንግሥቲቱ ግብዣ እንዲሄድ መከሩት።

በዚያኑ ሌሊት ንጉሡ እንቅልፍ አጥቶ በቤተ መንግሥቱ የታሪክ ማስታወሻዎች የተመዘገቡትን ነገሮች እንዲያነብቡለት አዘዘ። ባነበቡለትም ጊዜ በእርሱ ላይ ታቅዶ ስለነበረው ዐድማና እንደምን አድርጎ በመርዶክዮስ አማካይነት እንደከሸፈ ተነበበለት። በዚህ ጊዜ አገልጋዮቹን ታዲያ፥ ለመርዶክዮስ ምን ተደረገለት? ብሎ ጠየቀ። አገልጋዮቹም ለእርሱ ምንም የተደረገለት ነገር የለም አሉ። ንጉሡ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ከባለሥልጣኖቹ ማን አለ? ብሎ ጠየቀ። በዚያን ጊዜ ሃማ ባዘጋጀው እንጨት ለይ መርዶክዮስን ለመስቀል ይችል ዘንድ ከንጉሡ ፈቃድ ለመጠየቅ በመምጣት ላይ ነበር። ስለዚህ አገልጋዩቹ ሃማ አንተን ለማነጋገር በመጠየቅ ላይ ነው አሉት። ግባ በሉት አለ። ሃማም በገባ ጊዜ ንጉሡ ታላቅ ክብር ልሰጠው የፈለግሁት አንድ ሰው አለ፤ ታዲያ፥ ለዚህ ሰው ምን ባደርግለት የሚገባ ይመስልሃል? ብሎ ጠየቀው። በዚህ ጊዜ ሃማ ያ ክብር ሊሰጠው የታሰበለት ሰው እርሱ እራሱ እንደሆነ ገመተ። ስለዚህም ለንጉሡ እንዲህ ሲል መለሰለት:- «ለእንደዚህ ያለው ሰው አንተው ራስህ የለበስከውን ልብሰ መንግሥት እንዲያመጡለት አድርግ፤ አንተም በተቀመጥህበት ፈረስ ራስ ላይ የንጉሣዊ ዘውድ ምልክት




www.ethiopianorthodox.org

እንዲያደርጉበት እዘዝ፤ ከልዑላን መሳፍንትህ አንዱን አስጠርተህ ልብሰ መንግሥቱን እንዲያለብሰውና በተዘጋጀለት ፈረስ ላይ አስቀምጦ ፊት ለፊት እየመራ ወደ ከተማይቱ አደባባይ እንዲያወጣው አድርግ፤ ሁለቱም በሚጓዙበት ጊዜ መስፍኑ ንጉሡ ሊያከብረው የፈለገውን ሰው እንዴት እንደ ሸለመው ተመልከቱ» እያለ ዐዋጅ ይናገር።»

ንጉሡ ሃማን በል አሁን ያልከውን አንድ እንኳ ሳታስቀር ለአይሁዳዊው ለመርዶክዮስ አድርግለት አለው። ሃሚም እንደታዘዘው አደረገ።

ከዚህ በኋላ ንጉሡና ሃማ ለሁለተኛ ጊዜ ከአስቴር ጋር ለመጋበዝ መጡ። በመጠጣት ላይ እያሉ ንጉሡ አስቴርን ምን እንደምትፈልግ ጠየቃት። አስቴርም የእርስዋና የወገኖችዋ ሕይወት ለመጥፋት ማለት ሁሉም ለመገደል ስለተፈረደበት ከዚህ ጥፋት አድነን አለችው። ንጉሥ አርጤክስስ ይህን ያደረገ ማን እንደሆነ ጠየቃት፤ እርስዋም ሃማ መሆኑን ስለገለጠችለት ንጉሡ ተቈጥቶ ከመጠጡ ላይ በመነሣት ወደ ቤተ መንግሥቱ ያትክልት ቦታ ሄደ። ሃማም ንግሥት አሰቴር ይቅርታ ታደርግለት ዘንድ እርስዋ በተቀመጠችበት ድንክ አልጋ ላይ በግንባሩ ተደፋ። ንጉሡ ተመልሶ ሲመጣ ሃማን በዚያ ሁኔታ ላይ ስላየው ይህ ሰው በገዛ ቤተ መንግሥቴ ዐይኔ እያየ ንግሥቲቱን ሊደፍር ነው ወይ ብሎ ተቈጣ። ሃማ መርዶክዮስን ለመስቀል በቤቱ ግቢ የተከለው እንጨት ለንጉሡ ስለተገለጠለት እዚያ ላይ ወስደው ሃማን እንዲሰቅሉት አዘዘና ሰቀሉት። የንጉሡ ቍጣ የበረደው ከዚያ በኋላ ነው።



አስቴር በንጉሥ አርጤክስስ ፊት (አስቴር ም 7)

ከነዚህ ሁሉ ነገሮች በኋላ ንግሥት አስቴር ሃማ ያስተላለፈው የግድያ ዐዋጅ በሚሻርበት መላ ላይ ለንጉሡ ልመናዋን አቀረበች። መርዶክዮስም የቅርብ ዘመድዋ መሆኑን ለንጉሡ ነገረች። ንጉሡ የንጉሥ ዐዋጅ የማይሻር መሆኑን ቢገልጥም እንኳ፥ አይሁድ ግን ሊያጠቃቸው ከሚመጣ ከማንናውም ጠላት ለመከላከል እንዲደራጁና እንዲዘጋጁ በመርዶክዮስና በአስቴር በኩል በንጉሡ ስም ለሁሉም መመሪያ እንዲያስተላልፉ ፈቀደላቸው። ይህም መመሪያ



www.ethiopianorthodox.org

በንጉሡ ነገሥቱ ግዛት ሁሉ በፍጥነት እንዲዳረስ የቤተ መንግሥቱ ፈጣን ፈረሶች ተፈቀዱላቸው። በዚህም መሠረት አይሁድ ብዙ ጠላቶቻቸውን ገደሉ፤ ብዙ ሌሎች ወገኖችም ወደ አይሁድ ሃይማኖት ገቡ።

የዚህንም ከጠላቶቻቸው የዳኑበትን ቀን ለማስታወስ የፑሪም በዓል በየዓመቱ እንዲከበር አስቴርና መርዶክዮስ ትእዛዝ አስተላለፉ።

<u>መጽሐፈ ዮዲት</u>:- የፋርስ ንጉሥ ናቡከደነፆር በነገሠ በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት የሜዶንን ንጉሥ አርፋክስድን ድል አድርጎ አገሩን ያዘ። የሌላውን አገር አሸንፎ በመያዝ የሚገኘውን ጥቅም በተመለከተ ጊዜ በአካባቢው የሚገኙትን አገሮች ሁሉ የማስገበር ፍላጎት ዐደረበት። በዚህም መሠረት በአካባቢው ወዳሉት አገሮች ሁሉ በእርሱ ሥልጣን ሥር ገብተው እንዲገብሩ መልእክተኞችን ላከባቸው። ብዙዎቹ አገሮች እንቢተኛነታቸውን ገለጡ። ከእነዚህም ሕዝቦች መካከል የይሁዳ ሕዝብ ይገኝበታል። ብዙዎቹ እንቢተኞች ሕዝቦች ሆሎፌርኔስ በተባለው የናቡከደነፆር የጦር አዝማች አማካይነት የተሸነፉና አገሮቻቸውም በናቡከደነፆር ግዛት ሥር የወደቁ መሆናቸውን እስራኤላውያን ሰሙ የእነዚህም የናቡከደነፆር ወታደሮች ዓላማ ያሸነፉአቸውን ሕዝቦች ምሽጎችና ሕንጻዎቻቸውን ሁሉ አፈራርሰውና አገሮቹን ሁሉ ደምስሰው ገንዘባቸውን ለመዝረፍ፥ ሴቶችንና ሕፃናትን ለመግደል፥ ወንዶችንና ወጣቶችን ለመማረክ፥ ማምለኪያውን ለማፈራረስ መሆኑን እስራኤላውያን ተረዱ።

ሆሎፎርኔስም በንጉሡ ትእዛዝ አንድ መቶ ሃያ ሺህ እግረኞች፥ ዐሥራ ሁለት ሺህ ፈረሰኞች አሰለፈ። ዕቃዎችን ለመጫን እንዲረዱት ብዙ ግመሎችን፥ አህዮችንና በቅሎዎችን፥ እንዲሁም ለምግብነት ብዙ በጎችን፥ ከብትንና ፍየሎችን ይዞ ሄደ።

እስራኤላውያን ገና በቅርብ ጊዜ ከምርኮ ተመልሰው ቤተ መቅደሱን ጠግነውና ከርክሰት አንጽተውት ነበር። ይህ የናቡከደነፆር ሠራዊት በእነርሱ ላይና በቤተ መቅደሱ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጥፋት በማሰብ ይፈሩና ይጨነቁ ጀመር። ይሁን እንጂ ሀገራቸውንና ቤተ መቅደሳቸውን ለመከላከል በመወሰን ዝግጅት ጀመሩ። እግዚአብሔርም ይረዳቸው ዘንድ በጾምና በጸሎት ተማጠኑት። እነርሱም በሌላ ክፍል ለሚገኙት እስራኤላውያን ሁሉ በሊቀ ካህናቱ በኢያቄም አማካይነት መልእክት ላኩ። ለዚህም ጉዳይ በኢየሩሳሌም ስብሰባ ተደረገ። ካህናቱና የቤተ መቅደሱ አገልጋዮች ሁሉ ማቅ ለብሰው ከልብ ስለጸለዩ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰማ።

የአሦርያውያኑ የጦር መሪ ሆሎፌርኔስ የእስራኤልን ለጦርነት መዘጋጀት በሰማ ጊዜ በጣም ተናደደ። ከዚያም በናቡከደነፆር ሥልጣን ሥር ለመገዛት ተስማምተው የነበሩትን የአሞናውያንንና የሞአባውያንን ሰዎች ጠርቶ እናንተ የከነዓን ነዋሪዎች ናችሁ። ስለዚህ በእነዚህ ተራራዎች ላይ ስለሚኖሩት ሰዎች እስቲ ንገሩኝ። ከተሞቻቸው እነማን ናቸው? የሠራዊታቸው ብዛት ስንት ነው? ኀይልና ብርታታቸው በምን ላይ የተመሠረተ ነው? ሠራዊታቸውን የሚመ

ራው ንጉሥ ማን ነው? በምዕራብ በኩል ካሉት አገሮች ሁሉ እነርሱ ብቻ እጃቸውን ለእኔ ያልሰጡት ለምንድነው? ብሎ ጠየቃቸው።

የአሞናውያን መሪ የነበረው አክዮር ለሆሎፌርኔስ እንዲህ ሲል መልስ ሰጠው:- ፈቃድህ ሆኖ ብታደምጠኝ በዚህ በሰፈርህ አጠገብ ባሉት ተራሮች ላይ ስለሚኖሩት ሰዎች ሳልዋሽ እውነተኛ ታሪክ እነግርሃለሁ። እነዚህ ሰዎች ባቢሎናውያን የነበሩ ሰዎች ዘሮች ናቸው። እነርሱም የሰማይን አምላክ ለማምለክ ብለው ከቀድሞ አባቶቻቸው ተለዩ። በመጨረሻም የቀድሞ አባቶቻቸውን አማልክት ለማምለክ እንቢ ስላሉ ከሀገራቸው ተባረሩ። ከዚያም ወደ መስጴጦምያ ተሰድደው ለብዙ ጊዜ ኖሩ። ከዚያም አምላካቸው መስጴጦምያን ትተው ወደ ከነዓን እንዲሄዱ አዘዛቸው። እዚያም በወርቅ፥ በብርና በከብቶች መንጋ በጣም በለጸጉ። ቄየት ብሎም የከነዓንን ምድር ረሀብ ባጠቃት ጊዜ እነዚህ እስራኤላውያን ወደ ግብጽ ወረዱና በቂ ምግብ በዚያ እስከ ነበረ ድረስ ቈዩ። እዚያም በነበሩ ጊዜ ለመቈጠር የማይቻል እስኪሆኑ ድረስ በዙ። ስለዚህ የግብጹ ንጉሥ በጠላትነት ተነሣባቸው። እነርሱንም የሸክላ ሥራ እንዲሠሩ አደረጋቸው። በጣም ጨቍኖም ባሪያ አደረጋቸው። ለአምላካቸው በጸለዩ ጊዜ እግዚአብሔር በግብጾች ላይ ታላቅ ቍጣን አመጣባቸው። ግብጾችም በአስወጡአቸው ጊዜ አምላካቸው ቀይ ባሕርን አደረቀላቸውና ወደ ሲና ተራራና ወደ ቃዴሽ በርኔ መራቸው። እነርሱም ከከነዓን በስተደቡብ ባለው አገር ኖሩ። የአሞራውያንን፥ የከነዓናውያንን፥ የፔሩዛውያንን፥ የኢያቡሳውያንን፥ የሴኬማውያንንና የጌርጌሳውያንን አገሮች በማስለቀቅ ያዙ። እነዚህ እስራኤላውያን በእነዚህ ተራሮች ላይ ለብዙ ዘመን ኖረዋል። አምላካቸው ክፋትን ይጠላል። በእርሱ ላይ ኃጢአት እስካልሠሩ ድረስ በልጽገው ይኖራሉ። ትእዛዙን በሚያፈርሱበት ጊዜ ግን ብዙ ችግር ይደርስባቸዋል። እንዲያውም በመጨረሻ ተማርከው ወደ ውጭ ሀገር ተወስደዋል። ቤተ መቅደሳቸው ፈርሶአል፤ ከተሞቻቸውም የጠላቶቻቸው መኖሪያዎች ሆነዋል። አሁን ግን ወደ አምላካቸው በተመለሱ ጊዜ ከተበታተኑበት ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል። ቤተ መቅደሳቸው የሚገኝበትን የኢየሩሳሌምንም ከተማ በእጃቸው አስገብተዋል፤ ሌላ ሕዝብ ባልኖረባቸው በተራሮቹም መኖር ጀምረዋል።

ክቡር ሆይ፥ እነዚህ ወገኖች አሁን አምላካቸውን በድለው ከሆነ ሳያውቁ እንኳን ቢሆን አንዳች በደል ፈጽመው ከሆነ እነርሱን በቀላሉ አደጋ ልንጠልባቸው እንችላለን። የበደሉት በደል ከሌለ ግን አምላካቸው ስለሚከላከልላቸው ብንተዋቸው ይሻላል። አለበለዚያ ግን በዓለም ሁሉ ፊት እንዋረዳለን።

አኪዮር ንግግሩን በፈጸመ ጊዜ በድንኳን ዙሪያ ቆመው የነበሩት ሰዎች ሁሉ ተቃውሞ አሰሙ። እዚያ ከነበሩት አበዛኛዎቹ ሰዎች አክዮር በሞት እንዲቀጣ ጠየቁ።

የተቃዋሚዎቹ ድምፅ ጸጥ ባለ ጊዜ ሆሎፌርኔስ በሰው ሁሉ ፊት አክዮርን እንዲህ አለው:- ነቢይ ሆነህ የምትናገረው አንተ ማነህ መስለህ? አምላክ



www.ethiopianorthodox.org

ይረዳቸዋል ብለህ እስራኤልን ለመዋጋት ወደ ጦርነት እንዳንወጣ የምትነግረን አንተ ማነህ? የእኛ አምላክ ናቡከደነፆር መሆኑ በቂአችን ነው። እርሱ ወታደሮቹን ልኮ እስራኤላውያንን ከምድረ ገጽ ያጠፋቸዋል። አምላካቸው ሊረዳቸው አይችልም። እኛ የናቡከጸነፆር አገልጋዮች ነንና የእነርሱን ሠራዊት ሁሉ እንደ አንድ ሰው እንመታቸዋለን። በፈረሰኞቻችን ፊት መቆም አይችሉም። ተራሮቹ በደማቸው የተበከሉ ይሆናሉ፤ ሸለቆዎቻቸውም በእነርሱ በድኖች የተሞሉ ይሆናሉ። ዱካቸው እስከማይገኝ ድረስ ተጠራርገው ይጠፋሉ። ይህ የስንፍና ንግግር የማይናገረው የምድር ሁሉ ጌታ የሆነው የናቡከደነፆር ትእዛዝ ነው። አክዮር ሆይ፥ አንተ አንድ አሞናዊ ወዶ ዘማች ነህ እንጂ ምንም አይደለህም። ንግግርህም እንደ ከሐዲ ነው። ይህን ከጌታው የኰበለለ ባሪያ ዐይነቱን ዘር ለመቅጣት እስከመጣ ድረስ አታየኝም። በዚያን ጊዜ የእኔ ወታደሮች ይገድሉሃል። ይህም ማለት ያን ጊዜ ከሚገደሉት ሰዎች አንዱ ትሆናለህ ማለት ነው። አሁን የእኔ ሰዎች ከእስራኤል ከተሞች ወደ አንዱ ወስደው እዚያ ጥለውህ ይመጣሉ፤ አንተም ከሕዝቡ ጋር እዚያው ትሞታለህ። አክዮር ሆይ፥ ምን አሳሰበህ? ከተማይቱ ትቋቋመኛ ይመስልሃልን? ዛቻዬን ሁሉ በሥራ ላይ አውለዋለሁ። በዚህም እርግጠኛ ሁን።

ከዚያ በኋላ በሆሎፌርኔስ ትእዛዝ የሆሎፌርኔስ ወታደሮች አክዮርን ወስደው ከቤቱላ በታች ባለው ምንጭ አጠገብ ጥለውት ለመምጣት ሄዱ። የዚያ ከተማ ሰዎች የሆሎፌርኔስ ወታደሮች ወደዚያ መምጣታቸውን ባዩ ጊዜ መሣሪያቸውን ይዘው ወደ ተራራው በመውጣት በወንጭፍ የድንጋይ ናዳ ያወርዱባቸው ጀመር። በዚህም ወደተራራው ከመቅረብ ተገቱ። አክዮርንም በተራራው ግርጌ አስረው ጥለውት ወደ ሄሎፈርኔስ ተመለሱ። እስራኤላውያን ከተራራው በወረዱ ጊዜ አክዮርን እዚያ ታስሮ ስላገኙት ፈትተው ወደ እስራኤል ጉባኤ ፊት ወሰዱትና ለሆሎፌርኔስ ምን እንዳለውና ሆሎፌርኔስም ምን ብሎ እንደፎከረ ገለጠላቸው። ከባለሥልጣኖቹ አንዱ የነበረው ኦዝያስም አክዮርን ወደ ቤቱ ወሰደው።

በማግስቱ ሆሎፌርኔስ አንድ መቶ ሰባ ሺህ እግረኛ ወታደሮችንና ዐሥራ ሁለት ሺህ ፈረሰኞችን አሰልፎ እስራኤላውያን የመሸጉበትን ተራራ ከበባ አደረገ። እስራኤላውያንም የጠላትን ወታደር ብዛት ባዩ ጊዜ ፈሩ። ሞአባውያን፥ ኤዶማውያንና፥ የሜዲቴራንያን ጠረፍ ወታደሮች ማለት ከአሦራውያን ጋር ወዶ ዘማቾች የነበሩት ሆሎፌርኔስን እንዲህ አሉት:- እስራኤላውያንን በጦርነት ከመግጠም ይልቅ የሚጠጡትን ውሃ ምንጭ ብንዘጋባቸው አንድም በውሃ ጥም ያልቃሉ ያለዚያም እጃቸውን ይሰጣሉ፤ በዚህም ዓይነት ከእኛ አንድ ሰው ሳይሞት ልናሸንፋቸው እንችላለን ብለው ሐሳብ አቀረቡ። ይህ ሐሳብ በሆሎፌርኔስ ዘንድ ተቀባይነትን ስላገኘ በተራራው ላይ ያሉት ሰዎች የሚጠጡት ውሃ እንዳይኖራቸው የውሃውን ምንጭ ተቈጣ ጠሩባቸው።

እስራኤላውያን ወደ አምላካቸው ጮኹ። ውሃው ከማጠራቀሚያው እያለቀ ሕዝቡ ውሃ የሚያገኘው በቍጠባ በማከፋፈል ሆነ። ሰዎቹ ሁሉ ተሰብስበው

ወደ ያዝያን በመምጣት በውሃ ጥም ከምንሞት እጃችንን ለሆሎፌርኔስ ብንሰጥ ይሻላል፤ እንዲያውም እናንተ ከእነርሱ ጋር ስምምነት ባለማድረጋችሁ በደላችሁን በማለት ወቀሱአቸው። ሕዝቡም ድምፁን ከፍ በማድረግ ምርር ብሎ አለቀሰ። በዚህ ጊዜ ያዝያን ሕዝቡን አይዞአችሁ ተስፋ አትቍረጡ እስከ አምስት ቀን ድረስ ፈጣሪአችን የማያድነን ከሆነ እናንተ እንዳላችሁ አደርጋለሁ አለና ሕዝቡን ሸኘ።

ያዝያን ይህን ውሳኔ በወሰነ ጊዜ ዮዲት የተባለችው ባልዋ ከሞተባት ከሦስት ዓመት በላይ የሆነውና እርስዋም በጣም ሃይማኖተኛና መልከ መልካም የነበረች ሴት ታዳምጠው ነበር።

ዮዲት የከተማው ባለ ሥልጣኖች የነበሩትን ያዝያንን፥ ካብሪንና ካርሚን ወደ ቤትዋ ትጠራቸው ዘንድ አገልጋይዋን ላከቻት። እነርሱም በመጡ ጊዜ እናንተ የቤቱላ ሕዝብ መሪዎች ናችሁ፤ ነገር ግን ዛሬ ለሕዝቡ የገባችሁት ቃል እግዚአብሔርን መፈታተን ነው። እናንተ ማናችሁና ነው በወሰናችሁት ቀን እግዚአብሔር መልስ እንዲሰጣችሁ ልትፈታተኑት የምትፈልጉት? እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ነው እንጂ እናንተ በፈለጋችሁትና በወሰናችሁት ጊዜ መልስ የሚሰጥ አይደለም። ሊሰማና ሊቀበለን አይፈቅድ ይሆናል። እኛ የእርሱን እርዳታ መለመን እንጂ እርሱን ግዴታ ልናስገባ የምንችል አይደለንም።

ያዝያንም የተናገርሽው ነገር ሁሉ እውነት ነው። ግን ሕዝባችን በውሃ ጥም ሊያልቅ ነው። የሰማሽውንም ቃል የገባንላቸው ምንም ምርጫ ስላልነበረን ነው፤ አሁንም ሃይማኖተኛ ሴት ስለሆንሽ እግዚአብሔር ዝናብን ያዘንብልን ዘንድ ጸልይልን አላት።

እሺ፤ እኔ አሁን የእናንተ የቀጠሮ ቀን ከመድረሱ በፊት እግዚአብሔር እስራኤልን ለማዳን ይጠቀምብኛል። ጉዳዩ ተግባራዊ እስኪሆን ድረስ ምን ልታደርጊ ነው ብላችሁ አትጠይቁኝ።

ዮዲትም ማቅ ለብሳና አመድ በራስዋ ላይ ነስንሳ በመንበርከክ ወደ እግዚአብሔር ጸለየች። ጸሎትዋንም በፈጸመች ጊዜ ተነሥታ አከላትዋን ታጠበች፤ ልብስዋን ለወጠች፤ ጌጦችዋንም አደረገችና አገልጋይዋን አስከትላ፥ ስንቋንም አገልጋይዋ እንድትሸከም አድርጋ ወደ ቤቱላ በር ሲደርሱ ሦስቱን ባለሥልጣኖች እዚያ አገኘቻቸው። እነርሱም ዕቅድሽን ሁሉ እግዚአብሔር ያቃናልሽ ብለው መረቁአት። እርስዋም በምትመለስበት በማንኛውም ጊዜ በሩ እንዲከፈትላት ለጠባቂዎች ትእዛዝ ያስተላልፉላቸው ዘንድ ነገረቻቸው። እንደ ጥያቄዋም አደረጉ። ተራራውን ወርዳ ትንሽ እልፍ እንዳለች የአሦር ወታደሮች ያዝዋትና ማን እንደሆነችና ወደየት እንደምትሄድ ጠየቋት። እርስዋም እኔ ዕብራዊት ሴት ነኝ፤ ነገር ግን ከእስራኤላውያን ሰፈር ሸሽቼ የመጣሁት እናንተ እነርሱን እንድታጠፉ እግዚአብሔር የፈቀደላችሁ በመሆኑ ነው፤ አሁንም ምን ማድረግ እንደሚገባው ልነግረው ወደ ጦር መሪአችሁ ወደ ሆሎፌርኔስ እየሄድሁ ነው አለቻቸው።



አይዞሽ አትፍሪ ለእኛ እንደነገርሽን አድርገሽ ለእርሱም ንገሪው፤ እርሱም መልካም ያደርግልሻል ካልዋት በኋላ ሸኝተው ወደ ሆሎፌርኔስ የሚያደርሱአት አንድ መቶ ወታደሮች ከእርስዋ ጋር እንዲሄዱ አዘዙላት።

ወደ ሆሎፌርኔስ ድንኳን መጥታ ወደ እርሱ አጠገብ በደረሰች ጊዜ በግንባርዋ ተደፍታ የአክብሮት ስግደት ሰገደችለት። የሆሎፌርኔስ አገልጋዮች ግን ተነሥታ በእግርዋ እንድትቆም ረዱአት። ሆሎፌርኔስም አይዞሽ ምንም የሚያስፈራሽ ምክንያት የለም፤ የዓለም ሁሉ ንጉሥ ለሆነው ለናቡከደነፆር ለመታዘዝ ፈቃደኛ የሆነ ማንንም ጐድቼ አላውቅም፤ አሁንም ቢሆን በተራራ ላይ ያሉት ወገኖችሽ እኔን ባይሰድቡኝ ኖሮ ጦርነት አላውጅባቸውም ነበር። ይህን ሁሉ ችግር በራሳቸው ላይ ያመጡ እነርሱ ራሳቸው ናቸው። በይ እስቲ አሁን እነርሱን ትተሽ ወደ እኛ የመጣሽበት ምክንያት ምን እንደሆነ ንገሪኝ፤ አይዞሽ አትፍሪ እዚህ በሰላም ትኖሪአለሽ አላት። በዚህ ጊዜ ዮዲት ሆሎፌርኔስን ብልኅና ጀግና እንደሆነ አድርጋ አመሰገነችው። አክዮር በስብሰባቸው ጊዜ ምን እንደነገራቸው የሰማች መሆኑንና የእርሱም ቃል በንቀት መታለፍ የሌለበት መሆኑን ነገረችው። የእስራኤል ሕዝብ የአምላኩን ትእዛዝ በማፍረስ ኃጢአት ካልሠራ በቀር ማንም ሊጐዳው አይችልም፤ አንተ ግን ችግር የለብህም፤ ምክንያቱም የእስራኤል ሕዝብ በአሁኑ ጊዜ የአምላኩን ትእዛዝ እያፈረሰ ነው፤ በረሀቡና በውሃ ጥም ምክንያት ሰው ሁሉ እንስሳቱን እያረደ እየበላ ነው፤ ይህንንም ሲያደርግ ለእግዚአብሔር መቅረብ ያለበትን ዐሥራትና በኵራት መስጠቱን ትቶአል፤ ከዚያም ዐልፎ ከካህናት በቀር ለማንም ያልተፈቀደውን የተቀደሰ ኅብስት ለመብላት እንዲፈቀድለት ፈቃድ እየጠየቀ ነው፤ እኔ አገልጋይህ ግን ሃይማኖቴን አጥብቄ ስለማከብር በዚህ ኃጢአታቸው ምክንያት ከሚጠፉት ከእስራኤላውያን ዘንድ ሸሽቼ መጥቼአለሁ፤ በየሌሊቱም ወደሜዳ ወጥቼ የምጸልየው ጸሎት ስላለ ለአገልጋይህ ፈቃድ ትሰጣታለህ፤ እግዚአብሔርም እስራኤላውያንን በፍጹም የተለያቸው መሆኑን አምላኬ ስለሚነግረኝ በዚያን ጊዜ እነግርህና ትደመስሳቸዋለህ። ይህንንም እንደምታደርግ አስቀድሞ አምላኬ ነግሮኛል አለችው። ይህ ያልሽው ነገር በሚፈጸምበት ጊዜ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል፤ በናቡከደነፆር ቤተ መንግሥት ትኖሪአለሽ፤ በጣምም ዝነኛ ትሆኛለሽ አላት።

ዮዲት ለሦስት ቀኖች ከቤትዋ ይዛ የመጣችውን ምግብ ብቻ እየበላች በየሌሊቱ ወደ ውጭ ሄዳ ጸሎትዋን እየጸለየች ከቈየች በኋላ በአራተኛው ሌሊት ሆሎፌርኔስ በአዘጋጀው ግብዣ በጣም ሰክሮ ተኝቶ በነበረበት ጊዜ በራሱ ሰይፍ አንገቱን ቈርጣ ይዛ ወደ እስራኤላውያን ሰፈር ተመለሰች። እንደደረሰችም ተጣራችና የከተማውን መዝጊያ ከፈቱላት። ወዲያውም የከተማው ሕዝብ ሁሉ በዙሪያዋ ተሰበሰበ። ሰው ሁሉ እግዚአብሔርን አመሰገነ። ዮዲትንም አመሰገኑአት።



www.ethiopianorthodox.org



ዮዲት የሆሎፎርኔስን ራስ እንደቆረጠች ዮዲት 13 ፥ 8

እርስዋም የሆሎፎርኔስን ራስ በከተማው በር ላይ እንዲሰቅሉትና አሦርያውያንን እንዲያሳድዱ ምክር ሰጠቻቸው። ከዚያ በኋላ እስራኤላውያን ሁሉ ተሰባሰበው ጠላትን አሳደዱ፤ ምርኮም ሰበሰቡ። ምርኮውን ወስደው ለመጨረስ ብቻ ሠላሳ ቀን ፈጀባቸው። የድሉን በዓልም ለሦስት ወር ጊዜ ያኽል አከበሩት። ከሆሎፎርኔስ ድንኳን የተማረከውን ዕቃ ሁሉ ለዮዲት ሰጡአት። እርስዋ ግን መልሳ ለቤተ መቅደስ ሰጠችው። የእስራኤል ሴቶችም ከያለበት ተሰብስበው ስለዮዲት ክብር የረጅም ጊዜ በዓል አደረጉ። ሕዝቡ ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜ ራሳቸውን አንጽተው ለእግዚአብሔር ሰገዱ፤ የተለያዩ የመሥዋዕት ዐይነቶችንም ለእግዚአብሔር አቀረቡ።

## ሐዲስ ኪዳን

<u>ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ተለያዩ አገሮች መሄዱ</u>:- በአንጾኪያ በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ በርናባስ በመንፈስ ቅዱስ ቀስቃሽነት ተመርጠው ለማስተማር ተላኩ። በተላኩም ጊዜ ወደ ሴሌውቅያ፥ ወደ ቆጵሮስ፥ ወደ ስልማና ሄዱ፤ በስልማናም በአይሁድ ምኵራቦች የእግዚአብሔርን ቃል አስተማሩ። ጳፉ በደረሱ ጊዜ ባርየሱስ የተባለው ጠንቋይ ስለተቃወማቸው በተአምር ዐይኑ ታወረ። ከጳፉም ተነሥተው ወደ ጴርጌ ሄዱ። እዚያም ቅዱስ ጳውሎስ በሰንበት ቀን ስለእግዚአብሔር ቃል አስተማረ። የአይሁድ ወገኖች ግን ከዚያ አባረሩአቸው። ከዚያም ወደ ኢቆንዮ ሄደው ወደምኵራብ ገብተው በማስተማር ብዙዎችን አሳመኑ። እንደገናም የዚያ አገር አይሁድና አረማውያን ተቃውሞ ስላበዙ ወደ ልስጥራና ደርቤ ሸሽተው ሄዱ። በልስጥራ አንድ ሽባ ሰው ስለፈወሱ እንደ አማልክት ቈጥረዋቸው መሥዋዕት ሊያቀርቡላቸው ፈለጉ። ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ በርናባስ ግን ከለከሉአቸው።



አንዳንድ የአይሁድ ወገኖች ከአንጾኪያና ከኢቆንዮ ወደዚያ መጥተው ሕዝቡን በማሳደም ቅዱስ ጳውሎስን በድንጋይ ወገሩት። የሞተም መስሎአቸው ጐትተው ከከተማ አውጥተው ጣሉት። ደቀ መከሙርቱ ሲመጡ ተነሥና ወደ ከተማ ገባ። በማግስቱም ከቅዱስ በርናባስ ጋር ወደ ደርቤ ሄደ። ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ በርናባስ በደርቤ አስተምረው ብዙ ሰዎችን ካሳመኑ በኋላ ወደ አንጾኪያ ሄዱ። ከዚያም በጵስድያ ዐልፈው ወደ ጵንፍልያ ሄዱ። በጴርጌም ቃሉን ከተናገሩ በኋላ ወደ አጣሊያ ወረዱ። ከዚያም ወደ አንጾኪያ ተመለሱ። ከኢየሩሳሌም ጉባኤ በኋላ ቅዱስ ጳውሎስ ከሲላስ ጋር በሶርያና በኪልቅያ በኩል ዐልፎ ወደ ደርቤና ወደ ልስጥራ ሄደ። በልስጥራ አባቱ አረማዊ፥ እናቱ አይሁዳዊት የሆነች ጢሞቴዎስ የሚባል አማኝ ነበረ። ቅዱስ ጳውሎስም ጢሞቴዎስን ይዞት ለመሄድ ስለፈለገ በዚያ ስፍራ በነበሩት አይሁድ ምክንያት እንዲገረዝ አደረገው። ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ በሚስያ በኩል ዐልፈው ወደ ጢሮአዳ ወረዱ። እዚያም በሌሊት አንድ የመቄዶንያ ሰው ወደ መቄዶንያ ተሻገርና እርዳን ሲለው በራእይ አየ። ከጢሮአዳ በመርከብ ተሳፍረው ወደ ሳሞትራቄ ሄዱ። በማግስቱም ወደ ናጱሌ ሄዱ። ከዚያም ተነሥተው ወደ ፊልጵስዩስ ደረሱ፤ ፊልጵስዩስ በመቄዶንያ የምትገኝ ታላቅ ከተማ ነች።

በፊልጵስዩስ ከተማ ወደፊት የሚሆነውን ነገር በጥንቈላ የሚያናግር ርኩስ መንፈስ ያደረባት አንዲት አገልጋይ ልጃገረድ በመንገድ ላይ አገኛቻቸው። ይህችም ልጃገረድ ለአሳዳሪዎችዋ በጥንቈላ ብዙ ገንዘብ ታስገኝላቸው ነበር። እርስዋም እነ ቅዱስ ጳውሎስን እየተከተለች እነዚህ ሰዎች የልዑል እግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው፤ እነርሱ የመዳንን መንገድ ያበሥሩላችኋል እያለች ጮኸች። ይህንንም አባባል ብዙ ጊዜ ስለደጋገመችው ቅዱስ ጳውሎስ ተበሳጭቶ ርኩስ መንፈሱን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከእርስዋ እንድትወጣ አዝዝሃለሁ ሲለው ርኩስ መንፈሱ ወዲያውኑ ከእርስዋ ወጣ። አሳዳሪዎችዋ ግን ከእርስዋ ጥንቈላ ያገኙት የነበረው ጥቅም ስለተቋረጠባቸው ቅዱስ ጳውሎስንና ሲላስን ይዘው እየጐተቱ ወደ ባለሥልጣኖች አመጡአቸው። በባለሥልጣኖቹም ፊት እነዚህ ሰዎች የአይሁድ ወገኖች ናቸው፤ እኛ ሮማውያን ልንቀበለው የማይገባንን ነገር ያስተምራሉ ብለው ከሰሱአቸው። ባለሥልጣኖቹም የጳውሎስንና የሲላስን ልብስ ገፍፈው በዱላ እንዲደበደቡ አዘዙ። ብዙ ከተደበደቡ በኋላ ወደ ወህኒ ቤት አስገቡአቸው። የወህኒ ቤቱም ጠባቂ እግሮቻቸውን በግንድና በግንድ መካከል አጣብቆ አሰራቸው። ወደ እኩለ ሌሊት ገደማ ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ ሌሎቹ እስረኞች እየሰሙ በጸሎትና በመዝሙር እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ የወህኒ ቤቱ መሠረት እስኪናጋ ድረስ የምድር መናወጥ ሆነ። በሮቹ ሁሉ ከመከፈታቸውም በላይ የእስረኞቹ ሰንሰለት ሁሉ ተፈታ። በዚህ ጊዜ ጠባቂው እስረኞቹ ሁሉ ያመለጡ መስሎት ሰይፉን መዝዞ ራሱን ሊገድል ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ተው በራስህ ላይ ጉዳት አታድርስ፤ ሁላችንም አለን አለው። ጠባቂውም መብራት አስመጥቶ ወደ እስር ቤቱ ገባና በቅዱስ ጳውሎስና በሲላስ እግር ሥር በግንባሩ ተደፋ። ወደ ውጭም አወጣቸውና ለመዳን ምን ማድረግ እንደሚገባው

www.ethiopianorthodox.org

ጠየቃቸው። እነርሱም በጌታችን ኢየሱስ እንዲያምን ነገሩት። በዚያች ሌሊት እርሱና ቤተሰቡ ተጠመቁ። በነጋም ጊዜ ባለሥልጣኖቹ እነዚያ ሰዎች ይለቀቁ ብለው ወደ ወህኒው ቤት መልእክት ላኩ። እነቅዱስ ጳውሎስ ግን እኛ የሮም ዜጋዎች ስንሆን ያለፍርድ ደብድበው አስረውን አሁን ደግሞ በመሥጢር ሊያስወጡን የሚፈልጉት እንዴት ነው? አሁንም እነርሱ ራሳቸው መጥተው ያስወጡን አሉ። ባለ ሥልጣኖችም እነ ቅዱስ ጳውሎስ የሮም ዜግነት ያላቸው መሆናቸውን ባወቁ ጊዜ ፈሩ። ወደ ወህኒ ቤትም መጥተው ይቅርታ ጠየቁአቸውና ከወህኒ ቤት አስወጡአቸው። ከከተማውም እንዲወጡ ለመኑአቸው። እነርሱም በአንፊጶሊስና በአጶሎንያ ዐልፈው ወደ ተሰሎንቄ ሄዱ። ቅዱስ ጳውሎስም እንደልማዱ ወደ አይሁድ ምኵራብ እየገባ ያስተምር ጀመር። ብዙዎች ቃሉን ተረድተው ሲተባበሩ አይሁድ ግን ቀንተው የሚበጠብጡ ሥራ ፈቶችን ከየመንገዱ ሰበሰቡና አሳደሙ። ቅዱስ ጳውሎስንና ሲላስን አውጥተው ለሕዝቡ ለመስጠትም የኢያሶንን ቤት ከበቡ። እነ ቅዱስ ጳውሎስን ስላላገኙአቸው ኢያሶንንና አንዳንድ አማኞችን ጐትተው ወደ ከተማው ባለሥልጣኖች ወሰዱአቸው። ኢየሱስ የሚባል ከቄሳር ሌላ ንጉሥ አለ ብለው ያስተምራሉ በማለት ከሰሱአቸው። ባለሥልጣኖቹም እነ ኢያሶንን ዋስ አስጠርተው ለቀቁአቸው። አማኞችም ቅዱስ ጳውሎስንና ሲላስን በሌሊት ወደ ቤርያ እንዲሄዱ አደረጉአቸው። በቤርያ ያሉት አይሁድ በተሰሎንቄ ካሉት አይሁድ በተሻለ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቃል በመቀበል አመኑ። ብዙዎች አረማውያንም በማመን ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ። ነገር ግን በተሰሎንቄ ያሉት አይሁድ ቅዱስ ጳውሎስ በቤርያ የእግዚአብሔርን ቃል እንዳበሠረ በሰሙ ጊዜ ወደ ቤርያ መጥተው ሕዝቡን በማሳደም ብጥብጥ አስነሡ። በዚህ ጊዜ ምእመናን በቶሎ መጥተው ቅዱስ ጳውሎስን ከዚያ እንዲሄድ አደረጉት። ቅዱስ ጳውሎስንም የሸኙት ሰዎች እስከ አቴና አደረሱት።። በአቴና ከተማም ከአደረጋቸው ድርጊቶች መካከል ወደ አርዮስፋጎስ መሰብሰቢያ ቦታ መጥቶ የአቴና ሰዎች ሃይማኖተኞች መሆናቸውንና ይህም እነርሱ ሳያውቁ ስለሚያ መልኩት አምላክ ዘርዝሮ ያስረዳቸው መሆኑ ነው። ከዚያም ወደ ቆሮንቶስ በመሄድ ብዙዎችን አስተማረ፤ ብዙዎችንም አጠመቀ። ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን በመጣ ጊዜ ጥቂት አማኞችን አገኘ። እነርሱ ግን የተጠመቁት የዮሐንስን ጥምቀት ብቻ ስለነበረ ትክክለኛውን የጥምቀት ሥርዓት ፈጽሞ ላቸው መንፈስ ቅዱስ ወረዳባቸው። እግዚአብሔርም ታላላቅ ተአምራትን በቅዱስ ጳውሎስ እጅ ያደርግ ነበር። በዚህም መሠረት የቅዱስ ጳውሎስን አካል የነካውን ልብስና መሐረብ ወስደው በሽተኞችን ሲያስነኩአቸው ከበሽታ ቸው ይፈወሱ ነበር። ርኩሳን መናፍስትም ይወጡላቸው ነበር።

በኤፌሶን አንድ ድሜጥሮስ የሚባል ብር አንጥረኛ ሌሎች አንጠረኞችን ሰብስቦ እንዲህ አላቸው:- እንደምታውቁት ዋናው የገቢአችን ምንጭ የጣዖት ምስሎችን በመሥራት የምናገኘው ነው። አሁን ግን ይህ ጳውሎስ የሚባል ሰው ጣዖት ዋጋ እንደሌለው እያስተማረ ብዙዎችን በማሳመን ላይ ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ የእኛ የገቢ ምንጭ መቋረጡ ነው። ከዚያም ሁሉ በላይ ታላቂቱ



www.ethiopianorthodox.org

የኤፌሶን አርጤምስ ክብርዋ ሊቀነስ ነው። ይህ ታዲያ፥ እንዴት ሊሆን ይችላል በማለት የሕዝቡን ስሜት አነሣሣና ታላቅ ሁከት ሆነ። የከተማይቱ ዋና ጸሐፊ ሕዝቡን ጸጥ ባያሰኝ ኖሮ ሁናቴው ከቍጥጥር ውጪ በሆነ ነበር። ሁከቱ ጸጥ ካለና ቅዱስ ጳውሎስ ምእመናንን ሰብስቦ በምክር ቃል ካጽናናቸው በኋላ ተሰናብቶአቸው ወደ መቄዶንያ ሄደ። ከእርሱም ጋር ሱሲ. ጳጥሮስ ከቤርያ፥ አርስጥሮኮስና ሲኮንዱስ ከተሰሎንቄ፥ ጋይዮስ ከደርቤ፥ ቲኪቆስ ጥሮፊሞስ ከእስያ፥ ጢሞቴዎስም አብረው ሄዱ። እነርሱም ቀድመው ሄደው በጢሮአዳ ጠበቁት። በጢሮአዳም ሰባት ቀን ከቈየ በኋላ ለመሄድ አንድ ቀን ሲቀረው ለተሰበሰቡት ምእመናን ያደረገውን ንግግር እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ አስረዘመ። ንግግሩንም በማስረዘሙ ኤውጢኮስ የተባለ በመስኮት ላይ የተቀመጠ አንድ ወጣት እንቅልፍ ስላሸነፈው ከሦስተኛ ፎቅ ወድቆ ሞተ።



ሐዋርያው ጳውሎስ በጢሮአዳ ከፎቅ ላይ ወድቆ የሞተውን ሰው በጸሎት እንዳስነሣው

( የሐ: ሥ ም 20 ቍ 7–12)

ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ ወርዶ ዐቀፈውና ነፍሱ ተመለሰች። ከጢሮአዳም ወደ ሚሊጢ ሄደ። ከዚያ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ወሰነ። ይሁን እንጂ በኢየሩሳሌም ችግር እንደሚደርስበት መንፈስ ቅዱስ ቢነግረውና ነቢያትም ቢያስጠነቅቁት እምቢ ብሎ ጉዞውን ወደ ኢየሩሳሌም ቀጠለ።

<u>ወደ ኤፌሶን ሰዎች የተላከ መልእክት:-</u> ይህ መልእክት ሐዋርያው ቅዱስ
ጳውሎስ በሮም ታስሮ በነበረ ጊዜ ከጻፋቸው መልእክቶች አንዱ እንደሆነ
ይታመናል። ለዚህም የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት:-

«እንግዲህ በጌታ ምክንያት እስረኛ የሆንሁ እኔ ለተጠራችሁበት ጥሪ ተገቢ
የሆነ ሕይወት ይኑራችሁ ብዬ እለምናችኋለሁ» (ኤፌ 4÷1)።

«የወንጌልን ምሥጢር ያለ ፍርሃት እንድገልጥ በምናገርበት ጊዜ አስፈ
ላጊውን ቃል እንዲሰጠኝ ለእኔም ጸልዩልኝ። አሁን እንኳ ታስሬ ሳለሁ የዚህ
ወንጌል አምባሳደር ነኝ፤ ስለዚህ እንደሚገባኝ ያለ ፍርሃት እንድናገር ጸል
ዩልኝ» (ኤፌ:ም:6ቍ:19–20)።

የኤፌሶን ሰዎችም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በብዙ ድካም ወደ እግዚአ
ብሔር እንዲመለሱ እስከ አደረጋቸው ጊዜ ድረስ በጣዖት አምልኮ፥ በጥን
ቈላና በሌሎችም ክፉ ሥራዎች ሁሉ የተበከሉ ነበሩ። ስለዚህም በምዕራፍ
4ቍ:22: ላይ:- «አታልሎ ወደ ኃጢአት በሚመራ ምኞት የተበላሸውን፥
አስቀድሞ ትኖሩበት የነበረውን፥ አሮጌውን ሰውነት አስወግዱ» ብሏቸዋል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን ያስተማረው ትምህርት ምን ዐይነት
ውጤት እንዳመጣ የሚገልጠውን ማስረጃ ቀጥለን እንመልከት።

«ከአማኞች ብዙዎቹ ክፉ ሥራቸውን በግልጥ እየተናዘዙ ይመጡ ነበር።
ብዙ አስማተኞችም የአስማት መጽሐፎቻቸውን ሰብስበው በሕዝቡ ሁሉ ፊት
አቃጠሉአቸው፤ የመጻሕፍቱም ዋጋ ሲተመን ኀምሳ ሺህ ጥሬ ብር ሆኖ ተገኘ»
(የሐ:ሥ:ም:19ቍ:18–19)።

ኤፌሶን የምትባለዋ አገር በእስያ ውስጥ የሮም ቅኝ ግዛትና በአግያን ባሕር
አጠገብ የንግድ መናኸሪያ ነበረች። በዚያም አርጤምስ የተባለች ጣዖት
ነበረች። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ብዙ ተቃውሞ የደረሰበት በአርጤምስ
ጣዖት ምክንያት ነው።

ወደ ኤፌሶን ሰዎች የተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት
ስድስት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን በአጠቃላይ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች
ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ ሦስት ድረስ ስለመሠረተ
እምነትና በክርስቶስ ደም ስለመዳን ገለጻዎች ቀረበውበታል።

እግዚአብሔር በልጁ ደም ዋጅቶን ልጆቹ እንድንሆን አስቀድሞ የወሰነልን
መሆኑን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ገለጠላቸው። ይኸውም
ቅዱሳንና ነቀፋ የሌለብን ሆነን በፊቱ እንድንገኝ ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ
ስለመረጠን ነው ብሎአል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው እኛ እግዚአ
ብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካም ነገር እንድንሠራ በኢየሱስ ክርስቶስ
አማካይነት እንደገና የተፈጠርን የእግዚአብሔር ፍጡሮች ነን።



www.ethiopianorthodox.org

ለተመለሱ ምእመናን የቀድሞውንና አሁን ያሉበትን ሁኔታ በማነጻጸር እንዲህ
ብሎ ጽፎላቸዋል።

«ስለዚህ በሰውነታቸው በሰው እጅ የተደረገ መገረዝ «የተገረዝን ነን»
የሚሉት ወገኖች ቀድሞ በትውልድ አረማውያን የነበራችሁትን እናንተን
«ያልተገረዙ» ይሉአችሁ እንደነበረ አስታውሱ። የእስራኤልን ዜግነት አጥታ
ችሁ ለተስፋው ቃል ኪዳን እንግዶች ሆናችሁ፥ በዚህ ዓለምም ተስፋ አጥታ
ችሁና ከእግዚአብሔር ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ። አሁን ግን
እናንተ ከዚህ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁት በኢየሱስ ክርስቶስ ሆናችሁ በእርሱ
ደም ቀርባችኋል። ለያይቶን የነበረውን የጥል ግድግዳ ያፈረሰና አይሁድንና
አረማውያንን አንድ ያደረገ ሰላማችን ክርስቶስ ነው። ከሁለቱ ሕዝቦች ከእርሱ
ጋር የሚተባበር አንድ አዲስ ሕዝብ ለመፍጠር የሕግን ትእዛዞችና ደንቦች
በሥጋው ሽሮ ሰላምን አደረገ። በመስቀል ላይ በመሞትም ጠላትነትን
አስወገደ፤ ሁለቱንም አንድ አካል አድርጎ ከእግዚአብሔር ጋር አስታ
ረቃቸው። መጥቶም ለእናንተ ርቃችሁ ለነበራችሁትና ቀርበው ለነበሩት ለአ
ይሁድ የሰላምን የምሥራች ቃል ሰበከ» (ኤፌ:ም:2ቍ:11–17)።

እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አረማውያን ለነበሩና ወደ ክርስትና
ለተዛወሩ ምእመናን እንደገለጠላቸው ባለፉት ዘመናት ያልተገለጠ ምሥጢር
ለእርሱና ለሌሎቹ ሐዋርያት እግዚአብሔር የገለጠላቸው መሆኑን ዘርዝሮ
ጽፎላቸዋል። ይህም ምሥጢር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው አረማ
ውያን ከአይሁድ እኩል በክርስትናው ዓለም ተቀባይነት ያላቸው መሆኑ ነው።
ይህም ማለት በክርስቶስ እስካመነ ድረስ ከዚያ በፊት አይሁዳዊ ወይም አረማዊ
የነበረ መሆኑ ልዩነትን አያመጣም ማለት ነው። ክርስቶስ የሁሉም ነው፤
ለሁሉም ነው።

ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከምዕራፍ አራት እስከ ምዕራፍ ስድስት ድረስ
ሲሆን በዚህም ውስጥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ምእመናን ምን
ማድረግ እንደሚገባቸውና ከምን ዐይነት ድርጊት መገታት እንዳለባቸው
ዘርዝሮ ያስረዳቸዋል።

ቀደም ብሎም ያቀረበው የመሠረተ እምነት ውጤት ምን መሆን እንደሚ
ገባው በዝርዝር አመልክቶአል።

በምዕራፍ 4 ከቍጥር 1 እስከ 16 በእግዚአብሔር የተመረጡት ወገኖች
ለተመራጭነታቸው ብቁዎች መሆን እንዳለባቸው ያመለክታል። ይህንንም
የሚያሳስባቸው ለተጠራችሁበት ጥሪ ተገቢ የሆነ ሕይወት ይኑራችሁ ብዬ
እለምናችኋለሁ፤ በፍቅር እርስ በርሳችሁ እየተረዳዳችሁ ዘወትር በትሕትና፥
በገርነትና በትእዕግሥት ኑሩ በማለት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንዳን
ዶቹ ሐዋርያት፥ አንዳንዶቹ ነቢያት፥ አንዳንዶቹ የወንጌል ሰባኪዎች፥ አንዳ

ንዶቹ የምእመናን እረኞች፥ አንዳንዶቹ አስተማሪዎች እንዲሆኑ ስጦታዎችን የሰጠው የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ፥ ምእመናንን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ለማዘጋጀት ነው ብሎአል።

በምዕራፍ 4ቍ:17 እስከ ም:5 ቍጥር 2 ድረስ የቀድሞ አኗኗራቸውን እንዲተዉ እንጂ እንዳይመለሱበት ተነግሮአቸዋል። አረማውያን የኀፍረት ስሜታቸው ስለጠፋ ርኵሰቶችን ሁሉ ለመፈጸም ራሳቸውን ለሥጋዊ ስሜት ምኞታቸው አሳልፈው የሰጡ በመሆናቸው እንደ እነርሱ አትኑሩ ብዬ በጌታችን ስም አስጠነቅቃችኋለሁ ብሎአቸዋል። የሰጣቸውም መመሪያ እንደሚከተለው ነው።

«ውሸት አትናገሩ፤ ሁላችንም የአንድ አካል ክፍሎች ስለሆንን እርስ በርሳችን እውነት እንናገር። ምንም ያኽል ብትቈጡ ኃጢአት አትሥሩ፤ ቍጣችሁም ሳይወገድ ፀሐይ አይጥለቅባችሁ፤ ለዲያብሎስም ስፍራ አትስጡት፤ ይሰርቅ የነበረ ከእንግዲህ ወዲህ አይስረቅ፤ ... ከቶ ከአፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ፤ ነገር ግን ለሚሰሙት ጸጋን የሚሰጥና ለማነጽ የሚጠቅም፥ ለሰዎችም አስፈላጊ የሆነውን ቃል ተናገሩ፤ ለምትዋጁበት ቀን መያዣ እንዲሆናችሁ የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ። መራራነት፥ ንዴት፥ ቍጣ፥ ጩኸት፥ ስድብና ማናቸውም ዐይነት ክፋት ሁሉ ከእናንተ ወዲያ ይራቅ፤ (ኤፌ:ም:4ቍ:25–31)።

ከምዕራፍ 5 ቍ:3 እስከ ቍ:20 ድረስ ክርስቲያናዊ በጎ ተግባር ምን ዐይነት እንደሆነ የሚያስተምር ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ ካቀረባቸው ትምህርቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«እንደዚህ ዐይነቱ ነገር ለክርስቲያኖች ስለማይስማማ፥ ዝሙት ወይም ማናቸውም ዐይነት ርኵሰት ወይም ንፍገት ማድረግ ይቅርና ወሬው እንኳ ሊሰማባችሁ አይገባም። ይልቅስ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅርቡ እንጂ የሚያሳፍርና ረብ የሌለው ወይም ጸያፍ ነገር መናገር አይገባችሁም፤ እንዲህ ያለ ነገር ለእናንተ ተስማሚ አይደለም። አመንዝራም ቢሆን፥ ማናቸውንም የርኵሰት ሥራ የሚያደርግ፥ ወይም ጣዖት አምላኪ የሆነ ንፉግም ቢሆን በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት እንደማይኖረው ዕወቁ።... የደግነት ሁሉ፥ የጽድቅና የእውነት ፍሬ የሚገኘው ከብርሃን ነው፤ ስለዚህ ጌታን ደስ የሚያሰኘው ምን እንደሆነ መርምሩ። ወደ ብርሃን አውጥታችሁ አጋልጡት እንጂ ፍሬቢስ ከሆነ ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ» (ም:5 ቍ: 3–11)።

እንዲሁም በወይን ጠጅ እንዳይሰክሩ የሚመክረው ወደ ጥፋት የሚመራ ስለሆነ ነው። በመዝሙርና በውዳሴ እርስ በርሳቸው እንዲነጋገሩና እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑት መክሮአቸዋል።



ከም: 5ቍ:21 እስከ ም:6ቍ:9 ድረስ በፍቅርና በመከባበር የመኖርን ትምህርት አስተምሮአል።

አንዱ ለሌላው እንዲታዘዝ ዐደራ ከማለቱም በላይ ወደ ዝርዝር ሁኔታ ገብቶ ሚስት ለባልዋ እንድትታዘዝ፥ ባል ደግሞ ልክ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በወደዳት ዐይነት ሚስቱን እንዲወድድ መክሮአል። ለዚህም የሰጠው መንፈሳዊ ምክንያት ባልና ሚስት አንድ አካል ስለሆኑ ባልም ሚስቱን በሚወድድበት ጊዜ የገዛ ራሱን ይወድዳል ማለት ነው። የገዛ ራሱንም የሚጠላ ስለሌለ ሚስቱን መውደድ አዲስ ነገር መሆን የለበትም።

ልጆችን ሲያዝዝ ደግሞ አባትህንና እናትህን ብታከብር ሁሉ ነገር ይሰምርልሃል፤ ዕድሜህም ይረዝማል ብሎአል። ከዚህም በማያያዝ ወላጆችን ሲመክር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሥነ ሥርዓት አሳድጓቸው እንጂ ልጆቻችሁን በማስቈጣት አታስመርሩአቸው ብሎአል።

አገልጋዮችን ደግሞ ሰውን ሳይሆን ጌታን እንደምታገለግሉ አድርጋችሁ በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑት በልባችሁ ቅንነት ታዘዙላቸው ብሎአቸዋል። እንዲሁም ለጌቶቹ ለሰው ፊት የማያዳላ የእናንተና የእነርሱ ጌታ በሰማይ እንዳለ በማስታወስ ዛቻችሁን ትታችሁ ለአገልጋዮቻችሁ መልካም አድርጉላቸው ብሎአቸዋል።

በምዕራፍ 6 ከቍ:10 እስከ 20 ደግሞ ኃጢአትንና ርኩስ መንፈስን ለመዋጋት የእግዚአብሔርን የጦር መሣሪያ ልበሱ ብሎ መክሮአቸዋል። እነዚህንም ቃላት በሚከተለው ሁኔቴ አቅርቦአቸዋል:-

«በቀረውስ በጌታና በእርሱም ታላቅ ኀይል በርቱ፤ የዲያብሎስን የተንኰል ሥራ መቃወም እንድትችሉ የእግዚብሔርን የጦር መሣሪያ በሙሉ ልበሱ። የእኛ ውጊያ ከሰዎች ጋር ሳይሆን በዚህ በጨለማ ዘመን ከሚሠሩት ገዥዎች፥ ከባለ ሥልጣኖችና ከዓለም ኀይሎች፥ ይህም ማለት በሰማይ ካሉት ክርኩሳን መናፍስት ሠራዊት ጋር ነው። ስለዚህ በክፉ ቀን የጠላትን ኀይል ለመቋቋም እንድትችሉና ሁሉንም ፈጽማችሁ ጸንታችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር መሣሪያ አንሡ።

እንግዲህ እውነትን እንደ ዝናር በወገባችሁ ታጥቃችሁ፥ ጽድቅን እንደ ጥሩር ለብሳችሁ፥ ለእግራችሁ ጫማ እንደምታድርጉ የሰላምን ወንጌል ለማብሠር የሚያዘጋጃችሁን ነገር ሁሉ በማድረግ ጸንታችሁ ቁሙ።

ከዚህም ሁሉ በላይ እንደ እሳት የሚንበለበሉትን የዲያብሎስን ፍላጻዎች ሁሉ ማጥፋት የምትችሉበትን እምነት እንደ ጋሻ አንሡ» (ኤፌ:ም: 6ቍ : 10–16)።



www.ethiopianorthodox.org

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

የእስራኤል ልጆች ቀይ ባሕርን ከተሻገሩ በኋላ ሦስት ቀኖች ሲጓዙ ውሃ አላገኙም ነበር። ከሦስት ቀን በኋላ ማራ ወደተባለ ቦታ ሲደርሱ ውሃ አገኙ። ይሁን እንጂ ያ ያገኙት ውሃ መራራ ስለነበረ ሊጠጡት ባለመቻላቸው ማጉረምረም ጀመሩ። ይህም የሆነው የእነርሱን የእምነት ጥንካሬ ለመፈተን ነው። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር በጸለየ ጊዜ እግዚአብሔር ለሙሴ አንድ እንጨት አሳየውና ያን እንጨት በውሃው ላይ በጣለው ጊዜ ውሃው ጣፈጠና ሊጠጡት ቻሉ። እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባን ውሃውን ያጣፈጠው የእግዚአብሔር ኀይል እንጂ አንድ እንጨት አለመሆኑ ነው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር በቃሉ ማድረግ ቢችል በቁሳዊ ነገሮች ላይ ኀይሉን የሚገልጥባቸው ወቅቶች አሉ። ለምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዕውሩን ዐይን በቃሉ ለመፈወስ የሚችል ሲሆን በምራቁ ዐፈሩን ጭቃ አድርጎ የዕውሩን ዐይን በመቀባት ፈውሶታል (ዮሐ: ም:9ቍ:6)። እዚህም እንደምናስተውለው የዕውሩን ዐይን የፈወሰው አምላካዊ ኀይሉ ነው እንጂ ዐፈሩ ወይም ጭቃው አይደለም (ዘጸ:ም:15ቍ:22–25)።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እንደገመቱት እስራኤላውያን ከምድረ ግብጽ በወጡ ጊዜ ለረዥም ጊዜ የሚበቃ ምግብ ይዘው ወጥተው ነበር። በሙሴና በአሮን ላይ በምድረ በዳ በረሀብ ልትገድሉን አወጣችሁን ብለው ከግብጽ በወጡ በሁለት ተኩል ወራቸው ማጉረምረም የጀመሩት በዚህ ምክንያት ነው። ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ ሁለት በደሎችን ፈጽመዋል። የመጀመሪያው በደል በታላቅ ኀይሉና በአስደናቂ ተአምራቱ ከግብጽ የባርነት ኑሮ ያስወጣቸውን እግዚአብሔርን ክደውና ምስጋናቢስ ሆነው ያን ሁሉ ድርጊት ለሙሴና ለአሮን መስጠታቸው ሲሆን ሁለተኛው በደል ደግሞ በእሳትና በደመና ዐምድ እየመራና አስፈላጊውን ነገር ሁሉ እያደረገ በሚንከባከባቸው አምላክ በማመን ፈንታ በበረሓ ውስጥ በረሀብ ልንሞት ነው ብለው ማሰባቸው ነው። ሆኖም እግዚአብሔር አምላክ ለፍጥረቱ እንደ ወላጅ አባት ስለሆነ ለበረሓው ጉዞአቸው ያቀደውን የሰማይ መናንና ድርጭቶችን አዘነበላቸው እንጂ በበደላቸው ምክንያት አላስቀረባቸውም (ዘጸ:ም:16)።

እስራኤላውያን በበረሓው ጉዞአቸው ቃዴስ ወደ ተባለው ቦታ በደረሱ ጊዜ ውሃ ስላልነበረ እንደገና በሙሴ ላይ አጕረመረሙ። እግዚአብሔርም ሙሴን ተአምራት በሚያደርግበት በትር አመካይነት ከአለት ላይ ውሃ እንዲያወጣ ነገረው። ይህ ታሪክ ግን በበለጠ ተብራርቶ የሚገኘው በኦሪት ዘኍልቍ: ም: 20 ቍ: 1–13 ላይ ነው። በዚህኛው ክፍል እንደተገለጠው ሙሴንና አሮንን እግዚአብሔር እንደተቈጣባቸውና ወደ ተስፋ ምድር ከመግባት እንደተከለከሉ ተገልጦአል። የተለያዩ ምሁራን ስለሙሴና አሮን መቀጣት የተለያዩ ምክንያቶችን አቅርበዋል። ነገር ግን ሁሉም ካቀረቡአቸው ምክንያቶች መካከል ዋነኛ ምክንያት ሆኖ የቀረበው ሙሴ አለቱን ከመምታቱ በፊት እስራኤላውያንን የተናገራቸው የቍጣ ቃል ነው። ይህም፦ «እናንተ ዐመፀኞች ከዚህ አለት ውሃ እናውጣላችሁን?» የሚለው የትዕቢት አነጋገር ነው። በዚህ አነጋገሩ ውሃውን የሚያወጣው በእግዚአብሔር ኀይል መሆኑ ቀርቶ በራሱ ኀይልና ችሎታ እንደሆነ አድርጎ ስላቀረበ ለክብሩ ቀናተኛ የሆነው አምላክ ቀጣው።

ሙሴ የቃል ኪዳኑን ጽላት ከእግዚአብሔር ለመቀበል ወደ ሲና ተራራ ላይ ወጥቶ እስኪመለስ ድረስ እስራኤላውያን የጥጃ ጣዖትን ሠርተው ሰገዱለት። በዚህ ጉዳይ እግዚአብሔር በጣም ተቈጥቶ ሳጥፋቸው ባለ ጊዜ ሙሴ አማላጅ ስለሆነላቸው ይቅርታ አድርጎላቸዋል። ይህም ሁኔታ የእግዚአብሔር ሰዎች አማላጅነት ምን ያህል እውነት እንደ ሆነ ያስተምረናል። ሙሴ በበኩሉ ግን በሌዋውያን አማካይነት ሦስት ሺህ ሰዎች እንዲገደሉ አድርጓል።

ከዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች አንዳንድ ሰው በድምሩ ዐሥራ ሁለት ሰዎች ተመርጠው የከነዓንን ምድር እንዲሰልሉ ተልከው ነበር። ከተላኩት ዐሥራ ሁለት ሰዎች ኢያሱና ካሌብ ብቻ የሚያበረታታ ዘገባ ሲያቀርቡ ሌሎቹ ዐሥሩ መልእክተኞች ግን እስራኤላውያንን የሚያስፈራራ ወሬ ተናገሩ። በዚህ ጊዜ ሁሉም በፍርሀት ተዋጡ። እንዲያውም መሪ መርጠን ወደ ግብጽ እንመለስ ተባባሉ። እግዚአብሔር ግብጾችን ቀጥቶ ከባርነት ቀንበር ነጻ ያወጣቸው፥ ቀይ ባሕርን ለሁለት ከፍሎ በደረቅ መሬት ላይ ያሳለፋቸው፥ እንዳይራቡ መናንና ድርጭትን የሰጣቸው፥ እንዳይጠሙ ከአለት ውሃን ያፈለቀላቸው በማርና በወተት የበለጸገችውን ምድር ሊያወርሳቸው ዐቅዶ መሆኑን እያወቁ በዐሥሩ የሰላዮች ማስፈራሪያ ተመርተው ወደ ግብጽ ለመመለስ ማቀዳቸው ምን ያኽል አንገተ ደንዳኖች መሆናቸውን ያመለክታል። እግዚአብሔርም በዚህ ምክንያት በዚያን ጊዜ ከኻያ ዓመት ዕድሜ በላይ የነበረው ሰው ሁሉ ከኢያሱና ከካሌብ በቀር በበረሌ ውስጥ ሞቶ እንደሚያልቅ እንጂ አንድም ሰው ወደዚያች ምድር እንደማይገባ ወሰነ።

ከሌዊ ነገድ የቀዓት ጕሣ የሆነው ቆሬ፥ ከሮቤል ነገድ ዳታንና አቤሮን የእግዚአብሔርን የአምልኮ ሥነ ሥርዓት በተለየም የዕጣንን ሥርዓት አፍርሰው በራሳቸው ሥርዓት ስለተመሩ እነርሱንና ደጋፊዎቻቸውን ሁሉ እግዚአብሔር በሞት ቀሥፎአቸዋል።

እንደገናም እስራኤላውያን በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ ክፉ ነገር በመናገር ማጉረምረም በጀመሩ ጊዜ ተናዳፊ እባብ ልኮባቸው ብዙዎቻቸው በእባብ እየተነደፉ ሞቱ። አጥፍተናል ብለው በተናዘዙ ጊዜ ግን በክርስቶስ መስቀል የተመሰለውን የነሐስ እባብ እየተመለከቱ ድነዋል።

ከኦሪት ዘጸአት ጀምሮ እስከ መሳፍንት መጽሐፍ ድረስና በሌሎቹም በተለያዩ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ እንደሚነበበው የእስራኤል ልጆች በተመቻቸው ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕግጋትና ትእዛዛት በማፍረስ ኃጢአት ይሠሩ እንደነበረ ተመልክቶአል። ኃጢአት በሚሠሩበት ጊዜ እግዚአብሔር በተለያዩ ቅጣቶች ይቀጣቸውና በኃጢአታቸው ተጸጽተው የእግዚአ





www.ethiopianorthodox.org

ብሔርን ይቅርታ ሲለምኑ ደግሞ ይቅርታ ያደርግላቸው ነበር። እግዚአብሔርም እስራኤላውያንን ከሚቀጣባቸው የቅጣት ዐይነቶች አንዱ በጠላቶቻቸው ተሸንፈው መማረክ ነበር። በዚህም መሠረት የእስራኤል ልጆች በናቡከደነፆር ጊዜ ተማርከው ወደ ፋርስ መወሰዳቸው ይታወሳል።

በፋርስ ንጉሥ በአርጤክስስ ዘመን በዋና ከተማዋ በሱሳ ከሚኖሩት ምርኮኞች መካከል ከብንያም ነገድ የሆነ መርዶክዮስ የተባለው አይሁዳዊና እንደ ልጁ ያሳደጋት አስቴር የተባለችው የአጎቱ ልጅ ይገኙበታል። በዚያን ጊዜ እስራኤላውያን ጭቈና በዝቶባቸው ወደ አምላካቸው ስለጸለዩ፥ በተለይም ሃማ የተባለ የንጉሡ ከፍተኛ ባለሟል በጠላትነት ስለተነሣባቸው በመርዶክዮስና በአስቴር አማካይነት የመዳኛውን መንገድ አመቻቸላቸው። እግዚአብሔር ዕቅዱን በሥራ ላይ ለማዋል የተለያዩ መንገዶችን ይከተላል። በዚህም መሠረት መርዶክዮስ የዐድማውን ምሥጢር አጋልጦ የንጉሡን ሕይወት በማትረፉ ከንጉሡ ቀጥሎ ያለ ከፍተኛ የሹመት ደረጃ ተሰጠው፤ አስቴር ደግሞ ከተመረጡ ልጃገረዶች መካከል የበለጠ ተወዳጅነትን አግኝታ ወደ ንግሥትነት ደረጃ ከፍ አለች። ስለዚህ እነዚህ ሁለቱ እስራኤላውያን ለንጉሡ በነበራቸው ቅርብነት ወገኖቻቸውን ከጥፋት ማዳን ብቻ ሳይሆን የወገኖቻቸው ጠላቶች የነበሩትን ሰዎች ለመበቀል ችለዋል። ሃማም ለእስራኤል ሕዝብ ያቀደው ጥፋት በእርሱና በቤተሰቡ ላይ ደርሶአል። ኩራትና ትዕቢት ጥፋትና ውድቀትን እንደሚያስከትሉ ሃማ ሊገነዘብ አልቻለም።

«ትዕቢት ወደ ጥፋት፥ ትምክሕተኛነትም ወደ ውድቀት ያደርሳሉ» (ምሳ:ም:16ቍ:18)።

እኛ ምን ያኽል በእግዚአብሔር ላይ እምነት ሊኖረን እንደሚገባና አዳኝነቱንም ምን ያኽል በትዕግሥት መጠበቅ እንደሚገባን የዮዲት ታሪክ፥ ያስተምረናል። ድልም የሚገኘው በእግዚአብሔር እርዳታ እንጂ በድፍረትና በወታደራዊ ብቃት አለመሆኑን የምንረዳው ብዙ አገሮችን ድል አድርጎ የነበረው የናቡከደነፆር ሠራዊት በአንዲት ሴት አማካይነት በመሸነፉ ነው።

ሌላው ከዮዲት ታሪክ የምንማረው ጠቃሚ ትምህርት ደግሞ የጸሎትና የንስሓ ውጤት ምን እንደሚመስል ነው። የእስራኤል ልጆች ተስፋ በሚያስቈርጥ ሁናቴ ላይ በነበሩበት ጊዜ ወደ አምላካቸው ምርር ብለው አለቀሱ፤ ዮዲት ደግሞ ወገኖችዋን የማዳን መሣሪያ ያደርጋት ዘንድ ከልብዋ ጸለየች፤ እግዚአብሔርም የእርስዋንና የሕዝቡን ጸሎት ሰምቶ ተአምራዊ መልሱን ሰጠ።

እንዲሁም በሆሎፌርኔስ ላይ የደረሰው ውርደት በምድራዊ ኀይሉና በባዕድ አምልኮ የሚመካ ሰው እንዴት ያለ ውድቀት እንደሚደርስበት ያመለክተናል።

እዚያ ላይ ሊተኰርበት የሚገባ ዋናው ነገር የወታደሮች ብዛትና የሰዎች ጀግንነት ሳይሆን የተጨቋኞች ረዳት፥ ደካሞችን የሚያበረታ፥ ረዳት ላጡ ደጋፊና ተስፋ ያጡትን አዳኝ በሆነው የትሑታን አምላክ ላይ መተማመን



ነው። ዮዲትም ምንም እንኳ ንጹሕ በሆነና ንጹሕ ባልሆነ በሚለው በኦሪት ሥርዓት ላይ ጠንካራ አቋም ቢኖራት የእግዚአብሔርን ዓላማ በተግባር ላይ ለማዋል ግን አጠያያቂ የሆነውን ነገር ከመፈጸም አላመነታችም። እግዚአብሔርም ሊደርስ ከሚችል ነገር ጠብቋታል። ይህንንም መጽሐፍ ብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ቈጥረው ተቀብለውታል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ካደረጋቸው የተለያዩና ብዛት ያላቸው የማስተማር ተልእኮዎች የምንማረው የእግዚአብሔርን ቃል ላልሰሙ ሰዎች ለማሰማት ባለን ኀይል ሁሉ መሥራት ያለብን መሆኑን ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጣም አክራሪዎች በነበሩት በአይሁድ ምኵራብ ውስጥ እየገባ በድፍረት ስለክርስቶስ ያስተምር ነበር። በዚህም ምክንያት እስራቶች፥ ግርፋቶችና መወገር ደርሶበታል። ይህም ሁሉ ሲሆን ከማስተማር፥ ለጥያቄ መልስ ከመስጠትና መልእክቶችን ከመጻፍ አልተቈጠበም። መልእክቶቹንም ይጽፍ የነበረው ተዘዋውሮ አስተምሮአቸው ለነበሩት ምእመናን ሲሆን ይኸውም ያስተማራቸውን ትምህርቶች ለማጠናከር ብሎ ነበር። እነዚህን የማስተማር ተልእኮዎች በሚያካሄድበት ጊዜ ራሱ ሠርቶ በሚያገኘው ገቢ እንጂ በሌላ በማንም ላይ ተጽዕኖ አያደርግም ነበር። የሌት ተቀን ድካሙም የእግዚአበሔርን ቃል ላልሰሙ ወገኖች ለማዳረስ ካልሆነ በቀር ሌላ ዓላማ አልነበረውም። በዚህም ድካሙ ብዙ ወገኖችን ወደ ክርስቶስ በማምጣት ከፍተኛ የሥራ ፍሬ አሳይቶአል። የክርስቶስን ወንጌል ማስተማር ግዴታው እንደሆነ ቈጥሮ ባላስተምር ወዮልኝ ይል ነበር። ይህም አስተሳሰብ በሁላችንም ዘንድ ሊኖር የሚገባው ነው። ይኸውም ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ እንዳለው መልካም ነገር ማድረግን እያወቀ የማያደርግ ሰው አለማድረጉ ኃጢአት ይሆንበታልና»። ሌላውን ሰው የማስተማር ችሎታ እያለን ካላስተማርን እኛም ወዮልን (ያዕ:ም 4ቍ:17)።

## ጥያቄዎች

1. መራራውን ውሃ ለማጣፈጥ ሙሴ ምን አደረገ?
2. ያን እንዲያደርግ ማን ነገረው?
3. እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡ በሁለት ወር ተኩል የደረሱበት ቦታ ምን የሚባል ነበር?
4. በዚያን ጊዜ ምን አደረጉ?
5. እግዚአብሔርስ ምን አደረገላቸው?
6. እስራኤላውያን ወደ ቃዴስ በደረሱ ጊዜ በሙሴ ላይ ያጕረመረሙት በምን ምክንያት ነው?
7. እግዚአብሔር ለሙሴ ምን ነገረው?
8. ያ ቦታ ማሳህና መሪባ የተባለው በምን ምክንያት ነው? ማሳህና መሪባ ማለትስ ምን ማለት ነው?

www.ethiopianorthodox.org

9. በዚህ ጊዜ በሙሴና በአሮን ላይ ምን ደረሰባቸው?

10. ለዚህስ ምክንያቱ ምንድነው?

11. ሙሴ ወደ ሲና ተራራ ላይ የወጣው ለምንድነው?

12. በተራራው ላይ ስንት ጊዜ ቈየ?

13. ሙሴ በመዘግየቱ ሕዝቡ ምን አደረገ?

14. እግዚአብሔርስ ምን አደረገ?

15. ሙሴስ ምን አደረገ?

16. ከነዓንን ለመሰለል ሙሴ የላካቸው ሰዎች ስንት ነበሩ?

17. ከሰለላው ሲመለሱ ስንቶቻቸው ደግ ነገር አወሩ? ስንቶቻቸውስ ክፉ አወሩ?

18. ደግ ያወሩት የየትኞቹ ነገዶች ተወካዮች ነበሩ?

19. እነርሱስ እነማን ይባሉ ነበር?

20. በተወራው ወሬ ምክንያት የሕዝቡ ስሜት እንዴት ነበር?

21. ደግ ወሬ ያወሩት ሰዎች ምን አገኙ?

22. ክፉ ወሬ ያወሩትስ ምን ደረሰባቸው?

23. እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ምንን ወሰነ?

24. ቆሬ፥ ዳታን፥ አቤሮንና ኦን ምን አደረጉ?

25. ከእነርሱስ ጋር ማን ተባበረ?

26. በእነርሱና በተባባሪዎቻቸው ላይ ምን ደረሰ?

27. ሕዝቡ በሙሴና በአሮን ላይ ምን ብሎ አጕረመረመ?

28. ስንት ሰው በመቅሠፍት ሞተ?

29. መቅሠፍቱ እንዲቆም ሙሴና አሮን ምን አደረጉ?

30. ከሖር ተራራ ተነሥተው ወደ ቀይ ባሕር በሚወስደው መንገድ ሲሄዱ እስራኤላውያን ምን አደረጉ?

31. እግዚአብሔር ምን አደረገባቸው?

32. ንስሓ በመግባታቸው ምክንያት ሙሴ ምን እንዲያደርግላቸው ታዘዘ?

33. በመጽሐፈ አስቴር ስንት ምዕራፎች አሉ?

34. በመጽሐፉ ውስጥ የእግዚአብሔር ስም ያልተጠቀሰበት ምክንያት ምንድነው?

35. የእግዚአብሔር ስም ሳይጠቀስ እንዴት መጽሐፉ ተቀባይነትን ሊያገኝ ቻለ?

36. ንጉሥ አርጤክስስ ንግሥት አስጢንን የሻሩት በምን ምክንያት ነው?



37. አስቴር እንዴት ንግሥት ለመሆን ቻለች?

38. የአጐቷ ልጅ መርዶክዮስ አስቴርን ምን መከራት?

39. መርዶክዮስ በአስቴር በኩል ለንጉሡ ያስተላለፈለት መልእክት ስለምን ጉዳይ ነበር?

40. መርዶክዮስ ይህን በማድረጉ ምን አገኘ?

41. ስለ ንግሥት አስጢን የንጉሡ አማካሪዎች ምን ብለው መከሩት?

42. መርዶክዮስ እንደ ልጁ አድርጎ ያሳደገው ማንን ነው?

43. የአርጤክስስ መናገሻ ከተማ ምን ትባል ነበር?

44. አስቴር ወደ ቤተ መንግሥት የተወሰደችው አርጤክስስ በነገሠ በስንተኛው ዓመት ነው?

45. ንጉሡ ሃማ ለተባለ ሰው ምን አደረገለት?

46. ሃማ በመርዶክዮስ ላይ ለምን ተቈጣ?

47. በመቈጣቱስ ምክንያት ምን አደረገ?

48. በመርዶክዮስ ላይስ ምን ዐቅዶ ነበር?

49. የሃማ ዕቅድና ሥራ ሁሉ እንደምን ከሸፈ?

50. መርዶክዮስና አስቴር እንዴት አድርገው የአይሁድን ሕዝብ ከጥፋት አዳኑት?

51. ሃማ ለመርዶክዮስ ዐቅዶት የነበረው ዕድል ፈንታ ያጋጠመው በምን ዐይነት ነው?

52. ሃማ መዋረድ የጀመረው እምን ላይ ነው?

53. እስራኤላውያን ከሃማ ክፉ ዕቅድ የዳኑበትን ቀን ለማስታወስ የሚከበረው በዓል ምን ይባላል?

54. ናቡከደንፆር በነገሠ በስንተኛው ዓመት ነው የሜዶኑን ንጉሥ አርፋክስድን ድል ያደረገው?

55. በአካባቢው ያሉትን አገሮች ሁሉ ለማስገበር ፍላጎት ያደረበት በምን ምክንያት ነው?

56. ናቡከደነፆር እንዲገብሩለት መልእክተኞች የላከባቸው አገሮች ሁሉ እሺ ብለው ገበሩን?

57.የናቡከደንፆር የጦር አዝማች ስም ማን ነበር?

58. እስራኤላውያን ምን በሰሙ ጊዜ ነው የፈሩት?

59. የጦር መሪው ያሰለፋቸው የወታደሮች ብዛት ስንት ነበር?

60. እስራኤላውያን እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ምን አደረጉ?

61. ሆሎፎርኔስ የተናደደው መቼ ነው?



www.ethiopianorthodox.org

62. ሞአባውያንንና አሞናውያንን ምን ብሎ ጠየቃቸው?

63. የአሞናውያን መሪ የነበረው አክዮር ምን መልስ ሰጠው?

64. በአክዮር መልስ ተደሰተን?

65. አድማጮቹስ ምን አሉ?

66. ሆሎፈርኔስ አክዮርን ምን አደረገው?

67. በማግስቱ ሆሎፈርኔስ ስንት ወታደር አሰለፈ?

68. እስራኤላውያን መሪዎቻቸውን ምን አሉአቸው?

69. እነርሱስ ምን መልስ ሰጡአቸው?

70. ስለመሪዎቹ መልስ ዮዲት ምን አለች?

71. ከዚያስ በኋላ ዮዲት ምን አደረገች?

72. ዮዲት ሆሎፈርኔስን ምን አለችው?

73. ወደ እስራኤላውያን ሰፈር የተመለሰችው ምን አድርጋ ነው?

74. እስራኤላውያንንስ ምን መከረቻቸው?

75. እነርሱስ ምን አደረጉ?

76. ከሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የማስተማር ተልእኮዎች ምን እንማራለን?

77. እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡ በሁለት ተኩል ወራቸው ስለ ምግብ ማጉረምረማቸው ምንን ያመለክታል?

78. የቆሬና የጓደኞቹ ዐመፅ ምን ነበር?

79. የዮዲት ታሪክ ምንን ያስተምረናል?

80. በሆሎፈርኔስ ላይ የደረሰው ውርደት ምንን ያስተምረናል?

## ምዕራፍ 3

# ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ

## የጌታችን ትምህርቶች

ጌታችን ስለ ፍቅር ታላቅነት የሰጠው ትምህርት:- አንድ የኦሪት ሕግ መምህር ጌታችንን ሊፈትነው ፈልጎ ከሁሉ የሚበልጥ ትእዛዝ የትኛው ነው?» ብሎ ጠየቀው። ጌታችንም «እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹም ነፍስህ፥ በፍጹም አሳብህ ውደድ፤ ከሁሉ የሚበልጠውና የመጀመሪያው ይህ ነው፤ ይህንንም የሚመስለው ሁለተኛው ትእዛዝ ሰውን ሁሉ እንደራስህ አድርገህ ውደድ የሚለው ነው፤ የሙሴ ሕግና የነቢያት ትምህርት



ሁሉ የተመሠረቱት በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዞች ላይ ነው» ብሎ መልስ ሰጥቶታል (ማቴ፥22–34–40)። እንዲሁም ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ ብሎ አዝዞአቸዋል:- «እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ እኔ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ እኔ እንደወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፤ እርስ በርሳችሁ ከተዋደዳችሁ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደሆናችሁ ሰው ሁሉ ያውቃል» (ዮሐ:ም:13ቍ:34–35)።

የስድስቱን ቃላተ ወንጌል ትእዛዛትንም ባስተላለፈ ጊዜ ስለ ፍቅር ጠንክር አድርጎ ማዘዙን ቀጥለን እንመልከት:-

«ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ የሚረግሙአችሁን መርቁ፤ ለሚጠሉአችሁ በጎ አድርጉ፤ ክፉ ለሚያደርጉባችሁና ለሚያሳድዱአችሁ ጸልዩ እላችኋለሁ። ይህን ብታደርጉ በሰማይ ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆናላችሁ።.. የሚወድዱአችሁን ሰዎች ብቻ ብትወድዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ኃጢአተኞችስ ይህንኑ ያደርጉ የለምን? (ማቴ: ም:5 ቍ: 44–46)።

እንደገናም ጌታ ስለፍቅር በጣም አስፈላጊነትና ጠቃሚነት አጠናክሮ የተናገረበትን ትእዛዝ ቀጥለን እንመልከት:-

«አብ እኔን እንደወደደኝ እኔም እናንተን ወደድኋችሁ፤ ስለዚህ በፍቅሬ ኑሩ። እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደፈጸምሁና በፍቅሩ እንደምኖር እናንተም የእኔን ትእዛዝ በትፈጽሙ በፍቅሬ ትኖራላችሁ።...

የእኔ ትእዛዝ እኔ እንደወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ነው። ሰው ሕወቱን ስለወዳጁ አሳልፎ ከመስጠት የበለጠ ፍቅር የለውም» (ዮሐ:ም:15ቍ:9–13)።

ጌታችንም የፍቅርን ነገር ማዘዝና ማስተማር ብቻ ሳይሆን እርሱ ራሱም ተግባራዊ አድርጎታል። ለዚህም የራሱን አገላለጥ እንመልከት:-

«በእርሱ ያመነ ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር ዓለምን እንደዚህ አድርጎ ስለወደደው፥ አንድያ ልጁን ሰጠ» (ዮሐ:ም:3ቍ:16)።

ከሁሉ የሚበልጥ ማነው?:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ቅፍርናሆም መጥቶ ወደ ቤት ከገባ በኋላ ደቀ መዛሙርቱን በመንገድ ላይ ትከራከሩበት የነበረው ጉዳይ ምን ነበር ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱ ግን በመንገድ ላይ ሳሉ ከሁላችን የሚበልጥ ማነው እያሉ ይከራከሩ ስለነበረ ለጌታችን ጥያቄ መልስ ሳይሰጡ ዝም አሉ። ዐሥራ ሁለቱንም ጠርቶ መጀመሪያ መሆን የሚፈልግ ማናቸውም ሰው የሁሉ አገልጋይ መሆን አለበት አላቸው። አንድ ሕፃንም ጠርቶ በመካከላቸው አቆመና በእውነት እላችኋለሁ፤ ካልተወለወጣችሁና እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ በቀር ወደ መንግሥተ ሰማይ አትገቡም፤ እንደዚህ ሕፃን ራሱን ዝቅ የሚያደርግ በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ ይሆናል በማለት የትሕትናን አስፈላጊነት አስተማራቸው። ስለትሕትናም

www.ethiopianorthodox.org

አስፈላጊነት እና ጠቃሚነት በተለያዩ ጊዜዎችና ሁኔታዎች አስተምሮአል። ለምሳሌ በስቅለቱ ዋዜማ የደቀ መዛሙርቱን እግር ካጠበ በኋላ እነርሱም እርስ በርሳቸው እንደዚያ እንዲያደርጉ ነግሮአቸዋል። ሰዎችም በሚፈጽሙአቸው ተግባሮች በመኩራራት ፈንታ ያ ያደረጉት ድርጊት ከግዴታቸው አንዱ መሆኑን እንጂ የሚያስመሰግናቸው ተግባር እንዳልፈጸሙ ሊገነዘቡት እንደ ሚገባ የገለጸላቸው በሚከተለው ሁናቴ ነው:-

«አገልጋይ የታዘዘውን ስለፈጸመ ጌታው ያመሰግነው ይመስላችኋልን? እናንተም እንዲሁ የታዘዛችሁትን ሁሉ ከፈጸማችሁ በኋላ፥ የማንጠቅም አገልጋዮች ነን፤ የፈጸምነውም ግዳጃችንን ብቻ ነው በሉ» (ሉቃ: ም:17 ቍ:9–10) (ማቴ: ም:18 ቍ: 1–5፥ ማር: ም:9ቍ: 33–37፥ ሉቃ:ም: 9 ቍ: 46–48፥ ዮሐ:ም: 13ቍ: 4–15)።

<u>ስለ አባቶች ወግ</u>:- ከኢየሩሳሌም የመጡ ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ወደ ጌታችን ዘንድ ቀርበው እንዲህ ብለው ጠየቁት:- «ደቀ መዛሙርትህ እጃቸውን ሳይታጠቡ በመብላት ለምን የአባቶችን ወግ ያፈርሳሉ» አሉት። ይህንንም ያሉት የጌታችን ደቀ መዛሙርት እጃቸውን ሳይታጠቡ ምግብ መብላታቸውን ስለአዩ ነው። አይሁድ የአባቶችን ወግ በመጠበቅ እጃቸውን ሳይታጠቡ ምግብ አይበሉም ነበር። እንዲሁም ዋንጫን፥ ማሰሮን፥ ሳሕንንና አልጋን እንደማጠብ ያለ ሌላም ብዙ ወግ ይጠብቁ ነበር። ወጋቸውንም ለመጠበቅ ሲሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እስከማፍረስ ይደርሱ ነበር። በዚህም ምክንያት ጌታችን እንዲህ ሲል መለሰላቸው:-

«እናንተ ግብዞች፥ ኢሳይያስ ስለ እናንተ ይህ ሕዝብ በአፉ ብቻ ያከብረኛል እንጂ ልቡ ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤ ሰው ሠራሽ ሥርዓትን እያስተማረ በከንቱ ያመልከኛል› ብሎ የተናገረው ትንቢት ትክክል ነው፤ ስለዚህ እናንተ የእግዚ አብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ የሰውን ወግ ትጠብቃላችሁ፤ ወጋችሁን ለመጠበቅ ስትሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትተዋላችሁ። ለምሳሌ ሙሴ ‹አባትህንና እናትህን አክብር።... በአባቱ ወይም በእናቱ ላይ ክፉ የሚናገር ሰው በሞት ይቀጣ› ይላል። እናንተ ግን ‹አንድ ሰው አባቱን ወይም እናቱን በመርዳት ፈንታ ለአባቱና ለእናቱ ማድረግ የሚገባውን ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ያቀረብሁት መባ ነው› ቢላችሁ አባቱንና እናቱን ከመርዳት ነጻ ታወጡታ ላችሁ፤ በዚህም ዐይነት የራሳችሁን ወግ ለመጠበቅ ስትሉ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ፤ እንዲሁም ይህን የመሰለ ብዙ ነገር ታደርጋላችሁ» ብሎአ ቸዋል (ማር:ም:7ቍ:6–13)።

## <u>የጌታችን ተአምራት</u>

<u>የአንዲት መበለትን ልጅ ከሞት ማስነሣቱ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አንዲት ናይን ወደምትባል ከተማ ሲሄድ ሳለ ደቀ መዛሙርቱና ሌሎችም ብዙ ሰዎች ተከተሉት። እዚያም ደርሶ ወደ ከተማይቱ በር ሲገባ ሬሳ የተሸከሙ



ሰዎች ከከተማው እየወጡ ነበር። የሞተው ሰው ለእናቱ አንድ ነበር። እናቱም ባልዋ የሞተባት ሴት ነበረች። ጌታችንም ባያት ጊዜ ራራላትና «አይዞሽ አታልቅሺ› አላት። ከዚያም በኋላ ጌታችን ወደ ፊት ራመድ ብሎ ቃሬዛውን በነካ ጊዜ የተሸከሙት ሰዎች ቆሙ። እርሱም «አንተ ወጣት ተነሥ እልሃለሁ» አለ። የሞተው ሰው ቀና ብሎ ተቀመጠና መነጋገር ጀመረ። ለእናትየዋም «እነሆ ልጅሽ ብሎ ሰጣት (ሉቃ:ም:7ቍ:11–17)።

<u>ሽባውን ሰው መፈወሱ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቅርፍናሆም መጥቶ በቤት ውስጥ መሆኑ ተሰማ። ቤቱ የማይበቃ ከመሆኑም በላይ ደጁ እንኳ እስኪጠብብ ድረስ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡና ያስተምራቸው ነበር። በዚያን ጊዜ አራት ሰዎች አንድ ሽባ ሰው ተሸክመው ወደ እርሱ መጡ። ከሕዝቡም ብዛት የተነሣ ሽባውን ሰው ወደ ጌታችን ማቅረብ ቢያቅታቸው የቤቱን ጣራ እርሱ ባለበት በኩል ከፍተው ሽባውን ሰው ከነአልጋው አወረዱት። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን «ልጄ ሆይ ኃጢአትህ ተደምስሶ ልሃል» አለው። በዚያ ተቀምጠው የነበሩ አንዳንድ የሕግ መምህራን በልባ ቸው እንዲህ አሉ:- «ይህ ሰው ለምን እንዲህ ያለ ስድብ በእግዚአብሔር ላይ ይናገራል? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአትን ይቅር ማለት የሚችል ማነው? ጌታችንም የልባቸውን አሳብ በመንፈሱ ዐውቆ:- «ስለምን በልባችሁ ይህን ታስባላችሁ? ሽባውን ኃጢአትህ ይቅር ተብሎልሃል ከማለትና ተነሥ ተህ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ከማለት የትኛው ይቀላል?» አላቸው። «ነገር ግን የሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ይቅር ለማለት ሥልጣን ያለው መሆኑን እንድታውቁ ብሎ ሽባውን «ተነሥ፤ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ» አለው። ሽባውም ወዲያውኑ ተነሣና አልጋውን ተሸክሞ በሰዎቹ ሁሉ ፊት ወጣ። ስለዚህም ሰዎቹ ሁሉ ተደንቀው «እንዲህ ያለ ነገር ከቶ አይተን አናውቅም» እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ (ማር:ም:2ቍ:1–12)።



የሽባው መፈወስ (ማር 2 1–12)

www.ethiopianorthodox.org

__ሁለት ዕውራንን መፈወሱ__:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያልፍበት መንገድ ሁለት ዕውራን:- «የዳዊት ልጅ ሆይ እባክህ ማረን» እያሉ በመጮኽ ተከተሉት። ጌታችንም ወደ ቤት በገባ ጊዜ ዕውራኑ ወደ እርሱ ቀረቡ፤ ጌታችንም «እኔ ይህን ማድረግ እንደምችል ታምናላችሁን? አላቸው። እነርሱም «አዎ ጌታ ሆይ፥» ብለው መለሱ። ጌታችንም ዓይኖቻቸውን በእጁ ዳሰሰና «እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ» አላቸው። ወዲያው ዐይኖቻቸው ተከፈቱና «ስለዚህ ጉዳይ ማንም እንዳያውቅ ብሎ በጥብቅ አዘዛቸው። እነርሱ ግን ሄደው በዚያ አገር ሁሉ ስለ እርሱ ዝና አወሩ (ማቴ:ም:9ቊ:27–31)።

__ዕውርና ድዳ የነበረውን ሰው መፈወሱ__:- ጋኔን ያደረበትን አንድ ዕውርና ድዳ ሰው ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምጥተውለት ፈወሰው፤ ሰውየ ውም መናገርና ማየት ቻለ። ሕዝቡ ሁሉ ተገርመው ይህ የዳዊት ልጅ ይሆንን ብለው በሚጠያየቁበት ጊዜ ፈሪሳውያን «እርሱ ብዔልዜቡል በተባለው በአጋንንት አለቃ አማካይነት ካልሆነ በቀር አጋንንትን አያወጣም» አሉ። ጌታችንም አሳባቸውን ዐውቆ እንዲህ አላቸው:-

«አንድ መንግሥት ተከፋፍሎ እርስ በርሱ የሚጋጭ ከሆነ ያ መንግሥት ይወድቃል። እንዲሁም አንድ ከተማ ወይም አንድ ቤተሰብ እርስ በርሱ ከተለያየ ጸንቶ መኖር አይችልም። ሰይጣንም ሰይጣንን የሚያስወጣ ከሆነ እርስ በርሱ ተለያየ ማለት ነው፤ ታዲያ መንግሥቱ እንዴት ጸንቶ ሊኖር ይችላል? ደግሞም እኔ አጋንንትን የማስወጣቸው በብዔልዜቡል ከሆነ ልጆቻችሁስ በምን ያስወጡአቸዋል? ስለዚህ ልጆቻችሁ በእናንተ ላይ ይፈርዱባችኋል። እኔ አጋንንትን የማስወጣው በእግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ፥ እንግዲህ የእግዚ አብሔር መንግሥት በእናንተ ላይ መጥታለች ማለት ነው። ደግሞስ አንድ ሰው አስቀድሞ ኀይለኛውን ሳያስር ወደ ኀይለኛው ቤት ገብቶ ንብረቱን መዝረፍ እንዴት ይችላል? ኀይለኛውን ካሰረው በኋላ ግን ንብረቱን ሊዘርፍ ይችላል። ከእኔ ጋር ያልሆነ ተቃዋሚዬ ነው፤ ከእኔም ጋር የማይሰበስብ ይበትናል። ስለዚህ ሰው የሚያደርገው ማናቸውም በደል ወይም የስድብ ቃል ሁሉ ይቅር ይባልለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሰው ግን በደሉ ይቅር አይባልለትም። በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ በደሉ ይቅር ይባልለታል። በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ ግን በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም በደሉ ይቅር አይባልለትም» (ማቴ:ም: 12ቊ:25–32)።

## የጌታችን ምሳሌዎች

__ትዕቢተኛው ፈሪሳዊና ትሑቱ ቀራጭ__:- ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቃን ነን ብለው ለሚመኩና ሰውን ለሚንቁ ሰዎች የሚከተለውን ምሳሌ ተናግሮአል።

«ሁለት ሰዎች ለመጸለይ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዱ፡ አንዱ ፈሪሳዊ ሲሆን ሌላው ቀራጭ ነበር። ፈሪሳዊው ቆሞ እንዲህ ሲል በልቡ ጸለየ፡ <እግዚአ ብሔር ሆይ፥ እኔ እንደ ሌሎች ሰዎች ቀማኛና ዐመፀኛ፥ አመንዝራም ስላልሆንሁ አመሰግንሀለሁ፤ ይልቁንም እንደዚህ እንደ ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ፤ እኔ በሳመንት ሁለት ቀን እጾምለሁ፤ ከማገኘውም ሁሉ ዐሥራት እያወጣሁ እሰጣለሁ። > ቀራጩ ግን በሩቅ ቆመና፡ ቀና ብሎ ወደ ሰማይ ለማየት እንኳ አልደፈረም፤ ነገር ግን በእጁ ደረቱን እየመታ <አምላክ ሆይ፥ እኔን ኀጢአተኛውን ማረኝ› ይል ነበር። ጽድቅን አግኝቶ ወደ ቤቱ የተመለሰው ይህ ቀራጭ ነው እንጂ ፈሪሳዊው አይደለም እላችኋለሁ። ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ ይላል» (ሉቃ:ም:18ቊ:9–14)።



የትዕቢተኛው ፈሪሳዊና የትሑቱ ቀራጭ ምሳሌ ሉቃ 18 ፡9–14

__የሀብታሙ ሰው ሞኝነት__:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚከተለውን ምሳሌ ተናግሮአል:-

«እርሻው ብዙ ሰብል ያስገኘለት አንድ ሀብታም ሰው ነበር፤ እርሱም በአ ሳቡ:- ‹ይህን ሁሉ እህል የማከማችበት ስፍራ ስለሌለኝ ምን ላድርግ?› እያለ ያሰላስል ነበር። እንዲህም አለ:- ‹የማደርገው ይህ ነው፤ ጎተራዎቼን ሁሉ አፈርስና ሌሎች ትልልቅ ጎተራዎችን እሠራለሁ፤ በዚያ እህሌንና ንብረቴን ሁሉ ሰብስቤ አከማቻለሁ። ከዚህም በኋላ ራሴን:- እነሆ ለብዙ ዓመት የሚ በቃህ ብዙ ሀብት አለህ፤ እንግዲህ ዕረፍት በማድረግ ተዝናና፤ ብላ ጠጣ፥ ደስ ይበልህ እለዋለሁ› አለ። እግዚአብሔር ግን ‹አንተ ሞኝ፡ ዛሬ በዚህች

www.ethiopianorthodox.org

ሌሊት ነፍስህ ከአንተ ትወሰዳለች፤ ታዲያ ይህ ያከማቸኸው ሀብት ሁሉ ለማን ይሆናል? >አለው። ለራሱ በምድር ላይ ሀብትን የሚያከማች፥ በእግዚአብሔር ፊት ግን ድኻ የሆነ ሰው እንዲሁ ይሆናል» (ሉቃ:ም:12 ቍ: 16–21)።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

በእግዚአብሔር ሕጎች ርእስ ሥር እንደተገለጠው በጽላቱ ላይ ተቀርጸው በሲና ተራራ ላይ በሙሴ አማካይነት ከእግዚአብሔር የተሰጡት ዐሥሩ ትእዛዛት በሁለት የሚከፈሉ መሆናቸው ይታወቃል። የመጀመሪያዎቹ አራቱ ትእዛዞች የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙት ላይ የተመሠረቱ ሲሆኑ ተከታዮቹ ስድስቱ ትእዛዛት ደግሞ ሰዎች ከፍጡራን ጓደኞቻቸው ጋር ባላቸው ግንኙት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። የእግዚአብሔር ፍቅር፥ አምልኮትና አክብሮት የመጀመሪያውና መሠረታዊው ትእዛዝ ነው። እግዚአብሔርን የሚወድና ለእግዚአብሔር አክብሮት ያለው ሰው ሌሎቹን ትእዛዞች አይተላለፍም። ጌታችንም ያስተማረው ትምህርት የሚገኘው በኦሪት ዘሌዋውያን ም:19ቍ:18 እና በኦሪት ዘዳግም ም:6ቍ:5 ላይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እውነተኛ መንፈሳዊ ፍቅር ያለው ሰው አባቱንና እናቱን ያከብራል፤ ሰውን አይገድልም፤ አያመነዝርም፤ አይሰርቅም በሌላ ሰው ላይ በሐሰት አይመሰክርም፤ የሌላውን ሰው ሀብትና ንብረት ለራሱ ለማድረግ አይመኝም። ስለዚህም ነው እግዚአብሔርንና ሰውን መውደድ የሕግ መሠረቶች ናቸው፡ ወይም የኦሪትና የነቢያት ትምህርት የተመሠረቱት በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዞች ላይ ነው የተባለው። ሰውም እግዚአብሔርን የሚወድድ ከሆነ ሕጎች ሁሉ ከእግዚአብሔር የተገኙ እንደመሆናቸው ሕጎችን ያከብራል። ሰውንም የሚወድደው እግዚአብሔርን የመውደድ ምልክት ስለሆነ ነው።

ከትእዛዛት ሁሉ የትኛው ይበልጣል የሚለው ጥያቄ በብዙዎቹ የአይሁድ ምሁራን ዘንድ ሲያከራክር የኖረ ጉዳይ ነበር። እነርሱ ጌታችንን ለመፈተን ብለው ያቀረቡት ጥያቄ መፍትሔ ሊያገኙለት ያልቻሉትን ጌታችን በቀላሉ ያስገኘላቸው በመሆኑ ከመደነቅ በቀር ሌላ መልስ አልነበራቸውም።

ጌታችንም በስቅለቱ ዋዜማ ለደቀ መዛሙርቱ አዲስ ትእዛዝ ነው ብሎ የነገራቸው እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ ነው። ታዲያ እርስ በርስ መዋደድ እንዴት አዲስ ትእዛዝ ይሆናል? ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል። አዲስ የተባለበት ምክንያት እኔ እንደወደድኋችሁ አድርጋችሁ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ በማለቱ ነው። እርሱ የወደደው ሕይወቱን አሳልፎ እስከመስጠት ድረስ ስለሆነ እኛም ወዳጆቻችንን ሕይወታችንን አሳልፈን እስክንሰጥ ድረስ እንድንወድዳቸው አዝዞናል። እርሱ ሕይወቱን አሳልፎ የሰጠው ዘመድና ወዳጅ፡ ጠላትም ሳይል ለሁሉም ነው። እኛም እንደዚህ እንድናደርግ አዝዞናል። አዲስ ትእዛዝ ያለውም ይህን ነው።



ጌታችን በተራራ ላይ ስብከቱ ሰዎች ጠላት ሊሆኑን የሚችሉበትን ሦስት መንገዶች ዘርዝሮአል። እነርሱም:- 1. በጥላቻ ጠላት መሆን፥ 2. በሥሳደብ ጠላት መሆንና፥3. በማሳደድ ጠላት መሆን ናቸው። ጌታችንም እነዚህን የጠላትነት ስሜቶች በምን ዐይነት እንድንቀበላቸው ሲያገዘን ጥላቻን በፍቅር፥ ስድብን በምርቃትና በመልካም አነጋገር፥ ማሳደድን ደግሞ ለአሳዳጁ ደኅንነት በመጸለይ እንጂ በበቀል እንዳንቀበለው አዝዞናል። እርሱም ምሳሌ ሲሆንልን አይሁድ በሰቀሉት ጊዜ አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ብሎ ጸልዮላቸዋል (ሉቃ:23ቍ:34)።

እነዚህን ሦስት ትእዛዞች ለመፈጸም በዚህ በደካማው ሰውነታችን እንዴት እንችላለን ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል። ትእዛዙን ለመፈጸም የሐሳብ ቍርጠኝነት ካለና እግዚአብሔርን በጾምና በጸሎት ከለመኑት ችሎታውን ይሰጣል።

ቀደም ተብሎ በሌላ ርእስ ሥር እንደተገለጠው ጌታችን የመጨረሻውን ሕማምና ሞት ተቀብሎ ከሞት ከመነሣቱ በፊት ደቀ መዛሙርቱ እንኳ በመለኮታዊ ክብሩ አላመኑበትም ነበር። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው ከደቀ መዛሙርቱ ለጌታችን ቅርብ ናቸው ተብለው ከሚነገርላቸው መካከል የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስ በመንግሥትህ በምትመጣበት ጊዜ በቀኝ ህና በግራህ እንድንቀመጥ አድርገን ብለው መጠየቃቸውና አሁን ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ እርስ በርሳቸው እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ እያሉ መከራከራቸው ነው። ጥቂት ቀደም ብሎ ጌታችን ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት መካከል ጴጥሮስን፥ ያዕቆብንና ዮሐንስን ብቻ በማስከተል ወደ ታቦር ተራራ ላይ ወጥቶ መለኮታዊ ክብሩን ገልጦላቸው ነበር። በዚህም ምክንያት ሌሎቹ ቅናት አድሮባቸው የመበላለጥን ጉዳይ አንሥተው ተከራከሩ የሚሉ ተርጓሚዎች አሉ። ጌታችን ግን ይህን ምድራዊ አስተሳሰባቸውን ለመለወጥ ሕፃን አምጥቶ በመካከላቸው አቆመ። የእርሱ መንግሥት ማለት መንግሥተ ሰማያት እንደ ምድራዊ መንግሥት በጮሌነትና በብልጣብልጥነት የሚታደግባት ሳትሆን እንደ ሕፃን ትሑትና የዋህ በመሆን የሚታደግባት መሆኗን ገለጠላቸው።

ፈሪሳውያን በጌታችን ላይ ስሕተት የሚያገኙ እየመሰላቸው የማይፈነቅሉት ድንጋይ አልነበረም። በዚህም መሠረት እጃቸውን ሳይታጠቡ ምግብ የበሉትን የጌታችንን ደቀ መዛሙርት አይተው ለምን የሽማግሌዎችን ወግ ያፈርሳሉ ብለው ጠየቁት። እርሱም እጅን ሳይታጠቡ መብላት ማንንም እንደማያረክሰው ገለጠላቸው። ቅዱሳት መጻሕፍት፥ ልጆች ወላጆቻቸውን እንዲያከብሩና እንዲረዱ ያዘዙ ሲሆን ፈሪሳውያን ግን አንድ ልጅ ለወላጆቹ የሚሰጠውን እርዳታ የሃይማኖት ቍርባን አድርጎ ቢያቀርበው ወላጆቹን ከመርዳት ነጻ ይሆናል ብለው ራሳቸው ባወጡት ወግ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ማፍረሳቸውን ጌታችን ገለጠላቸው። ስለዚህም ነው ይህ ሕዝብ በአፉ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ ጋር አይደለም የሚለውን የነቢዩን የኢሳይያስን አባባል ጠቅሶ የገሠጻቸው።

www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርዩ ርኅሩኅ ስለሆነ በኑሮ ረዳትዋ እርሱ ብቻ የሆነው ልጅዋ ሞቶባት ስታለቅስ ባየ ጊዜ ለመበለቲቱ ራራላት። ያን የሞተውን ልጇን ከሞት አስነሥቶ በፍጹም ተስፋ ቆርጣ የነበረችውን ድኻ እንደገና ተስፋዋ እንዲመለስ አደረገ። በዚህም ድርጊቱ ለእኛ የሰጠን ትምህ ርት እኛ አንድን ችግረኛ ልንረዳው የምንችል ከሆነ እንድንረዳው እንጂ ከንፈር መምጠጥ ለችግረኛው ምንም ጠቀሜታእንደማያመጣለት ነው። ለተቸገረ ሰው የምንራራና እርሱንም ከችግሩ ለማላቀቅ ወይም ችግሩን በጥቂቱም ቢሆን ለመቀነስ የምንችል ከሆነ ያን በጎ ድርጊት ከማድረግ ይልቅ ዝም ብሎ ከንፈር እየመጠጡ መመልከት ጭካኔ እንጂ ርኅርኄ አይደለም። ስለዚህ ጌታችን በናይን ከተማ ለምትግኘው መበለት ራራላትና ልጅዋን አስነሣላት። እኛም የተቸገረን ሰው አይተን በመራራት የምንችለውን እርዳታ እንድናደርግ ያስተማረን መሆኑን እንድንገነዘብ ያስፈልጋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቅፍርናሆም መጥቶ ወደቤት በገባ ጊዜ እዚያ መኖሩ ስለተሰማ ወዲያው ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ። ያ የገባበት ቤትም የደቀ መዝሙሩ የጴጥሮስ ቤት ነው ይባላል። አራት ሰዎች አንድ ሽባ ሰው በአልጋ ተሸክመው መጡና ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ወደ ጌታችን ሊቀርቡ አልቻሉም። በዚህ ጊዜ በሽተኛውን ይዘው ወደ ቤቱ ጣራ ላይ በመውጣት ጌታችን ተቀምጦበት በነበረው አቅጣጫ ጣራውን ከፍተው በሽተኛውን ከነአልጋው አወረዱት። ይህም ከፍተኛ እምነታቸው ለበሽተኛው መዳን ምክንያት ሆኗል። በዚህም መሠረት ጌታችን እምነታቸውን አይቶ በሽተኛውን ኃጢአትህ ተደምስሶልሃል አለው። ይህም የሚያመለክተው ለሥጋ ሕመሙ ወይም ለሽባነቱ ምክንያት የነበረው ኃጢአቱ መሆኑን ነው። ስለዚህም በቅድሚያ የኃጢአቱ መደምሰስ አስፈላጊ ስለነበረ ኃጢአትህ ተደምስሶልሃል ብሎታል። ይህን በማለቱ አይሁድ ባጕረመረሙ (በልባቸው) ጊዜ ኃጢአትን ለማስተሰረይ ሥልጣን እንዳለው አረጋገጠላቸው። የሕመምተኛውንም ኃጢ አት አስቀድሞ አስተሰርዮለት ስለነበረ አሁን ደግሞ ሕመሙን በመፈወስ ተነሥና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ስላለው ተነሥቶ አልጋውን ተሸክሞ ሄደ።

ሁለት ዕውራን፥ ጌታ የዳዊት ልጅ ሆይ፥ እባክህ ማረን እያሉ ተከተሉት። እነርሱም ከዳዊት ዘር ይመጣል የተባለው ክርስቶስ መሐሪ ነው ተብሎ ሲነገር ሰምተው ነበር (መዝ.72፥13)። ጌታችንም እነርሱን ከመፈወሱ በፊት እምነታ ቸውን ፈተነ። «እኔ ይህን ማድረግ እንደምችል ታምናላችሁን?» አላቸው። እነርሱም የሚያምኑ መሆናቸውን አረጋገጡ። ይህም ጥያቄ እያንዳንዳችን ወደ እግዚአብሔር በምንጸልይበት ጊዜ ጸሎታችንን ሰምቶ እንደሚፈጽምልን ማመን እንደሚገባን ያስተምረናል። ጌታችንም የፈወሳቸው እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ በማለት ነው። ይህን ጉዳይ ለማንም እንዳይናገሩ ቢያዝዛቸውም ይህን የሚያኽል ታላቅ ተአምር ሊደብቁ ስላልቻሉ ከዚያ ወጥተው አሠራ ጩት። ለማንም እንዳይናገሩ ማዘዙ እርሱ ክርስቶስ መሆኑ ቀስ በቀስ እንጂ በአንድ ጊዜ እንዲታወቅ ስላልፈለገ ነው። አለበለዚያ ግን የእርሱ መንግሥት ምድራዊ መንግሥት መስሎአቸው አይሁድ በግድ ሊያነግሡት እንዳይፈ



ልጉና ከዚያም በላይ [illegible] ዝንባሌ ነው። በዮሐንስ ወንጌል ም:6ቊ15 ላይ:- «ሰዎቹ ግን በግድ ወስደው ሊያነግሡት እንዳሰቡ ባወቀ ጊዜ ኢየሱስ ብቻውን እንደገና ራቅ ብሎ ወደ ኮረብታ ሄደ» ተብሏል። እንደዚህ ያለውን ዝንባሌ ለመግታት የግድ ከትን ሣኤው በኋላ መንፈሳዊ መንግሥት ማቋቋም አስፈላጊ ነበር። ይህም የእርሱን ማንነትና የተልእኮውንም ምንነት በትክክል የሚያስረዳ ነበር።

ርኩስ መንፈስ በእርሱ ዐድሮ ዕውርና ድዳ ያደረገውን ሰው ሰዎች ወደ ጌታችን ባመጡት ጊዜ መድኀኒታችን ጋኔኑን አስወጣለት፤ በዐይኑ እንዲያይ አደረገው፤ በአንደበቱም እንዲናገር አደረገው። ሕዝቡ ሁሉ በተደረገው ድንቅ ነገር አድናቆታቸውን ገለጡ። ፈሪሳውያን ግን ምንም የተደረገ ተአምር የለም እንዳይሉ ሰው ሁሉ ያየ ስለሆነ ሊክዱ አልቻሉም። ስለዚህ ያላቸው ምርጫ አንድም በእርሱ ክብር ማመን፥ አለበለዚያም ሌላ ዘዴ መፈለግ ነው። እነርሱ ግን የመንፈስ ቅዱስን ወይም በሌላ አነጋገር አምላካዊውን ሥራ አክብሮና አምኖ ከመቀበል ይልቅ የጽርፈት አነጋገርን መረጡ። በዚህም መሠረት እርሱ ሰይጣንን የሚያስወጣው በሰይጣን አለቃ አማካይነት ነው አሉ። ይህም የሰይጣን አለቃ ብዔልዜቡል የሚባለው ነው። ይህ አባባል የሚሉትን ካጡና ግራ ከተጋቡ ቀናተኞች የተነገረ ከመሆኑ በቀር መሠረት ያለው አነጋገር አይደለም። የሰይጣን ዓላማ ሁሉ ጥፋት ብቻ እንደመሆኑና ይህንንም የሚያ ደርገው ሰዎችን ማደሪያ እያደረገ ስለሆነ እርሱን በትእዛዝና በተግሣፅ ከማደ ሪያው ለማስወጣት ጌታችን ከሰይጣን አለቃ ጋር ስምምነት አደረገ የሚለው የፈሪሳውያን ጽርፈት መሠረተቢስነቱ ገልጽ ነው። እንዴት ሰይጣን የጥፋት ዓላማውን ክዶ ሰውን ለማዳን (ለመፈወስ) ዓላም ከክርስቶስ ጋር ተስማማ ተብሎ ይታመናል? የእግዚአብሔር ዓላማ ድኅነት ነው፤ የሰይጣን ዓላማ ግን ጥፋት ነው። ታዲያ የልማትና የጥፋት ዓላማዎች ሊስማሙ ይችላሉን? የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰው ሁሉ ይድን ዘንድ ነው፤ የሰይጣን ፍላጎት ግን ሰው ሁሉ ይጠፋ ዘንድ ነው። ድኅነትን ወይም ልማትን ተግባራዊ ለማድረግ ጥፋትን ማስወገድ እንጂ ከጥፋት ጋር መስማማት ምክንያታዊ አሠራር ስላልሆነ አይደረግም፤ በዚህም መሠረት ጌታችን ሰይጣንን ከተቈራኘውና ማደሪያ ካደረገው ሰው ላይ የሚያላቅቀው በኀይሉና በሥልጣኑ ነው እንጂ ፈሪሳውያን እንደሚሉት ከሰይጣኖች አለቃ ከብዔልዜቡል ጋር ስምምነት በማድረግ አይደለም። ጌታችንም ይህን የፈሪሳውያንን አባባል በቀማኛና በባለቤት፥ እንዲሁም አንድ እርስ በርሱ በሚቃረን መንግሥት ወይም ቤተሰብ ምሳሌነት በማቅረብ በቂ መልስ ሰጥቶበታል። በተአምራቱ ላይ የእግዚአብሔር ኀይልና ሥልጣን እየታየ ያን ታላቅና ድንቅ ኀይል የሰይጣን ተባባሪነት ያለበት አድርጎ ማውራት በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም ምሕረት የማይ ደረግለት መሆኑን ገለጠላቸው።

በትዕቢተኛው ፈሪሳዊና በትሑቱ ቀራጭ ምሳሌ ጌታችን ሊያስተምረን የሚ ፈቅደው ትምህርት ትዕቢት ምን ያኽል ጉዳት እንዳለውና ትሕትና ደግሞ ምን ያኽል ጠቃሚ እንደሆነ ነው። በምሳሌው ላይ የተጠቀሰው ፈሪሳዊ



www.ethiopianorthodox.org

የራሱን ጽድቅ ዘርዝሮ ሲያስረዳና የሌሎችን በደለኛነት ሲዘረዝር ሁለት
ታላላቅ በደሎችን መፈጸሙ አልተስማውም። የመጀመሪያው በደል ትዕቢት
ነው ሁለተኛው በደል ደግሞ በሌላ ሰው ላይ ያለው ንቀትና ጥላቻ ነው።

ፈሪሳዊው የሚፈጽማቸውን ሃይማኖታውያን ሕጎች በመዘርዘር በሚመ
ጻደቅበት ጊዜ ራሱን ለእግዚአብሔር ባለውለታ እንደሆነ አድርጎ ከማቅረቡም
በላይ የእግዚአብሔር ትእዛዞች መፈጸም ያለባቸው ገዴታዎች እንጂ ትሩፋት
አለመሆናቸውን የተገነዘበ አይመስልም (ሉቃ: ም: 17ቍ: 10)።

እንዲሁም «ኩራትንና ትዕቢትን እጠላለሁ» የተባለውን የእግዚአብሔርን
ቃል ያስተዋለ አይመስልም (ምሳ:ም:8ቍ13)።

በሌላ በኩል ደግሞ ጌታችን በሰማይ ያሉት መልአኮቻቸው ዘወትር በሰማይ
ያለውን የአባቴን ፊት ስለሚያዩ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱንም እንዳትንቁ
ተጠንቀቁ» ይለናል (ማቴ:18÷10)። እንዲሁም ሐዋርያው ዮሐንስ ወንድ
ሙን የሚጠላ ወንጀለኛ መሆኑን ያስተምረናል (1ኛ:ዮሐ:ም:3ቍ:15)።

ፈሪሳዊው በጸለየ ጊዜ እግዚአብሔርን ያመሰገነው ስለ ጸጋውና ስለስጦ
ታዎቹ ሳይሆን እርሱ እንደመሰለው እንደ ሌሎች ሰዎች ቀማኛ፥ ዐመፀኛና
አመንዝራ ባለመሆኑ ነው። በተለየም በዚያ ቆሞ ይጸልይ የነበረውን ቀራጭ
በተመለከተ ነቀፋውን ሰነዘረ። ይህ ፈሪሳዊ ከሰው ሁሉ ተለይቶ እርሱ ብቻ
ጻድቅ እንደሆነ ተናገረ። ኀሊና የተበላሸ ከሆነ፥ ልብ ቅን ካልሆነ፥ አስተሳሰብ
ክፉ ከሆነ፥ ተግባር አሳፋሪ ከሆነ፥ አነጋገር ደግሞ በእግዚአብሔርና በሰዎች
ላይ ራስን ከፍ የማድረግ ትዕቢት እስካለበት ድረስ የጾምና ዐሥራትን
የመክፈል ጠቀሜታ ምንድነው? በእነዚህም ምክንያቶች ነው ጌታችን ከዚያ
ፈሪሳዊ ይልቅ ቀራጩ ጸድቆ ወደቤቱ እንደተመለሰ የገለጠው።

የሀብታሙ ሰው ሞኝነት በተሰኘው ምሳሌው ምንም ያኽል ንብረት ብናከ
ማችና ሀብታሞች ብንሆን በአልታሰበ ጊዜ ከዚህ ዓለም መለየታችን ስለማ
ይቀርና ከዚያም በኋላ በዚያ ሀብት ምንም ልንጠቀምበት ስለማንችል እንደዚህ
ቀሪ ለሚሆነው ምድራዊ ሀብት በጣም መጨነቅ እንደማይገባን ያስተምረናል።
ባዶ እጃችንን እንደተወለድን እንዲሁም ወደ ተፈጠርንባት ምድር ባዶ
እጃችንን እንመለሳለን። ይህም ታላቅ ክስረት ነው። ነገር ግን ትጋታችንና
ጭንቀታችን በሥራችንና በሁናቴአችን ሁሉ ለጽድቅ ሥራ ቢሆን፥ ለእግ
ዚአብሔር ስጦታዎችና ምድራዊ ሞት ሊያስቀርብን ለማይችል ሰማያዊ ለሆኑ
መንፈሳውያን በረከቶች ከሆነ በመንግሥተ ሰማይ የምንደሰትበት ዘለዓለማዊ
ድልብን አከማቸን ማለት ነው።

ይህ ብዙ ምርት ያገኘው ሀብታም ያ የተገኘው እህል የእርሱ የራሱ መሆኑን
መገመቱ ሞኝነት ነው። ያለን ሀብት ሁሉ ለጊዜው እንድንጠቀምበት ከእግዚ
አብሔር የተሰጠን ነው። ንብረትነቱ የእግዚአብሔር ነው። እኛ ከአምላካችን
በመጋቢነት ደረጃ ያለን እንጂ ሀብቱ፥ ፍሬው፥ ንብረቱ ሁሉ የእግዚአብሔር
ነው። ዝም ብሎ ለሥጋው ስለራሱ ብቻ በማሰብ ለወደፊት ብሎ ማከማቸቱ



www.ethiopianorthodox.org

ሞኝነት ነው። እንግዲህ ከዚያ በጐተራ ከተከማቸው እህል ለድኾች፥ ለእን
ግዳ፥ ለወላጅ አልባዎች፥ ባሎቻቸው ለሞቱባቸው መበለቶች ምንም አይሰ
ጥም። አስተሳሰቡን ከሁናቴው ጋር ከፍ አድርጎ ያ ትልቅ ጐተራ ለሚቀጥለው
ዓመት ያንሳል፥ ወይስ ይበዛል? እያለ መጨነቅ ሞኝነት ነው። ያለምንም
ማወላወል በዚህ ዐይነት ችግሩን እወጣዋለሁ ብሎ በቍርጠኝነት መወሰኑ
ሞኝነት ነው። እግዚአብሔር ቢፈቅድ በማለት ፈንታ የፍጡር እርግጠኛ መሆን
ሞኝነት ነው (ያዕ:ም:4ቍ:13–15)። ጊዜያችን ሁሉ በእግዚአብሔር እጅ
ነው እንጂ በእኛ እጅ አይደለም። እህሌን በጐተራ ውስጥ ከአከማቸሁ በኋላ
ራሴን ብላ፤ ጠጣ፤ ለብዙ ዓመትም የተከማቸ ሀብት ስላለህ ዐርፈህ ተደሰት
እለዋለሁ ማለቱ ሞኝነት ነው። የመደሰቻውን ጊዜ ወደፊት ማስተላለፉ ሞኝነት
ነው። በዚያን ጊዜ ሊቃጠል፥ መብረቅ ሊያጠፋው፥ ብልና ዝገት ሊያበ
ላሸው፥ ወይም ሌባ ሰብሮ ገብቶ ሊሰርቀው ይችላል። ዕረፍትና ደስታን በዕቅድ
ውስጥ ማስገባት ሞኝነት ነው፤ በብልጽግናም መካከል ብዙ ዕረፍት የሚያሳ
ጡና የሚያሳዝኑ ነገሮች ይገኛሉ። ታዲያ የእግዚአብሔር መልስ ምን ነበር?
አንተ ሞኝ በዚህች ሌሊት ነፍስህ ካንተ ትወሰዳለችና ይህ ያከማቸኸው ሀብት
ሁሉ ለማን ይሆናል? የሚል ነበር።

## ጥያቄዎች

1. የሕግ መምህሩ ከሁሉ የሚበልጥ ትእዛዝ የትኛው ነው ብሎ ጌታችንን የጠየቀው ለምንድነው?
2. ጌታችንስ ምን መለሰለት?
3. ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው አዲስ ትእዛዝ የትኛው ነው?
4. ጌታችን ከስድስቱ ቃላተ ወንጌል መካከል ስለ ፍቅር ያስተላለፈው ትእዛዝ ምን የሚል ነው?
5. ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ስለ ፍቅር ያዘዛቸው ከምን ጋር በማነጻጸር ነው?
6. ሐዋርያት የጌታችን ደቀ መዛሙርት መሆናቸው የሚታወቀው በምን ነው?
7. ጌታችን ፍቅርን እንዴት ተግባራዊ አደረገው?
8. ጌታችን ወደ ቅፍርናሆም መጥቶ ወደ ቤት በገባ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ምን ብሎ ጠየቃቸው?
9. እነርሱስ ምን መልስ ሰጡ?
10. ደቀ መዛሙርቱስ ምን ተባብለው ነበር?
11. ከዚያ በኋላስ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ምን ዐይነት ትምህርት ሰጣቸው?

12. ጌታችን በስቅለቱ ዋዜማ ለደቀ መዛሙርቱ ምን ዐይነት የትሕትና ትምህርት አስተማራቸው?

13. የታዘዝነውን ስንፈጽም ምስጋና የማንጠብቀው በምን ምክንያት ነው?

14. የጌታችን ደቀ መዛሙርት የአባቶችን ወግ ያፈርሳሉ የተባሉት በምን ምክንያት ነው?

15. ጌታችን ፈሪሳውያንን ሰው ሠራሽ ወጋቸውን ለመጠበቅ ሲሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንደሚያፈርሱ በመግለጥ የወቀሰበት ምክንያት ምን ነበር?

16. ስለናይን ከተማ የሙት ማስነሣት ተአምር ግለጥ።

17. በቤቱ ጣራ፥በኩል እንዲወርድ ተደርጎ ስለተፈወሰው ሽባ ተአምር ታሪክ ተናገር።

18. የሁለቱን ዕውራን መፈወስ ታሪክ ተናገር።

19. ዕውርና ዱዳ ስለነበረው ሰው መፈወስ ታሪክ ተናገር

20. ስለ ትዕቢተኛው ፈሪሳዊና ትሑቱ ቀራጭ ምሳሌ ተናገር።

21. ስለ ሀብታሙ ሰው ሞኝነት ምሳሌ ተናገር።

22. ዐሥሩ ትእዛዛት በስንት ይከፈላሉ?

23. አከፋፈላቸውስ በምንና በምን ነው?

24. ጌታችን እርስ በርስ መዋደድን አዲስ ትእዛዝ ያለው ለምንድነው?

25. ሰዎች ጠላት ሊሆኑ የሚችሉባቸው ሦስት መንገዶች ምን ምን ናቸው?

26. ጠላትነትን በምን ዐይነት እንድንቀበል ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያዘዘን?

27. በዚህ በደካማው ሰውነታችን ጠላትን ለመቀበል በምን መንገድ እንችላለን?

28. ደቀ መዛሙርቱ ስለመበላለጥ ጉዳይ የተከራከሩት በምን ምክንያት ነው?

29. ወደ ከፍተኛ ቦታ ለመድረስ በሚደረግ እንቅስቃሴ በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም መካከል ምን ልዩነት አለ?

30. በናይን ከተማ የመበለቲቱን ልጅ ባስነሣ ጊዜ ጌታችን የሰጠን የአርአያነት ትምህርት ምንድነው?

31. ጣራውን ከፍተው ላወረዱት ሕመምተኛ መዳን ዋና ምክንያት የሆነው ምንድነው?

32. ጌታችን ሕመምተኛውን ኃጢአትህ ተደምስሶልሃል ባለው ጊዜ አይሁድ ምን አሉ?

33. ጌታችንስ ምን መልስ ሰጣቸው?



34. ጌታችን ሁለቱን ዕውራን ከመፈወሱ በፊት እምነታቸውን እንደምን አድርጎ ፈተነ?

35. ይህስ ጥያቄ ለእኛ ምን ትምህርትን ይሰጠናል?

36. ጌታችን ዕውራኑን ከፈወሰ በኋላ ለማንም እንዳይናገሩ ያዘዛቸው በምን ምክንያት ነው:

37. ዕውርና ድዳ የሆነውና ርኩስ መንፈስ ያለበትን ሰው ጌታችን በፈወሰው ጊዜ ሰዎች ምን አሉ?

38. ፈሪሳውያንስ ምን አሉ?

39. ጌታችንስ ምን መልስ ሰጣቸው?

40. ለመልሱ የተጠቀመባቸው ሁለት ምሳሌዎች ምንና ምን ናቸው?

41. ከትዕቢተኛው ፈሪሳዊና ከትሑቱ ቀራጭ ምሳሌ ምንን እንማራለን?

42. ፈሪሳዊው እግዚአብሔርን ያመሰገነው ምን ስላደረገለት ነው?

43. የሀብታሙ ሰው ሞኝነት ምሳሌ ምንን ያስተምረናል?

44. የሀብታሙ ሰው አስተሳሰብ ለምን እንደሞኝነት ተቈጠረበት?

45. ዕረፍትና ብልጽግናን በዕቅድ ውስጥ ማስገባት እንደሞኝነት የተቈጠረው በምን ምክንያት ነው?

46. የወደፊትን ሁኔታ በእርግጠኛነት መወሰን እንደሞኝነት የተቈጠረው በምን ምክንያት ነው?

## ምዕራፍ 4

## ቤተ ክርስቲያን

### የቤተ ክርስቲያን ኀላፊነት

ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የክርስቶስ ተወካይ ሆና የምትሠራ አካል በመሆንዋ ብዙ ኀላፊነት አለባት። ክርስቶስ አካሉ ለሆነችው ለቤተ ክርስቲያን ራስዋ ነው፤ እኛም የክርስቶስ አካል ክፍሎች ነን (ኤፌ: ም:5 ቍ:30፥ ቈላ፥ ም:1 ቍ:18)።

ጌታችንም የቤተ ክርስቲያንን ኀላፊነት ሲያመለክት እንዲህ ብሏል:-

«ወንድምህ ቢበድልህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ በደሉን ንገረው፤ ቢሰማህ እንደገና ወንድምህ እንዲሆን ታርገዋለህ፤ ባይሰማህ ግን የሁለት ወይም የሦስት ሰዎች ምስክርነት ስለሚጸና፥ ሁለት ወይም ሦስት ሰዎችን ይዘህ ወደ እርሱ ሂድ። እነርሱንም አልሰማም ቢል ለቤተ ክርስቲያን ንገር፤



www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያንንም የማይሰማ ከሆነ እንደ አረመኔና ተጸጽቶ እንደማይመለስ ኀጢአተኛ ቍጠረው» (ማቴ:ም:18ቍ:15–17)።

ጉዳዩ በግልና በምስክሮች ፊት ንግግር ከተደረገበት በኋላ በመጨረሻ የሚቀርበው ለቤተ ክርስቲያን መሆኑና ከዚያ በኋላ የሚወሰድበት ቦታ አለመኖሩ፥ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ስም የክርስቶስ ተወካይ ሆና የምትሠራ መሆኑን ያመለክታል።

ቤተ ክርስቲያን ብዙ ኀላፊነት ማለት ብዙ ግዴታዎች ያሉባት መሆኑ ቢታወቅም ለጊዜው ግን ጐላ ብለው በሚታዩት በሚከተሉት የትምህርት ርእሶች ሥር ተጠቃልሎ እንዲቀርብ ተደርጎአል:-

1. ወንጌልን የማስተማር ኀላፊነት
2. የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት የማከናወን ኀላፊነት
3. የተለያዩ ሥርዓተ ጸሎቶችን የማካሄድ ኀላፊነት
4. ችግረኞችን የመርዳት ኀላፊነት
5. የአምልኮ ሥነ ሥርዓትን የመጠበቅና የማስጠበቅ ኀላፊነት

ወንጌልን የማስተማር ኀላፊነት:- ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ ዓለም ወደ ሰማያዊ ዙፋኑ ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ የሚከተሉትን መመሪያዎች ሰጥቶአቸዋል:-

«መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፤ በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም፥ በይሁዳ አገር ሁሉና እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» (የሐ:ሥ:ም:1ቍ:8)።

«ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ፤ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው የእኔ ደቀ መዛሙርት አድርጉአቸው። ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲፈጽሙ አስተምሩአቸው፤ እነሆ፥ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴ: ም:28 ቍ:19–20)።

«ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም ለሰው ሁሉ አስተምሩ» (ማር: ም:16ቍ:15)።

እንደዚህ ያለውን የጌታችንን ትእዛዝ ከተቀበሉ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ለሕይወታቸው ሳይሳሱ ወንጌልን ለአይሁድ፥ ለአረማውያንና እንዲሁም ለተለያዩ ሕዝቦች አስተምረዋል። ይህን ኀላፊነታቸውንም ለመወጣት ባደረጉት የድፍረት ተልእኮ መገረፍ፥ መሠቃየት፥ መሰደድና መገደል ደርሶባቸዋል። ኀላፊነታቸውን በተገቢው መንገድ ለመወጣት ሕይወታቸውን እንኳ እስከ መሠዋት ድረስ ስለደረሱ ይኸው የወንጌል ትምህርት እነርሱ ባስቀሩልን ቅርስ መሠረት በመላው ዓለም ተስፋፍቶ ይገኛል።

ሐዋርያትም ኀላፊነት የሚሰማቸው መሆኑን በቃልም ሆነ በተግባር ገልጠውታል። ለምሳሌ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:-



«ወንጌልን ማስተማር ግዴታዬ ስለሆነ የምመካበት ነገር አይደለም፤ እንዲያውም ወንጌልን ሳላስተምር ብቀር ወዮልኝ» (1ኛ: ቆሮ:ም:9ቍ:16)።

የምሥጢራትን ሥርዓት የማከናወን ኀላፊነት:- በሚታዩና በሚሰሙ የአገልግሎት ሥነ ሥርዓቶች አማካይነት ቤተ ክርስቲያን ለምእመናንዋ የእግዚአብሔርን ጸጋና በረከት የምታስገኝባቸው ሰባት ምሥጢራት እንዳሉ ቀደም ተብሎ ተገልጦአል።

ጥምቀት ወደ ክርስትና ሃይማኖት መግቢያ በርና መታወቂያ ከመሆኑም በላይ በጥምቀት አማካይነት ከተወረሰው ኃጢአት ነጻ እንሆናለን፤ ከግል ኃጢአታችን ይቅር እንባላለን፤ የመንፈስ ልደት እንወለዳለን፤ የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን። በውሃና በጸሎት አማካይነት ምእመናንን የማጥመቅ ኀላፊነት ያለባት ቤተ ክርስቲያን ነች።

የጥምቀትን ጸጋ ከተቀበልን በኋላ መንፈሳዊ ዕድገታችንን የሚያጠናክረውን የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ የምንቀበለው በቅብዓ ሜሮን አማካይነት ሲሆን ቤተ ክርስቲያንም ሜሮኑን የመቀባት ኀላፊነት አለባት።

የጌታችንን ሥጋና ደም ለመሳተፍ የምንችለው በኅብስቱና በወይኑ ላይ ካህናቱ በቅዳሴ ጸሎቱ አማካይነት አስፈላጊውን የጸሎት ሥርዓት ከአከናወኑ በኋላ ነው። ይህም የቤተ ክርስቲያን ኀላፊነት ነው።

ካህናትና ዲያቆናት የክህነት ማዕረጋቸውን ሊያገኙ የሚችሉት ጳጳሱ የሚመተ ክህነትን ሥርዓት ከአካሄደ በኋላ ነው። ይህም የቤተ ክርስቲያን ኀላፊነት ነው።

ምእመናን ኃጢአታቸውን ተናዝዘው ካህኑ የኃጢአት ማስተስረይን ሥርዓት የሚያከናውንላቸው አስፈላጊውን ምክርና ትእዛዝ ከሰጣቸው በኋላ ነው። ይህም አሠራር የቤተ ክርስቲያን ኀላፊነት ነው።

የባልና የሚስት የጋብቻ አንድነት የሚመሠረተው ካህናቱ አስፈላጊውን ጸሎት ከአካሄዱ በኋላ ነው። የዚህም የጋብቻ ሥርዓት ማካሄድ ኀላፊነት የቤተ ክርስቲያን ነው።

አንድ ሕመምተኛ ከሥጋ ሕመሙና ከኃጢአቱ እንዲድን የሚደረገው የቀንዲል ሥነ ሥርዓት የቤተ ክርስቲያን ኀላፊነት ነው።

ልዩ ልዩ ሥርዓተ ጸሎቶችን የማከናወን ኀላፊነት:- ከቅዳሴው ጸሎትና ከምሥጢራት ጸጋ ማስገኛ ጸሎት ሌላ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ጊዜዎችና ሁኔታዎች የምታካሂዳቸው የጸሎት ዐይነቶች አሉአት። ከእነዚህም መካከል ከእኩለ ሌሊት ጀምሮ እስከ ንጋት ድረስ የሚካሄደው የሰዓታት ጸሎት፥ እንደየሁኔታው በቀን ወይም በሌሊት በቅኔ ማኅሌት የሚካሄደው ስብሐተ እግዚአብሔር፥ የኪዳን ጸሎት፥ የነግህ ጸሎት፥ የሠርክ ጸሎት፥ ጸሎተ ፍትሐት፥ በየበዓላቱና በየአጽዋማቱ የሚካሄዱ ልዩ ልዩ የጸሎት ዐይነቶች፥ እንዲሁም ሌሎች የጸሎት ዐይነቶች በቤተ ክርስቲያን ኀላፊነት የሚከናወኑ



www.ethiopianorthodox.org

ናቸው። ምእመናንም ወደየአብያተ ክርስቲያኑ እየሄዱ በቤተ ክርስቲያን ኀላፊነት በሚካሄደው ጸሎት ውስጥ የሚችሉትን ያኽል ተሳትፎ ያደርጋሉ። ቤተ ክርስቲያን ጸሎትን ከምትመራበትና ከምታሳርግበት አንዱ መንገድ ዕጣን ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር በእስራኤል ልጆች ላይ ተቈጥቶ መቅሠፍት ባወረደባቸው ጊዜ አሮን በዕጣን አማካይነት ለሕዝቡ ማስተስረዩን በኦሪት ዘኁልቍ ም: 16ቍ:46–47 ይመለከቷል።

<u>ችግረኞችን የመርዳት ኀላፊነት</u>:- ችግረኞች በሚባልበት ጊዜ ምግብ፥ ልብስና መጠለያ ለማገኘት የሚቸገሩ ማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ መንፈሳዊ ችግርም አለ። ጌታችን እንዳረጋገጠልን «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም» (ማቴ:ም:4ቍ:4)።

ስለ ሃይማኖታቸው የማያውቁአቸው ጉዳዮች ስላሉ እንዲያውቁ ፈልገው፥ የሃይማኖትን ትምህርት ከዓለማዊ ትምህርት ጋር በማገናዘብ የሁለቱ አስተ ሳሰብ የማይስማማ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ በሐሳባቸው ላይ የሚመጣውን ጭንቀትና ጥርጣሬ ለማስወገድ ፈልገው፥ ከኃጢአት ርቀው ለመኖርና ያለፈ ውን ኃጢአታቸውን እንዴት ለማረም እንደሚችሉ ለማወቅ መላው ጠፍቶ ባቸው፥ አንድ ክርስቶስን በምናመልክና በምሥጢረ ሥላሴ በምናምን ክርስ ቲያኖች መካከል ለምን ልዩነት ሊኖር እንደቻለ ለማወቅ ፈልገው፥ ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች ከምእመናን በሚመጡበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በካህናትዋ አመካይነት ተገቢውን መልስ የመስጠት ኀላፊነት አለባት። ካህና ቱም ጥያቄ ለመመለስ፥ ለማስተማርና ምክር ለመስጠት የትምህርት ብቃት ሊኖራቸው ይገባል። ተጠያቂ ከጠያቂው የተሻለ ትምህርት ወይም አስተያየት ከሌለው በጠያቂው በኩል ትዝብትና ንቀት የሚያተርፍ ብቻ ሳይሆን መላው የጠፋበት ጠያቂ ከሃይማኖቱ ጉራ ኰብልሎ የመሄድና ለነበረበት ሃይማኖት ዋና ጠላት የመሆን ሁናቴ ይከሠታል። ካህኑ ሃይማኖቱን ከነማስረጃው ደኅና አድርጎ ማወቅ የሚገባው ከመሆኑም በላይ በጥቂትም ቢሆን የዘመናዊው ትምህርት አስተሳሰብ ቢኖረው የበለጠ ይጠቅመዋል። ምን ጊዜም ቢሆን አንድ የማያውቀው ጥያቄ ሲመጣ ለጥያቄው መልስ ለማግኘት ሰው እስኪጠይቅ ወይም መጻሕፍት እስኪያነብ ድረስ ቀጠሮ መስጠት ይገባዋል እንጂ ጠያ ቂውን መሳደብ ወይም ጥያቄውን የማይመለከት ሌላ መልስ መስጠት ተገቢ አይደለም። ማንም ሰው ሁሉን ነገር ዐውቃለሁ ብሎ ራሱን ማታለል የለበ ትም። ሁሉን ዐዋቂ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እነርሱ ከተማሩት ትምህርትና ከሚያውቁት ዕውቀት ውጪ የሆነ ትምህርት ሁሉ ክሕደት እንደሆነ አድርገው የሚያወግዙ ሰዎች ዐልፎ ዐልፎ ይገኛሉ። እንደዚህ ያሉት ሰዎች ማንነታቸውን በማያውቅ ሕዝብ ዘንድ ራሳቸውን ዐዋቂ ለማድረግ ካልሆነ በቀር ለራሳቸውም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን የሚያስገኙት ጥቅም የለም። ዓለማችን ሰፊ እንደመሆኑ ሌሎች ወገኖች የሚሉትን አይቶና ሰምቶ ከራስ ሃይማኖት ጋር በማስተያየት ለሃይማኖቱ ተገቢውን መልስ ማዘጋጀት ነው እንጂ ጥያቄ ዎች በሚመጡበት ጊዜ ከጥያቄው ጋር ግንኙት የሌለው መልስ መስጠት



ወይም ጠያቂውን መሳደብ ተገቢ አይደለም። ቤተ ክርስቲያንም እነዚህን ሁሉ ሁናቴዎች የማመቻቸት ኀላፊነት አለባት።

በሌላ በኩል ደግሞ ችግረኞች በሚባልበት ጊዜ በፍጥነት ወደ ሐሳባችን የሚመጣው ለዚህ ዓለም ኑሮ አስፈላጊ ነገሮችን ያላገኙ ወይም ያነሳቸው የሚለው አስተሳሰብ ነው። እንደዚህ ያለውን ችግረኛ የመርዳት ኀላፊነት ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ከመጀመሪያዎቹ የክርስትና ዘመናት ጀምራ ስትሠራበት ኖራለች። ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 6 ላይ ብንመለከት ቤተ ክርስቲያን ችግረኞችን ትረዳ እንደነበረ እንገነዘባለን። ቤተ ክርስቲያን ከቀድሞ ጀምራ ችግረኞችን የመርዳት ኀላፊነት እንደነበረባት የሚያስረዳን ሌላው ማስረጃ ደግሞ የሐዋርያት ትምህርት የሆነው ዲድስቅልያ ነው። ይህንንም በሚከተሉት ጥቅሶች ይመለከቷል:-

«ለድኾች የሚመጣው ገንዘብ በሥነ ሥርዓት ይከፋፈል፤ ገንዘቡ ለዕጓለ ማውታ፥ ለመበለቶች፥ ለተጨነቁ፥ ለዕንግዶችና ለችግረኞች ይከፋፈል። ኤጲስ ቆጶሳትም እንደየችግሩ አመዛዝነው ተገቢ በሆነ መንገድ (ፍትሕ) ያከፋፍሉት» (ዲድ:አን:5)።

«በአንድ ባል ጸንተው የነበሩና ባሎቻቸው የሞቱባቸው፥ በበጎ ተግባ ራቸው ብዙዎች የመሰከሩላቸው፥ ልጆቻቸውን በመልካም ሁኔታ ያሳደጉ፥ እንደ እነዚህ ያሉት መበለቶች በዐደራነት ለእኛ ከእግዚአብሔር የተሰጡን ስለሆነ ልንረዳቸው ይገባል። ኤጲስ ቆጶስ ሆይ፥ እጅህን ለእነርሱ ዘርጋ፥ የእግዚአብሔር ተወካይ እንደመሆንህም እንክብካቤ አድርግላቸው፤ ለመበ ለቶች፥ ለዕጓለ ማውታ፥ መጠጊያ ለሌላቸው፥ ለተጨቈኑና ለምእመናን ሁሉ፥ እንዲሁም እርዳታ ለሚያስፈልገው ሁሉ ትኵረት ስጥ (ዲድ:አን:19)።

<u>የአምልኮን ሥነ ሥርዓት የመጠበቅና የማስጠበቅ ኀላፊነት</u>:- ቀደም ተብሎ በተለያዩ ክፍሎች እንደተገለጠው ሥነ ሥርዓትን የማስከበር ኀላፊነት የዲያ ቆናት ድርሻ መሆኑ ታውቋአል። ይሁን እንጂ ጉዳዩ መሠረተ እምነትን የማይነካ በመሆኑ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓትን ለማስከበር የተለያዩ መንገዶችን ተከትለዋል። አንዳንዶቹ ለዚሁ ጉዳይ የሚያገለግሉ የደመወዝ ሠራተኞችን ቀጥረዋል፤ ሌሎች ምእመናን በየተራቸው ሥነ ሥርዓትን እንዲያስከብሩ አድርገዋል፤ እንዲሁም ሌሎች ደግሞ በዲያቆናት አማካይነት ሥነ ሥርዓቱ እንዲከበር አድርገዋል። በማንኛውም መንገድ ቢሆን ዋናው ነገር የአምልኮው ሥነ ሥርዓት እንዲከበር ነው። ምእመናን የቤተ ክርስቲያኑን በር ከሚገቡበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚወጡበት ጊዜ ድረስ የአምል ኮውን ሥርዓት መከተል አለባቸው። የተሰጥዎውን ዜማ የሚያውቁት ካልሆነ በቀር ዝም ብለው በዘፈቀደ መጮኽ የለባቸውም። አለበለዚያ ግን የዜማውን ምልክት ተከትሎ ለሚያዜመው ሰው መሰናክል በመሆን እንዲደናገር ያደር ጉታል። የቅዳሴው ጸሎት በሚካሄድበት ጊዜ ሌላ የድግምት ጸሎት ሲጀምሩ የቅዳሴውን ጸሎት እንደ ጸሎት አልቈጠሩትም ማለት ነው። የቅዳሴው ጸሎት ራሱ መመሪያዎች አሉት። ስግደት በሚያስፈልግበት ጊዜ ዲያቆኑ ስገዱ ብሎ



www.ethiopianorthodox.org

ያዝዛል፤ ራስን ዝቅ ማድረግ በሚያስፈልግበት ጊዜ ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ ይላል፤ ለሰላም ጸልዩ ብሎ እርስ በርሳችሁ እጅ ተነሣሡ የሚልበት ጊዜ አለ፤ እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ የሥነ ሥርዓት ትእዛዞች አሉ። በዚህ ጊዜ ምእመናኑ ከትእዛዞቹ የተለየ ድርጊት ሲያደርጉ ቢታዩ ሥነ ሥርዓት አስከ ባሪው ሊያርማቸው ይገባል።

ሌሎች የሥነ ሥርዓት ጉድለቶች ደግሞ ብዙዎቹ ምእመናን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጥሞና በሚጸልዩበት ጊዜ አንዳንድ ሰዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በመጸለይ፥ ሌሎች ደግሞ አጠገባቸው ከተቀመጠ ሰው ጋር በመነጋገር በጥሞና የሚጸልዩትን ምእመናን ኅሊና ይበታትኑባቸዋል። በዚህ ጊዜ ሥነ ሥርዓት አስከባሪው እነዚያን ሥርዓተ አልበኞች የማረም ኀላፊነት አለበት።

## የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳንና ቅዱሳት

<u>ቅዱስ ያዕቆብ የስሩግ ኤጲስቆጶስ</u>:- ቅዱስ ያዕቆብ በሶርያ፥ በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ ኵርታም በተባለ ከተማ በ451 ዓ.ም ተወለደ። ያዕቆብ እየተባሉ የሚጠሩ ሶርያውያን አባቶች ብዙዎች ስለ ሆኑ ከእነዚያ ለመለየት ይህ ያዕቆብ «የስሩግ ያዕቆብ» እየተባለ ይጠራል። ስሩግ የተሾመባት ሀገረ ስብከት ናት። የምትገኘውም በጤግሮስና በኤፍራጥስ መካከል ነው። ያዕቆብ ለአባቱና ለእናቱ አንድ ነበር። በሮሐ (በእዴሳ) የክርስትናን ትምህርት እየተማረ ዐድጓል። ያዕቆብ ክህነትን ተቀብሎ በስሩግ አውራጃ ውስጥ ሃውራ በተባለው ከተማ ያገለግል ነበር። በአገልግሎቱም እጅግ የተመሰገነ ነበር። ሀገሩ በፋርስ ወታደሮች ወረራ ምክንያት ትጨነቅ በነበረችበት ጊዜ ሕዝቡን ያበረታታቸው ነበር።

በ519 ዓ.ም የባትናይ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ተሾመ። ባትናይ የስሩግ ዋና ከተማ ናት። ቅዱስ ያዕቆብ ከኤጲስ ቆጶስነቱ በፊትና በኋላ በደረሳቸው መንፈሳውያን መዝሙሮቹ ምክንያት የመንፈስ ቅዱስ እንዚራ (ዋሽንት) የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቶታል።

ቅ/ያዕቆብ 760 ድርሳናትን ጽፎአል። አብዛኛዎቹ በቅኔ (በግጥም) ዐይነት የተዘጋጁ ናቸው። ከእነዚህ ድርስናቱ መካከል ሁለቱ በአባ ሰላማ መተርጉመ መጻሕፍት ትጋት ወደ ግእዝ ተተርጉመው ‹ግብረ ሕማማት በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ ተጽፈዋል። ሁለት ድርስናት ስለ አብርሃምና በጌታችን ቀኝ ስለ ተሰቀለው ፈያታዊ የደረሳቸው ናቸው። እነዚህም ድርስናት በየዓመቱ በሕማማት ሳምንት በዕለተ ስቅለት ዐርብ በቤተ ክርስቲያን ይነበባሉ።

ሌላው የታወቀ ድርስቱ በስሙ የሚጠራው ቅዳሴው ነው። ይህም ከዐሥራ አራቱ ቅዳሴያት 12ኛ ተራ ላይ የሚገኘው ነው። ከዚህም ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ፥ መንፈሳዊ ምክርን ያካተቱ መልእክቶች፥ መዝሙራትና የመ ሳሰሉ ጽሑፎችን በብዛት ጽፎአል። ከመልእክቶቹ ውስጥ ፀጣም አጫጭር



www.ethiopianorthodox.org

የሆኑ አራት መልእክታት ወደ ግእዝ ተተርጉመው በሃይማኖተ አበው ውስጥ ይገኛሉ (ሃይ አበ. 379–381 ገጽ)።

ቅዱስ ያዕቆብ ሰኔ 27 ቀን 521 ዓ.ም ዐርፎአል። ዕለተ ዕረፍቱም በያመቱ ሰኔ 27 ቀን በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ይታሰባል።

<u>The Oxford Dictionary of the christian church</u> edited F.L. Gross, Oxford Universty press, 1974

<u>ማርያም መግደላዊት</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከተከተሉ ቅዱሳት አንስት አንድዋ ማርያም መግደላዊት ነች። ጌታችንም ሰባት አጋንንትን አስወጥቶላታል። በጌታ ሕማማት፥ በስቅለቱ፥ በሞቱና በቀብሩ ጊዜ ሁሉ አገልግላዋለች። ከሌላዋ ማርያም ጋር በጧት ወደ መቃብሩ ቦታ በመሄድ ድንጋዩ ተንከባልሎ አንድ መልአክ ተቀምጦበት ያየችው እርስዋ ናት። ያን በማየታቸው በፈሩ ጊዜ መልአኩ፥ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንደምትፈልጉ ዐውቃለሁና አይዞአችሁ አትፍሩ፤ እርሱ ተነሥቶአል እንጂ እዚህ የለም። ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፥ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዐርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው ብሎ የላካት ማርያም መግደላዊትን ነው። የጌታችን ከሞት መነሣት ዜና በመጀመሪያ ለደቀ መዛሙርቱ ያበሠረ ችው እርስዋ ነች። ጌታችንም ካረገ በኋላ ደቀ መዛሙርቱን ማገልገልዋን ቀጥላለች። የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ተቀብላለች። በዚህም ነቢዩ ኢዩኤል እንዲህ ሲል የተናገረው ትንቢት ተፈጸሚነትን አግኝቷል:-

«ከዚህ በኋላ መንፈሴን በሰው ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፤ ወጣቶቻችሁም ራእይ ያያሉ» (ኢዩ:ም:2ቍ:28)።

ማርያም መግደላዊትም ከሐዋርያት ጋር ሆና ወንጌልን በማስተማር ብዙ ሴቶችን ወደ ክርስቶስ መልሳለች። ሴቶችን እንድታስተምርና በሴቶች ጥምቀት ጊዜ እንድትረዳ ሐዋያት የዲቁና ማዕረግ ሰጥተዋታል። በአይሁድ ዘንድ ብዙ መነቀፍና መናቅ ደርሶባታል። ደቀ መዛሙርቱንም እስከ ሕይወትዋ ፍጻሜ ድረስ እያገለገለች በሰላም ከዚህ ዓለም ተለይታለች (የሐምሌ: 28 ቀን ስንክ ሳር)።

<u>ቅዱስ ሙሴ ጸሊም</u>:- ይህ ቅዱስ ቀደም ባለው የሕይወት ዘመኑ ፀሐይን ለሚያመልኩ ሰዎች ባሪያ ነበር። የእርሱም አበላልና የሚያሰክር መጠጥ አጠጣጡ ከልክ ያለፈ ነበር። ይገድል፥ ይሰርቅና ክፉ ነገሮችን ሁሉ ያደርግ ነበር። ማንም ሊቋቋመው የማይችል ጉልበት ነበረው። አብዛኛውን ጊዜውን ያሳልፍ የነበረው ወደ ፀሐይ በመመልከትና ከፀሐይ ጋር በመነጋገር ነበር። አንቺ ፀሐይ እውነተኛው አምላክ አንቺ ከሆንሽ ግለጪልኝ፤ እንዲሁም የማላውቅህ አምላክ ሆይ፥ ማንነትህን ግለጥልኝ እያለ ይናገር ነበር። አንድ ቀን እንዲህ የሚል ድምፅ ሰማ:- «የዋዴ ነጥሩን መነኰሳት እግዚአብሔርን

ያውቃሉና እነርሱ እንዲያሳውቁህ ወደ እነርሱ ሂድ።» እርሱም ወዲያው ተነሣና ሰይፉን ታጥቆ ወደ በረሓ ሄደ። ካህኑ ቅዱስ ኢሶዞሮስ በተገናኘው ጊዜ በሁናቴው ፈራው። እርሱ ግን ስለ እግዚአብሔር እንድትነግሩኝ ነው የመ ጣሁት በማለት አበረታታው። ከዚያም ወደ ትልቁ ቅዱስ መቃርዮስ ይዞት መጣ። ቅዱስ መቃርዮስም አስተምሮ በማጥመቅ ካመነኰሰው በኋላ በበረሓ እንዲኖር አደረገው። ቅዱስ ሙሴም የተከተለው አምልኮተ እግዚአብሔር ከብዙ ቅዱሳን የላቀ ሆነ።

ሰይጣን ቀድሞ ይወድደው በነበረ ምግብና መጠጥ ይዋጋው ጀመር። ይህን ጉዳይ ለቅዱስ ኢሶዞሮስ ነገረው። እርሱም እያበረታታው የሰይጣንን ተንኰል እንደምን አድርጎ ድል እንደሚነሣ አስተማረው።

የገዳሙ ሽማግሌዎች ከተኙ በኋላ በየከፍላቸው ሄዶ የውሃ ዕቃቸውን ይወስድና ከሩቅ ቦታ በሚያመጣው ውሃ ይሞላላቸው እንደነበር ይነገራል። ከብዙ ዓመቶች ተጋድሎ በኋላ ሰይጣን ተመቀኘውና በእግሩ ላይ ቍስል እንዲወጣበት አደረገ። ይህም ቍስል ሕመምተኛ ሆኖ እንዲቀመጥ አደረገው። የሰይጣን ጦርነት መሆኑን ባወቀ ጊዜ ብሕትውናውንና አምልኮቱን አጠናከረ።

ይህንንም ያደረገው ሥጋው የተቃጠለ እንጨት እስኪመስል ድረስ ነው። እግዚአብሔር ትዕግሥቱን ተመልክቶ ከበሽታው አዳነው። የእግዚአብሔርም ጸጋ በእርሱ ላይ ወረደ።

ከዘመናትም በኋላ አምስት መቶ ወንድሞች ወደ እርሱ ተሰባስበው አባት ሆነላቸው። ቅስና ሊሾሙት መረጡትና ለሹመቱ ወደ ፓትርያርኩ በቀረበ ጊዜ ሊፈትነው ፈልጎ ማነው ይህን ጥቁር ወደ እዚህ ያመጣ ብሎ ሽግሌዎቹን ከጠየቀ በኋላ አባርሩት አለ። እርሱም ትእዛዝ አክብሮ እየወጣ አንተ ጥቁር መልካም አደረጉብህ ብሎ ራሱን በራሱ ይናገረው ጀመር። ፓትርያርኩ ግን እንደገና አስጠርቶ ሾመውና፥ ሙሴ ሆይ፥ ሁለንተናህ ነጭ ሆኗል አለው።

ወደ ትልቁ ቅዱስ መቃርዮስ ለመሄድ ከሽማግሌዎቹ ጋር ተስማማና እዚያ በደረሰ ጊዜ ቅዱስ መቃርዮስ ከእናንተ አንዱ የሰማዕትነት አክሊል እንዳለው አያለሁ አላቸው። በሰይፍ የገደለ በሰይፍ ይገደላል ተብሎ ስለተጻፈ እኔ እሆናለሁ ሲል ቅዱስ ሙሴ መልስ ሰጠ። ወደ ገዳም ተመልሶ ብዙ ሳይቈይ በርበሮች በገዳሙ ላይ ወረራ አካሄዱ። በዚህ ጊዜ በእርሱ ዘንድ ለነበሩት ወንድሞች ለመሸሽ የሚፈልግ ካለ ይሽሽ ብሎ ነገራቸው። አንተስ አባታችን ለምን አትሸሽም አሉት። እርሱ ግን እኔ ይህችን ቀን ከብዙ ዘመን ጀምሬ ስጠብቃት ነበር አላቸው። በርበሮቹ ገብተው እርሱንና ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰባት ወንድሞችን ገደሉአቸው። ከወንድሞች አንዱ ተደብቆ ሳለ የእግዚ አብሔር መልአክ በእጁ አክሊል ይዞ ሲጠብቀው በማየቱ ወጥቶ እርሱንም ገደሉት።

<u>ቅዱስ አቡሊዲስ፥ የሮም ሊቀ ጳጳስ</u>:- ቅዱስ አቡሊዲስ በሕይወት በነበረበት ዘመን በትሩፋት የሚኖር ፍጹም ሰው ነበር። ከአግዮስ ቀጥሎ ለሮማ ቤተ ክርስቲያን መንበር ተመረጠ። ጊዜውም ቀላዲያኖስ የሚባለው ዘጠነኛው



www.ethiopianorthodox.org

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መሪ በተሾመበት ዓመት ነው። እርሱም ሕዝቡን ከአረማውያን ትምህርት እንዲጠነቀቁና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት እንዲጸኑ ያስተምር ነበር። ይህም ድርጊቱ በከሐዲው በቀላውዴዎስ ቄሳር ዘንድ ተሰማ። እርሱም አስሮ በጣም ደበደበው። በመጨረሻም በእግሩ ላይ ከባድ ድንጋይ አስሮ ወደ ባሕር ውስጥ ጣለው። ይህን ያደረገው የካቲት አምስት ቀን ሲሆን የካቲት ስድስት ቀን ድንጋዩ በእግሩ እንደታሰረ በውሃው ላይ ተንሳፍፎ አንድ ምእመን አገኘው። ያም ምእመን ወደ ቤቱ ወስዶ ከፈነው። ይህም ዜና በሮማና በአካባቢዋ ሁሉ ተሰማ። እንዲሁም በቄሳር ዘንድ ተሰምቶ አስከሬኑ እንዲመጣለት ጠየቀ። ነገር ግን ያ ያገኘው ሰው ለማንም ሳያሳይ ደበቀው።

<u>ድርሰቶቹ:-</u>

«የመናፍቃን መቃወሚያ» የተሰኘ ታላቅ መጽሐፍ ደርሶአል።

– የሮሜ ሊቀ ጳጳሳት የአቡሊዲስ ቀኖናዎች ተብለው በፍትሐ ነገሥት ውስጥ የተጠቀሱ ቀኖናዎችንም ጽፎአል።

– በመጽሐፈ ሃይማኖተ አበውም የተጠቀሱ ብዙ ድርሳናት አሉት።

– ከእነዚህም ሌላ የዳንኤል ትርጓሜ፥ ስለ ሐሳዊ መሲሕና ስለ ዘመን አቈጣጠር የጻፋቸው መጻሕፍት አሉት። ( የየካቲት 6 ቀን ስንክሳር)።

## <u>የቤተ ክርስቲያን ዜማ</u>

የሕዝብ ተሰጥዎ

### <u>በግዕዝ</u>

ይ:ሕ:- ንዌድሰከ እግዚኦ አሜን

አ: ሥሉስ ቅዱስ መሐረነ፥ አ:ሥሉስ ቅዱስ መሀከነ፥ አ: ሥሉስ ቅዱስ ተሣሃለነ።

ይ:ዲ:- ተንሥኡ ለጸሎት፤

ይ:ሕ:- እግዚኦ ተሣሃለነ።

ይ:ሕ:- ሰላም ለኵልክሙ

ይ:ሕ:- ምስለ መንፈስከ

ይዲ:- ጸልዩ በእንተ ወንጌል ቅዱስ

ይ:ሕ:- ረስየነ ድልዋነ ለሰሚዐ ወንጌል ቅዱስ።

ይ:ዲ:- ምስባክ እመዝሙረ ዳዊት

ይ:ዲ:- ሃሌ ሉያ፥ ቁሙ ወአጽምዑ ወንጌል ቅዱስ ዜናሁ ለእግዚእነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ

ይ:ካ:- እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ

ይ:ሕ:- ምስለ መንፈስከ

ይ:ካ:- ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ማቴዎስ፥ ማርቆስ ሉቃስ፥ ዘሰበከ ዮሐንስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር

ይ:ሕ:- ስብሐት ለከ ክርስቶስ እግዚእየ ወአምላኪየ ኵሉ ጊዜ

ይ:ሕ:- ተፈሥሑ በእግዚአብሔር ዘረድአነ ወየብቡ ለአምላከ ያዕቆብ፥ ንሥኡ መዝሙረ ወሀቡ ከበሮ፥ መዝሙር ሐዋዝ ዘምስለ መሰንቆ

(በጾም ህየንተ ተፈሥሑ)

ይ:ሕ:- በወንጌል መራሕከነ ወበነቢያት ናዘዝከነ፤ ዘለሊከ አቅረብከነ ስብሐት ለከ።

ይ:ካ:- (እምወንጌል)

ይ:ሕ:- (ዘማቴዎስ)

ነአምን አበ ዘበአማን፤ ወነአምን ወልደ ዘበአማን፤ ወነአምን መንፈሰ ቅዱሰ ዘበአማን፤ ህልወ ሥላሴሆሙ ነአምን።

(በማርቆስ)

እሉ ኪሩቤል ወሱራፌል ያዐርጉ ሎቱ ስብሐተ እንዘ ይብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ እግዚአብሔር አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

(በሉቃስ)

መኑ ይመስለከ እምነ አማልእክት እግዚኦ አንተ ውእቱ ዘትገብር መንክረ አርአይኮሙ ለሕዝብከ ኀይለከ ወአድኀንኮሙ ለሕዝብከ በመዝራዕትከ ሖርከ ውስተ ሲኦል ወአዕረገ ዔዋ እምህየ ወጸጎከነ ምዕረ ዳግመ ግዕዛነ እስመ መጻእከ ወአድኀንከነ በእንተ ዘንቱ ንሴብሐከ ወንጸርህ ኀቤከ እንዘ ንብል ቡሩክ አንተ እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ መጻእከ ወአድኀንከነ።

(በዮሐንስ)

ቀደሚሁ ቃል ውእቱ ቃል ቃለ እግዚአብሔር ውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ ወኀደረ ላዕሌነ ወርኢነ ስብሐቲሁ ከመ ስብሐተ አሐዱ ዋሕድ ለአቡሁ ቃለ እግዚአ ብሔር ተነሥአ ወሥጋሁነ ኢ.ማሰነ



www.ethiopianorthodox.org

ይ:ዲ:- ፃኡ ንኡሰ ክርስቲያን

ይ:ዲ:- ተንሥኡ ለጸሎት

ይ:ሕ:- እግዚኦ ተሣሃለነ

ይ:ካ:- ሰላም ለኵልክሙ

ይ:ሕ:- ምስለ መንፈስከ

ይ:ዲ:- ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን አሐቲ ቅድስት ጉባኤ እንተ ሐዋርያት ርትዕት በኀበ እግዚአብሔር

ይ:ሕ:- ኪርያላይሶን

ይ:ዲ:- ተንሥኡ ለጸሎት

ይ:ሕ:- እግዚኦ ተሣሀለነ

ይ:ካ:- ሰላም ለኵልክሙ

ይ:ሕ:- ምስለ መንፈስከ

ይ:ዲ:- ጸልዩ በእንተ ዛቲ ቤተ ክርሰቲያን ቅድስት ወማኀበርነ በውስቴታ

ይ:ሕ:- ማኀበረነ ባርክ ዕቀብ በሰላም

ይ:ዲ:- ንበል ኵልነ በጥበበ እግዚአብሔር ጸሎተ ሃይማኖት

ዘሊቃውንት

ይ:ሕ:- ነአምን በአሐዱ አምላክ እግዚአብሔር አብ አኀዜ ኵሉ ገባሬ ሰማያት ወምድር ዘያስተርኢ ወዘኢ.ያስተርኢ ወነአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አብ ዋሕድ ዘህልው ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ብርሃን ዘእምብርሃን አምላክ ዘእምአምላክ ዘበአማን ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ ዘቦቱ ኵሉ ኮነ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ ወኢ.ምንትኒ ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ ዘበእንቲአነ ለሰብእ ወበእንተ መድ ኃኒትነ ወረደ እምሰማያት ተሰብአ ወተሠገወ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል ኮነ ብእሴ ወተሰቅለ በእንቲአነ በመዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ ሐመ ወሞተ ወተቀብረ ወተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት በከመ ጽሑፍ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት፤ ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት፤ ወነበረ በየማነ አቡሁ፤ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት፤ ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ፤ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ፤ ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ፤ እግዚእ ማሕየዊ፥ ዘሠ ረጸ እም አብ፥ ንስግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለ አብ ወወልድ ዘነበበ በነቢያት፥ ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት፤ ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን ወሕይወተ ዘይመድእ ለዓለመ ዓለም።

## ዘሐዋርያት

ነአምን በአሐዱ አምላክ ገባሬ ኵሉ ፍጥረት አብ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ አልቦ ውስተ ህላዌሁ አመክንዮ፤ በከመ አቅደምነ ነጊረ አላ ባሕቱ ህልው በኵሉ መዋዕል አልቦቱ ጥንት ወኢተፍጻሜት ወቦቱ ብርሃን ዘኢይጠፍእ ወአልቦ ዘይክል ቀሪቦ ኀቤሁ ኢኮነ ክልዔተ ወኢሠለስተ ወኢይትዌሰክ አላ አሐዱ ውእቱ ዘይነብር ለዓለም እስመ ኢኮነ ስውረ ዘኢይትአመር ዳእሙ ጥዩቀ አእመርናሁ በኦሪት ወበነቢያት ከመ ውእቱ አኀዜ ኵሉ ወሥሉጥ ላዕለ ኵሉ ፍጥረት አሐዱ እግዚአብሔር አብ ለእግዚአነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተወልደ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ወልድ ዋሕድ ዘዕሩይ ምስሌሁ ገባሬ ኵሉ ሠራዊት ወሚመታት ወሥልጣናት ዘሠምረ ይኩን ሰብአ በደኃሪ መዋዕል ወነሥአ ሥጋ እማርያም እምቅድስት ድንግል ዘእንበለ ዘርአ ብእሲ ወተሐፅነ ከመ ሰብእ ዘእንበለ ኃጢአት ወአበሳ ወአልቦ ጕሕሉት ውስተ አፉሁ ወእምዝ ሐመ ወሞተ በሥጋ ወተንሥአ እሙታን በሣልስት ዕለት ወዐርገ ሰማያተ ኀበ አብ ዘፈነዎ ወነበረ በየማነ ኃይል። ወፈነወ ለነ ጰራቅሊጦስሃ መንፈስ ቅዱስ ዘወጽአ እምአብ ወአድኀነ ኵሎ ዓለመ። ዘህልው ምስለ አብ ወወልድ፤ ንብል እንከ ከመ ኵሉ ሠናይ ፍጥረተ እግዚአብሔር ወአልቦ ግዱፍ ወመንፈስሰ ሕይወተ ሥጋ ይእቲ ንጽሕት ወቅድስት በኵሉ ወንሕነሰ ንብል ከመ ሰብሳብ ንጹሕ ወልደት ዘአልቦ ርኩስ። እስመ ፈጠሮሙ እግዚአብሔር ለአዳም ወለሔዋን ከመ ይብዝኁ ሕዝብ ንለቡ እንከ ከመቦ ውስተ ሥጋን ነፍስ እንተ ኢትመውት ወኢትማስን ምስለ ሥጋ ንሕነሰ ናስቆርር ኵሎ ግብሮሙ ለዕልዋነ ሃይማኖት ወኵሎ ፍልጠቶ ወአሊወ ሕግ እስመ ርኩሳን እሙንቱ በኀቤነ ወካዕበ ነአምን ትንሣኤ ሙታን ጻድቃን ወኃጥአን ወዕለተ ኵነኔ አመ ይትፈደይ ኵሉ በከመ ምግባሩ ዓዲ ነአምን ከመ ክርስቶስ ኢኮነ ሕፁፀ እምትስብእት ወኢምንተኒ አላ ውእቱ እግዚአብሔር ቃል ዘኮነ ሰብአ በጽድቅ ወዐረቀ ትዝምደ ሰብእ ምስለ እግዚአብሔር ሊቀ ካህናቲሁ ለአብ፤ ኢንትገዘር እንከ ከመ አይሁድ። ነአምን ከመ መጽአ ዘይፌጽም ኦሪተ ወነቢያተ ዘኪያሁ ይሴፈዉ ምጽአቶ ኵሎሙ አሕዛብ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘሠረፀ እምይሁዳ ወእምሥርወ ዕሤይ ዘሥልጣኑ ዲበ መትከፍቱ፤ ሎቱ ስብሐት ወአኰቴት ዕበይ ወባርኮት ውዳሴ ወማኅሌት ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

## በአማርኛ

ይ:ሕ:- አቤቱ እናመሰግንሃለን አሜን ሥሉስ ቅዱስ ሆይ፥ ማረን፤ ሥሉስ ቅዱስ ሆይ፥ ራራልን፤ ሥሉስ ቅዱስ ሆይ፥ ይቅር በለን።



ይ:ዲ:- ለጸሎት ተነሡ፤

ይ:ሕ:- አቤቱ ይቅር በለን።

ይ:ካ:- ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

ይ:ሕ:- ከመንፈስህ ጋር

ይ:ዲ:- ክቡር ስለሚሆን ስለወንጌል ጸልዩ።

ይ:ሕ:- የከበረ ወንጌልን ለመስማት የበቃን አድርገን።

ይ:ዲ:- ከመዝሙረ ዳዊት ምስባክ።

ይ:ዲ:- ሃሌ ሉያ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ቅዱስ ወንጌል ቁማችሁ አድምጡ።

ይ:ካ:- እግዚአብሔር ከሁላችሁም ጋር ይሁን።

ይ:ሕ:- ከመንፈስህ ጋራ

ይ:ካ:- ማቴዎስ፥ ማርቆስ ወይም ሉቃስ የተናገረው። ዮሐንስ የሰበከው ቅዱስ ወንጌል የእግዚአብሔር ልጅ ቃል።

ይ:ሕ:- ጌታዬ፥ አምላኬ፥ ክርስቶስ ሆይ፥ በጊዜ ሁሉ ምስጋና ላንተ ይሁን

ይ:ሕ:- በረዳን በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ፤ ለያዕቆብ አምላክ ምስጋና አቅርቡ፤ ምዝሙር ዘምሩ፤ ከበሮ ምቱ፤ መዝሙር ከመሰንቆ ጋር ያማረ ነው።

(በጾም በተፈሥሖ ፈንታ)

ይ:ሕ:- በወንጌል መራኸን፤ በነቢያት አጽናናኸን፤ ላቀረብከን ለአንተ ምስጋና ይሁን።

ይ:ካ:- (ከወንጌል ያንብቡ)

ይ:ሕ:- (የተነበበው ከማቴዎስ ከሆነ) የማይለወጥ አብን እናምናለን፤ የማይለወጥ ወልድን እናምናለን፤ የማይለወጥ መንፈስ ቅዱስንም እናምናለን፤ ጸንቶ የሚኖር ሦስትነትን እናምናለን።

(የተነበበው ከማርቆሰ ከሆነ)

እሊህ ኪሩቤልና ሱራፌል ምስጋናን ያቀርቡለታል፤ እግዚአብሔር አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ አንተ ነህ እያሉ።

(የተነበበው የሉቃስ ወንጌል ከሆነ)

አቤቱ አማልክት ከሚባሉት ወገን የሚመስልህ ማነው? ድንቅ ሥራን የምትሠራ አንተ ነህ፤ ለሕዝብህ ኃይልህን አሳየሀቸው፤ ሕዝብህንም በክንድህ አዳንካቸው፤ ወደ ሲኦል ሄደህ ከዚያም ምርኮን አወጣህ፤ እንደገና አንድ ጊዜ ነጻነትን ሰጠኸን መጥተህ አድነኸናልና ስለዚህ እናመሰግንሃለን፤ ጌታ ኢየሱስ



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቶስ ሆይ፥ አንተ ቡሩክ ነህ እያልንም ወደ አንተ እንጮኻለን፤ ሰው ሁነህ አድነኸናልና።

(የተነበበው የዮሐንስ ወንጌል ከሆነ)

ቃል ቀዳማዊ ነው፤ ያ ቃል የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ያ ቃል ሥጋ ሆነ፤ በኛም ዐደረ፤ ላባቱ አንድ እንደሆነ ልጅ ክብር ክብሩንም አየን፤ የሕያው አብ ቃል አዳኝ ቃል፥ የእግዚአብሔር ቃል ተነሣ፤ ሥጋውም መፍረስ መበስበስ አላገኘውም።

ይ:ዲ:- የክርስቲያን ታናሾች ውጡ።

ይ:ዲ:- ለጸሎት ተነሡ።

ይ:ሕ:- አቤቱ ይቅር በለን።

ይ:ካ:- ሰላም ለሁላችሁም ይሁን።

ይ:ሕ:- ከመንፈስህ ጋራ

ይ:ዲ:- ለአንዲት፥ ቅድስት፥ አጽናፋዊትና ሐዋርያዊት ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን ሰላም ጸልዩ።

ይ:ሕ:- ኪርያላይሶን

ይ:ዲ:- ለጸሎት ተነሡ

ይ:ሕ:- አቤቱ ይቅር በለን።

ይ:ካ:- ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

ይ:ሕ:- ከመንፈስህ ጋር

ይ:ዲ:- ለዚህች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፥ በውስጥዋ ስላለው ማኅበራችንም ጸልዩ።

ይ:ሕ:- ማኅበራችንን ባርክ፤ በሰላም ጠብቅ

ይ:ዲ:- ከእግዚአብሔር በተሰጠን ዕውቀት ጸሎተ ሃይማኖት እንበል

## የሊቃውንት

ይ:ሕ:- ሁሉን በፈጠረ አንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን። ሰማይን፥ ምድርን፥ የሚታየውን የማይታየውን በፈጠረ፥ ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋራ በነበረ፥ ተቃደሚ፥ ተከታይ በሌለው በአብ ልጅ በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን፤ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከባሕርይ አምላክ የተገኘ የባሕርይ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፥ በመለኮቱ ከአብ ጋር ትክክል የሚሆን፥ ሁሉ በእርሱ የሆነ፥ በሰማይም ያለ በምድርም ያለ ያለ እርሱ ምንም የሆነ የለም፤ ስለ እኛ ስለ ሰዎችም እኛን ለማዳን ከሰማያት ወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆነ፤ ሥጋን ነሣ፤ ጐልማሳ ሆነ፤ ስለኛም በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ተሰቀለ፤ ታመመ፤ ሞተ፤ ተቀ



በረ፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ፥ በምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በአብ ቀኝ ተቀመጠ፤ ዳግመኛም በሙታንና በሕያዋን ይፈርድ ዘንድ በጌትነት ይመጣል፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።

ማሕየዊ ጌታ በሚሆን፥ ከአብ በሠረፀ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን። እንሰግድለት፤ እናመሰግነው፤ ከአብ ከወልድ ጋር በነቢያት ዐድሮ የተናገረ፥ ሐዋርያዊትና ዓለም ዐቀፋዊት በምትሆን በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምለን፤ ለኃጢአት ሥርየት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን፤ የሙታንን መነሣት ተስፋ እናደርጋለን የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለም።

## የሐዋርያት

በጌታችን በአምላካችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አባት ፍጥረቱን ሁሉ በፈጠረ በአንድ አምላክ እናምናለን። በመኖሩ መክንያት የለበትምና፤ አስቀድመን እንደተናገርን በዘመኑ ሁሉ ይኖራል እንጂ ጥንት ወይም ፍጻሜ የለውምና፤ የማይጠፋ ብርሃን አለው፤ ወደ እርሱም መቅረብ የሚቻለው የለም። ሁለት አይደለም፤ ሦስትም አይደለም፤ አይጨመርበትም። ለዘለ ዓለም የሚኖር አንድ ብቻ ነው እንጂ የማይታወቅ የተሰወረ አይደለምና በኦሪትና በነቢያት በጐላና በተረዳ ዐወቅነው እንጂ፤ ሁሉን ፈጠረ። በፍጥረት ሁሉ ላይም ሥልጣን ያለው እንደሆነ አንድ እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር ለተወለደ ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነው። ወልድ ዋሕድ ከእርሱ ጋራ የተካከለ ሠራዊትን መዓርጋትን ሥልጣናትንም ሁሉ ፈጠረ። በኋለኛው ዘመን ሰው ይሆን ዘንድ የወደደ ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለዘርአ ብእሲ ሥጋን ነሣ። ኃጢአት በደል ሳይኖርበት በሰው ሥርዓት ዐደገ። በአንደበቱም ሽንገላ አልተገኘበትም። ከዚህ በኋላ በሥጋ ታመመ፤ ሞተም፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፤ ወደላከውም ወደ አብ ወደ ሰማይ ዐረገ፤ ኃይል ባለውም ቀኝ ተቀመጠ።

ከአብ የሠረፀ ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስንም ሰደደልን። ዓለሙን ሁሉ አዳነ። ከአብ ከወልድ ጋር የሚኖር፤ እንግዲህ እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም እንደሆነ የሚጣልም እንደሌለ እንናገራለን። ነፍስ የሥጋ ሕይወት ናት በሁሉ ንጽሕት ቅድስት የሆነች እኛስ ጋብቻ ንጹሕ እንደሆነ መውለድም ርኩሰት እንደሌለበት እንናገራለን። ሕዝብ ይበዙ ዘንድ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮአቸዋልና። የማትሞት ከሥጋ ጋራ የማትፈርስ የማትበሰብስ ነፍስ በሥጋችን እንዳለች እንግዲህ እናስተውል። እኛስ ሃይማኖትን የሚለውጡ ሰዎች የሚሠሩትን ሁሉ እንነቅፋለን፤ መለየታቸውንም ሁሉ ሕግ መለወጣቸውንም እነርሱ በእኛ ዘንድ የረከሱ ናቸውና። ዳግመኛም የሞቱ የጻድቃንንና የኃጥአንን ትንሣኤ ሁሉ እንደ ሥራው የሚቀበልበትን የፍርድን ቀንም እናምናለን። ዳግመኛም ክርስቶስ ከሰውነት ምንም ምን የጐደለ እንዳይደለ እናምናለን። በእውነት ሰው የሆነ እግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ። አብ የሾማቸው የካህናት አለቃ የሰውን ወገን ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ።



www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ እንደ አይሁድ አንገዘር። ኦሪትንና ነቢያትን የሚፈጽም እንደመጣ እናውቃለን። አሕዛብ ሁሉ የእርሱን መምጣት ተስፋ የሚያደርጉት ኢየሱስ ክርስቶስ ከይሁዳ ከዕሤይም ሥር የተገኘ ሥልጣኑ ገንዘቡ የሆነው፤ ክብር፥ ምስጋና፥ ገናናነት፥ በረከት መስጠት፥ ውዳሴ ለርሱ ነው፤ ዛሬም፥ ዘወትርም፥ ለዘላዓለሙ አሜን።

## ጥያቄዎች

1. ቤተ ክርስቲያን ኀላፊነት ያለባት በምን ምክንያት ነው?
2. የቤተ ክርስቲያን ራስ ማነው?
3. የቤተ ክርስቲያንን ኀላፊነት በተመለከተ በስንት ርእሶች ሥር ቀረበ? እነርሱስ ምን ምን ናቸው?
4. የወንጌል ትምህርት የተስፋፋው እንዴት ነው?
5. ሰባቱን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ዘርዝር።
6. የምታስታውሳቸውን ሥርዓተ ጸሎቶች ዘርዝር።
7. ሁለቱን የችግር ዐይነቶች ግለጥ።
8. የዚህ ዓለም ኑሮ አስፈላጊ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
9. መጽሐፈ ዲድስቅልያ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት የሚያስከብር ማነው አለ?
10. አንዳንድ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ምን ዐይነት ሥርዓቶችን ያፈርሳሉ?
11. ወንጌላዊው ፊልጶስ ያጠመቀው አንድ የታወቀ ሰው ማነው?
12. ከፊልጶስ ጋር የሚያስተምሩ እነማን ነበሩ?
13. ማርያም መግደላዊት ማንን አገለገለች?
14. ሙሴ ጸሊም ቀደም ብሎ ምን ነበር?
15. ሙሴ ጸሊም ምን ድምፅ ሰማ?
16. ሰይጣን ሙሴ ጸሊምን በምን ተዋጋው?
17. ሙሴ ጸሊም ለገዳሙ ሽማግሌዎች ምን ያደርግላቸው ነበር?
18. ሙሴ ጸሊም ለስንት ወንድሞች አባት ሆነላቸው?



# ምዕራፍ 5

## መንፈሳዊነትና ግብረገብነት

### ከሰዎች ጋር የመወያየት ውጤት

ውይይት ወይም መወያየት የሚለው ቃል እንደዚህ ምዕራፍ አባባል ስለ አንድ ጉዳይ ወደ አንድ የስምምነት ውጤት ላይ ለመድረስ ሐሳብ ለሐሳብ መለዋወጥ ማለት ነው። ውይይቱ አንድ ሰው የራሱን እምነት በማብራራት ሌላውን ሰው እንዲያምንለት ለማድረግ፥ ወይም ሌሎችን ሰዎች ለማሳመን የሚያደርገው ማስረዳትና ለሚቀርብለትም ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያየ ሐሳብ ያላቸው ሰዎች ሐሳባቸውን ለማሳመን ሁላቸውም በየግላቸው ለጉባኤ አቅርበው የሚነጋገሩበት ጉዳይ ሊሆን ይችላል። ከዚህም ሌላ አንድ ችግር ያለ መሆኑ ታውቆ ለዚያ ችግር ስብሰባ በማድረግ ወደመፍትሔ ሐሳብ ለመድረስ የሚደረግ የሐሳብ መለዋወጥ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ በቀረበ ሐሳብ ወይም ሐሳቦች ላይ ሁልጊዜ ወደ ስምምነት ይደረሳል ማለት አይደለም፤ አንዳንድ ጊዜ ይደረሳል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ላይደረስ ይችላል።

<u>ወደ ስምምነት የመድረስ ወይም ያለመድረስ ሁናቴ</u>:- ወደ አንድ ስምምነት ላይ አለመድረስ ጠላትነት አይደለም። ሰዎች የሐሳብ ልዩነት ቢኖራቸውም ተግባብተው ለመኖር ይችላሉ። ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለቍጣ የሐሳብ ልዩነት ማድረግ ይገባል። ያመኑበትን ነገር ለሌላ ሰው ለማሳመን ሙከራ በሚደረግበት ጊዜ ተቀባይነት ሳያገኝ ቢቀር ያለውን ወዳጅነት መቀጠል እንጂ ጠባይን መለወጥ አይገባም። በሌላ በኩል ደግሞ ለትልቅ ዓላማና እምነት ፍጹም ታማኝ መሆን እንጂ ትክክለኛ ላልሆነ የጓደኛ ተጽዕኖ መሸነፍ የደካማነት ምልክት ነው። ሰውን ወደ ትክክለኛ አቅጣጫ የመምራት ኀላፊነት ሊሰማ ይገባል። ይሁን እንጂ ቢቻልም፥ ባይቻልም ከሰው ጋር ያለው የወዳጅነት ስሜት መቀዝቀዝ የለበትም። ኅብረተሰብ እንደማንኛውም ግለሰብ ሊሳሳት ስለሚችል የድምፅ ብልጫ ሊያሳስተን አይገባም። ዋናው የአስተሳሰብ መመዘኛ ቃለ እግዚአብሔር መሆን አለበት። ለቃለ እግዚአብሔር ታማኞች ከሆንን ለሰው ሁሉ ፍቅር አለን ማለት ነው። ፍቅርና ቅንነት ካለን ደግሞ ነፍሳትን የማዳን ዕድል ያጋጥመናል። በዚያ በምናድነው ነፍስ ምክንያትም በሰማይ ደስታ ይሆናል (ሉቃ:ም:15ቍ:7)።

መንፈሳዊ ውይይት በትሕትናና በመግባባት እንጂ በቍጣና በእምቢተኛነት አይሁን። ይህን አባባል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደምን አድርጎ እንደሠራበት ሲያመለክት እንዲህ ብሎአል:-



www.ethiopianorthodox.org

«እኔ የማንም ባሪያ ሳልሆን ነጻ ሰው ነኝ፤ ይሁን እንጂ በተቻለኝ መጠን ብዙዎችን በማዳን ለመጥቀም ብዬ የሁሉም ባሪያ ሆኜአለሁ። ከአይሁድ ጋር ስሆን አይሁድን ለማዳን እንደ አሁዳዊ ሆንኩ፤ ምንም እንኳ እኔ ከኦሪት ሕግ በታች ባልሆን ከኦሪት ሕግ በታች ያሉትን ለማዳን ስል ከኦሪት ሕግ በታች እንዳሉት ሰዎች ሆንኩ፤ ምንም እንኳ እኔ የእግዚአብሔር ሕግ ያለኝና ከክርስቶስ ሕግ ሥር ብሆን፥ ሕግ የሌላቸውን አረማውያንን ለማዳን ስል ሕግ እንደሌለው ሰው ሆንሁ። በእምነት ደካሞች የሆኑትን ለማዳን ስል እንደ ደካሞች ደካማ ሆንኩ፤ በተቻለ መጠን አንዳንዶችን ለማዳን ከሁሉም ጋር ሁሉን ነገር ሆንኩ» (1ኛ:ቆሮ:ም:9ቊ:19–22።:

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሁሉ እያደረገ በሚያስተምርበት ጊዜ ብዙ ችግሮች የደረሱበት ቢሆንም እንኳ ሥራው በጣም የተሳካለት ሰው ነበር (2ኛ:ቆሮ:ም:11ቊ21–33)።

ታዲያ እንዴት ይህ ሊሆን ቻለ? ይህ ሊሆን የቻለው ምንም ያኽል ችግር ቢበዛበት ሥራውን ያከናውን የነበረው በፍቅርና በትዕግሥት ስለነበረ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ብዙ ሥራዎቹ ተሳክተውለት ብዙ የክርስቶስ ቤተ ሰብ ቢያሰባስብም እንኳ አንድም ያልተቃወመው አልነበረም ማለት አይደለም። ምንም ሳይታክት በአይሁድ ጸሎት ቤቶች ሁሉ እየገባ ያስተምር ነበር። ብዙ አረማውያንንም ወደ ክርስትና መልሶአል። ይሁን እንጂ አይሁድም ሆኑ አረማውያኑ ብዙ ሥቃይ አድርሰውበታል። የመደብደቡ፥ የመገረፉ፥ የመሰደቡና የመታሰሩ ችግር ሲደርስበት ሁለተኛ አረማውያንን አላስተምርም፤ ወይም ዳግመኛ ወደ አይሁድ ምኵራብ አልገባም አላለም።

የሐሳብ ልዩነት መኖሩን ዐውቀን መቀበል አለብን። ሰዎችን ሁሉ ወደ እኛ ሐሳብ ለመመለስ ካልቻልን እነርሱ ጠላቶቻችን ናቸውና ሁለተኛ ከእነርሱ ጋር አንነጋገርም የምንል ከሆነ ሰው ሁሉ የተለያየ አስተሳሰብ ያለው መሆኑን አናውቅም ማለት ነው። እንዲሁም እንኳን በአስተሳሰብ ልዩነት ካለን ሰዎች ጋር ይቅርና ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚለውን የጌታችንን ትእዛዝ አላስተዋልነውም ማለት ነው። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከሰው ጋር ኖረን ብዙ ሥራዎችን መሥራት አንችልም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሁሉን ለማዳን ከሁሉም ጋር ሁሉን ነገር ሆንኩ ያለውን ጥበባዊ አስተሳሰብ ትክ ብለን ማስተዋል ይኖርብናል።

## ተስፋ መቍረጥ አይገባም

አንዳንድ ችግሮች በትዕግሥት ካልተቋቋሙአቸው በቀር ትዕግሥት ለሌላቸው ሰዎች ተስፋ ያስቈርጡ ይሆናል። ተስፋ መቍረጥ ደግሞ በእግዚአብሔር አለመተማመን ነው። እስከመጨረሻ የሚታገሥ ግን ባለ ድል እንደሚሆን የሚገልጡትን የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች እንመልከት:-



«እስከ መጨረሻ በትዕግሥት የሚጸና ግን ይድናል» (ማቴ:ም: 24ቊ: 13)።

«አንተም የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም ወታደር በመሆን መከራን ከእርሱ ጋር ተካፈል» (2ኛ:ጢሞ:ም:2ቊ:3)።

«ጌታ በቃል ኪዳኑ መሠረት ለወዳጆቹ የሚሰጠውን የሕይወት አክሊል ስለሚቀበል፥ ፈተናን ታግሦ የሚጸና ሰው የተባረከ ነው» (ያዕ:ም:1ቊ:12)።

ተስፋ መቍረጥ ራሱ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት ማጓደል ነው የሚባልበት ምክንያት መውደቅም ሆነ መነሣት ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የማይፈጸሙ መሆናቸውን አለማመን በመሆኑ ነው። ለምሳሌ ንጉሥ ሕዝቅያስ የመሞቻው ጊዜ ሲነገረው እግዚአብሔርን ስለለመነ ነው በዕድሜው ላይ ዐሥራ አምስት ዓመቶች የተጨመሩለት። ተስፋ ቈርጦ ዝም ቢል ኖሮ ያን ተጨማሪ የዐሥራ አምስት ዓመት ዕድሜ ሊያገኝ ባልቻለም ነበር። የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት አምኖ ልመናውን አቀረበ እግዚአብሔርም የለመነውን ሰጠው።

ተስፋ ከመቍረጥ የተነሣ ሰዎች ብዙ ጊዜ ተጨማሪ ኃጢአት ይሠራሉ፤ ወይም ራሳቸውን ይጐዳሉ። አንዳንድ ሰዎች ተስፋ በመቍረጣቸው የመጠጥና የሌሎች ነገሮች ሱሰኞችና ሰካራሞች ይሆናሉ። በስካርም ኅሊናቸውን ስለሚስቱ ራሳቸውን፥ ቤተሰባቸውንና ኅበረተሰቡን ይበድላሉ። ለምሳሌ የፋርስ መንግሥት የጦር አዛዥ የነበረው ሆሎፈርኔስ በአንዲት ሴት ራሱ ተቈርጦ ለፋርስ ሠራዊት መሸነፍ ምክንያት የሆነው በስካር ኅሊናውን ስቶ በነበረበት ጊዜ ነው።

ተስፋ የቈረጡ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ተስፋ ከመቍረጣቸው የተነሣ ተጨማሪ ኃጢአት ይሠራሉ። ለምሳሌ ንጉሥ ሳኦል እግዚአብሔር ከእርሱ ተለይቶት ተስፋ በቈረጠ ጊዜ ወደ መናፍስት ጠሪ ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ ማስጠንቈልን የመሰለ ተጨማሪ ታላቅ ኃጢአት ሠራ። እንዲሁም አስቆሮታዊው ይሁዳ ጌታውን አሳልፎ ከሰጠ በኋላ ወደ ኅሊናው ሲመለስ ተስፋ በመቍረጥ ራሱን የመግደል ተጨማሪ ኃጢአት ሠራ። በለመንነው ጊዜ ሁሉ ተገቢውን መልስ የሚሰጠን አባት፥ ጌታ፥ አምላክ እስካለልን ድረስ ለምን ተስፋ እንቈርጣለን። ማንኛውም ሁናቴ ያለ እርሱ ፈቃድ የማይፈጸም መሆኑን እስካወቅን ድረስና የችግር መፍትሔ ሁሉ በእርሱ እጅ መሆኑን እስካወቅን ድረስ ለምን እምነታችንን በማጓደል ተስፋ የመቍረጥ ኃጢአት እንፈጽማለን። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኮ ያለው:-

«ልባችሁ አይጨነቅ፤ በእግዚአብሔር እመኑ በእኔም እመኑ» ነው (ዮሐ: ም:14ቊ:1)።



www.ethiopianorthodox.org

## አንቀጸ ብፁዓን

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንቀጸ ብፁዓን የሚባለው ክፍል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የታወቀውን የተራራ ላይ ትምህርቱን ሲጀምር የተናገራቸው የበረከት ምንጮች ናቸው። አባባሉም እንደሚከተለው ነው:-

1. «በመንፈሳዊ ኑሮአቸው ድኾች መሆናቸው የሚሰማቸው፥ መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ስለሆነች የተባረኩ ናቸው (ብፁዓን ናቸው)።

2. የሚያዝኑ፥ እግዚአብሔር መጽናናትን ስለሚሰጣቸው የተባረኩ ናቸው (ብፁዓን ናቸው)።

3. የዋሆች፥ ምድርን ስለሚወርሱ የተባረኩ ናቸው (ብፁዓን ናቸው)።

4. ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ፥ ስለሚጠግቡ የተባረኩ ናቸው (ብፁዓን ናቸው)።

5. ምሕረትን የሚያደርጉ፥ ምሕረትን ስለሚያገኙ የተባረኩ ናቸው (ብፁዓን ናቸው)።

6. ንጹሕ ልብ ያላቸው፥ እግዚአብሔርን ስለሚያዩ የተባረኩ ናቸው (ብፁዓን ናቸው)።

7. በሰዎች መካከል እርቅና ሰላምን የሚያደርጉ፥ የእግዚአብሔር ልጆች ስለሚባሉ የተባረኩ ናቸው ( ብፁዓን ናቸው)።

8. ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ፥ መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ስለሆነች የተባረኩ ናቸው (ብፁዓን ናቸው)።

9. በእኔ ምክንያት ሰዎች ሲሰድቡአችሁና ሲያሳድዱአችሁ፥ በውሸትም ስማችሁን ሲያጠፉት የተባረካችሁ ናችሁ (ብፁዓን ናችሁ)። በመንግሥተ ሰማይ የምታገኙት ዋጋ ትልቅ ስለሆነ ደስ ይበላችሁ፤ ሐሴትም አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያት እንዲሁ ስደትና መከራ አድርሰውባቸዋል (ማቴ:ም:5ቍ:3–12)።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተራራ ላይ ትምህርቱን ሲጀምር እውነተኛዎቹ የበረከት ወይም የደስታ ምንጮች የሚለኩት በሰማያዊ መለኪያ እንጂ ጠፊና ከንቱ በሆነው ምድራዊ መለኪያ አለመሆኑን ገልጦአል። ሰዎች በሥጋዊ አስተሳሰብ የሚገምቱአቸው የደስታ ምንጮች ግን በስሕተት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት እነርሱ እንደሚገምቱት የደስታ ምንጩ ምድራዊ ሀብት ስለሚመስላቸው ነው። ጌታችን ይህን አስተሳሰብ አርሞ የደስታ ምንጮቹ ሌሎች መንፈሳውያን ሁኔታዎች እንጂ ምድራዊ ሀብት አለመሆኑን ስለሰጠው ዝርዝር ትምህርት የሚከተሉትን ማብራሪያዎች ይመለከቷል።

በመንፈሳዊ ኑሮአቸው ድኻ መሆናቸው የሚሰማቸው ስለዓለማዊው ሀብት እጅግም ሳይጨነቁ መንፈሳዊነት እንደጐደላቸው በማድረግ ራሳቸውን በራ

www.ethiopianorthodox.org



ሳቸው ዝቅ አድርገው የሚያዩ ናቸው። እነዚህም የክርስቶስ ቤተሰብ አባሎች ናቸው።

የሚያዝኑ ሲባል ስለዓለማዊ ጉዳይ የሚያዝኑ ሳይሆን ስለኃጢአታቸው በመጸጸት ወይም ስለሌሎች ሰዎች ኃጢአት የሚያዝኑ ማለት ነው። እነርሱም መጽናናትን ከምድር ሳይሆን ከሰማይ ያገኛሉ።

የዋሆች ማለት ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ለእግዚአብሔርና ለትእዛዛቱ የሚያስገዙ፥ ምንም ዐይነት ችግርና ማሳደድ ቢያደርሱባቸውም በሰዎች ሁሉ ፊት ራሳቸውን ዝቅ የሚያደርጉና ቂም የማይዙ ናቸው። እንደእነዚህ ያሉት የትሕትናቸውን ዋጋ በምድር ላይ እንኳ ያገኛሉ።

ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ማለት እንደ እውነተኛ በጎነት የሚቈጥሩትን መንፈሳዊ በረከት የሚናፍቁ ማለት ነው። እንደ እነዚህ ላሉት እግዚአብሔር ፍላጎታውን ሁሉ በመስጠት ያጠግባቸዋል፤ ያረካቸዋልም።

ምሕረትን የሚያደርጉ ማለት ከፍቅርና ከልባቸው ቅንነት የተነሣ ለችግረ ኞች የሚራሩና የሚረዱአቸው ማለት ነው። እንደ እነዚህ ያሉት ከእግዚአ ብሔርም ከሰውም ምሕረትን ያገኛሉ።

ንጹሕ ልብ ያላቸው ሲባል ርኩስ ሐሳብ ወይም ክፉ ዝንባሌ የሌላቸው ማለት ነው። እንደነዚህ ያሉት ፍጹም ንጹሖች በመሆናቸው እግዚአብሔርን ያዩታል። ይህም የተሟላ ደስታ ነው።

በሰዎች መካከል እርቅንና ሰላምን የሚያወርዱ ሲባል በእነርሱና በእግዚ አብሔር መካከል፥ በእነርሱና በሰዎች መካከል፥ እንዲሁም በእነርሱና በራ ሳቸው መካከል ሰላምን ለማስፈን የሚሠሩ ማለት ነው። እነዚህ የእግዚ አብሔር ልጆች የሚባሉበት ምክንያት ለሰላም በመሥራታቸው እግዚአ ብሔርን ስለሚመስሉ ነው።

·ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ማለት በእግዚአብሔርና በትእዛዛቱ በማመናቸው ማለት ነው። እነርሱም ለመሰደብ፥ በሐሰት ለመከሰስና ለመሰደድ የተጋለጡ ናቸው። የእውነት ጠላቶችም የክርስቶስ ጠላቶች ናቸው። እንደዚህ አድርገው የሚሳደዱትም በክርስቶስ መንግሥት የተከበሩ ይሆናሉ።

### ጥያቄዎች

1. በአሁኑ አባባል ውይይት ማለት ምን ማለት ነው?

2. ለውይይት ሌሎች አማራጭ ትርጉሞች ምን ምን ናቸው?

3. ውይይት ሁልጊዜ ወደ ስምምነት ያደርሳልን?

4. ሰዎች የሐሳብ ልዩነት ካላቸው ጠላቶች ናቸውን?

5. አንድ ሰው እምነቱን ለሌላ ሰው ለማስረዳት በሚፈልግበት ጊዜ ተቀባይነት ያጣ እንደሆነ ከዚያ ሰው ጋር የነበረውን ግንኙት ማቋረጥ ይገባል ወይስ አይገባም?

6. ትክክለኛው ብዙ ሰዎች ያመኑበት ጉዳይ ብቻ ነውን?

7. ኅብረተሰብ ይሳሳታል? ወይስ አይሳሳትም?

8. አንድን ነፍስ ያዳንን እንደሆነ በሰማይ ምን ዐይነት ስሜት ይኖራል?

9. መንፈሳዊ ውይይት እንዴት መሆን አለበት?

10. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ብዙዎችን በማዳን ለመጥቀም ሲል ምን አደረገ?

11. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሥራው የተሳካለት በምን ምክንያት ነው?

12. ሰውን ወደ እምነታችን ለመመለስ ባለመቻላችን ዳግመኛ ከእርሱ ጋር አንነጋገርም የምንለው ምን ዐይነት አስተሳሰብ ያለን እንደሆነ ነው?

13. ይህን ብናደርግ የትኛውን የጌታችንን ትእዛዝ አላስተዋልንም ማለት ነው?

14. ተስፋ መቍረጥ ምንን ያመለክታል?

15. ተስፋ ባለመቍረጥ ለሚገኝ ጥቅም አንድ ምሳሌ አቅርብ

16. ተስፋ መቍረጥ ወደ ተጨማሪ ኃጢአት የሚወስድ ለመሆኑ የተስጡትን ሁለት ምሳሌዎች አቅርብ።

17. አንቀጸ ብፁዓን የሚለው ቃል የተሰጠው ለየትኛው የጌታችን ትምህርት ነው?

18. ጌታችን በአንቀጸ ብፁዓን ትምህርት የደስታ ምንጮች መለኪያቸው ምን እንደሆነ አብራራ?

19. ስለደስታ ምንጭ መለኪያ ሰዎች የሚያስቡት ስሕተት ምንድነው?



# ስምንተኛ ክፍል

## ምዕራፍ 1

## ትምህርተ ሃይማኖት

### የእግዚአብሔር ቅጣቶች

እግዚአብሔር እንደ አባት ሆኖ ልጆቹን ለማስተማርና ለማስጠንቀቅ፥ እንደ ዳኛ ሆኖ ለሰው ሁሉ እንደየተግባሩ ተገቢ ዋጋውን ወይም ቅጣቱን የሚሰጥ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ። የእግዚአብሔር ቅጣቶች በአጠቃላይ ሁለት ዐይነቶች ናቸው።

የመጀመሪያው የቅጣት ዐይነት እንደ አባትነቱ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ወይም ለማስተማር ብሎ በዚህ ዓለም ላይ የሚቀጣው ጊዜያዊ ቅጣት ነው።

ሁለተኛው ዐይነት ቅጣት ደግሞ ለሰው ሁሉ እንደየተግባሩ በሚፈርድለት ወይም በሚፈርድበት ጊዜ ክፉ በሠሩ ሰዎች ላይ የሚያስተላልፈው ዘለዓለማዊ ቅጣት ነው።

<u>ምድራዊ ወይም ጊዜያዊ የእግዚአብሔር ቅጣት</u>:- እግዚአብሔር ክብሩን ለመግለጥ፥ የማስጠንቀቂያ ትምህርት ለመስጠት፥ ሰላማውያን ሰዎችን ከግፈኞች ለመታደግ ብሎ ሰዎችን የሚቀጣበት ጊዜ አለ። የቅጣቶቹም ዐይነቶች እስከ ሞት ድረስ ሊያደርሱ የሚችሉ ናቸው።

እንደሚታወቀው እግዚአብሔር ሰው ሁሉ እንዲድን እንጂ ማንም እንዲጠፋ አይፈልግም። በዚህም መሠረት ሰው ከኃጢአቱ ይመለስ ዘንድ በቅዱሳት መጻሕፍት፥ በሃይማኖት መምህራን፥ በምድራዊ ቅጣት ያስጠነቅቀዋል። የማይመለስ እልኸኛ በሚሆንበት ጊዜ ግን ቅጣቱን እያበረታበት ይሄዳል። በፍጹም የማይመለስና እንዲያውም የእግዚአብሔርን ክብር የሚዳፈር ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ግን እግዚአብሔር ክብሩን የሚገልጥበትን ቅጣት ያመጣበታል።

ለዚህ አባባል ምሳሌ ሊሆን የሚችለው የግብጹ ፈርዖን ነው። ፈርዖንና የግብጽ ሕዝብ እስራኤላውያንን በመጨቈን ባሰቃዩአቸው ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን ጥፋቱን እንዲነግሩትና እስራኤላውያን በነጻ እንዲለቅቅ የእግዚአብሔር ትእዛዝ መሆኑን እንዲያስታውቁት ላካቸው። ፈርዖን ግን ልቡን አደንድኖ እምቢተኛ በሆነ ጊዜ እነርሱ የተላኩት ከእግዚብሔር ዘንድ መሆኑን ለማሳመን ውሃን ወደ ደምነት ከመለወጥ አንሥቶ የበኵር ልጆችን በሞት እስከመቅጣት ድረስ ቅጣቱ ከፍ ከፍ እያለ እንዲሄድ በማድረግ ዐሥር ቅጣቶች በግብጽ ሕዝብ ላይ ደርሰዋል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን

www.ethiopianorthodox.org

በመጀመሪያው ጊዜ ከፍተኛውን ቅጣት ለማምጣት በቻለ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ማንም ሰው እንዲጠፋ ፈቃዱ ስላልሆነና ለፈርዖን በንስሐ እንዲመለስ ዕድል ለመስጠት ብሎ በተከታታይ ዘጠኝ መቅሠፍቶችን ወይም ቅጣቶችን አመጣበት። ፈርዖን ግን በነዚህ ሁሉ ቅጣቶች ደንግጦ በንስሐ ከመመለስ ይልቅ ልቡን አጸና። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር የግብጻውያንን ሁሉ በኵር ልጆች በሞት በመቅጣት ታላቅ ክብሩን አሳየ። ምንም እንኳ ፈርዖን ለጊዜው ተደናግጦ የእስራኤልን ሕዝብ ነጻ ቢለቅቅ፥ እንደገና ሐሳቡን ለውጦ እስራኤላውያንን እንዲያሳድድ ሠራዊቱን ልኮ ነበር። እግዚአብሔር ግን ክብሩን በበለጠ በመግለጥ የግብጽን ወታደሮች ከነፈረሶቻቸውና ከነሠረገላዎቻቸው በቀይ ባሕር ውስጥ እንዲሰጥሙ አደረገ። እነዚህም በግብጽ ሕዝብ ላይ የደረሱት የቅጣት ተአምራት ሁለት ዐላማዎች አሉአቸው። አንዱ ዐላማ የተጨቈነውን የእስራኤል ሕዝብ ነጻ ለማውጣት ሲሆን ሁለተኛው ዐላማ ደግሞ የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነትና ክብር እንዲገለጥ ነው (ዘጸ:ም:7 እስከ 14)።



የአሮን በትር ወደ እባብነት እንደተለወጠ (ዘጸ. ም 7 ቁ 8-13)።

እግዚአብሔር ክብሩን ከገለጠባቸው ቅጣቶች መካከል ሌላው ምሳሌ ደግሞ የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ነው። የሰናክሬም የጦር አዛዥ በይሁዳ ንጉሥ በሕዝቅያስና በሕዝቡ ላይ የንቀትና የዛቻ ንግግር ከማድረጉም በላይ በእግዚአብሔርም ላይ ተዳፈረ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ በይሁዳ ሕዝብ ላይ ተሰልፈው የነበሩትን በመፍጀት ክብሩን ገለጠ (2ኛ:ነገ: ም:19ቍ:35)።

ሌላው የምድራዊ ቅጣቶች ዐይነት ደግሞ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ የማስጠንቀቂያ ትምህርት የሚሰጥበት የአባትነት ተግሣጽ ነው። ይህም አንድ



ወላጅ አባት ልጁን ሁለተኛ እንዳይደግምህ ብሎ በመቈንጠጥ ወይም በአርጩሜ እንደሚቀጣው ያለ ትምህርት ነው።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ ብዙ ምሳሌዎችን ለማቅረብ የሚቻል ቢሆንም ለጊዜው ግን ሁለት ምሳሌዎች ብቻ ቀርበዋል።

የእግዚአብሔር አገልጋይ የነበረው ሙሴ በመሪባ ውሃ ጉዳይ ለእግዚአብሔር ክብር ሳይሰጥ በመቅረቱ አርባ ዓመት ሙሉ ተስፋ አድርጎ ይጠባበቀው ወደ ነበረው የከነዓን ምድር ከመግባት በመታገድ ተቀጣ (ዘኍ ም:20 ቍ:12)።

ሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ በዳዊት ላይ የተፈጸሙት የተለያዩ ቅጣቶች ናቸው። እግዚአብሔር ለዳዊት ሲመሰክርለት «ከልቤ የምወደውን፥ ፈቃ ዴንም የሚፈጽመውን የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ» ብሏል (የሐ: ሥ: ም:13ቍ:22)።

ዳዊት ኦርዮን አስገድሎ ሚስቱን በመውረሱ ምክንያት እግዚአብሔር ቀጣው። አንደኛ ከኦሪዮ ሚስት የወለደው ልጁ ሞተበት። ሁለተኛ ልጁ አቤሴሎም በእርሱ ላይ ዐምፆ ከዙፋኑ አባረረው። ዳዊትም ከአቤሴሎም ሸሽቶ ተሰደደ። ሦስተኛ ዳዊት ቤት እንዲጠብቁለት የተዋቸውን ሚስቶቹን በመደፈር አቤሴሎም የአባቱን አልጋ አረከሰ (2ኛ: ሳሙ:ም: 12ቍ: 1–23፥ም: 15 ቍ:1–31፥ ም:16ቍ: 15–23)።

እንደገናም ዳዊት የሕዝብ ቈጠራ በማድረጉ ምክንያት እግዚአብሔር ሰባ ሺህ ሰው በቸነፈር አለቀ (2ኛ:ሳሙ:ም:24)።

ስለምድራዊ ቅጣት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች:- «እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፤ ነገር ግን እኔን ባትሰሙና እነዚህን ትእዛዞች ሁሉ ባትፈጽሙ፥ ትእዛዛቴን ባትጠብቁ፥ ሕጎቼን ብትንቁ፥ ቃል ኪዳኔን ብታፈርሱና ሥርዓቴን ብትጸየፉ ታላቅ ድንጋጤን፥ ክሳትን ዐይንን የሚያፈዝዝ ሰውነትን የሚያመነምን የንዳድ በሽታ አመጣባችኋለሁ፤ ጠላቶቻችሁ ስለሚበሉት ዘራችሁን በከንቱ ትዘራላችሁ፤ በቍጣ ፊቴን እመልስባችኋለሁ፤ በጠላቶቻችሁ ትሸነፋላችሁ፤ የሚጠሉአችሁ ይገዙአችኋል፤ ማንም ሳያሳድዳችሁ ትሸሻላችሁ» (ዘሌ:ም:26ቍ: 14–17)።

«አባት ልጆቹን እንደሚገሥጽ አምላክህ እግዚአብሔርም አንተን የሚገሥጽ መሆኑን አስተውል» (ዘዳ:ም:8ቍ:5)።

«አባት የሚወድደውን ልጁን እንደሚገሥጽ እግዚአብሔርም የሚገሥጸው የሚወድደውን ነው» (ምሳ:ም:3ቍ:12)።

«እግዚአብሔር እንደልጆቹ አድርጎ እንዲህ ሲል የመከራችሁን ረሳችኋል:- ልጄ ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ አታቃልል፤ በቀጣህም ጊዜ ተስፋ አትቍረጥ፤ እግዚአብሔር የሚወድደውን ይገሥጻል፤ እንደ ልጁ

www.ethiopianorthodox.org

አድርጎ የሚያየውንም ይቀጣል። እግዚአብሔር እንደ ልጆቹ ስለሚቈጥራችሁ ቅጣትን ታገሡ፤ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማነው? ። (ዕብ: ም: 12ቊ: 5–7)።

«እኔ የምወድዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ፤ እቀጣቸዋለሁም፤ ስለዚህ ትጋ ንስሓም ግባ» (ራ:ዮ:ም:3ቊ:19)።

<u>ዘለዓለማዊው የመጨረሻው ቅጣት</u>:- እግዚአብሔር ሰው ሁሉ እንዲድን እንጂ እንዲጠፋ የማይፈቅድ፥ ደግና ርኅሩኅ ከመሆኑ ጋር ትክክለኛ ዳኝነትም ገንዘቡ ነው። ስለዚህ ለሰው ልጅ የመዳኛውን መንገድ ሁሉ ካመቻቸለት በኋላ ሰው ግን በተፈቀደለት ነጻ ውሳኔ መሠረት የጥፋትን መንገድ ብቻ ተከትሎ በንስሐ ለመመለስ በፍጹም ፈቃደኛ ሳይሆን ቢቀር እግዚአብሔር በትክክለኛ ዳኝነቱ በዘለዓለማዊ ቅጣት ይቀጣዋል። ይህንንም የሚያደርገው በምክርና በተግሣጽ የማይመለስ ሆኖ ሲያገኘው ነው።

ስለዘለዓለማዊ ቅጣት የሚከተሉትን የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች እንመልከት:-

«ወጥተውም ሲሄዱ በእኔ ላይ በማመፃቸው የተገደሉትን ሰዎች በድን ያያሉ፤ እነርሱን የሚበላቸው ትል አይሞትም፤ የሚያቃጥላቸውም እሳት አይጠፋም፤ እነርሱንም የሚያያቸው ሁሉ ይጸየፋቸዋል» (ኢ.ሳ:ም: 66ቊ: 24)።

«በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘለዓለም ሕይወት እኩሌቶቹም ወደ ዘለዓለም እፍረትና ወደ ዘለዓለም ጉስቊልና» (ዳን:ም:12ቊ:2)።

«በግራው በኩል ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል:- ‹እናንተ የተረገማችሁ፥ ከእኔ ወዲያ ራቁ፤ ለሰይጣንና ለተከታዮቹ መላእክት ወደ ተዘጋጀው ወደ ዘለዓለም እሳት ሂዱ።› ... ስለዚህ እነዚህ ወደ ዘለዓለም እሳት ሲሄዱ ጻድቃን ግን ወደ ዘለዓለም ሕይወት ይሄዳሉ» (ማቴ:ም:25ቊ:41 እና 46):

«መልካም የሠሩ ከሞት ተነሥተው በሕይወት ይኖራሉ፤ ክፉ የሠሩ ግን ከሞት ተነሥተው ይፈረድባቸዋል» (ዮሐ:ም:5ቊ:29)።

«እያንዳንዱ በምድራዊ ሕይወቱ ላደረገው ክፉም ሆነ ደግ ነገር እንደ የሥራው ዋጋውን ለመቀበል፥ ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት መቅረብ አለብን» (2ኛ:ቆሮ:ም5ቊ:10)።

«ሌላ ሦስተኛ መልአክም በታላቅ ድምፅ እንዲህ እያለ ተከተላቸው:- ‹ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግዱ፥ ምልክቱን በግንባራቸው ወይም በእጃቸው የሚያደርጉ ሁሉ፥ የእግዚአብሔርን ቊጣ የወይን ጠጅ ይጠጣሉ፤ ይህም የወይን ጠጅ ሳይበረዝ በቊጣው ጽዋ የተዘጋጀ ነው፤ እንዲሁም በቅዱሳን መላእክት ፊትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሠቃያሉ። እነርሱን ከሚያሠቃየው እሳት የሚወጣው ጢስ ለዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ወደ ላይ ይወጣል፤



www.ethiopianorthodox.org

ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግዱ የስሙንም ምልክት ያደረጉ ሁሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም» (ራ:ዮሐ:ም:14ቊ:9–11)።

## <u>እምነትና ተግባር</u>

የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት መሠረት በማድረግ አንዲት፥ ቅድስት፥ ዓለም ዐቀፋዊትና ሐዋርያዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን መዳን የሚገኘው ክርስቶስን በማመንና በንስሓ መሆኑን ከጥንት ጀምራ በማመን ለልጆችዋ ስታስተምር ኖራለች። ይህም ማለት አንድ ክርስቲያን ከተግባር ጋር የተጣመረ እምነት ያለው ካልሆነ በቀር መዳንን ድኅነት ሊያገኝ አይችልም ማለት ነው። ይህ ትምህርት ምክንያታዊ አስተሳሰብ የሚቀበለውና በቅዱሳት መጻሕፍትም ማስ ረጃዎች የተደገፈ ነው። ይህም በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን ከመጀመሪያው ጀምራ የተጓዘችበት የእምነት ጐዳና ነው።

ነገር ግን አንዳንድ ወገኖች ለመዳን ወይም ለመጽደቅ የሚያስፈልገን እምነት ብቻ ነው እንጂ ተግባር አይደለም ይላሉ። እንደ እነርሱ አባባል በጎ ተግባር የእምነት ውጤት ነው እንጂ ራሱ መዳንን ወይም ጽድቅን የሚያስገኝ አይደለም። ለዚህ አባባላቸውም ከሚያቀርቡአቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«በእምነት የጸደቀ ሁሉ ሕይወትን ያገኛል» ተብሎ ተጽፎአል። የእግዚ አብሔር ጽድቅም በሥራ ስለታየ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው ሰው የሚጸድቀው በእምነት ነው» (ሮሜ:ም:1ቊ:17)።

«ስለዚህ ማንም በእግዚአብሔር ፊት የኦሪትን ሕግ በመፈጸም አይጸ ድቅም፤ ሕግ የሚያሳየው፥ ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን ነው» (ሮሜ: ም:3ቊ:20)።

«ስለዚህ እግዚአብሔር ሰውን የሚያጸድቀው፥ ሰው የሕግን ሥራ በመፈ ጸሙ ሳይሆን በእምነት መሆኑን እንገነዘባለን» (ሮሜ:ም:3ቊ:28)።

«አብርሃም በእግዚአብሔር ስላመነ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት» (ሮሜ:ም:4ቊ:3)።

«እንግዲህ እኛ ጽድቅን ያገኘነው በእምነት ስለሆነ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን» (ሮሜ:ም:5ቊ:1)።

«ሰው የሚጸድቀው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ የኦሪትን ሕግ በመፈጸም እንዳልሆነ እናውቃለን፤ እኛም ሕግን በመፈጸም ሳሆን በክርስቶስ በማመን እንድንጸድቅ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነናል፤ ማንም ሰው ሕግን በመፈጸም አይጸድቅም» (ገላ:ም:2ቊ:16)።

«ሰው የሚጸድቀው የኦሪትን ሕግ በመፈጸም ከሆነ ክርስቶስ የሞተው በከንቱ ነው ማለት ነው» (ገላ:ም:2ቊ:21)።

«በኦሪት ሕግ መጽሐፍ በተጻፉት ትእዛዞች ሁሉ ጸንቶ የማይኖርና የማይፈጽማቸው ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ስለተጻፈ ሕግን በመፈጸም እንጸድቃለን የሚሉ ሁሉ የተረገሙ ናቸው። ጻድቅ ሰው ግን በእምነት ሕይወትን ያገኛል ተብሎ ስለተጻፈ፥ ሕግን በመፈጸም ማንም ሰው በእግዚአብሔር ፊት እንደ ማይጸድቅ ግልጥ ነው። ሕግ በእምነት ላይ የተመሠረተ አይደለም፤ እንዲያውም ሰው በሕግ ሊኖር የሚችለው፥ የሕግ ትእዛዞችን ሁሉ ሲፈጽም ነው ተብሎ ተጽፎአል» (ገላ:ም:3ቍ:10–12)።

«እናንተ የዳናችሁት በእምነት አማካይነት በጸጋው ነው፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ በእናንተ ሥራ የተገኘ አይደለም። ማንም ሰው እንዳይመካ በሥራ የተገኘ አይደለም። እኛ፥ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካም ሥራዎች እንድንሠራ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እንደገና የተፈጠርን የእግዚአብሔር ፍጡሮች ነን» (ኤፌ: ም:2ቍ :8–10)።

ከላይ የተዘረዘሩትን ጥቅሶች ከሌሎች ጥቅሶች ጋር አገናዝበን ብንመለከታቸው እምነት የሕግ ፈጻሚነትንና የበጎ ተግባርን ግዴታ ያስወግዳል ማለት አይደለም። ሕግ ፈጻሚነትና በጎ ተግባር ለእምነት ድጋፍ የማይሰጡት ከሆነ እምነት ብቻውን ጠቀሜታ ሊኖረው አይችልም። በዚህም መሠረት ከላይ የተዘረዘሩት ጥቅሶች አጠቃላይ ሐሳባቸው ምን እንደሆነ ቀጥለን እንመልከት።

የመጀመሪያው አስተሳሰብ እምነት ሲባል በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ማመን ነው፤ በጌታችንም ማመን ማለት እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ፥ የሰውን ሥጋ በመልበሱ፥ በእኛ ቦታ ሆኖ ሕማማትን ተቀብሎና ሞቶ ከሞት ተነሥቶ ሞትን ድል ማድረጉ፤ በዚህም እኛን ከሞት ፍርድ ማዳኑ፤ ከዚያም ወደ ሰማያዊ ዙፋኑ ማረጉ፤ በመጨረሻውም ዘመን ለሁሉም እንደየሥራው ዋጋውን ለሚሰጥበት ፍርድ ወደዚህ ዓለም ተመልሶ የሚመጣ መሆኑንና እርሱም ለዘመኑ ፍጻሜ የሌለው ጌታ መሆኑን ማመን ማለት ነው። ታዲያ ይህ እምነት ብቻውን ለጽድቅ የሚያበቃ ነውን? አይደለም። ይህማ ቢሆን ኖሮ በሰዎች ዐድረው የነበሩ አጋንንት ብዙ ጊዜ የክርስቶስን ማንነት እየተናገሩ የመሰከሩ በመሆናቸው እነርሱም በዳኑ ነበር። ጌታችን ያስተማረው ምን ብሎ ነው? የሚከተሉትን ሁለት ጥቅሶች እንመልከት:-

«ወደ ሕይወት ለመግባት ብትፈልግ ተእዛዛትን ጠብቅ» (ማቴ : ም: 19ቍ:17)።

«የምትወዱኝ ከሆነ ትእዛዞቼን ጠብቁ» (ዮሐ:ም:14ቍ:15)።

ጌታችንም ሰለ ትእዛዞቹ መፈጸም እንዳስተማረው ሁሉ በእርሱ ማመን እንደሚገባም ገልጾአል።

«የእግዚአብሔር ሥራ እግዚአብሔር በላከው ማመን ነው» (ዮሐ: ም:6 ቍ:29)።



www.ethiopianorthodox.org

«ይህ የተጻፈው ኢየሱስ መሲሕ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንድ ታምኑና አምናችሁም በእርሱ ስም የዘለዓለምን ሕይወት እንድታገኙ ነው» (ዮሐ: ም: 20ቍ:31)።

ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ ወንጌላውያኑ ያስተማሩት በእርሱ እንድናምን፥ እንዲሁም ትእዛዛቱን እንድንፈጽም እንጂ ማመን ብቻ ይበቃል አላሉም። በዚህም መሠረት እምነትና ተግባር ለመዳን እኩል አስፈላጊ መሆናቸውን እንገነዘባለን።

ሐዋርያት በክርስቶስ ማመንን አጠናክረው የተናገሩበት ምክንያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሃይማኖታችን አመንጪና ፈጻሚ በመሆኑ ነው (ዕብ: ም:12ቍ:2)። ነቢያት አብዛኛውን ትንቢታቸውን የተናገሩት ስለ ክርስቶስ ነበር። ክርስቶስ ወደዚያ ዓለም በመጣ ጊዜ ያ ትንቢት ተፈጻሚ ሆነ ማለት ነው። ያ ትንቢት ደግሞ ተፈጻሚ መሆኑን ማመን የሃይማኖቱ ግዴታ ነው። ስለዚህም ነው በክርስቶስ ሳይታመን መዳን አይገኝም የተባለው።

በክርስቶስ የማመንን አስፈላጊነት በተመለከተ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን ይላሉ?

«ስለዚህ መዳን ከክርስቶስ በቀር በሌላ በማንም የለም፤ እኛ ልንድንበት የሚገባን እግዚብሔር ለሰዎች የሰጠው ስም ከእርሱ በቀር በመላው ዓለም ማንም የለም» (የሐ:ሥ:ም:4ቍ:12) ።

«ወደ ውጪም አወጣቸውና ‹ጌቶቼ ለመዳን ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው። እነርሱም በጌታ በኢየሱስ እመን፤ ትድናለህ፤ ቤተ ሰቦችህም ይድናሉ› አሉት» (የሐ:ሥ:ም:16ቍ:30–31)።

«ኢየሱስ ጌታ መሆኑን በአፍህ ብትመሰክርና እግዚአብሔር ከሞት እንዳስ ነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህ» (ሮሜ:ም:10ቍ:9)።

«ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በሚመሰክር ሰው ውስጥ እግዚ. አብሔር ይኖራል፤ እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል» (1ኛ: ዮሐ:ም: 4ቍ: 15)።

«ዓለምን የሚያሸንፍ ማነው? ዓለምን የሚያሸንፈው ኢየሱስ የእግዚአ ብሔር ልጅ መሆኑን የሚያምን ብቻ ነው» (1ኛ:ዮሐ:ም:5ቍ:5)።

«ኢየሱስ ወደቤት በገባ ጊዜ ዐይነ ስውሮቹ ወደ እርሱ ቀረቡ፤ ኢየሱስም እኔ ይህን ማድረግ እንደምችል ታምናላችሁን? አላቸው» (ማቴ: ም:9ቍ :28–29)።

«በወልድ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ በወልድ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖርበታል እንጂ ሕይወትን አያገኝም» (ዮሐ:ም:3ቍ:36)።

«ሰውዬውን ከምኵራብ እንዳስወጡት ኢየሱስ ሰማ፤ ባገኘውም ጊዜ በሰው ልጅ ታምናለህን? አለው። ሰውዬውም ጌታ ሆይ፥ በእርሱ እንዳምን እርሱ ማነው? አለ። ኢየሱስም መልሶ ገና ድሮ አይተኸዋል፤ አሁንም የሚያነጋግርህ እርሱ ነው አለው (ዮሐ:ም:9ቍ:35–37)።

«እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ የሚያምን እኔ የምሠራውን ሥራ ይሠራል፤ እንዲያውም ከዚያ የበለጠ ሥራ ይሠራል» (ዮሐ: ም14ቍ :12)።

ጌታም እምነት ብቻውን በቂ አለመሆኑን ለማመልከት ስለ እምነት ከተናገረ በኋላ:- «እኔን የሚወድደኝ ትእዛዜን የሚቀበልና በሥራ ላይ የሚያውለው ነው» ብሏል (ዮሐ:ም:14ቍ:21)።

ሁለተኛው አስተሳሰብ እምነት ሲባል እግዚአብሔር ከብዙ ችግር የሚጠብቅ፥ በቃል ኪዳኑ የሚጸናና ለጸሎትም መልስ የሚሰጥ መሆኑን መተማመን ማለት ነው። በዚህም መሠረት አብርሃም በሽምግልና ዕድሜው፥ ልጅ የመውለጃ ዕድሜዋ ዐልፎ ከነበረው ከሣራ ልጅ ይወለድልሃል ተብሎ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ተስፋ አምኖ መቀበሉ፥ ይህንኑ የሽምግልና ልጁን መሥዋዕት አድርጎ እንዲያቀርበው በታዘዘ ጊዜ እግዚአብሔር እንደሚያድንለት ስለተማመነ ትእዛዙን ያለ ቅሬታ መቀበሉና፥ ሌሎቹም ከእግዚአብሔር የተሰጡት የተስፋ ቃሎች ሁሉ እንደሚፈጽሙለት በእግዚአብሔር መታመኑ ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት። አብርሃም ጽድቅ ሆኖ የተቈጠረለት እምነቱ ብቻ ሳይሆን ታዛዥነቱም ጭምር ነው።

ሌላ ምሳሌ ደግሞ እመቤታችን ዘመድዋን ኤልሳቤጥን ለመጐብኘት በሄደች ጊዜ ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ «ከጌታ የተነገረላት እንደሚፈጸም ያመነችው የተባረከች ነች» ብላ እመቤታችንን አመሰግናለች። ይህንንም ያለችው እመቤታችን በድንግልና ያለወንድ ዘር ክርስቶስ ከእርስዋ እንደሚወለድ መልአኩ ባበሠራት ጊዜ እኔ የእግዚአብሔር ባሪያ ነኝ፤ እንደቃልህ ይሁንልኝ ብላ እምነትዋን በእግዚአብሔር ላይ በማሳረፍዋ ነው (ሉቃ: ም: 1ቍ: 45)።

ሦስተኛ አስተሳሰብ ሰው የሚድነው በእምነት ነው እንጂ የኦሪትን ሕግ በመፈጸም አይደለም በሚባልበት ጊዜ ለክርስቶስ በምሳሌነት ማለት በጥላነት ይቀርቡ የነበሩትን የአሠራር ሥርዓቶች እንጂ መላውን ሕግ ማለት አይደለም። የኦሪት ሕግጋት ለመዳን አይጠቅሙም የምንል ከሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠውን ማረጋገጫ ማስተባበላችን ይሆናል። ጌታችን በተራራ ላይ ከሰጠው ትምህርት መካከል እርሱ ሕግጋትን ሊፈጽም እንጂ ሊሽራቸው እንዳ ልመጣ ገልጦአል።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ላይ የተጠቀሰው የሐዋርያት ጉባኤ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት እንደ ግዝረት ያሉት ሥርዓቶች ግዴታዎች እንዳልሆኑ ተመልክቶአል። ግዝረትም የጥምቀት ምሳሌ ስለሆነ ለክርስትና ሃይማኖት



ግዴታ አይደለም። የእንስሳት መሥዋዕትም ለክርስቶስ ቤዛነት ጥላ ስለነበር በክርስቲያን ሃይማኖት ውስጥ ቦታ የለውም።

አራተኛው አስተሳሰብ ደግሞ ሰው በእምነት እንጂ ሕግን በመፈጸም አይጸድቅም በሚባልበት ጊዜ ሕግጋቱን ሙሉ በሙሉ ሊፈጽማቸው የሚችል ሰው የለም ለማለት ነው። ይህም ማለት ምንም እንኳ ሕግጋቱን ሙሉ ለሙሉ ለመፈጸም ባንችል እግዚአብሔር ጥረታችንን ተመልክቶ ይቅርታ እንደሚያደርግልን ብንተማመንበት ያ መተማመናችን ከጥረታችን ጋር ለማለት ነው እንጂ ምንም ሳያደርጉ እምነት ብቻ ማለት አይደለም። ይህማ ቢሆን ኖሮ ባለ ዐሥሩ ምናን በዐሥር አገር ላይ የመሾሙ፥ ባለ አምስቱ ምናን በአምስት አገር ላይ የመሾሙና ባለ አንዱ ምናን የመወቀሱ ምሳሌ ትርጉም ባልኖረውም ነበር (ሉቃ:ም:19ቍ:12–24)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሕግን ሁሉ መፈጸም የማይቻል መሆኑን ሲያመለክት እንዲህ ብሏል:-

«ሕግ መንፈሳዊ መሆኑን እናውቃለን፤ እኔ ግን የኃጢአት ባሪያ ለመሆን የተሸጥሁ ሥጋዊ ነኝ፤ የምወድደውን ነገር ማድረግ ትቼ የምጠላውን ነገር የማደርግ ስለሆነ እኔ የማደርገውን አላውቅም፤ ማድረግ የማልፈልገውን ነገር የሚያደርገው በእኔ ውስጥ ያለው ኃጢአት ነው እንጂ እኔ አይደለሁም። ምንም እንኳ መልካም ነገር የማድረግ ፍላጎት ቢኖረኝ ያን መልካም ነገር የማድረግ ችሎታ ስለሌለኝ በእኔ ሥጋዊ ባሕርይ ውስጥ ምንም መልካም ነገር እንደሌለ ዐውቃለሁ። ማድረግ የምፈልገውን መልካም ነገር አላደርግም፥ ነገር ግን የማልፈልገውን ክፉ ነገር አደርጋለሁ። እንግዲህ ማድረግ የማልፈልገውን ክፉ ነገር የማደርግ ከሆንኩ፥ ይህን የሚያርገው በእኔ ውስጥ ያለው ኃጢአት ነው እንጂ እኔ አይደለሁም ማለት ነው። እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ? ወደ ሞት ከሚወስደኝ ከዚህ ሰውነትስ ማን ያድነኛል?» (ሮሜ:ም: 7ቍ:14፥ 15፥ 17–20፥ 24)።

«ከሰው ባሕር ደካማነት የተነሣ ሕግ ሊያደርገው ያልቻለውን እግዚአብሔር አድርጎታል፤ የገዛ ልጁን በኃጢአተኛው ሥጋ ምሳሌነት ልኮ የኃጢአት መሥዋዕት ባደረገው በዚሁ በልጁ ሥጋ ኃጢአትን በፍርድ አስወገደ» (ሮሜ:ም:8ቍ:3)።

<u>በእምነት ብቻ የሚለው አስተሳሰብ ችግር</u>:- የሚዳነው ወይም ጽድቅ የሚገኘው በእምነት ብቻ ነው ብለው የሚያምኑት ወገኖች የሚከተሉትን ጉዳዮች ትክ ብለው ያስተዋሉአቸው አይመስልም።

አንደኛ/ ሰው የሚድነው ያለ ተግባር ወይም ያለ ሕግ ፈጻሚነት በእምነት ብቻ ከሆነ የእግዚአብሔር ትእዛዛትና ሕግጋት ዋጋ እንደሌላቸው መቍጠራቸው ነው። ምንም ዐይነት ከፍተኛ ኃጢአት ቢሠራ እምነት እስካለ ድረስ ይጸደቃል ማለት ነው። በዚህ አስተሳሰብ ሕግ ፈጻሚነት ወይም በጎ ተግባር ተጨማሪ ትሩፋት እንጂ ሌላ ጠቀሜታ ስለሌለው የሕግጋቱ መኖርም ሆነ



www.ethiopianorthodox.org

አለመኖር ምንም ልዩነት አያመጣም ማለት ነው። በሌላ አባባል ሕግን የሚንቅና ሕግን የሚፈጽም በአንድ ደረጃ መታየታቸው ነው። የሕጉ ባለቤት ራሱ ምን እንዳለ እንመልከት:-

«እኔ የምነግራችሁን አትፈጽሙም፤ ታዲያ ስለምን ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ እያላችሁ ትጠሩኛላችሁ? ወደ እኔ የሚመጣና ቃሌን ሰምቶ የሚፈጽም ማንን እንደሚመስል ልንገራችሁ፤ እርሱ በጥልቅ ቈፍሮ ቤቱን በአለት ላይ የመሠረተውን ሰው ይመስላል፤ ጐርፍ መጥቶ ያን ቤተ ገፋው፤ ነገር ግን በጽኑ መሠረት ላይ ስለተሠራ ሊያነቃንቀው አልቻለም። ቃሌን ሰምቶ የማይፈጽም ግን ያለ መሠረት በምድር ላይ ቤቱን የሠራ ሰውን ይመስላል፤ ጐርፍ መጥቶ ያን ቤት በገፋው ጊዜ ወዲያውኑ ወደቀ፤ አወዳደቁም እጅግ ታላቅ ሆነ» (ሉቃ: ም 6 ቊ:46–49)።

ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ሕግጋት ምን እንደሚሉ ቀጥለን እንመልከት:-

«ለሚፈጽመው ሁሉ ሕይወት የሚያስገኝለትን ትእዛዜን ሰጠኋቸው፤ ሕግጋቴንም አስተማርኋቸው» (ሕዝ:ም:20ቊ:11)።

«በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም» (ማቴ: ም:7 ቊ: 21)።

«ወደ ሕይወት ልትገባ ብትፈልግ ትእዛዛትን ጠብቅ» (ማቴ: ም:19 ቊ:17)።

«ሕግ ቅዱስ ነው፤ ትእዛዝም ቅዱስና እውነት፥ መልካምም ነው» (ሮሜ:ም:7ቊ:12)።

«ሕግን የሚፈጽም በሕግ ሊኖር ይችላል» (ገላ:ም:3ቊ:2)።

«ሰው በሚገባ ከሠራበት ሕግ መልካም መሆኑን እናውቃለን» (1ኛ: ጢሞ:ም:1ቊ:8)።

እንግዲህ ስለ ሕግና ትእዛዛት ፈጻሚነት ቅዱሳት መጻሕፍት እነዚህን አባባሎች የሚያቀርቡ ከሆነ መዳን የሚገኘው በእምነት ብቻ ነው ማለት ምን ማለት ነው?

ሁለተኛ (የሚዳነው ወይም ጽድቅ የሚገኘው በሕግ ፈጻሚነትና በበጎ ተግባር ሳይሆን በእምነት ብቻ ነው በሚባለበት ጊዜ የእግዚአብሔርን የበጎ ተግባር ፈጹምነት መካድ ነው። አባባሉ እኔ ፍጹም እንደሆንኩ እናንተም ፍጹማን ሁኑ የሚለውን የእግዚአብሔርን የበጎ ተግባር ፍጹምነት ይቃወማል። በጎ ወይም ክፉ ተግባራቸውን ሳይመለከት እግዚአብሔር በእምነታቸው ብቻ የሚያድናቸው ከሆነ እግዚአብሔር ፍጹምና ቅዱስ ነው የሚባለው እንዴት ነው? እንደ እርሱ ፍጹምና ቅዱስ የምንሆነውስ እንዴት ነው? ስለዚህስ ጉዳይ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን ይላሉ?



«እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ፤ እኔ ቅዱስ ስለሆንኩ እናንተም ራሳችሁን የተቀደሰ አድርጉ» (ዘሌ:ም:11ቊ:44)።

እርሱ ምሽጋችን ነው፤ ሥራዎቹም ፍጹሞች ናቸው፤ መንገዶቹም ሁሉ የቀኑ ናቸው፤ የማይሳሳት ታማኝ አምላክ፥ እርሱም ቀጥተኛና እውነተኛ ነው» (ዘዳ:ም32ቊ:4)።

«የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹሞች ሁኑ» (ማቴ:ም :5ቊ:48)።

«የጠራችሁ እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ በኑሮአችሁ ቅዱሳን ሁኑ፤ እኔ ቅዱስ ስለሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ተጽፎአል» (1ኛ: ጴጥ: ም:1ቊ:15–16)።

ሐዋርያው ጴጥሮስ በኑሮአችሁ እንደ ጠራችሁ እንደ እግዚአብሔር ቅዱሳን ሁኑ ካለ በኋላ ምን መደረግ እንዳለበት በጎ ተግባሮችን ይዘረዝራል። ራሳችሁን ቅዱሳን አድርጉ፤ ፍጹሞች ሁኑ፤ ማለት ከክፉ ተግባር ርቃችሁ በጎ ተግባርን ተከተሉ ማለት እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። እንደ ቸርነት፥ መሐሪነት፥ ርኅርኄ፥ ፍቅር፥ ቀጥተኛነትና እነዚህን የመሳሰሉ በጎ ተግባሮች የእግዚአብሔር ገንዘቦች እንደመሆናቸው እኛም የታዘዝነው እነዚህን ተግባሮች በመፈጸም እግዚአብሔርን እንድንመስል ነው።

ሦስተኛ/የምንድነው ወይም የምንጸድቀው በእምነት ነው እንጂ በሕግ ፈጻሚነት ወይም በበጎ ተግባር አይደለም በሚባልበት ጊዜ በሥራችን፥ በአነጋገራችንና እንዲያውም በአስተሳሰባችን ፍርድ የሚሰጥበትን የእግዚአብሔርን የፍርድ መመዘኛ እንደመቃወም ይቈጠራል። ቅዱሳት መጻሕፍት ምን እንደሚሉ ቀጥለን እንመልከት:-

«የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ሆኖ ከመላእክቱ ጋር ይመጣል፤ በዚያን ጊዜ ለያንዳንዱ እንደየሥራው ዋጋውን ይከፍለዋል» (ማቴ:ም:16ቊ:27)።

«እግዚአብሔር ለያንዳንዱ እንደየሥራው ስለሚሰጠው አንተ ንስሓ ባለመግባትህና እልኸኛ በመሆንህ የእግዚብሔር ቍጣና ትክክለኛ ፍርድ በሚገለጥበት ቀን ቅጣትህ እንዲበዛ ታደርጋለህ። በመልካም ሥራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርን፥ የማይጠፋ ሕይወትንም ለሚፈልጉ እግዚአብሔር የዘለዓለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል። ነገር ግን የራሳቸውን ጥቅም በሚፈልጉ ዐመፀኞች በሆኑትና ትክክለኛ የሆነውን መልካም ነገር ትተው ክፋትን በሚከተሉት ላይ የእግዚአብሔር ቍጣና መቅሠፍት ይመጣባቸዋል» (ሮሜ: ም: 2ቊ : 5–10)።

«ሁላችንም በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለን» (ሮሜ: ም:14ቊ:10)።



www.ethiopianorthodox.org

እያንዳንዱ በምድራዊ ሕይወቱ ላደረገው ክፉ... ሆነ ደግ ነገር እንደየ ሥራው ዋጋውን ለመቀበል ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት መቅረብ አለበን» (2ኛ:ቆር:ም:5ቊ:10)።

«ሰው ሁሉ የሚያጭደው የዘራውን ስለሆነ በእግዚአብሔር ላይ መቀለድ አይቻልምና ራሳችሁን አታታልሉ። ሥጋውን ለማስደሰት የሚዘራ፥ ከሥጋው ሞትን ያጭዳል፤ መንፈስን ለማስደሰት የሚዘራ ከመንፈስ የዘለዓለም ሕይወትን ያጭዳል» (ገላ:ም:6ቊ:7–8)።

«አገልጋይም ሆነ ጌታ፥ እያንዳንዱ በሠራው መልካም ሥራ ከጌታ ኢየሱስ ዋጋውን የሚቀበል መሆኑን ታውቃላችሁ» (ኤፌ:ም:6ቊ:8)።

«እነሆ፥ እኔ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለያንዳንዱ እንደ ሥራው የምሰጠውን ዋጋ ይዤለሁ» (ራ:ዮሐ ም:22ቊ:12)።

ከላይ በዝርዝር የቀረቡት ጥቅሶች እንደሚያመለክቱት ሰው ሁሉ የሚፈረድለት ወይም የሚፈረድበት፥ ማለት የሚጸድቀው ወይም የሚኰነነው በዚህ ዓለም በሚኖርባቸው ዘመናት በሚፈጽመው ተግባር ነው። እነዚህም ተግባሮች እርሱን ለማጽደቅ የእግዚአብሔር የፍርድ መመዘኛ መሆናቸው ግልጽ ነው።

አራተኛ/ ሰው የሚድነው ወይም የሚጸድቀው በእምነት ብቻ ነው እንጂ በሕግ ፈጻሚነት ወይም በበጎ ተግባር አይደለም ብሎ ማመን እግዚአብሔር የጥፈት ዋጋችንን የሚረሳና የማይከፍል ግፈኛ እንደሆነ አድርጎ ማቅረብ ነው። ስለዚህ ጉዳይ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን ይላሉ?

«በእውነት እላችኋለሁ፤ የእኔ ደቀ መዝሙር በመሆኑ ከእነዚህ ታናናሾች ለአንዱ አንድ ብርጭቆ ቀዝቃዛ ውሃ የሚሰጥ ሰው ዋጋውን አያጣም» (ማቴ:ም:10ቊ:42)።

«በፊትም ሆነ አሁን ቅዱሳንን በመርዳት ያደረጋችሁት ሥራና ስለ ስሙም ያሳያችሁት ፍቅር አይረሳም» (ዕብ:ም:6ቊ:10)።

«ለስጦታዎችህ ሁሉ የፈገግታ ገጽታ አክልባቸው፤ የዐሥራት ግዴታህንም ደስ ብሎህ ክፈል፤ ጌታ መልካም ውለታ ከፋይ ስለሆነ ሰባት ጊዜ አስበልጦ ይከፍልሃልና፤ አስቀድሞ ለሰጠህ ለልዑል እግዚአብሔር ዐቅምህ በሚችለው መጠን በልግስና ስጥ» (ሢራክ ም: 35ቊ:9–11)።

ብዙ ደጋግ ሰዎች በጎ ተግባርን የሚያከናውኑት ለሰው ሁሉ የበጎ ተግባርን ዋጋ የሚከፍል አምላክ መኖሩን ስላመኑ ነው እንጂ ያለምክንያት አይደለም። መነኵሴ ከዓለም ተለይቶ በገዳም መወሰኑ፥ ባሕታዊ የብቸኝነትን ኑሮ መምረጡ፥ ሌላው ሰው ደግሞ በገንዘቡ የበጎ አድራጎት ሥራ ማካሄዱ ሁሉም ከእግዚአብሔር ዋጋ እናገኛለን ብለው በመተማመን ነው። እግዚአብሔርም በቅዱሳት መጻሕፍቱ አማካይነት የማንንም ዋጋ እንደማያስቀር በተለያዩ ሁናቴዎች ገልጾአል።



www.ethiopianorthodox.org

ለምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ስለ እኔ ብሎ ቤቶችን፥ ወይም ወንድሞችን፥ ወይም እኅቶችን፥ ወይም አባትን፥ ወይም እናትን፥ ወይም ልጆችን፥ ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል፤ የዘለዓለም ሕይወትንም ያገኛል» ብሏል። (ማቴ:ም:19ቊ:29)።

አምስተኛ/ እግዚአብሔር ሰውን የሚያድነው ወይም ሚያጸድቀው በእምነቱ ነው እንጂ በተግባሩ አይደለም በሚባልበት ጊዜ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈውን ቅዱስ መጽሐፍ እንደመቃወም ይቈጠራል። ይህን ጉዳይ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በማያሻማና ግልጥ በሆነ ቋንቋ ሲያቀርበው እንዲህ ብሏል።

«ወንድሞቼ ሆይ፥ ሰው እምነት አለኝ ቢል፥ ነገር ግን እምነቱን በመልካም ሥራ ባይገልጥ ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን? ለምሳሌ የሚለብሱትና የሚመገቡት የሌላቸው ወንድሞችና እኅቶች ቢኖሩ፥ ከእናንተ አንዱ፥ ለኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሳይሰጣቸው በሰላም ሂዱ ይሙቃችሁ፤ ጥገቡ» ቢላቸው ምን ይጠቅማቸዋል? ከመልካም ሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።

ነገር ግን አንተ እምነት አለኝ ብለህ ብትመካ፥ እኔ መልካም ሥራ አለኝ የሚል ቢኖር፥ እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳየኝ፤ እኔም በሥራዬ እምነቴን አሳይሃለሁ እለዋለሁ። አንተ አንድ እግዚአብሔር አለ ብለህ ታምናለህ፤ ይህም መልካም ነው፤ ማመንማ አጋንንትም ያምናሉ፤ በፍርሃትም ይንቀጠቀጣሉ። አንተ ሞኝ ከሥራ የተለየ እምነት ፍሬቢስ መሆኑን ታያለህን? አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንዲሆን ባቀረበው ጊዜ፥ በሥራ አልጸደቀምን? ስለዚህ እምነቱ ከሥራው ጋር አብሮ እንደነበርና እምነቱም በሥራ ፍጹም እንደሆነ ታያለህን? በመጽሐፍም አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ እምነቱም ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት የተባለው ቃል ተፈጸመ፤ በዚህ ሁኔታ አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ተባለ። እንግዲህ ሰው የሚጸድቀው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራም ጭምር መሆኑን ታያለህ።

አመንዝራይቱ ረዓብ የእስራኤልን መልእክተኞች በቤትዋ በተቀበለች ጊዜና በሌላም መንገድ እንዲሄዱ ባደረገቻቸው ጊዜ እርስዋስ በሥራዋ ጸድቃ የለምን?

ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ ነው፤ እንዲሁም ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው» (ያዕ:ም:2ቊ:14–26)።

እምነት ያለ በጎ ተግባር ዋጋ እንደሌለው ከዚህ የበለጠ የሚያረጋግጥና ግልጽ የሆነ ማስረጃ ሊኖር አይችልም።

የምንድነው በእምነት ብቻ ነው ብለው የሚከራከሩት ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ማስረጃ ብለው የሚያቀርቡት ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክቶች ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ግን ስለ እምነት በሚናገርበት ጊዜ ቀደም ተብለው

በቀረቡት የእምነት ትርጉሞች እንጂ ተከራካሪዎቹ እንደሚሉት አይደለም። ይህማ ቢሆን ኖሮ ቀጥለው የተመለከቱትን ማረጋገጫዎች ባላቀረበም ነበር።

«በእግዚአብሔር ፊት የሚጸድቁ ሕጉን ሰምተው በሥራ ላይ የሚያውሉት ናቸው እንጂ ሕጉን ሰምተው በሥራ ላይ የማያውሉት አይደሉም» (ሮሜ: ም:2ቍ:13)።

«በሰዎች ወይም በመላእክት ቋንቋ የመናገር ችሎታ ቢኖረኝ እንኳ ፍቅር ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስና እንደሚንሿሿ ጸናጽል መሆኔ ነው። ትንቢት የመናገር ችሎታ ቢኖረኝና ምሥጢርንም ሁሉ ብረዳ፥ ዕውቀትም ሁሉ ቢኖረኝ፥ ተራራን ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ የሚያዛውር እምነትም ሁሉ ቢኖረኝ፥ ፍቅር ከሌለኝ ከንቱ ነኝ» (1ኛ:ቆሮ:ም:13ቍ:1–2)።

እንዲሁም ስለራሱ የተግባር ግዴታ ሲናገር:- «የምሥራቹን ቃል ማብሠር ግዴታዬ ስለሆነ የምመካበት ነገር አይደለም፤ እንዲያውም የምሥራቹን ቃል ሳላበሥር ብቀር ወዮልኝ» ብሏል (1ኛ: ቆሮ:ም9: ቍ:16)። ይህን ግዴታውን ከተወጣ በኋላ ነው የሚከተለውን መግለጫ የሰጠው:-

«ጦርነትን በመልካም ተዋግቼአለሁ፤ ሩጫን እስከ መጨረሻው ሮጫለሁ፤ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ። ከእንግዲህ ወዲህ የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶ ይጠብቀኛል፤ ይህን አክሊል ትክክለኛ ፍርድ ፈራጁ ጌታ በዚያን ቀን ይሰጠኛል፤ የሚሰጠውም ለእኔ ብቻ ሳይሆን የእርሱን መገለጥ ለሚናፍቁ ሁሉ ነው» (2ኛ:ጢሞ:ም:4ቍ:7–8)።

በእነዚህም ሁሉ የተለያዩ ማስረጃዎች መሠረት መዳን ወይም መጽደቅ የምንችለው በእምነትና በተግባር መሆኑን ተገንዝበን የምንድነው በእምነት ብቻ ነው ከሚለው የተሳሳተ አስተሳሰብ እንጠንቀቅ።

## ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ሰውን የሚቀጣው እንደምን ሆኖ ነው?
2. የእግዚአብሔር ቅጣቶች በአጠቃላይ ስንት ናቸው?
3. የእግዚአብሔር ጊዜያዊ ቅጣቶች ምን ምን ናቸው?
4. ለእግዚአብሔር ከባድ ቅጣት ምሳሌ ሆኖ የተጠቀሰው ማነው?
5. እግዚአብሔር በመጀመሪያው ከፍተኛ ቅጣትን የማያመጣው በምን ምክንያት ነው?
6. በግብጽ ሕዝብ ላይ የደረሱት ቅጣቶች ስንት ዐላማዎች አሉአቸው? እነርሱስ እነማን ናቸው?
7. የእግዚአብሔርን ክብር የተዳፈረው የአሦር ንጉሥ ስም ማን ነበር?
8. በእርሱ ጊዜስ የነበረው የይሁዳ ንጉሥ ስም ማን ነበር?
9. እግዚአብሔር በአሦር ንጉሥ ላይ ክብሩን የገለጠው እንደምን አድርጎ ነው?
10. እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ማስጠንቀቂያ እንዲሆን ከሚሰጥባቸው ቅጣቶች መካከል አንድ ምሳሌ ስጥ።
11. እግዚአብሔር ሰውን በዘለዓለማዊ ቅጣት የሚቀጣው በምን ምክንያት ነው?
12. ስለ እምነትና ተግባር የቤተ ክርስቲያን እምነት ምን የሚል ነው?
13. ሌሎች ወገኖችስ ምን ይላሉ?
14. እምነት ሲባል በስንት ዐይነት አስተሳሰብ ይከፈላል? እነርሱስ ምን ምን ናቸው?
15. በእግዚአብሔር የመተማመንን ምሳሌ ተናገር።
16. የኢየሩሳሌሙ የሐዋርያት ጉባኤ ባሳለፈው ውሳኔ እንዴት ያለውን የኦሪት ሥርዓት ሻረ?
17. የመጥምቁ ዮሐንስ እናት ኤልሳቤጥ ድንግል ማርያምን ምን ብላ አመሰገነቻት?
18. ሰው በእምነት ብቻ ይጸድቃል የሚለው አስተሳሰብ ስንት ዐይነት ችግሮች አሉበት?
19. እነርሱስ ምን ምን ናቸው?

## ብሉይ ኪዳን

<u>መልከጼዴቅ</u>:- መልከጼዴቅ ማነው? ከአዳም ልጆች አንድ ሰው ነውን? አባት፥ እናትና የዘር ሐረግ የለውም መባሉ ምን ለማለት ነው? (ዕብ: ም:7:ቍ:3)።

ለዘመኑ መጀመሪያና ለሕይወቱ መጨረሻ የለውም ማለት ምን ማለት ነው? አንዳንዶች እንደሚሉት እርሱ ዘለዓለማዊ ነውን? እርሱ ክርስቶስ ነውን? ወይስ የክርስቶስ ምሳሌ? እርሱ ሰው ነውን? ወይስ እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት ሁኔታ? እርሱ እግዚአብሔር ነው ብለን ለማመን እንችላለንን? የቤተ ክርስቲያንስ አቋም እንዴት ነው? በመልከጼዴቅ የሹመት ሥርዓት አንተ ለዘለዓለም ካህን ትሆናለህ ተብሎ የተነገረው ምን ለማለት ነው (መዝ:110ቍ:4)።

መልከጼዴቅ በአብርሃም ዘመን የነበረ አንድ ሰው ለመሆኑ እርግጠኞች እንሁን። መጽሐፍ እንደሚለው እርሱ የልዑል እግዚአብሔር ካህንና የሳሌም ንጉሥ ነበር። አብርሃም ዶርላዖሜርና ከእነርሱ ጋር አብረው የነበሩትን ነገሥታት ድል አድርጎ ሲመለስ በምርኮ ካገኘው ሀብት ሁሉ ዐሥራት ሰጠው፤


www.ethiopianorthodox.org

መልከጼዴቅም ኅብስትና የወይን ጠጅ ለአብርሃም አመጣለት ተብሎአል (ዘፍ:ም:14ቍ:17–20)።



ምልከ ጼዴት

መጽሐፉ ግን ስለ ክህነቱና ንጉሥ ስለመሆኑ ምልክት ከመስጠቱ በቀር ስለ መልከጼዴቅ ሌላ የተናረው ነገር የለም።

በኦሪት ዘፍጥረት ም:14 ላይ የልዑል እግዚአብሔር ካህን መሆኑ ተገልጦአል። አንዳንድ የካህናት ተግባሮችንም በሥራ ላይ በማዋል አብርሃምን ባረከው፤ ከአብርሃምም ዐሥራት ተቀበለ፤ የሐዲስ ኪዳን ክህነት ምልክት የሆነውን ኅብስትና ወይን ይዞ መጣ።

በመዝሙር 110 ቍ:4 ላይ እግዚአብሔር በመልከጼዴቅ የክህነት ሥርዓት አንተ ለዘለዓለም ካህን ትሆናለህ ተብሎ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረውን የክህነት ትንቢት የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ቃል በቃል ጠቅሶታል (ዕብ:ም:5ቍ:6)።

ይህንንም አባባል በመድገም:- «ወደዚህም መቅደስ ኢየሱስ በመልከጼዴቅ የክህነት ሹመት ለዘለዓለም ሊቀካህናት ሆኖ ስለ እኛ ቀድሞ ገብቶአል» ብሎ አል።

በዕብራውያን መልእክት ም:7ላይ የመልከጼዴቅን ክህነት መሠረት በማድረግ እንዴት የእርሱ ክህነት ከአሮን ክህነት እንደሚበልጥና ይህም ክህነት የክርስቶስን ክህነት የሚመስል እንደመሆኑ የክርስቶስን ክህነት ታላቅነት አመልክቶአል። «በመልከጼዴቅ የክህነት ሥርዓት አንተ ለዘለዓለም ካህን ነህ» የሚለውን አባባል ከአንድ ጊዜ በላይ ደጋግሞታል (ዕብ: ም7: ቍ: 11፥ 15፥ 17፥ 21)።

ሁሉም ነገር በመልከጼዴቅ ክህነት ላይ መሠረት የተደረገው ለምንድነው?



መልእክቱ የተጻፈው ለዕብራውያን እንደመሆኑና ዕብራውያን ደግሞ የሚ ምኑት በአሮን ክህነት ስለሆነ ካህን የሚሆን ሰው የግድ ከአሮን ዘር መሆ ነበረበት። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተወለደው ከአሮን ዘር አልነ ረም። እንዲያውም ከሌዊ ነገድ እንኳ አልነበረም። እርሱ ግን የዳዊት ዘርና ከሁዳ ነገድ ነበር።

ታዲያ፥ የዕብራውያኑ መልእክት ጸሐፊ የክርስቶስን ክህነት የሚያረ ጋግጠው እንዴት ነው?

ክህነቱን ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም የክርስቶስ ክህነት ከአሮን ክህነት የሚበልጥ መሆኑን የሚያረጋግጠው በኦሪት ዘፍጥረት ም:14 እና በመዝሙር 110 የተነገሩትን ማስረጃዎች በማቅረብ ነው። ማስረጃዎቹም መልከ ጼዴቅና ክህነቱ ናቸው።

የመልከጼዴቅ ክህነት የክርስቶስን ክህነት የሚያረጋግጥ ሲሆን፥ እርሱም ከአሮን ክህነት የላቀ ነው።

ይህም የሆነበት ምክንያት መልከጼዴቅ የአባቶች አባት የሆነውን አብርሃምን በመባረኩ ነው። ይህንንም በሚያደርግበት ጊዜ የሌዊ፥ የያዕቆብ፥ የይስሐቅ፥ የአብርሃም ልጅ የሆነውን አሮንን መባረኩ ነው። ይህም ማለት የአሮን ክህነት ተባረከ ማለት ነው። የሚባርክ ከሚባረከው ታላቅ መሆኑ ግልጽ ነው (ዕብ:ም:7ቍ:7፥10)።

ከዚያም በላይ አብርሃም ለመልከጼዴቅ ዐሥራት ሰጥቶታል። ይህም ለመልከጼዴቅ ክህነት ከአሮን ክህነት ታላቅነት ሌላ ማስረጃ ነው።

እዚህ ላይ የዕብራውያኑ መልእክት የመልከጼዴቅን ክህነት ምንጭ ይገል ጣል። ምን አለ?

መልከጼዴቅ አባት፥ እናት፥ የዘር ሐረግ የሌለው ነው ይላል። ይህ አባባል ምን ማለት ነው? እንዴትስ እንረዳዋለን? ይህስ ጉዳይ ከክርስቶስ ጋር ያለው ግንኙት እንዴት ነው? መልከጼዴቅስ በእነዚያ ለእርሱ በተሰጡት መግለ ጫዎች ክርስቶስን የሚመስለው እንዴት ነው?

ክርስቶስ አባት የለውምን? እግዚአብሔር አብ ያለ እናት የባሕርይ አባት ነው። እናት የለውምን? ድንግል ማርያም በሥጋ እናቱ ነች።

የዘር ሐረግ የለውምን? በማቴዎስ ወንጌል ም:1 እና በሉቃስ ወንጌል ም:3 በሥጋ የዘር ሐረጉ ተዘርዝሮአል።

ታዲያ፥ አባት፥ እናት፥ የዘር ሐረግ የለውም፤ የእግዚአብሔር ልጅን ይመስላል የተባለው እንዴት ነው?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አሮን ልጆች ክህነትን በሥጋ ውርስ የወረሰው አይደለም። ክህነትን ለመውረስ አባት፥ እናት፥ የዘር ሐረግ የለ ውም።

www.ethiopianorthodox.org

ይህም ማለት እርሱ ከይሁዳ ነገድ በመሆኑ ክህነትን ለመውረስ ካህን የሆነ አባት፥ ከካህናት ወገን የሆነች እናት፥ ወይም ከካህናት ወገን መሆኑን ለማሳየት የሚዘረዝረው የዘር ሐረግ የለውም።

እርሱ ግን ሌላ ዐይነት ክህነት አለው። ምን ዐይነት? መጽሐፈ መዝሙር 110 ቍ: 4 ላይ:- «እግዚአብሔር በመልከጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘለዓለም ካህን ትሆናለህ ብሎ ማለ፤ መሐላውም የማይሻር ነው» ተብሎአል። የመልከ ጼዴቅ ክህነት ምንድነው?

መልከጼዴቅ በክህነቱ አባት፥ እናት፥ ወይም የዘር ሐረግ የለውም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ልጅ ይመስላል።

መጽሐፉ ለመልከጼዴቅ ካህን የሆነ አባት፥ ከካህናት ወገን የሆነች እናት፥ ወይም የካህናት የዘር ሐረግ የለውም፤ እንዲያውም ምንም ስለ እርሱ የተነገረ ነገር የለም ሲል ምን ማለቱ ነው?

መልከጼዴቅ ድንገት በታሪክ ውስጥ ብቅ አለ። በኦሪት ዘፍጥረት ስለ መልከጼዴቅ ሲነገር ከወዴት እንደሆነ የተወለደበትን ጊዜ፥ ከማንኛው ቤተሰብ እንደተወለደ አልተነገረም። አባት አብርሃምን ከተገናኘ በኋላ ምን እንደሆነ፥ ወይም ምን እንዳደረገ፥ የሕይወቱስ ፍጻሜ እንዴት እንደሆነ አልተገለጠም። በዚህም ምክንያት ነው በዕብራውያን መልእክት ውስጥ «ለዘመኑ መጀመሪያና መጨረሻ የለውም» የተባለው (ዕብ:ም:7ቍ:3)።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዕብራይውያን መልእክት ትርጓሜው:- «እኛ የምናውቀው ማለት በመጽሐፍ ውስጥ የተመዘገበ መጀመሪያ የለውም፤ በዚሁም ዐይነት መጨረሻ የለውም የሚለውን አባባል እንረዳ» ብሎአል።

ይህም ማለት በፍጹም መጀመሪያ የለውም ማለት ሳይሆን የተመዘገበ ወይም የታወቀ ቀን የለም ማለት ነው። ነገር ግን የተመዘገበ ቀን ባለመኖሩና ባለመታወቁ አንዳንድ ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር ነው የሚሉት አስተሳሰብ ተቀባይነት ያለው አይደለም። ይህንንም አባባል ከቅዱሳን አንዳቸው እንኳ አልተናገረውም። ምናልባት ይህ አስተሳሰብ ፊሎ ከተባለው ፈላስፋ የተወሰደ ሊሆን ይችላል። የፊሎ አስተሳሰብ መልከጼዴቅ ሰው ነው ከሚለው ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አተረጓጎም ተቃራኒ ነው።

አይሁድ ይጠብቁት የነበረው መሲሕ ወይም መሳያ የዳዊት ዘር ሆኖ ከይሁዳ ነገድ የሚመጣ ንጉሥ ነበር። ከካህናት ነገድም ስላይደለ ካህን ይሆናል የሚል አስተሳሰብ በፍጹም አልነበራቸውም። የዕብራውያኑ መልእክት ያን ሁናቴ አስታወሳቸው። ያስታወሳቸውም መልከጼዴቅ ንጉሥና ካህን መሆኑን ነው።

ንጉሥነቱ ካህን መሆንን ስላልከለከለ የልዑል እግዚአብሔር ካህንና የሳሌም ንጉሥ ነበር ተብሎአል። በዚህም መሠረት የእርሱ ክህነት ከማንኛውም ነገድ ጋር የተያያዘ አልነበረም። ነገር ግን አባት፥ እናትና የዘር ሐረግ ያልነበረው በመሆኑ ለክርስቶስ ምሳሌ ነበር።



www.ethiopianorthodox.org

የዕብራውያኑ መልእክት የዘር ሐረግ እንደሌለው በሚገልጥበት ጊ... የዘረዘረው ከካህናቱ ዘር ከሌዊ ነገድ ጋር ምንም ግንኙት የሌለው መልከጼዴ... የሌዊ ቅድመ አያትና ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የተገባለትን አብርሃምን ባረከው ብሎአል (ዕብ:7፥6)።

የካህናት ዘር መሆኑን ለማረጋገጥ የማይችል ሰው የክህነት አገልግሎት እንዲያካሄድ አይፈቀድለትም ነበር። ይህም ሁናቴ በዕዝራና በነህምያ ዘመን ተከሥቶአል። የበርዚላይ ልጆች ከካህናት ዘር መሆናቸው በዘር ሐረጋቸው ሊያረጋግጡ ስላልቻሉ ከክህነት አገልግሎት ተከልክለዋል (ዕዝ:ም:2ቍ:62 እና ነህ ም:7:ቍ:64)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የአሮን የክህነት ዘር ሐረግ የለውም። የዕብራውያኑ መልእክት መልከጼዴቅም እንደዚሁ የዘር ሐረግ የለውም ይላል።

በክህነቱ አባት፥ ወይም እናት የሌለው ከመሆኑ ጋር የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነው ተብሎአል (ዘፍ:ም:14ቍ:18፥ዕብ:ም:7ቍ:1)። በዚህም መሠረት የአሮን ዘር ሳይሆን አንድ ሰው ካህን ለመሆን ይችላል ማለት ነው። የመል ከጼዴቅንም ክህነት ልዩ የሚያደርገው ያለ ውርስ፥ ማለት ያለ አባት፥ ያለ ናትና ያለ ዘር ሐረግ መሆኑ ነው።

መልከጼዴቅ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር። ነገር ግን እርሱ ክርስቶስ አልነበረም፤ ወይም በዘመነ ብሉይ ወልደ እግዚአብሔር ከተገለጠባቸው ሁናቴዎች አንዱ አልነበረም።

. መልከጼዴቅ በክህነቱ የክርስቶሰ ምሳሌ ነበር (መዝ:110ቍ:4)። ይህም ክህነት በውርስ አልነበረም፤ ክህነቱም ከአሮን ክህነት የላቀ ነበር። ይህ ክህነት የሚያቀርበው የእንስሳትን መሥዋዕት ሳይሆን ኅብስትንና ወይንን ነበር። እርሱም ለንጉሥነትና ለክህነት ምሳሌ ነበር። ነገር ግን ምሳሌ ነበር እንጂ ራሱ ክርስቶስ አልነበረም።

ብዙዎች ለክርስቶስ ምሳሌ ሆነዋል። እነርሱ ራሳቸው ግን ክርስቶስ አልነበሩም።

ይስሐቅ በአንድያ ልጅነቱ ለክርስቶስ ምሳሌ ነበር፤ በወንድሞቹ ስለተሸጠ ዮሴፍ የክርስቶሰ ምሳሌ ነበር፤ ሰሎሞን በጥበበኛነቱ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር። ነገር ግን ከእነዚህ አንዳቸው እንኳ ራሱ ክርስቶስ አይደለም።

አንዳንድ ሰዎች በስሙ ትርጕምና በሥራው ምክንያት ክርስቶስ መሰላቸው።

መልከጼዴቅ ማለት የጽድቅ ንጉሥ ማለት ስለሆነ በእርግጥም በስሙ የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ክርስቶስ የጽድቅ ንጉሥ ነው። በሥራውም የሳሌም ንጉሥ መባሉ የሰላም ንጉሥ ማለት ስለሆነ በእርግጥ ክርስቶስ የሰላም ንጉሥ ነው።

የስሞች ትርጉም ማስረጃ ሊሆን አይችልም። ብዙዎች ሰሞች ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ እነዚያ ትርጉሞች ግን የስሙን ባለቤት ሁናቴ የሚያመለክቱ አይደሉም። ለምሳሌ ኢሳይያስ ማለት እግዚአብሔር ያድናል ማለት ሲሆን የዚያ ስም ባለቤት የሚያድን አምላክ ነው ማለት አይደለም፤ ኢያሱ ማለት አዳኙ ያህዌ ማለት ሲሆን የስሙ ባለቤት ያህዌ ነው ማለት አይደለም፤ ዳንኤል ማለት እግዚአብሔር ፈራጅ ነው ማለት ሲሆን ዳንኤል የተባለው ሰው ፈራጁ እግዚአብሔር ነው ማለት አይደለም። እንዲሁም ሳሙኤል ማለት የእግዚአ ብሔር ስም ነው፤ እስማኤል ማለት እግዚአብሔር ይሰማል ማለት ነው። እነዚህ ሁሉ ስሞች ለባለቤቶቻቸው የሰጡት አንዳችም የመለኮታዊ ክብር የለም። ከእነዚህም ሌላ ኢዮአብ ማለት አባት እግዚአብሔር ማለት ነው፤ ኢዩኤል ማለት ያህዌ አምላክ ነው ማለት ነው። የእነዚህ ስሞች ትርጉሞች ሁሉ በተግባር የተገለጡ ናቸው ማለት አይደለም። እንደገናም ዮሐንስ ማለት እግዚአብሔር ርኅሩኅ ነው ማለት ነው፤ ይሁን እንጂ ዮሐንስ ርኅሩኅ አምላክ ነው ማለት አይደለም።

በዚህም ዐይነት የመልከጼዴቅ ትርጉም የሰላም ወይም የጽድቅ ንጉሥ ማለት ስለሆነ እርሱ ራሱ የሰላሙ ንጉሥ ክርስቶስ ነው ማለት አይደለም።

የዕብራውያኑ መልእክት መልከጼዴቅ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነው አላለም። በመልእክቱ የተነገረው የእግዚአብሔርን ልጅ ይመስላል ተብሎ ነው። በእግዚአብሔር ልጅና የእግዚአብሔርን ልጅ በመምሰል መካከል ትልቅ ልዩነት አለ።

የተነገረውም ክርስቶስ መልከጼዴቅ ነው ተብሎ ሳይሆን ነገር ግን ክርስቶስ በመልከጼዴቅ የክህነት ሥርዓት ካህን መሆኑ ነው።

መልከጼዴቅ አምላክ ቢሆን ኖሮ መጽሐፉ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገለጠለት ባለ ነበር። እግዚአብሔር በተለያዩ ሁናቴዎች ለሰዎች በሚገለጥበት ጊዜ የሚባለው አባባል እግዚአብሔር ለእገሌ ተገለጠለት በማለት ነው።

በዚህም መሠረት መጽሐፉ የተናገረው የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነው ብሎ ነው እንጂ እግዚአብሔር ነው ብሎ አይደለም። በሁለቱ አባባሎችም መካከል ታላቅ ልዩነት ያለ መሆኑ ግልጥ ነው።

መልከጼዴቅ የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነው ሲባል የክህነት አገልግሎቱን የሚሰጠው ለማን ነበር? በክህነቱ የሚያገለግለው ሕዝብ የሳሌም ሕዝብ ነበር።

መልከጼዴቅ ሥራና አገልግሎት የነበረው ሰው ነበር። አምላክ ራሱን የገለጠበት ሁናቴ አልነበረም። የመገለጥ ጉዳይ ብቻ ቢሆን ኖሮ ያቀረባቸው ኅብስትና ወይንም የመገለጥ ጉዳይ ብቻ ነበሩ ማለት ነውን? ከአብርሃምስ የተቀበለው ዐሥራት ወዴት ሄደ?

የልዑል እግዚአብሔር ካህን የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሠተው ስለ መልከጼዴቅ በተነገረው ታሪክ ውስጥ ነው።

ያዕቆብ የክህነት ተግባርን በማከናወን መሥዋዕትን ያቀርቡ ነበር። እንደ መልከጼዴቅ ግን ካህናት አልተባሉም። ካህን የመባል ስም በመጀመሪ የተሰጠው ለመልከጼዴቅ ነው።

ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ካህን የሚል ስም የተሰጠው ሰው መገለጥ እን በእውነት የነበረ ሰው አይደለም የሚለው አባባል ምክንያታዊነትን የተከተለ አይደለም። እንዲሁም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ተባለ እንጂ ልዑል እግዚአብሔር አልተባለም።

በኦሪት ዘፍጥረት ም:32 ቍ:19 ያዕቆብ፥ በኦሪት ዘጸአት ም:3ቍ:13 ሙሴ፥ በመጽሐፈ ኢያሱ:ም:5ቍ:13 ኢያሱ፥ በመጽሐፈ መሳፍንት ም: 3ቍ:17 የሶምሶን አባት ማኑሄ እንዳደረጉት ሳይሆን አብርሃም የመልከ ጼዴቅን ማንነት ሳይጠይቅ ከመልከጼዴቅ በረከትን መቀበሉና ለመልከ ጼዴቅም ዐሥራት መስጠቱ ምንን ያመለክታል?

ይህ ሁናቴ ሚያመለክተው አብርሃም መልከጼዴቅን አስቀድሞ ያውቀው የነበረ መሆኑን ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ ግን ለማያውቀው ሰው ዐሥራትን መክፈል ምክንያትዊ ሊሆን ባልቻለም ነበር።

የሚያውቀውም ከሆነ ደግሞ እርሱ አንድ ማንነቱ የታወቀ ሰው ነበር ማለት ነው። እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህንና የሳሌም ንጉሥ ነበር ማለት ነው። ስለዚህ እርሱ ራሱ ክርስቶስ አይደለም። አብርሃም የማያውቀው ቢሆን ኖሮ አንተ ማነህ ብሎ በጠየቀው ነበር።

መልከጼዴቅ አብርሃምን የባረከበት መንገድ እግዚአብሔር ሰዎችን ከሚባ ርክበት ዐይነት የተለየ ነው።

እርሱ አብርሃምን የባረከው እንዲህ ብሎ ነው።

«ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ልዑል እግዚአብሔር አብራምን ይባርክ፡ በጠላቶችህ ላይ ድልን ያቀዳጀህ ልዑል ግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን» (ዘፍ:ም:14ቍ:19–20)።

እግዚአብሔር ግን በሚባርክበት ጊዜ በቀጥታ ይባርካል እንጂ ሌላ ባራክ አይጋብዝም። አብርሃምን በባረከበት ጊዜ እንዴት እንደባረከው ቀጥለን እንመ ልከት።

«ዘርህን አበዛዋለሁ፤ ታላቅ ሕዝብም ይሆናል፤ እባርክሃለሁ፤ ስምህንም ገናና አደርገዋለሁ፤ ለሌሎችም በረከት ትሆናለህ፤ የሚመርቁህን እመርቃ ለሁ፤ የሚረግሙህንም እረግማቸዋለሁ፤ በአንተም አማካይነት ሕዝቦች ሁሉ ይባረካሉ» (ዘፍ:ም:12ቍ:2–3)።

መልከጼዴቅ ግን እግዚአብሔር ይባርክህ በሚልበት ጊዜ ከበረከቱ ምንጭ ከእግዚአብሔር የመጣ ሳይሆን የካህን በረከት መሆኑን እንገነዘባለን። ከዚያም ቀጥሎ ልዑል እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን እያለ እግዚአብሔርን ሲያመ



www.ethiopianorthodox.org

ሰግን እናገኘዋለን። እርሱ ማለት መልከጼዴቅ አምላክ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ብሎ ራሱን ባላመሰገነም ነበር።

አብርሃም በኦሪት ዘፍጥረት ም:18ቍ:2 ላይ ለሦስቱ እንግዶች እንደ ሰገደ ለመልከጼዴቅ እንደ አምላክ አልሰገደለትም።

እግዚአብሔር በቍጥቋጦው እሳት ውስጥ ሆኖ ለሙሴ በተገለጠለት ጊዜ ሙሴ እግዚአብሔርን ማየት ስለፈራ ፊቱን ሸፈን (ዘጸ: ም: 3ቍ:6)። የእግዚአብሔር መልአክ ለማኑሄና ለሚስቱ በተገለጠላቸው ጊዜ ማኑሄ ለሚስቱ እግዚአብሔርን ስላየን እንሞታለን አላት (መሳ:ም:13ቍ:22)። ኢያሱም ወደ ምድር ሰገደና ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድነው? አለ (ኢያ: ም:5ቍ:14)።

ለመልከጼዴቅ ግን ከእነዚህ የአክብሮት ምልክቶች አንዱ እንኳ አልተደረገለትም። እንደ ካህንነቱ ግን ዐሥራት ተሰጥቶታል።

ከዚያ በፊት በተከሠቱ በተለያዩ የእግዚአብሔር መገለጦች የሰው ስም ተጠቅሶ፥ ማዕረጉና ሥራው ተገልጦ፥ አገሩና ያደረጋቸው ድርጊቶች ተዘርዝረው እንደ መልከጼዴቅ የሆነ ሁናቴ የቀረበ የለም። ይህም የሚያመለክተው መልከጼዴቅ አንድ ሰው እንጂ የእግዚአብሔር መገለጥ አለመሆኑን ነው።

በዮናታንና በኢየሩሳሌም የተልሙድ ትርጕም፥ እንዲሁም በዝነኛው ይሁዳዊ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ በዮሴፈስ እንደ ተረጋገጠው መልከጼዴቅ በመጽሐፉ ውስጥ እንደ ተገለጠው በዚያን ጊዜ የነበረ ሰው መሆኑ የአይሁድ እምነት ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅም:- «መልከጼዴቅ የሕይወቱ መጀመሪያና መጨረሻ ተመዝግቦ ባይገኝም እንኳ መጽሐፉ ሥራውንና ማዕረጉን የገለጠለት ዐይነት ሰው ነው» ብሎአል።

በዚህም ዐይነት በዕብራውያን መልእክት ምዕራፍ 7 እንደ ተገለጠው ስለ ክህነት እንጂ ስለ ሰው አይደለም። ይህም ማለት ያ ገለጻ የሚያመለክተው ስለ መልከጼዴቅ ሳይሆን ስለ ክህነቱ ትልቅነት ነው። እንዲሁም ስለ አብርሃም ሳይሆን ከአብርሃም ሥር ስለ ተገኘው ስለ አሮን ክህነት፥ በመልከጼዴቅ ስለ መባረኩና ለመልከጼዴቅ ዐሥራት መክፈሉ ነው።

እንዲሁም በዕብራውያን መልእክት ምዕራፍ 5 እና 6 የተገለጠው ስለ ክህነት ነው እንጂ ስለ ራሱ ስለ መልከጼዴቅ አይደለም።

(የፖፕ ሺኖዳ ጥያቄዎችና መልሶች አምስተኛ መጽሐፍ ከገጽ 71 እስከ ገጽ 80 ይመለከቷል)።

አንዳንድ ምሁራን መልከጼዴቅ ከሴም ዘር የሆነ የኢየሩሳሌም ንጉሥ ነበር ሲሉ ከዚህ ለየት ያለውን የቅዱስ ቁርሎስን ድርሳን እንመልከት።



<u>ቅዱስ ቁርሎስ ስለመልከጼዴቅ</u>

<u>ድርሳን 1</u>

እናንተ የተጠማችሁ ኑ፤ ከጠቢቡ ከጳውሎስ ውሃን ወስደን ጥማችሁን እናረካላችኋለን። እርሱ የሕይወት ምንጭ ነውና። እነሆ እንግዲህ ጳውሎስ ስለ ክቡር መልከጼዴቅ እንዲህ ይላል:-

ይህ መልከጼዴቅ የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነው፥ ስለእርሱም በብዙዎች የተጻፈውና የተነገረው ነገር ሁሉ ብዙ ነው። ራሱ ጳውሎስ እንደ ተናገረ:- መልከጼዴቅ ትርጓሜው ከባድ ነው፥ ቀላልም አይደለም። ይልቁንም ለማያስተውሉና ለመስማት ለደነዘዙ ሰዎች ቀላል አይደለም። ነገር ግን እንደ ነበረ ስለ እርሱ እናገራለሁ።

መልካጼዴቅ መንፈስ ቅዱስ ወይም እግዚአብሔር ነው እንጂ እንደ እኛ ሰው አይደለም የሚሉ አሉ። ይህን የሚያስቡ ሰዎች በድለዋል፥ ከማስተዋልም ርቀዋል።

እንግዲህ ስለዚህ በቅድሚያ እንነግራቸዋለን። መልከጼዴቅ የእግዚአብሔር ካህን ሲባል ሰምታችሁ እንዴት መንፈስ ቅዱስ ወይም እግዚአብሔር ነው ትሉታላችሁ? መንፈስ ቅዱስ እንደ ወልድ ክህነትን ተሾመ አይባልምና። የክህነትም ስም ለእርሱ ፈጽሞ አይዋሐድምና (አይስማማምና)።

መልከጼዴቅ የጽድቅ ንጉሥና የሰላም ንጉሥ ቢባልም እንኳ ለክርስቶስ ምሳሌ ስለሆነ እንጂ እርሱ ራሱ የጽድቅና ሰላም ንጉሥ ሊባል አይችልም። ... ይህ የሚገባ ለመለኮት ነው። ... ከሙሴ ቀጥሎ ለእስራኤል ስለተሾመው መስፍን እናገራለሁ:- የዚህ ሰው ስሙ ኢያሱ ተባለ። ትርጓሜውም መድኃኒት ማለት ነው። ቢሆንም ይህ ስም ከእውነተኛ ማዳን ጋር አይተባበርም። ማዳን ለጌታችንና ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነውና።

<u>ቅዱስ ቁርሎስ ስለ መልከጼድቅ</u>

<u>ድርሳን 2</u>

... ሽማግሌውና በእግዚአብሔር ሕግ ጠቢብ የሆነው ሰው ስለመልከጼዴቅ አረጋግጦ ይናገራል:-

መልከጼዴቅ ከካም ወገን ነው። ከካም ወገን ቅዱስ ልጅ ሆኖ ተገኘ። እግዚአብሔርንም ደስ አሰኘው። እግዚአብሔር አብርሃምን ከሀገሩ እንዳወጣው መልከጼዴቅን ከሀገሩ ወደ ዮርዳኖስ አወጣው። ጻድቁ ሰው መልከ ጼዴቅ የልዑል እግዚአብሔር ካህን ሆነ። ሁልጊዜ በኅብስትና በወይን የምስጋና መሥዋዕት ያቀርብ ነበር።

እግዚአብሔርንም ስለ ወገኖቹ እንዲህ እያለ ይለምነው ነበር። «አቤቱ ከሀገሬ አውጥተህ ዲያብሎስን ከመከተል የመለስኸኝ ይቅር ያልኸኝም አመሰግንሃለሁ። እነርሱንም ይቅር በላቸው። እግዚአብሔርም አለው:- ልጄን ከግብጽ



www.ethiopianorthodox.org

በጠራሁት ጊዜ እኔ አድናቸዋልሁ። እግዚአብሔር ይህን ትእዛዝ ለመል ከጼዴቅ ሰጠው።

በዚያም ወራት አብርሃም እንደተጻፈ ነገሥት ከሎዶጎሞርን ድል አድርጎ በሚመለስበት ጊዜ ከመልከጼዴቅ ጋር ተገናኘ። ከመገናኘታቸው በፊት ግን አብርሃም ለራሱ እንዲህ እያለ ይጸልይ ነበር:- «አቤቱ ልጅህን በዘመኔ ወደ ዓለም ትልካለህን? ያችንስ ቀን አያታለሁን?»

እግዚአብሔርም አለው:- የለም አታያትም፤ ነገር ግን የዚያችን ቀን ምሳሌ አሳይሃለሁ። እነሆ ውረድ፥ ዮርዳኖስንም ተሻገረው። የክብሬንም ቀን ታያለህ። አብርሃምም ከሠራዊቱ ጋር ዮርዳኖስን ተሻገረ።

ያንጊዜም መልከጼዴቅ መጥቶ አብርሃምን ተገናኘው በእጁም ኅብስትና ጽዋ ይዞ ነበር። አብርሃምንም ባረከው። አብርሃምም መልከጼዴቅን ባያየው ኖሮ ዮርዳኖስን ባልተሻገረም ነበር። ይህም የጥምቀት ምሳሌ ነው።

አብርሃም:- መልከጼዴቅን በእጁ ኅብስተ በረከትና ጽዋዕ አኰቴት ይዞ ሲመጣ ባየው ጊዜ በግንባሩ ወድቆ ሰገደለት። የእግዚአብሔርን ቀን አይቶ ደስ ብሎታልና።

መልከጼዴቅ በእውነት ሰው ነው። ብርግጥም እግዚአብሔር በዮርዳኖስ ማዶ ትርጉሙ ሰላም ወደሚባል ወደ ሳሌም ያወጣው ከካም ወገን የተወለደ ነው። የልዑል እግዚአብሔር ካህንም ተባለ። ብፁዕ ጳውሎስ እንደ ተናገረ:- አባትና እናት የሉትም። ልደቱም አልተጻፈም። መልከጼዴቅ ከከነዓን ወገን ነውና።

(ይህ ስለ መልከጼዴቅ የተዘጋጀው ዝግጅት ከፍኖተ ብርሃን መጽሐፍ የተወሰደ ነው)።

<u>ኢያሱ ወልደ ነዌ</u>:- የነዌ ልጅ ኢያሱ ከኤፍሬም ነገድ ነበር። እርሱም በሙሴ ጊዜ የሙሴ ረዳት የነበረ ሲሆን ሙሴ ከሞተ በኋላ በሙሴ ምትክ የእስራኤል ሕዝብ መሪ ሆኗል። የቀድሞ ስሙ ሆሼዕ ነበር። በበረሓው ጉዞ ሁሉ ኢያሱ የሙሴ ታማኝ አገልጋይ ነበር። አማሌቃውያን ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ጦርነት በገጠሙ ጊዜ በእስራኤል በኩል ጦሩን እንዲመራ ሙሴ ያዘዘው ኢያሱን ነው። ኢያሱም ሙሴን በጦርነት ብቻ ያገለገለ ሳይሆን በደቀ መዝሙርነቱም ከሙሴ ጋር ወደ ሲና ተራራ ላይ ተከትሎ ወጥቶአል። እዚያም ሙሴ እግዚአ ብሔርን እየተገናኘ ሳለ አርባ ቀንና ሌሊት ቈይቶአል። (ዘጸ:24፥ 13–18፤ ም:32ቍ: 15–17)። እንዲሁም ለማደሪያው ድንኳን ኀላፊ በመሆን ሙሴን ይረዳ ነበር:

የከነዓንን ምድር እንዲሰልሉ ሙሴ ከላካቸው ዐሥራ ሁለት ሰላዮች አንዱ ኢያሱ ነበር። ከተላኩት ዐሥራ ሁለት ሰላዮች መካከል በእግዚአብሔር እርዳታ ተማምነውና ሕዝቡም በእግዚአብሔር እንዲተማመን ጥረት ያደረጉ ኢያሱና ካሌብ ብቻ ናቸው። ዐሥሩ ሰላዮች እስራኤላውያንን የሚያስፈራራና የሚያስ



ደነግጥ ዘገባ አቅርበው ስለነበረ ሕዝቡ ሁሉ በመሸበር ላይ ነበሩ። እንዲያውም ኢያሱና ካሌብ ከዐሥሩ ሰላዮች አስተሳሰብ ስለተለዩ ሕዝቡ ሊወግራቸው ተነሣ። በዚህም እምነታቸውና ድፍረታቸው ከቀድሞው ትውልድ ወደ ከነዓን ምድር እንዲገቡ የተፈቀደላቸው ለካሌብና ለኢያሱ ብቻ ነው (ዘኍ: ም:26 ቍ:65)።

በእግዚአብሔርም ትእዛዝ መሠረት የእስራኤልን ሕዝብ በእርሱ ምትክ እንዲመራ ሙሴ በኢያሱ ላይ እጁን ጫነበት። ኢያሱም እንደ ሙሴ በጥበብ መንፈስ የተሞላ ሆነ።

መጽሐፈ ኢያሱን ለተመለከተ ሰው የኢያሱ የመሪነት ሁናቴ ከሙሴ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ያገኘዋል።

በኢያሱ መሪነት የእስራኤል ሕዝብ የከነዓናውያንን ጠንካራ ተቃውሞ ድል አድርጎ በምድሪቱ ላይ ራሱን በጽኑ መሠረተ። ከእነዚህም ከመጀመሪያዎቹ ድሎች በኋላ ኢያሱ ምድሪቱን ለየነገዱ በርስትነት ማከፋፈል ጀመረ። በሕይወቱም ወደመጨረሻው ዘመን እስራኤላውያንን ሁሉ ሰብስቦ በእምነታቸው እንዲጸኑና ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ቃል ኪዳን እንዲያድሱ ነገራቸው። ከዚያም ዕድሜው አንድ መቶ ዐሥር ዓመት ሲሆን ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

<u>መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ</u>:- መጽሐፈ ኢያሱ ኻያ አራት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን በአጠቃላይ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የእስራኤል ልጆች በተአምር ዮርዳኖስን ተሻግረው በእግዚአብሔር እርዳታና በኢያሱ መሪነት ድል አድርገው የከነዓንን ምድር መያዛቸው ተገልጾአል። ይህም ክፍል የሚጀምረው ከሙሴ ሞት በኋላ እግዚአብሔር ለኢያሱ በሰጠው መመሪያ ነው። ይህም መመሪያ ኢያሱ በሙሴ ተተክቶ እስራኤልን በመምራት ዮርዳኖስን ተሻግሮ የከነዓንን ምድር እንዲያገዝ ነው። ኢያሱ የእግዚአብሔርን ሕግጋትና ትእዛዛት እስከጠበቀ ድረስ በሁሉም ነገር እግዚአብሔር እንደሚረዳው ቃል ገብቶለታል። ከዚያም በኋላ ኢያሱ ሕዝቡ ለጦርነት ይዘጋጅ ዘንድ ትእዛዝ አስተላላፈ። ለዝግጅትም ያመች ዘንድ ኢያሱ ሁለት ሰላዮችን ወደ ኢያሪኮ ላከ። እነዚህም ሁለት ሰላዮች ወደ ኢያሪኮ ከተማ ውስጥ ገብተው በአንዲት ረዓብ በተባለች ሴተኛ ዐዳሪ ቤት ተደብቀው ከቈዩ በኋላ በሽሽግ ተመልሰው ወደ እስራኤላውያን ሰፈር መጡ። ደብቃ ካቈየቻቸው ከረዓብ በተረዱት መሠረት የኢያሪኮ ሕዝብ በእስራኤል ላይ በጣም ፍራቻ ያደረበት መሆኑን ገለጡ።

በሚቀጥለው ቀን ኢያሱና የሕዝቡ መሪዎች ሕዝቡ ራሱን አንጽቶ በማግስቱ ለሚፈጸመው የእግዚአብሔር ተአምር እንዲዘጋጅ ትእዛዝ አስተላለፉ። ከሕዝቡም ፊት የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙት ካህናት ቀድመው እንዲሄዱ አደረጉ። ልክ ታቦቱን የተሸከሙት ካህናት ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ



www.ethiopianorthodox.org

ሲደርሱ ዮርዳኖስ ወንዝ መውረዱን አቆመ። የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙት ካህናት ወንዙ ይወርድበት በነበረው መካከል ቆመው ሳለ ሕዝቡ ሁሉ በደረቅ መሬት ላይ እየተራመደ ሲሻገር ውሃው እንደ ግድግዳ ቆሞላቸው ነበር። ሁሉም ተሻግረው ከጨረሱ በኋላ ካህናቱ ተሻገሩ። ከዚያ በኋላ ውሃው እንደበፊቱ ይፈስስ ጀመር።

ኢያሱም የግዝረት ተራራ በተባለው በጌልጌላ የእስራኤላውያንን ወንዶች ሁሉ ገረዛቸው። ይህም የሆነው ከግብጽ የወጡት እስራኤላውያን ወንዶች ሁሉ በኃጢአታቸው ምክንያት ተስፋ የተሰጣቸውን ምድር ሳያዩ በምድረ በዳው ጕዞ ሞተው ሰላለቁና እነርሱ የወለዱአቸው ልጆች በጕዞ ላይ በነበሩ ጊዜ ስላልተገረዙ ነው። በዚያን ቀን ማግስት እስራኤላውያን በከነዓን የበቀለውን እህል መመገብ ጀመሩ። ከዚያም ቀን ጀምሮ ከሰማይ ይወርድላቸው የነበረው መና መውረዱን አቆመ። በጌልጌላ ሰፍረው ሳለም ለመታሰቢያነት እንዲሆን ዐሥራ ሁለት ድንጋይ አስቀመጡ።

ሰይፍ በያዘ አንድ ጐልማሳ መልክ የእግዚአብሔር ሠራዊት አዛዥ ለኢያሱ ከተገለጠለት በኋላ እስራኤላውያን በኢያሪኮ ላይ ከበባ ጀመሩ። በኢያሪኮም ግንብ ዙሪያ በታቦት ተሸካሚው መሪነት ሰባት ቀኖች ከዞሩ በኋላ በሰባተኛው ቀን የከተማይቱ ግንብ ፈረሰ። እስራኤላውያንም የእስራኤልን ሁለት ሰላዮች በቤትዋ ሸሽጋ ካስቀመጣቻቸው ረዓብና ዘመዶችዋ በቀር የኢያሪኮን ከተማ ነዋሪዎች ሁሉ ገደሉ። ወንዱንና ሴቱን፥ ሽማግሌውንና ሕፃኑን፥ እንዲሁም እንስሳቱ እንኳ ሳይቀሩ ሁሉንም ፈጁ። እግዚአብሔርም ከኢያሱ ጋር ስለነበረ ሁሉ ነገር በእግዚአብሔር እርዳታ ይሳካላቸው ነበር።



የኢያሪኮ ግንብ መፍረስ

www.ethiopianorthodox.org

የእስራኤል ...

ታማኞች ሆነው አልተገኙም። ከነገደ ይሁዳ የነበረ አንድ ዓካን የተባለ ሰው እግዚአብሔር እንዳይወሰዱ የከለከላቸውን አንዳንድ ዕቃዎች በጦርነቱ ጊዜ በድብቅ ወስዶ ሸሸጋቸው። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር እስራኤላውያን ስላልረዳ ዐይ በምትባል ትንሽ አገር ፊት ተሸነፉ። ኢያሱ ወደ እግዚአብሔር በጸለየ ጊዜ እስራኤላውያን በተከለከሉ ጉዳዮች እምነተቢስ ሆነው መገኘ ታቸው ተነገረው። ኢያሱም ምርመራ ባደረገ ጊዜ ይህን ያደረገ ዓካን መሆኑን ሊማወቅ ቻለ። ዓካን በሕዝቡ ሁሉ ፊት በድንጋይ ተወግሮ ከተገደለ በኋላ በእግዚአብሔር እርዳታ የዐይን ከተማ ድል አድርገው ለመያዝ ቻሉ።

ሙሴ እስራኤላውያንን እንዲህ ብሎ አዝዞአቸው ነበር:- «እግዚአብሔር ወደምትወርሱአት ምድር በሚያስገባችሁ ጊዜ በረከቱን በገሪዛን ተራራ፥ መርገሙንም በጌባል ተራራ ታውጃላችሁ» (ዘዳ: ም:11 ቍ:29)። ይህንንም ትእዛዝ በኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 27 ላይ ዘርዝሮ አቅርቦታል።

ኢያሱም በጌባል ተራራ ላይ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠርቶ የሚቃጠልና የኅብረት መሥዋዕት አቀረበበት። ከዚያም ኢያሱ ሕዝቡን ሰብስቦ የቃል ኪዳኑን ታቦት ከተሸከሙት ከሌዋውያን ፊት ለፊት ግራና ቀኝ እኩሌቶቹን ከገሪዚም ተራራ ፊት ለፊት፥ እኩሌቶቹን ደግሞ ከጌባል ተራራ ፊት ለፊት አቆማቸውና በሕጉ መጽሐፍ በተጻፈው መሠረት በረከቱንም መርገሙንም በሙሉ አነበበ።

ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉት አገሮች የእስራኤል ሕዝብ ምን ያኽል ብዙ ሕዝቦችን ድል እያደረገ እዚህ ድረስ እንደረሰ በሰሙ ጊዜ ጊዜ ኀይላቸውን አስተባብረው በኢያሱና በእስራኤላውያን ላይ ለመዝመት መጡ። የገባዖን ሰዎች ግን ኢያሱን ማታለል እንደሚሻል ወሰኑ። እነርሱም ስንቃቸውን አዘጋጅተው፥ አሮጌ ስልቻና ቀዳዳው ተለጥፎ የተሰፋ የወይን ጠጅ አቁማዳ በአህዮች ጫኑ፤ ተቀዳድዶ ያለቀ አሮጌ ልብስ ለብሰውም የተጠጋገነ እላቂ ጫማ አደረጉ፤ ለስንቅ የያዙትም እንጀራ ደረቅና የሻገተ ነበር። ይህን ሁሉ ካደረጉ በኋላ በጌልጌላ ወደሚገኘው ሰፈር ሄደው ኢያሱንና እስራኤላውያንን እኛ የመጣነው ከሩቅ አገር ነው፤ የመጣነውም ከእናንተ ጋር የቃል ኪዳን ውል ለማድረግ ነው አሉ። ንግግራቸውንም በመቀጠል አምላካችሁ እግዚአብሔር በግብጽና ከዮርዳኖስ ማዶ በስተምሥራቅ በነበሩት በሁለቱ አሞራውያን ነገሥታት ላይ ያደረገውን ሁሉ ሰምተናል፤ ስለዚህ መሪዎቻችንና በምድራችን የሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ ከእናንተ ጋር እንድንገናኝ ልከውናል፤ ለናንተ የምንታዘዝ አገልጋዮች እንድንሆንና እናንተም ከእኛ ጋር የሰላም ውል እንድታደርጉ እንጠይቃችሁ ዘንድ አዝዘውናል አሉ። ኢያሱና የእስራኤል መሪዎችም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይጠይቁ ከገባዖን ሰዎች ጋር የሰላም ስምምነት አደረጉ። ይህ ስምምነት በተደረገ በሦስተኛው ቀን እነዚያ ሰዎች ጐረቤቶች መሆናቸውንና ያታለሉአቸው መሆናቸውን ዐወቁ። በዚህም ምክንያት

እንጨት በመቍረጥና ውሃ በመቅዳት ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለዘለዓለም አገልጋዮች እንዲሆኑ ፈረዱባቸው።

ገባዖን ከእስራኤል ጋር የሰላም ስምምነት ስላደረገች አምስቱ የአሞራውያን መንግሥታት ማለት የኢየሩሳሌም፥ የኬብሮን፥ የያርሙት፥ የላኪሽና የዔግሎን መንግሥታት በገባዖን ላይ አደጋ ጣሉባት። በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን ገባዖንን ረድተው በእነዚያ ወገኖች ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሱባቸው። እግዚአብሔርም ለእስራኤላውያን ሁለት ታላላቅ ተአምራትን በማድረግ ረዳቸው።

የመጀመሪያው ተአምር ከሰማይ ታላላቅ የበረዶ ድንጋይ አውርዶባቸው እስራኤላውያን ከገደሉአቸው ይልቅ በበረዶው ድንጋይ የሞቱት እጅግ ብዙዎች ሆኑ።

ሁለተኛው ተአምር ኢያሱ እግዚአብሔርን በለመነው መሠረት እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን እስኪበቀሉ ድረስ ፀሐይና ጨረቃ ሳይንቀሳቀሱ ቆዩ። ከዚያም ሁሉንም ድል አደረጋቸውና ፈጃቸው።

የሐጾር ንጉሥ ያቢን የእስራኤልን ድል አድራጊነት በሰማ ጊዜ በአካባቢው የነበሩትን ብዙ ነገሥታት እንዲተባበሩት ጠይቆ በጣም ብዙ ተዋጊዎች በእስራኤል ሕዝብ ላይ አሰለፉ። ነገር ግን የእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር እርዳታ ሁሉንም አሸነፉአቸው። ከእነርሱም አንድ ሰው እንኳ ሳይተርፍ ፈጁአቸው። የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ ባዘዘው መሠረት ኢያሱ እነዚህን ከተሞችና ንጉሦቻቸውን ሁሉ ማረከ፤ በሰይፍ ስለትም መታቸው፤ ፈጽሞም አጠፋቸው። እግዚአብሔር ትእዛዙን ለአገልጋዩ ለሙሴ ሰጠ፤ ሙሴም ለኢያሱ ሰጠ፤ ኢያሱም ትእዛዛቱን ፈጸመ፤ እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ኢያሱ ሁሉን ነገር አደረገ፤ አንዳችም አላስቀረም።

እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ኢያሱ ምድሩን ሁሉ በእጁ አደረገ፤ ለያንንዱም ነገድ አንዳንድ ድርሻ በመስጠት ለእስራኤላውያን በሙሉ አከፋፈለ።

ሁለተኛው ክፍል ከምዕራፍ ዐሥራ ሦስት እስከ ምዕራፍ 22 ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ምድሪቱን ለነገዶች ማከፋፈል፥ ለሌዊ ልጆች አርባ ስምንት ከተሞችን መስጠትና የመማጸኛ ከተሞችን መወሰን ይገኙበታል። ኢያሱም ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ ከወንድሞቻቸው ጋር በጦርነት ለመሰለፍ ዮርዳኖስን ተሻግረው የነበሩትን የሮቤልን፥ የጋድንና እኩሌታ የምናሴ ነገዶችን ወደ ርስታቸው እንዲመለሱ አሰናበታቸው። ሙሴ ከመሞቱ በፊት ለእነዚያ ለሁለት ተኩል ነገዶች በዮርዳኖስ በስተምሥራቅ በኩል ርስት ሲሰጣቸው ከወንድሞቻቸው ጋር ዮርዳኖስን ተሻግረው እንደሚዋጉ ቃል ገብተው ነበር። አሁን ግዴታቸውን ስለተወጡ ኢያሱ አሰናበታቸው።

ሦስተኛው ክፍል ምዕራፍ ኻያ ሦስትና ኻያ አራት ነው። በዚህም ክፍል ውስጥ የኢያሱ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር መሰነባበቻ መሰል ጠቃሚ ምክሮች



ያሉበት ንግግር፥ የቃል ኪዳን ማደስና በመጨረሻም የኢያሱና የአልዓዛር ሞትና መቀበር ይገኙበታል።

<u>መጽሐፈ መሳፍንት</u>:- ኢያሱ የእስራኤልን ሕዝብ ይመራ በነበረበት ጊዜ ሁሉ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ሕግ ተገዥ ሆኖ ኖሯል። ኢያሱና በዚያ ዘመን የነበረው ትውልድ ካለፈ በኋላ የመጣው ትውልድ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ያደረገውን መልካም ነገር ሁሉ ረሳ። እስራኤላውያን ባዕዳን አማልክትን አመለኩ። ይህም በመሆኑ ጠላቶች ተነሥተው በማጥቃት ድል እንዲያደርጉአቸውና ጨቍነው እንዲገዙአቸው እግዚአብሔር ፈቀደላቸው። ይሁን እንጂ እነዚህ የውጭ ገገርዎች በጭቈና አገዛዝ በአስጨነቁአቸው ጊዜ ሁሉ የእስራኤል ሕዝብ በንስሓ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ይለምኑ ነበር። እግዚአብሔርም መሪ እያስነሣላቸው በዚያ በመሪ አማካይነት ይታደጋቸው ነበር። በኢያሱና በንጉሥ ሳኦል ዘመን መካከል በዚህ ዐይነት መሳፍንት በሚል ስም እግዚአብሔር ያስነሣቸው መሪዎች ከዔሊና ከሳሙኤል በቀር ዐሥራ ሁለት ናቸው። እነርሱ ግን ከመሳፍንቱ ቍጥር ከገቡ ዐሥራ አራት ይሆናሉ። በመጽሐፉ ውስጥ እንደሚታየው ነገሥታቱ የተለየ ከፍተኛ ክብር የሚጠብቁ ከመሆናቸው በቀር የመሳፍንቱ ሥልጣን እንደ ነገሥታት ሥልጣን ነው። በነገሥታት በኩል በሕዝብ ላይ ሊደርስ የሚችለው በገንዘባቸውም ሆነ በልጆቻቸው ላይ የሚመጣው ተጽዕኖ በመሳፍንቱ በኩል አይደርስባቸውም ነበር። እያንዳንዱ መስፍን የሚተዳደረው እንደማንኛውም ተራ ሰው ሠርቶ እንጂ ሌላ የተለየ ገቢ አልነበረውም። ሰዎችም ልጆቻቸውን ለመስፍኑ የማስገዛት ግዴታ አልነበረባቸውም። እነዚህ መሳፍንት የገዙበት ዘመን ወደ አራት መቶ ዓመት ይጠጋል። ከእነርሱም መካከል ዲቦራ የተባለች ሴት ትገኝበታለች፥ የአገዛዝ ዘመናቸውም ወዲያው ወዲያው የሚከታተል አልነበረም። አንዱ ዐልፎ ሌላው እስኪተካ ድረስ ረጅም ጊዜ ይፈጅ ነበር። የሚነሡትም ከተለያዩ አካባቢዎች ነበር። ለምሳሌ ኤሁድ፥ ዮፍታሔ፥ ኤሎንና ያኢር የነበሩት በዮርዳኖስ በስተምሥራቅ፥ ዲቦራና ቶላዕ በስተሰሜን፥ ጎብዖን በመሐል አገር፥ ኢብጻንና ሶምሶን በስተደቡብ ይኖሩ ነበር።

መጽሐፈ መሳፍንት ኻያ አንድ ምዕራፎች ያሉት ሆኖ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ምዕራፍ አንድና ሁለት ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ በኢያሱ ዘመን የነበሩት የነገዶች ታሪክ ይገኝበታል። እነርሱም ኢያሱን ተከትለው የሄዱ ናቸው። ከእነርሱ በኋላ የመጣው ትውልድ እንዴት እግዚአብሔርንና ለእስራኤል ሕዝብ ያደረገውን መልካም ነገር የማያውቅ እንደነበረ ያመለክታል። እነርሱም ከአካባቢው ጣዖት አምላኪዎች ጋር በመተባበር ባዕዳን አማልክትን አመለኩ። በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔርን ቍጣ አስነሡ። እየ መጡ አደጋ የሚጥሉባቸው ወራሪዎች እንዲነሡባቸው እግዚአብሔር ፈቀደ። በጦርነትም ላይ መሸነፍ እንጂ መቋቋም እስኪያቅታቸው ይደርሱ ነበር። በእንደዚህ ያለ ጭንቀት ላይ በሚወድቁበት ጊዜ ኃጢአታቸውን

www.ethiopianorthodox.org

እየተናዘዙ የእግዚአብሔርን እርዳታ ለመኑ። እግዚአብሔርም ወደ ንስሐ ተመልሰው ወደ እርሱ በጮኹ ቍጥር ይቅርታ እያደረገ ከጠላት ጭቈና የሚያወጣቸው አንድ መሪ ያስነሣላቸላዋል። እነዚህም መሪዎች መሳፍንት ይባሉ ነበር። ይሁንና አንዱ መስፍን ተነሥቶ ባለበት ዘመን እግዚአብሔርን ሲያመልኩ ይቆዩና ያ መስፍን ሞቶ ሌላ መስፍን እስኪተካ ድረስ ወደ ጣዖት አምልኮአቸው ይመለሳሉ።

ሁለተኛው ክፍል ከምዕራፍ ሦስት እስከ ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የእስራኤል ልጆች በፈጸሙት በደል የደረሰባቸውን ችግር፥ ከዚያም ወደ አምላካቸው በጮኹ ቍጥር እንዴት የሚያድኑአቸው መሪዎችን እንዳስነሣላቸው ያመለክታል። በዚህም መሠረት የመሳፍንቱ ቅደም ተከተል ቀጥሎ የቀረበው ነው።

1. እስራኤላውያን በኃጢአታቸው እግዚአብሔርን ባስቈጡት ጊዜ ለመስጴጦምያው ንጉሥ ለኩሻን ራሽዓታይም አሳልፎ ሰጥቶአቸው ነበር። እነርሱም ስምንት ዓመት ተገዙለት። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰምቶ የካሌብን ታናሽ ወንድም የቄኔዝን ልጅ ዖትኒኤልን (ጎታንያል) አስነሣላቸው። እርሱም ኩሻንን ድል አድርጎ እስራኤልን ነጻ አወጣ። ምድሪቱም ለአርባ ዓመት ያኽል ካረፈች በኋላ ዖቲኒኤል ሞተ።

2. እስራኤላውያን እንደገና በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረጉ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር የሞአቡን ንጉሥ ዔግሎንን በእስራኤል ላይ እንዲበረታ አደረገው። እስራኤላውያንም ለዔግሎን ዐሥራ ስምንት ዓመት ተገዙለት። ከዚያ በኋላ እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን እርዳታ ስለለመኑ ከብንያም ነገድ ግራኝ የነበረውን የጌራን ልጅ ኤሁድን (ናዖድ) አስነሣላቸው። ኤሁድም ዔግሎንን ከገደለው በኋላ እስራኤላውያን ሞአባውያንን ድል አደረጉአቸው። በምድሪቱም ሰማንያ ዓመት ሙሉ ሰላም ሆነ።

3. ኤሁድ (ናዖድ) ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን እንደገና በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠሩ። ስለዚህም እግዚአብሔር በከነዓናዊው ንጉሥ በያቢን እጅ አሳልፎ ሰጣቸው። ያቢንም እስራኤላውያንን በጭካኔና በዐመፅ ለኻያ ዓመት ገዛቸው። ከዚያም በኋላ እስራኤላውያን እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ። እግዚአብሔር በዲቦራ፥ በባራቅና በያዔል አማካይነት እስራኤላውያንን ካያቢን ጭቈና አድኖአቸዋል። ከዚያ በኋላ በምድሪቱ ላይ አርባ ዓመት ሙሉ ሰላም ሰፈነ።

4. እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ፊት እንደገና በደል ሠሩ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር በምድያማውያን እጅ አሳልፎ ሰጣቸው፤ ምድያማውያንም ሰባት ዓመት ገዙአቸው። እስራኤላውያንም እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ። እግዚአብሔርም በጌዴዎንና በሦስት መቶ ተከታዮቹ አማካይነት እስራኤልን ከምድያማውያን ጭቈና አላቀቃቸው። ጌዴዎንም እስከሞተ ድረስ በምድሪቱ ላይ አርባ ዓመት ሙሉ ሰላም ሆነ።

5. ጌዴዎን ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን ጣዖት አምላኪዎች በመሆን የእግዚአብሔርን ቍጣ አነሣሡ። ጌዴዎን ብዙ ሚስቶች ስለነበሩት ሰባ ወንዶች ልጆች ተወልደውለት ነበር። ከአንድ ቁባቱ ደግሞ አቢሜሌክ የተባለ ልጅ ወለደ። ይህም አቢሜሌክ በአባቱ ቦታ ተተክቶ የእስራኤል መሪ ለመሆን ሰባ ወንድሞቹን ገደላቸው። ከሰባዎቹ ግን የጌዴዎን የመጨረሻ ልጅ ኢዮአታም ብቻ ተደብቆ ሳይሞት ተረፈ። በመጨረሻም በቶቤጽ ከተማ አንዲት ሴት አቢሜሌክን በወፍጮ ድንጋይ ናዳ አናቱን ፈጥፍጣ ገደለችው።

6. አቢሜሌክ ከሞተ በኋላ የዶዶ የልጅ ልጅ የፑአ ልጅ ቶላዕ እስራኤልን ለማዳን ተነሣ፤ እርሱም ከይሳኮር ነገድ ሲሆን የሚኖረው በኮረ ብታማው በኤፍሬም አገር ሻሚር ተብላ በምትጠራ ስፍራ ነበር፤ ይህ ሰው ኻያ ሦስት ዓመት የእስራኤል መሪ ሆኖ ከቈየ በኋላ ሞተ፤ በሻሚርም ተቀበረ።

7. ከቶላዕ ቀጥሎ ገለዓዳዊው ያኢር ተነሣ። እርሱም ኻያ ሁለት ዓመት የአስራኤል መሪ ሆነ። ያኢር ሞተ፤ በቃሞንም ተቀበረ።

8. እስራኤላውያን ባዕዳን አማልክትን በማምለክ እንደገና በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠሩ። ስለዚህ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ በመቈጣቱ በፍልስጥኤማውያንና በዐሞናውያን እጅ አሳልፎ ሰጣቸው። ዐሞናውያንና ፍልስጥኤማውያንም በገለዓድ ውስጥ የሚኖሩትን እስራኤላውያንን ለዐሥራ ስምንት ዓመት በጭቈና አገዛዝ አስጨነቁአቸው።

ከዚህ በኋላ እስራኤላውያን አንተን አምላካችንን ትተን ባዕዳን አማልክትን በመከተላችን በአንተ ላይ በደል ሠርተናል በማለት ወደ እግዚአብሔር ጮኹ። እግዚአብሔር መንፈሱን በዮፍታሔ ላይ አወረደ። ዮፍታሔም ዐሞናውያንን ድል በማድረግ እስራኤልን ነጻ አወጣ።

ዮፍታሔ ስድስት ዓመት የእስራኤል መሪ ከሆነ በኋላ ሞተ።

9. ከዮፍታሔ በኋላ የቤተልሔም ተወላጅ የሆነው ኢብጻን የእስራኤል መሪ ሆነ። እርሱም ሰባት ዓመት መሪ ከሆነ በኋላ ሞቶ በቤተልሔም ተቀበረ።

10. ከኢብጻን ቀጥሎ የዛብሎን ወገን የሆነው ኤሎን እስራኤልን ዐሥር ዓመት መራ። እርሱም ሞተ።

11. ከኤሎን ቀጥሎ የፒርዓቶን ተወላጅ የሆነው የሂሌል ልጅ ዓብዶን የእስራኤል መሪ ሆነ። እርሱም ስምንት ዓመት እስራኤላልን ከመራ በኋላ ሞተ።

12. እስራኤላውያን እንደገና በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠሩ፤ ስለዚህም ፍልስጥኤማውያን አርባ ዓመት ሙሉ እንዲገዙአቸው እግዚአብሔር አሳልፎ ሰጣቸው። ከዚህ በኋላ ከነገደ ዳን የሆነው የማኑሄ ልጅ ሶምሶን ተነሥቶ እስራኤላውያንን ከአርባ ዓመት የፍልስጥኤም አገዛዝ ነጻ አወጣቸው።

ሦስተኛው ክፍል ደግሞ ከምዕራፍ ዐሥራ ሰባት እስከ ምዕራፍ ኻያ አንድ ነው። በዚህ ክፍል ሁለት አሳዛኝ ታሪኮች ቀርበዋል።

www.ethiopianorthodox.org

የመጀመሪያው አሳዛኝ ታሪክ ኤፍሬማዊው ሚካና የዳን ነገድ ሰዎች ጣዖት አምልኮን መከተላቸው ነው።

ሚካ ከእናቱ ገንዘብ ሰርቆ ነበር። እናትየው ገንዘቧን የሰረቀባትን ሰው ስትራገም ሰምቶ ኅሊናው ወቀሰውና ገንዘቡን መለሰላት። እርስዋም በገንዘቡ ጣዖትና ኤፉድ አሠርታበት ለልጅዋ ሰጠችው። ሚካ ሌሎች ያሠራቸው ጣዖታትም ስለነበሩት ከልጆቹ አንዱን ለጣዖታቱ አገልግሎት የተለየ አድርጎት ነበር። በኋላም አንድ ሌዋዊ አግኝቶ ቀጥሮ ነበር። ከእስራኤል ነገዶች መካከል የርስት ድርሻ ያልነበራቸው ከዳን ወገኖች ስድስት መቶ ሰዎች የሚሰፍሩበትን ስፍራ በማፈላለግ ላይ እያሉ ወደ ሚካ ቤት መጥተው ሌዋዊውን፥ ጣዖታቱንና ኤፉዱን ነጥቀው ወሰዱበት። ይህም ማለት ጣዖት የማምለኩን ተግባር ከሚካ ተረከቡት ማለት ነው።

ሁለተኛው አሳዛኝ ታሪክ ደግሞ የብንያም ነገድ ክፍል በሆነችው በጊብዓ የተፈጸመው ወንጀል ነው። አንድ ሌዋዊ ከሚስቱ ጋር በእንግድነት በጊብዓ ዐድሮ ነበር። የዚያ አገር ሰዎች ሚስቱን ከእርሱ ወስደው ሌሊቱን ሙሉ በወሲባዊ ግንኙነት ሲፈራረቁባት ስላደሩ ሕይወትዋ ዐለፈ። ሌዋዊውም የደረሰበትን በደል ለማሳየት ሥጋዋን ለዐሥራ ሁለት ቦታ ቈራርጦ ወደ ዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ላከው። እስራኤላውያን ተሰብስበው ይህን በደል የፈጸሙትን ሰዎች ለመበቀል በብንያም ግዛት ላይ ዘመቱ። ከብንያም ነገድ ተደብቀው የነበሩ በመቶዎች ከሚቈጠሩ በቀር የተረፈ አልተገኘም። ሁሉንም ፈጁአቸው።

## ሐዲስ ኪዳን

<u>የቅዱስ ጳውሎስ መያዝ፥ መከሰስና መታሰር</u>:- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችኛ ምእመናን በደስታ ተቀበሉት። ሆኖም በተለያዩ አገሮች ለተበታተኑ የአይሁድ ወገኖች የኦሪትን ሕግ መጠበቅ አያስፈልጋችሁም እያለ ያስተምራል ተብሎ በብዙዎች ዘንድ የተስማ ስለሆነ ስጋታቸውን ገለጡለት። ስለዚህም ያን በእርሱ ላይ የተወራውን ወሬ ለማስተባበል ከአይሁድ መንፈሳዊ ሥርዓቶች አንዱን ሲፈጽም እንዲታይ መከሩት። ለዚሁም ጉዳይ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ሳለ በሌላ አገር ሲያስተምር አይተውት የነበሩ የአይሁድ ወገኖች ሕዝቡን አነሣሥተው ከቤተ መቅደስ ይዘው አወጡትና ደበደቡት። ወንድሞች የሰጡት ምክር ምንም አልጠቀመ ውም ማለት ነው። አይሁድ ይዘው ያንገላቱት በነበረም ጊዜ ከወንድሞች ምንም ዐይነት እርዳታ እንደተደረገለት አልተገለጠም። ከተከሰሰባቸው ምክን ያቶች አንዱ አረማውያንን ወደ ቤተ መቅደስ አስገባ የሚል ነው። እነዚህ ከእስያ የመጡ የአይሁድ ወገን የሆኑ ከሳሾች ሕዝቡን አሳድመው ከያዙት በኋላ በእርሱ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ እንዲህ ሲሉ አቅርበዋል።

«የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ እርዱን፤ ሕዝባችንንና ሕጋችንን፥ ይህንንም ስፍራ እየተሳደበ በየአገሩ ያለውን ሕዝብ ሁሉ የሚያስተምር ይህ ሰው ነው፤

www.ethiopianorthodox.org



ይህም አልበቃ ብሎት አረማውያንን ወደ ቤተ መቅደስ በማስገባት ይህን የተቀደሰ ስፍራ አርክሶአል፤ እያሉ ጮኹ። ይህንንም ያሉበት ምክንያት ከዚህ ቀደም የኤፌሶኑን ተወላጅ ጥሮፊሞስን ከእርሱ ጋር በከተማ አይተውት ስለነበረ እርሱን ወደ ቤተ መቅደስ ይዞት የገባ መስለሎአቸው ነው» (የሐ:ሥ: ም:21ቍ:28–29)።

ከተማዋ በሙሉ ታውካ ቅዱስ ጳውሎስን እየደበደቡ ሊገድሉት በነበረ ጊዜ ወሬው ወደ ሮማው የጦር አዛዥ ደረሰ። እርሱም ወታደሮችንና የጦር መኰንኖችን አስከትሎ ወደ ቦታው በመድረሱ ሰዎቹ ቅዱስ ጳውሎስን መደብደባቸውን አቆሙ። ቅዱስ ጳውሎስም የሁከቱ ምክንያት እንደሆነ ታምኖ ተያዘና በጥበቃ ሥር ሆነ።

የሁከቱ ምክንያት ምን እንደሆነ ለማወቅ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲናገር ቢፈቀድለትም የተሰበሰበው ሕዝብ አንዱ አንድ ነገር ሲናገር ሌላው ሌላ ነገር ይናገር ስለነበረ አዛዡ ግራ ተጋባ። ቅዱስ ጳውሎስ በሚናገርበት ጊዜ የሰዉ ሁካታና ጩኸት ስለበዛ አዛዡ ሕዝቡ ለምን ይህን ያኽል እንደሚጮኽ ለማወቅ ቅዱስ ጳውሎስ እየተገረፈ እንዲመረመር አዘዘ። ነገር ግን በጠፍር ወጥረው ሊገርፉት ሲዘጋጁ፥ ቅዱስ ጳውሎስ አጠገቡ የቆመውን የመቶ አለቃ የሮም ዜግነት ያለውን ሰው ያለ ፍርድ ልትገርፉት ተፈቅዶላችኋልን? አለው። አዛዡም ይህን በሰማ ጊዜ ደነገጠ ሊመርምሩት ተዘጋጅተው የነበሩት ሰዎችም ወዲያውኑ ከእርሱ ራቁ። አዛዡም ቅዱስ ጳውሎስ የተከሰበትን ትክክለኛ ምክንያት ለማወቅ ፈልጎ በማግስቱ በአይሁድ ሸንጎ አባሎች ፊት አቀረበው። የሸንጎውም አባሎች ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ስለነበሩባቸው የቅዱስ ጳውሎስ ንግግር ሸንጎውን ለሁለት ከፈለው። እርሱም ሲናገር ይህ ሁሉ ችግር የደረሰብኝ በትንሣኤ ሙታን የማምን ፈሪሳዊ በመሆኔ ነው አለ። ፈሪሳውያኑ ቅዱስ ጳውሎስ ምንም ስሕተት የለበትም ማለት ጀመሩ። በዚህ ጊዜ በሁለቱ ወገኖች መካከል ታላቅ ጠብና ክርክር ተነሣ። ስለዚህም አዛዡ ቅዱስ ጳውሎስን ይቦጫጭቁታል ብሎ ስለሰጋ ከመካከላቸው አውጥተው ወደ ጦሩ ሰፈር እንዲወስዱት አዘዘ።

በዚሁ ጊዜ ከአርባ የሚበልጡ ሰዎች ቅዱስ ጳውሎስን ሳይገድሉ እህል እንደማይበሉ መማማላቸውን አዛዡ ስለሰማ ቅዱስ ጳውሎስ በወታደር ታጅቦ የክፍለ ሀገሩ ዋና ከተማ ወደ ነበረው ወደ ቂሣርያ እንዲወሰድ አደረገ። እዚያም ወደ አገረ ገዢው ወደ ፊልክስ እንዲቀርብ ተደረገ።

አዛዡ ለአገረ ገዢው ለፊልክስ በጻፈው ሸኚ ደብዳቤ ጳውሎስ የሮም ዜጋ መሆኑን፥ አይሁድ እንዴት ሊገድሉት እንደነበረና እርሱ ከወታደሮች ጋር ሄዶ እንዳዳነው፥ አሁን ደግሞ ሊገድሉት ማቀዳቸውን ስለሰማ የእርሱ ጉዳይ በራሱ በአገረ ገዥው በኩል እንዲታይ የላከው መሆኑን ገለጠለት። ፊልክስም የቅዱስ ጳውሎስ ከሳሾች ሲመጡ ጉዳዩን እንደሚሰማ ገልጦለት እስከዚያ በሄድሮስ ግቢ ውስጥ እንዲጠበቅ አዘዘ።

ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ ከአምስት ቀን በኋላ ከአንዳንድ ሽማግሌዎችና ከጠበቃ ጋር ሆኖ ወደ ቂሣርያ መጣ። ቅዱስ ጳውሎስም ተጠርቶ በፊልክስ ፊት ቀረበ። የሊቀ ካህናቱ ጠበቃ ያልተጨበጠና ማስረጃ የሌለው ክስ በቅዱስ ጳውሎስ ላይ አቀረበ። ቅዱስ ጳውሎስም ተገቢ መልሱን ሰጠ። ፊልክስ ግን የጦር አዛዡ ሉስዮስ ሲመጣ ጉዳያችሁን አያለሁ ብሎ አሰናበታቸው። ፊልክስ ከቅዱስ ጳውሎስ ጉቦ ለመቀበል ተስፋ ያደርግ ነበር፤ በዚህም ምክንያት ብዙ ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስን እያስጠራ ያነጋግረው ነበር። ከሁለት ዓመት በኋላ ፌስጦስ በፊልክስ ቦታ ተተካ። ፊልክስ አይሁድን ደስ ለማሰኘት ፈልጎ ቅዱስ ጳውሎስን እንደታሰረ ተወው።

ፌስጦስ ወደ ግዛቱ ወደ ቂሣርያ ገብቶ ሦስት ቀን ከቈየ በኋላ ከዚያ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። እዚያም አይሁድ ቅዱስ ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲያ ዛውርላቸው ጠየቁት። እርሱ ግን ጳውሎስን የምትከስሱበት ጉዳይ ካለ እዚያው መጥታችሁ ክሳችሁን አቅርቡ አላቸው። እነርሱ ይህን ያሉበት ምክንያት ወደ ኢየሩሳሌም ሲወሰድ በመንገድ ላይ አድፍጠው ሊገድሉት አቅደው ስለነበረ ነው። ፌስጦስ ወደ ቂሣርያ በደረሰ ማግስት ቅዱስ ጳውሎስን አስጠርቶ በከሳሾቹ ለቀረበበት ክስ መልስ ከሰጠ በኋላ ፌስጦስ አይሁድን ለማስደሰት ፈልጎ ቅዱስ ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም ሄደህ ስለዚህ ጉዳይ እዚያ በእኔ ፊት ልትፋረድ ትፈልጋለህን? አለው። ቅዱስ ጳውሎስ ግን የአሁድን ዓላማ ስለሚያውቅ በአይሁድ እጅ ተላልፎ ላለመሰጠት ወደ ሮም ንጉሠ ነገሥት ይግባኝ አለ። ቅዱስ ጳውሎስም ይግባኝ ያለው ከአይሁድ ለመገላገል ብሎ ብቻ ሳይሆን ወደ ሮም ለመሄድ ስለፈለገም ነው (የሐ:ሥ: ም:26ቍ:17–18÷20)።

<u>ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች የተላከ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት</u>:- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው በእስር ቤት ሆኖ ነው። የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችውም በእርሱ አስተማሪነት ነው። ብዙ ምሁራን እንደተስማሙበት መልእክቱ የተጻፈው በ61 እና በ63 ዓ.ም መካከል በሮም ነው። የፊልጵስዩስ ሰው የሆነው ኤፓፍሮዲጡስ ከፊልጵስዩስ ምእመናን የተዋጣ ገንዘብ ለሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይዞለት ሄዶ ነበር። መልእክቱንም ካደረሰ በኋላ በጠና መታመሙን የፊልጵስዩስ ምእመናን ሰሙ። በአንድ በኩል ኤፓፍሮዲጡስ አገሩን ስለናፈቀ፥ በሌላ በኩል ደግሞ መታመሙን ሰምተው በመጨነቅ ላይ የነበሩትን ሰዎች ለማረጋጋት ብሎ ሐዋርያው መልእክቱን የላከው በኤፓፍሮዲጡስ እጅ ነው።

መልእክቱ በአጠቃላይ በሦስት ጉዳዮች ላይ ያተኰረ ነው። የመጀመሪያው ትኩረት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፥ ሁለተኛው ትኩረት የፊልጵፋስዩስ ክርስቲያኖች፥ ሦስተኛው ትኩረት ደግሞ የሐሰተኞች መምምህራን አስጊነት ናቸው።

1. <u>ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእስር ላይ</u>:- እግዚአብሔር በምንም ሁኔታ ፈቃዱን እንደሚፈጽም እምነት ስላለው ሐዋርያው በራሱ ሁኔታ ይተማመናል። የእርሱ መታሰር እርሱን የሚቃወም ትምህርት የሚያሠራጩትን ሰዎች

www.ethiopianorthodox.org



ዕድል ቢሰጣቸውም እንኳ እርሱ በመታሰሩ አላዘነም (ም:1ቍ:15–18)። እርሱ መታሰሩና የተቃዋሚዎች መስበክ፥ ምንም እንኳ ዓላማቸው ክፉ ቢሆን የክር ስቶስ ስም በብዙ ሰዎች ዘንድ መሰማቱ መልካም ነው። እርሱ ያለበት ሁናቴ ወደሞት የሚያመራ መሆኑን ያውቃል። ይሁን እንጂ በፊልጵስዩስ ሰዎች ጸሎ ትና የእግዚአብሔርም ዓላማ ተግባራዊ የሚሆነው በዚህ ሁኔታ ስለሆነ ከእስር እንደሚፈታ ተስፋ ያደርጋል (ም:1ቍ:19÷24–26)። ይሁን እንጂ ለእርሱ ሞት ማለት ከክርስቶስ ጋር መሆን ስለሆነ ሞትን ይመርጣል። ነገር ግን ቢኖርም፥ ቢሞትም ክርስቶስ እንደሚከብር ያምናል። እርሱም ባለበት ሁናቴ ላይ የፊልጵስዩስ ሰዎች ደስ በመሰኘት ከእርሱ ጋር እንዲተባበሩ ይጠይ ቃቸዋል። ለአደረጉለት እርዳታ የሚያመሰግን ቢሆንም እንኳ ከውጭ በሚመ ጣለት እርዳታ ላይ በመተማመን ብቻ ራሱን ዝቅ ማድረግ አይፈልግም (ም:4 ቍ:11–13)።

2. <u>የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች</u>:- ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች የሚናገረው አብዛኛው ነገር በእነርሱና በእርሱ መካከል ባለው ልባዊ ፍቅር ላይ የተመሠረተ ነው። የእርስ በርስ መተሳሰብም ስላለ የገንዘብ ስጦታ ላኩለት። በእርሱም በኩል ለእነርሱ ያለውን ስሜት ሲገልጥ እንዲህ ብሏል:-

«እናንተን በማስታውስበት ጊዜ ሁሉ አምላኬን አመሰግናለሁ፤ ስለሁላ ችሁም በምጸልይበት ጊዜ ጸሎቴ በደስታ የተሞላ ነው። ከመጀመሪያው ቀ አንሥቶ እስከ አሁን ወንጌልን በማብሠር የሥራዬ ተባባሪዎች ስለሆናችሁ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤ ይህን መልካም ሥራ በእናንተ ሕይወት ውስጥ የጀመረ አምላክ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ በሚመለስበት ቀን ወደ ፍጻሜ እንደሚያደርሰው እርግጠኛ ነኝ። ወንጌልን ለማስፋፋትና ለወንጌል ለመ ላከል በምሠራበት ጊዜ፥ እንዲሁም በእስራቴ ሁላችሁም ከእኔ ጋር የጸጋው ተካፋዮች ስለሆናችሁ እናንተን ከልብ መውደዴ ተገቢ ነው። በኢየሱ ክርስቶስ ፍቅር ሁላችሁንም ምን ያኽል እንደምናፍቅ እግዚአብሔር ምስክሬ ነው። ፍቅራችሁ ዕውቀትና ማስተዋል የሞላበት ሆኖ እያደገ እንዲሄድ እጸልያለሁ። ይኸውም የተሻለውን ነገር መርምራችሁ እንድታውቁና ክርስቶስ ተመልሶ በሚመጣበት ቀን ንጹሐችና ነውር የሌለባችሁ ሆናችሁ እንድትገኙ ነው። በዚህም ዐይነት ሕይወታችሁ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚሰጣችሁ የጽድቅ ፍሬ የተሞላ ሆኖ ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና የምታስገኙ ትሆናላችሁ» (ም:1ቍ:3–11)።

በዚህም የጠበቀ ግንኙት ምክንያት ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የራሱን ሁኔታ የገለጠው (ቍ:19–26)። በሌላ በኩል ደግሞ የእነርሱንም ግዴታ አስረ ድቶአቸዋል (ቍ:27:28)። የፊልጵስዩስ ሰዎችም በእምነታቸው ምክንያት ችግር የሚደርስባቸው መሆናቸውን ይገልጥላቸዋል (ቍ:29–30)።

የፊልጵስዩስ መልእክት አንድ ልዩ ገጽታ ስለ ደስታና ስለ መደሰት ደጋግሞ ማንሣቱ ነው። ይህም ስለደስታ የተሰጠው ትኩረት በቅዱስ ጳውሎስና በሥራ

ጓደኞቹ በአንድ በኩል፥ በፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች በሌላ በኩል ባለው ግንኙት ላይ ነው፤ እንዲሁም ደስታ በዓለም ላይና በምእመናን ላይ የወንጌሉ ትምህርት ተግባራዊ በመሆን ላይ ሚና ይኖረዋል። ቅዱስ ጳውሎስም ወንጌል ስለተሰበከ በደረሰበት ሁናቴ ይደሰታል፤ ከእስራቱ እንደሚፈታ ተስፋ ስለሚያርግ ይደሰታል፤ በፊልጵስዩስ ክርስቲያኖችና በስጦታቸው ይደሰታል፤ እርሱ ራሱ ባለበት ሁናቴ ላይ በደስታ ከእርሱ ጋር እንዲተባበሩ ይጋብዛቸዋል። ኤፖፍሮዲጡስ ከሕመሙ ድኖ ወደ እነርሱ በመመለሱ እንዲደሰቱ ይፈልጋቸዋል። በእግዚአብሔር እንዲደሰቱ ያስተምራቸዋል። ደስታ ከእነርሱ ጋር ባለው አገልግሎት የሚያበረታታ የክርስቲያን ሕይወት ገጽታ ነው። ይህም ወደ አንድነት ሚያመራ ሲሆን እርሱን ራሱን ያበረታታዋል። በፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች መካከል አንድ ዐይነት መለያየት መኖሩን ስለተገነዘበ ጠብንና ክርክርን እንዲያስወግዱ ይመክራቸዋል። ሁለት ሴቶችን በስም ጠርቶ ተስማምተው እንዲኖሩ ይመክራቸዋል። ስሙን ያልጠራው የሥራ ጓደኛውም በዚህ ረገድ እንዲረዳቸው ጠይቆታል። እነዚህም ሴቶች ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጠቃሚ መሆናቸውን ገልጦአል። ስለ ትሕትና በሰጠው ትምህርት እንዲህ ብሏል።

«እርሱ የመለኮት ባሕርይ አለው፤ ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የሚያደረገውን የመለኮት ባሕርይ እንደያዘ መቅረት አልፈለገም፤ ያለውን ክብር ትቶ እንደ ባሪያ ሆነ፤ እንደ ሰውም ተወለደ፤ በሰው አምሳልም ተገለጠ፤ በትሕትና ራሱን ዝቅ አደረገ፤ እስከ ሞት ድረስ፥ ያውም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ ወዳለው የክብር ስፍራ ከፍ አደረገው፤ ከስም ሁሉ የሚበልጠውንም ሰጠው፤ ስለዚህ ለኢየሱስ ስም ክብር በሰማይና በምድር፥ ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በጉልበታቸው ይንበረከካሉ፤ በአንደበታቸውም ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው ብለው በመመስከር ለእግዚአብሔር አብ ክብር ይሰጣሉ» (ፊልጵ: ም:2ቍ: 6–11)።

ይህም ለፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች እናንተ ክርስቲያን እስከሆናችሁ ድረስ ክርስቶስን ምሰሉትና ትሑቶች ሁኑ፤ በኋላም እግዚአብሔር ከፍ ከፍ ያደርጋችኋል ለማለት ነው።

3. <u>ተቃዋሚዎች</u>:- እዚህ ላይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሁለት የተቃዋሚ ወገኖችን ያቀርባል። አንዱ ወገን በክርስቶስ አዳኝነት፥ በክርስቶስ መስቀል ሳያምኑ የኦሪትን ሕግ በመፈጸም ብቻ እንጸድቃለን የሚሉት ወገኖች ናቸው። ይህንንም በግልጥ ሲያብራራ እንዲህ ብሏል:- «ከዚህ በፊት ጠቃሚዎች ናቸው ብዬ አምንባቸው የነበሩትን ነገሮች ሁሉ ስለ ክርስቶስ ብዬ ዋጋ እንደሌላቸው ከንቱ ነገሮች አድርጌ እቈጥራቸዋለሁ፤ ከዚህም በቀር ጌታዬን ኢየሱስ ክርስቶስን ከማወቅ የበለጠ ሌላ ምንም ነገር እንደሌለ ስለማምን ሁሉን ነገር እንደ ኪሣራ እቈጥረዋለሁ፤ ስለ እርሱም ሁሉን ነገር አጥቼአለሁ፤



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቶስንም ለማግኘት ሁሉን ነገር እንደቤት ጥራጊ እቈጥረዋለሁ» (ፊል: ም:3ቍ: 7–8)።

ሁለተኛዎቹ ወገኖች ደግሞ ጸድቀናል ወይም ድነናል ብለው የሚመጻደቁት ናቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለእነዚያ ወገኖች ምክር ሲሰጥ:-

«በትሕትና ተሞልታችሁ ሌሎች ሰዎች ከእናንተ እንደሚሻሉ አድርጋችሁ ቍጠሩ እንጂ ወገን በመለየትና በራስ ወዳድነት ወይም ያለ እኔ ማን አለ በሚል ትምክሕት ምንም ነገር አታድርጉ» ብሎአቸዋል (ፊል:ም2ቍ:3)።

እንዲሁም ሐዋርያው ራሱ እንኳን ስለራሱ ምን እንደሚል ቀጥለን እንመልከት:-

«ይህን ሁሉ ገና አላገኘሁም፤ ወይም በዚህ ሁሉ ፍጹም ሆኜአለሁ ለማለት አልችልም፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ እኔን የእርሱ አድርጎ ያዘጋጀልኝን ሽልማት ለማግኘት ወደፊት በመሮጥ እተጋለሁ። ወንድሞቼ ሆይ፥ ገና ወደዚያ እንደደረስሁ አልቈጥርም» (ፊል:ም:3ቍ:12–13)።

<u>የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ቆላስይስ ሰዎች</u>:- የቆላስይስ ከተማ የምትገኘው በፍርግያ ክፍል ከታናሽቱ እስያ ደቡባዊ ምዕራብ በላዶቂያና በኤራጶሊስ መካከል ነበር። የቆላስይስን ቤተ ክርስቲያን የመሠረተው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሳይሆን የሥራ ጓደኛው ኤፓፍራ ነው። ኤፓፍራም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእስር ቤት ሆኖ ሊጠይቀው ሄዶ ሳለ በቆላስይስ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእስር ቤት ሆኖ ሊጠይቀው ሄዶ ሳለ በቆላስ[illegible]ስ ተቃዋሚ ወገኖች መነሣታቸውን ስለገለጠለት መልእክቱን የጻፈበት ዋና[illegible] ምክንያት ለዚሁ ነው። የተቃዋሚዎቹ የክሕደት ትምህርት ነው የተባለው[illegible] እነዚያ የአይሁድ ተመላሽ ክርስቲያኖች ከአሕዛብነት የተመለሱት ክር[illegible]ቲያኖች የግድ መገረዝ፥ ልዩ ልዩ የአይሁድ በዓላትን፥ ለምሳሌ እንደ [illegible] መባቻና ሰንበትን ማክበር፥ ከአንዳንድ ምግቦች መከልከልና መላእክትን [illegible] ለክ አለባቸው ይሉ ነበር ማለት ነው (ም:2 ቍ: ቍ:8፥ 11፥ 16፥ 1[illegible]፥ 21፥ ም4 ቍ:11)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ብዙዎቹ የኦሪት ሥርዓቶች እንደ ጥላ ሆ[illegible]ው በምሳሌነት ያለፉ መሆናቸውን ሲያስረዳ እንዲህ ብሏል:-

«እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ፥ በዓላትን ወይም የወር መባቻን፥ ወይም ሰንበትን በማክበር ምክንያት ማንም አይፍረድባችሁ። እነዚህ ሁሉ ወደፊት ይመጡ ለነበሩት ነገሮች እንደ ጥላ ናቸው፤ እውነቱ የሚገኘው ግን በክርስቶስ ነው» (ም:2ቍ:16–17)።

«ከክርስቶስ ጋር ሞታችሁ ከዚህ ዓለም ሥርዓቶች የተለያችሁ ከሆናችሁ፥ ታዲያ፥ ከእነርሱ እንዳልተለያችሁ ዐይነት ሆናችሁ ስለምን እንደዚህ ላሉት ትእዛዞች ትገዛላችሁ? ትእዛዞቹም «አትያዝ፤ አትቅመስ፤ አትንካ» የሚሉት ናቸው። እነዚህ ሁሉ በሰው ሠራሽ ትእዛዝና ትምህርት ላይ የተመሠረቱ ስለሆኑ ሥራ ላይ ከዋሉ በኋላ ለመጥፋት የተወሰኑ ናቸው (ም:2ቍ:20–22)።

የሐዋርያት ጉባኤ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት ከአረማዊነት ወደ ክርስትና የተመለሱትን ምእመናን አስፈላጊ ባልሆኑ ሥርዓቶች ማስቸገር እንደማይገባ ስምምነት ቢደረግበትም እንኳ ከአይሁዳዊነት ወደ ክርስትና የገቡት ወገኖች ግን በየጊዜው ማስቸገራቸው አልቀረም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለተ ለያዩ ጉዳዮች የተለያዩ መልሶችን ሰጥቶባቸዋል። ለምሳሌ ስለ ግዝረት እንዲህ ብሏል:-

«በእርሱም በማመናችሁ ተገርዛችኋል፤ ይህም መገረዛችሁ ኃጢአተኛውን ሥጋ የማስወገድ በክርስቶስ የተደረገ ነው እንጂ ሰው ሠራሽ መገረዝ አይደ ለም። በተጠመቃችሁ ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ተቀበራችሁ፤ ከእርሱመ ጋር ከሞት ተነሣታችኋል፤ ከሞት የተነሣችሁትም ክርስቶስን ከሞት ባስነሣው በእግዚአ ብሔር ኀይል በማመናችሁ ነው። በኃጢአተኛነታችሁና ኃጢአተኛ ሥጋ ችሁ በክርስቶስ በማመን ባለመገረዙ ምክንያት ሙታን ነበራችሁ፤ አሁን ግን እግዚ አብሔር ከክርስቶስ ጋር ሕያዋን አድርጓችኋል፤ ኃጢአታችንንም ሁሉ ይቅር ብሎልናል» (ቆላ:ም:2ቊቊ:11–13)።

ሌላው እነዚህ ሐሰተኞች መምህራን የተባሉት የሚያቀርቡት አስተሳሰብ አይሁዳዊነትና ክርስቲያንነት ከግሪኮች አስተሳሰብ ጋር የተቀላቀለ ሆኖ የግኖስ ቲኮች አስተሳሰብ ሳይሆን አይቀርም የሚል ነው። ከግኖስቲኮች አስተሳሰብ መካከልም ሰው እግዚአብሔርን የሚያገኘው በዕውቀት መሆኑ፥ ሰው የሚድ ነው ከተፈጠረው ዓለም በመለየት መሆኑና ይህን ለማድረግ ሥጋን ማድከምና ከጋብቻ መከልከል መሆኑ፥ ሰው የሚድነው በዐዋቂዎች መካከል በሚደረግ ሥርዓትና ወግ መሆኑ ይገኙባቸዋል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህን አስተሳሰብ በመቃወም መልስ ሰጥ ቶአል። ለምሳሌ እግዚአብሔርን ማግኘት የሚቻለው በዕውቀት ማለት በዓ ለማዊ ፍልስፍና ሳይሆን ክርስቶስን በማመን መሆኑን ሲገልጥ እንዲህ ብሏል:-

«በክርስቶስ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በሰው ሠራሽ ወግና በዓለማዊ ሥር ዓት ላይ በተመሠረተ በፍልስፍናና በከንቱ ሽንገላ ማንም እንዳያጠምዳችሁ ተጠንቀቁ» (ቆላ:ም:2ቊ:8)።

ሰው የሚድነው የክርስቶስን ወንጌል በመቀበል እንጂ እነርሱ እንደሚሉት በዐዋቂዎች መካከል በሚደረግ ሥርዓትና ወግ አለመሆኑን ሲገልጥ እንዲህ ብሏል:-

«ቀድሞ ከእግዚአብሔር ርቃችሁ ትኖሩ ነበር፤ በአሳባችሁና በክፉ ሥራ ችሁም ምክንያት ጠላቶቹ ነበራችሁ። አሁን ግን ቅዱሳንና ንጹሓን፥ ነቀፋም የሌለባችሁ አድርጎ በፊቱ ሊያቀርባችሁ፥ ልጁ በሥጋ በመሞቱ፥ ምክንያት እግዚአብሔር ከራሱ ጋር አስታረቃችሁ። ይህም የሚሆነው ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ በወንጌሉ ከተገኘው ተስፋ ሳትናወጡ በእምነት ጸንታችሁ ስትኖሩ ብቻ ነው፤ ይህም ወንጌል እናንተ የሰማችሁትና በዓለም ላይ ላሉት



www.ethiopianorthodox.org

ሰዎች ሁሉ የታወጀ ነው፤ እኔ ጳውሎስም አገልጋይ የሆንኩት ለዚሁ ወንጌል ነው» (ቆላ:1፥21–23)።

እነርሱ እንደሚሉት ዕውቀት ማለት ዓለማዊ ፍልስፍና ሳይሆን ክርስቶስን ማወቅ መሆኑን እንዲህ ብሎ ገልጦታል:-

«የእግዚአብሔርን ቃል ለእናንተ በሙሉ እሰብክ ዘንድ ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ኃላፊነት መሠረት የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆኜአለሁ። ይህም የእግዚአብሔር ቃል ባለፉት ዘመናት ከሰው ልጆች ተሰውሮ የቆየውና አሁን ግን እግዚአብሔር ለሚያምኑት ሁሉ የገለጠው ምሥጢር ነው። እግዚአ ብሔርም ለቅዱሳኑ ሊገልጥላቸው የፈቀደው ያለውን የዚህን ምሥጢር የክብር ብልጽግና በእናንተ በአሕዛብ መካከል ምን ያኽል ታላቅ መሆኑን ነው። ይህም ምሥጢር በተስፋ የምንጠባበቀው ክብር የሚገኝበት ክርስቶስ በእናንተ መካከል መሆኑ ነው። እያንዳንዱ ሰው በክርስቶስ የተሟላ ሰው እንዲሆን አድርጎ ማቅረብ ለሰው ሁሉ ጥበብን በማስተማርና በመምከር ስለ ክርስቶስ እንሰብካለን» (ም:1ቊ:26–28)።

ዕውቀት ማለት በክርስቶስ ማመንና ክርስቶስን ማወቅ መሆኑን ከመግለጹም ጋር የክርስቶስን መለኮታዊ ክብርና ከእግዚአብሔር አብ ጋር ያለውን መለኮ ታዊ እኩልነት ዘርዝሮ ገልጦአል።

ክርስቲያኖችም እንደመሆናቸው ኃጢአት መሥራትን ሁሉ አስወግደው መንፈሳዊውን ተግባር እንዲያከናውኑ በዝርዝር መክሮአቸዋል። ኃጢአትን የቀድሞው ሕይወት ሲለው አዲሱ ሕይወት የሚለው ደግሞ ከክርስትና በኋላ ያለውን ሕይወት ነው። እንዲሁም በቤተሰብ ስላለው ሕይወት በተመለከተ የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ከሌላው አባል ጋር ሊኖረው የሚገባውን ግንኙ ትና ግዴታ በዝርዝር አስረድቶአል።

በመጨረሻም የተለያዩ ምክሮችን ከሰጠና ሰላምታዎችን ካቀረበ በኋላ መልእክቱን ፈጽሞአል።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

በመጽሐፈ ኢያሱ ውስጥ የምናስተውለው ትልቁ ጉዳይ እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ማለትም ለሰጠው ተስፋ ምን ያኽል ታማኝ መሆኑን ነው።

እግዚአብሔር ለአብርሃም:-

«ይህችን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ» ብሎት ነበር (ዘፍ:ም:12ቊ:7)።

ለይስሐቅ:- «በዚህች ምድር ተቀመጥ፤ ከአንተ ጋርም እሆናለሁ፤ እባርክ ሃለሁም፤ ይህንንም ምድር ለአንተና ለዘርህ እሰጣለሁ፥ ለአባትህ ለአብርሃም የማልሁለትንም መሐላ አጸናለሁ» ብሎት ነበር (ዘፍ:ም:26ቊ:3)።

ለያዕቆብም:- «የአባትህ የአብርሃም አምላክ፥ የይስሐቅም አምላክ እኔ እግዚአብሔርን ነኝ፤ ይህችን አንተ የተኛህባትን ምድር ለአንተም፥ ለዘርህም እሰጣለሁ» ብሎት ነበር (ዘፍ:ም:28ቍ:13)።

በበረሓ ይንከራተቱ ለነበሩ ልጆቻቸው:- «አንተ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነህና አምላክህ እግዚአብሔር ይህችን መልካም ምድር ርስት አድርጎ የሰጠህ ስለጽድቅህ እንዳይደለ ዕወቅ» ብሎአቸዋል (ዘዳ:ም:9ቍ:6)።

የእስራኤል ልጆች በተለያዩ ሁናቴዎች እግዚአብሔርን ያስቈጡት ቢሆኑም እንኳ እግዚአብሔር ግን ለቃሉ ታማኝ በመሆኑ በድል ላይ ድልን በማጐናጸፍ የከነዓንን ምድር በርስትነት ሰጥቶአቸዋል። በርስትነትም ሲሰጣቸው ሁሉን ነገር አመቻችቶላቸዋል። ለምሳሌ የዮርዳኖስን ወንዝ በተአምር ለሁለት ከፍሎ በደረቅ መሬት ላይ እየተራመዱ እንዲሻገሩ ረድቶአቸዋል። ከዚያም የኢያሪኮን ከተማ ግንብ አፍርሶላቸው ከተማይቱን ለመውረር ችለዋል። ወደ ኋላ የምንመለስበት ችግር ደርሳ ለችግሩ መፍትሔ ከተገኘለት በኋላ ዐይ የተባለችውን ከተማ ድል አድርገው ወርረዋታል።

እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች የሰጠውን የተስፋ ቃል ተግባራዊ ለማድረግ ተአምራትንና ድንቅ ነገሮችን አድርጎአል። ለምሳሌ የኢየሩሳሌም፥ የኬብሮን፥ የያርሙት፥ የላኪሽና የዔግሎን ነገሥታት ከእስራኤላውያን ጋር ጦርነት በገጠሙ ጊዜ እስራኤላውያን ብዙዎቹን የጠላት ወታደሮች የፈጁ ከመሆናቸውም በላይ ሰልፉ የእግዚአብሔርም ጭምር ስለነበረ በእስራኤል ጠላቶች ላይ የበረዶ ድንጋይ አወረደባቸው። እስራኤላውያን ከገደሉአቸው ይልቅ በበረዶው ድንጋይ የሞቱት በዙ። እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን ተበቅለው እስኪጨረሱ ድረስ ፀሐይና ጨረቃ እንዲቆሙና ቀኑ እንዲረዝምለት ኢያሱ እግዚአብሔርን ለመነ፤ እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰማው። ጠላቶቻቸውንም ድል ነሥተው ወደ ሰፈራቸው ተመለሱ። እግዚአብሔር ለእነርሱ ይዋጋላቸው ነበር። እንደገናም እስራኤላውያን መቄዳን፥ ሊብናን፥ ላኪሽን፥ ዔግሎንን፥ ኬብሮንን፥ ደቢርንና ኔጌብን አሸንፈው ያዙ። ከእነዚህም ሌላ ብዙ አገሮችን አሸንፈው እንዲይዙ እግዚአብሔር ረዳቸው። ብዙ አገሮ ችን ድል አድርገው ቢይዙም እንኳ ገና መያዝ ያለባቸው ያልተያዙ አገሮች ነበሩ። ኢያሱ አርጅቶ የመሞቻው ጊዜ በመቃረቡ ገና ያልተያዙት አገሮች በእርሱ እርዳታ ወደፊት የሚያዙ መሆናቸውን እግዚአብሔር ከገለጠለት በኋላ ምድሪቱን በእስራኤል ነገዶች መካከል እንዲያከፋፍል ለኢያሱ መመሪያ ሰጠው። ይህም የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የሚፈጸመው በፍጹምነት እንጂ በግማሽ የሚቀር አለመሆኑን ነው። ስለዚህም የእስራኤል ልጆች በተዋጉና ድል ባደረጉአቸው ጦርነቶች ሁሉ የእግዚአብሔር እርዳታ አልተለያቸውም።

እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች የቀድሞ አባቶች የገባው ቃል ኪዳንና ለቃል ኪዳኑም ተግባራዊነት ያደረገላቸው እርዳታ የከነዓን ሰዎች ከደረሰባቸው መሸነፍና መፈጀት ጋር በማስተያየት በእግዚአብሔር ዳኝነት ላይ



ጥያቄ የሚያቀርቡ ሰዎች አሉ። በእግዚአብሔር ጠባዮች ውስጥ ተዘርዝሮ እንደተገለጠው የእግዚአብሔርን ዕውቀት ጊዜና ቦታ አይወስነውም። በዚህም መሠረት የከነዓን ሕዝብ በጣም በደለኛ በመሆን መቀጣት ያለበት መሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ አስቀድሞ የታወቀ ነበር። በዚህም መሠረት እግዚአብሔር ለአብርሃም ከአራት መቶ ዘመን በፊት ሲነግረው:-

«ልጆችህ በአራተኛው ትውልድ ወደዚህ ይመለሳሉ፤ የአሞራውያን ኃጢአት ገና አልተፈጸመምና» (ዘፍ:ም:15ቍ:16) ብሎታል።

እንዲሁም በሌላ ጊዜ እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች ሲነግራቸው:-

«አምላክህ እግዚአብሔር ከፊትህ ካወጣቸው በኋላ፥ ስለጽድቄ እወርሳት ዘንድ ወደዚች ምድር እግዚአብሔር አገባኝ ስትል በልብህ አትናገር፤ እነዚህን አሕዛብ ስለ ኃጢአታቸው እግዚአብሔር ከፊትህ ያወጣቸዋል» (ዘዳ:ም: 9:ቍ:4)።

«ለሌሎች አማልክት ብትሰግድ፥ ብታመልካቸውም፥ ፈጽማችሁ እንደምትጠፉ እኔ ዛሬ እነግራችኋለሁ፤ ዮርዳኖስን ተሻግረህ ትወርሳት ዘንድ በምትገባባት ምድር ዘመናችሁን አታስረዝሙም» (ዘዳ:ም: 30ቍ: 17–18)።

ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም ሊጠቀሱ የሚችሉ ጥቅሶች እንደሚያመለክቱት እግዚአብሔር፥ የከነዓን ሕዝብ ወደፊት ሊፈጽም ያለውን በደል አስቀድሞ በማወቁ ለልጆቻቸው የከነዓንን ምድር እንደሚሰጣቸው ቃል ይግባላቸው እንጂ እስራኤላውያንም ኃጢአት ቢሠሩ እንደ ከነዓናውያን እንደሚቀጡ ገልጾላቸዋል። ይህም ትክክለኛው የእግዚአብሔር ፍርድ ነው። ከነዓናውያን የተቀጡት በእስራኤላውያን አማካይነት ይሁን እንጂ እስራኤላውያንም ሲበድሉ በሌሎች ሕዝቦች መሣሪያነት ተቀጥተዋል። በዚህም እግዚአብሔር ለማንም የማያዳላ ትክክለኛ ዳኛ መሆኑን እንረዳለን።

እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ እንደመሆኑ እርሱም ከሰዎች የቃል ኪዳን ታማኝነትን ይጠብቃል። ያን ቃል ኪዳን የማይጠብቅ ሰው ይቀጣል። በዚህም መሠረት እግዚአብሔር በጦርነቱ ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለእስራኤል ልጆች ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአቸው ሳለ ከእነርሱ መካከል ዓካን የተባለው ሰው ቃል ኪዳኑን አፍርሶ በድብቅ ምርኮ ስለወሰደ እስራኤላውያን ዐይ በምትባል ትንሽ አገር በመሸነፍ ተዋረዱ። በኋላ ግን ዓካንና ሥራው ተጋልጠው ዓካን በሞት ከተቀጣ በኋላ እስራኤላውያን ያቺን አገር ድል ለማድረግ ችለዋል።

ኢያሱ በነበረበት ዘመን ሁሉ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ያደረገውን ድንቅ ነገር ሁሉ ያዩት የዚያ ዘመን ሰዎች እግዚአብሔርን እያመለኩ ኖረዋል። ይሁን እንጂ በዚያም ዘመን ቢሆን ዐልፎ ዐልፎ እግዚአብሔርን የሚያስቆጡ ተግባሮች መፈጸማቸው አልቀረም ነበር። ስለዚህም የእግዚአብሔርን ውሳኔ ቀጥለን እንመልከት:-



www.ethiopianorthodox.org

«የእግዚአብሔር መልአክ ከጌልጌላ ወደ ቦኪም ሂዶ እስራኤላውያንን» እንዲህ አላቸው፤ እኔ ከግብጽ ምድር አውጥቼ ለቀድሞ አባቶቻችሁ ልሰጣቸው ቃል ወደገባሁላቸው ምድር አመጣኋችሁ፤ እንዲህም አልሁ:- ከእናንተ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳን ከቶ አላፈርስም፤ እናንተ በዚህ ምድር ከሚኖሩ ሕዝብ ጋር ምንም ዐይነት ቃል ኪዳን አታድርጉ፤ መሠዊያዎቻቸውንም አፍርሱ፥ እናንተ ግን አልታዘዛችሁም፤ ይህንስ ያደረጋችሁት ለምንድን ነው? ስለዚህ አሁን እነዚህን ሕዝቦች ከፊታችሁ እንደማላስወጣቸው እነግራችኋለሁ፤ እነርሱ ለእናንተ ጠላቶች ይሆናሉ፤ ባዕዳን አማልክታቸውም ወጥመድ ይሆኑባችኋል» (መሳ:ም:2ቍ:1–3)።

እግዚአብሔር የእስራኤልን ጠላቶች ሙሉ ለሙሉ ሳያስወጣ ለመቅረቱ አራት ምክንያቶች ተሰጥተዋል።

የመጀመሪያው ምክንያት ሕዝቡ እግዚአብሔርን ማምለክ ትቶ ባዕዳን አማልክትን በመከተሉ ሊቀጣው ዐቅዶ መሆኑን የሚያስረዳውን የእግዚአብሔርን ቃል ቀጥለን እንመልከት።

እግዚአብሔር መስፍን ባስነሣላቸው ጊዜ ሁሉ እርሱ ከመስፍኑ ጋር ነበር፤ በሚያሳድዱአቸውና በሚጨቍኑአቸው ጠላቶች ምክንያት ሕዝቡ ወደ እግዚብሔር በሚጮኹበት ጊዜ እግዚአብሔር ያዝንላቸው ስለነበረ በመስፍኑ ዘመን ሁሉ ከጠላቶቻቸው እጅ ያድናቸው ነበር። ነገር ግን መሪ በሚሞትበት ጊዜ ሁሉ ተመልሰው ሌሎች አማልክትን በመከተል፥ ለእነርሱም በመስገድና እነርሱንም በማምለክ ከአባቶቻቸው የከፋ በደል ይፈጽሙ ነበር፤ መጥፎ ድርጊታቸውንና ልበ ደንዳና መሆናቸውን አልተዉም። ስለዚህ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ እጅግ ተቈጥቶ እንዲህ አለ:- «ይህ ሕዝብ ከአባቶቹ ጋር የገባትን ቃል ኪዳን አፈረሰ፤ ትእዛዝን አልጠበቀም። ስለዚህ ኢያሱ በሞተ ጊዜ በምድሪቱ የነበሩትን ሰዎች አንዳቸውንም አላስወጣላቸውም» (መሳ:ም:2ቍ:18–22)።

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር በእነዚያ ሳይወጡ በቀሩት ሰዎች አማካይነት እስራኤላውያንን ሊፈትናቸው ፈልጎ ለመሆኑ የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት።

«እነዚህ እስራኤላውያን እንደ ቀድሞ አባቶቻቸው መንገዴን ይከተሉ ወይም አይከተሉ እንደሆነ በእነዚህ አሕዛብ መሣሪያነት እፈትናቸዋለሁ» (መሳ:ም:2ቍ:22)።

ሦስተኛው ምክንያት የጦርነት ልምድ ያልነበራቸውን እስራኤላውያንን የጦርነት ልምድ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው። ይህንንም በሚከተለው ጥቅስ እንመልከት።

«በከነዓን ምድር ጦርነት ያልተለማመዱ እስራኤላውያንን ለመፈተን እግዚአብሔር በምድሪቱ የተዋቸው ሕዝቦች እነዚህ ናቸው። ይህንንም ማድረጉ



www.ethiopianorthodox.org

ቀድሞ የጦርነት ልምድ ያልነበራቸውን የእስራኤል ትውልድ የጦርነት ስል ለማስተማር ብሎ ነው» (መሳ:ም:3ቍ:1–2)።

አራተኛው ምክንያት ሀገሪቱ ባዶ ሆና አራዊት እንዳይበዙባት ተብ ለመሆኑ የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት።

«አምላክህ እግዚአብሔር እነዚህን አሕዛብ በጥቂት በጥቂቱ ከፊት ያወጣቸዋል፤ የምድረ በዳ አራዊት እንዳይበዙብህ ሁሉንም በአንድ ጊ አታስወጣቸውም» (ዘዳ:ም:7ቍ:22)።

ኢያሱና በኢያሱ ጊዜ የነበረው ትውልድ በሙሉ ሞቶ እግዚአብሔርን ለእስራኤል ያደረገውን መልካም ነገር የማያውቅ ሌላ ትውልድ በተነሣ ጊዜ የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ብዙ ክፉ ነገሮችን ማድረግ ጀመሩ። እግዚአብሔርም በዚህ ተቈጥቶ በዙሪያቸው ያሉ ጠላቶቻቸው እንዲበረ ቱባቸው አደረገ። እነርሱም በጣም አስጨንቀው ገዙአቸው። እስራኤላውያን ግን የጠላት አገዛዝ ቀንበር በከበደባቸው ጊዜ ሁሉ ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ። እግዚአብሔርም እስራኤላውያን በንስሓ በተመ ለሱ ቍጥር አንድ መሪ እያስነሣላቸው በዚያ መሪ አማካይነት ከጭቈና ቀንበር አወጣቸው። እነርሱ ግን አንድ መሪ ሞቶ ሌላ መሪ እስኪነሣላቸው ድረስ ወ ኃጢአት ሥራቸው ይመለሱ ነበር። አሁንም የጭቈናው ቀንበር ሲበረታባቸው ወደ እግዚአብሔር በንስሓ ይመለሳሉ፤ በንስሓ እስከተመለሱ ድረስ ደግ አሁንም እግዚአብሔር ሌላ መሪ አስነሥቶ ያድናቸዋል።

በዚህ በመሳፍንት መጽሐፍ እንደተመለከተው የእስራኤል ልጆች ምን ዐይነት ኃጢአት ቢሠሩ በንስሓ ወደ እግዚአብሔር በተመለሱ ቍጥር ይቅር አድርጎላቸዋል። ይህም ሁናቴ እግዚአብሔር ምን ያኽል ይቅር ባይ አምላ መሆኑን ያመለክታል።

እንግዲህ እግዚአብሔር በመሳፍንት መጽሐፍ ውስጥ ከእስራኤል ሕዝ ጋር በነበረው ግንኙነት በቃል ኪዳኑ ምን ያኽል የጸና መሆኑን እንመለከታለን ማንም ሰው ኃጢአት ቢሠራ እንደሚፈርድበትና በንስሓ የእግዚአብሔር ይቅርታ ቢለምን እንደሚምረው የማይለወጠው ወይም የማይሻረው የእግዚ ብሔር ቃል ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ምን ያኽል ችግር እንደሚደርስበት አስቀድ በመንፈስ ቅዱስ ቢነገረውም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመፈጸም ለነፍሱ እን የማይሳሳ መሆኑን ሲያመልክት ምን እንዳለ እንመልከት:-

«እዚያ ስደርስ ምን እንደሚደርስብኝ ሳላውቅ፥ በመንፈስ ቅዱስ ታዝ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዴ ነው፤ ይሁን እንጂ እስራትና ስደት እንደሚያጋጥመ በየከተማው መንፈስ ቅዱስ ነግሮኛል። እኔ ግን አገልግሎቴን እስክፈጽም ጌታ ኢየሱስ የሰጠኝን ሥራ እስካከናውን ድረስ፥ ለገዛ ሕይወቴ እን አልሳሳም፤ አገልግሎቴም የእግዚአብሔርን የጸጋ ወንጌል ማብሠር ነው (የሐ:ሥ:ም:20ቍ:22–24)። በሌላ ጊዜ ደግሞ እንዲህ ብሏል:-

«እንደዚህ እያለቀሳችሁ ለምን ልቤን ትሰብሩታላችሁ? እኔ ስለጌታ ኢየሱስ ስም በኢየሩሳሌም ለመታሰር ብቻ ሳይሆን ለመሞትም ዝግጁ ነኝ» (የሐ:ሥ:ም:21ቍ:13)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የፈጣሪውን ፈቃድ ለመፈጸም እንደዚህ አድርጎ ለእስራት ብቻ ሳይሆን ለመሞት እንኳ ዝግጁ መሆኑን ያመለከተው በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም ጭምር ነው። ለምሳሌ ከቤተ መቅደስ ጐትተው በማውጣትና በመደብደብ ሊገድሉት ተቃርበው በነበረ ጊዜ የጦር አዛገፉ ያዳነው መሆኑ ይታወሳል። ጉዳዩ በዚህ አላበቃም፤ ነገር ግን ሐዋርያው የጦር አዛገፉን ፈቃድ ጠይቆ እንደዚያ ሊቦጫጭቀው ለነበረው ሕዝብ እንዴት ወደ ክርስቶስ እንደተመለሰ ተረከ። ወደ ክርስቶስ የመመለሱን ታሪክ በፊሊክስ ፊትም ተናግሮአል። ይህን ሁሉ በሚያደርግበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ከመትጋቱ በቀር ምንም ለሕይወቱ አይሳሳም ነበር። ይህ ድርጊቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተደረገ መሆኑ የሚታየው ጌታችን በሌሊት በአጠገቡ ቆሞ «አይዞህ በኢየሩሳሌም እንደመሰከርህልኝ እንዲሁም በሮም ልትመሰክርልኝ ይገባል» ማለቱ ነው ( ም:23ቍ:11)።

ይህም የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቃሉ ታማኝነት የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር ችሎታ ኖሮአቸው ኀላፊነት ያለባቸው ሰዎች ምን ያኽል መንፈስ ጠንካሮች መሆን እንደሚገባቸው ያስተምረናል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች በላከው መልእክቱና በሌሎችም መልእክቶች ሁሉ በተለየ ሁናቴ ምስጋናውንና ደስታውን ይገልጣል። አጻጻፉም በአባትና በልጆች መካከል መሰል ግንኙነት ነው። ፍቅሩንም በተለየ ሁናቴ ገልጦላቸዋል።

እርሱ በመታሰሩ ምክንያት አንደኛ የወንጌሉ ትምህርት ሳይስፋፋ ይቀራል፤ ሁለተኛ አይሁዳዊነቱ የሚጐትታቸው ክርስቲያኖች ይበረታቱና ወደ አልሆነ አቅጣጫ ይመሩት ይሆናል ተብሎ የነበረውን ስጋት ስላወቀ ይመስላል:- «ወንድሞቼ ሆይ፥ በእኔ ላይ የደረሰው ነገር ሁሉ ወንጌል በይበልጥ እንዲስፋፋ ማድረጉን እንድታውቁ እወድዳለሁ» ያለው።

የእርሱ መታሰር ወንጌልን እንዴት ሊያስፋፋው ቻለ? ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው ገና በኢየሩሳሌም በነበረ ጊዜ በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለክርስቶስ መስክሮአል። ጌታችንም በሕልሙ ተገልጦለት «በኢየሩሳሌም እንደመሰከርህልኝ በሮም ልትመሰክርልኝ ይገባል» ብሎታል። በዚህም መሠረት በሮም በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለክርስቶስ ሲመሰክር እንደነበረ ይታመናል። በሚመሰክርበትም ጊዜ የክርስቶስ ስም በብዙዎች ዘንድ ይሰማል ማለት ነው። የቤተ መንግሥቱ ሠራተኞች ስለ እርሱና የእርሱን ትምህርት ሰምተው የሚያውቁ ከሆነ እርሱ መታሰሩን በማየታቸው ደንግጠው ሸሽተው የነበሩት ወይም ወደ እርሱ ለመምጣት ፈርተው የነበሩ አማኞች ድፍረት ተሰማቸው ማለት ነው። ስለዚህም ነው ይህን ማረጋገጫ የሰጠው:-



www.ethiopianorthodox.org

«በእኔ መታሰር ምክንያት ከአማኞች ወንድሞች ብዙዎቹ በይበልጥ በጌታ የሚተማመኑ ሆነዋል፤ ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ያለ ፍርሃት ለማብሠር ከቀድሞ የበለጠ ድፍረት አግኝተዋል» (ም:1ቍ:14)።

እንዲሁም ክርስቶስን የሚያበሥሩት ሁለት ዐይነት ሰዎች መሆናቸውን አመልክቷል። አንዳንዶቹ በቅንአትና በጥላቻ ሲያበሥሩ ሌሎቹ ግን በቅን ልቡና ያበሥሩታል ብሏል። በቅንአትና በጥላቻ ያበሥሩታል ያላቸው ክርስቲያኖች ሁሉ የኦሪቱን ሥርዓት መፈጸም አለባቸው ብለው የሚከራከሩት የአይሁድ ተመላሾች ናቸው። በቅንነት ያበሥሩታል ያላቸው ደግሞ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን መንገድ የሚከተሉትን መምህራን ነው። እንደ እርሱ አባባል በዚህም ሆነ በዚያ ክርስቶስ የሚሰበክ ስለሆነ ደስ ይለኛል ብሎአል። ሌላው የሚደሰትበት ምክንያት በጌታችን እርዳታና በእነርሱ ጸሎት ከእስራቱ የሚፈታ መሆኑን ስለሚያምን ነው። እርሱ እንዳለው መሞት ማለት ከክርስቶስ ጋር መኖር ስለሆነ ለእርሱ መሞት በተሻለው ነበር። ይሁን እንጂ መኖሩ እነርሱን የሚጠቅም ከሆነ መኖሩን እንደሚመርጥ ገልጾአል።

ለሥጋዊ ሕይወት ሞት ማለት ክስረት ሲሆን ለመንፈሳዊ ሕይወት ግን ጥቅም አለው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ለእኔ ሕይወት ማለት በክርስቶስ መኖር ነው፥ ሞትም ማለት ጥቅም የሚገኝበት ነገር ነው» በማለት ያብራራል። ይህም ማለት ክርስቶስን በዚህ ዓለም ማገልገል ወይም በወዲያኛው ዓለም ከእርሱ ጋር በመኖር መደሰት ማለት ነው።

በትሕትና የክርስቶስን ምሳሌነት እንዲከተሉ በጥብቅ ገልጾላቸዋል።

## ጥያቄዎች

1. ኢያሱ ከማንኛው የእስራኤል ነገድ ነበር?
2. በበረሓው ጉዞ ኢያሱ ምን ነበር?
3. ኢያሱ ሙሴ ከሞተ በኋላ ምን ሆነ?
4. መጽሐፈ ኢያሱ ስንት ምዕራፎች አሉት?
5. እግዚአብሔር ለኢያሱ ቃል የገባለት ምን ብሎ ነው?
6. የከነዓንን ምድር ለመውረር ዝግጅት ያመች ዘንድ ኢያሱ ምን አደረገ?
7. ረዓብ የተባለችው ሴተኛ ዐዳሪ ምን አደረገች?
8. የእስራኤል ሕዝብ ዮርዳኖስን እንዴት ተሻገሩ?
9. ኢያሱ በጌልጌላ ምን አደረገ?
10. ዓካን የሚባል ሰው ምን አደረገ?
11. በእርሱስ ድርጊት ምክንያት እስራኤላውያን ምን ሆኑ?
12. በመጨረሻስ ዓካን ምን ደረሰበት?

13. እስራኤላውያን ወደሚወርሱት ምድር ሲገቡ በረከቱን የት መርገሙን ደግሞ የት ሆነው እንዲያውጁ ነው ሙሴ አዝዞአቸው የነበረው?

14. ኢያሱ መሠዊያ ሠርቶ የሚቃጠልና የኅብረት መሥዋዕት ያቀረበበት ተራራ ማን ይባላል?

15.ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉት አገሮች ኀይላቸውን አስተባብረው በኢያሱና በእስራኤላውያን ላይ የመጡት በምን ምክንያት ነው?

16. የገባዖን ሰዎች ኢያሱን ያታለሉት እንዴት አድርገው ነው?

17. የኢየሩሳሌም፥ የኬብሮን፥ የያርሙት፥ የላኪሽና የዔግሎን መንግሥታት ለምን በገባዖን ላይ አደጋ ጣሉባት?

18. እስራኤላውያን ከአምስቱ የአሞራውያን መንግሥታት ጋር በተዋጉ ጊዜ እግዚአብሔር ያደረጋቸው ተአምራት ምንና ምን ናቸው?

19. እስራኤላውያን በጠላቶቻቸው ተሸንፈው የጭቈና ቀንበር የሚጠነክር ባቸው በምን ምክንያት ነበር?

20. እስራኤላውያን ከጨቋኞቻቸው የሚገላገሉት ምን ሲያደርጉ ነበር?

21. መሳፍንት የተባሉት ስንት ነበሩ?

22. መሳፍንት የተባሉት ምን ዐይነት ሰዎች ነበሩ?

23. እስራኤላውያን ኃጢአት በፈጸሙ ቍጥር እግዚአብሔር የሚቀጣቸው እንዴት ነበር?

24. ይቅርታስ የሚያደርግላቸው መቼ ነበር?

25. መጽሐፈ መሳፍንት በአጠቃላይ በስንት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል? በምን በምን?

26. በመጽሐፈ መሳፍንት ሁለት አሳዛኝ ታሪኮች ምንና ምን ናቸው?

27. ሐዋርያው ጳውሎስ የተያዘው የት ነው?

28. ከእስያ የመጡ አይሁድ ቅዱስ ጳውሎስን ባስያዙት ጊዜ ምን ብለው ከሰሱት?

29. አይሁድ ሐዋርያውን ቅዱስ ጳውሎስን በመደብደብ ሊገድሉት በተቃረቡ ጊዜ ደርሶ ከእጃቸው ያደነው ማነው?

30. ቅዱስ ጳውሎስ እየተገረፈ እንዲመረመር ያዘዘ ማነው?

31. ለምንስ ትእዛዙ ተግባራዊ ሳይሆን ቀረ?

32. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት በቀረበ ጊዜ ሸንጎው ለምን ለሁለት ተከፈለ?

33. ቅዱስ ጳውሎስን ከመካከላቸው አውጥተው ወደ ጦሩ ሰፈር የወሰዱት በምን ምክንያት ነው?



34. ቅዱስ ጳውሎስን ሳንገድል እህል አንበላም ብለው የተማማሉት ሰዎች ስንት ነበሩ?

35. ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቂሣርያ የተወሰደው በምን ምክንያት ነበር?

36. ሊቀ ካህናቱ ወደ ቂሣርያ የሄደው ከስንት ቀን በኋላ ነው?

37. የሄደውስ ከምን ጋር ነው?

38. ምን ዐይነት ክስ አቀረቡ?

39. ፊልክስስ ምን መልስ ሰጣቸው?

40. ፊልክስ ከቅዱስ ጳውሎስ ጉቦ ለመቀበል ፈልጎ ምን ያደርግ ነበር?

41. በፊልክስ ቦታ ለመተካት የመጣው ሰው ማን ይባላል?

42. እርሱንስ የኢየሩሳሌም አይሁድ ምን ጠየቁትና ምን መለሰላቸው?

43. ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮማው ቄሳር ይግባኝ ያለው በምን ምክንያት ነው?

44. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የፊልጵስዩስ መልእክቱን የጻፈው የት ሆኖ ነው?

45. መልእክቱን የላከው በማን እጅ ነው?

46. የፊልጵስዩስ መልእክት በአጠቃላይ በስንት ይከፈላል?

47. እነርሱስ ምን ምን ናቸው።

48. የቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመችው በማን አማካይነት ነው?

49. በመጽሐፈ ኢያሱ የምናስተውለው ምንድነው?

50. ከመሳፍንት መጽሐፍ የምንማረው ትልቅ ትምህርት ምንድነው?

## ምዕራፍ 3

## ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ

### የጌታችን ትምህርቶች

እምነትን በእግዚአብሔር ላይ ማድረግ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ሲል አስተማራቸው:- «ምን እንበላለን? ምን እንለብ ሳለን? በማለት ስለ ኑሮአችሁ አትጨነቁ፤ እስቲ የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ፤ እነርሱ አይዘሩም፤ ወይም አያጭዱም፤ የእህል ማከማቻ ቦታ ወይም ጎተራ የላቸውም፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ይመግባቸዋል፤ እናንተ ግን ከወፎች ትበልጣላችሁ። መሆኑን ከአናንተ መካከል በማሰብና በመጨነቅ በዕድሜው ላይ አንድ ቀን ወይም በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን

www.ethiopianorthodox.org

ነው? የዱር አበቦች እንዴት እንደሚያድጉ ተመልከቱ፤ እነርሱ በሥራ አይደክሙም፤ አይፈትሉም፤ ይሁን እንጂ ሰሎሞን እንኳ በዚያ ሁሉ ክብሩ ከእነርሱ እንደ አንዲቱ አልለበሰም። ዛሬ ታይቶ ነገ በእሳት ውስጥ የሚጣለውን የዱር ሣር እንደዚህ የሚያስጌጠው አምላክ እንዴት ለእናንተ የበለጠ እንደሚያደርግላችሁ አታምኑም? ስለዚህ እናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት ብቻ ፈልጉ። ሌሎቹ የሚያስፈልጉአችሁ ነገሮች ሁሉ ይጨመሩላችኋል» (ሉቃ: ም: 12ቍ: 22–31)።

ስለ ጠባብዋ በር:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ በየከተማውና በየገጠሩ እያስተማረ ያልፍ ነበር። አንድ ሰው «ጌታ ሆይ÷ የሚድኑ ጥቂቶች ብቻ ናቸውን?» ብሎ ጠየቀው። ጌታችንም:- «በጠባብዋ በር ለመግባት ተጣጣሩ፤ በጠባብዋ በር ለመግባት የሚፈልጉ ብዙዎች ናቸው፤ ነገር ግን መግባት አይችሉም፤ የቤቱ ጌታ ተነሥቶ በሩን ይዘጋዋል፤ እናንተም በደጁ ቆማችሁ በሩን በማንኳኳት ጌታ ሆይ÷ እባክህን በሩን ክፈትልን ትሉታላችሁ። እርሱ ግን ከየት እንደመጣችሁ አላውቅም ብሎ ይመልስላችኋል። እናንተም አብረን በልተናል፤ አብረን ጠጥተናል፤ በአደባባያችንም አስተምረሃል ስትሉት÷ እርሱ ግን ከየት እንደመጣችሁ አላውቅም ብሎ ይመልስላችኋል። ብዙ ሰዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ÷ ከሰሜንና ከደቡብ ይመጣሉ፤ በእግዚአበሔር መንግሥትም በማዕድ ይቀመጣሉ፤ ኋለኞች ፊተኞች ይሆናሉ፤ ፊተኞችም ኋለኞች ይሆናሉ» (ሉቃ: ም: 13ቍ: 22–30)።

ከመጥምቁ ዮሐንስ ወደ ጌታችን የተላኩ መልእክተኞች:- የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ጌታችን የሚያደርጋቸውን ተአምራት ለመምህራቸው በነገሩት ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ጠርቶ:- «ይመጣል የተባለው መሲሕ አንተ ነህን? ወይስ ሌላ እንጠብቅ» ብለው እንዲጠይቁ ላካቸው። እነርሱም ሄደው መልእ ክቱን ለጌታችን አደረሱ። በዚያኑ ሰዓት ጌታችን ብዙ ተአምራትን አደረገ። ከዚያ በኋላ መልእክተኞቹን እንዲህ አላቸው:- ተመልሳችሁ ሂዱና ያያችሁ ትንና የሰማችሁትን ለዮሐንስ ንገሩት፤ ዕውሮች ያያሉ፤ አንካሶች ቀጥ ብለው ይሄዳሉ፤ ለምጻሞች ይድናሉ፤ ደንቆሮዎች ይሰማሉ፤ ሙታን ይነሣሉ፤ ለድኾችም ወንጌል ይሰበካል። በእኔም የማይጠራጠር የተመሰገነ ነው አላቸው። መልእክተኞቹ ከሄዱ በኋላ መጥምቁን ዮሐንስን አመስግኖ ተናገረ። ሴቶች ከወለዱአቸው ሰዎች መካከል ከዮሐንስ መጥምቁ የሚበልጥ እንደሌለ ገለጠ፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል አለ (ሉቃ: ም: 7ቍ:18–30)።

## የጌታችን ተአምራት

የአንዲት ጐባጣ ሴት መፈወስ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰንበት ቀን በምኵራብ ያስተምር ነበር። በምኵራቡም ውስጥ ከዐሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ ርኩስ መንፈስ ያጐበጣት አንዲት ሴት ነበረች። እርስዋም ወገብዋ

www.ethiopianorthodox.org



በመጕበጡ ቀና ለማለት አትችልም ነበር። ጌታችን እርስዋን ጠርቶ ከበሽታሽ ተፈውሰሻል አላት። በእጁም ዳሰሳትና ወዲያውኑ ቀጥ ብላ በመቆም እግዚአብሔርን አመሰገነች። የምኵራቡ አለቃ ግን ሴትዮዋ በሰንበት ቀን ስለተፈወሰች ተቈጣ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ:- እናንተ ግብዞች ከእናንተ መካከል በሰንበት ቀን በሬውንና አህያውን ፈትቶ ውሃ ወደሚያጠጣበት ቦታ የማይወስድ ማነው? ታዲያ ዐሥራ ስምንት ዓመት በሰይጣን ታስራ ስትሠቃይ የነበረችው የአብርሃም ዘር ከምትሠቃይበት በሽታ በሰንበት ቀን መፈታት አይገባትምን? በማለት ተቃዋሚዎቹን አሳፈራቸው (ሉቃ: ም:1 3ቍ: 10–17)።

ዕውር ሆኖ የተወለደው ሰው መፈወስ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንገድ ላይ ሲያልፍ አንድ ዕውር ሆኖ የተወለደ ሰው አየ። በመሬት ላይ እንትፍ ብሎ በምራቁ ዐፈር ለወሰና በጭቃው የዕውሩን ዐይኖች ቀባ። ከዚያም ሄደህ በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ ብሎ አዘዘው። ሰውዬውም ሄዶ ታጠበና እያየ ተመለሰ። ፈሪሳውያን ዕውር የነበረውን ሰው እንዴት እንደዳነ ጠየቁት። እርሱም ኢየሱስ የሚባል ሰው ጭቃ በዐይኔ ላይ አድርጎልኝ ከታጠብሁ በኋላ ዳንሁ አላቸው። ከፈሪሳውያን አንዳንዶቹ ይህ ሰው ሰንበትን ስለማያከብር ከእግዚአብሔር አይደለም አሉ። ሌሎቹ ደግሞ ኃጢአተኛ ሰው እንዴት ይህን ሁሉ ተአምር ሊያደርግ ይችላል? አሉ። በመካከላቸውም መለያየት ሆነ። ዕውር የነበረውን ሰው ያንተስ አስተያየት እንዴት ነው ብለው? ጠቁት። እርሱም ነቢይ ነው አለ። ፈሪሳውያንም ይህ ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን እኛ እናውቃለንና እውነቱን በመናገር እግዚአብሔርን አክብር አሉት። ዕውር የነበረውም ሰው እርሱ ኃጢአተኛ መሆኑን አላውቅም፤ እኔ የማውቀው ዕውር እንደነበርሁና አሁን ማየት እንደቻልሁ ብቻ ነው ሲል መለሰላቸው። ከእርሱ ጋር ብዙ ከተከራከሩ በኋላ ከምኵራባቸው አስወጡት ( ዮሐ:ም:9)።

## የጌታችን ምሳሌዎች

<u>ሀብታሙ ሰውና ድኻው አልዓዛር</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተናገራቸው ምሳሌዎች አንዱ የሚከተለው ነው።

የተዋበ ልብስ የሚለብስና በቅንጦት የሚኖር አንድ ሀብታም ሰው ነበር። ሌላ ደግሞ መላ ሰውነቱ በቍስል የተወረሰ አልዓዛር የሚባል አንድ ድኻ ሰው ከሀብታሙ ደጃፍ ተኝቶ ነበር። ይህ ድኻ ሰው ከሀብታሙ ማእድ የሚወድቀውን ፍርፋሪ ለመመገብ ይመኝ ነበር። ውሾችም እየወጡ ቍስሉን ይልሱ ነበር። ድኻው ሰው ሞተና መላእክት ወደ አብርሃም አጠገብ ወሰዱት። እንዲሁም ሀብታሙ ሰው ሞተና ተቀበረ። በሲኦልም ሲሠቃይ ሳለ ቀና ብሎ አብርሃምንና በአጠገቡ ያለውን አልዓዛርን በሩቁ አያቸው። እርሱም ድምፁን ከፍ አድርጎ አብርሃምን ጠራው። አብርሃም አባት ሆይ፥ እዚህ በእሳት ውስጥ እየተሠቃየሁ ነው። እባክህ አልዓዛርን ላክልኝና የጣቱን ጫፍ በውሃ ነክሮ ምላሴን ያብርድልኝ። አብርሃምም እንዲህ ሲል መልስ ሰጠው:- ልጄ ሆይ፥ በምድራዊ ሕወትህ ጊዜ አንተ ምን ያኽል እንደተደሰትህ አስታውስ፤ አልዓዛር ግን የኖረው በችግር ነው። ስለዚህ አሁን እርሱ ይደሰታል፤ አንተ ግን ትሠቃያለህ። ከዚህም ሁሉ በላይ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል አለ። ከእኛ ወደ እናንተና ከእናንተ ወደ እኛ መሻገር የሚችል ማንም የለም። ሀብታም የነበረውም ሰው እንግዲያውስ እባክህ አልዓዛርን ወደ አባቴ ቤት ላከው። አምስት ወንድሞቼ ወደዚህ ወደ ሥቃይ ቦታ እንደይመጡ ያስጠንቅቃቸው። አብርሃምም:- ለእነርሱ ሙሴና ነቢያት አሉላቸውና እነርሱን ይስሙ አለው። ሀብታም የነበረውም ሰው:- አይደለም፤ አብርሃም አባት ሆይ፥ ይህ አይበቃም፤ ነገር ግን አንድ ሰው ከሞት ተነሥቶ ቢነግራቸው ተጸጽተው ንስሐ ይገባሉ አለው። አብርሃም ግን መልሶ ሙሴንና ነቢያትን የማይሰሙ ከሆነ ከሞት የተነሣ ሰውም ቢነግራቸው አያምኑትም አለው (ሉቃ:ም: 16 ቍ:19–31)።





ሀብታሙ ሰውና ድኻው አልዓዛር (ሉቃ ም 16 ቍ 19-31)።

<u>ጠፍቶ የተገኘው በግ ምሳሌ</u>:- ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህች ምድር ላይ ሰው ሳይለይ ሁሉንም ያስተምር ነበር። ቀራጮችና ኃጢአተኞች ወደ ትምህርቱ ሲሰበሰቡ ባዩ ጊዜ ፈሪሳውያንና የኦሪት ሕግ መምህራን አጕረመረሙ። ስለዚህም ይህን ምሳሌ ነገራቸው:- ከእናንተ መካከል መቶ በግ ያለው ሰው አንድ በግ ቢጠፋበት ምን ያደርግ ይመስላችኋል? ዘጠና ዘጠኙን በዱር ትቶ የጠፋውን አንዱን እስኪያገኘው ድረስ ሲፈልገው ይሄድ የለምን? ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በትከሻው ተሸክሞት ይመጣል። ወደ ቤቱም በሚደርስበት ጊዜ ወዳጆቹንና ዘመዶቹን ጠርቶ የጠፋውን በጉን በማግኘቱ ከእርሱ ጋር እንዲደሰቱ ይነግራቸዋል። በዚህም ዐይነት ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል ብሎአቸዋል (ሉቃ: ም: 15 ቍ:1–7)።

<u>የብልኅ መጋቢ ምሳሌ</u>:- አንድ ሀብታም ሰው ቤቱን የሚያስተዳድርለት መጋቢ ነበረው። ይህ መጋቢ ንብረትህን ያባክናል ብለው ለሀብታሙ ሰው ነገሩት። ሀብታሙም ሰው መጋቢውን አስጠርቶ ይህ በአንተ ላይ የምሰማው ምንድነው? ከእንግዲህ ወዲህ መጋቢዬ ልትሆን አትችልምና በመጋቢነትህ የሠራህበትን የንብረቴን ሒሳብ አስረክበኝ አለው። በዚህ ጊዜ ያ መጋቢ አሁን ከሥራዬ ስባረር ምን አደርጋለሁ? ማረስ አልችልም፤ መለመን ያሳፍረኛል ብሎ አሰበ። ከጌታው ባለ ዕዳዎች ጋር በመስማማት ከሥራው ሲሰናበት በቤታቸው እንዲቀበሉት ለማድረግ ወሰነ። የጌታውን ባለ ዕዳዎች እያንዳንዳቸውን ጠርቶ አንዱን ባለ ዕዳ ለጌታዬ የምትከፍለው ምን ያኽል ዕዳ አለብህ? ብሎ ጠየቀው። እርሱም መቶ ማድጋ ዘይት አለብኝ ብሎ ነገረው።

እርሱም መልሶ መዝገብህን እንካ ኀምሳ ብለህ ጻፍ አለው። ሌላውን ደግሞ ጠርቶ አንተስ ስንት ዕዳ አለብህ? አለው። እርሱም መቶ ዳውላ ስንዴ አለው።

www.ethiopianorthodox.org

መጋቢውም ይኸው መዝገብህ ሰማንያ ደውላ ብለህ ጻፍ አለው። ሀብታሙም ሰው እምነት ያጐደለውን መጋቢ በብልኅነቱ አደነቀው፤ ይህም ከእግዚአብሔር ሰዎች ይልቅ የዓለም ሰዎች በዓለማዊ ኑሮአቸው ብልኆች መሆናቸውን ያሳያል።.

ስለዚህ ጌታችን እንዲህ አለ:- በዚህ ዓለም ሀብት ወዳጆችን አብጁ እላችኋለሁ፤ ይህን ብታደርጉ ገንዘባችሁ አልቆባችሁ ባዶ እጃችሁን ስትቀሩ ወዳጆቻችሁ ለዘለዓለም በሚኖሩበት ቤት ይቀበሉአችኋል። በትንሽ ነገር የታመነ ሰው በትልቅ ነገርም የታመነ ይሆናል። በትንሽ ነገር የማይታመን ሰው፥ በትልቅ ነገርም አይታመንም፤ ታዲያ፥ የዚህን ዓለም ሀብት በማስተዳደር የማትታመኑ ከሆናችሁ እውነተኛውን ሀብትማ ማን አምኖ ይሰጣችኋል? ደግሞም በሌላው ሰው ሀብት የማትታመኑ ከሆነ ለእናንተ የሚሆነውንስ ማን ይሰጣችኋል? (ሉቃ:ም:16ቊ:1–12)።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን እንበላለንና ምን እንለብሳለን ብላችሁ አትጨነቁ ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ሲናገር ለሁላችንም መናገሩ መሆኑ ግልጥ ነው። አትጨነቁ ማለት ግን አትሥሩ ማለት አይደለም። ይህማ ቢሆን ኖሮ መክሊቱን የሠሩበት ተመስግነው ያልሠራበት ባልተወቀሰም ነበር (ማቴ: ም:25ቊ:15–28)። ሰው አስቦና ተጨንቆ ባለው ሁናቴ ላይ ሊጨምር ወይም ካለው ሁናቴ ምንም ሊቀንስ የማይችል በመሆኑ ወደፊት ያሰጋል ብሎ በሚያስበው ጉዳይ የእግዚአብሔርን እርዳታ ከመለመን በቀር ማሰቡና መጨነቁ ምንም ጥቅም የሌለው ጉዳይ ነው። በሀገሪቱ ላይ የረሀብ ችግር ይከሠት ይሆናል፤ የእርሻ መሬቴ በቂ ምርት አይሰጠኝ ይሆናል፤ ከሥራ ተባርሬ የወር ደመወዝ በማጣት እቸገር ይሆናል፤ በተለያዩ ምክንያቶች የገቢ ምንጬ በመቋረጡ የምበላውን ምግብ፥ የምለብሰውን ልብስ ለመግዛት ወደማልችልበት ደረጃ እደርስ ይሆናል ብሎ መጨነቅ በእግዚአብሔር ላይ አለመተማመን ነው። ምንጊዜም ቢሆን የሥራችን መልካም ውጤት የሚገኘው በእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ በእኛ ጥረት ብቻ አይደለም። ወደፊት እንዲህ ይሆናል ወይም እንዲህ ያለ ነገር ይደርሳል ብሎ በማሰብ ገንዘብ ማከማቸት ማንኛውም ሰው መቼ እንደሚሞት ስለማያውቅ ያን ያጠራቀመውን ገንዘብ ትቶ ሊሞት እንደሚችል መገንዘብ አለበት። ሕይወትንና ሰውነትን የሰጠን አምላክ ከነዚያ ያነሱትን ምግብንና ልብስን እንደሚሰጠን መተማመን አለብን። ሕይወትንና ሰውነትን ለመጠበቅ ምግብና ልብስ እንደሚያስፈልጉ ከዕውቀት ፈጣሪ የተሰወረ አይደለም። ስዚህ ትልቁን ነገር የሰጠን አምላክ ትንሹን ነገር እንደማይከለክለን ዐውቀን ከመጨነቅ እንቈጠብ። ከሰው ያነሰ ተፈጥሮ ያላቸውን የሰማይ ወፎች የሚመግብ ከሆነ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን ሰውንማ እንዴት ሳይመግበው ይቀራል። እንዲሁም የሜዳ አበቦችን ያጌጠ ልብስ የሚያለብሳቸው ከሆነ ታዲያ እኛ ከአበቦች አንበልጥምን? ይህንንም

www.ethiopianorthodox.org



አለማሰብ ሃይማኖተ ደካማነትን ያመለክታል። ለእነዚህ ነገሮች መጨነቃች ዕረፍት የሚነሡን ከመሆናቸው በቀር ፍሬቢስ፥ ከንቱና ኢምንት ናቸው የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ምግባችንን በየዕለቱ ስጠን ብለው እግዚአብሔር ይለምኑ እንጂ ስለምግብ አይጨነቁ። ይህን ባያደርጉ ግን ከሌሎች ምድራውያን ሰዎች በምን ይለያሉ። እነዚህንማ ነገሮች የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ይፈልጉአቸዋል። የሰማዩ አባታችሁ እነዚህ ነገሮች እንደሚያስፈልጉአችሁ ያውቃል ስላለ ለእነዚህ ነገሮች መጨነቅ አስፈላጊም ተገቢም አይደለም።

ስለዚህ እኛ የእግዚአብሔርን መንግሥት ብቻ እንድንፈልግ፥ ማለት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ብቻ እንድንጸልይ እንጂ የቀረው ለሕይወት አስፈላጊ የሆነው ነገር ሁሉ እንደሚሰጠን ተነግሮናል።

ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም ያመራ በነበረበት ጊዜ አንድ ሰው መጥቶ የሚድኑ ጥቂቶች ብቻ ናቸውን? ብሎ ጠየቀው። ይህን ጥያቄ የጠየቀው ወዳጅ ይሁን ወይም ጠላት አልተገለጠም። ወዳጅ ወይም እውነቱን የፈለገ ሰው ቢሆን የእኔስ ዕድል ፈንታ ምን ሆን? ብሎ ለማወቅ ፈልጎ ነው። የጠላት ጥያቄም ከሆነ ጌታችንን ለመክሰስ ምክንያት ሊያገኝ ፈልጎ ነው። ምናልባትም ከአይሁድ ትምህርት የተለየ መልስ ይሰጥና ሃይማኖታችንን ያቃውሳል ብለው ሊከስሱት ፈልገው ነው። ያለዚያም ምንም ዐይነት መልስ ቢሰጥ ለመልሱ ተቃራኒ ትርጒም በመስጠት እናሰጣዋለን ብለው በማሰብ ነው። ይኸውም የሚድኑት ብዙዎች ናቸው ያለ እንደሆነ የአይሁድ የሃይማኖት ሰዎች አክረረውና አጠናክረው የሚያስተምሩትን ትምህርት በማቃለል የመዳን በቂ ግምት አልሰጠውም ብለው ለማሳጣት፥ የሚድኑት ጥቂቶች ብቻ ናቸው ያለ እንደሆነ ደግሞ የአይሁድ ሕዝብ በእርሱ ላይ እንዲቈጣ ለማድረግ ነው። አይሁዳዊ የሆነ ሰው ሁሉ አይሁዳዊ በመሆኑ ብቻ ይድናል ብለው ያምኑ ስለነበረ የሚድኑ ጥቂቶች ናቸው በሚልበት ጊዜ ብዙዎቹ የአይሁድ ወገኖች አይድኑም አለ ብለው ሊከሰሱት ፈልገው ነው። በዚህም ሆነ በዚያ ጌታችን ለጥያቄው የሰጠው ቀጥተኛ መልስ የመዳኛውን መንገድ በማስተማር ነው፤ እርሱም የነገራቸው በጠባቡ በር ለመግባት ተጣጣሩ፤ በጠባብዋ በር ለመግባት የሚፈልጉ ብዙዎች ናቸው፤ ነገር ግን ለመግባት አይችሉም ብሎ ነው። በዚህም አባባሉ የመዳን መንገድ ቀላል አለመሆኑን ገለጠላቸው። አይሁዳዊ በመሆኑ ብቻ ለመግባት ለሚፈልግ ሁሉ መንገዱ ሰፊ አለመሆኑን ገለጠ ላቸው። ወይም እውነት ባልሆነ አስተሳሰብ ጻድቅ ነኝ ብሎ ለሚያምን ሰው ሁሉ መንገዱ ሰፊ ነው ማለት አይደለም። የመዳን መንገድ ግን ብዙ ውጣ ውረድና ችግር የበዛበት መሆኑን ገለጠ ላቸው። እንዲሁም የመዳን መንገድ በአስቸጋሪ መከራዎች፥ በመወገዝና በመጠላት ዐይነቶች፥ በብዙ ችግሮች፥ የዚህ ዓለም ፈተናዎችን ድል በመንሣት ትዕግሥት፥ ከልብ በሆነ እውነተኛ እምነት፥ ከዓለማዊ ምኞቶችና ሥራዎች በመራቅ፥ ከሰማያዊ ምኞትና ተግባር ጋር በፍጹም በመጣበቅ የተሞላ ነው። የመዳኑ መንገድም እንደዚህ አስቸጋሪ በመሆኑ ወደ መዳንም የመግቢያው በር ጠባብ ነው። ሊገቡባትም የሚችሉ ያን ሁሉ ፈተና ያለፉ ጥቂቶች ብቻ ናቸው። በአስመሳይነት ራሳቸውን ሲያታልሉ የኖሩት ሰዎች:- አብረን የበላን፥ አብረን

የጠጣንና በአደባባያችንም ያስተማርህ ስለሆነ እባክህን ጌታ ሆይ ክፈትልን ሲሉት እርሱ አላውቃችሁም፤ ወዲያ ሂዱ ይላቸዋል ብሎአል። እንደዚህ ያሉት ምክንያቶች ግን ለማዳን የሚያበቁ አይደሉም። ለምሳሌ አስቆሮታዊው ይሁዳ ከጌታችን ጋር ከበላና ከጠጣ በኋላ ነው ከሐዲ ሆኖ ጌታውን ለጠላቶቹ አሳልፎ የሰጠው። ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁድ አደ ባባይ አስተምሮአል። እነርሱ ግን ሕማም አድርሰውበት ሰቀሉት። በጌታችን ማእድ የበሉ ሁሉ ጻድቃን አይደሉም፤ ትምህርቱን ከእርሱ የሰሙ ሁሉ ንጹሐች አይደሉም። እርሱን እስከካዱ ድረስ ትምህርቱንም ክደዋል። ይህም የሆነው በዚህ ምድር በነበረበት ዘመን ብቻ ሳይሆን ከዚያም በኋላ በነበረው ዘመንና ወደፊትም በሚመጡት ዘመናት ሁሉ የሚሆን ነው። ስለዚህም መድኀኒታችን እነርሱ የሚሰጡትን ምክንያት አይቀበልም። ከመዳን በር ውጪ ሆነው ይቀራሉ ማለት ነው። እነርሱም በገሃነመ እሳት ውስጥ ሆነው የብሉይና የሐዲስ ኪዳንን ጻድቃን በመንግሥተ ሰማይ ሲደሰቱ በማየት በለቅሶ፥ በቅናትና በቍጭት ጥርሳቸውን ያፋጫሉ። በመጀመሪያ የመዳን መንገድ ቀርቦላቸው የነበረው ለአይሁድ ሲሆን እነርሱ የመዳን መንገድ ስላልተቀበሉና ከሌሎች ወገኖች ግን ብዙዎቹ ስለተቀበሉት ያን መንገድ የተከተሉ ሁሉ ሲያገኙ ያልተቀበሉት ግን አዳኙ ጌታ አባርሮአቸዋል፤ ያባርራቸዋልም። ስለ ዚህም ነው ፊተኞች ኋለኞች፥ ኋለኞች ደግሞ ፊተኞች ይሆናሉ ያለው።

ከዮሐንስ መጥምቁ ደቀመዛሙርት መካከል አንዳንዶቹ እስራኤልን ለማዳን ይመጣል ብለው ነቢያት የተናገሩለት ክርስቶስ እርሱ መሆኑን ለማመን በማወላወል ላይ የነበሩ መሆናቸው ይገመታል። በእርሱ ላይ ፍጹም የሆነ እምነት ሊኖራቸው ያልቻለው እነርሱ የሚጠብቁት ክርስቶስ በኀያል ንጉሥ መልክ በአጃቢዎቹ ታጅቦ የሚመጣውን ንጉሥ እንጂ እነርሱ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እንዳዩት ያለ የትሕትና መልክ ስላልነበረ ነው።ቀደም ብሎ ለጌታችን የመሰከረለት ቢሆንም እንኳ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ጠርቶ ይመጣል የተባለው መሲሕ አንተ ወይስ ሌላ እንጠብቅ ብሎ ወደ ጌታችን ላካቸው። ይህንንም ያደረገው ጌታችን የሚያደርጋቸውን ተአምራት አይተው የጌታችንን ማንነት በማወቅ እንዲያረጋግጡ ብሎ ነው እንጂ አስቀድሞ ከመሰከረለት በኋላ እንደገና ተጠራጥሮት አይደለም። እነዚያም የዮሐንስ ሁለት ደቀ መዛሙርት ተልከው ወደ ጌታችን በመጡ ጊዜ ጌታችን ብዙ ሰዎችን እያስተማረና ሲያስፈልግም ተአምራት እያደረገ ነበር። በፊታቸውም ብዙ ሕመምተኞችን ፈወሰ፤ ርኩሳን መናፍስት የነበሩባቸውን ሰዎች አስወጣላቸው፤ የብዙ ዕውራንን ዐይን አበራ፤ ከዚያም በእርሱ ማንነት ጥርጣሬ ወደነበራቸው ወደ ሁለቱ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት መለስ ብሎ ወደ ዮሐንስ ሄዳችሁ ያያችሁትንና የሰማችሁትን ለዮሐንስ ንገሩት፤ ዕውሮች ያያሉ፤ አንካሶች ይሄዳሉ፤ ለምጻሞች ይነጻሉ፤ ደንቆሮዎች ይሰማሉ፤ ሙታን ይነሣሉ፤ ለድኾች ወንጌል ይሰበካል፤ በዚህም በነቢዩ ኢሳይያስ ስለ ክርስቶስ የተነገረው ነገር በዐይናቸው አዩ፤ በጆሮአቸውም ሰሙና አረጋገጡ።



«በዚያን ጊዜ ዕውሮች ያያሉ፤ ደንቆሮዎችም ይሰማሉ፤ አንካሶች እንደሚዳቋ ይዘልላሉ፤ መናገር የማይችሉ ድዳዎች ይዘምራሉ» (ኢሳ: ም:35 ቍ:5–6)።

የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ከሄዱ በኋላ ጌታችን በዮሐንስ ላይ ሊኖር ይችል የነበረውን የሕዝብ ስሜት ለማስተካከል ስለዮሐንስ ተናገረ። ሕዝቡ ምናልባት ዮሐንስ ቀድሞ የሰጠውን የምስክርነት ቃሉን በመለወጥ በጌታችን ላይ እንደተጠራጠረ እንዳይመስላቸው ሁለቱ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ከሄዱ በኋላ ዮሐንስን በማመስገን ተናገረ። በንግግሩም ነቢይ ለማየት ወጥታችኋልን? አዎ እላችኋለሁ፤ ከነቢይ የሚበልጠውን ለማየት ነው። ሴቶች ከወለዱአቸው ሰዎች መካከል ከዮሐንስ የሚበልጥ ማንም የለም። በእግዚአብሔር መንግሥት ግን ከሁሉ ያነሰ ይበልጠዋል ብሏል። ከነቢያት ይበልጣል የተባለለት ክርስቶስ ይመጣል ብለው ትንቢት የተናገሩት የብሉይ ኪዳን ነቢያት አንዳቸውም ቢሆኑ ክርስቶስን የማየት ጸጋ አላገኙም፤ ዮሐንስ ግን በዐይኑ ከማየቱም በላይ አጥምቆታል። የእግዚአብሔር ጥበብም ዮሐንስ የክርስቶስን መንገድ አዘጋጅ እንዲሆን መርጣዋለች። እነሆ፥ መልእክተኛዬን እልካለሁ፤ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል» ተብሎ የተነገረለት ይህ ዮሐንስ ነው (ሚል:ም:3 ቍ:1)።

ምንም እንኳ መጥምቁ ዮሐንስ ከብሉይ ኪዳን ሰዎች ቢበልጥና ከሴቶች ከተወለዱ ሰዎች መካከል ከእርሱ የሚበልጥ እንደሌለ ቢነገር በመንግሥተ ሰማያት ግን የሚያንሰው ይበልጠዋል ተብሎአል።

ለዚህ አባባል ሁለት አማራጭ ትርጉሞች አሉ።

የመጀመሪያው ትርጉም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተወለደው ከዮሐንስ መጥምቁ ከስድስት ወር በኋላ በመሆኑ በዕድሜው ታናሽ መሆኑ ነው። እርሱም ፈጣሪ እንደመሆኑ ከፍጡሩ ይበልጣል ለማለት ነው።

ሁለተኛው ትርጓሜ ደግሞ ዮሐንስ ጌታችንን ያየው ቢሆንም እንኳ እርሱ ግን ያየው ሕማማትና ሞት ሳይደርስበት ነው። ስለዚህ እርሱ የዳነበት የድኅነት መንገድ በክርስቶስ የዳኑ ምእመናን ከዳኑበት የመዳኛ መንገድ በማነስ ይለ ያል። ስለዚህ የሚያንሰው የመዳኛው መንገድ እንጂ እርሱን ራሱን ለማለት አይደለም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ልማዱ ወደ አንድ ምኵራብ ገብቶ ያስተምር በነበረበት ጊዜ አንዲት ከዐሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ ርኩስ መንፈስ ያጐበጣት ሴት አይቶ ራራላት። ሴቲቱንም ጠርቶ አንቺ ሴት ከበሽታሽ ተፈውሰሻል በማለት እጁን ጫነባትና ተፈወሰች። እርስዋም ወዲያውኑ ድና እግዚአብሔርን አመሰገነች። ያ ቀን የሰንበት ቀን ስለነበረ የምኵራቡ አለቃ ተቈጥቶ ለመፈወስ የምትፈልጉ ሁሉ በሳመንት ካሉት በስድስቱ ቀኖች ውስጥ እንጂ በሰንበት ቀን አይሆንም አለ። ጌታችንም ለምኵራብ አለቃው ግብዝነቱን ሲያስረዳው ከእናንተ መካከል በሬ ወይም አህያ ያለው ሰው በሰንበት ቀን ውሃ ለማጠጣት ከታሰረበት ቦታ ፈትቶ የሚወስደው ከሆነ ይህች

www.ethiopianorthodox.org

የአብርሃም ልጅ ዐሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ ከታሰረችበት ከሰይጣን ሰንሰለት መፈታት አይገባትምን? ብሎ ተቃዋሚዎቹን አሳፈራቸው።

ያች ሴት እንዲፈውሳት አልለመነችውም ነበር። ጌታችን ግን የሰው ችግርና ጭንቀት የሚያሳዝነው በመሆኑ ፈወሳት። እርስዋም በሰይጣን የታሰረች ብት ሆንም እንኳ ለጸሎት ወደ ቤተ መቅደስ መሄድን አለማቋረጧና መድኀኒታችን የአብርሃም ልጅ ብሎ መጥራቱ መንፈሳዊነትዋ የአብርሃምን አርአያነት የተከ ተለ መሆን አለበት። የአብርሃም ልጅነትዋ በዘርዋ ብቻ ሳይሆን በግብርዋም ጭምር መሆን አለበት። ስለዚህም ወደ ቤተ መቅደስ ሄዳ ስለ ኀጢአትዋ ስርየት በምትጸልይበት ጊዜ ጌታችን በቃሉ መሠረት የሥጋ ፈውስንም ሰጥቶአታል። ጌታችን በተራራ ላይ ትምህርቱ:- እናንተ ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን ፈልጉ፤ የሰማዩ አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ነገር ሁሉ ስለሚያውቅ የቀረውን ነገር ሁሉ ይጨምርላ ችኋል ብሏል (ማቴ :ም: 6 ቊ :32–33)።

ስለዚህ ያች ሴት የእግዚአብሔርን ጽድቅ ፈልጋ ስለጸለየች የሥጋ ፈውስም እንደሚያስፈልጋት ጌታችን የሚያውቅ በመሆኑ ከሰይጣን እስረኛነት አላቅቋታል። ይህ ተአምር የጌታችንን ማንነት መመስከር የሚገባው ቢሆንና በሰንበትም ቀን እንደዚህ ያለው በጎና ድንቅ ነገር መደረጉ እግዚአብሔርን የሚያስመሰግን መሆን ቢገባውም እንኳ ለምን እንደዚህ ያለ በጎ ነገር በሰንበት ቀን ተደረገ ብሎ የምኵራቡ አለቃ ቅሬታ ማሰማቱ ከምን አንጻር ይሆን? ሰንበት የተሠራው ለሰው ከሆነ ታዲያ ሰው ለሰንበት ብሎ በጎ ተግባር ማድረግን ይከልከል ማለትን ምን አመጣው?

የዚህችም ሴት ሕመም ታሪክ የሚያስተምረን ታላቅ ቁምነገር፥ ሕመሞች ሁሉ በሰብአዊ ሕዋሳታችን ልናውቃቸው የምንችላቸው ብቻ ሳይሆኑ እኛ የሕመሙን መንሥኤ ሳናውቅ ሰይጣን በበሽታ ሊያስረን የሚችል መሆኑን ነው።

ጌታችን ተአምራት የሠራባቸው ምክንያቶች ለሰዎች ርኅራኄ በማድረጉ፥ መለኮታዊ ከሃሊነቱን ለማረጋገጥና ዓለምን ለማዳን እንደሚመጣ ነቢያት ትንቢት የተናገሩለት የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ እርሱ መሆኑን ሰዎች እንዲያምኑ ለማድረግ ናቸው።

በርኅርኄና በጸሎት ተቀባይነቱ ምክንያት የተደረጉ ተአምራት ለምሳሌ ያኽል የናይን ከተማን የመበለት ልጅ ከሞት ማስነሣት፥ የአባቱን ጸሎት በመቀበል የምኵራብ አለቃውን ልጅ ከሞት ማስነሣት፥ እጁ የሰለለበት ሰውና ለዐሥራ ስምንት ዓመት የጐበጠችው ሴት አንዳቸውም ሳይጠይቁት ራርቶ ላቸው የፈወሳቸው ሰዎች ይገኙባቸዋል። እንዲሁም ከእርሱ ጋር ቈይተው ለነበሩ ሰዎች እየራባቸው ተመልሰው እንዳይሄዱ ስለዛነላቸው በተአምር መግቦአቸዋል። (ማቴ:ም:12 ቊ:9–14፤ ም:9 ቊ:18–26፤ ማር:ም:3 ቊ:1–6፤ ም:5 ቊ: 22–43፤ ሉቃ:ም:7 ቊ:11–17፤ ም:8 ቊ: 40–42፤ 49–56፤ ም:13ቊ:11–17)።

ሰዎች በማንነቱ እንዲያምኑ ለማድረግ ተአምራት የሚሠራ ለመሆኑ ለምሳሌ አልዓዛር በሞተ ጊዜ ጌታችን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደሌላ ቦታ ሄዶ ነበር። ስለዚህ ለደቀ መዛሙርቱ:- «እናንተ እንድታምኑ እዚያ ባለመኖሬ ደስ ብሎኛል» ብሎአቸዋል። ከተቀበረ አራት ቀን የሆነውን አልዓዛርን ከሞት በሚያስነሣበት ጊዜ እምነታቸው ስለሚጠናከር እዚያ ባለመኖሬ ደስ ብሎኛል ብሎአቸዋል (ዮሐ:ም:11ቊ:15)።

በሌላ ጊዜ ደግሞ ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ ብሏል:- «ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ብዙ ተአምራትን በደቀ መዛሙርቱ ፊት አድርጓል። ይህ ግን የተጻፈው ኢየሱስ መሲሕ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንድታምኑና አምናችሁም በእርሱ ስም የዘለዓለም ሕይወት እንድታገኙ ነው» (ዮሐ:ም: 20ቊ:30–31)።

ጌታችንና ደቀ መዛሙርቱ በመንገድ ላይ ሲያልፉ ሳለ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ባዩ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ጌታችንን «መምህር ሆይ፥ ይህ ሰው ዕውር ሆኖ የተወለደው በራሱ ኃጢአት ነው ወይስ በወላጆቹ ኃጢአት ነው?» ብለው ጠየቁት። ጌታችንም:- «ይህ ሰው የታወረው በራሱ ወይም በወላጆቹ ኃጢአት ምክንያት ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ሥራ (ክብር) በእርሱ እንዲገለጥ ነው» አላቸው።

ጌታችን በዚህ ተአምር ፈጣሪነቱን አረጋግጦአል። ጭቃን በምራቅ ከለወሰ በኋላ ቀድሞ ዐይን ባልተፈጠረበት ቦታ ላይ በማስቀመጥ ያልነበረ ዐይንን ፈጥሮአል። ቀደም ብሎ ሰውን በፈጠረ ጊዜ ከምድር ዐፈር እንደፈጠረ ሁሉ ሲወለድ ያለ ዐይን ተፈጥሮ ለነበረው ሰው ከምድር ዐፈር ዐይን አበጀለት፤ ፈጠረለት (ዘፍ:ም:2ቊ:7)። ስለዚህ ሲወለድ አካሉ ተሟልቶለት ያልነበረው ሰው ቀድሞውኑ ሰውን ሲፈጥር በፈጠረበት ንጥረ ነገር ማለት በዐፈር አሟላለት ማለት ነው።

ዐይኑ እንዲያይ የተደረገለትን ሰው ብዙ ጊዜ መላልሰው እርሱንና ቤተሰቡን ፈሪሳውያን የጠየቁበትም ምክንያት ይህ ተአምር ከሌሎቹ ተአም ራት ሁሉ ስለከበደባቸው ነው።

ስለ ድኻው አልዓዛርና ስለ ሀብታሙ ሰው የተነገረው ምሳሌ በመንፈሳዊ ማለትም በሰማያዊ ትምህርት የተሞላ ነው። ምሳሌውም እውነተኛ ታሪክ ሊሆን የማይችልበት ምክንያት የለም። በተለየም መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድኻውን አልዓዛርና የአማኞች አባት አብርሃምን በስም ጠርቶ መናገሩ ታሪኩ በእውነት የተከሠተ ታሪክ ስለሆነ ነው። የአልዓዛር በባለጸጋው ቤት በር መውደቅ፥ ውሾች፥ መጥተው መላሳቸው፥ ባለጸጋው አምስት ወንድሞች ያሉት መሆኑ ተስተካክሎ መቅረቡ ምሳሌው እውነተኛ ታሪክ መሆን አለበት ወደማለት ውሳኔ ያደርሳል። ጌታችን የባለጸጋውን ስም ያልጠቀሰው ያ ሰው


www.ethiopianorthodox.org

ኃጢአተኛ ስለነበረ ስሙን ሊናገር ባለመፈለጉ ነው። እኛም ስሙን ያወቅን እንደሆነ በየጊዜው በኃጢአተኛ ምሳሌነት ለመጥቀስ ስለሚቃጣንና እኛ ግን በማንም ላይ መፍረድ የሌለብን በመሆኑ ነው። አልዓዛር ግን መዳንን ካገኙ ሰዎች አንዱ በመሆኑ እርሱን በደግነት እንጂ በክፋት ስለማናስታውሰው ስሙን እንድናውቅ ተደርገናል።

በዚህም የምሳሌ ታሪክ የምናስተውላቸው የሚከተሉት ጉዳዮች ናቸው:-

አንደኛ/ መላእክት የጻድቃንን ነፍሳት ለማረፊያ ወደተዘጋጀላቸው ቦታ የሚወስዱ መሆናቸው ነው።

ሁለተኛ/ ሲኦል ደግሞ ክፉ አድራጊዎች እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ እየተሠቃዩ የሚቈዩበት ቦታ መሆኑን ነው።

ሦስተኛ/ በባለጸጋው እንደተነገረው በሲኦል ያለው የሥቃይ መጠን ተገልጦአል።

አራተኛ/ አብርሃም ከሙሴና ከነቢያት ከብዙ ዓመቶች በፊት የነበረ ሆኖ ሳለ ለሀብታሙ ሰው ሙሴና ነቢያት አሉላቸው ማለቱ ከዚህ ዓለም ወደ ሌላው ዓለም ያለፉት ሰዎች በዚህ ዓለም ላይ ምን እንደተደረገና ምን እንደሚደረግ የሚያውቁ ለመሆናቸው ማስረጃ ነው።

አምስተኛ/ በወዲያኛው ዓለም ያሉ ነፍሳት እርስ በርሳቸው የሚተዋወቁ ለመሆናቸው ሀብታሙ ሰው አባት አብርሃምንና አልዓዛርን በማወቁ ለመረዳት ይቻላል።

ስድስተኛ/ ሀብታሙ ሰው አብርሃምን እባክህ አልዓዛርን ወደ ወንድሞቼ ወደ ዓለም ላክልኝና እኔ ወደምገኝበት የሥቃይ ቦታ እንዳይመጡ ያስጠንቅቅልኝ ማለቱ ሰው ከሞተ በኋላ ክፉ እንኳ ቢሆን በዓለም ላይ ያለውን ሁሉ የማይረሳ፥ የነበረው ስሜት ሁሉ ማለትም የዝምድና ስሜቱና ፍቅሩ የማይቀር መሆኑን ያመለክታል። ኃጢአተኛው ሰው ይህን ካደረገ ጻድቃንማ በዓለም ላሉ ወዳጆቻቸው ምንኛ ይጸልዩላቸው ይሆን?

ሰባተኛ/ ይህ ምሳሌ የሚያመለክተው ማንም ሰው በወዲያኛው ዓለም የዘራውን እንደሚአጭድ ነው። በዚህ ዓለም ግፍ የሚሠራ በወዲያኛው ዓለም ቅጣቱን ያገኛል፤ በዚህ ዓለም በእምነቱ ሆኖ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየፈጸመ ግፍ የተሠራበት ሰው በወዲያኛው ዓለም ይፈረድለታል ማለት ነው።

ጸሐፍትና ፈሪሳውያን፥ እንዲሁም የአይሁድ የሃይማኖት ሰዎች ሁሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይጠሉት የነበረው በቅናትና በምቀኝነት ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ጌታችን በትምህርቱና በተአምራቱ ሰዎች በአክብሮትና በፍቅር ወደ እርሱ ስለ ተሰባሰቡ ነው። እነዚያ ቀናተኞቹ የአይሁድ የሃይማኖት ሰዎች የሕዝቡን አክብሮትና ፍቅር ለራሳቸው ብቻ ለማስቀረት ይፈልጉ ነበር። ስለዚህም በጌታችን ላይ የሃይማኖት ሕግና ሥርዓትን በተመለከተ፥ ምክንያት ፈልገው በማሳጣት በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንዳያጣ ለማድረግ ሙከራ ማድረጋቸውን ቀጠሉ። በዚህም መሠረት በሰንበት ቀን



በሽተኞችን በመፈወስ ሰንበትን ይሽራል በማለት፥ በመታጠብ አፍአዊ ሰውነትን ስለማጽዳት ጉዳይ ግድ የለውም በማለትና በሌሎችም እነዚህን በመሳሰሉ ጉዳዮች ያሳጡት ነበር። ጌታችን ግን ለክሳቸው ሁሉ በቂ መልስ በመስጠት በየጊዜው አሳፍሮአቸዋል። ቀራጮችን እንደ ኃጢአተኞች ይቈጥሩበት ከነበሩት ምክንያቶች መካከል በጭቈና ከሚገዛቸው ከሮማ መንግሥት ጋር ተባባሪዎች የነበሩ በመሆናቸው፥ ብዙዎቹ ቀራጮች ደግሞ በሕግ ከታዘዘው በላይ ያስከፍሉአቸው ስለነበረና ጨካኞች ስለነበሩ ነው። ስለዚህ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን በጌታችን ላይ ከሚያቀርቡት ክስና ወቀሳ መካከል ሌላው አይሁዳዊ እንደሚያደርገው ሁሉ ለምን እነዚህን ቀራጮችና ኃጢአተኞች አያባርርም የሚል ነበር። እርሱ ግን ቀራጮችንና ኃጢአተኞችን ይቀበል ነበር።

ከእነርሱም ጋር በማእድ ይቀመጥ ነበር። ስለዚህም የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች የከሰሱበት ዋነኛው ምክንያታቸው እርሱ ኃጢአተኞችን የሚቀበል ከሆነ እንደ እነርሱ ኃጢአተኛ ነው በማለት ነው።

በዚህም ምክንያት ነው ጌታችን የጠፋውን በግ ምሳሌ ያቀረበላቸው። እንደ ምሳሌው አባባል አንድ ሰው ከመቶ በጎች አንዱ በግ ቢጠፋበት ያልጠፋትን ዘጠና ዘጠኙን ትቶ የጠፋውን አንዱን በግ ለመፈለግ እንደሚሄድ ሁሉ ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ በንስሐ በሚመለሰው በአንዱ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል ብሎአል። ጌታችንም ከመለኮታዊ ክብሩ ራሱን ዝቅ አድርጎ የሰውን ሥጋ በመልበስ ሕማማትንና ሞትን የተቀበለው ኃጢአተኞችን ለመታደግ ብሎ ነው። እርሱም በምሳሌ እንደተናገረው ሕሙማን ተኞች እንጂ ጤነኞች ሐኪም አያስፈልጋቸውም። እርሱም:- እኔ ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም ብሎአል (ሉቃ: ም:5ቍ:31፥32)።

ስለዚህ ጌታችን ወደዚህ ዓለም የመጣበት ዋናው ምክንያት በኃጢአት ጠፍተው የነበሩትን ሰዎች በንስሐ ለመመለስ በመሆኑ ጠፍቶ የተገኘውን በግ ምሳሌ ነገሮአቸዋል።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካቀረባቸው ምሳሌዎች መካከል የብልጉ መጋቢ ምሳሌ ይገኝበታል። መድኀኒታችን ደቀ መዛሙርቱ የእርሱን ትምህርት ለማስተማር ብቃት እንዲኖራቸው ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ትምህርቶችን ሁሉ ያስተምራቸው ነበር። በዚህም መሠረት በብልጉ መጋቢ ምሳሌነት በዚህ ዓለም በእጃቸው ያለውን ሀብትና ንብረት በሚገባ እንዲጠቀሙበት አስተምሮአቸዋል። ይህም ንብረት የእነርሱ ሳይሆን የእግዚአብሔር ነው። እነርሱ ወኪሎች ብቻ በመሆናቸው በዚሁ በውክልናቸው አጠቃቀምን ማሳመር ይኖርባቸዋል። ብልኆችና ታማኞችም መሆን ይኖርባቸዋል። ይህንንም ደኅና አድርጎ ሊያብራራላቸው ብሎ የብልጉን መጋቢ ምሳሌ ዘርዝሮ አስረዳቸው።

በዚህ ምሳሌ ውስጥ ሁሉም ነገር የእርሱ ስለሆነ እግዚአብሔር በሀብታሙ ሰው ይመሰላል፤ ሰው ሁሉ በመጋቢው ይመሰላል። ሰውም በመጋቢ የሚመ

www.ethiopianorthodox.org

ስልበት ምክንያት በዚህ ዓለም ላይ ያለ ማንኛውም ንበረት የሰዎች ስላልሆነ ነው። ሰዎችም ከእግዚአብሔር በውክልና የተሰጣቸውን ሀብትና ንብረት በተገቢው መንገድ ሊጠቀሙበት፥ ሊሠሩበትና ፍሬያማ እንዲሆን ሊያርጉት ኀላፊነት አለባቸው። ይሁን እንጂ ብዙዎች ሰዎች እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ላይ የሰጣቸውን ሀብትና ንብረት ተገቢ በሆነ መንገድ አያሠሩትም፤ አይሠሩ በትምም። ነገር ግን በከንቱ ሁሉንም ወይም ከፊሉን ያባክኑታል። ለነገው ለነፍሳቸው የመዳን ሳያስቡ ልክ እንደ ግላቸው ንብረት ቈጥረውት ለዓለማዊ ደስታና ምቾት ያባክኑታል። በምሳሌው እንደተገለጠው ሀብታሙ ሰው ወኪሉ ገንዘቡን በከንቱ የሚያባክን መሆኑን በሰማ ጊዜ በውክልናው ሥር ስላለው ንብረት አቅርቦ እንዲተሳሰበው አስጠራው። ይህንንም ያደረገው ወኪሉ በውክልናው ታማኝ ሆኖ ስላልተገኘ ሊያባርረው ፈልጎ ነው። በዚህ ጊዜ ወኪሉ ጌታው ከሥራው ሲያባርረው የኑሮ ችግር እንዳይገጥመው የብልኀነት ሥራ ሠራ፤ በዚያም ተመሰገነበት። የተመሰገነውም የጌታውን ገንዘብ ስላባከነ ወይም በጌታው ባለ ዕዳዎች በኩል ታማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ ሳይሆን ለወደፊት ኑሮ ዋስትና የሚያስገኝለትን መንገድ በማመቻቸት ረገድ ብልኀተኛ ሆኖ በመገኘቱ ነው። ይህም አሠራሩ ከእግዚአብሔር ሰዎች ይልቅ የዓለም ሰዎች በዓለማዊ ኑሮአቸው ብልኆች መሆናቸውን ያሳያል ብሏል። ይህም ማለት ለዓለማዊ ኑሮአቸው እንጂ ለመንፈሳዊ ወይም ለሰማያዊ ኑሮአቸው ማለት አይደለም።

ከዚያም ቀጥሎ ጌታችን «የዐመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘለዓለም ቤቶች እንዲቀበሉአችሁ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ» ማለት በዚህ ዓለም ሀብት ወዳጆች አብጁ እላችኋለሁ፤ ይህን ብታደርጉ ገንዘባችሁ አልቆባችሁ ባዶ እጃችሁን ብትቀሩ ወዳጆቻችሁ ለዘለዓለም በሚኖሩበት ቤት ይቀበሉ አችኋል ብሎአል። የዐመፅ ገንዘብ የተባለበትም ምክንያት እኛ በዚህ ዓለም ላይ በምንኖርበት ዘመን የሚኖረን ሀብት ሁሉ እግዚአብሔር ለእኛ በውክልና የሰጠንና በተገቢው መንገድ እንድንጠቀምበት የሚጠበቅብን እንጂ የእኛ የግላችን ሆኖ እንደምንም የምናባክነው መሆን የማይገባ በመሆኑ ነው። እንዲሁም በትንሽ የታመነ በብዙም የታመነ ነው፤ በትንሽ ያልታመነ ደግሞ በብዙም ያልታመነ ነው፤ በዐመፃ ገንዘብ ካልታመናችሁ እውነተኛውንስ ገንዘብ ማን ዐደራ ይሰጣችኋል? በሌላ ሰው ገንዘብ ካልታመናችሁ የእናንተ የሆነውን ገንዘብ ማን ይሰጣችኋል? ይህም ማለት የዚህን ዓለም ሀብት በማስተዳደር የማትታመኑ ከሆናችሁ እውነተኛውን ሀብትማ ማን አምኖ ይሰጣችኋል? ደግሞም በሌላው ሰው ሀብት የማትታመኑ ከሆነ ለእናንተ የሚሆንውንስ ማን ይሰጣችኋል? ብሎአል። እውነተኛ ያልሆነው፥ ወይም የዐመፅ ገንዘብ፥ ወይም የሌላ የሆነ እንጂ የራስ ያልሆነ ገንዘብ የተባለው በዚህ ዓለም ባለበት ጊዜ የሚኖረው ገንዘብ እግዚአብሔር በዐደራነት እንዲሠራበት ለሰው የሰጠው ሀብትና ገንዘብ ነው ለማለት ነው። ሰው በሚሞትበት ጊዜ ከዚያች ሀብትና ገንዘብ አንዳች እንኳ የእርሱ ስለማይሆን ባለቤትነቱም የእግዚአብሔር እንጂ የእርሱ አለመሆኑ ግልጽ ነው። እውነተኛ ያልሆነ የተባለውም ለዚህ ነው። ሰው ከሞተ በኋላ ሀብቱ ሁሉ የእርሱ እንዳልነበረ ይሆናል። እውነተኛው በረከትና



መንፈሳዊው ጸጋ ግን ዘለዓለም ነዋሪ የሆነው ሰማያዊ ሀብት ነው። ይህም በወዲያኛው ዓለም ዘወትር የሚደሰትበትና መቼም የማይጠፋ ነው።

እንግዲህ የእርሱ የራሱ ባልሆነው በሚጠፋውና እንደ ትንሽ በሚቈጠረው በዚህ ዓለም ገንዘብ የሚጠበቅበትን ተግባር ለማከናወን ታማኝ ሆኖ ካልተገኘ እንደምን አድርጎ ለሰማያዊው ሀብት የተገባ ሊሆን ይችላል?

• ሰው ለሁለት ጌታ መገዛት እንደማይችል ሁሉ በዚሁም ዐይነት ማንም ሰው በአንድ ላይ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ ሊገዛ አይችልም። በገንዘቡ ምን ማድረግ እንደሚገባው እግዚአብሔር የሚጠብቅበት ሰው የሚጠበቅበትን ተግባር ሳይፈጽም ቢገኝ ያ ሰው እግዚአብሔርን ትቶ ገንዘብን እንደማምለክ ይቈጠርበታል። ገንዘብን ማምለክ ደግሞ እንደ ጣዖት አምልኮ ስለሚቈጠር መጀመሪያውንና ታላቁን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ማፍረስ ነው።

ታማኝ ሆኖ ያልተገኘው መጋቢ የተመሰገነው በብልኀነቱ ነው እንጂ እምነተቢስ በመሆኑ አይደለም። እንደ እባብ ብልኆች እንደ ርግብ የዋሆች ሁኑ ሲል እንደ እባብ ተንኰለኛ ሁኑ ለማለት አይደለም። አንድ ሰው አንበሳ ነው በሚባልበት ጊዜ እንደ አንበሳ ጐበዝ ነው ለማለት ነው እንጂ እንደ አንበሳ አውሬ ነው ለማለት አይደለም። ስለዚህ እምነተቢሱ መጋቢ የተመሰገነው በብልኀነቱ ነው እንጂ እምነተቢስ በመሆኑ አይደለም።

## ጥያቄዎች

1. መጨነቅ የማይገባ ለመሆኑ ጌታችን ያቀረባቸው ሁለት ምሳሌዎች ምንና ምን ናቸው?

2. በዚህ ትምህርቱ ጌታችን ከመጨነቅ ይልቅ አማራጩ ምን እደሆነ ገለጠ?

3. ጌታችን ስለ ጠባብዋ በር የተናገረው ምን ስለ ተጠየቀ ነው?

4. በጠባብዋ በር የሚገቡት ሰዎች ብዛት ምን ያኽል ነው?

5. ለመግባት የሚፈልጉትስ ምን ያኽል ናቸው?

6. በር ለሚያንኳኩት ጌታ ምን ይላቸዋል?

7. እነርሱስ ምን ይላሉ?

8. በማእድ ይቀመጣሉ የተባሉት እነማን ናቸው?

9. መጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ጌታችን የላካቸው ምን በሰማ ጊዜ ነው?

10. የላካቸውስ ምን ብሎ ነው?

11. መልእክተኞቹ በመጡ ጊዜ ጌታችን ምን አደረገ?

12. ለእነርሱስ ምን አላቸው?

13. መልእክተኞቹ ከሄዱ በኋላ ጌታችን ስለ ዮሐንስ ምን አለ?

www.ethiopianorthodox.org

14. ጌታችን በሰንበት ቀን በምኵራብ ስለፈወሳት ሴት የተቈጣው ማነው?

15. ጌታችንስ ለእርሱ ምን መልስ ሰጠው?

16. ጌታችንስ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው እንዴት ፈወሰው?

17. ፈሪሳውያን የዳነውን ሰው ምን ብለው ጠየቁት?

18. እርሱስ ምን ብሎ መለሰ?

19. በዚህ ፈውስ ምክንያት ፈሪሳውያን እንዴት ተለያዩ?

20. ፈሪሳውያን የዳነውን ሰው ምን አስተያየት ጠየቁት?

21. እርሱስ ምን መልስ ሰጣቸው?

22. ፈሪሳውያን ዐይኑ ያየለትን ሰው ለምን ከምኵራብ አስወጡት?

23. በሀብታሙ ሰውና በድኻው አልዓዛር ምሳሌ ታሪክ ውስጥ አልዓዛር ይመኝ የነበረው ምንድነው?

24. ድኻው አልዓዛር በሞተ ጊዜ በምን፥ ወዴት ተወሰደ?

25. ሀብታሙ ሰው ከሞተ በኋላ የት ሆኖ ነው አብርሃምን የጠራው?

26. አብርሃምን ምን ብሎ ለመነው?

27. እርሱስ ምን ብሎ መለሰለት?

28. ከዚያስ በኋለ ምን ሌላ ልመና ለመነው?

29. አብርሃምስ ምን መልስ ሰጠው?

30. ሀብታሙ ሰው ከሞት የተነሣ ሰው ቢነግራቸው ያምናሉ ላለው ሐሳብ አብርሃም ምን መልስ ሰጠው?

31. ጠፍቶ ስለተገኘው በግ ምሳሌ ተናገር?

32. ምን ሲሆን ነው በሰማይ ደስታ ይሆናል የተባለው?

33. ለሀብታሙ ሰው ስለመጋቢው ምን ተነገረው?

34. ስለዚህ ሀብታሙ ሰው መጋቢውን ምን አለው?

35. በዚህ ጊዜ መጋቢው ምን አሰበ?

36. አሰቦስ ምን አደረገ?

37. ሀብታሙ ሰው እምነተቢሱን መጋቢ ስለምን አመሰገነው?

38. በዚህ ዓለም ሀብት ወዳጆችን አብጁ ሲል ለምን እንዲጠቅም ብሎ ነው?

39. ምን እንበላለን፥ ምንስ እንለብሳለን ብላችሁ አትጨነቁ ማለት ምንም ሥራ አትሥሩ ማለት ነውን?

40. ዝም ብሎ መጨነቅ ከምን ይቈጠራል?

41. ምግብና ልብስ ከምን ጋር ሲነጻጸሩ ነው እንደ ትንሽ ነገር የሚቈጠሩት?

www.ethiopianorthodox.org



42. የሚድኑ ጥቂቶች ናቸውን ብሎ የጠየቀው ሰው ወዳጅ ቢሆን የጥያቄው ዓላማ ምን ሊሆን ይችላል?

43. ጠላት ከሆነስ ዓላማው ምን ሊሆን ይችላል?

44. ጌታችን ግን ለጥያቄው የሰጠው ምን ዐይነት መልስ ነው?

45. ወደ መዳን የሚያስገባው በር ጠባብ የሆነው በምን ምክንያት ነው?

46. ከጌታችን ጋር በአንድ ማእድ የበሉ ሁሉ የሚድኑ ላለመሆናቸው ምሳሌ ስጥ።

47. የጌታችንን ትምህርት ያዳመጡ ሁሉ የሚድኑ ላለመሆናቸው ምሳሌ አቅርብ

48. ፊተኞች ኋለኞች፥ ኋለኞች ደግሞ ፊተኞች ይሆናሉ ያለው ምን ለማለት ነው?

49. ነቢያት ዓለምን ለማዳን ይመጣል ብለው ትንቢት የተናገሩለት ክርስቶስ እርሱ መሆኑን የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት የተጠራጠሩት ለምንድ ነው?

50. መጥምቁ ዮሐንስ ሁለት ደቀ መዛሙርቱን ወደ ጌታችን የላከበት ዋና ዐላማ ምንድነው?

51. እነዚያ መልእክተኞች ምን አረጋግጠው ተመለሱ?

52. የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ከሄዱ በኋላ ጌታችን ስለ ዮሐንስ የተናገረው ንግግር ምንን ያመለክታል?

53. ከሴቶች ከተወለዱ ሰዎች መካከል ዮሐንስን የሚበልጠው እንደሌለ ከተናገረ በኋላ፥ ነገር ግን በመንግሥተ ሰማይ የሚያንሰው ይበልጠዋል ለሚለው ሁለት ትርጓሜዎች አቅርብ።

54. ጌታችን እንዲፈውሳት ሳትለምነው አዝኖላት የፈወሳት ሴት በሽታዋ ምን ነበር? በምንስ ምክንያት?

55. በሽታው ከያዛት ስንት ጊዜ ሆኖአት ነበር?

56. ጌታችን ያቺን በሽተኛ የአብርሃም ልጅ ነች ማለቱ ምንን ያመለ ክታል?

57. እንዲፈውሳት ሳትለምነው መፈወሱ የትኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ያመለክታል?

58. የዚህች ሴት ሕመም ታሪክ የሚያስተምረን ታላቅ ቁም ነገር ምንድ ነው?

59. ጌታችን ተአምራት የሠራባቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?

60. ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው እንዲያይ ማድረጉ ምንን ያረጋግጣል? በምን ምክንያት?

61. ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ባዩ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ጌታችንን ምን ብለው ጠየቁት?

62. እርሱስ ምን መልስ ሰጣቸው?

63. ዕውር ሆኖ ተወልዶ የነበረውን ሰው ፈሪሳውያን መላልሰው የጠየቁት በምን ምክንያት ነው?

64. የድኻው አልዓዛርና የሀብታሙ ሰው ምሳሌ እውነተኛ ታሪክ ነው የሚያሰኙት ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?

65. የሀብታሙ ሰው ስም ያልተነገረው በምን ምክንያት ነው?

66. በዚህ የምሳሌ ታሪክ ውስጥ የምናስተውላቸው ሰባት ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?

67. የአይሁድ የሃይማኖት ሰዎች ጌታችንን የሚጠሉበት ምክንያት ምን ነበር?

68. በመጥላታቸው ምክንያትስ ምን ያደርጉ ነበር?

69. አይሁድ ቀራጮችን የሚጠሉአቸው በምን ምክንያት ነበር?

70. ጌታችን ሕመምተኞች እንጂ ጤነኞች ሐኪም አያስፈልጋቸውም ያለው በምን ምክንያት ነው?

71. በብልጉ መጋቢ ምሳሌ ውስጥ በሀብታሙ ሰው የሚመሰለው ማነው? ለምን?

72. በመጋቢው የሚመሰለው ማነው? ለምን?

73. በዚህ ምሳሌ ላይ የዐመፃ ገንዘብ የተባለው የቱ ነው?

# ምዕራፍ 4

# ቤተ ክርስቲያን

## ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን

ቀደም ተብሎ በአንደኛ ክፍል መጽሐፍ በምዕራፍ አራት ላይ ቤተ ክርስቲያን ለሚለው ቃል ትርጉም በተሰጠበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን አራት ትርጉሞች እንዳሉአት ተገልጦ ነበር። እነዚህም ትርጉሞች:- ምእመናን፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፥ የቤተ ክርስቲያን አስተደርና ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ናቸው።

ትምህርቱን ግልጽ ለማድረግ በዚህ አሁን በያዝነው ምዕራፍ ውስጥ የሚቀርበው ትምህርት በምእመናንና በቤተ ክርስቲያን መሪዎች፥ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መካከል ያለውን ግንኙት በተመለከተ ነው።



በዚህም መሠረት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወይም አስተዳደሩ ለምእመናን ወይም ለሕዝበ ክርስቲያኑ የሚያቀርቡአቸው ግልጋሎቶች ምን ምን ተብለው ሊዘረዘሩ ይችላሉ? ከእነዚህ ግልጋሎቶች መካከል ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፥ የሃይማኖት ትምህርት፥ ችግረኞችን መርዳት፥ ያዘኑትን ማጽናናት፥ የተጣሉትን ማስታረቅ፥ ቡራኬ መስጠት፥ ጸሎተ ቅዳሴንና ሌሎች ልዩ ልዩ ጸሎቶችን ማካሄድ ይገኙባቸዋል። እነዚህም ግልጋሎቶች በተለያየ የክህነት ደረጃ የሚቀርቡ ናቸው።

ምእመናን ወደ ክርስትናው ማኅበረሰብ የሚገቡበት መታወቂያቸው ጥምቀት ነው። በጥምቀትም አማካይነት የተለያዩ መንፈሳውያን ጸጋዎች ይገኛሉ።

ሰው በሚጠመቅበት ጊዜ ከተወረሰውም፥ ከተፈጸመውም ኃጢአት ይቅር የመባል ጸጋ ቢያገኝም ከሥጋችን ደካማነት የተነሣ ኃጢአት እንዳንሠራ በጸላኤ ሠናይ ላይ ብርታት የሚሰጠንን መንፈስ ቅዱስን የምንቀበልበት የሜሮን መቀባት ሥነ ሥርዓት የምታከናውንልን ቤተ ክርስቲያን ነች።

የተቀደሰውን የጌታችንን ሥጋና ደም በመቀበል የኃጢአት ስርየትና ከጌታችን ጋር ኅብረት የምናገኘው በቤተ ክርስቲያን የቅዳሴ ጸሎት አማካይነት ነው።

ካህናት ለምእመናን የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ ለማድረግ በጳጳሳትዋ አማካይነት የምትሰይማቸው ቤተ ክርስቲያን ነች።

ባልና ሚስት በጋብቻ እንዲጣመሩ የተክሊል ሥነ ሥርዓት የምታከናውነው ቤተ ክርስቲያን ነች።

ለሥጋ ሕመም ፈውስና ለኃጢአት ስርየት የሚፈጸመውን የቀንዲል ጸሎት ሥነ ሥርዓት የምታከናውነው ቤተ ክርስቲያን ነች።

<u>የሃይማኖት ትምህርት</u>:- ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ትምህርትዋን ለምእመናንዋ የምታቀርበው በጳጳሳትዋና በቀሳውስትዋ አማካይነት ነው። ለዚህም የሐዋርያት ትምህርት የሆነው መጽሐፈ ዲድስቅልያ ምን እንደሚል እንመልከት።

«ኤጲስ ቆጶስ ሆይ፥ የመጻሕፍትን ቃላት ሁሉ ተርጉም፤ በቅዱሳት መጻሕፍት ብርሃንም ሕዝብህን አርካ፤ ሕዝቡም በትምህርትህ ብዛት ይበለጽጋል። ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ እንዳለው ብርሃን ከእናንተ ጋር እስካለ ድረስ በብርሃን ተመላለሱ» (ዲድስቅልያ አንቀጽ 3)።

«ምእመናን ሆይ፥ ቀሳውስት በእግዚአብሔር እምነት ላይ በቂ ዕውቀት ያላቸው አስተማሪዎች ይሁኑ። እነርሱም ከእኛ ተቀብለው እውነተኛውን እምነት ያስተምሩአችኋል፤ ጌታም እኛን እንድናስተምር በላከን ጊዜ:- ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ፤ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው የእኔ ደቀ መዛሙርት አድርጉአቸው። ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲፈጽሙ አስተምሩአቸው፤ እነሆ እኔም እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ ብሎናል» (ዲድስቅልያ አንቀጽ 6)።

www.ethiopianorthodox.org

በመጽሐፈ ዲድስቅልያ አንቀጽ 4 ላይ ተዘርዝሮ እንደተገለጠው ኤጲስ ቆጶሱ ማለትም የቤተ ክርስቲያን መሪ የሆነው ሰው አንድ ኃጢአተኛ ወደ ጥፋት ሲሄድ ዝም ብሎ ማየት እንደሌለበት ከማዘዙም በላይ እርሱ ሳያስተምር ቀርቶ ኃጢአተኛው ኃጢአት በመሥራቱ ቢፈረድበትም እንኳ ኤጲስ ቆጶሱ፥ መምህሩ፥ ማለትም የቤተ ክርስቲያን የበላይ ኀላፊው መላልሶ ባለማስተማሩና ኃጢአተኛውን ባለመመለሱ በኀላፊነት ይጠየቅበታል። የዲድስቅልያውም መጽሐፍ ይህን በሚልበት ጊዜ በትንቢተ ሕዝቅኤል የተነገረውን አባባል ይጠቅሳል።

«የሰው ልጅ ሆይ፥ በአንድ አገር ላይ ሰይፍን በማመጣበት ጊዜ የሚሆነውን ነገር ሁሉ ለሕዝብህ ንገራቸው፤ የዚያች አገር ሕዝብ ቃፊር ሆኖ የሚጠብቅ ሰው ከመካከላቸው ይመርጣሉ፤ ጠባቂውም ጠላት ሲመጣ በሚያይበት ጊዜ ከአደጋ መጠንቀቅ የሚያስችል የመለከት ድምፅ ለሰዎች ሁሉ ያሰማል። ማንም ሰው ይህን የማስጠንቀቂያ ድምፅ ሰምቶ ባለማጤኑ ምክንያት ጠላት አደጋ ጥሎበት ቢሞት ጥፋቱ የራሱ ነው፤ ማስጠንቀቂያውን ባለማጤኑ ለሞት ያበቃው የራሱ ስሕተት ነው፤ ማስጠንቀቂያውን ቢያጤንማ ኖሮ ከጥፋት ባመለጠ ነበር፤ ነገር ግን ቃፊሩ ጠላት ሲመጣ እያየ የአደጋ ማስጠንቀቂያውን ድምፅ ሳያሰማ ቢቀር ጠላት መጥቶ እነዚያን ኃጢአተኞች ሰዎች ይገድላል፤ እኔ ግን ስለ እነርሱ ደም ለመበቀል በኀላፊነት የምጠይቀው ጠባቂውን ነው። አሁንም የሰው ልጅ ሆይ፥ እነሆ፥ እኔ አንተን ለእስራኤል ሕዝብ ጠባቂ አድርጌሃለሁ፤ እኔ የምሰጥህን ማስጠንቀቂያ ሁሉ ለእነርሱ ማስተላለፍ አለብህ፤ ኃጢአተኛውን ሰው:- ኃጢአተኛ ሆይ፥ በእርግጥ ትሞታለህ በምለው ጊዜ አንተ ከክፉ ሥራው እንዲመለስ ባታስጠነቅቀው ያ ሰው ኃጢአተኛ እንደሆነ በኃጢአቱ ይሞታል፤ ስለ እርሱም ሞት አንተን ራስህን በኀላፊነት ተጠያቂ አደርግሃለሁ። ኃጢአተኛውን ሰው ከክፉ ሥራው እንዲመለስ ካስጠነቀቅኸው በኋላ፥ ከክፉ ሥራው ሳይመለስ በኃጢአቱ ጸንቶ ቢሞት ግን አንተ ራስህን ከኀላፊነት ነጻ ታደርጋለህ» (ሕዝ:ም:33ቍ:2–9)።

የነቢዩ አባባል ትርጓሜም:- ሰይፉ በፍርድ፥ ድምፁ በወንጌል፥ ጠባቂው በኤጲስ ቆጶሱ ይመሰላሉ። ኤጲስ ቆጶሳትና ቀሳውስትም ያልተማረውን እንዲያስተምሩ፥ የተማረውን እንዲያጠናክሩት፥ ያጠፉትን እስኪመልሱ ድረስ መላልሰው እንዲያስተምሩ ታዝዘዋል፤ መላልሰው ቢያስተምሩ ምናልባት አንዳንዱ ኃጢአተኛ ከኃጢአቱ ይመለስ ይሆናል። ባይመለስም እነርሱ መላልሰው ስላስተማሩ በኃጢአቱ ለሚጠፋው ሰው በኀላፊነት አይጠየቁም (ዲድስቅልያ አንቀጽ 3)።

ኤጲስ ቆጶሱም ምእመናንን እንደ ልጆቹ በመውደድ ዶሮ እንቍላሎችዋ ወደጫጬትነት እስኪለወጡና ከዚያም ራሳቸውን እስኪችሉ ድረስ በክንፎችዋ ሥር እንደምታቅፍ የፍቅርን ሥነ ምግባር ያስተምራቸው፤ እንደ ልጆቹም ይቀበላቸው። የጭካኔ ሳይሆን የአባትነት ተግሣጽ ይገሥጻቸው። በኃጢአታቸው እንዲያፍሩ ይገሥጻቸው እንጂ አፍረው ዳግመኛ እንዳይመጡ

www.ethiopianorthodox.org



አያድርጋቸው። ነገር ግን እነርሱ ወደ እርሱ ተመልሰው ቀጥ ብሎ የመሄ[illegible] ሁናቴአቸውን እንዲያስተካክሉ ያስተምራቸው። በኃጢአት የጠፋውንና የተ[illegible] በረውን ሰው በማስተማር መድኀኒትነት እንደ ጥንቁቅ ሐኪም ይፈውሰ[illegible] (ዲድ አንቀጽ:4)።

መጽሐፈ ዲድስቅልያ ለኃጢአተኛ እንክብካቤ ማድረግ እንደሚገባ ሲያመ ለክት እንዲህ ይላል:-

«አንድ ሰው በባሕር ዳር ሲራመድ ቢያዳልጠውና አንተ እርሱን ለማዳን እጁን ይዘህ ከባሕሩ ወደ ውጪ በመጐተት ፈንታ ወደ ባሕሩ ብትገፋና ብትጥለው ወንድምህን ገደልከው ማለት ነው፤ አንተ ማድረግ ያለብህ አዳልጦት ሊወድቅ የተቃረበውን ሰው እንዲድን መርዳት እንጂ እንዲጠፋ መተው አይደለም።

ኤጲስ ቆጶስ ሆይ፥ ንስሓ የሚገባውን ሰው በማባረር የሕዝቡን ኃጢአት ችላ አትበል፤ ይህን ብታደርግ የጌታህን መንጋዎች እንዲጠፉ ማድረግህ ነው። ይህም ከሆነ የሃይማኖቱ ስም ይሰደባል። አንተም:- ብዙ እረኞች የወይኑን ቦታዬን አጥፍተዋል፤ ዕድል ፈንታዬንም ረግጠዋል እንደተባሉት እረኞች ትነቀፋለህ» (ዲድ:አን:4፥ኤር:ም12ቍ:10)።

ከላይ በቀረቡት ገለጻዎች መሠረት ቤተ ክርስቲያን በመሪዎችዋና በቀሳውስትዋ አማካይነት ምእመናንን በትጋት እንድታስተምር ይጠበቅባታል።

<u>ችግረኞችን መርዳት</u>:- እንደ ዲድስቅልያ አባባል እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ችግረኞች ቤተ ክርስቲያን የምትረዳው በኤጲስ ቆጶሱ አማካይነት ነው (አንቀጽ 5 እና 19)።

ቤተ ክርስቲያን ራስዋ እየተረዳች የምትኖር እስከሆነ ድረስ ከወዴት አምጥታ ችግረኞችን ትረዳለች? ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል። በኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 26 ቍ 12 ላይ የተሰጠውን ትእዛዝ ቀጥለን እንመልከት:-

«በሦስተኛው ዓመት፥ ማለት በዐሥራት ዓመት ዐሥራትህን ሁሉ አጠናቅቀህ ከሰበሰብህ በኋላ በከተማህ ለሚገኙ ለሌዋውያን፥ ለመጻተኞች፥ ለሙት ልጆችና ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ሴቶች ሰጥህ ጠግበው እንዲበሉ አድርግ» (ዘዳ:ም:26ቍ:12)።

ይህንኑ አባባል መጽሐፈ ዲድስቅልያ ሲደግመው እንዲህ ብሏል።

«በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት ለቤተ ክርስቲያን የሚከፈሉት ዐሥራትና በኵራት ለእግዚአብሔር አገልጋዮች የተለዩ ይሁኑ፤ ለድኆች የሚመጣው ደግሞ በትክክል መከፋፈል ይኖርበታል፤ እርሱም ለዕጓለ ማውታ፥ ለመበለቶች፥ ለመጻተኞችና ለችግረኞች መከፋፈል ይኖርበታል። ይህንንም በእጃችሁ የገባውን ገንዘብ በትክክልና ፍትሓዊ በሆነ መንገድ እንደየአስፈላጊነቱ አከፋፍሉት» (ዲድስቅልያ አንቀጽ 5)።

ስለዚህ ቤት ክርስቲያን ድኾችን የምትረዳው ምእመናንን ወክላ ከምእመናን በሚመጣው ገንዘብ ነው።

<u>ያዘኑትን ማጽናናትና የተጣሉትን ማስታረቅ</u>:- ቤት ክርስቲያን በካህናትዋ አመካይነት በሐዘን ላይ ያሉትን ምእመናን እንድታስተዛዝን፥ የተጨነቁትን እንድታጽናና፥ የተጣሉትን እንድታስታርቅ ታዝዛለች። በዚህም መነሻነት ተጸጽቶ በንስሓ የሚመጣውን ኃጢአተኛ አይዞህ በርታ ብላ በማበረታታት እንድትቀበለው የሐዋርያት ትምህርት የሆነው ዲድስቅልያ ያሳስባል። ስለእነዚህ ጉዳዮች በዲድስቅልያው አንቀድ 8 ውስጥ ከታዘዙት ትእዛዞች መካከል በአጠቃላይ የሚከተሉት ጉዳዮች ይገኙባቸዋል።

ከተወለደበት አገር ርቆ በመሄድ የአባቱን ገንዘብ ከዘማውያን ጋር እንዳባከነውና ገንዘቡንም ከጨረሰ በኋላ ተቸግሮ ከዐሣማዎች ምግብ እንኳ ለመብላት ቢፈልግ ያን ምግብ የሚሰጠው እንዳጣው ልጅ ዐይነት አንድ ሰው ተመልሶ የንስሓ ፍሬ ቢያሳይ እርሱን ተቀበሉት። ያም ልጅ በንስሓ ወደ አባቱ ተመልሶ አባቴ ሆይ በሰማይና በአንተ ፊት በድዮአለሁና ልጅህ ልባል አይገባኝም ባለው ጊዜ ነው አባቱ በፍቅር የተቀበለው።

በዚሁ በመጽሐፈ ዲድስቅልያ አንቀጽ 8 ውስጥ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ያቀረበው ትምህርት ይነበባል።

በመካከላችሁ የሚኖር ክፋትን ትታችሁ እያንዳንዱ የሌላውን በደል ይቅር ይበል። እርስ በርሳችሁ ይቅር ተባባሉ። እኔ ጴጥሮስ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው ሰባት ጊዜ ነውን ብዬ ጌታን ለጠየቅሁት ጥያቄ ሰባት ጊዜ ብቻ አልልህም፤ ሰባ ጊዜ ሰባት ነው ብሎ መልሶልኛል። ጌታችንም በዚህ አባባሉ በደቀ መዛሙርቱና በወንድሞቻቸው መካከል ምንም ዐይነት ቂም፥ ጥላቻና ክፉ ስሜት እንዲኖር የማይፈልግ መሆኑን ያመለክታል። ጌታችን ሰዎችን የሚያስታርቁ የእግዚአብሔር ልጆች ስለሚባሉ ብፁዓን ናቸው ባለው መሠረት የተጣሉትን፥ የተቀያየሙትንና የተኰራረፉትን አስታርቁ፤ የማይስማሙትንም እንዲስማው አድርጉ።

ኤጲስ ቆጶሱም የሁለቱን ጠበኞች ጉዳይ በዳኝነት በሚያይበት ጊዜ ቀሳውስትና ዲያቆናትም ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ ያድርግ።

<u>መባረክ</u>:- መባረክ ሲባል እንደየጉዳዩ አመጣጥ የተለያዩ ትርጉሞች አሉት።

1. ልዩ ልዩ ድርጊቶችን በማድረግና ጸሎትን በመጸለይ ሰዎችን፥ ቦታዎችን፥ ወይም ዕቃዎችን ለእግዚአብሔር የተለዩ ማድረግ መቀደስ ወይም መባረክ ይባላል። ለምሳሌ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ተመሥርቶ በዚያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአምልኮ ሥርዓት ከመጀመሩ በፊት አንድ ጳጳስ ይባርከዋል። ወደ አሪቱ ሥርዓት መለስ ያልን እንደሆነ ደግሞ ለምሳሌ ንጉሥ ሕዝቅያስ ሌዋውያንን ቤተ መቅሱን እንዲያነጹ፥ እንዲቀድሱት ማለት ሌሎች ነገሥታት አርክሰውት ስለነበረ እንደገና ለእግዚአብሔር አምልኮ ቦታነት



መንፈሳዊ ብቃት እንዲኖረው በጸሎትና በድርጊት እንዲባርኩት አደረጋቸው (2ኛ:ዜ:መ:ም:29)። እንዲሁም ነቢያትና መምህራን በነበሩባት በአንጾኪያ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ሁሉም ሲጾሙና እግዚአብሔርን ሲያመልኩ ሳለ መንፈስ ቅዱስ «እኔ ለመረጥኋቸው ሥራ በርናባስንና ሳውልን ለዩልኝ አላቸው»። እነርሱም የመንፈስ ቅዱስን ቃል በማክበር ከጾሙና ከጸለዩ፥ እጃቸውንም ከጫኑባቸው በኋላ አሰናበቱአቸው። ይህም ማለት ባርከው አሰናበቱአቸው ማለት ነው (የሐ:ሥ:ም:13ቍ:1–3)። እንዲሁም ካህኑ አዳዲስ ንዋያተ ቅድስትን በጥቅም ላይ ከማዋሉ ከቅዳሴው ጸሎት በፊት በንዋያተ ቅድሳቱ ላይ ጸልዮ ይባርካቸዋል (ሥርዓተ ቅዳሴ)።

2. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በረከቱን ይሰጥ ዘንድ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ካህናት የሚያቀርቡት ጸሎት:- ለአሮንና ለልጆቹ የተሰጠ በረከትን የመስጠት መመሪያ:-

«እግዚአብሔር ይባርክህ፤ ይጠብቅህም፤

እግዚአብሔር የፊቱን ብርሃን ያብራልህ፤ ይራራልህም፤

ሰላሙንም ይስጥህ» (ዘኍ:ም:6ቍ:22–26)።

ሐዲስ ኪዳን:- «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥

የእግዚአብሔር ፍቅር፥

የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን» (2ኛ:ቆሮ: ም: 13ቍ: 14)።

3. ካህናት ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ሥልጣን በእግዚአብሔር ስም ይባርካሉ። ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ሥልጣን ሲሰጥ እንዲህ ብሎአቸዋል:-

«በእውነት እላችኋለሁ፤ በምድር የምታስሩት በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የምትፈቱት በሰማይ የተፈታ ይሆናል» (ማቴ:ም:18ቍ:18)።

በዚህም መሠረት ካህናት ለመእመናን አስፈላጊውን ምክርና መንፈሳዊ ትእዛዝ ከሰጡና ትእዛዙም ተግባራዊ ከሆነ በኋላ ኃጢአትን በማስተስረይ ሥጋ ወደሙ እንዲቀበሉ ይፈቅዱላቸዋል። ይህም ኃጢአትን የማስተስረይ በረከት የተሰጠው ለካህናት ብቻ መሆኑን አንዘንጋ።

በእርግጥ ሌሎችም የመባረክ ትርጉሞች አሉ። ለምሳሌ ሰው እግዚአብሔርን ይባርካል ሲባል እግዚአብሔርን ያመሰግናል ማለት ነው። አንድ አባት ልጁን፥ ወይም አንድ ተራ ምእመን ሌላውን ሰው ይባርካል ሲባል ይመርቃል ማለት ነው እንጂ በትክክለኛ ትርጉሙ ይባርካል ማለት አይደለም። ይህን አባባል በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5ቍ:50 ላይ ብንመለከት «ኤጲስ ቆጶስ ይባርካል እንጂ አይባረክም፤ እንዲሁም በአንቀጽ 6ቍ:12 ላይ ደግሞ «ቄሱ ይባርካል እንጂ አይባርክም» ተብሎ ይገኛል።

www.ethiopianorthodox.org

አንዳንድ ካህናት ያልሆኑ ምእመናን ዕድሜ ሳይለዩ ማንንም ተባረክ እግዚአብሔር ይባርክህ ማለታቸው ትክክል አለመሆኑን ሊገነዘቡት ይገባል።

<u>ጸሎተ ቅዳሴንና ሌሎችን ጸሎቶች መምራት</u>:- እንደሚታወቀው ጸሎት በአጠቃላይ በግልና በኅብረት ጸሎት ይከፈላል። የግል ጸሎት ሲባል አንድ ግለሰብ በቤተ ክርስቲያን ወይም በሌላ ቦታ ሆኖ በግሉ የሚያካሄደው ጸሎት ሲሆን የኅብረት ጸሎት ግን በካህናት መሪነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በኅብረት የሚካሄድ ነው።

ለምሳሌ ክርስቲያኖች ምእመናን ሁሉ በእሑድ ቀንና በተለያዩ በዓላት ቀኖች ወደየ አብያተ ክርስቲያን የሚሄዱት በካህናት መሪነት በሚካሄደውን የቅዳሴ ጸሎት ላይ ተሳታፊ ለመሆን ነው።

ለሀገሪቱና ለሕዝብዋ ደኅንነት፥ ብልጽግናና ሰላም በቅዳሴ፥ በምህላና በማኅሌት ምስጋና የዘወትር ጸሎትዋን ለእግዚአብሔር የምታቀርበው ቤተ ክርስቲያን ነች።

ቀደም ተብሎ እንደተገለጠውም በጸሎት አማካይነት የምሥጢራትን ጸጋ ለምእመናን ታበረክታለች። ከምእመናንም መካከል ሰዎች ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩ ቊጥር የጸሎተ ፍትሐትን አገልግሎት ትሰጣለች።

ጸሎቶችም እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ብቻ ሳይሆኑ የሰዓታት፥ የነግህና የሠርክ እንዲሁም ሌሎች የጸሎት ዐይነቶች አሉ። በእነዚህም ጸሎቶች አማካይነት ስለ ሀገርና ስለሕዝብ ደኅንነት ሳይጸለይ አይታለፍም።

እነዚህ ከላይ የተገለጡት ዝርዝር ሐሳቦች የሚያመለክቱት ቤተ ክርስቲያን ለሕዝበ ክርስቲያኑ ምእመናን የምታቀርባቸው ግልጋሎቶች ሲሆኑ ምእመናንስ ለቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡት ግልጋሎት አለ? ወይስ የለም? የሚያቀርቡት ግልጋሎት አለ የሚባል ከሆነስ ቤተ ክርስቲያን ከምእመናን የምትጠብቀው ግልጋሎት እንደምን ያሉትን ነው?

<u>በቤተ ክርስቲያን የምእመናን ሚና</u>:- በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያሉት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች አበዛኛዎቹ ያላቸው ዕውቀት የሃይማኖት ትምህርት ነው። ለተሰለፉበትም ሥራ የሚጠቅመው ይኸው የሃይማኖት ትምህርት ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ ግን ከመንፈሳዊ ትምህርቱና ከጸሎቱ ሌላም የሚያስፈልጓት ነገሮችና እንዲያውም እነዚሁኑ ተግባሮችን ያለ ችግር ለማካሄድ እንድትችል የሚረድዋት ሰዎች መኖር ይኖርባቸዋል። የቤተ ክርስቲያኑ ሕንጻና አጥር ጥገና ሲያስፈልጋቸው የምሕንድስና ሙያ ያለው አማካሪ ያስፈልጋል። ለንግድ ሳይሆን ለሥራዋ መቃናት አንዳንድ የልማት ዕቅዶችን ስታቅድ የምጣኔ ሀብትና የንግድ ሙያ ያለው አማካሪ ያስፈልጋታል። በልማቱ ውስጥ ለተሠማሩትና በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ለሚያገለግሉ ሠራተኞች አስተዳደራዊ መዋቅር ለማዘጋጀትና በዚያ ለመመራት ከተፈለገ የአስተዳደር ሙያ ያለው አማካሪ ያስፈልጋል። ከዚያም ሁሉ በላይ ሠራተኞችዋን የማስተዳደር፥ ትምህርት ቤት የመክፈትና ነዳያንን የመርዳት ተግባርዋን ያለ ችግር ለማራ-



መድ የግድ በቂ ገንዘብ ያስፈልጋታል። ዋነኛው የገቢ ምንጭዋ ደግሞ ከምእ-መናን የሚሰበሰበው የሙዳየ ምጽዋት፥ የዐሥራትና የስለት ገንዘብ ነው። ምእ-መናንም ይህን የዐሥራት ግዴታ ለመክፈል የግድ ቀስቃሽ ያስፈልጋቸዋል። በትእዛዙ መሠረት ሁሉም ግዴታውን ከከፈለ ደግሞ ገቢው ጥቂት ስለማይሆን የገንዘብ ጉዳይ ባለሙያ የሚሆን አንድ የፋይናንስ አማካሪ ያስፈልጋል። ስለ ዚህ እነዚህን የመሰሉ ባለሙያዎች የሚገኙት ከቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መካከል ሳይሆን ከምእመናን መካከል ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የሁሉም እንጂ የካህናት ብቻ ስላልሆነች ምእመናን በምክርም ሆነ በሙያቸው እንዲያ ገለግልዋት ያስፈልጋል። የምእመናንን ግዴታ በተመለከተ መጽሐፈ ዲድስቅ ልያ ምን ይላል?

«የተመረጠች የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሆይ፥ ስሙ፤ ሕዝቡ በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ሕዝብ፥ ምርጥ ሕዝብ ይባል ነበር፤ እናንተም አሁን በሰማይ የተመዘገበችው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፥ የእግዚአብሔር መንግሥትና ካህናት፥ ንጹሕ ሕዝብ፥ የጌታ ሕዝብ፥ ታላቋ ቤተ ክርስቲያን፥ አማኝዋ ቤተ ክርስቲያን ናችሁ። በመጀመሪያ የተነገረውና እኛም ደግመን የምንነግራችሁ ከቀድሞ ጀምሮ ስለት፥ ዐሥራትና በኵራት ለኢየሱስ ክርስቶስ ካህናት እንዲቀርቡ የተወሰነ መሆኑን ነው» (ዲድስቅልያ አንቀጽ 6)።

«ወንድሞቻችን ምእመናን ሆይ፥ ቊርባናችሁን አምጥታችሁ የካህናት አለቃ እንደመሆኑ ለኤጲስ ቆጶሱ በቀጥታ በእጃችሁ፥ ወይም በዲያቆናት አማካይነት አስረክቡት፤ የምታስረክቡትም ልታመጡ የሚያስፈልጋችሁን በኵራትን፥ ዐሥራትንና ስእለትን ነው። እርሱም ችግረኞችን በትክክል ስለሚያውቃቸው በትክክል እንዲከፋፈል ያደርጋል» (ዲድስቅልያ አንቀጽ 6)።

ለማጠቃለል ያኽል የቤተ ክርስቲያንና የምእመናን አብሮ መሥራት የሚታየው ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ተግባሮችን በምታከናውንበት ጊዜ ምእመናን ደግሞ የቴክኒክና የገንዘብ እርዳታ በማድረግ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

## የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን

<u>ተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ</u>:- የቅዱስ ጴጥሮስ አባት ከእስክንድርያ ትላልቅ ካህናት አንዱ ሲሆን ስሙም ታኦዶስዮስ ይባል ነበር። የእናቱ ስም ደግሞ ሶፊያ ይባል ነበር። እነዚህ የተፈጻሜተ ሰማዕት ወላጆች እግዚአብሔርን በጣም ይፈሩ የነበሩ ሰዎች ሲሆኑ ልጅ ሳይወልዱ ብዙ ጊዜ ቈይተው ነበር። ሐምሌ 5 ቀን በሚውለው በቅዱስ ጴጥሮስና በቅዱስ ጳውሎስ በዓል እናቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዳ ልጆቻቸውን የታቀፉ ሴቶች ባየች ጊዜ በጣም አዘነችና በማልቀስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ልጅ ይሰጣት ዘንድ ተማ ጠነችው። በዚያችው ሌሊት ጴጥሮስና ጳውሎስ ተገልጠውላት ጸሎትዋ ተቀባይነት ማግኘቱንና ወንድ ልጅ ወልዳ ጴጥሮስ የሚል ስም እንደም

www.ethiopianorthodox.org

ታወጣለት ገለጹላት። ወደ ፓትርያርኩ ሄዳ እንዲባርካትም ነገሩአት። ከእንቅልፍዋም እንደነቃች ለባልዋ ነግራው ባየችው ራእይ ደስ ተሰኘ። ከዚያም ወደ ፓትርያርኩ ሄዳ የራእዩን ዝርዝር ከገለጸችለት በኋላ እንዲጸልይላት ለመነችው። እርሱም ጸለየላትና ባረካት። ከጥቂት ጊዜም በኋላ ይህን ቅዱስ ጴጥሮስን ወለደች። አባትና እናቱም ልክ በሰባት ዓመቱ ለነቢዩ ሳሙኤል እንደተደረገው ለፓትርያርክ ታኦና አስረከቡት። እርሱም ልክ እንደ ግል ልጁ በማሳደግ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት አስገባው። በትምህርቱ፥ በተለየም በስብከት እጅግ የበረታ ሆነ። ከዚያም አናጕንስጢስነት ቀጥሎም ዲቁና ተሾመ። ከጥቂት ጊዜም በኋላ የቅስና ማዕረግ ተሾመ። በቤተ ክርስቲያንም አስተዳደር ጉዳይ ፓትርያርኩን ይረዳ ጀመር።

ፓትርያርኩ ታኦና ከእርሱ በኋላ ጴጥሮስ በእርሱ ቦታ እንዲተካ በመናዘዝ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። በማርቆስ መንበር ላይ በተቀመጠ ጊዜ በትምህርቱ ለቤተ ክርስቲያን ብርሃንን አበራ።

በዚህ ፓትርያርክ ዘመን በአንጾኪያ አንድ ሁለት ወንዶች ልጆች የነበሩት ትልቅ ባለ ሥልጣን ወደ ጣዖት አምላኪነት ለመመለስ ከዲዮቅልጥያኖስ ጋር ስምምነት አድርጎ ነበር። የልጆቹ እናት በአንጾኪያ ልጆችዋን ለማስጠመቅ ስላልተቻላት ለዚሁ ዐላማ ወደ እስክንድርያ አመራች። በመንገድ ላይ እያለች የባሕር ሞገድ ተነሣና በጣም የሚያስጋ መሰለ። በዚህ ጊዜ ያቺ እናት ልጆቼ ሳይጠመቁ ይሞቱብኛል ብላ በመስጋት በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም ብላ በባሕሩ ውስጥ በመዝፈቅ ልጆችዋን አጠመቀቻቸው። ሁለቱን ጡቶቿን በመብጣት በደምዋ አማካይነት የሁለቱን ልጆቿን ግንባሮች በመስቀለኛ አማተበችባቸው (ባረከቻቸው)። ከዚያ በኋላ ማዕበሉ ጸጥ ብሎ ከልጆችዋ ጋር በሰላም ወደእስክንድርያ ደረሰች። አንድ ቀን ከሌሎች ለጥምቀት ከቀረቡ ሕፃናት ጋር ልጆችዋን ለማጥመቅ አቀረበቻቸው። ፓትርያርኩ እነዚያን ልጆች ለማጥመቅ በሞከረ ቍጥር ውሃው እንደ ድንጋይ ይጠጥርበት ጀመር። ይህ ሁኔታ ሦስት ጊዜ ከተከሠተ በኋላ ጉዳዩዋን እንድታስረዳ ብትጠየቅ በባሕሩ ማዕበል ጊዜ ምን እንዳደረገች ዘርዝራ አስረዳች። ስለዚህም እግዚአብሔርን አመስግኖ ቤተ ክርስቲያንም ያላት አንድ ጥምቀት ብቻ ነው አለ።

ከሐዲው አርዮስም የተነሣው በዚህ ቅዱስ ዘመን ነው። ከክሕደት ትምህርቱ ተመልሶ ንስሓ እንዲገባ ፓትርያርኩ መላልሶ መክሮት ነበር። እርሱ ግን ምክሩን ተቀብሎ ስላልተመለሰ አውግዞ ከቤተ ክርስቲያን ኅብረት ለየው።

አርዮስ፥ ጣዖት አምላኪ ወደ ነበረው ወደ ንጉሥ መክሲሚያኖስ በላከው መልእክት፥ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ጴጥሮስ ሰዎች አማልክታቸውን እንደያመልኩ ያሳድማል ብሎ ከሰሰው። በዚህ ጊዜ ንጉሡ በጣም በመቈጣት የፓትርያርኩን ራስ እንዲቈርጡ መልእክተኞች ላከ። መልእክተኞቹም ወደ እስክንድርያ በመሄድ ሕዝቡን ጨፈጨፉ። አብዛኛውን የግብጽ አገር አፈራረሱ፤ ገንዘቡን ዘረፉ፤ ሕፃናትንና ሴቶችን ማረኩ፤ የገደሉትም ሰው ብዛት ስምንት መቶ አርባ ሺህ ደረሰ። እኩሌታውን በሰይፍ፥ ሌላውን ደግሞ በእስር



ቤትና በረሀብ ፈጁት። ከዚያም ወደ እስክንድርያ ሄደው ፓትርያርኩን ይዘው ወደ እስር ቤት አስገቡት። ምእመናንም መሪያቸው መታሰሩን በሰሙ ጊዜ በእስር ቤቱ በር ላይ ተሰባሰቡ። ፍላጎታቸውም ፓትርያርኩን በኃይል ለማስለቀቅ ነበር። ፓትርያርኩን ለመግደል የተላከው ባለ ሥልጣን ትእዛዙን ተግባራዊ ለማድረግ ለሚቀጥለው ቀን ማስተላለፍ አሰጋው። ፓትርያርኩ ይህን ባየ ጊዜ ስለ ሕዝቡ ሕይወቱን ለመስጠት ፈለገ። በእርሱ ምክንያት ሁከት ከመነሣቱ በፊት ከጌታ ጋር ለመኖር እንዲሄድ ተመኘ። ልጆቹን አስጠርቶ በቀጥተኛው እምነት ጸንተው እንዲኖሩ ዐደራ በማለት አጽናናቸው።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ጽርፈትን የተዳፈረው አርዮስ ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳወገዘው ወደ ጌታ የሚሄድ መሆኑን በማወቁ በትላልቅ ካህናት አማላጅነት ከውግዘቱ ይፈታው ዘንድ ለምኖት እሺ አላለውም። አማላጅ ሆነው ለመጡት ሰዎችም እንዲህ ብሎ ነግሮአቸዋል። ዛሬ ሌሊት ጌታችን ኢየሱስ በራእይ ተገልጦአለት የተቀደደ ነጭ ልብስ ለብሶ ባየው ጊዜ ጌታ ሆይ፥ ልብስህን ማን ቀደብህ ብሎ ቢጠይቀው ከአባቴ ስለለየኝ ልብሴን የቀደደብኝ አርዮስ ነውና እንዳትቀበለው ተጠንቀቅ ብሎኛል አላቸው።

ከዚህ በኋላ ፓትርያርኩ ቅዱስ ጴጥሮስ የንጉሡን የጦር መሪ በምሥጢር አስጠርቶ ክርስቲያኖች በሌሉበት በኩል ያለውን የእስር ቤቱን ግድግዳ እንዲቀድድ አመለከተው። በድፍረቱ ተገርሞ እንዳዘዘው በማድረግ ከእስር ቤቱ በምሥጢር አወጣውና ቅዱስ ማርቆስ ወደተቀበረበት የከተማው ጀርባ ወደሆነ ቦታ አመጣው። እዚያም በጉልበቱ ተንበርክኮ እንዲህ በማለት ወደ እግዚአብሔር ጸለየ:- «በደሜ የጣዖት አምልኮና የክርስቲያኖች ደም መፍሰስ ፍጻሜ ይሁን»። ከሰማይም «አሜን አንተ እንደ ፈለግከው ይሁንልህ» የሚለውን ድምፅ አንዲት በቅርብ ቦታ የነበረች ቅድስት የሆነች ድንግል ሰማችው። ጸሎቱንም እንደፈጸመ ባለሰይፉ መጥቶ አንገቱን ሰየፈው። በድኑም ሕዝቡ ከከተማው እስኪወጣ ድረስ በነበረበት ቦታ ቈየ። ሕዝቡ ሁናቴውን ገና አላወቀም ነበር። አስከሬኑን ወስደው የክብር ልብሱን በማልበስ በማርቆስ መንበር ላይ አስቀመጡት። በዚያ መንበር ላይ የጌታችን ኀይል ተቀምጦበት ያይ ስለነበረ በዚያ ላይ መቀመጥ አልደፍርም በማለት በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ተቀምጦበት አያውቅም ነበር። ከዚያም የቅዱሳን ዐፅም በነበረበት ቦታ አኖሩት። በፓትርያርክነት መንበር ላይ የኖረበት ዘመን ዐሥራ አንድ ዓመት ነው (የኅዳር: 29 ቀን ስንክሳርን ይመለከቷል)።

<u>ሐዋርያዊው ቅዱስ አትናቴዎስ</u>:- ቤተ ክርስቲያን ለቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ የሚል ቅጽል ስም የሰጠችበት ምክንያት የክርስትና መሠረተ እምነት ዕውቀቱ እንደ ሐዋርያት ጥልቀት ያለው ስለነበረ፥ ለክርስቲያን ሃይማኖት ስላደረገው የመከላከያ ትግል፥ ለክርስትናው ሃይማኖት ሲል የደረሱበትና የታገሣቸው ሥቃዮች የሚያበሩ ኮከብ አድርገው ስላስገመቱት ነው። ይህም አባባል በእስክንድርያ መንበር ብቻ ሳይሆን በክርስቲያኑ ዓለም በመላ የታወቀለት ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ይህ አባት ኢ.አማንያን ከነበሩ ወላጆች በ296 ዓ.ም ተወለደ።

አትናቴዎስ ገና ልጅ በነበረበት አንድ ጊዜ ክርስቲያኖች የሆኑ ልጆች ተሰብስበው አንዳቸው ጳጳስ፥ ሌሎቹ ቀሳውስትና፥ ሌሎቹ ደግሞ ዲያቆናት ሆነው ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በቲአትር መልክ ሲያካሄዱ አይቶ እኔንም ከእናንተ ጋር አሳትፉኝ ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱ ግን አንተ ክርስቲያን ስላልሆንክ ከእኛ ጋር አብረህ ልትሆን አትችልም አሉት። እርሱም እኔ ከአሁን ጀምሮ ክርስቲያን ነኝ ቢላቸው በደስታ ተቀብለውት ለእርሱ የፓትርያርክነቱን ማዕረግ በመስጠት ከፍ ባለ ቦታ አስቀመጡት። ከዚያም በኋላ አክብሮት አቀረቡለት። በዚህ ጊዜ ፓትርያርኩ እለስክንድሮስ በዚህ ልጆቹ በሚጫወቱበት ቦታ ሲያልፍ ስለነበረ አያቸው የሚለው አንድ ታሪክ ነው፤ በቤቱ ሆኖ በመስኮት በኩል አያቸው የሚለው ደግሞ ሌላ ታሪክ ነው። ፓትርያኩም የሚጫወቱትን ልጆች ሁናቴ አይቶ አብረውት ለነበሩ ሰዎች ስለ አትናቴዎስ ይህ ልጅ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንደሚደርስ እርግጠኛ ነኝ ብሎ ነገራቸው።

አትናቴዎስ ገና በትንሽ ልጅነቱ አባቱ ሞቶበት ስለነበረ ያሳደገችው እናቱ ነበረች። እርሱም አብሮ የሚጫወተውና ግንኙነት የነበረው ከክርስቲያኖች ልጆች ጋር ነበር። ከእነዚህም ክርስቲያኖች ልጆች ጋር ወደ ፓትርያርኩ ወደ እለስክንድሮስ ይመላለስ ነበር። ይህም ሁናቴ የክርስትናን መሠረታዊ እምነት ለማጥናት አስችሎታል። የእርሱም ፍላጎት የድንግልና ኑሮ ነበር።

ዕድሜው ለጋብቻ መድረሱን ባየች ጊዜ እናቱ ልትድረው ፈለገች፤ ያላት ልጅም እርሱ ብቻ ነበር። እርሱ ግን የጋብቻን ችግር ካብራራላት በኋላ ቀስ በቀስ የክርስትናን ሃይማኖት ትክክለኛነት ይገልጽላት ጀመር። እናትዮዋም ከልጅዋ ከአትናቴዎስ ጋር ወደ ፓትርያርኩ መጥተው አጠመቃቸው። ለአትናቴዎስም በፓትርያርኩ መኖሪያ ቤት እንዲኖር ፈቀደለት። ከዚያም በመንፈሳዊ ትምህርት ቤት እየተማረ እንዲያድግ አደረገው። በዕውቀቱ በጣም እያደገ ሄዶ ገና ከተማሪነቱ በኢ.አማንያን ላይ በ318 ዓ.ም ያቀረበው ጽሑፍ የጥልቀቱና የምክንያታዊነቱ ኀይል ከፍ ያለ ነበር።

ለተወሰነ ጊዜ ከቅዱስ እንጦንስ ጋር በመኖር የብሕትውናንና የአምልኮ ሕይወትን አጥንቶአል። ከቅዱስ እንጦንስ ቦታ በተመለሰ ጊዜ ፓትርያርኩ እለስክንድሮስ በጣም ተደስቶ በ319 ዓ.ም የዲቁናን ማዕረግ ሰጠው። ከዚያም ሊቀ ዲያቆን አደረገው። ከዚያም የራሱ ረዳት አደረገው። ረዳትነቱም በበለጠ ስለ አርዮስ ችግር ነበር። በአርዮስ ምክንያት የኒቅያ ጉባኤ በተሰበሰበ ጊዜ ፓርትያርኩ እለስክንድሮስ አትናቴዎስን አስከትሎት ሄደ። በዚያ ጉባኤ ላይ አትናቴዎስ ይሰጠው የነበረው መልስ ከፍተኛ ግምት የተሰጠው ነው። ሶቅራጥስ የተባለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ እንደመዘገበው በኒቅያ ጉባኤ ላይ ያሳየው የአትናቴዎስ አንደበተ ርቱዕነት በሕይወቱ ያጋጠሙትን ችግሮች አድርሰውበታል ብሏል።

በ329 ዓ.ም ፓትርያርኩ እለስክንድሮስ አትናቴዎስ በእርሱ ቦታ ለመተካት እንዲመረጥ ተናዘዘ። አትናቴዎስ ግን ይህን በሰማ ጊዜ ለቦታው ብቁ

www.ethiopianorthodox.org



አይደለሁም በሚል የትሕትና አስተሳሰብ ወደ ተራራ ላይ ወጥቶ ተደበቀ። ሕዝቡ ግን ፍለጋውን ቀጥሎ ባገኘው ጊዜ አምጥቶ እንዲሾም አደረገው።

አትናቴዎስ የፓትርያርክነቱን ሥልጣን ከተረከበ በኋላ ሶርያዊውን ፍሬምናጦስን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ እንዲሆን ሾሞታል።

አትናቴዎስም ከአርዮሳውያን ጋር ባደረገው ተጋድሎ ምክንያት ለአምስት ጊዜ ከመንበሩ ተነሥቶ ወደ ግዞት ተባርሮአል።



ሐዋርያዊው አትናቴዎስ

<u>የመጀመሪያው ግዞት</u>:- አርዮስ በደጋፊዎቹ አማካይነት ወደ እስክንድርያ ለመመለስ ፈልጎ ተጸጽቶ በንስሓ የተመለሰ በማስመሰል ለንጉሥ ቈስጠንጢኖስ ደብዳቤ አቀረበ። ንጉሡም እውነት መስሎት አርዮስ ከግዞት እንዲፈታ፥ ከእርሱም ጋር አብረው የተጋዙት ደጋፊዎቹ እንዲፈቱ ትእዛዝ አስተላለፈ። ንጉሡም አርዮስን እንዲቀበለው ትእዛዝ ለአትናቴዎስ ቢልክለት የዓለም ዐቀፉን ጉባኤ ውሳኔ አልሽርም ብሎ ምክንያቱን ዘርዝሮ በማስረዳት የንጉሡን ትእዛዝ አልቀበልም አለ።

በዚህ ጊዜ አርዮሳውያን በዚህ ዕድል በመጠቀም ከንጉሡ ጋር ሊያጣሉት ጥረታቸውን ቀጠሉ። ከዚያም አራት የሐሰት ክሶችን መሠረቱበት፤ ክሶቹም የሚከተሉት ናቸው:-

1. የመንግሥት ተቃዋሚዎችን ይረዳል ብለው

2. የቄስ አስኪራን ጽዋ ሰብሮ መንበሩን አስገልብጦአል ብለው:-

3. ኤጲስ ቆጶስ አርሳንዮስን ገድሎ እጁን ከቈረጠው በኋላ ለጥንቈላ ይጠቀምበታል በሚል፥

4. እንዲቷን መነኮሲት አስገድዶ አስነውሮአታል በማለት ያቀረቡበትን በጢሮስ ከተማ ሲኖዶስ ተበስብቦ እንዲያየው ንጉሡ አዘዘ። ይህም አርዮሳውያን የበዙበት ጉባኤ ተሰብስቦ በአትናቴዎስ ላይ የቀረበውን ክስ አንድ በአንድ ተመለከተ።

ስለ ቄስ አስኪራ መደብደብ ጉዳይ የቀረበው ክስ ሐሰት መሆኑን ቄስ አስኪራ ራሱ ኅሊናው አስገድዶት ሐሰት መሆኑን መሰከረ።

አርሳንዮስ ኅሊናው ስለወቀሰው በጉባኤው ፊት በመገኘት እጁ አለመቈረጡንና አለመገደሉን መሰከረ።

ተደፍራለች የተባለችው ሴት የአትናቴዎስን ማንነት አታውቅም ነበር። ከፓትርያርክ አትናቴዎስ ጋር ከነበሩት መካከል ቀሲስ ጢሞቴዎስ ተነሥቶ አንቺ እንዴት አድርገሽ ነው እኔ እንደደፈርኩሽ አድርገሽ ደፍረሽ የምትናገሪው ቢላት አዎን አንተ ራስህ ነህ የደፈርከኝ ብላ በመናገርዋ ውሸትነቱ ተረጋገጠ። ይሁን እንጂ በአርዮሳውያን መከላከል ምክንያት አትናቴዎስ ንጉሡን ለመገናኘት አልቻለም። እንዲያውም በፈረንሳይ አገር ወደምትገኘው ወደ ትሬቭ ደሴት እንዲጋዝ ንጉሡ ወሰነበት።

ንጉሡ የአርዮስን አሟሟት በሰማ ጊዜ አትናቴዎስ ንጹሕ መሆኑን ዐውቆ ከግዞቱ እንዲመለስ ወሰነ።

<u>ሁለተኛው ግዞት</u>:- አርዮሳውያን ምንም እንኳ በሐሰት ክሳቸው ባይሳካላቸው ተንኰላቸውን ቀጠሉ እንጂ አላቆሙም። አርዮሳዊ በነበረው በቈስጠንጢዮስና በግብጹ ገገር እርዳታ አትናቴዎስን እንደገና ከመንበሩ አስነሥተው አርዮሳዊውን ጎርጎርዮስን ለመሾም ተነሣሡ። አትናቴዎስም የአርዮሳውያንን ተንኰል በማጋለጥ ለዓለም አብያተ ክርስቲያን ሁሉ በጽሑፍ አስተላለፈ። በስቅለት በዓል ቀን አርዮሰውያን የግብጽን አብያተ ክርስቲያን በመውረር በጸሎት ላይ የነበረውን ሕዝብ ፈጁ፤ ብዙ ደናግልን አስነወሩ። በዚህ ጊዜ አትናቴዎስ ተነሥቶ ወደ ሮም ሄደ። እዚያም ሲኖዶስ ተሰብስቦ የአትናቴዎስንና የኒቅያ ጉባኤን ውሳኔ ትክክለኛነት አጸደቀ። በዚህም የግብጽ ክርስቲያኖች በአርዮሳውያን ላይ በመነሣት ጎርጎርዮስ የተባለ ፓትርያርካቸውን በ349 ዓ.ም ገደሉባቸው። ይህም ሁናቴ ለአትናቴዎስ ወደ መንበሩ መመለስ ምክንያት ሆነ።

<u>ሦስተኛው ግዞት</u>:- የኢጣልያው ገገር ቆስጣስ ከሞተ በኋላ አርዮሳውያን ቈስጠንጢዮስን በማሳመን የአርዮሳውያን ስብሰባ ተደርጎ አትናቴዎስ እንዲጋበዝ ተወሰነ። በግድ አትናቴዎስን ለመያዝ ወታደሮች ወደሚጸልይበት ቤተ ክርስቲያን ገቡ። እግዚአብሔር ግን ዐይናቸውን ስለሸፈነ ሰው ሊለዩ አልቻሉም። በዚህም ላይ መብራቶቹ ሁሉ ስለጠፉ አትናቴዎስ ወደ ምድረ በዳ በመሄድ ከአባቶች መነኰሳት ጋር ለተወሰነ ጊዜ ቈየ። አርዮሳውያንም ጊዮርጊስ የተባለውን ቀጳጶቂያዊ ፓትርያርክ አድርገው ሾሙት ይህም ሰው የቤተ ክርስቲያንን ንብረት ሁሉ በመዘረፍ ክርስቲያኖችን በወታደሮች በማስፈጀት፥

www.ethiopianorthodox.org



ዐሥራ ሁለት ኤጲስ ቆጶሳትን በማሰር ብዙ ግፍ ፈጽሞአል። ነገር ግን ኢአማንያን ተነሥተው ስለገደሉት ብዙ ጊዜ አልቈየም።

<u>ወደ መንበሩ መመለሱና ለአራተኛ ጊዜ ከመንበሩ መታገዱ</u>:- ቈስጠንጢዮስ ሞቶ በቦታው ዩልያኖስ ሲተካ እስረኞች ሁሉ እንዲፈቱ ስላዘዘ አትናቴዎስም ከተፈቱት መካከል ነበር። አሁን እንግዲህ አትናቴዎስ ወደ መንበሩ ተመልሶ ከአርዮሳዊነት ወደ ትክክለኛው የክርስትና እምነት ለሚመለሱ አርዮሳውያን ግዴታዎችን ያዘጋጅና በኢአማንያን ዘንድ የክርስትናን ትምህርት ያስፋፋ ጀመር። ዩልያኖስ ግን ኢአማኒነትን ይወድድ ስለነበረ የአትናቴዎስ ሥራ አላስደሰተውም። በዚህም ምክንያት አትናቴዎስ እንዲያዝ ትእዛዝ አስተላለፈ። አትናቴዋስም በመርከብ ተሳፍሮ ወደ ላዕላይ ግብጽ ሄደ። አገረ ገገርው ቢከተለውም አትናቴዎስ ስለተደበቀ ሊያገኘው አልቻለም። ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎች መሳደዱ የበዛበት መሆኑን ባዩ ጊዜ የሐዘን ስሜታቸውን ገለጡለት። እርሱ ግን በስደት ጊዜ ጸጋ ስለሚበዛልኝ በውስጤ ሰላም ይሰማኛል አላቸው። የዩልያኖስ ማሳደድ እንደ በጋ ደመና ነውና ቶሎ ይጠፋል አለ። ይህን ሲናገሩ ሳለ ዩልያኖስ በፋርስ ጦርነት ሞተ ተብሎ ወሬ መጣላቸው። የተገደለውም:- ቅዱስ ባስልዮስና ቅዱስ ጎርጎርዮስ በቅዱስ መርቆርዮስ ሥዕል ፊት በጸለዩ ጊዜ ካልታወቀ አቀጣጫ በተወረወረ ፍላጻ ነው። ከሰውነቱ ደም እየፈሰሰ ሳለ የማርያም ልጅ ሆይ፥ አሸነፍከኝ? ይል ነበር።

<u>ለአራተኛ ጊዜ መመለሱና ለአምስተኛ ጊዜ ከመንበሩ መራቁ</u>:- ዩልያኖስ ከሞተ በኋላ ዮብያኖስ መንግሥቱን ሲወርስ የሃይማኖት ነጻነትን ዐወጀ። በአትናቴዎስ ላይ የተላፈውም ትእዛዝ እንዲሻር ወሰነ። እንዲሁም ብርታትና ጽናቱን በማመስገን መልእክት ላከለት። ከዚያም ቀጥተኛዋን እምነትና የኒቅያ ጉባኤ ውሰኔዎችን እንዲልክለት ጠይቆት ልኮለታል። ይሁን እንጂ ዮብያኖስ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሞቶ አርዮሳዊ የነበረው ቫሌንስ መንግሥቱን ወረሰ። እርሱ በ367 ዓ.ም አትናቴዎስ ወደ ግዞት እንዲሄድ ትእዛዝ አስተላለፈ። በዚህ ጊዜ አትናቴዎስ ከእስክንድርያ ወጥቶ በአባቱ መቃብር መደበቅ ግድ ሆነበት። እዚያም አራት ወር ተቀመጠ። በእነዚህም ጊዜዎች ቤተ ክርስቲያን ሁለት ነገሮች አጋጠሙአት። ንጉሡ የአናቴዎስ ደጋፊዎች የነበሩትን ሠላሳ ጳጳሳት ገደለ። እስር ቤቶችን በክርስቲያን እስረኞች ከመሙላቱም በላይ ንብረታቸው እንዲዘረፍ አደረገ። ከዚህ በኋላ ግን ክርስቲያኖች በሃይማኖታቸው ላይ ያላቸውን ጽናትና ወደ አርዮሳውያን ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ለመጸለይ እምቢተኞች መሆናቸውን ባየ ጊዜ ሁከት ይነሣ ይሆናል ብሎ በመፍራት ማሳደዱን አቁሞ በ368 ዓ.ም አትናቴዎስን ወደ መንበሩ መለሰው።

በዚህ ጊዜ የአትናቴዎስ ዕድሜ ሰባ ሁለት ዓመት ቢሆንም እንኳ ሽምግልናውና የደረሰበት መሳደድ ከግዴታው ሊገቱት አልቻሉም። ቤተ ክርስቲያኖችን አሠራ፤ ሌላም፥ ሌላም።

በ373 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ (የግንቦት 7 ቀን ስንክሳርን ይመልከቱ)።

<u>ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ</u>:- ይህ ቅዱስ፥ አፈወርቅ የሚል ቅጽል የተሰጠው ከአንደበቱ ይወጣ ለነበረው መልካም ምክር መታሰቢያ ነው። የተወለደው በ347 ዓ.ም አካባቢ ሰክሎንዶስ ከተባለ ከአንድ ባለጸጋ አባትና አንቶሳ ከተባለች መንፈሳዊት እናት ነው። ወላጆቹ መልካም ክርስቲያናዊ አስተዳደግ አሳድገውታል። ወደ አቴና ከተማ ሄዶ ትምህርት ቤት በመግባት የግሪኮችን ጥበብ ተምሮአል። በትምህርቱና በበጎ ተግባሩ ከብዙዎች እጅግ የላቀ ነበር። የዚህንም ዓለም ከንቱነት ንቆ ገና በልጅነቱ ወደ አንድ ገዳም በመግባት መነኰሰ። በዚያም እርሱ በገባበት ገዳም ቀደም ብሎ የመነኰሰ ባስልዮስ የተባለ ጓደኛ ነበረው። ዝንባሌአቸው ተመሳሳይ በመሆኑ በአንድነት ሆነው ብዙ የትሩፋት ሥራ ይሠሩ ነበር። አባቱ በሞተ ጊዜ ከወረሰው ውርስ ምንም ሳያስ ተርፍ ለድኾች ዐደለው። ከዚያም የብሕትውናና የተጋድሎ መንገዱን በሰፊው ቀጠለ በዚያ ገዳም አንሶሲኖስ የተባለ የሶርያ እስረኛ ባሪያ ነበር። ይህ ሰው በአንድ ሌሊት ሐዋርያቱ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ ወደ ዮሐንስ አፈወርቅ ሲገቡ ያያል። እንዲሁም ሐዋርያው ዮሐንስ ወንጌል ሲሰጠውና አይዞህ አትፍራ የአሰርከው የታሰረ የፈታኸው የተፈታ ይሆናል ሲለው ይሰ ማል። ይህም ሽማግሌ እስረኛ ዮሐንስ አፈወርቅ ታማኝ እረኛ እንደሚሆን ዐወቀ።

የእግዚአብሔርም ጸጋ በእርሱ ላይ ስለወረደ ገና ዲያቆን ሳለ የስብከት መጻሕፍት ጽፎአል፤ የብዙ መጻሕፍትም ትርጓሜ አዘጋጅቷል። በዚያም ገዳም ውስጥ ለአራት ዓመት ኖረ። ይህም ሆኖ ለነፍሱ እርካታን አልሰጠውም። በዋሻ ውስጥ የብቸኝነትን ኑሮ መኖር ጀምሮ በዚያን ጊዜ በቂ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን በማጥናት ጊዜውን ያሳልፍ ነበር። የዋሻው ኑሮ ግን ጤንነቱን ስላቃወ ሰበት ዋሻውን ትቶ ወደ አንጾኪያ ከተማ መሄድ ግድ ሆነበት። ጤንነቱ መለስ ሲልለት መስበክ ጀመረ። በ381 ዓ.ም የአንጾኪያው ኤጲስ ቆጶስ መላትዮስ የዲቁና ማዕረግ ሰጠው። አብሮት የነበረው ጓደኛው ለኤጲስ ቆጶስነት ሹመት ሐሳብ ቀርቦለት ሐሳቡን ተቀበለው። ይህን ሲያደርግ ዮሐን ስም እንደዚህ ያለ ሐሳብ ቢቀርብለት እንደሚቀበለው ይተማመን ነበር። እውነታው ግን እንደዚህ አልነበረም። አንዳንድ ኤጲስ ቆጶሳት የዮሐንስን ስም ለኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ አቅርበውት ተደብቆ ጠፍቶባቸዋል። በዚህም ምክንያት አዲሱ ኤጲስ ቆጶስ በጣም ተቈጣ። ዮሐንስ ግን ለኤጲስ ቆጶሱ በላከው መልእክት ኤጲስ ቆጶስነቱን የሸሸው ማዕረጉን ንቆ ሳይሆን ለዚያ ደረጃ ብቁ ባለመሆኑ እንደሆነ ገለጠለት። መልእክቱ ያዘለው ሌላ ጉዳይ ደግሞ ስለ ክህነት ክብርና የካህናትን ግዴታዎች የሚዘረዝር ነበር። ከዚያ በኋላ የኤጲስ ቆጶሱ ቍጣ በረደ።

በ386 ዓ.ም የአንጾኪያው ኤጲስ ቆጶስ በእግዚአብሔር መልአክ መሪነት ዮሐንስን ወደ ቅስና ማዕረግ ከፍ አደረገው። በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ መስ በክ ጀምሮ ዝነኛ ሆነ። ነክታርዮስ በመሞቱ ምክንያት የቍስጥንጥንያ መንበር ባዶ በሆነ ጊዜ ንጉሥ ነገሥቱ አርቃድዮስ ዮሐንስ አፈወርቅ የቍስጥንጥንያን መንበር እንዲረከብ እንዲያስገድደው ለአንጾኪያው ፓትርያርክ መልእክት ላከበት። የአንጾኪያ ሕዝብ ሐሳቡን በ[illegible]

www.ethiopianorthodox.org



በላከው ምሥጢራዊ መልእክት በዘዴ ከከተማ እንዲወጣ ካደረገው በኋላ ወደ ቍስጥንጥንያ እንዲላክ አዘዘው። በዚህ ዘዴ ነው ንጉሥ ነገሥቱ ዮሐንስ አፈወ ርቅን በ397 ዓ.ም የቍስጥንጥንያ ፓትርያርክ ሊያደርገው የቻለው።

<u>ዮሐንስ አፈወርቀ ከንጉሡ ሚስት ከአውዶክስያ ጋር ያደረገው ትግል</u>:- ዮሐንስ ሰዎችን በበጎ ተግባር እንዲኖሩ ይገፋፋ ነበር። ንግሥቲቱንም ቀጥለው በተዘረዘሩት ጉዳዮች ይወቅሳትና ይገሥጻት ነበር።

1. የአርሻ መሬትዋን የነጠቀቻት አንዲት መበለት ለዮሐንስ አፈወርቅ ችግርዋን አዋየችው። እርሱም የመበለቲቱን መሬት እንድትመልስ ለንግሥቲቱ ነገራት። እርስዋ ግን እምቢ አለች። አማላጅም ቢልክባት እሺ አላለችም። ከዚያ በኋላ የስቅለት በዓል ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመግባት ሊከለክላት አሰበ። ስትመጣም ባያት ጊዜ እርሱ ራሱ ወጥቶ ከለከላት። ከጠባቂዎችዋ አንዱ ዮሐንስ አፈወርቅን ሊገድል ሳይፋን ሲመዝዝ እጁ ደርቆ ቀረ። ንግሥቲቱ በንዴት እየጋለች ተመለሰች። ዮሐንስንም ለመበቀል ፈለገች።

2. የእስክንድርያው ገዢ ከአንዲት መበለት ላይ የነጠቀውን አምስት መቶ ዲናር ወሰደች። ይህንንም ያደረገችው መበለቲቱ አገረ ገዢውን በንግሥቲቱ ላይ በከሰሰችው ጊዜ ከእርሱ ላይ አምስት መቶውን ዲናር ወስዳ ለመበለቲቱ ሠላሳ ስድስት ዲናር ብቻ ሰጥታ ቀሪውን ለራስዋ በማስቀረት ነው። መበለቲቱ አገረ ገዢው ገንዘቧን እንዲመልስላት በዮሐንስ አፈወርቅ ላይ ከሰሰችው። እርሱም ስላልከፈላት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አሰረው። ንግሥቲቱ አገረ ገዢውን ለማስለቀቅ ጥቂት ወታደሮች ብትልክ የእግዚአበሔር ኀይል ስለመ ለሳቸው ሊያስለቅቁት አልቻሉም። የሆነውንም ሁናቴ ባወቀች ጊዜ ገንዘቡን ለመበለቲቱ መለሰችላት።

3. በአጊያ ሶፊያ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ የንግሥቲቱ ሐውልት ነበረ። በሐውልቱም ፊት ለፊት ሕዝቡ ግብረ ገብነት የጐደለው ጨዋታ ይጫወት ነበር። ዮሐንስ በመደጋገም ሕዝቡን ገሠጸ። ወቀሳውና ግሣጼው የማይጠቅም ሆኖ ባገኘው ጊዜ ሐውልቱ ከዚያ ቦታ እንዲነሣ ጠየቀ። ይህ ጥያቄው እርስዋን እንደማዋረድ ቈጥራው ለመበቀል በጣም አሰበችበት። ዮሐንስ ግን ጉዳዩ ምንም ስላሳሳሰበው ሄሮድያዳ ወንጀል ትሠራለች፤ ትጨፍራለች፤ የዮሐ ንስንም ራስ በሳሕን እንዲሰጣት ትጠይቃለች ብሎ በበዓላት ስብከቱ በንግ ሥቲቱ ላይ ወቀሳውን ቀጠለ።

በግብጹ ቴዎፍሎስና በዮሐንስ መካከል አለመግባባት ነበር። ይህም የሆነው ቴዎፍሎስ ያወገዛቸውን ግብጻውያን መነኰሳት ዮሐንስ ተቀብሎአቸው ስለነ በረ ነው። በዚህ ዕድል በመጠቀም ንግሥቲቱ ቴዎፍሎስንና ሌሎች ኤጲስ ቆጶሳትን በማግባባት ዮሐንስን እንዲያወግዙ አድርጋቸዋለች። ስለዚህ በ403 ዓ.ም በእርሱ ላይ የውግዘት ፍርድ ተላለፈ። ከዚያ በኋላ የንግሥቲቱ ተከታዮች በሌሊት ወደ ግዞት ወሰዱት። በሌሊት የወሰዱትም በቀን የወሰዱት እንደሆነ የሕዝብ ተቃውሞ ይነሣ ይሆናል ብለው ስለፈሩ ነው። ከቍስጥንጥንያ ሲወጣ

ሪመሬት መንቀጥቀጥ ሆነ። ንግሥቲቱም ስለፈራች ወደ ነበረበት ለመመለስ ተገደደች።

የሐውልቱ ጉዳይ ግን ከሁለት ወር በኋላ እንደገና አገርሽቶበት ንግሥቲቱ ከጥቍር ባሕር በስተጀርባ ወደሚገኘው ወደ ቀውቃዝ ተራራ ልታግዘው ወሰነች። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በዚያ ቦታ መገኘቱን ዕድል በመጠቀም ለኢአማንያን ወንጌልን ያስተምር ጀመር። ወታደሮቹ በሞቃት ጊዜ በባዶ እግሩ እንዲሄድ በማድረግ አሠቃዩት። ከዚያ በኋላ ከባድ ንዳድ ያዘውና በቅርብ ወደ ነበረው ወደ ቅዱስ ባስልዮስ ገዳም ወሰዱት ቅዱስ ቍርባንን ተቀብሎም ነፍሱን ሰጠ። ከመሞቱ በፊት በተለመደ አነጋገሩ በሁሉም ነገር ጌታ የተባረከ ይሁን» አለ። ይህም የሆነው በ407 ዓ.ም ነው።

በትንሹ ቴዎዶስዮስ ዘመን ዐፅሙ በታላቅ ክብር ተወስዶ በቍስጥንጥንያ ተቀበረ (የኅዳር 17 ቀን ስንክሳር ይመለከቷል)።

<u>የኢሩሳሌም ኤጲ.ስቆጶስ አባ ዮሐንስ</u>:- ዮሐንስ ገና በሕፃንነቱ ከቆጵሮሱ ኤጲስ ቆጶስ ከቅዱስ ኤጲ.ፋንዮስ ጋር በታላቁ በአባ ኤላርዮን ገዳም መነኰሰ። በምንኵስናም ሕይወት ጸንቶ ታላቅ ተጋድሎ ተጋደለ፤ እግዚአብሔርንም አገለገለ፤ የዕውቀቱና የትሩፋቱ ዜናም በሁሉ ተሰማ። ስለዚህም በኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ተሾመ። እርሱ በኢየሩስሌም ተሹሞ ሳለ ቅዱስ ኤጲ.ፋንዮስ በቆጵሮስ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ተሹሞ ነበር።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሰይጣን በፍቅረ ንዋይ አሳተውና አባ ዮሐንስ ብዙ ገንዘብ አከማቸ። ገንዘብ ከመውደዱ የተነሣም ለድኾች ቁራሽ እንጀራ እንኳ አይሰጥም ነበር፤ የማዕድ ዕቃዎቹን ሁሉ ከብር አሠራና በእነርሱ ይመገብ ጀመር።

ጓደኛው የቆጵሮሱ ኤጲ.ስቆጶስ ኤጲ.ፋንዮስ ይህን በሰማ ጊዜ አባ ዮሐንስ በመንፈስ ቅዱስ ወንድሙ ስለነበረ የቀድሞ ፍቅሩንና ተጋድሎውን፥ ምናኔውንና ለድኾች የሚያደርገውን ምጽዋት ሁሉ እያሰበ እጅግ አዘነለት። ከስሕተቱም ሊመልሰው ፈልጎ ከቆጵሮስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። ከሄደም በኋላ አባ ዮሐንስን ከስሕተቱ በስውር ሊያድነው ስለ ወደደ ወደ ኢሩሳሌም ለስግደት እንደ ሄደ አድርጎ ለሰዎች ይናገር ነበር። አባ ዮሐንስም የኤጲ.ፋንዮስን ወደ ኢየሩሳሌም መምጣት በሰማ ጊዜ ወደ ቤቱ ጠራውና ከብር በተሠሩ ዕቃዎች ማዕድ አቀረበለት። ኤጲ.ፋንዮስም አባ ዮሐንስ ለድኾች ምንም ዐይነት ርኅራኄ እንደሌለው ተመለከተና በጣም አዘነ። ከእርሱም ተለይቶ ከወጣ በኋላ በምን መንገድ አባ ዮሐንስን ከስሕተቱ እንደሚመልሰው ያስብ ጀመረ። በኋላም በኢየሩሳሌም ከሚገኙት ገዳማት በአንዱ ገዳም ተቀምጦ የሚከተለውን መልእክት ለአባ ዮሐንስ ላከበት። «... ከቆጵሮስ ታላላቅ የሕዝብ ሽማግሌዎች በእንግድነት ወደ እኔ ስለ መጡ ለእነርሱ ምግብ ማቅረቢያ ከብር የተሠሩ የማዕድ ዕቃዎችህን ላክልኝ፥ ይህንም በማድረግ እባክህ አክብረኝ።»

አባ ዮሐንስም የተባሉትን የብር ዕቃዎች ሁሉ ለቅዱስ ኤጲ.ፋንዮስ ላከለት። ቅዱስ ኤጲ.ፋንዮስም እነዚያን ዕቃዎች ሁሉ ሸጠና ገንዘቡን ለነዳያን መጸወተው። ከጥቂት ጊዜ በኋላም አባ ዮሐንስ ከብር የተሠሩ የማዕድ ዕቃዎቹን



www.ethiopianorthodox.org

እንዲመልስለት ደጋግሞ ቢጠይቀው ቅ/ኤጲ.ፋንዮስ የማይሰጠው ሆነ። ስለዚህም ከዕለታት በአንድ ቀን አባ ዮሐንስ የጌታችን የትንሣኤው መታሰቢያ ወደ ሆነው ቤተ ክርስቲያን ሄደ፤ በዚያም ቅዱስ ኤጲ.ፋንዮስን አገኘውና የልብሱን ጫፍ ይዞ «ከብር የተሠሩ ዕቃዎቼን ካልሰጠኸኝ በምንም አልለቅህም» ስላለው ቅ/ኤጲ.ፋንዮስ ጸለየ። የአባ ዮሐንስም ሁለት ዐይኖቹ ታወሩ። በዚህ ጊዜ አባ ዮሐንስ እያለቀሰ ቅ/ኤጲ.ፋንዮስን ማለደው። እርሱም ወደ ክርስቶስ ጸለየና አንዲት ዐይኑ እንድትበራለት ካደረገ በኋላ «ነፍስህን እንድታስብ ጌታ አንዲት ዐይንህን አበራልህ፤ ከእንግዲህ ወዲህ የቀደመ ገድልህን አስብ፤ ብር ዕቃዎ ችህን ግን ሸጬ ገንዘቡን ለድኾች ምጽዋት ሰጥቻቸዋለሁ። የእኔም ወደ ኢየሩሳሌም መምጣት ስለዚህ ነው እንጂ ስለ ሌላ ነገር እንዳይደለ ዕወቅ» ብሎ ገሠጸው።

ያን ጊዜ አባ ዮሐንስ ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው ነቅቶ ለኤጲ.ስቆጶስነቱ የማይገባ፥ በስሕተት የፈጸመውን ተግባር ሁሉ አስታውሶ ገንዘቡን ሁሉ፥ ልብሱን ሳይቀር ሸጦ ለድኾች ሰጠ፤ በሞተ ጊዜ በቤቱ ውስጥ አንድ ሣንቲም እንኳ እስከማይገኝ ድረስ በቤቱ ያለውን ንብረት ሁሉ ለድኾች መጸወተ።

እግዚአብሔርም የፈውስ ጸጋን ሰጠው፤ ብዙዎች ተአምራትም በእጁ ተደረጉ። አባ ዮሐንስ በመጨረሻ በዚህ ዐይነት የተቀደሰ ሕይወት ኖሮ እግዚአብሔርን አገልግሎ፥ መንፈሳዊ ገድሉን ፈጽሞ፥ ብዙ ትሩፋትንም ሠርቶ ሰኔ 13 ቀን ዐርፎአል ( የሰኔ 13 ቀን ስንክሳርን ይመለከቷል)።

«ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃል፤ ሰባት ጊዜ ይነሣል» (ምሳሌ : 24፥16) እንደተባለ ክርስቲያን እስከ ኤጲ.ስቆጶስነት መዐርግ ቢደርስም እንደአባ ዮሐንስ በሰይጣን ወጥመድ ተሰናክሎ ሊወድቅ ይችላል። ነገር ግን እንደ እነ ቅዱስ ኤጲ.ፋንዮስ ባሉ ቅዱሳን እርዳታ፥ በእግዚአብሔር ምሕረት ከውድቀቱ ሊነሣ እንደሚችል ማመን ይገባዋል።

<u>የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ቴዎዶስዮስ</u>:- በእስክንድርያ በቅዱስ ማርቆስ መንበር 33ኛ ሊቀ ጳጳሳት ነው። ይህ አባት ሊቀ ጳጳሳት ሆኖ ከተሾመ በኋላ በንጉሡ አነሣሺነት ክፉዎች ሰዎች በጠላትነት ተነሡበት። በእርሱ ፋንታም አቃቅያኖስ የተባለ አንድ የእስክንድርያ ዲያቆን ሾሙ። ይህም ዲያቆን ቴዎዶስዮስ ለሊቀ ጵጵስና እንደሚገባ በእጃቸው ከጻፉ ሰዎች አንዱ ነበረ። ቅዱስ ቴዎዶስዮስንም ግርስማኖስ ወደተባለ ቦታ አሳደዱት። በዚያም በስደት ለ3 ወራት ተቀመጠ። በዚያም ወራት በግብጽ የነበረ አባ ሳዊሮስ የሚባል መነኵሴ:- በሐዋርያት ላይ እንደዚሁም በቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ላይ የደረሰውን ስደትና መከራ እየጠቀሰ ቅዱስ ቴዎዶስዮስን ያጽናናው ነበረ።

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ቴዎዶስዮስ ከግርስማኖስ ተነሥቶ ወደ መሊግ ሄደ። በዚያም ለሁለት ዓመታት ኖረ። በዚህ ጊዜ የእስክንድርያ ሰዎች ተነሥተው ወደ ሀገረ ገዥው በመሄድ ስለ ጠባቂያቸው ተከራከሩ፤ አገረ ገዥውም ቅዱስ ቴዎዶስዮስን ወደ መንበሩ መልሶ አቃቅዮስን አባረረው። ይህም ዜና ወደ

ንጉሡ ዮስጣትያኖስና ወደ ንግሥቲቱ ታዎድራ ተሰማ። ንግሥቲቱም:- «አስቀድሞ የተሾመው በመንበሩ ይቀመጥ» ብላ መልእክት ጽፋ ላከች። በዚህ ጊዜ አንድ መቶ ሃያ ካህናት የተገኙበት ጉባኤ ተደረገና ሁሉም «በመጀመሪያ የተሾመው አባ ቴዎዶስዮስ ነው» ሲሉ ተስማምተው ጻፉ። ያን ጊዜ አቃቅዮስ በጉባኤው ፊት ተነሥቶ «እኔ፥ ክፉዎች ሰዎች ስለ ገፋፉኝ ሥርዐትን ተደፋፍሬአለሁ» አለ።

ከዚህ በኋላ ሕዝቡ አቃቅያኖስን ከግዝት እንዲፈታው አባ ቴዎዶስዮስን ለመኑት፤ ለአቃቅዮስ ግን ምንም ዐይነት ክህነት ምንጊዜም ቢሆን እንደ ማይገባው ተነገረው፤ እርሱም አዎ አለ። ንጉሡ ግን የተሳሳተ ሃማኖትን የያዘ ነበር። ሊቀ ጳጳሳቱ ቅዱስ ቴዎዶስዮስም በእርሱ የተሳሳተ ሃይማኖት የሚስማማ መስሎት በእስክንድርያ ለነበሩ መኳንንት ሁሉ:- «አባ ቴዎዶስዮስ ከእኛ ጋር በሃይማኖት የሚስማማ ከሆነ በሊቀ ጵጵስናው ላይ ሌላ ሹመት ይጨመርለታል፤ በእስክንድርያም ከተማ ገዥ ይሆናል፤ ነገር ግን ከእኛ ጋር በሃይማኖት ካልተስማማ አሁን ካለው ሹመት እንኳ ይሻራል» ሲል ደብዳቤ ጻፈላቸው። ቅዱስ ቴዎዶስዮስም ይህን በሰማ ጊዜ:- «ሰይጣን ‹ለእኔ ወድቀህ ብትሰግድልኝ የዓለምን መንግሥታትና ክብራቸውን ሁሉ እሰጥሀለሁ› ብሎ ጌታችንን እንደ ፈተነው አንተም እኔን በዚህ ዓለም ሹመት ልታታልለኝ አሰብህን? ሹመትህ ለራስህ ይሁን» ብሎ ከእስክንድርያ ወጣና ወደ ላይኛው ግብጽ ሄደ። በዚያም ምእመናንን በቀናች ሃይማኖት እያጸናቸው ለጥቂት ጊዜ ኖረ። ንጉሡም ቅዱስ ቴዎዶስዮስ ከእስክንድርያ እንደ ወጣ ሰማና ሊያታልለው ፈልጎ «ከአንተ ጋር እንድገናኝና እንድትባርከኝ፥ እንድታማክረኝም እፈልጋለሁ» ብሎ መልእክት ላከበት።

በዚህም ምክንያት ቅዱስ ቴዎዶስዮስ ወደ ንጉሡ ወደ ቊስጥንጥንያ ሄደ፤ ሊቀ ጳጳሳቱና ሕዝቡ፥ ሠራዊቱም ከፍ ያለ መንበር ዘርግተው ተቀበሉት። ቀጥሎም ስለ ቀናቸው ሃይማኖት እርስ በእርሳቸው ተወያዩ። ንጉሡም:- ቅዱስ ቴዎዶስዮስን ሊያታልለው ብዙ ጊዜ ይሞክር ነበር፤ ቅ/ቴዎዶስዮስ ግን ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከአባቶች ትምህርት እየጠቀሰ ይረታው ነበር። ከንጉሡ ጋር በሃይማኖት ባልተስማማ ጊዜ ንጉሡ ወደ ላይኛው ግብጽ እንዲሰደድ አደረገው። በእርሱም ፋንታ ጳውሎስ የተባለ አንድ ሰው ሾመ። ጳውሎስም ተሹሞ ወደ ግብጽ በሄደ ጊዜ ሕዝቡ አልተቀበሉትም፤ በዚህ ዐይነት ለአንድ ዓመት ሲቆይ ከጥቂቶች በቀር በእጁ ቅዱስ ቊርባንን የተቀበለ ማንም አልነበረም።

ንጉሡም ይህን ሁኔታ ሰምቶ ሕዝቡ ለጳውሎስ እስኪታዘዙ ድረስ አብያተ ክርስቲያናት እንዲዘጉ አዘዘ። ካህናቱና ምእመናን ግን ከእስክንድርያ ውጭ በቅዱስ ማርቆስ፥ በቆዝሞስና በድምያኖስ ስም አብያተ ክርስቲያንን አሠርተው ልጆቻቸውን ያጠምቁና ይቀድሱ ነበር። ንጉሡም ይህን ሰምቶ ያዘጋቸው አብያተ ክርስቲያን እንዲከፈቱላቸው እንደገና ትእዛዝ አስተላለፈ። ቅዱስ ቴዎዶስዮስ ግን ንጉሡ አብያተ ክርስቲያኑን ማስከፈቱ ምእመናኑን

www.ethiopianorthodox.org



ለማዘናጋትና ለማታለል መሆኑን ተገንዘቦ እጅግ ፈራ። ስለዚህም ከቀናች ሃይማኖታቸው እንዳይናወጡ የሚያጽናና መልእክት ጻፈላቸው። በመልእክቱም ውስጥ «ተጠንቀቁ፤ ለከሓዲው ንጉሥ አትታዘዙለት» የሚል ምዕዳን ይገኝበታል።

ቅዱስ ቴዎዶስዮስ ከተሾመ በኋላ በላይኛው ግብጽ በስደት 28 ዓመት፥ በእስክንድርያ 4 ዓመት ኖሮአል። ብዙ ድርሳናትንና ትምህርቶችን ጽፎአል። ከድርሳናቱም በርካታዎቹ በሃይማኖተ አበው ተጽፈዋል። የዚህን አባት ትምህርት ተቀብለው በስደቱ ጊዜ በሕገ ወጥ የተሾሙትን ሰዎች ያልተቀበሉ ምእመናን በግብጽ አገር ቴዎዶስዮሳውያን እየተባሉ በስሙ ይጠሩ ነበር። ቴዎዶስዮስ መልካም ተጋድሎውን ፈጽሞ ሰኔ 28 ቀን ዐርፎአል (ስንክሳር ሰኔ 28)።

<u>የቤተ ክርስቲያን ዜማ</u>

የሕዝብ ተሰጥዎ

## <u>በግዕዝ</u>

ይ:ዲ:- ጸልዩ በእንተ ሰላም፥ ፍጽምት ወፍቅር፥ ተአምኆ በበይናቲክሙ በአምኃ ቅድሳት።

ይ :ሕ:- ክርስቶስ አምላክነ ረስየነ ድልዋነ ከመ ንትአማኃ በበይናቲነ በአም: ቅድሳት።

ይ:ካ:- እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ።

ይ:ሕ:- ምስለ መንፈስከ፤

ይ:ካ:- አእኵትዎ ለአምላክነ

ይ:ሕ:- ርቱዕ ይደሎ፤

ይ:ካ:- አልዕሉ አልባቢክሙ።

ይ :ሕ:- ብነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ፤

ይ:ዲ:- አውሥኡ፤

ይ:ሕ:- ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉእ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ።

ይ:ሕ:- ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ፤ ተዘከረነ እግዚኦ ኦሊቅ በውስተ መንግሥትከ፤ ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ

በከመ ተዘከርኮ ለፈያታዊ ዘየማን እንዘ ሀሎከ ዲበ ዕፀ መስቀል ቅዱስ።

ይ:ሕ:- ነአምን ከመ ዝንቱ ውእቱ በአማን ነአምን።

አሜን:- አሜን፥ አሜን፥ ነአምን ወንትአምን ንሴብሐከ ኦ:እግዚእነ ወአምላክነ

ከመ ዝንቱ ውእቱ በአማን ሥጋከ ነአምን

አሜን፥ አሜን፥ አሜን ነአምን ወንትአመን ንሴብሐከ ኦእግዚእነ ወምላክነ ከመ ዝንቱ ውእቱ በአማን ደመከ ነአምን።

ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድስተ፤ ነአምን ዕርገተከ ወዳግመ ምጽአተከ ንሔብሐከ ወንትአመነከ ንስእለከ ወናስተበቍዓከ ኦእግዚእነ ወአምላክነ።

አሜን እግዚኦ መሐረነ እግዚኦ መሀከነ፤ እግዚኦ ተሣሀለነ።

ይ:ዲ:- በኵሉ ልብ ናስተብቍዖ ለእግዚአብሔር አምላክነ በኅብረተ መንፈስ ቅዱስ ሠናይ ከመ ይጸግወነ

ይ:ሕ:- በከመ ሀሎ ሕልወ ወይሄሉ ለትውልደ ትውልድ ለዓለመ ዓለም።

## በአማርኛ

ይ:ዲ:- ፍጽምት ስለምትሆን ሰላምና ፍቅር ጸልዩ፤ ቅድስና ባላት እጅ መነሣሣትም እርስ በርሳችሁ እጅ ተነሣሡ።

ይ:ሕ:- ፈጣሪአችን ክርስቶስ ሆይ፥ ቅድስና ባላት እጅ መነሣሣት እርስ በርሳችን እጅ እንነሣሣ ዘንድ የበቃን አድርገን

ይ:ካ:- እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

ይ:ሕ:- ከመንፈስህ ጋራ፤

ይ:ካ:- ፈጣሪያችንን አመስግኑት።

ይ:ሕ:- እውነት ነው፤ ይገባል።

ይ:ካ:- ልባችሁን ከፍ ከፍ አድርጉ።

ይ:ሕ:- ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ዘንድ አለን።

ይ:ዲ:- ተሠጥዎውን መልሱ፤

ይ:ሕ:- ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ አሸናፊ እግዚአብሔር ሆይ፥ የጌትነትህ ምስጋና በሰማይና በምድር ፍጹም ነው።

ይ:-ሕ:- አቤቱ በጌትነትህ አስበን፤ ጌታ ሆ፥ አቤቱ በጌትነትህ አስበን፤ አቤቱ በጌትነትህ አስበን፤

በቅዱስ ዕፀ መስቀል ላይ ሳለህ፥ በቀኝህ በኩል ተሰቅሎ የነበረውን ወንበዴ እንዳሰብከው።

ይ :ሕ:- በእውነት ይህ እንደ ሆነ እናምናለን።

አሜን፥ አሜን፥ አሜን፥ እናምናለን እንታመናለን፤ ጌታችን አምላካችን ሆይ፥ እናመሰግንሃለን።



በእውነት ሥጋህ እንደሆነ እናምናለን።

አሜን፥ አሜን፥ አሜን፥ እናምናለን፤ እንታመናለን፤ ጌታኝ አምላካችን ሆይ፥ እናመሰግንሃለን፤ ይህ በእውነት ደምህ እንደሆነ እናምናለን።

አቤቱ ሞትህን፥ ቅድስት ትንሣኤህንም እናስተምራለን፤ ዕርገትህን፥ ዳግመኛም መምጣትህን እናምናለን እናመሰግንሃለን፤ እንማልድሃለን፤ ጌታችን አምላካችን ሆይ።

አሜን አቤቱ ማረን፤ አቤቱ ራራልን፤ አቤቱ ይቅር በለን።

ይ:ዲ:- በፍጹም ልብ አምላካችንን እግዚአብሔርን እንማልደው፤ ያማረ የመንፈስ ቅዱስን አንድነት ይሰጠን ዘንድ።

ይ:ሕ:- ጸንቶ እንደኖረ፥ እንደሚኖር፥ ለልጅ ልጅ፥ ለዘለዓለም ይኖራል።

## ጥያቄዎች

1. ቤተ ክርስቲያን ለምእመናን ወይም ለሕዝበ ክርስቲያን ምታቀርባቸው ግልጋሎቶች ምን ምን ናቸው?
2. ወደ ክርስትናው ማኅበረሰብ መግቢያ መታወቂያ ምንድነው?
3. የቅብዐተ ሜሮን ጥቅሙ ምንድነው?
4. ሥጋ ወደሙ መቀበል ለምን ይጠቅማል?
5. የምሥጢረ ቀንዲል አገልግሎት ምንድነው?
6. ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ትምህርትን የምታቀርበው በማን አማካይነት ነው?
7. ኤጲስ ቆጶስ የሁለት ጠበኞችን ጉዳይ በሚያይበት ጊዜ ከእርሱ ጋር አብሮ መሆን ያለበት ማነው?
8. እግዚአብሔር የመባረክን ሥልጣን የሰጠው ለማን ነው?
9. ከሓዲው አርዮስ የተነሣው በማንኛው የግብጽ ፓትርያርክ ዘመን ነው?
10. ከአንጾኪያ የመጣችው ሴት በባሕር ውስጥ ምን አጋጠማት?
11. ልጆችዋን ለማጥመቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን በሄደች ጊዜ ምን ተአምር ተከሠተ?
12. ፓትርያርኩስ ምን አለ?
13. አርዮስ ፓትርያርኩን ምን ብሎ ከሰሰው?
14. በዚህስ ምክንያት ንጉሡ ምን አደረገ?
15. አርዮስ ወደ ፓትርያርኩ ምን የሚል አማላጅ ላከ?
16. በዚህስ ጉዳይ ፓትርያርኩ ምን ራእይ አየ?
17. ፓትርያርኩ ከመሞቱ በፊት ምን ብሎ ጸለየ?

www.ethiopianorthodox.org

18. ፓትርያርኩ በማርቆስ መንበር ያልተቀመጠው በምን ምክንያት ነበር?

19. ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ የተባለው በምን ምክንያት ነው?

20. በልጅነቱ ከክርስቲያን ልጆች ጋር ምን ተባባለ?

21. ፓትርያርኩ ያያቸው ምን ሲያደርጉ ነው?

22. በዚያን ጊዜ የነበረው የፓትርያርክ ስም ማን የባል ነበር?

23. ይህ ፓትርያርክ አትናቴዎስን እስከምን የሹመት መዐርግ አደረሰው?

24. አትናቴዎስ ከፓትርያርክነት መንበሩ ለስንት ጊዜ ተባረረ?

25. በጢሮስ ከተማ ተሰብስቦ የነበረው ጉባኤ በአትናቴዎስ ላይ የቀረቡ ስንት ክሶችን ተመለከተ?

26. ክሶቹስ ምን ምን የሚሉ ነበሩ?

27. አትናቴዎስ የንጉሡን ትእዛዝ ለምን አላከበረም?

28. በአትናቴዎስ ላይ ከቀረቡት ክሶች መካከል ሦስቱ ክሶች ከሳሾቹን ያሳፈሩት እንዴት ነው?

29. አትናቴዎስ በመጀመሪያ የተጋዘበት ቦታ ማን ይባላል?

30. ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ አትናቴዎስን ከግዞት የመለሰው በምን ምክንያት ነው?

31. አፈወርቅ የሚለው ቅጽል ለዮሐንስ የተሰጠው በምን ምክንያት ነው?

32. ዮሐንስ አፈወርቅ ከግብጹ ቴዎፍሎስ ጋር አለመግባባት የነበራቸው በምን ምክንያት ነው?

33. ንግሥቲቱ ይህን የሁለቱን አለመግባባት በምን ዐይነት ተጠቀመች በት?

34. ንግሥቲቱ ዮሐንስ አፈወርቅን ወደ ግዞት ከላከችበት ከመንገድ ላይ ለምን አስመለሰችው?

35. ከዚያስ በመጨረሻ ላይ ወዴት አጋዘችው?

36. ወታደሮች ዮሐንስ አፈወርቅን በምን መንገድ አሠቃዩት?

37. በስንት ዓ.ም ዐረፈ?



# ምዕራፍ 5

## መንፈሳዊነትና ግብረ ገብነት

### ጠቃሚ ካልሆነ ተጽዕኖ መጠንቀቅ

ተጽዕኖ ማድረግ ማለት የግልን እምነትና የድርጊት ፍላጎት ሌላውን ሰው በማግባባት ወይም በማስገደድ ለማሳመን፥ ወይም ለማስደረግ መሞከር ነው። ተጽዕኖ የሚደረግበት ሰው ያን ሊያምን፥ ወይም ሊያደርግ የሚፈለግበትን እምነትና ድርጊት የማያውቀው ወይም የማይፈልገው ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ የዚያ ሰው የተፈጥሮ ጠባይ ተጽዕኖውን የማይቀበል ሊሆን ይችላል። በዚህም ሆነ በዚያ ተጽዕኖ አድራጊው ሰው ለተጽዕኖ የሚጠቀምባቸው መንገዶች:- ተፈሪነት፥ በጥቅም መደለል፥ የማግባባት ችሎታ፥ ወዳጅነትና ጓደኝነት ሊሆኑ ይችላሉ።

ጠቃሚ ያልሆነ ተጽዕኖ የተባለው ጠቃሚ የሆነ ተጽዕኖ ከወላጆች፥ ከመምህራን፥ ከሃይማኖት ሰዎች፥፣ ከመልካም ዘመድ፥ ወዳጅና ጓደኛ ሊመጣ ስለሚችል ነው። ጠቃሚ ያልሆነ ብለን እኛ ልንነጋገርበት ያሰብነው ጉዳይ ተጽዕኖው ከእግዚአብሔር መንገድ የሚያርቅ በመሆኑ ሲሆን ጠቃሚ አለመሆኑም ለመንፈሳዊ ሕይወታችን እንጂ ለሥጋዊ ፍላጎታችን አይደለም።

<u>ከባለሥልጣን፥ ከቅርብ አለቃ ወይም ከአሠሪ የሚመጣ ተጽዕኖ</u>:- ባለ ሥልጣኖች፥ የቅርብ አለቆች፥ ወይም አሠሪዎች ሁሉ ክፉ ተጽዕኖ ያደርጋሉ ማለት አይደለም። ዐልፎ፥ ዐልፎ ግን ከእነርሱ መካከል ክፉ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ይገኙባቸዋል። እንደዚህ ያሉ በበላይነት ስሜት ተጽዕኖ የሚያደርጉ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ የራሳቸውን ፍላጎት ለማግኘት እንጂ ስለሌላው ሰው ፍላጎታዊ ስሜት ግድ የላቸውም። የእነርሱ ፍላጎት እስከተሟላላቸው ድረስ ያ ተጽዕኖ የሚያደርጉበት ሰው ፍላጎት ይኑረው ወይም አይኑረው፥ ይፈልግ ወይም አይፈልግ ስለ እርሱ ምንም ዐይነት ሰብአዊ ስሜት የላቸውም። ይህም በመሆኑ እነርሱ ተጽዕኖውን የሚያደርጉባቸው መንገዶች ማዘዝ፥ ማስገደድ፥ ማስፈራራት፥ የሚቻልም ከሆነ ማግባባት ናቸው።

አብዛኞቹ በሥልጣናቸው ተጽዕኖ ሚያደርጉ ሰዎች ኀሊናቸው ስለማይ ወቅሳቸው በሃይማኖትም ሆነ በባህል ያልተደገፈ ማንኛውንም ድርጊት ቢያደርጉ ግድ የላቸውም። በዚህም መሠረት እንደነዚህ ያሉት ሰዎች ደመወዝ በማስጨመር ወይም የደረጃ ዕድገት በማስጠት ተስፋ፥ በእነርሱ ሥር ያሉ ሴቶች ሠራተኞች በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ ይቅርታ የማይደረግለትን በደል እንዲሠሩ ተጽዕኖ ያደርጉባቸዋል። በዚህ ጊዜ ሴቶች እኅቶቻችን መንፈ ሳዊ ጥንካሬ ሊኖራቸው ይገባል። ለእንደዚያ ያለ ክፉ ተጽዕኖ ሳይሸነፉ እምነ ትን በእግዚአብሔር ላይ ያደረጉ እንደሆነ ያ ክፉ አለቃ ከሰጠው ተስፋ የተሻለ

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ይሰጣቸዋል። በዚህ ረገድ የሶስናን አርአያነት መከተል ጠቀሜታ አለው። የሶስናን ታሪክ በሦስተኛው ክፍል መጽሐፍ፥ ምዕራፍ ሁለት ላይ ይመለከቷል። እርስዋ በፈጣሪዋ ተማምና ተጽዕኖውን እምቢ ስላለች እግዚአብሔር ከመወገር የአዳናት ብቻ ሳይሆን በሐሰት የከሰሰዋትንም ሰዎች ወዲያው ተበቀለላት።

ሌላ ምሳሌ ደግሞ በዓለም ላይ የኮሚዮኒስት አገዛዝ ሰፍኖ በነበረበት ዘመን ይፈጸም የነበረው ሁናቴ ነው። በየመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የነበሩት የፖለቲካ ካድሬዎችና የክፍል አለቆች በመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ላይ የተለየ ተጽዕኖ ያደርጉባቸው ነበር። ሠራተኛውን ለደረጃ ዕድገት ተስፋ በመስጠት፥ ካልሆነም በማስፈራራት የኮሚዩኒስት ፓርቲ አባል እንዲሆን ተጽዕኖ ያደርጉበት ነበር። የሚያስፈራሩትም ካለበት የሥራ ደረጃ ዝቅ ማለትንና እንዲያውም ከሥራ መታገድን በመሰሉ ሁኔታዎች ነበር። የኮታሚዩኒስት አባል የሆነ ሰው ደግሞ የእግዚአብሔርን ህልውና መካድ ይጠበቅበት ነበር። ምንም እንኳ ብዙዎች ለተጽዕኖው ተሸንፈው በአባልነቱ ቢመዘገቡ፥ ዐልፎ ዐልፎ ግን ለተጽኖው ሳይሸነፉ የዘለቁም ሰዎች ነበሩ።

<u>የዘመድ፥ የጓደኛ፥ ወይም የወዳጅ ተጽዕኖ</u>:- ይህ ዐይነቱ ተጽዕኖ ከባለሥልጣን፥ ከቅር፥ አለቃና ከአሠሪ እንደሚመጣው በሥልጣን በማስፈራራትና በአስገዳጅነት ሳይሆን በማግባባት፥ መላልሶ ለማሳመን በመሞከርና ዘወትር በመጨቅጨቅ የሚመጣ ተጽዕኖ ነው።

ለምሳሌ ታላቁ ጥበበኛ ንጉሥ ሰሎሞን በአረማውያን ሴቶች ተጽዕኖ ያን ሁሉ ጥበብና ሀብት ሰጥቶ ከዓለም ነገሥታት ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ ያደረገውን እግዚአብሔር አምላክን በመተው የጣዖት ቤቶችን አሠራ፤ ለጣዖትም ሰገደ። እግዚአብሔርም በዚህ በሰሎሞን አድራጎት ተቈጥቶ ጠላቶችን አስነሣበት። እንዲሁም እግዚአብሔር ለዳዊት ልጆችህ ሕግጋቴንና ትእዛዛቴን የሚጠብቁ ከሆነ ዘወትር በዙፋንህ ላይ ይቀመጣሉ ብሎት የነበረውን ቃል ኪዳኑን ሰሎሞን ስላፈረሰው ዐሥሩ የእስራኤል ነገዶች ከይሁዳ ነገድ ተለይተው ሌላ ንጉሥ አነገሡ (1ኛ:ነገ:ም:1እና:12)።

ተመሳሳይ ተጽዕኖ በንጉሥ ኢዮአስ ላይ ተፈጽሞአል። ኢዮአስ በሰባት ዓመቱ ንጉሥ ለመሆን የበቃው በሊቀ ካህናቱ በዮዳሄ እርዳታ ነበር። እርሱም በዮዳሄ መንፈሳዊ ተጽዕኖ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ነገር ሲያደርግ ኖሮአል። ዮዳሄ ከሞተ በኋላ ግን የይሁዳ መሪዎች ተሰባስበው ወደ ንጉሥ ኢዮአስ በመሄድ አምልኮተ እግዚአብሔርን እንዲተው ተጽዕኖ አደረጉበት። እርሱም ምክራቸውን ተቀብሎ ተግባራዊ አደረገው። ሕዝቡም ጣዖትን ማምለክ ጀመረ። ድርጊታቸውን በመቃወም የተናገረውን የዮዳሄን ልጅ ዘካርያስን በቤተ መቅደሱ አደባባይ ውስጥ በድንጋይ ወግረው ገደሉት። እግዚአብሔርም ኢዮአስን በሶርያ ሠራዊት አማካይነት ቀጣው። በጦርነቱ ቈሰለ፤ ባለሟሎቹም በአልጋው ላይ እንዳለ ገደሉት (2ኛ:ዜ: መ:ም: 24 ቍ:15–25)።



www.ethiopianorthodox.org

ሌላው የተጽዕኖ ምሳሌ ደግሞ ጲላጦስ ነው። ጲላጦስ ሚስቱ ሕልም አይታ ብታስጠነቅቀውና እርሱ ደግሞ የጌታችንን ከበደል ንጹሕ መሆን ቢያምንም እንኳ ፥ በአይሁድ ተጽዕኖ በጌታችን ላይ ፈረደ። አይሁድም በጲላጦስ ላይ ተጽዕኖ ያደረጉበት:- «ራሱን ንጉሥ የሚያደርግ ሁሉ የቄሳር ተቃዋሚ ስለሆነ ይህን ብትፈታው የቄሳር ወዳጅ አይደለህም» በማለት ነው (ማቴ: ም: 27ቍ:15–26፥ዮሐ:ም:19ቍ:12–16)።

<u>የዓለማዊ ፍላጎት ተጽዕኖ</u>:- አንዳንድ ሰዎች ሥጋዊ ፍላጎታቸውን ለማግኘት ሲሉ ያልሆኑትን ይሆናሉ፤ የማይፈልጉትን ያደርጋሉ።

ለጋብቻ ያልፈቀዱአቸውን ሴቶች ለማግባት ሲሉ ሃይማኖታቸውን ለውጠው ወደ ሴትዋ ሃይማኖት ይገባሉ፤ ወይም ሴቶቹ አንድን ወንድ ለማግባት ወደ ወንዱ ሃይማኖት ይሄዳሉ።

የዚህ ዓለም የኑሮ ደረጃቸውን ለማሻሻል ሲሉ የእግዚአብሔርን ህልውና ከሚክዱ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ይተባበራሉ፤ በሰው ፊትም እግዚአብሔርን ይክዱታል። ከእነዚህ አንዳንዶቹ ደግሞ ሰው ሳያያቸው በድብብቆሽ እግዚአብሔርን ማምለክ ይፈልጋሉ። እርሱ ግን ያለው በሰው ፊት የሚክደኝን በሰማዩ አባቴ ፊት እክደዋለሁ» ነው። (ማቴ:10፥33)።

እንዲሁም ሌሎች ለገንዘብና ለሥጋዊ ጥቅም ሲሉ በሐሰት ይመሰክራሉ ሐሰትም ይናገራሉ።

ሃይማኖት እኮ የእግዚአብሔርና የሰው መገናኛ መንገድ ነው እንጂ ከሥጋዊ ፍላጎት ጋር ግንኙነት የለውም። እንደ ዓለማዊ የተለያዩ ማኅበሮች የሚገባበትና የሚወጣበት አይደለም። የራሱን ሃይማኖት በቀላሉ ትቶ ወደ ሌላ ሃይማኖት የሚሄድ ሰው የሃይማኖት መሠረታዊ አስተሳሰብ ስላልገባው ቀድሞውንም ቢሆን እምነት አልነበረውም ማለት ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእኔ ይልቅ አባቱን፥ እናቱን፥ ሚስቱን፥ ልጆቹን፥ ወንድሙንና እኅቱን፥ ቤቱንና ንብረቱን የሚወድድ የእኔ ሊሆን አይገባውም ካለ፥ ገና የርሱ ላልሆነችው ሴት፥ ወይም የእርስዋ ላልሆነው ወንድ ሲባል ሃይማኖትን መለወጥ ምን ትርጒም ይሰጠዋል?

በፈጣሪነቱ፥ በአምላክነቱና በአዳኝነቱ የታመነበት እግዚአብሔር እንዲሁ በቀላሉ ይለወጣልን? ጌታችን ያለው «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጠፉ ምን ይጠቅመዋል» ነው (ማቴ:ም:16ቍ:26)።

በኮሙኒስት አገሮች የፓትርቲው አባሎች የነበሩት ሁሉ አሁን ወዴት ናቸው? እነርሱ ህልውናውን የካዱት እግዚአብሔር ግን ቀድሞም ነበር፥ አሁንም አለ፥ ወደ ፊትም ኖራል እንጂ እንደ እነርሱና እንደ ከሐዲው ድርጅታቸው የሚያልፍ አይደለም።

ከማይጠቅም ተጽዕኖ እንዴት መከላከል ይቻላል? ቀደም ተብሎ እንደተ ገለጠው ጠቃሚ ያልሆነ ተጽዕኖ ማለት በዓለማዊ ፍላጎት ላይ ብቻ ወስኖ ከእግዚአብሔር መንገድ የሚያርቅ ድርጊት ወይም አስተሳሰብ ማለት ነው።

ከማይጠቅም ተጽዕኖ ለመከላከል የሚቻለው እምነትን በእግዚአብሔር ላይ በማጠናከርና ራስን ለእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዛት በማስገዛት ነው።

ስለዚህ ጉዳይ ከቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ ምሳሌዎችን ለመጥቀስ የሚቻል ቢሆንም ለጊዜው ግን የሚከተሉትን ምሳሌዎች ማቅረብ በቂ ይሆናል።

1. የጶጢፋር ሚስት ለዮሴፍ የጌታው ሚስት ስለነበረች ዮሴፍ ከእርስዋ ጋር ኃጢአት እንዲሠራ በሥልጣንዋ ብትጠይቀው ይህን የመሰለ ኃጢአት አልሠራም ብሎ እምቢ አላት። በዚህም ኃጢአት ከእርስዋ ጋር ስላልተባበረ በሐሰት ከስሳ አሳሰረችው። እርሱ በአምላኩ የሚተማመንና የፈጣሪውን ትእዛዝ የሚጠብቅ በመሆኑ እግዚአብሔር ከእስረኛነት ወደ መላዋ ግብጽ አስተዳዳሪነት ከፍ አደረገው። ስለዚህ ዮሴፍ በእግዚአብሔር ስለታመነና በሕግጋቱ ስለጸና ለጲጢፋር ሚስት ተጽዕኖ አልተንበረከከም። ለእርስዋ ተጽዕኖ ባለመንበርከኩም ተጠቀመ እንጂ አልተጐዳም (ዘፍ:ም:39–41)።

2. በጊዜው የበጎች ጠባቂ የነበረው ዳዊት የጎልያድ ድንፋታ የፍርሀት ተጽዕኖ ሳያሳድርበት በአምላኩ ተማምኖ የተናገረውን የእምነቱን ማረጋገጫ ቀጥለን እንመልከት:-

«አንተ፥ ሰይፍ፥ ጦርና ጋሻ ይዘህ ትመጣብኛለህ፤ እኔ ግን ዛሬ አንተ በተገደደርኸው፥ በእስራኤል አምላክ፥ በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ፤ እግዚአብሔር ዛሬ አንተን በእጄ አሳልፎ ይሰጣል፤ እመታ ህማለሁ፤ ራስህንም ከአንተ አነሣዋለሁ» (1ኛ: ሳሙ: ም:17ቍ: 45–46)።

በልቡ አምኖ በቃሉ በገለጠውም መሠረት ዳዊት ጎልያድን በወንጭፍ ገድሎ በራሱ በጎልያድ ሰይፍ ራሱን ቈረጠው።

3. ዳዊት ለአምላኩ ያለው ታማኝነት በእረኝነቱም ጊዜ ሆነ በንጉሥነቱ ጊዜ ምንም ልዩነት አልነበረውም። የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ከዖቤድኤዶም ቤት ወደ ዳዊት ከተማ በመጣበት ቀን ንጉሥ ዳዊት አክብሮትና ደስታውን በተመሰጦ እየዘለለ ስለገለጠ የሳኦል ልጅ የነበረችው ሚስቱ ሜልኮል ንቀትዋን በንግግር ገለጠችለት። በዚህ ጊዜ ዳዊት ለአምላኩ ለእግዚ አብሔር ያለውን የማያወላውል አክብሮት እንዲህ ሲልገልጠላታል:-

«እኔ የጨፈርሁት የሕዝቡ የእስራኤል መሪ ያደርገኝ ዘንድ በአባትሽና በቤተሰቡ ፈንታ ለመረጠኝ እግዚአብሔር ክብር ነው፤ አሁንም ቢሆን እርሱን ለማክበር ከመጨፈር አልገታም፤ ከዚህም የባሰ ራሴን አዋርዳለሁ» (2ኛ:ሳሙ : ም:6ቍ:21–22)።

ስለዚህ የጎልያድ የማስፈራራትና የሚስቱ የነቀፋ ተጽዕኖ ዳዊትን ለእግዚ አብሔር ካለው ታማኝነት ሊያነቃንቀው አልቻለም።



4. የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር የወርቅ ጣዖት አሠርቶ ሰው ሁሉ እንዲሰ ግድለት ትእዛዝ አስተላለፈ። ሲድራቅ፥ ሚሳቅና አብዶናጎ ለዚያ ጣዖት የማይሰግዱ መሆናቸው ለናቡከደነፆር ተነገረው። ንጉሡም በጉዳዩ ተቈጥቶ ለጣዖቱ መስገድ ያለባቸው መሆኑና ባይሰግዱ ግን ከነነፍሳቸው ወደ እሳት ውስጥ እንደሚጣሉ አስጠነቀቃቸው። እነዚያ በእግዚአብሔር ይተማመኑ የነበሩት ወጣቶች ግን የናቡከደነፆር የተጽዕኖ ሙከራ ሳይበግራቸው እንዲህ ሲሉ መለሱለት:-

«ንጉሥ ሆይ፥ በዚህ ጉዳይ ላይ ራሳችንን የምንከላከልበት መልስ ልንሰጥ አንፈልግም፤ እኛ የምናመልከው አምላክ ከዚህ ከሚነድደው ከእሳት ነበልባ ልም ሆነ ከአንተ እጅ ሊያድነን ይችላል፤ እርሱ ሊያድነን ፈቃዱ ባይሆን እንኳ አማልክትህን እንደማናመልክና ላቆምኸውም የወርቅ ምስል እንደማ ንሰግድ ዕወቅ» (ዳን:ም:3ቍ:16–18)።

ንጉሡም እሳቱ ከነበረበት በሰባት እጥፍ እንዲነድድ አዘዘ። ሦስቱ ወጣቶች በእዚያ የእሳት ነበልባል ውስጥ ቢጣሉም የእሳቱ ነበልባል እነርሱን ወደ እሳቱ ውስጥ የጣሉአቸውን ሰዎች ከማቃጠሉ በቀር ወጣቶቹ ምንም ሳይደርስባቸው ከእሳቱ ውስጥ ወጥተዋል። ከዚያም ንጉሡ የእስራኤልን አምላክ አከበረ፤ ለወጣቶቹም ከፍተኛ ሹመት ሰጣቸው።

5. ንጉሥ ዳርዮስ ዳንኤልን በክብር ከፍ ስላደረገው ሌሎች ባለሥልጣኖች ቀኑበት። እርሱን የሚከስሱበትንም ምክንያት በመፈለግ ወደ ንጉሡ ቀርበው ለሚቀጥሉት ሠላሳ ቀኖች ለአንተ በቀር ለማንኛውም አምላክ ወይም ሰው እንዳይሰገድ ይህን ትእዛዝ የማያከብር ማንኛውም ሰው በአንበሳ ጕድጓድ ውስጥ እንዲጣል ትእዛዝ አስተላልፍ ብለው ምክር አቀረቡለት። እርሱም በምክሩ ተስማምቶ ትእዛዙን አስተላለፈ። ከዚያ በኋላ ዳንኤል ለአምላኩ ለእግዚአብሔር ስለሚሰግድ የንጉሡን ትእዛዝ አያከብርም ብለው ከሰሱት። በዚህ ጊዜ ንጉሡ በጣም አዘነ፤ ዳንኤልንም ሊያድነው ፈለገ። ነገር ግን የዳንኤል ከሳሾች በእነርሱ ባህል አንድ ንጉሥ ያስተላለፈውን ዐዋጅ ሊጥስ አይችልም ብለው ምክንያት በመስጠት ፍርዱን በዳንኤል ላይ ተግባራዊ እንዲ ያርግ ጨቀጨቁት። ስለዚህም እያዘነ ዳንኤል በአንበሳው ጕድጓድ ውስጥ እንዲጣል አዘዘ። በዚያ ሌሊት ሲጨነቅ ዐድሮ ጧት በማለዳ ወደ አንበሶቹ ጕድጓድ በመሄድ በሐዘን ድምፅ ዳንኤል ሆይ፥ ሁልጊዜ በታማኝነት የምታ መልከው አምላክ ከአንበሶች ያድንህ ዘንድ ችሎአልን? አለው። ዳንኤልም እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ የአንበሶቹን አፍ እንደዘጋለት ነገረው። ንጉሡም ደስ ተሰኝቶ ዳንኤልን ከጕድጓዱ እንዲያወጡት፥ የዳንኤል ከሳሾች ደግሞ ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር ወደ አንበሳው ጕድጓድ እንዲጣሉ አዘዘ። እነርሱንም አንበሶቹ በሜጨቁአቸው።

በዚህም ዐይነት ዳንኤል ከእግዚአብሔር ጋር ባለው አምልኮታዊ ግንኙት ላይ የተደረገበትን ተጽዕኖ ድል ለመንሣት ችሎአል (ዳን:ም:6)።



www.ethiopianorthodox.org

## ጥያቄዎች

1. ጠቃሚ ያልሆነ ተጽዕኖ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ጠቃሚ ያልሆነ ተጽዕኖ በምን ላይ የተመረኰዘ ነው?
3. ከበላይ ባለሥልጣን የሚመጣ ተጽዕኖ ከወዳጅ ወይም ከጓደኛ ከሚመጣ ተጽዕኖ በምን ይለያል?
4. ከአለቃ ለሚመጣ ተጽዕኖ የቀረቡ ሁለት ምሳሌዎች ምንና ምን ናቸው?
5. ከበላይ ባለሥልጣን ያልሆኑ ሦስቱን ምሳሌዎች ዘርዝረህ አስረዳ።
6. ስለ ዓለማዊ ፍላጎት ተጽዕኖ የቀረቡ ሁለት ምሳሌዎች ምንና ምን ናቸው?
7. ከማይጠቅም ተጽዕኖ ለመጠንቀቅ የሚቻለው እንዴት ነው?
8. የጶጢፋር ሚስት በዮሴፍ ላይ ምን ዐይነት ተጽዕኖ አደረገችበት? እርሱስ እንዴት ተጽዕኖውን ድል ነሣ?
9. ዳዊት ድል የነሣቸው ሁለት ተጽዕኖዎች ምንና ምን ናቸው?
10. ሦስቱ ወጣቶች ምን ዐይነት ተጽዕኖ ተደረገባቸው?
11. እነርሱስ ተጽዕኖውን እንዴት ድል ነሡት?
12. ዳንኤል ምን ዐይነት ተጽዕኖ ተደረገበት?
13. እርሱስ እንዴት ድል ሊነሣ ቻለ?

www.ethiopianorthodox.org